ሃያ የገጠር ማህበረሰቦች በኢትዮጵያ

በለውጥና ትራንስፎርሜሽን ላይ የሚያተኩሩ

የተመረጡ የውይይት መነሻ አጫጭር የጥናት መግለጫዎች

አርታኢ

አሉላ ፓንክረስት

የ20 ገጠር ማህበረሰቦች ጥናት
ከ1989 ጀምሮ

መስከረም 2010

© 2010 በጸሃፊዎቹ
በአዲስ አበባ ታተመ

በ2010 ታተመ

ISBN: 978-99944-70-97-6

መብቱ የተጠበቀ ነው።።

አድራሻ፡-
C/o ፓንክረስት የልማት ምርምርና አማካሪ ኃ.የተ.የግል ማህበር
ፖ.ሳ.ቁ. 1896
ስልክ ቁ. +251 (0)11 154 0121
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
http://ethiopiawide.net

ዲዛይነር፡- አግአዚ ጥዑመልሣን

ምስጋና፡- ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀው በስዊዲን ዓለም አቀፍ የልማት ተቋም ድጋፍ ሲሆን የWIDE ኢትዮጵያ ቡድን ለዚህ ድጋፍ ልባዊ ምስጋናውን ያቀርባል።። ይህንን የአማርኛ ቅጂ ከእንግሊዝኛው የተረጎመውን የአዲስ አድማስ ጋዜጣ ምክትል ዋና አዘጋጅ የሆነውን አቶ እዮብ ካሣን፤ እንዲሁም የአማርኛውን ቅጂ ጥራት የተመለከተውን የትርጉም አርታኢ የሆነውን አቶ ሚክያስ ሲሣይን ከልብ እናመሰግናለን።።

ማሳሰቢያ፡- በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት አስተያየቶች የጸሃፊዎቹ ሲሆኑ ጥናቱን ስፖንሰር ያደረገውን ወይም የደገፈውን ተቋም አመለካከት ወይም አቋም አይወክሉም።።

መታሰቢያነቱ፡- ለሃያዎቹ የWIDE ማህበረሰቦች ነዋሪዎች፤ ከእነርሱ ለተማርናቸው እጅግ ብዙ ቁም ነገሮች ከምስጋና ጋር።።

ማውጫ

ምህጻረ ቃላት i

መቅድም iii

የWIDE ኢትዮጵያ የውይይት መነሻ አጫጭር የጥናት መግለጫዎች መግቢያ 1

የገጠር ከተሜነት መስፋፋት፣ የከተማ ወደ ገጠር አካባቢዎች መስፋፋት እና የገጠር-ከተማ ትስስሮች መደርጀት 21

ኢ-እኩልነት እና የኑሮ ደረጃ ልዩነቶች በገጠር ማህበረሰቦች (2010-13) 39

ከወጣትነት ወደ አዋቂነት በገጠር ማህበረሰቦች ያሉ ሽግግሮች (2010-13) 59

ትምህርት በገጠር ኢትዮጵያ (2010-13)፡- ራዕይና ጥርጣሬ 79

በኢትዮጵያ የገጠር አካባቢዎች በእናቶችና በጨቅላ ህጻናት ጤንነትና ደህንነት ዙሪያ የታዩ ለውጦች (2003-13) 97

የሴቶችና ልጃገረዶች ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ በገጠር ኢትዮጵያ ማህበረሰቦች (2010-13) 117

በገጠር ማህበረሰቦች ለሥራ ፍለጋ የሚደረግ ፍልሰት (2010-13) 137

በገጠር ኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ ስኬት ላይ የሚስተዋሉ ዕይታዎች (2010-13) 155

የትራንስፎርሜሽን አርአያዎች (ሞዴሎች) እና እውነታዎች 173

የዕውቀት ስርጸት፣ ከተሞክሮዎች መማር፣ “የቴክኖሎጂ ሽግግር” እና ለውጥ በገጠር ማህበረሰቦች 189

ምህጻረ ቃላት

ኢልምተ	የኢትዮጵያ የልማት ምርምር ተቋም
ኢህአዴግ	የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲ ግንባር
HA	ሄክታር
ኬሜጂ	ከምባቲ ሜንቲ ገዚማ (የከምባታ ሴቶች ራስ አገዝ ማዕከል መያድ)
መያድ	መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት
ሕወሃት	ሕዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ
ዩኒሴፍ	የተባበሩት መንግስታት የሕጻናት ፈንድ
ቴሙትሥ	የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና
EDHS	የኢትዮጵያ ስነ ሕዝብና ጤና ዳሰሳ
GTP	የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ
FGC/FGM	የሴት ልጅ ግርዛት/የብልት ትልተላ
WIDE	Wellbeing Illbeing Dynamics in Ethiopia (የደህንነትና ኢ-ደህንነት መስተጋብር በኢትዮጵያ)

መቅድም

የኢትዮጵያ የልማት ምርምር ተቋም (ኢልምት)፣ እንደ አውሮፓውያን ቀን አቆጣጠር ከ1999 ዓ.ም. ጀምሮ፣ በዘርፈ ብዙ የኢኮኖሚ ጉዳዮች ላይ ፖሊሲ ለማውጣትና ለማስፈጸም የሚያግዙ፣ መረጃ ላይ የተመሰረቱ ግብአቶችን ለማቅረብ፣ ጥልቅና ጥብቅ የኢኮኖሚ ጥናትና ትንተና ያለመታከት ሲያካሂድ ቆይቷል። ከዚህም ባሻገር የኢትዮጵያ የልማት ምርምር ተቋም፤ ዕውቀት ለማሰራጨት፣ ለመለዋወጥና ለመወያየት መድረክ በመሆንም ቁልፍ ሚና ተጫውቷል።

ኢልምት፤ ከ2000 ዓ.ም. አንስቶ የWIDEን ጥናት ሲደግፍ ቆይቷል። አቶ ነዋይ ገብረአብ፤ እንደ ኢልምት ዋና ዳይሬክተርነታቸው፣ ጥናቱን በማቀላጠፍና ለጥናት ውጤቶቹን ለውይይት መድረክ በማብቃት ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርገዋል። ኢልምት፤ የWIDEን ጥናት ከከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣናትና ምሁራን ጋር ለማስተዋወቅ ከ2010-2013 ስብሰባዎችን አዘጋጅቷል፣ ከሦስት የጥናቱ ምዕራፎችና በ2014 እና በ2016፣ ከሁለት ተከታታይ አጫጭር የጥናት መግለጫዎች ዝግጅት በኋላ፣ ለፖሊሲ ፋይዳ ባላቸው የጥናት ድምዳሜዎች ላይ ለመወያየት አስችሏል።

የWIDE ጥናት፤ የተለያዩ የገጠር ማህበረሰቦች ዓይነተኛ ናሙናዎች ተብለው በተመረጡና የኑሮ መተዳደርያ ዓይነቶች፣ የተደራሽነት ወይም ተደራሽ ያለመሆን እንዲሁም የባህል ስብጥርን ጨምሮ በፈርጀ-ብዙ ቁልፍ መለኪያዎች፣ ሰፊ ልዩነቶችን በሚያንጸባርቁ 20 የገጠር መንደሮች ላይ የሚያተኩር ነው። እነዚህ አካባቢዎች፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ የትምህርት ክፍል፣ በ"የኢትዮጵያ የገጠር ቤተሰብ የጥናት ቅኝት"፣ ከ1994-2009፣ በተከታታይ ዙሮች ክትትል ያደረገባቸው ሲሆኑ በ2003፣ ሁለት የአርብቶ አደር አካባቢዎች በWIDE የጥናት ቡድን፣ ታክሎባቸዋል። የWIDE ጥናት፤ ከረዥም ጊዜ ዕይታ አንጻር፣ የተወሰኑ አካባቢዎች ላይ አተኩሮ፣ በጥልቀትና በቅርበት የማጥናት አቅጣጫን በመጠቀም፣ በረዥም ጊዜ ሂደት እነዚህ ማህበረሰቦችና አብረዋቸው የሚኖሩ የተለያዩ ሰዎች፣ (በጾታ፣ ዕድሜ፣ ሃብትና፣ [በህብረተሰብ ውስጥ ያላቸው ደረጃ] ተመስርቶ) እንዴት በተለያዩ መንገዶች እንደተለወጡ፣ ግንዛቤ ይሰጣል።

ከዚህ ጥናት የተገኘው ማስረጃ እንደሚያረጋግጠው፤ በመላው የገጠር ማህበረሰብ፣ ከፈርጀ ብዙ የማዘመን እንቅስቃሴዎች ጋር በመተሳሰር፣ የመንግስት የለውጥ እንቅስቃሴ፣ ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት፣ ጉልህ ለውጥና እመርታ አምጥቷል። ጥናቱ፤ በመሰረተ ልማት፣ በዘመነኛ የመገናኛ ቴክኖሎጂ አገልግሎቶች አቅርቦት ረገድ፣ በመንግስት የለውጥ እንቅስቃሴዎች የተገኙ ከፍተኛ መሻሻሎችን ይዘረዝራል። የጥናት አቅጣጫው፤ በጥቅል አማካይ ነጥቦች ላይ አትኩሮት በመስጠት በአብዛኛው ለከፍተኛ የፖሊሲ ውሳኔዎች ያገለግላል ተብሎ በምጣኔ ሃብት ባለሙያዎች የተመሰከረለትን፣ የገጠር ቤተሰብ ጥናት ትንተና የሚያካትት መሆኑ የተሟላ ምስል እንዲሰጥ ያግዛል። በአንጻሩ የWIDE ጥናት፣ በአሃዛዊ መረጃዎች ብቻ ሣይታጠር - በተለያዩ አብነታዊ የገጠር ማህበረሰቦች ምሣሌ እየሰጠ ህይወት በማላበስ እውነታውን ያሳያል።

የWIDE ጥናትን ለፖሊሲ አውጭዎች አገልግሎት ይሰጥ ዘንድ፣ በ2013 በአንኳር የጥናት ግኝቶች ላይ የተመሰረቱ ተከታታይ አጫጭር መግለጫዎች ለማዘጋጀት ተወሰነ። ኢልምት፤ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ትንተና ክፍሉን አጥኚዎች በማሳተፍ፣ 3 ከግብርና ልማት ጋር ፋይዳ ያላቸው ርዕሰ ጉዳዮችን አዘጋጅቷል። እነርሱም- 1) የግብርና ልማትን ማነቃቃት፤ 2) እርሻና የግብይት ሰንሰለቶች፤ እና 3)

ለገጠር ወጣቶች የሥራ ፈጠራ ናቸው፡፡ እነዚህና ሌሎች በግል አጥኚዎች የተዘጋጁ ሁለት አጫጭር የጥናት መግለጫዎች፣ ከኢትዮጵያ መንግስት ከፍተኛ ፖሊሲ አውጭዎች ጋር በመጋቢት 2014 ውይይት የተደረገባቸው ሲሆን አሁን በWIDE ድረገጽ ላይ ይገኛሉ፡፡ ይሄን ተከትሎም ከመንግስት ባለሥልጣናት ጋር በመመካከር በተለይ የፖሊሲ አውጭዎች የሚያተኩሩባቸው ፈርጀ ብዙ፣ ቁልፍ ርዕሰ ጉዳዮች ተነቅሰው ወጥተዋል፡፡ እነዚህ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ሁለተኛዎቹ፣ አስር ተከታታይ አጫጭር የጥናት መግለጫዎች፣ በ2016 በኢልምተ በተዘጋጀ ከፍተኛ የውይይት መድረክ ላይ፣ ለከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣናት ቀርበዋል፡፡ በእነዚህ አጫጭር መግለጫዎች ውስጥ የተካተቱ መረጃዎችና የውይይት ሃሳቦች፣ " *Change and Transformation in Twenty Rural Communities in Ethiopia: Selected aspects and implications for policy.*" በሚል ርዕስ፣ በጃንዋሪ 2017 በታተመ መጽሃፍ ምዕራፎች ውስጥ ተብራርተው ቀርበዋል፡፡

ይህ ስብስብ፤ በWIDE ጥናት ላይ የተመሰረቱ 10 አጫጭር መግለጫዎችን የሚያካትት ነው - ዘጠኙ በ2015 የተዘጋጁ ሲሆን፤ አንደኛው በ2014 ቀደም ብለው የቀረቡ አምስት አጫጭር መግለጫዎች አካል ሆኖ ከመንግስት ጋር የተደረጉ ውይይቶችና ጥልቅ የጥናት ጽሁፎች ዳራ ላይ በመመስረት የተሻሻለ ነው፡፡ እነዚህ የጥናት ጽሁፎች የመጽሐፉ ምዕራፎች መሰረት ነበሩ፡፡ የተሠናዱት አጫጭር መግለጫዎች፣ የተከለሱትና የተሻሻሉትም በዚህ ሥራ ላይ ተመርኩዞ ነው፡፡ አሁን በዚህ መልክ ተተርጉሞ የቀረበውም ለሰፊው የህብረተሰብ ክፍል ተደራሽ እንዲሆን ነው፡፡

የአስሩም አጫጭር የጥናት መግለጫዎች ትኩረት፤ በማህበረሰብ፣ በቤተሰብና በግለሰብ ደረጃ በተመዘገቡ ለውጦች ላይ ነው፡፡ በተለያዩ የኑሮ ዘርፎች በተለይም በኑሮ መተዳደሪያዎች፣ በጤናና ትምህርት እንዲሁም በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች (ሴቶች፣ እናቶች፣ ህጻናት፣ ወጣት ወንዶችና ሴቶች፣ የተማሩና ሃብታሞች፣ ሥራ ፈጣሪዎች፣ እንዲሁም ችግረኞችና ምስኪኖች ፣ለአደጋ ተጋላጭ ቡድኖችና ስደተኞችን ጨምሮ) ለውጦቹ ያስከተሉትን ውጤቶች ያሣያሉ፡፡

ጸሃፊዎቹ፤ የእመርታው አካል፣ በከተማ መስፋፋት ሂደቶች በከፊል የማህበረሰቦቹን የገጠር የአኗኗር ብሂል እየቀነሰ መምጣቱን፣ እንዲሁም ከዕድገቱ ጎን ለጎንም እየጎላ የሚመጣ የአስተሳሰብ ብሎም የኑሮ ደረጃ ልዩነቶች መፈጠራቸውን ያሣያል፡፡ አጫጭር መግለጫዎቹ፤ የስኬታማ አርሶ አደሮችና ነጋዴዎችን ሚና፣ የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎና ከስደት መመለስን በተመለከተ የተፈጠረ በጎ አመለካከትን ጨምሮ የአካባቢውን ነዋሪዎች የተነቃቃ እንቅስቃሴ ያትታሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ከወጣትነት ወደ አዋቂነት በሚደረግ ሽግግር ወጣቶች ከሚጋፈጧቸው ፈተናዎች፣ ወጣት ሴቶች፣ እናቶችና ህጻናት ከሚገጥማቸው አደጋዎች እንዲሁም ድህነትና ኋላ ቀርነት፣ ለኑሮ ደህንነት ዋነኛ እንቅፋቶች ከመሆናቸው ጋር የተያያዙ ጉዳዮችንም አጫጭር መግለጫዎቹ ይጠቅሣሉ፡፡

አስሩም መግለጫዎች፤ የሚያስቀድሙት በአንኳር ነጥቦች ላይ የሚያተኩር ማጠቃለያ ሃሳቦችን ተከትለው ነው የተዘጋጁት፡፡ መግቢያው፤ አንኳር ነጥቦችንና ድምዳሜዎችን አሳጥሮ ያቀርባል፣ የWIDE የአጠናን አቅጣጫን፣ የጥናት ዘዴዎችና ማህበረሰቦችን ያስተዋውቃል፤ የጥናቱን ፋይዳ ያብራራል፤ በጥናቱ ላይ ለተሳተፉ አጥኚዎች ምስጋና ያቀርባል፤ እንዲሁም በድረገጽ ላይ የሚገኙ ሌሎች ህትመቶችን ይዘረዝራል፡፡

እንደ ኢትዮጵያ የልማት ምርምር ተቋም የፕሮግራም ዳይሬክተርነቴ፣ በዚህ መለስተኛ መጽሃፍ ውስጥ የተካተቱ አጫጭር የጥናት መግለጫዎች፣ በታችኛው ማህበረሰብ፣ በቀበሌ ደረጃ ያሉትን እውነታዎች፣ ግንዛቤ ለማሳደግ፣ ጠቃሚ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል ብዬ አምናለሁ፡፡ እነዚህ እገዛዎችና ምሣሌዎች በለውጥ እንቅስቃሴዎችና ንድፎች፣ እንዲሁም ልማትን ለማስፋፋት በሚቀረጹ ፖሊሲና ፕሮግራሞች ላይ ለሚደረጉ ውይይቶች የሚያነቃቁ ጠቃሚ ግብአቶችን ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡

ገብረህይወት አገባ ከበደው (ዶክ. በፍልስፍና)

የፕሮግራሞች ዳይሬክተር

የኢትዮጵያ የልማት ምርምር ተቋም (ኢልምተ)

የጥናቱ ሂደት

የWIDE[1] ኢትዮጵያ የውይይት መነሻ አጫጭር የጥናት መግለጫዎች መግቢያ

<u>ዋና ዋና ነጥቦች</u>

- *WIDE ኢትዮጵያ ምንድን ነው?*
  - በአራት የኢትዮጵያ አራት ማዕከላዊ ክልላዊ መንግስታት ውስጥ በሚገኙ 20 የገጠር ማህበረሰቦች፣ በሁሉም የህይወት ዘርፎች ላይ፣ እንደ አውሮፓውያን ቀን አቆጣጠር[2] ከ1995 ጀምሮ በ3 ዙሮች የተካሄደ ገለልተኛ፣ ጥብቅና የተደራጀ፣ ቅርበትንና ጥልቀትን የተላበሰ፣ የረዥም ዓመታት ዓይነተኛ ጥናት ሲሆን፤ የቅርብ ጊዜ መረጃዎቹም የተሰበሰቡት ከ2011 እስከ 2013 ባሉት አመታት ነው።
- *የWIDE ኢትዮጵያ የት ሰፍራ ተሰማራ?*
  - ዋና የግብርና ሥነ ምህዳሮች ዓይነተኛ ምሳሌዎች በሆኑ፣ 20 የቀበሌና ንኡስ ቀበሌ አካባቢዎች ፡- 9 በትርፍ አምራችነት ወይም በእርሻ ልማት አቅም የሚታወቁ አካባቢዎች፤ 2 የአርብቶ አደር አካባቢዎች እና 9 ዝናብ አጠር ተብለው የሚመደቡ አካባቢዎች ስራውን አከናውኗል።
- *WIDE ኢትዮጵያ እንዴት ነው የሚሠራው?*
  - በጥናቶቹ የተካተቱት ማህበረሰቦች፣በጊዜ ሂደት በለውጥ ጉዞ ላይ የሚገኙ፣ በመስተጋብር የተሳሰሩ፣ ባለ ብዙ ፈርጅ ማህበራዊ ሥርዓቶች እንደሆኑ ይገነዘባል። መረጃዎቹ የተሰበሰቡት፣ የተተረጎሙትና የተተነተኑት ከህብረተሰብና ስነሰብዕ የማህበራዊ ሳይንስ ዘርፎች በተወሰዱ፣ ከፍተኛ ተቀባይነትን ባተረፉ ዓይነተኛ የጥናት ስልቶችን በመጠቀም ነው።
- *WIDE ኢትዮጵያ፤ ለፖሊሲ አውጭዎችና ባለሙያዎች ጥቅሙ ምንድን ነው?*
  - ትልቁን የገጠር ህይወት፤ በትንሿ መንደር እስከ ጓዳ በመዝለቅ፣ ምሉዕ የገጠር ህይወትን ግንዛቤ ያስጨብጣል።
  - አድሎ የሌለው፣ በወጉ የተሠናዳ፣ ግዙፍ እና የዳበረ መረጃ ያቀርባል - ከቁጥሩ ጀርባ ያለውን እውነታ ለፖሊሲ አውጪዎች ቁልጭ አድርጎ የሚያሣይ ነው።
  - በመካሄድ ላይ ያለውን የለውጥ ሂደት እና የአካባቢን እድገት ወሣኝ የሆኑ ኩነቶች ጋር ያለውን መስተጋብር ግንዛቤ ያዳብራል።

[1] WIDE is the name of the research project. It stands from Wellbeing Illbeing Dynamics in Ethiopia (የደህንነትና ኢ-ደህንነት መስተጋብር በኢትዮጵያ).

[2] እዚህ መጽሃፍ ውስጥ ቀኖች በሙሉ በአውሮፓውያን አቆጣጠር መሆኑን ልብ ይሏል።

- *በዚህ መለስተኛ መጽሐፍ ውስጥ ምን ተካትቷል?*
  - WIDE በውል በተለዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የሰራው ጥናት፣ አንኳር ግኝቶችን ጨምቀው የሚያቀርቡ 10 አጫጭር መግለጫዎች የሚገኙ ሲሆን የኢትዮጵያ ዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ያለውን ጽንሰ ሃሣብ እና የሚገኙ ውጤቶችን ማሻሻል በሚቻልባቸው ሁኔታዎች ላይ ቀጣይ ውይይት እንዲኖር ግብአት እንዲሆኑ የታሰቡ ናቸው፡፡ የሚዳስሷቸው ርዕሰ ጉዳዮችም፡-
    - የገጠር ከተሜነት መስፋፋት፣ የከተማ ወደ ገጠር አካባቢዎች መስፋፋት እና የገጠር-ከተማ ትስስሮች መደርጀት (አጭር መግለጫ ቁ. 1፡- የገጠር ከተሜነት መስፋፋት)
    - ኢ-እኩልነት እና የኑሮ ደረጃ ልዩነቶች በገጠር ማህበረሰቦች ፤ 2010-2013 (አጭር መግለጫ ቁ. 2፡- ኢ-እኩልነት)
    - ከወጣትነት ወደ አዋቂነት በገጠር ማህበረሰቦች ያሉ ሽግግሮች ፤ 2010-2013 (አጭር መግለጫ ቁ. 3፡- ወጣትነት)
    - ትምህርት በገጠር ኢትዮጵያ 2010-2013 ፡- ህልምና ጥርጣሬ (አጭር መግለጫ ቁ. 4፡- ትምህርት)
    - በኢትዮጵያ የገጠር አካባቢዎች በእናትና በጨቅላ ህጻናት ጤንነትና ደህንነት ዙሪያ የታዩ የለውጥ ሁኔታዎች፤ 2003-2013 (አጭር መግለጫ ቁ. 5፡- እናቶችና ጨቅላ ህጻናት)
    - የሴቶችና ልጃገረዶች ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ በገጠር ኢትዮጵያ ማህበረሰቦች፤ 2010-2013 (አጭር መግለጫ ቁ. 6፡- ሴቶች)
    - በገጠር ማህበረሰቦች ለሥራ ፍለጋ የሚደረግ ፍልሰት፤ 2010-2013 (አጭር መግለጫ ቁ. 7፡- ፍልሰት)
    - በገጠር ኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ ስኬት ላይ የሚስተዋሉ ዕይታዎች 2010-2013 (አጭር መግለጫ ቁ. 8፡- ስኬት)
    - የለውጥ ጽንሰ ሃሣብ (ትራንስፎርሜሽን) እውነታዎች እና አርአያዎች/ሞዴሎች፤ 2010-2013 (አጭር መግለጫ ቁ. 9፡- አርአያዎች/ሞዴሎች)
    - የዕውቀት ስርጸት፣ ትምህርት መቅሰም፣ “የቴክኖሎጂ ሽግግር” እና ለውጥ በገጠር ማህበረሰቦች፤ 2010-2013 (አጭር መግለጫ ቁ. 10፡- ለውጥ)

<u>ዋና ዋና ድምዳሜዎች</u>

- አጫጭር የጥናት መግለጫዎቹ፤ WIDE በተከታተላቸው 20 ማህበረሰቦች ውስጥ የታየውን ለውጥና እመርታ ያትታሉ፡፡ ከ1995 ወዲህ ባሉት ጊዜያት ማህበረሰቦች ያሳዩት ፈርጀ ብዙ ለውጥ ከግምት በላይ ነው ::
- ማህበረሰቦቹ ከውጭው ዓለም ጋር ለመገናኘት ይበልጥ በራቸውን ከፍተዋል፡፡ ይኸውም በነዋሪዎቹ የራዕይና የህልም ስፋት ላይ ይንጸባረቃል፡፡

- የየአካባቢው ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ዘርፎች በዓይነቶች የበለጠ ተስፋፍተዋል፡፡ የገጠር ማህበረሰቦች እንዲያድጉ ኢኮኖሚያቸውን በዓይነትና በዘርፍ ይበልጥ ማበራከት እንዳለባቸው የWIDE ጥናት ይጠቁማል፡፡ ይህም ከእርሻ ውጭ ለሆነ ዘርፍ የላቀ ትኩረት መስጠትን ይጠይቃል፡፡
- በተመሳሳይ የኑሮ ደረጃ ልዩነት ጨምሯል፡፡ የድሃ ወይም የተጋላጭ ነዋሪዎችን ሁኔታ በተመለከተ ይበልጥ ግንዛቤ ማዳበር ለቀጣይ የለውጥ እርምጃዎች መነሻ መሆን እንደሚገባው እንዲሁም የተደራሽነት ችግሮችን ይበልጥ ለማቃለልም መሰረት መሆን እንደሚኖርበት ጥናቱ በአጽንኦት ይገልጻል፡፡ አንድም ሰው ወደ ኋላ እንዳይቀር እንዲህ ዓይነቱ ግንዛቤ ወሳኝ ነው፡፡
- የታዳጊ ወጣቶች ምኞትና ራዕይ ጨምሯል፡፡ ይሁን እንጂ ወደ አዋቂነት የሚያደርጉት ሽግግር ፈተናዎች በዛው ልክ ጨምሯል፡፡ WIDE፤ ለወጣቶች የኑሮ መተዳደርያ አማራጮችን የበለጠ ማስፋት እንደሚያስፈልግ ይጠቁማል፡፡ ከእነዚህም መካከል፤ ከእርሻ ውጭ የሆኑ ዘርፎችን መደገፍና ብሎም ከቀዬያቸው ውጪ ተዟዙሮ የመሥራትና የማደግ ዕድሎችን ማመቻቸት አስፈላጊነት ይጠቁማሉ፡፡
- እየተስፋፋ የመጣው የጤና አገልግሎትና ሌሎች የለውጥ እንቅስቃሴዎች፣ የሴቶችን ህይወት የበለጠ ለማሻሻል ጠቅመዋል፡፡ ነባር ማህበራዊ ልማዶችን ለመለወጥ መትጋትና የወንዶችን ስጋቶች በሚያስተናግድ መልኩ እርምጃውን ማፋጠን እንደሚያስፈልግ ጥናቱ ያስገነዝባል፡፡
- በመጨረሻም የጥናት መግለጫዎቹ፤ ለቀጣይ ሁሉን አቀፍ ለውጥ፣ የፖሊሲ ዝግጅትና አፈጻጸምን የሚያሻሽሉ ሦስት መንገዶችን ይጠቁማሉ፡፡ እነርሱም፡-
  - የተለያዩ ዘርፎችን የሚያስተሳስር ሁሉን አቀፍ አቅጣጫ መቅረጽ
  - የአካባቢውን ነባራዊ ሁኔታ በአገናዘበ መልኩ የተቃኙ ምላሽ የሚሰጡ የለውጥ እንቅስቃሴዎችን ማስፋፋት፤ እና
  - ለየአካባቢው ግንዛቤና በጋራ የመማማር እንዲሁም አዲስ ነገር የመሞከር ጥረት ቅድምያ መስጠት

- *ከWIDE ኢትዮጵያ፤ ባሻገር ምንምን የህትመት ውጤቶችና የመረጃ ምንጮች ይገኛሉ?*
  - በእንግሊዝኛ የተሰናዳው እና የእነዚህ የውይይት አጫጭር መግለጫዎች፣ መነሻ የሆነው ረዥም ከፍል፣ በአሉላ ፓንክረስት አርታኢነት፤ 'Change and Transformation in 20 rural communities in Ethiopia: selected aspects and implications for policy' (2017) በሚል ርዕስ ታትሟል፡፡
  - የ WIDE ኢትዮጵያ ሙሉ ዝርዝር መረጃ፤ በ2016 በተከፈተው ድረገጽ www.ethiopiawide.net. ላይ ይገኛል፡፡ በድረገጹ ላይ የሰፈሩ መረጃዎች፤ የተለያዩ ዘርፈ ብዙ የጥናት መረጃ ዝርዝሮችን፣ የመንደር አጫጭር መግለጫዎችን፣ የጥናት ዘገባዎችንና ህትመቶች ከብዙ በጥቂቱ ናቸው፡፡

- *በWIDE ኢትዮጵያ የተሣተፉት እነማን ናቸው?*
  - ከዋናዎቹ የጥናት ቡድኑ በተጨማሪ ከ100 በላይ ዘርፈ - ብዙ ኢትዮጵያውያን ተመራማሪዎች፣ በጥናቱ አመራርና የመረጃ አሰባሰብ ላይ ተሳትፈዋል። (በአባሪ ቁ. 1 ላይ ይመልከቱ)።
  - የተለያዩ የኢትዮጵያ የልማት አጋሮች ጥናቱን ለዓመታት በገንዘብ ደግፈዋል።
  - እነዚህ አጫጭር የጥናት መግለጫዎች፤ በ2014 እና 2016 በኢትዮጵያ የልማት ምርምር ተቋም (ኢልምተ) የተዘጋጁ ከፍተኛ መድረኮችን ጨምሮ በተለያዩ መድረኮች፣ የኢትዮጵያ ከፍተኛ ፖሊሲ አውጭዎችን ትኩረት በማግኘታቸውና ለውይይት በመቅረባቸው በእጅጉ ተጠቅመዋል።

- *ማሰታወሻ፡-*
  - በዚህ ጥራዝ ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች፣ የኢልምተን ወይም የኢትዮጵያ መንግስትን አሊያም የልማት አጋሮቹን አመለካከት የግድ አይወክሉም፤ ይልቁንም በፖሊሲ ላይ የሚደረጉ ውይይቶችን ለማነቃቃት የታለሙ ናቸው።

የWIDE ኢትዮጵያ ጥናት ምንድን ነው?

WIDE ኢትዮጵያ፤ በኢትዮጵያ 20 የገጠር ማህበረሰቦች፣ለ20 ዓመት የተካሄደ ጥብቅና የደረጀ፣ ራሱን የቻለ፣ የረዥም ጊዜ ክትትል ጥናት ነው። 20ዎቹ የWIDE ማህበረሰቦች፤ በአራት የአገሪቱ ማዕከላዊ ክልሎች የሚገኙ ዋና የግብርና ምህዳሮች ዓይነተኛ ምሳሌዎች ናቸው። እነዚህ ቦታዎች፤ 9 ትርፍ አምራች ወይም የእርሻ ልማት አቅም ያላቸው አካባቢዎችን፣2 አርብቶአደር አካባቢዎችንና 9 ዝናብ አጠር ተብለው የተለዩ አካባቢዎችን ያካትታሉ።

በዝናብ አጠር ወረዳዎች ውስጥ የሚገኙ 6 አካባቢዎች በኋላ WIDE ኢትዮጵያ የጥናት ክትትል በሚያደርግባቸው አካባቢዎች ውስጥ የተካተቱ ሲሆን ቀደም ብሎም በ1980ዎቹ ፣"በኢትዮጵያ የገጠር ቤተሰብ ዳሰሳ" (Ethiopian Rural Household Survey) ተጠንተው ነበር። በ1990ዎቹ አጋማሽ ላይ WIDE1፤ የ15 ማህበረሰቦችን አጫጭር የመንደር መግለጫዎች ያዘጋጀ ሲሆን እነዚህ አካባቢዎችም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ የትምህርት ክፍል፣ በዓለም አቀፍ የምግብ ፖሊሲ ምርምር ተቋምና በኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ የአፍሪካ የኢኮኖሚ ጥናት ማዕከል፣ የተለያዩ የግብርና ምህዳሮችን ይወክላሉ ተብለው የተመረጡ ነበሩ[3]። እነዚህ አካባቢዎች ሦስት የገበያ እህል አምራች ማህበረሰቦች የታከሉባቸው ሲሆን በ2003 WIDE2፤ ሁለት የአርብቶአደር አካባቢዎችን ጨምሮባቸዋል[4]። ከዚያም WIDE 3፤ በሦስት ምዕራፎች፣ ወደ 20ዎቹ ማህበረሰቦች በመመለስ አጥንቷቸዋል። በ2010፣ የWIDE3 ምዕራፍ1 ጥናት፤ በWIDE2 በጥልቀት የተጠኑ 6 ማህበረሰቦች ላይ ያተኮረ ነበር (3 የምግብ ዋስትና

[3] እነዚህ፤ የአፍሪካ ኢኮኖሚዎች ጥናት ማዕከል ጥናት (the Centre for the Study of African Economies) (1994) ድረገጽ ላይ ይገኛሉ፡- http://www.csae.ox.ac.uk/evstudies/main.html

[4] ደህንነት በማደግ ላይ ባሉ አገራት (Wellbeing in Developing (WED) Countries በሚለው ጥናት ወቅት፡- http://www.welldev.org.uk

የተረጋገጠባቸውና 3 ዝናብ አጠር)። ከ2011-12፣ የWIDE3 ምዕራፍ2 ጥናት፤ ስምንት ዝናብ አጠር አካባቢዎችን ያካተተ ሲሆን በ2013፣ WIDE 3 ምዕራፍ3፤ የተቀሩትን የእርሻ ልማት አቅም ያላቸው 6 አካባቢዎች አጥንቷል።

WIDE ኢትዮጵያ የት ነው የሰራው? 20 የWIDE ማህበረሰቦች ካርታ



WIDE ኢትዮጵያ እንዴት ይሰራል?

WIDE ኢትዮጵያ፤ በትን ኗ የኢትዮጵያ መንደር እስከ ጓዳ በመዝለቅ፣ምሉዕ የገጠር ህይወትን የመገንዘብ ሁሉን አቀፍ የአጠናን አቅጣጫ ተጠቅሟል። WIDE ኢትዮጵያ፤ የሚጠኑትን ማህበረሰቦች፣ በጊዜ ሂደት በለውጥ ጉዞ ላይ የሚገኙ፣በመስተጋብር የተሳሰሩ፣ ባለ ብዙ ፈርጅ፣ ማህበራዊ ሥርዓቶች እንደሆኑ ይቀበላል። መረጃዎቹ የተሰበሰቡት፣የተተረጎሙትና የተተነተኑት ከህብረተሰብና ስነሰብዕ የማህበራዊ ሳይንስ ዘርፎች በተወሰዱ፣ ከፍተኛ ተቀባይነት ያገኙ፣ አብነት-ተኮር የጥናት ስልቶችን በመጠቀም ነው። ጥናቱ፤ የቀበሌ ወይም ንኡስ ቀበሌ ማህበረሰቦችን የለውጥ ሂደት፤ በተለያዩ ግለሰቦችና ቤተሰቦቻቸው ተሞክሮዎች አማካኝነት ይከታተላል።

ሃያ ዓመታት የሚሸፍኑ የሦስት ዙር ጥናቶች ከተደረጉ በኋላ፣ የWIDE ጥናት ፕሮግራም፤ እነዚህ ማህበረሰቦች እንዴት እንደተለወጡ፣ በረዥም ጊዜ ክትትል የተገኘ ግንዛቤ መስጠት ችሏል። ጥብቅና የደረጀ፣ ጥልቀትና ቅርበት የተላበሰ ዓይነተኛ የአጠናን ሥርዓትና አቅጣጫው፤ በገጠር የታየውን ለውጥ በተመለከተ (ይበልጥ ከተለመደው) ከአሃዛዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ የቁጥር መረጃ የተለየ ጠቃሚ ማንጸርያ ይሰጣል። እንዲህ ያለው መረጃ በአብዛኛው ለከፍተኛ ደረጃ ውሳኔ አሰጣጥ (በመንግስትም ይሁን የልማት ኢጋሮቹ) የሚውል ነው፤ ነገር ግን የገሃዱ አለም እውነተኛ ህያው የለውጥ ተሞክሮ፣ አካባቢያዊ ስሜት/ቀለም፣ የዕይታ አንጻርና ውስብስብነት በአብዛኛው ያዳፍነዋል ወይም ያድበሰብሰዋል አሊያም ያዛባዋል። WIDE ኢትዮጵያ በአንጻሩ አብነታዊ በሆኑ በርካታ የገጠር መንደሮች፤ ለቁጥሮች ነፍስ በመዝራት ለፖሊሲ አውጭዎች፣ "ከቁጥሮቹ ጀርባ ያሉትን እውነታዎች" ለመገንዘብ የሚያስችል ገለልተኛ መረጃ ይሰጣል።

WIDE ኢትዮጵያ ለፖሊሲ አውጭዎች ለምን ያሰፈልጋቸዋል?

WIDE ኢትዮጵያ፤ ለፖሊሲ አውጭዎችና የልማት አጋሮቻቸው፣ በተለይ በአሁኑ መንግስት- መር ልማታዊ ድባብ ውስጥ ጠቃሚ መሆን አለመሆኑ ሊያከራክር ይችላል። የኢትዮጵያ መንግስት፤ ከውሳኔ ወደ ኋላ የማይልና በተግባር የተጠመደ ነው - ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት በማህበረሰቦች ውስጥ ከዳር እስከ ዳር ጉልህ ለውጥ አስመዝግቧል። በታህሳስ 2010፣የቀድሞው ጠ/ሚ መለስ ዜናዊ፣ የላኦ ትዙ "ከህዝብ ተማሩ"[5] የሚል ዝነኛ ተግሳጻዊ ምክር ያረበበበት አስተያየታቸውን ሰንዝረዋል። የየአካባቢው አገር በቀል ግኝት (ፈጠራ) ያለውን ፋይዳ አጽንኦት ሰጥተው የተናገሩ ሲሆን መንግስት መፍጠር ስለሚፈልገው ሥርዓት ሲናገሩም፡-

> *"እያንዳንዱ ቡድን፣እያንዳንዱ መንደር፣ የየራሱን ዕቅድ መቅረጽ ይችላል [ይህም---] ሰዎች በአገር አቀፉ ዕቅዳችን ጥላ ሥር ሆነው፣ የራሳቸውን አቅምና ጉልበት ለማውጣት፣የራሳቸውን ጥሪት አሟጠው ለመጠቀምም ያስችላቸዋል"*[6] ብለው ነበር።

የWIDE መረጃ ትልቁ ፋይዳው ዜጎች ለውጡን በዕውን እየኖሩትና መልሰው እየቀረጹት፤ ሰፊውን የገጠር ህይወት ወካይ በሆነችው በትንሿ መንደር ያለውን መሰረታዊ ቀጣይ ለውጥን ግንዛቤ ማሳደጉ ነው። የተለያዩ አካባቢያዊ ንቅናቄዎች ከፊርጆ ብዙ የማዘመን እንቅስቃሴዎች ጋር የሚፈጥሩትን መስተጋብር ያሣያል። ምን እንደሚለወጥና ምን እንደማይለወጥ፤ እንዴት የማህበራዊ፣ባህላዊ፣ኢኮኖሚያዊ ወይም ፖለቲካዊ ግንዛቤ አካባቢያዊ ስርዓቶች እንደሚሻሻሉ ወይም እንደሚጠናከሩ ፣አካባቢ በቀል የፈጠራ ሂደቶች ወይም ለውጦች እንዴት እንደሚጀመሩ እና እንደሚዘልቁ፣ አንዳንዴም እንደሚሰናከሉ ያሳያል። በተጨማሪም አዳዲስ አሰራሮች ወይም የዕድገት ሂደታቸው እንዴት እንደሚቀረጹ፣ በጅምር እንደሚቀሩ በዜጎችም ይሁን በሌሎች ቡድኖች አቻዎችና ቤተሰቦች ወይም በቀበሌ/ወረዳ አስተዳደሮች፣ ተወካዮች፣ ፖለቲከኞችና

---

[5] "ከህዝቡ ተማር፤ ከህዝቡ ጋር አቅድ። ህዝቡ ባለው ነገር ጀምር፤ በሚያውቁት ላይ ገንባ። ለምርጥ መሪዎች፣ ሥራው ሲሳካ፣ ህዝቡ 'ራሳችን ነን የሰራነው ' የሚል አስተያየት ይሰጣል" አስተያየቱ በቅርቡ በ Pascale, Sternin & Sternin (2010) *The Power of Positive Deviance: How Unlikely Innovators Solve the World's toughest problems*, Boston: Harvard Business Press ተጠቅሷል።

[6] የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በ5ኛው ዓለም አቀፍ የፌደራሊዝም ጉባኤ ላይ (ታህሳስ 4፣2010) በሾን ሆሊሃን የተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ፤ ከኢትዮጵያ ፌደራሊዝም፡ http://www.ethiopianfederalism.org/ ላይ የተገኘ ቪዲዮ።

የአገር ሽማግሌዎች፤ በነጠላም ይሁን በጋራ ተቀባይነት እንደሚያገኙ፣ ተቃውሞ እንደሚገጥማቸው ወይም ውድቅ እንደሚሆኑ ያሣያል።

ከቀድሞው ሁለት አሥርት ዓመታት (1990ዎቹ፣2000ዎቹ) መረጃዎች ጋር ሲነጻጸር፣ የ WIDE 3 የማህበረሰብ አጭር መግለጫዎች (በ2010-13 ጥናት ላይ ተመስርቶ)፤ በተከታታይ የተነቃቃ የለውጥ ሂደቶች የታጀበ የገጠር እመርታን ያትታሉ። ከእነዚህ ውስጥ፤ አንዳንዶቹ መንግስት መር ናቸው። በእነሱ አማካኝነት የተገኘውን ፈጣንና ጥልቅ የግለሰብና ማህበራዊ የለውጥ ሂደቶችንም ይዘግባሉ። እነዚህ ለአብዛኞቹ የለውጡ ተሳታፊዎች በእጅጉ ውጤታማ፣ አርኪ ወይም ትርፋማ ነበሩ። ጥናቱ ፤ የልማት ጥቅሎችንና የፖሊስ ማዕቀፎችን በተመለከተ (በWIDE ኢትዮጵያ፣ የ2014 ከፍተኛ የውይይት መድረክ ላይ በአንድ ከፍተኛ ባለሥልጣን እንደተገለጸው፤) ለሁሉም ችግር አንድ ብቸኛ መፍትሄ የለም[7] የሚለውን ሃቅ የሚያበለጽግ በቂና ጠቃሚ መረጃም ያቀርባል።

የአካባቢ ባለሥልጣናት ወይም የልማት አጋሮች፣ ያሰቡትና ያቀዱት ሁሉ በቅጡ ተሰርቷል፤ መልዕክቱ በብልሃት ደርሷል ወይም ተፈጻሚ ሆኗል፤ አሊያም ሁሉም በሙሉ ልብ፣ በጉጉት ተቀብለውታል ማለት አይደለም። አብዛኞቹ የተለወጡ ነገሮችም፤ የሚኖሩበትን ማህበረሰብ፣ ማህበራዊ እሴት ለመጠቀም በራሳቸው የተጉ ግለሰቦች አቅም፣ ኢንቨስትመንት፣ ሃብትና ገንዘብ ውጤት ናቸው። ፈጣን ዕድገት ለሁሉም ባይሆንም - ለተወሰኑ ግለሰቦች የተሻለ የኑሮ ሁኔታ፣ ትልቅ ሃብትና ከፍተኛ ዕድሎችን አምጥቶላቸዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ ሁሉም ሣይሆን አንዳንድ የማህበረሰብ የተወሰኑ ክፍሎችም አስመዝግበዋል። የ WIDE መረጃ፤ የተለያዩ ውጤቶች መቼ፣ እንዴትና ለምን እንደተከሰቱ ለማብራራት ይጠቅማል። እነዚህ መልዕክቶች (ነጥቦች)፤ በአነስተኛ ደረጃ ለአዲስ የፈጠራ ውጤታማ የኑሮ መተዳደሪያዎችና አሰራሮች እንዲሁም ለሁሉን አቀፍ ልማታዊ እመርታ፣ ምላሽ በመስጠት ሥራ ላይ ለተሠማሩ ትልቅ ፋይዳ አላቸው።

የ WIDE ኢትዮጵያ ማህበረሰቦች አጠቃላይ የሃገሪቱን እውነታ ይወክላሉ?

የWIDE ማህበረሰቦች፤ በአቦሰጥ እንዳስፈላጊው ሁኔታ እንደሚመረጡና በአግባቡ እንደሚመጠኑ ናሙናዎች፣ ሰፊ እውነታን "ወካይ" (representative) አይደሉም። ሆኖም ግን በፈርጀ- ብዙ ቁልፍ መለኪያዎች፣ መጠነ ሰፊ ልዩነቶችን ያቀፉ፣ የተለያዩ የገጠር ማህበረሰቦች ዓይነተኛ ምሳሌዎች ተብለው የተመረጡ ናቸው። እነዚህም የኑሮ መተዳደርያ፣ የባህልና ከማንነት ጋር የተዛመዱ ጉዳዮች፣ የሃይማኖት ጥንቅርና የመሳሰሉት ይገኙባቸዋል (ከዚህ በታች፣ በዚህ አጭር መግለጫ ማብቂያ ላይ፣ የተለያዩ የኑሮ መተዳደርያና የባህል ዘርፎችን ነቅሰው የሚያሳዩና ጠቅለል የሚያደርጉ ካርታዎች ተካትተዋል)። ይህ የጥናት አቅጣጫ፤ እንደየማህበረሰቡ መልክና ፈርጅ ከፍተኛ ተቀባይነት ያገኙ፣ አብነት-ተኮር ስልቶችን ተጠቅሞ፣ መረጃዎቹን በመተንተን ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ፣በእነዚህ አካባቢዎች የተገኙ የመረጃና ተሞክሮ ዝንባሌና አዝማሚያዎች፣ በሌሎች ማህበረሰቦችም መኖራቸው አፍ ሞልቶ መናገር ያስችላል። በዚህ የተነሳም፣ በአጠቃላይ

[7] የተከበሩ አቶ ነዋይ ጉበረአብ፤ በሸራተን አዲስ፣ መጋቢት 2014፣ በከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣናት ደረጃ፣ በ WIDE የጥናት ግኝቶች እንደምታዎች ላይ ለመወያየት በተዘጋጀ ፎረም ላይ የተናገሩት።

በጥናቱና በተለይ በእነዚህ የውይይት መነሻ አጫጭር መግለጫዎች የተደረሱባቸው ድምዳሜዎች፣ ሰፊ የማህበረሰብ እውነታን የሚያንጸባርቁ ናቸው ለማለት ያስደፍራል።

በቅርቡ የተሰራው ጥናት (WIDE3)፣ ለንፅፅርና ለድምዳሜ መነሻነት የማዋል ጉዳይ ላይ፣ ጥቂት የጥንቃቄ ማሳሰቢያዎችን ማስቀደም ያስፈልጋል። WIDE3፣ ከ2010 እስከ 2013 አራት ዓመታትን የሚሸፍንና፣ በየተራ የተለያዩ የማህበረሰብ ዓይነቶች ላይ ያተኩሩ ሦስት ምዕራፎችን የሚያካትት ጥናት ነው። በዚህም የተነሳ፣ ጥናቱን ለማነፃፀሪያነት ማዋል ትንሽ የተወሳሰበ ባህርይ አለው። ምክንያቱም ከማህበረሰቡ ዓይነትና መልክ ጋር የተያያዙ፣ እንዲሁም ከ2010 እስከ 2013 ድረስ፣ በፖሊሲ አፈጻጸምና በሰፊው አውድ ላይ ከተከሰቱት ሂደቶች ጋር የተሳሰሩ፣ የተለያዩ ውጤቶችና ተጽዕኖዎች እርስ በእርስ የተጠላለፉ በመሆናቸው፣ እያንዳንዱን በተናጠል መለየትና አንጥሮ ማየት ያስቸግራል። ለምሳሌ በ2010፣ የመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን (GTP1) አፈጻጸም ገና አልተጀመረም፤ የጥናት አካባቢዎቹም ጋር አልደረሰም ነበር። በ2011 እና በ2012 መግቢያ ላይ ደግሞ፣ በወቅቱ እየተነበኙ በነበሩት ማህበረሰቦች ውስጥ፣ የእቅዱ አፈጻጸም ገና ከለጋነት አላለፈም ነበር። ከመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን አፈጻጸም የፈለቀ ውጤትና ተጽዕኖ በጨረፍታም ቢሆን ለማየት የተቻለው፤ በ2013 በጥናቱ የመጨረሻ ምዕራፍ ላይ ብቻ ነበር፣ ለዚያውም ከፍተኛ የግብርና ምርታማነትና የልማት አቅም አላቸው በተባሉ አካባቢዎች ብቻ።

የWIDE ኢትዮጵያ የውይይት መነሻ አጫጭር የጥናት መግለጫዎች

በዚህ ጥራዝ ውስጥ የተካተቱት የውይይት መነሻ አጫጭር የጥናት መግለጫዎች፤ ቀደም ብለው በተገለጹት 10 ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ናቸው። ዘጠኙ አጫጭር መግለጫዎች በ2016 የተዘጋጁ ሲሆኑ አስረኛው (አጭር መግለጫ ቁ. 9፡- አርአያዎች) ደግሞ በማርች 2014 በኢትዮጵያ መንግስት ከፍተኛ ፖሊስ አውጭዎች ውይይት የተደረገባቸው የመጀመሪያዎቹ አምስት ተከታታዮች አካል ነበር። ከእነዚህም ውስጥ ሦስቱ ፡- የግብርና ልማትን ማነቃቃት፣ እርሻና የገበያ ሠንሰለቶች እንዲሁም የሥራ ፈጠራ ለገጠር ወጣቶች በሚሉ ርዕሶች፣ በኢትዮጵያ የልማት ምርምር ተቋም (ኢልምተ)፣ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ትንተና ክፍል የተዘጋጁ ናቸው። አንድ ሌላ ደግሞ በፍትሃዊ የአገልግሎት አቅርቦት ላይ በቤቨርሊ ጆንስ ተዘጋጅቷል።

ሁለተኛው የአጫጭር መግለጫዎች ስብስብ፤ የረዥም ዓመት ልምድ ባካባቱ የኢትዮጵያውያን ቡድን ሙያዊ ግምገማ የተደረገበት ሲሆን እያንዳንዱ የቡድኑ አባላት በተያያዥ የሙያ ዘርፍ የምርምር ክህሎት ያላቸው ናቸው[8]። አብዛኞቹ መግለጫዎች፤ *Change and Transformation in Twenty Rural Communities in Ethiopia* በተሰኘው መጽሐፍ ውስጥ በጥር 2017 የታተሙትን ረዥም የትንተና ጥናታዊ ጽሁፎች ጨምቀው ያቀርባሉ። ጽሁፎቹ አንድም ምሁራዊነት የጎላባቸው አልያም በእያንዳንዱ ዘርፍ መረጃዎች ላይ በመመስረት ይበልጥ የተሟላ ትንታኔ ይሰጣሉ። ይሄ ሁለተኛው ስብስብ፤ በመጋቢት 2016 ማብቂያ ላይ በተደረገ መድረክ፣ ከኢትዮጵያ መንግስት ፖሊሲ አውጭዎች ጋር ውይይት ተደርጎበታል። የጥናት ጽሁፎቹም፤ በተሰጡት አስተያየቶችና ምላሾች ላይ ተመስርቶ በጥቂቱ ተሻሽለዋል።

[8] በእያንዳንዱ አጭር የጥናት መግለጫ ላይ የአዘጋጁ ወይም የአዘጋጆቹ ቡድን እንዲሁም ባለሙያ ገምጋሚዎች ተጠቅሰዋል።

በስብስብ 1 እና ስብስብ 2 የተካተቱት እያንዳንዱ የጥናት መግለጫዎች፤ የፖሊሲ ሃሳቦችን ፈትፍቶ ባያጎርስም፣ በኢትዮጵያ መንግስትና በልማት አጋሮች ቀጣይ የትብብር ጉዞ ላይ፣ ፖሊሲ አውጭዎች የሚያተኩሩባቸው ጉዳዮችንና ታሳቢዎችን በየጭብጣቸውና በየፈርጃቸው ነቅሶ በማውጣት ለማሣየት ይሞክራል። ይህም፣ የኢትዮጵያ የገጠር ነዋሪዎች ተዳፍኖ የቆየ ውስጣዊ አቅማቸውን፣ ኃያል ጉልበታቸውን፣ አይበገሬ ብርታታቸውን፣ የብልሀት ፀጋቸውን፣ ከታመቀበት አውጥተው እንዲያቀጣጥሉና እንዲገሰግሱ፤ እንደየአካባቢው ሁኔታ በልዩ ልዩ መልክ ለተከሰተው የፈጠራ ተነሳሽነትና የለውጥ ሕብር የሚቀርበው ድጋፍ፣ ለአገራዊ እድገት የላቀ ውጤት እንዲኖረው ለማድረግ ሲባል ነው። በስብስብ 1 እና ስብስብ 2 የተካተቱት የእንግሊዝኛ የውይይት መነሻ አጫጭር መግለጫዎች ቅጂ፤ ከጥናት ቡድኑ ወይም በድረገጽ ላይ ይገኛሉ። www.ethiopiawide.netን መመልከት ይቻላል።

<u>ድምዳሜዎች</u>

በአጠቃላይ በዚህ ጥራዝ ውስጥ የተካተቱ አጫጭር የጥናት መግለጫዎች እንደሚያሳዩት፤ በሁለት አስርት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ማህበረሰቦቹ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ትርጉም በሚሰጥ መልኩ ለሚመለከት ሰው ለመገመት በሚያስቸግር ሁኔታ ተለውጠዋል። በነዋሪዎቹ የራዕይና የህልም ስፋት ላይ እንደሚንጸባረቀው ሁሉ፣ ማህበረሰቦቹ፤ ለሥራ ከቀዬ ውጭ ሄዶ ስራ መፈለግን ጨምሮ፣ ከውጭው ዓለም ጋር ለመገናኘት ይበልጥ በራቸውን ከፍተዋል። የየአካባቢው ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች በዓይነት የበለጠ ሰፍተዋል - ይሄም ለሥራ ፈጣሪ ግለሰቦችና ለሴቶች የላቀ የተሳትፎ ዕድሎችን ፈጥሮላቸዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ የኑሮ ደረጃ ልዩነቶች የሰፉ ሲሆን ከትምህርት ዕድሎች መጨመር ጎን ለጎን፣ የወጣቶች ምኞትና ራዕይ አድጓል። በዛው ልክ ወጣቶች ወደ ጎልማሣ ዕድሜ ሲሸጋገሩ የኑሮ መተዳደሪያቸውን ለማሻሻል የሚገጥሟቸው ፈተናዎች በርክተዋል። ልጃገረዶች አሁንም ፈርጀ-ብዙ አደጋዎችን ይጋፈጣሉ፤ ድህነትና የአካባቢ ርቀት የእናቶችን የኑሮ ደህንነት ያቃውሳሉ። በአንጻሩ የጤና አገልግሎት መስፋፋት ደግሞ በተለይ የወጣት ሴቶች፣የእናቶችና ህጻናትን ጤና ታድጓል።

በ2017 በታተመው፤ "*Change and Transformation in 20 rural communities in Ethiopia: selected aspects and implications for policy*" በሚለው መጽሐፍ መግቢያ ላይ የቀረቡትን የአጫጭር መግለጫዎች ሰፊ የጥናት ግኝቶች ለመረዳት ሦስት ሁሉን አቀፍ ንድፈ ሃሳቦች ተጠቅመዋል፦ 1) ዕድገት፣ ድህነትና የኑሮ ደረጃ ልዩነቶች፤ 2)የለውጥ የቦታና የጊዜ ቅኝት፤ እና 3) የሴቶችና ወጣቶች የለውጥ ተሞክሮ። እንደሚከተለው በአጭሩ ተጨምቀው ቀርበዋል።

<u>የገጠር ማህበረሰቦች ለማደግ ኢኮኖሚያቸውን በዓይነት ማስፋት አለባቸው</u>

የWIDE ጥናት መረጃ፦

- ግብርና ትኩረት የሚሰጠው ከፍተኛ የፖሊሲ ጉዳይ ሆኖ ይቀጥላል የሚለውን ሃሳብ ይደግፋል፤ መስኖ ለዕድገት ያለውን ፋይዳ የሚያሳይ ማስረጃም ያቀርባል።
- የከተማ መስፋፋትና ኢኮኖሚያዊ እመርታ ለየአካባቢው ኢኮኖሚ ያላቸውን ፋይዳ

ይጠቁማል፤ የተሻለ ትስስር የፈጠሩና በገበያ የተዋሃዱ ማህበረሰቦች ከፍተኛ ዕድገት ማስመዝገባቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ያቀርባል፡፡

- ከእርሻ ውጭ ለሆኑ ሥራዎች የላቀ ትኩረት መስጠት አስፈላጊ መሆኑን ይጠቁማል፤ በተለይ በገጠር ማዕከሎች አነስተኛ የንግድ ተቋማትን የሚያስፋፉ ፕሮግራሞችን መደገፍ፡- የመሬት አቅርቦት ውስን ለሆኑባቸው ቁጥራቸው እያደገ ለመጣ ወጣቶች ዕድሎችን ለመፍጠር፤ ልጃገረዶችና ሴቶች በኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች የሚያደርጉትን ከፍ ያለ ተሳትፎ ለመደገፍ፤ ለየአካባቢው ሥራ ፈጣሪዎች ያሉትን ዘርፈ ብዙ ዕድሎች ለመክፈት፤ እንዲሁም ማህበረሰቦች እየጨመረ ከመጣው የከተማ መስፋፋት የሚያገኙትን ጠቀሜታዎች ለማሳደግ ወሳኝ ነው ይላል፡፡

<u>አንድም ሰው ወደኋላ መቅረት የለበትም፡- የድሃ/ተጋላጭ ሰዎችን ሁኔታ በመገንዘብ፤ የተደራሽነትን ችግር መቀነስ</u>

በ2014 የወጣው ብሔራዊ የማህበራዊ ዋስትና ፖሊሲ፤ "ማንንም ከኋላ አለማስቀረት " የሚል አቋም ወስዷል፡፡ በዚህ ረገድ የWIDE ጥናት፤ የድሃና የተጋላጭ ሰዎችን ሁኔታ ለማሻሻል የታለሙ የለውጥ እርምጃዎች ላይ የአስተሳሰብና የአሰራር ቅኝቶችን መለወጥ እንደሚያስፈልግ ይጠቁማል፡፡ ይሄም ያለባቸውን ውስንነትና ግንዛቤያቸውን በመረዳት እንዲሁም ለቅድሚያ ፍላጎታቸው፣ ውጥናቸውና ዕቅዳቸው ዋጋ በመስጠት ላይ የተመሰረተ መሆን እንዳለበት ጥናቱ ያስገነዝባል፡፡ የጥናት ግኝቶቹ በተጨማሪም፤ ውጭያዊ የለውጥ እርምጃን ከማህበረሰብ ተቋማት እንቅስቃሴ ጋር ማቀናጀት ያለውን ፋይዳ ይጠቁማሉ፡፡

ከመገናኛ አውታሮች ርቆ መነጠል፤ያለጥርጥር ከመንግስት የለውጥና የማዘመን እርምጃዎች ተደራሽ አለመሆን ጋር በግልጽ የተሳሰረ መሆኑን የ WIDE ጥናት ያሳያል፡፡ መንግስት ራቅ ያሉ የገጠር አካባቢዎችን የተደራሽነት ችግር ለመቀነስ እያደረገ ያለው ጥረት ውጤት እያመጣ ሲሆን፤ ጥናቱ የተደራሽነትን ችግር በመቀነስ ረገድ ፋይዳ ያላቸው ተጨማሪ የመፍትሄ ሃሳቦችን ይጠቁማል፡-

- የመንገድ ትስስርን የበለጠ ማሻሻል - በተለይ በውስጥ ለውስጥ መንገዶችና በእግረኛ መንገዶች ላይ በማተኮር፣ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ እርስ በእርስ ለመገናኘት ያለውን የተደራሽነት ችግር መቀነስ፡፡
- ከመስመር ውጭ የሆኑ የኤሌትሪክ ሃይል አማራጮችን ማጎልበትና ማስፋፋት - ዘመናዊ ሞባይሎች፣ ታብሌት ኮምፒዩተሮችና ላፕቶፖችን የባትሪ ሃይል በመሙላት፣ በተለያዩ ዘርፎች በዘመነኛ የመገናኛ ቴክኖሎጂ አማካኝነት የሚገኙ አገልግሎቶችን ተደራሽ ማድረግ፡፡

<u>የሴቶችና ወጣቶችን ህይወት ማሻሻል መቀጠል</u>

የWIDE ጥናት፤ የጾታ እኩልነትን በተመለከተ የመሻሻል ውጤቶች መታየታቸውን አሳይቷል፤ ወዲያውም በሌላ በኩል ደግሞ መፍትሄ ያልተበጀላቸው ጉልህ መሰናክሎችና ገደቦች እንዳሉም ይጠቁማል፡፡ ወጣቶች ወደ አዋቂነት የሚያደርጓቸው ሽግግሮች እንዴት ይበልጥ አስቸጋሪና ረዥም እየሆኑ እንደመጡ ጥናቱ ያሳያል፡፡ የጥናት ግኝቶቹ፤ ሴቶችንና ወጣቶችን (ከአጠቃላይ የህዝቡ ቁጥር ግማሹን ይወክላሉ) ብዙ ጊዜ በፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ላይ ከሚቀርቡት ይበልጥ በጠለቀ መልኩ

መረዳት ያለውን ፋይዳ ይጠቁማሉ፡፡ ለምሳሌ ከጾታና ዕድሜ ጋር የተያያዙ ፍላጎቶች፣ አቅምና ገደቦች እንዳሏቸው፣ እንዲሁም የኑሮ ውሳኔዎችን ሲወስኑም ሁሉንም የህይወታቸውን ገጽታዎች ከግምት ውስጥ እንደሚያስገቡ መገንዘብ እንደሚያስፈልግም ግኝቶቹ ያስገነዝባሉ፡፡

ጥናቱ ወደ ጾታ እኩልነት የሚደረገውን ግስጋሴ ለማፋጠን የሚከተሉትን ሃሣቦች ይሠነዝራል ፡-

- በትምህርት፣ በሥነ ተዋልዶ ጤና፣ በግብርና ኤክስቴንሽን፣ በወጣቶች የኑሮ መተዳደሪያ ማስፋፋት ወዘተ--- ተጨማሪና የተሻሻሉ የለውጥ እርምጃዎች ያስፈልጋሉ፤
- ፈርጀ - ብዙ የማዘመን እንቅስቃሴዎችን የሚያነለብቱ የለውጥ እርምጃዎችን ለምሳሌ፡- የገጠር ማህበረሰቦችን ተደራሽ የሚያደርግ የመሰረተ ልማት ዝርጋታ፤ ማከናወን አስፈላጊ ነው፤
- ነባር ማህበራዊ ልማዶችን ለመቀየር የሚጥሩ የለውጥ እንቅስቃሴዎች አስፈላጊ ናቸው፡፡ እነዚህ ሂደቶች በወንዶች ሚና ላይ እንዲሁም በሴቶችና በወንዶች ግንኙነት መካከል መሰረታዊ ለውጦች ሲከሰቱ አይቀሬ የሆኑትን ስጋቶች ከግምት ውስጥ ማስገባትን ይፈልጋሉ፡፡ በተጨማሪም አዋቂ ወንዶችና ወጣት ወንዶችን እንዲሁም ተጽዕኖ ፈጣሪዎችን ጨምሮ ከፈርጀ ብዙ የለውጥ አቀንቃኞች ዘንድ ንቁ ተሣትፎ እና ድጋፍ መሰብሰብን ይጠይቃል፡፡

ጥናቱ፤ ወጣቶች ወደ ጎልማሣነት የሚያደርጓቸውን ሽግግሮች የሚያሻሽሉ መንገዶች የሚከተሉትን ሊያካትቱ እንደሚችሉም ይጠቁማል፡-

- የዕይታ አንጻሮችን በማስተካከል፣ የወጣት ወንዶችን የሥነ ተዋልዶ ሚና እና የወጣት ሴቶችን የምርታማነት ሚና ይበልጥ በተሟላ መልኩ መገንዘብ፤
- ቀደም ብሎ እንደተገለጸው፣ ከእርሻ ውጭ በሆኑ ሥራዎች ላይ ማተኮርና ጥቃቅን / አነስተኛ የንግድ ተቋማት ማስፋፋትን ጨምሮ፤ ለወጣቶች አካባቢ በቀል የኑሮ መተዳደሪያ ዕድሎችን ማሳደግ፤
- በከተሞች፣ በኢንዱስትሪና በውጭ የሥራ ዕድል ለሚሹ ወጣቶች፣ የበለጠ ውጤታማ የሆነ ድጋፍ መስጠት - ይሄም ለትውልድ ቀዬአቸው ማህበረሰብ ዕድገት፣ጉልህ አስተዋጽኦ ማድረግ ለሚፈልጉ ወጣቶች ውጤታማ መንገድ ሊሆን ይችላል፡፡

<u>የፖሊሲ ዝግጅትና አፈጻጸም የአሰራር ቅኝትን ማሻሻል</u>

የWIDE ጥናት እንደሚያመለክተው፤ ለፖሊሲ ዝግጅትና አፈጻጸም በስርዓት፣ ከላይ ወደ ታች የተዘረጋ በየእርከኑ የሚወርድ የአሰራር ቅኝት፣ በኢትዮጵያ የልማት ትራንስፎርሜሽንን ለማስጀመር ወሳኝ እንደነበር በቂ ምሣሌዎችን ያቀርባል፡፡ ሆኖም ሁሉን አቀፍ ለውጥ እንዲዘልቅ የአሰራር ቅኝቱን እያሻሻሉ መጓዝን እንደሚጠይቅ ጥናቱ ይጠቁማል፡፡ መጽሐፉ 3 መንገዶችን ይጠቁማል፡-

- በተለያዩ ዘርፎች መካከል ሁሉን አቀፍ አቅጣጫ መቅረጽ፤
- እንደየአካባቢው ተጣጥሞ የተቃኘ ምላሽ የሚሰጡ የለውጥ እንቅስቃሴዎችን ማስፋፋት፤ እና

- ለየአካባቢው ግንዛቤና የጋራ መማማር እንዲሁም አዲስ ነገር የመሞከር ጥረት ቅድሚያ መስጠት፡፡

እንዴት ነው የWIDE ኢትዮጵያ ጥናት፤ በገንዘብ የተደገፈውና የተከናወነው?

WIDE ኢትዮጵያን የተለያዩ በርካታ የልማት አጋሮች ለዓመታት ደግፈውታል፡፡ የመጀመሪያው ዙር ጥናት (WIDE 1) በእንግሊዝ፣ የባህር ማዶ የልማት ፕሮግራም (DFID) የተደገፈ ሲሆን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ምርምር ካውንስል ደግሞ (WIDE2)ን በገንዘብ ደግፏል፡፡ በWIDE3 ሥር (ከ2010-13) የተደረጉ ጥናቶች የተከናወኑት፤ ሞኮሮ ሊሚትድ (ኦክስፎርድ፣ ዩናይትድ ኪንግደም) ከፓንክረስት የልማት ምርምርና አማካሪ ተቋም (አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ) ጋር በትብብር በመስራት ነው፡፡ በዓለም ባንክ የመንግስት አስተዳደር ግምገማና ምዘና ትብብር ትረስት ፈንድ አማካኝነት የካናዳ ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ፣ የእንግሊዝ መንግስት ዓለም አቀፍ የልማት ተቋምና የኔዘርላንድ መንግስት WIDE3ን ደግፈዋል - አይሪሽ ኤይድ፣ የስዊድን ዓለም አቀፍ የልማት ትብብርና የእንግሊዝ መንግስት ዓለም አቀፍ የልማት ተቋም፣ የአሁኑን አጫጭር የጥናት መግለጫዎች፣ በ2015/16 የሽግግር ምዕራፍ ላይ በገንዘብ ደግፈዋል፡፡

ማሳሰቢያ፡-

በዚህ ጥራዝ ውስጥ የቀረቡት የውይይት መነሻ አጫጭር መግለጫዎች፤ የፖሊሲና አፈጻጸም ጥያቄዎች እንዲሁም ሊፈጥሩ የሚችሏቸው አንደምታዎች የፖሊሲ አውጭዎችን ትኩረት እንዲያገኙ የWIDEን የጥናት ማስረጃ ያቀርባሉ፡፡ ዓላማቸውም በተነሱ ቁልፍ ጉዳዮች ላይ ለሚደረጉ ወቅታዊ ውይይቶች አስተዋጽኦ ማድረግና ከመንግስትና ከለጋሾች ጋር በተዛማጅ ውይይቶች ላይ ለመሳተፍ ነው፡፡ በዚህ ጥራዝ ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች፣ የኢልምተን ወይም የኢትዮጵያ መንግስትን አሊያም በገንዘብ የሚደግፉትን የልማት አጋሮች አመለካከት አይወክሉም፤ ይልቁንም የፖሊሲ ውይይት ለማነቃቃት ብቻ የታለሙ ናቸው፡፡

ለተጨማሪ መረጃ

የWIDE ቡድንን በ www.ethiopiawide.net/contact/ ድረ-ገጽ ወይም በኢ-ሜይል contact@ethiopiawide.net ማግኘት ይቻላል፡፡

አባሪ 1፡- በWIDE ኢትዮጵያ ማነው የተሳተፈው?

በ1990ዎቹ የWIDE1 ኢትዮጵያ ጥናት፤ 41 ኢትዮጵያውያን የመስክ ጥናት መኮንኖች፣2 ኢትዮጵያውያን የመስክ ጥናት አስተባባሪዎች (በረከት ከበደ እና ሹክሪ አህመድ)፤ እንዲሁም 9 የሪፖርት አርቃቂ ቡድን አባላት (4ቱ ኢትዮጵያውያን ነበሩ) ተሳትፈዋል፡፡

WIDE1 እና WIDE 2 የተቀረጹትና የተመሩት በፊሊፓ ቤቫንና በአሉላ ፓንክረስት ነበር፡፡ የ WIDE2 የመስክ ሥራ የተካሄደው በ2003፣ በ20 አካባቢዎች ነበር፡፡ ማለትም 15 የWIDE1 ማህበረሰቦች እና 2 በአርብቶ አደር ማህበረሰቦች እንዲሁም 3 እያደገ የመጣው የገበያ ሰብል አምራች ማህበረሰቦች ነው፡፡ ይሄ የጥናት ዙር "የኑሮ ደህንነት በታዳጊ አገራት" በሚል ርዕስ አራት አገራትን

የሸፈነ ጥናት አካል ነው፡፡ ጥናቱ ለተለያዩ ዓይነት ሰዎች የህይወት ጥራት ፋይዳ ባላቸው የገጠር ማህበረሰብ ዋና ገጽታዎች ላይ የመነሻ ፍተሻ ለማድረግ ያለመ ነበር፡፡ WIDE2፤ 43 ኢትዮጵያውያን የመስክ ጥናት መኮንኖችና 3 ኢትዮጵያውያን የመስክ ጥናት አስተባባሪዎችን አሳትፏል፡፡

በWIDE 3 የጥናት ወቅት፣ ካትሪን ዶም፤ በፊሊፓ ቤቫንና አሉላ ፓንክረስትን ሲመራ የነበረውን የጥናት ቡድን ተቀላቀለች፡፡ ዓላማውም፤ መረጃውን ከ WIDE1 እና WIDE2 መረጃ ጋር አቀናጅቶ በመጠቀም፣ ከ1995 ጀምሮ 20ዎቹ ማህበረሰቦች የተጓዙበትን የዝመና ጎዳና ለውጥ እንዲሁም የመንግስት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ለዚህ የዝመና ጉዞ ከ2003 ወዲህ ያበረከቱትን አስተዋጽኦ መፈተሽ ነበር፡፡ በ20 ማህበረሰቦች ላይ የተካሄደው ጥናት፤ 29 ኢትዮጵያውያን የመስክ ጥናት መኮንኖችን ያሳተፈ ሲሆን ዘጠኙ በWIDE2 የተሳተፉ ነበሩ፤ ብዙዎቹም በበርካታዎቹ ወይም በሦስቱም ምዕራፎች ተሳትፎአቸውን የቀጠሉ ናቸው፡፡ ሦስት ኢትዮጵያውያን የጥናት አስተባባሪዎች ሥራውን በተለያዩ ምዕራፎች ተቆጣጥረዋል (አግአዚ ጥኡመልሳን፣ ወርቅነህ አበበና መንግስቱ ደሳለኝ)፡፡ ሪፖርት ለመጻፍ፤ በምዕራፍ አንድ- 3 የቡድን አባላትን፤ በምዕራፍ ሁለት 4 (አስኳል የጥናት ቡድን እና ሬቤካ ካርተር) እና በምዕራፍ ሦስት 5 (አስኳል የጥናት ቡድን እንዲሁም ቶም ሌቨርስ እና አንቴያ ጎርደን) አሳትፏል፡፡ የWIDE ኢትዮጵያ የመስክ ጥናት፤ ከ1995 አንስቶ ባሉት ጊዜያት የሚከተሉትን ሴቶችና ወንዶች የጥናት መኮንኖች አሳትፏል፤ ስማቸውም በቅደም ተከተል ተዘርዘሯል፡፡ (listed alphabetically)[9]

ሴት የመስክ ጥናት ኣጥኚዎች

ህልፍቲ አረጋዊ፣ መሠረት ነጋሽ፣ መዕልተ ገብረጊዮርጊስ፣ ማጂ ሐይለማርያም፣ ሰላማዊት ሃይሉ፣ ሰላማዊት መንክር፣ ሰናይት ዮሐንስ፣ ሰብለወንጌል አያሌው፣ ቤተልሄም ተኮላ፣ ቤቴል ተረፈ፣ ብዙአየሁ አየለ፣ ትርሃስ ረዳ፣ ትዝታ ጀምበሩ፣ ትግስት ተፈራ፣ አሊማ ጂብሪል፣ አበበች በላይነህ፣ አስመረት ገ/ህይወት፣ አስቴር ሺበሺ፣ አስናቀች ገብረኪዳን፣ አይዳ ይመር፣ አጀቡሽ አርጋው፣ ኢየሩሳሌም ይህዴጎ፣ ኪሮስ ብርሐኑ፣ ዘውዴ ስንሻው፣ የኔነሽ ታደሰ፣ ይርገዱ ምልክት፣ ይርገዱ ተፈራ፣ ደናሜ ኢዮኤል፣ ደራርቱ አበራ፣ ጸጋ መለሰ፣ ፍሬወይኒ ዘራይ፡፡

ወንድ የመስክ ጥናት ኣጥኚዎች

ሃብታሙ ደምሌ፣ መለሰ ጌቱ፣ ሙሉጌታ ኢዮኤል፣ ሙሉጌታ ጋሻው፣ ሚሊዮን ታፈሰ፣ መስፍን ታደሰ፣ ምኒሊክ ጥበበ፣ መከተ ረታ፣ ሰለሞን ተገኝ፣ ሰለሞን ገ/ስላሴ፣ ሳሙኤል ኡርካቶ፣ ሳምሶን አበበ፣ ሰጥአርገው ቀናው፣ ሽፈራው ፉጂ፣ በሃይሉ አበበ፣ በሪሁን መብራቴ፣ ብርሃኑ ደስታ፣ በቃሉ ሞላ፣ ብዙአየሁ አንደርሳ፣ ተፈሪ አባተ፣ ተፈራ ጎሹ፣ ታረቀኝ ገ/የሱስ፣ ቴሶ በሪሶ፣ ቴድሮስ ወ/ጊዮርጊስ፣ ቶሎሳ ማሙዬ፣ ኃይለየሱስ ሴባ፣ አለሙ ታፈሰ፣ አለምአንተ አመራ፣ አሉላ አየለ፣ አማሃ ቀነኒ፣ አሰፋ ቴዎድሮስ፣ አሰፋ ቶሌራ፣ አበጀ ብርሃኑ፣ አቡ ግርማ፣ እውነቱ ስብሃት፣ አያሌው ገብሬ፣ አግአዚ ጥዑመልሣን፣ ከልክላቸው አሊ፣ ክፍሌ መንገሻ፣ ኪሮስ ገብረእግዚአብሄር፣ ካሣሁን ከበደ፣

[9] የWIDE1 የመስክ ሥራ፣ በወንድ የጥናት ባለሙያዎች የተከናወነ ሲሆን የWIDE2 እና WIDE3 የመስክ ሥራ ቡድኖች ቢያንስ አንድ ወንድና አንድ ሴት አሳትፈዋል፡፡

ወርቅነህ አበበ፣ ውብሸት ደሞዙ፣ ዘላለም አበራ፣ ዘላለም ከበደ፣ ያሬድ ተፈራ፣ ያሬድ ደርበው፣ ይልቃል ከፋለ፣ ይሳቅ ታፈረ፣ ዮሐንስ ገዛኸኝ ደምሴ፣ ጉደታ፣ ደምረው ዳኜ፣ ደረጀ ፈይሳ፣ ዳምጠው ይርጉ፣ ዳታ ዲአ፣ ዳኜ ሽብሩ፣ ድጋፌ ፈለቀ፣ ገብሬ በዳዳ፣ ገብሬ ይንጢሶ፣ ጌቱ አምባዬ፣ ጌታቸው ፉሌ፣ ጌታነህ መሃሪ፣ ግርማ ከበደ፣ ጣሰው ሽፈራው፣ ጳውሎስ አለማየሁ፣ ፈቃዱ አዱኛ።

በ2014 ዓ.ም የWIDE3 የመጀመሪያ የውይይት መነሻ አጫጭር የጥናት መግለጫዎች ስብስብ ዝግጅት ላይ ኤደን ተክላይ እና ግሩም አበበ (የኢኮኖሚ ፖሊሲ ትንተና ክፍል/ የኢትዮጵያ ልማት ምርምር ተቋም)፣ እንዲሁም ቤቨርሊ ጆንስና ሣራ ቮን ተሳትፈዋል። በቅርቡ የሽግግር ምዕራፍ ወቅት (2015/17) ሣራ ቮን አስኳል የጥናት ቡድኑን የተቀላቀለች ሲሆን ሊሊ ላቭዴይ፣ ናታን ንጉሴና ተፈራ ጎሹም አጫጭር መግለጫዎቹን በማዘጋጀትና በመጻፍ በቅርበት ተሳትፈዋል። ሁለተኛው የጥናት መግለጫዎች ስብስብ፤ ሙያዊ ግምገማ የተደረገበት በኢትዮጵያውያን የባለሙያዎች ቡድን ነበር።

ባለሙያ ገምጋሚዎች (2016)

አስናቀ ከፍአለ፣ ደሳለኝ ራሃማቶ፣ እመቤት ሙሉጌታ፣ ኢዛና አምደወርቅ፣ ሄለን አምደሚካኤል፣ ስጦታው ይማም፣ ተገኘ ገብረእግዚአብሔር፣ ይሳቅ ታፈረ እና ዘሪሁን ሞሃመድ።

<u>አባሪ 2፡ ከWIDE ኢትዮጵያ ምን ሌሎች የመረጃ ውጤቶችና ህትመቶች ይገኛሉ?</u>

በእንግሊዝኛ የተሰናዳው የእነዚህ የውይይት መነሻ አጫጭር መግለጫዎች ረዥም ክፍል፣ በአሉላ ፓንክረስት አርታኢነት በ2017፣ "*Change and Transformation in 20 rural communities in Ethiopia: selected aspects and implications for policy*" በሚል ርዕስ ታትሟል። የእነዚህ አጫጭር መግለጫዎች ስብስብ ዋና ቅጂ የሆነው "*Twenty rural communities in Ethiopia: selected discussion briefs on change and transformation*" በሚል ርዕስ በእንግሊዝኛ ታትሟል።

ባለፉት 20 ዓመታት በ WIDE ኢትዮጵያ ጥናት የተሰበሰቡ አብዛኞቹ መረጃዎችና የትንተና ውጤታቸው በድረገጽ ላይ ሰፍረዋል። በ<u>www.ethiopiawide.net</u> ማግኘት ይቻላል።

የ WIDE 1 ግኝቶች በ15 መንደሮቹን የተመለከቱ ጽሑፎች (Village Profiles) ቀርበው የነበረ ሲሆን በፊሊፓ ቤቫን እና አሉላ ፓንክረስት (1996) *A Social Analysis of Fifteen Rural Economies in Ethiopia*, Report for HMG Overseas Development Administration, UK. ተጨምቀው ተካትተዋል።

በ WIDE2 ጥናት ወቅት የተሰበሰቡ መረጃዎች፣ የኑሮ ደህንነት ሥነ ልቦናዊ መለኪያ ለመቅረጽ ያገለገሉ ሲሆን በእንግሊዝ ባዝ ዩኒቨርሲቲ፣ የዶክትሬት ዲግሪ መመረቂያ ጥናትም ተሰርቶባቸዋል። ከ WIDE2 የጥናት መረጃ የተሰሩ ሌሎች የጥናት ጽሁፎች እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡-

- Pankhurst, A. (2004) 'Conceptions of and Responses to HIV/AIDS: Views from Twenty Ethiopian Rural Villages'

- Derese Getachew (2004) 'Peasant Reflections on the Agricultural Development Led Industrialisation Programme (ADLI)'
- Bevan, P. (2004) 'Hunger, Poverty and Famine in Ethiopia: Mothers and Babies Under Stress in 2003'
- Pankhurst, A. & P. Bevan (2004) 'Hunger and poverty In Ethiopia: local perceptions of famine and famine response' in Humanitarian Exchange, no.27 pp. 2-5

በWIDE3፣ የመጨረሻውን ዙር ጥናት ተከትሎ፣ ለ20ዎቹ አካባቢዎች፣ ሦስት የጥናት ምዕራፎችን የሚሸፍን፣ የማህበረሰብ ሁናቴ ሪፖርቶች ተዘጋጅተዋል። ፍላጎት ባላቸው ድርጅቶችና ግለሰቦች በተመሰረቱ የኤሌክትሮኒክ የግንኙነት መረብ አማካኝነት አዳዲስ የገለጻ ማስታወሻዎች ይሰራጩ ነበር። ቁልፍ የጥናት ግኝቶች፤ በኢትዮጵያ የልማት ምርምር ተቋም (ኢልምተ) ድጋፍ፣ በተዘጋጁ መድረኮች ለትላልቅ የመንግስት ባለድርሻ አካላት እንዲሁም ከሚኒስትሮች፣ ለጋሾችና ዓለማቀፍ ድርጅቶች ጋር በተደረጉ ስብሰባዎች ላይ ቀርበዋል። ተከታዮቹ የምርምር ጽሁፎችና ለውይይት የቀረቡ ጥናታዊ ጽሁፎችም በ WIDE ኢትዮጵያ ይገኛሉ፡-

- በሰኔ 2010፣ በኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ጉባኤ ላይ የቀረቡ 6 የጥናት ጽሁፎች
- Bevan, P. (2010) *'Tracing the 'War Against Poverty' in rural Ethiopia since 2003 Using a Complexity Social Science Approach*', Chronic Poverty Research Centre International Conference, Manchester
- Bevan, P. (2010) *'The MDG-ing of Ethiopia's Rural Communities 2003-10: Some Meso, Micro and Macro Consequences.'* Symposium on 'Promoting social inclusion in South Asia: policies, pitfalls and the analysis of welfare/insecurity regimes' University of Bath
- Bevan, P. (2010) '*Inter-acting, competing and evolving models of 'wellbeing' in development policy in Ethiopia 2003-10: some consequences for individual and social life qualities in Ethiopia and an ethical quandary for donors',* presentation at Development Studies Association Conference Nov 2010
- Panel and papers for the 18th ICES, 29 Oct - 2 Nov 2012 '*Movements in Ethiopia, Ethiopia in Movement*', Panel 5.06 - '*Where are rural Ethiopian communities heading?'* convened by Alula Pankhurst with Philippa Bevan (shared with the worknet)
    - Bevan, P., Samuel Urkato & Shiferaw Neda 'A Comparison of Two Food-Insecure Sites in North Omo: Where have they come from and Where

might they be Heading?' *Presented by Shiferaw*[10]

- Bevan, P., R. Carter & C. Dom: 'A Tale of Two Productive Safety Net Programme Sites' (two Stage 1 sites) *Presented by Bevan*
- Carter, R., & Eyerusalem Yihdego: 'How are Urbanisation and Irrigation affecting food-deficit communities in Ethiopia: a Comparison of two *kebeles* near Lalibela and Harar' *Presented by Eyerusalem*
- Dom, C.: 'Where are Ethiopian rural communities heading? Youth, education and migration in two food-deficit communities in Eastern Tigray and Kambata' *Presented by Dom*[11].
- Pankhurst, A.: 'Agropastoralism in Transition: a Comparison of two communities in Oromia and Southern Region' *Presented by Alula*[12]
- Tefera Goshu & Aster Shibeshi: Social Change: Impact of Development Interventions on the Gelcha community of the Karrayu pastoralists of the Upper Awash Valley of Ethiopia *Presented by Tefera*

- Bevan, P., R. Carter & C. Dom (2013) '*A tale of two PSNP sites*' in Pankhurst, A., G-J. van Uffelen and Dessalegn Rahmato (eds) '*Food Security, Safety Nets and Social Protection: the Ethiopian Experience'*, Addis Ababa: Forum for Social Studies, and Wageningen: Wageningen University, Disaster Studies
- Bevan, P. (2014) 'Researching social change and continuity: a complexity-informed study of twenty rural community cases in Ethiopia 1994 – 2015' in Camfield, L. (ed.) *Research in International Development: A Critical Review* London: Palgrave.
- 'Change and continuity in rural Ethiopia 1994 (and before) to 2013 (and beyond): a longitudinal study of twenty communities using complexity methods'. Presentation to the ESRC Seminar on Complexity and Method in the Social Sciences, Warwick University, available at: http://blogs.cim.warwick.ac.uk/complexity/seminar-3-qualitative-complexity/
- Papers for the 19th ICES in August 2015 in Warsaw.
  - Bevan, P. 'Evolving relations between the State and rural societies in Ethiopia 1855-2013: similarities and differences in twenty exemplar places'.
  - Dom. C, 'Labour Outmigration in rural Ethiopia 1995-2010/13'.
  - Pankhurst, A. 'Women transitions to adulthood: change and continuity in

[10] Published in E. Ficquet, Ahmed Hassen and T. Osmond (eds) 2016 *Movements in Ethiopia; Ethiopia in Movement, Proceedings of the 18th International Conferences of Ethiopian Studies*, V. II pp. 413-426, Centre Français des Etudes Ethiopiennes, Addis Ababa University and Tsehai Publishers.

[11] Published in proceedings V. II pp.427-440.

[12] Published in proceedings V. II pp. 441-470.

female circumcision/FCG'.

አባሪ 3፡- የኑሮ መተዳደሪያዎች፣ የከተማ ትስስሮችና የባህል ልዩነቶች ማሳያ ካርታዎች

የWIDE3 ማህበረሰቦች የኑሮ መተዳደሪያ ልዩነቶች



የWIDE3 ማህበረሰቦች በሰፊዋ ኢትዮጵያ ውስጥ



የWIDE3 ማህበረሰቦች የባህል ልዩነቶች



የገጠር ከተሜነት መስፋፋት

የገጠር ከተሜነት መስፋፋት፣ የከተማ ወደ ገጠር አካባቢዎች መስፋፋት እና የገጠር-ከተማ ትስስሮች መደርጀት

WIDE የውይይት መነሻ አጭር መግለጫ ቁ. 1/...10[1]

ዋና ዋና ነጥቦች - ከ WIDE መረጃ

- የከተማ መስፋፋት የገጠር አካባቢዎች፤ ከዕለት ዕለት እየተበራከተ በሚመጣ የህንጻዎች ግንባታና የመሰረተ ልማቶች ዝርጋታ፣ ይብዛም ይነስም፣ ደረጃ በደረጃ፣ ተጨባጭ ነባራዊ ሁኔታ የማህበራዊ እመርታ የሚያሳዩበት ሂደት ነው::
- ከላይ - ወደ ታች የከተማ መስፋፋት የሚጀመረው፣ በከፍተኛ የመንግስት ተቋማት (መዋቅሮች) ሲሆን ከታች የሚነሳ የከተማ መስፋፋት በአካባቢ መስተዳድሮች፣ በመሬት ባለቤቶችና በማህበረሰብ አባላት መካከል በሚፈጠሩ መስተጋብሮች ላይ የተመሰረተ ነው:: ሁለቱ ሂደቶች ብዙ ጊዜ በተግባር ይመጋገባሉ::
- WIDE ጥናት ባደረገባቸው አካባቢ የሚኖሩ ማህበረሰቦች፤ አዳዲስ የከተማ ቦታዎችን በማልማትና ነባሮቹን በማስፋፋት ሂደት መንግስት፣ የገጠር ነዋሪዎችና ሥራ ፈጣሪዎች ተሳትፈዋል::
- የተፋጠነ የከተማ መስፋፋት የእነዚህ ማህበረሰቦች ህይወት ላይ ተጽዕኖ የሣድራል:: የገጠር ቀበሌዎች የገጠር ከተሜነት መስፋፋት፣ የከተማ ወደ ገጠር መሬት መንሰራፋት፣ እንዲሁም
- የገጠር-ከተማ ትስስሮች መደርጀት ህይወታቸው ላይ ተጽዕኖ የራሱን አሻራ ያሣርፋል:: ብዙዎቹ እኒህ የከተማ መስፋፋቶች በይፋዊ አሃዛዊ መረጃ አይዳሰሱም::
- እኒህ እየተቀየሩ ያሉት የገጠር-ከተማ የለውጥ ሂደቶች፤ ለአካባቢ የእርሻ መዘመን፣ ለኢንዱስትሪ መስፋፋት፣ ለአገልግሎት አሰጣጥ ማደግ፣ ለማህበረሰብ እምነቶችና ልማዶች እንዲሁም ለሰዎች የኑሮ ዘይቤ፣ ህልምና የኑሮ ደህንነት ለውጦች አስተዋጽኦ አድርገዋል::

---

[1] ይህ አጭር የጥናት መግለጫ፤ በWIDE የውይይት መነሻ አጭር የጥናት መግለጫዎች ሁለተኛ ጥራዝ (ስብስብ) ውስጥ ከተካተቱት አስር መግለጫዎች አንዱ ነው:: መግለጫው፤ በፊሊፓ ቤቫን የተዘጋጀ ሲሆን በተገኘ ገ/እግዚአብሔር ሙያዊ ግምገማ ተደርጎበታል:: አዘጋጅዋ፤ መግለጫዎቹ ይሰናዱ ዘንድ በገንዘብ ለደገፉት ለእንግሊዝ ዓለም አቀፍ የልማት ተቋም ፣ ለኢሪሽ ኤይድና ለስዊድን ዓለምአቀፍ የልማት ኤጀንሲ ልባዊ ምስጋናዋን ታቀርባለች:: በተጨማሪም የጥናት ሪፖርቱን በማርቀቅ ሂደት የተሳተፉና አጭር የጥናት መግለጫው የትኩረት አቅጣጫ እንዲሰላ እገዛ ያደረጉ ሌሎች የጥናት ቡድን አባላትና ባለሙያ ገምጋሚዎች፣ ለሥራው ለሰጡት ጊዜና ድጋፍ ታመሰግናለች:: ሌሎች ምስጋናና ዕውቅና የሚያሻቸውም አሉ:- (1) ለዓመታት የጥናት መግለጫው የተዘጋጀበትን መረጃዎች ያሰባሰቡና ያደራጁ የጥናት መኮንኖችና ተቆጣጣሪዎች ሙሉ ጊዜያቸውን ሰጥተው ላበረከቱት አስተዋጽኦ፤ (2) በሶስት ዙሮች ለተካሄደው የWIDE ጥናት የገንዘብ ዕገዛ ላደረጉ የተለያዩ ድጋፍ ሰጪ ተቋማት፤ እና (3) በኢልምተ ሰብሳቢነትና በኢኮኖሚ ፖሊሲ ትንተና ክፍሉ በWIDE አጭር የጥናት መግለጫዎች ሁለተኛ ጥራዝ ላይ ለመወያየት መጋቢት 28 ቀን 2016 ዓ.ም በተዘጋጀው መድረክ ላይ የተሳተፉ ከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣናት፣ ላሳዩት ፍላጎትና ለከፈሉት የጊዜ መስዋዕትነት--- ምስጋና ይገባቸዋል:: የጥናት መግለጫው፤ በከፍተኛ ደረጃ በተዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ፣ ከመንግስት ባለሥልጣናት ጋር በተደረገው ውይይት የተሰጡ አስተያየቶችን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ከለሳና ማሻሻያ ተደርጎበታል:: አጭር የጥናት መግለጫው፤ የኢትዮጵያ የልማት ምርምር ተቋምን (ኢልምተ) ወይም የኢትዮጵያ መንግስትን አሊያም የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርጉለትን የልማት አጋሮች አመለካከትም ሆነ አቋም አይወክልም፤ ይልቁንም የፖሊስ ውይይት ለማነቃቃት የታለመ ነው:: ሌሎች የጥራዝ ሁለት የውይይት መነሻ አጭር መግለጫዎችንና የጥናትና ምርምር ውጤቶችን በhttp://ethiopiawide.net/ ድረ-ገጽ ላይ ማግኘት ይቻላል::

- የገጠር ከተሜነት መስፋፋት፡- አጠቃላይ መሻሻሎች የነበሩ ቢሆንም በውስጥ ለውስጥ መንገዶች፣ በቀበሌ ህንጻዎች ጥራት፣ በቀበሌ ማዕከሎች የከተሜነት ደረጃ፣ በመብራትና ሞባይል ስልኮች እንዲሁም በመጠጥ ውሃና በመስኖ መሰረተ ልማት አቅርቦት ረገድ በማህበረሰቦች መካከል ልዩነቶች ነበሩ፡፡
- በጥናቱ በተካተቱት በ20ዎቹም ማህበረሰቦች ያሉት የውስጥ ለውስጥ መንገዶች በሙሉ በደረቅ ወቅት ብቻ የሚያገለግሉ ነበሩ፤ ፲፩ ማህበረሰቦች በደረቅ ወቅትም ጭምር ተደራሽነትን የሚያስተጓጉሉ ጥቂት ወይም በወጉ ያልተሰሩ መንገዶች ነበራቸው፡፡
- ፲3ቱ የዋይድ ማህበረሰቦች (ስምንቱ ለድርቅ ተጋላጭ ናቸው) ለአካባቢው ኢኮኖሚያዊ ዕድገት አስተዋጽኦ ያደረጉ የመስኖ መሰረተ ልማቶች ወይም ቴክኖሎጂዎች ነበራቸው፡፡
- ለቀበሌ መሰረተ ልማቶችና ለ"ከተማ" ህንጻዎች ግንባታና እድሳት የገንዘብ፣ የቁሳቁስና የጉልበት አስተዋጽኦ በማድረግ ረገድ የአካባቢው ማህበረሰብ ግንባር ቀደም ነበር፡፡
- ወረዳው ወይም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (አንዳንዴ በሁለቱም አካላት) የቁሳቁስ፣ የገንዘብ ይሁን የቴክኒክ ምክር (ወይም ሁለቱም) ድጋፍ ባደረጉባቸው ጥቂት አጋጣሚዎች፣ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች፣ የመስኖ መሰረተ ልማቶችና ት/ቤቶች ጥራት የላቀ ነበር፡፡
  - ለቀበሌ መሰረተ ልማትና ህንጻዎች፣ የወረዳውን ኢንቨስትመንት መጨመር፣ ለገጠር ኢኮኖሚያዊ ዕድገት አስተዋጽኦ ሊያደርግና የአገልግሎቶች አቅርቦት ልዩነቶችን ሊቀንስ ይችላል፡፡
- ብዙ ማህበረሰቦች የኤሌክትሪክ አቅርቦት የላቸውም፤ በሁለት ማህበረሰቦች ጥቂት በጸሃይ ብርሃን የሚሰራ ኤሌክትሪክ (ሶላር) ተተክሏል፤ በአንደኛው በነፋስ ሃይል የሚሰራ የውሃ መሳቢያ ሞተር ነበር፡፡
  - አረንጓዴ የኤሌክትሪክ ቴክኖሎጂዎችን ለማዳረስ በመንግስትና በሥራ ፈጣሪዎች መካከል የሚፈጠር ትብብር፣ ከማዕከላዊው የኤሌክትሪክ መስመር ሁሌም ተነጥለው በርቀት ለሚኖሩማህበረሰቦች፣ የኤሌክትሪክ ሃይል ሊያቀርብ ይችላል፡፡
- የከተማ መንሰራፋት ወደ ገጠር መሬት በ15 የዋይድ ማህበረሰቦች፣ የገጠር መልክአ ምድሮች ቅርጽ ተለውጧል፡፡ አምስት ማህበረሰቦች የቀበሌ ውስጣዊ ከተሞችን ያስፋፉ ሲሆን አራቱ ዋና መንገዶችን ተከትለው የከተማ መስፋፋት አካሂደዋል፡፡ በሁለት የከተማ መስተዳድሮች መሬት ተወስዷል ወይም ተመድቧል፤ ሁለት መለስተኛ ከተሞች እና ሁለት ከተሞች፡፡ የፖሊሲ ትኩረትን የሚሹ በርካታ ስጋቶች ተነስተው ነበር፡-
  - ለአንድ ተመሳሳይ ትልቅ የማህበረሰብ መሬት፣ በመንግስት ተይዘው የነበሩ ዕቅዶች ጥርጣሬን ፈጥረው ነበር፤ ይሄም በሚኒስቴር መ/ቤቶች መካከል በትብብር መሥራት እንደሚያስፈልግ ያሳያል፡፡
  - የእርሻና የግጦሽ መሬት ማጣት ስጋት ፈጥሮ ነበር፡፡
  - በማዕከሎች፣ በመንገዶችና በከተማ ድንበሮች አቅራቢያ ያለ መሬት መከተም ምን ያህል ተጽዕኖ እንደሚኖረው አይታወቅም ነበር፡፡
  - የወደፊት ዕቅዶች፣ በጊዜና ካሳ አከፋፈል ረገድ ጥርጣሬን ፈጥረው ነበር፡፡

- በገጠርና ከተማ ነዋሪዎች መካከል ከመሬትና ውሃ አጠቃቀም ጋር በተገናኘ የሚፈጠሩ ግጭቶች፣ በተጎራባች የገጠርና የከተማ ማህበረሰቦች መካከል ቅንጅት እንደሚያሻ አስገንዝቧል፡፡

- የገጠርና ከተማ ፅምረት፡- ከገጠር ወደ ከተማ ለገበያ የሚላኩ የሰብል እህሎች፣ የቀንድ ከብትና ምርቶች እንዲሁም የግንባታ ቁሳቁሶች፤ የትላልቅና ትናንሽ ከተሞችን ፍጆታ ከመደገፋቸውም ባሻገር ለገጠር ነዋሪዎች ገቢ ፈጥሮላቸዋል፤ በተጨማሪም ከእርሻ ውጭ በሆነ ሥራና በትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፍ የመሰማራት ዕድሎችንም ከፍቶላቸዋል፡፡
- መካከለኛና ትላልቅ የንግድ ተቋማትን በያዙ ከከተሞች አቅራቢያ በሚገኙ የዋይድ ማህበረሰቦች፤ ሥራ ፍለጋ የፈለሡ፣ ወይም ሥራና ትምህርትን አጣምረው የሚያስኬዱ፣በርካታ የተማሩ ወጣቶችን አማራጭ በማጣት ወደ ከተማ የተሰደዱ ችግረኛ ወጣቶች፣ ለአዳዲስ ከድህነት ጋር የተያያዙ ፈተናዎችን ይዳረጋሉ፡፡
  - መንግስት በገጠርና ከተማ አካባቢዎች ያለውን ትስስር ለማጎልበት የሚያደርገው ኢንቨስትመንት፣በሁለቱም ዘንድ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ማስፋፋቱን ይቀጥላል፡፡
  - በከተማ ያለውን ድህነት ለመቀነስና ድሃ የከተማ ስደተኞችን ለመደገፍ የሚያግዙ ፖሊሲዎች ያስፈልጋሉ፡፡

- ሁሉን አቀፍ ጉዳዮች፡- የገጠር ከተሜነት መስፋፋት፣ ወደ ገጠር አካባቢዎች የከተማ መንሰራፋትና የገጠር-ከተማ ፅምረት መደርጀት፣ በብዙዎቹ የዋይድ የገጠር ቀበሌዎች፣ ከእርሻ ውጭ የሆኑ ሥራዎችንና የንግድ ዕድሎችን ለማሳደግ ወሳኝ ነበሩ፡፡
  - ከመሃል ወይም መንገዶችን ተከትለው ከተሜነትን የሚያስፋፉ ቀበሌዎች ይሄ ሂደት ገበያ ያሏቸውን ምርቶችና አገልግሎቶች በመለየት፣ ሁሉንም አገልግሎቶች በአንድ ላይ የሚያቀርቡ፣ ሥራ ፈጣሪዎችን ከብድር ሰጪ ተቋማትና ከሥልጠና ዕድሎች ጋር በማስተሳሰር እንዲሁም ከእርሻ ውጭ ለሆኑ ሥራዎች የመሬት አቅርቦት ለማመቻቸት ከባለሥልጣናትና ከማህበረሰቡ ጋር ተባብሮ በመስራት ማፋጠን ይቻላል፡፡
  - በትናንሽና መካከለኛ ከተሞች እሴት ጨማሪና የውጭ ምርቶችን በአገር ውስጥ የሚተኩ ትናንሽና መካከለኛ የንግድ ተቋማትን ለማስፋፋት፣ በመንግስትና በግል ዘርፉ መካከል አጋርነት በመፍጠር የአካባቢውን የሥራ ዕድሎች መጨመር ይችላል፡፡

- በርካታ ርቀው የተነጠሉ የገጠር ማህበረሰቦች እዚህ ግባ የማይባል የከተሜነት መስፋፋት አላቸው፡፡ ግና ከአጎራባች ከተማ በአስቸጋሪ ርቀት ላይ ነው የሚገኙት ማለትም ከትላልቅ የከተማ ገበያዎችና ከከፍተኛ የጤና እና የትምህርት ተቋማትም የራቁ ናቸው፡፡ የተሻለ ትስስር የፈጠሩ የቀበሌ ማዕከሎች ያሏቸው በርካታ ማህበረሰቦች፤ ርቀው የተነጠሉ አካባቢዎችን ይዘዋል፡፡ በከተሞችና ወደ ከተሜነት እየተስፋፉ ባሉ የቀበሌ ማዕከሎች፣ በመገልገያዎችና በአገልግሎቶች ላይ የሚደረገው ቀጣይ ኢንቨስትመንት፣ በርቀት ሳቢያ ወደ ኋላ የቀሩ አካባቢዎችን አይጠቅማቸውም፡፡
  - መንግስት ርቀው የተነጠሉ የገጠር ነዋሪዎችን፣ በከተማ መስፋፋት ከሚገኙ ጠቀሜታዎች፣ ከተወሰኑት ጋር የሚያስተሳስሩ፣ የማህበረሰብ አገልግሎቶችን ለመደገፍ፣ ማዕከላዊ ያልሆነ

የኤሌትሪክ አገልግሎትና የዘመነኛ መገናኛ ቴክኖሎጂን ጨምሮ፣ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች ጥቅም ላይ መዋል የሚችሉበትን መንገዶች ሊፈትሽ ይችላል፡፡

<u>መግቢያ፡- የገጠር ማህበረሰቦች ለከተማ መስፋፋት አስተዋጽኦ ያደረጉባቸው ሦስት መንገዶች</u>

የከተማ መስፋፋት፡ - የገጠር አካባቢዎች፤ እየዳጎሰ በሚመጣ የህንጻዎች ግንባታና የመሰረተ ልማቶች ዝርጋታ፣ ይብዛም ይነስም፣ደረጃ በደረጃ፣ተጨባጭ የገጽታና የማህበራዊ እመርታ የሚያሳዩበት ሂደት ነው፡፡ በኢትዮጵያ ባለፉት 10 ዓመታት የከተማ መስፋፋት ሂደት ተፋጥኗል፡፡ በይፋ የሚታወቀው የከተማ የህዝብ ብዛት፣ በ2005 ዓ.ም ከተመዘገበው ፲ሚ.958ሺ.476፣ በ2016[2] ዓ.ም ወደ 20ሚ.202ሺ.815 (ከአጠቃላይ የህዝቡ ቁጥር 19.8 በመቶ) አድጓል፡፡ ከ2010 እስከ 2015 የተገመተው ዓመታዊ እድገት 4.89 በመቶ ነበር[3]፡፡ በኢትዮጵያ ኦፊሴላዊ ትርጉም፤ "ከተማ" ማለት፤ "2ሺ ወይም ከዚያ በላይ ነዋሪዎች የያዙ አካባቢዎች" ማለት ነው[4]፡፡ ነገር ግን ከዚያ ያነሰ ነዋሪዎች የያዙ ብዙ የ"ንኡስ የከተማ" አካባቢዎች፣ የከተማ መሰረተ ልማትና ህንጻዎች ያሏቸው ሲሆን የገጠር አካባቢዎች የከተማ መስፋፋት ሂደትም በፍጥነት እየገሰገሰ ነው፡፡

በማንኛውም ዘመን ላይ የኢትዮጵያን መልክአ ምድር ብንመለከት፣ ቀጣይነት ያለው የ"ከተሜነት" ሂደት እናስተውላለን፡፡ ከቀበሌ የመንግስት ህንጻዎች ዙሪያ ከሚያቆጠቁጡ ቡቃያ "ከተሞች" አንስቶ በፍጥነት በመንሰራፋት ላይ እስካለው የአዲስ አበባ ከተማ ድረስ ይስተዋላል፡፡ የ2012-13 የዋይድ መረጃን በቅርበት ሲጨን፣ ሁሉም ማህበረሰቦች በቅርቡ ሁለት ከከተማ መስፋፋት ጋር የተያያዙ ሂደቶች ውስጥ እንደነበሩ ያሳያል፡፡ ይኸውም በቀበሌ ክልል ውስጥ የ"ከተማ" የመሠረተ ልማትና ህንጻዎች ግንባታ ላይ ያተኮረ የገጠር የከተሜነት መስፋፋት እና የገጠር-ከተማ ትስስሮች መደርጀት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ከ20 ማህበረሰቦች ስምንቱ በቅርቡ በከተማ መንሰራፋት ወይም በድንበር አዋሳኝ ከተሞች "መለጠጥ[5]" ሳቢያ የገጠር መሬታቸውን ያጡ ሲሆን ሌሎች ስድስትም በአጭር ጊዜ ውስጥ መሬታቸውን ሊያጡ ይችላሉ፡፡

አዳዲስ የከተማ ቦታዎችን በማልማትና ነባሮቹን በማስፋፋት ሂደት መንግስት፣ የገጠር ነዋሪዎችና የግል ሥራ ፈጣሪዎች ተሳትፈዋል፡፡ ከላይ-ወደ ታች የከተማ መስፋፋት የሚጀመረው በከፍተኛ የመንግስት ተቋማት ወይም መዋቅሮች ሲሆን ከታች የሚጀመረው የከተማ መስፋፋት በአካባቢ መስተዳድሮች፣በመሬት ባለቤቶችና በማህበረሰብ አባላት መካከል በሚፈጠሩ መስተጋብሮች ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ሁለቱ ሂደቶች በተግባር ይቆራኛሉ፡፡

እነዚህ እየተቀየሩ ያሉ የገጠር-ከተማ የለውጥ ሂደቶች፤ ለአካባቢ የእርሻ መዘመን፣ ለኢንዱስትሪ መስፋፋት፣ ለአገልግሎት አሰጣጥ ማደግ፣ ለማህበረሰብ እምነቶችና ልማዶች እንዲሁም ለሰዎች የኑሮ ዘይቤዎች፣ ህልሞችና የኑሮ ደህንነት ለውጦች አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡

[2] http://www.worldometers.info/world-population/ethiopia-population/

[3] https://www.cia.gov/library/publications/the-world-factbook/fields/2212.html. This urbanisation rate of 4.89% compares with a population growth rate of 2.71% in 2010 and 2.48% in 2016.

[4] http://unstats.un.org/unsd/demographic/sconcerns/densurb/Defintion_of%20Urban.pdf

[5] This useful concept acknowledges a process which is likely to continue.

የገጠር ከተሜነት መስፋፋት

የገጠር ከተሜነት መስፋፋት፤በገጠር ቀበሌ ክልሎች ውስጥ የመሠረተ ልማትና የ"ከተማ" ህንጻዎች ግንባታና እድሳት ላይ ያተኮረ ነው፤ ይሄም ባለፉት አምስት ዓመታት ባልተቋረጠ ዕድገት በሁሉም አካባቢዎች የተፋጠነ ሂደት ነው፡፡ መሰረተ ልማቶቹና ህንጻዎቹ የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፡-

1. የውስጥ ለውስጥ መንገዶችና የእግረኛ መንገዶች፤
2. የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት፤
3. የሞባይል ስልክ መሠረተ ልማት፤
4. የውሃ መሠረተ ልማት፡- የውሃ ማጠራቀሚያዎች፤የመስኖ መሰረተ ልማቶች፣ የተከለሉ፤ ምንጮች፣የተቆፈሩ ውሃ ማቆሪያዎች፣ የውሃ ጉድጓዶች፤
5. የጤና አገልግሎት ህንጻዎች፤
6. ት/ቤቶች፤
7. የቀበሌ ህንጻዎች፡- የአስተዳደር፣የገበሬዎች የሥልጠና ማዕከላት፣የልማት ኤጀንትና የእንስሳት ህክምና ቢሮዎች ወዘተ፤
8. የከተማ የመኖርያና ከእርሻ የተለዩ የንግድ ተቋማት ህንጻዎች፡፡

በእያንዳንዱ ማህበረሰብ ያለው የመልክአ ምድር አስቸጋሪነት፣ የአሰፋፈር ጥንቅርና እነዚህ መሰረተ ልማቶችና ህንጻዎች የሚገኙባቸው ቦታዎች ልዩነቶች፣ በንጹህ የመጠጥ ውሃ፣ በመስኖ፣ በመብራት፣ በሞባይል ስልክ፣ በዘመናዊ የጤናና የትምህርት አገልግሎቶች እንዲሁም በከተማ የግል አገልግሎት ረገድ የአቅርቦት አለመመጣጠኖችን ፈጥረዋል፡፡

የውስጥ ለውስጥ መንገዶችና የእግረኛ መንገዶች

የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ጥራት በሚከተሉት ላይ ተጽዕኖ አሳድሯል፡-

- የእህልና የቁም ከብት ምርቶች፣ ድንጋይ፣ ጠጠርና አሸዋ ወደ ከተማ ገበያ የመላክ እንዲሁም ለግብርና ወይም ለኢንዱስትሪ አገልግሎቶች የሚውሉ ዘመናዊ ግብአቶችና ማሽኖች የማስገባት ምቹነት፤
- ለአገልግሎት ሊቀርቡ የሚችሉ የመጓጓዣ ዓይነቶች፤
- ነዋሪዎች በቀበሌያቸው ውስጥና ከቀበሌያቸው ውጭ የጤናና የትምህርት አገልግሎቶችን ለማግኘት የሚያደርጉት ጉዞ ምቹነት፡፡

በሁሉም ማህበረሰቦች፤ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች፣ ለደረቅ ወቅት ብቻ የሚያገለግሉ መሆናቸው፣ በክረምት ወራት በየትኛውም አካባቢ በተሽከርካሪዎች መጠቀም እንዳይቻል ዳርገዋል፡፡ በጨቀዩ የውስጥ መንገዶችም ሆነ በእግረኛ መንገዶች መጓዝም እጅግ አስቸጋሪ ነው፡፡ ይሄ በአጣዳፊ ሁኔታ ወደ ጤና ጣቢያዎች ወይም ሆስፒታሎች መድረስ ለነበረባቸው ሰዎች የተለዩ ችግሮችን አስከትሏል፡፡ በስድስት ማህበረሰቦች ጥቂት ወይም በዝቅተኛ ደረጃ የተገነቡ መንገዶችም ይሁን ድልድዮች፣ ከዓመት እስከ ዓመት የእርሻና የግንባታ ምርቶች ለከተማ ገበያ እንዳይጓጓዙ እንቅፋት ሆነዋል፡፡

የምግብ ዋስትና ዕገዛ ፕሮገራም (Productive Safetynet Programme [PSNP]) እና የድንገተኛ ምግብ እርዳታ (Emergency Food Aid [EFA]) የማህበረሰብ ሥራዎች፣ለበጋ ወቅት መንገዶች

መሻሻል አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ አዲስና የተሻሻሉ የበጋ ወቅት መንገዶች ከነበሯቸው 9 ማህበረሰቦች፣ 7ቱ የምግብ ዋስትና ዕገዛ ፕሮገራም የማህበረሰብ ሥራዎች፣ ነበሯቸው፡፡ ነገር ግን የምግብ ዋስትና ዕገዛ ፕሮገራም የማህበረሰብ ሥራዎች፣ ለአስቸጋሪ የመሬት አቀማመጥ መፍትሄ ማበጀት አልቻሉም፡፡ ለምሳሌ አንድ የምግብ ዋስትና ዕገዛ ፕሮገራም ማህበረሰብ ጥገና የሚሻ 19 ኪ.ሜ. የአፈር መንገድ ነበረው፤ በሌላኛው ደግሞ የመሬቱ አቀማመጥና ርቀቱ፣ በቀላል መሳሪያዎች መንገድ ለመገንባት የተደረገውን ሙከራ አስቸጋሪ አድርጎታል፡፡ በሦስተኛው፣ የማህበረሰብ ሥራ ተሣትፎ ቡድን ወደ ቀበሌው የሚያሻግር ድልድይ መገንባት አልቻለም፡፡

በአንዳንድ አቅም ባላቸው ማህበረሰቦች፣ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ለመስራት፣የማህበረሰብ ንቅናቄ አልተደረገም፡፡ በሌሎች በርካታ ማህበረሰቦች ደግሞ፣የመንገዶች ማስፋፋትና ጥገና ፍላጎቱ፤ ሊደራጅ ከሚችለው የማህበረሰብ አገልግሎት ንቅናቄ የሚልቅ ነበር። ይህ በተለይ ከአካባቢ ጥበቃና ከመንግስት ህንጻ ፕሮጀክቶች ፉክክሮች በሚኖሩበት ወቅት ተስተውሏል፡፡

የምዕተ ዓመት የልማት ግቦች የወረዳ የገንዘብ ድጋፍና የቴክኒክ እርዳታ፤ በሁለት የምግብ ዋስትና እገዛ ባልታቀፉ ሃብታም ማህበረሰቦች ውስጥ ጉልህ ለውጥ አምጥቷል፡፡ ወረዳው በምዕተ ዓመት የልማት ግቦች ፕሮግራሙ አማካኝነት፣50 በመቶ የገንዘብ ድጋፍና የቴክኒክ እርዳታ ያደረገ ሲሆን በውስጥ ለውስጥ የመንገድ አውታሮች ዝርጋታ ረገድ ከፍተኛ መሻሻሎች ለመቀዳጀት ተችሏል፡፡

የኤሌክትሪክ አገልግሎት አቅርቦት

የኤሌክትሪክ መሰረተ ልማት አቅርቦትና ተደራሽነት በሚከተሉት ላይ ተጽዕኖ አሳድሯል፡-

- ለትላልቅ የመስኖ ፓምፖች የኤሌክትሪክ ሃይል የመጠቀም ዕድሎች፤
- ከእርሻ ውጭ የሆኑ የሥራ እንቅስቃሴዎች፡- ለምሳሌ የእንጨት ሥራ ፣ የብረታ ብረት ሥራ፣ ጸጉር አስተካካዮች፣ የሆቴል መስተንግዶ እንዲሁም በሌሊት የመስራት ዕድሎች፤
- ተማሪዎች ሌሊት ማጥናት መቻላቸውና፤ ሰዎች መብራት በበራባቸው የእግረኛ መንገዶች በሰላም ያለ ስጋት መጓዛቸው ይገኙበታል፡፡

ስድስቱ የWIDE ማህበረሰቦች ኤሌክትሪክ አልነበራቸውም፤ በሁለቱ ማህበረሰቦች ደግሞ አንድም ኤሌክትሪክ የነበረው ሰው የለም፡፡ በሰባት ማህበረሰቦች፣ በቀበሌ ማዕከል ውስጥ ወይም አጠገብ ያሉ ህንጻዎች፣ ኤሌክትሪክ የነበራቸው ሲሆን በአምስቱ ማህበረሰቦች፣ ከሁሉም ቦታ የሚያገኙ፣ ጥሩ ወይም ለጥሩ የተቃረበ በሚል ይገለጹ ነበር ፡፡

ባለ ቆጣሪ የኤሌትሪክ መስመር ለመኖሪያ ቤት ማስገባት ዋጋው ውድ ነው፤ በአቅራቢያ ከሚገኙ ባለ ቆጣሪ መስመር ያላቸው ቤቶች መብራት መቀጠል፣ መደበኛውን መስመር ለማስገባት አቅሙ ለሌላቸው ድሃ የገጠር ቤተሰቦች፣ የኤሌትሪክ ብርሃን በመስጠት ረገድ ትልቅ ሚና ተጫውቷል፡፡ ይሄንን ልማዳዊ አሰራር መደበኛ የማድረጊያ ፍትሃዊ መንገዶችን መፈተሽ ይቻላል፡፡

በቤተሰብ ወይም በትናንሽ መንደር ደረጃ፣ በፀሃይ ብርሃን የሚሰራ (ሶላር)፣ የነፋስ ወይም ማይክሮ - ሃድል የሃይል ምንጮችን በማልማትና በማስፋፋት፣ ተነጥለው በሩቅ ለሚገኙማህበረሰቦች ወይም በማህበረሰቦች ውስጥ ለሚገኙ ሩቅ አካባቢዎች፣ የኤሌክትሪክ አገልግሎት የማዳረስ ጥረት ሊሳካ ይችላል፡፡

የሞባይል ስልኮች አገልግሎት አቅርቦት

የሞባይል ስልኮች የገጠሩ ማህበረሰብ በተለያዩ ቦታዎች ያለውን የግብርና ምርቶችና ግብአቶች ዋጋ ለማወቅ፣ ከነጋዴዎች ጋር ለመገናኘት እንዲሁም የእንስሳት ሃኪም፣ ትራንስፖርት፣ አምቡላንስ ለመጥራትና የምክር አገልግሎቶች ለማግኘት አስችለውታል። ሞባይል ስልኮች ከተለያዩ የልማት ዘርፎች ጋር የተገናኙ ጠቃሚ መረጃዎችን የያዙ የመጠቀሚያ ስልቶች (በእንግሊዘኛው አፕሊኬሽኖችን) ስልካቸው ላይ በመጫን በስፋት ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ። አስራ አንዱ የዋይድ ማህበረሰቦች፤ በመደበኛነት ጥሩ የስልክ ቅበላ የነበራቸው ሲሆን ሁለት ማህበረሰቦች በ2010 የሞባይል አገልግሎት ሽፋን ከነጭራሹ አልነበራቸውም። ሰባቶቹ ደግሞ የሲግናል ችግር ገጥሟቸዋል አልያም የስልኮቻቸውን ባትሪ ለመሙላት ኤሌክትሪክ አልነበራቸውም።

በማዕከል የማይከፋፈል የኤሌክትሪክ አማራጭ ፣ በተነጠሉ አካባቢዎች፣ የሞባይል ስልኮች ባትሪ መሙላትን ሊያቀላጥፈው ይችላል።

የመስኖ መሰረተ ልማት

13ቱ የዋይድ ማህበረሰቦች የተወሰኑ፤ የመስኖ መሰረተ ልማቶች ወይም ቴክኖሎጂ ነበራቸው። የመስኖ አቅርቦት ያላቸው ገበሬዎች መጠን ይለያያል። የመስኖ መሬት ያላቸው፣ ሃብታም የመሆን አዝማሚያ አሳይተዋል። የቀን ሥራ ዕድሎችም ጨምረው ነበር።

በ8 ለድርቅ ተጋላጭ በሆኑ ቀበሌዎች፣ ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው አትክልቶችና ፍራፍሬ ለማብቀል እንዲሁም በአንድ አካባቢ ጫት ለማልማት መስኖ የሚጠቀሙ ሲሆን ወደ ከተማ ገበያ ማቅረብ በተለያዩ ደረጃዎች አድጎ ነበር። ይሄ በውሃ አቅርቦት እና በከተማ ገበያ ተደራሽነት ላይ ይወሰናል። በሌሎቹ ሦስት ለድርቅ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች የማደግ አቅም የነበረ ሲሆን ይሄም ቀደም ብሎ ታውቋል።

- በአራቱ ቀበሌዎች በመስኖ የመሰረተ ልማት ማስፋፋት ላይ የወረዳ ተሳትፎ የነበረበት ሲሆን ከእነዚህ በሦስቱ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም ተሳትፈዋል።
- በሌሎቹ አራት ቀበሌዎች በመስኖ የመሰረተ ልማት ማስፋፋትና መጠበቅ ረገድ የወረዳ ተሳትፎ አልነበረም።
  - አልዩ አምባ አቅራቢያ፣ በዲንኪ፣ የመስኖ መሰረተ ልማት ግንባታ የተጀመረው የ1984/5 ድርቅን ተከትሎ፣ በአንድ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ነበር፤ ድርጅቱ አካባቢውን ለቆ ከሄደ በኋላ ማህበረሰቡ መሰረተ ልማቱን ጠብቆ መያዝ የቻለ ሲሆን በጥቂቱም አስፋፍቶታል።
  - በ1980ዎቹ በዶአማ የመልሶ ሰፈራ አካባቢ (ያለመስኖ ሊኖር አይችልም ነበር) በዩኒሴፍ የተገነባው የመስኖ መሰረተ ልማት፤ አስቸኳይ የማሽን ጥገና ያስፈልገው የነበረ ቢሆንም ከማህበረሰቡ አቅም በላይ ነበር።
  - በጫት አብቃይ አካባቢ ከአንድ ይልቅ በሦስት የምርት ወቅቶች የሚገኘው ትርፍ፣ የማህበረሰቡ አባላት ለውሃ ጉድጓድ ቁፋሮና ለፓምፖች ግዢ፣ ገንዘብና ጉልበታቸውን እንዲያፈሱ አነሳስቷቸዋል።

- በገልቻ (አርብቶ አደር፤ መተሃራ አቅራቢያ) አንድ አነስተኛ የህብረት ሥራ ማህበር (20) በአዋሽ ወንዝ ላይ ፓምፕ በመጠቀም፣ እንዲሁም ጥቂቶቹ ከስኳር ፋብሪካው የሚወጣውን ፍሳሽ በመጠቀም ያለሙ የነበረ ሲሆን በዓለም ባንክ የሚደገፍ ግዙፍ የመስኖ ኢንቨስትመንት ዕቅድ ነበር።

ከዘጠኙ አካባቢዎች በአምስቱ ባህላዊ የእርሻ ምርቶችን በመደበኛነት ለከተማ ገበያ ከሚያቀርቡ ራሳቸውን የቻሉ ማህበረሰቦች ወደ ከተሞች የሚላኩ የመስኖ ልማት አትክልቶችና ፍራፍሬዎች ዕድገት አስመዝግበዋል።

- ራሳቸውን በቻሉ አምስቱ አካባቢዎች ያሉ የመስኖ መሰረተ ልማቶች የተዘረጉት በገበሬዎች ነበር። ወረዳው ለአንድ ማህበረሰብ (ምስራቅ ጎጃም) ለውሃ ማውጫ ሞተር መግዣ ብድር በመስጠት እገዛ ያደረገ ሲሆን በሁለት አካባቢዎች (ምስራቅ ሸዋና ምዕራብ ሸዋ) መንግስትን ያካተተ ከፍተኛ የፕሮጀክት ዕቅዶች ነበሩ።

በ13ቱም አካባቢዎች፣ የውሃ አቅርቦት፣ በመስኖ ሊለማ የሚችለውን የመሬት መጠን ውሡን አድርጎት ነበር።

በአምስት አካባቢዎች ወቅታዊ ችግሮች አልነበሩም።

- በ3 ማህበረሰቦች በስበት የሚሰሩ የመስኖ ልማቶችን የሚመግቡ ወንዞች አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የአቅማቸው የመጨረሻ ደረጃ ላይ የደረሱ ሲሆን በውሃ አጠቃቀም ረገድ ውስጣዊ አልያም ውጫዊ ግጭቶች ተከስተዋል።
- በአንድ ማህበረሰብ፣ ወንዞችንና ምንጮችን የሚመግብ የከርሰ ምድር ውሃ፣ በተራዘሙ የደረቅ ወቅቶችና በከፍተኛ አጠቃቀም የተነሳ፣ ሙሉ በሙሉ ከአገልግሎት ውጪ መሆኑ ታውቋል።
- ሁለት የምስራቅ ትግራይ አካባቢዎች የተጠራቀሙ ውሃዎችን ተጠቅመዋል፤ ሆኖም እነዚህ በድርቅ ወቅትና በበጋ ወራት ደርቀዋል።
- በገልቻ የመስኖ አልሚዎች ከመተሃራ ስኳር ፋብሪካ የሚፈሰውን ውሃ ተገቢ ባልሆነ መንገድ ያስቀይሱ የነበረ ሲሆን፤ አንዳንዴ የሚቋረጥበት ሁኔታም ነበር።

የውሃ እጥረት ሲከሰት የጠብታ መስኖ[6] ቴክኖሎጂን ማስተዋወቅ የውሃ አጠቃቀም ብቃትን ሊያሻሽል ይችላል። ይሄ ቴክኖሎጂ በአንድ አካባቢ በመንግስት የተጀመረ ሲሆን በሌላ አካባቢ በአነስተኛ ባለሃብት ነበር የተጀመረው።

[6] የጠብታ መስኖ = drip irrigation

የመጠጥ ውሃ መሰረተ ልማት

ለድርቅ ተጋላጭ የሆኑ ማህበረሰቦች (11)

- ስምንቱ ጥቂት የንጹህ መጠጥ ውሃ መሰረተ ልማቶች ነበሯቸው፤ሁሉም የተገነቡት ከለጋሾች፣ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ወይም ቤ/ክርስቲያናት ድጋፍ ነው፡፡
- ቤተሰቦች በዋናነት የወንዝ ውሃ በሚጠቀሙባቸው ሌሎች 3 ማህበረሰቦች መሠል ዓይነት ድጋፍ አልነበረም፡፡
- በአራት ቀበሌዎች ውስጥ ርቀው የተነጠሉ አካባቢዎች፣ ንጹህ የመጠጥ ውሃ ጣቢያዎች አልነበራቸውም፤ በድርቅና በደረቅ ወቅት አንዳንድ ጣቢያዎች ደርቀዋል፡፡
- ከተለያዩ አካባቢዎች የተጠቆመው አንድ ችግር፣ የተበላሹ የውሃ ጣቢያዎችን በወረዳው ለማስጠገን በቧንቧ ሰራተኞችና በመለዋወጫ ዕቃዎች እጥረት የተነሣ ለረዥም ጊዜ ይጓተታል የሚል ነው፡፡
- በአንዳንድ አካባቢዎች የውሃ ጣቢያዎች የሚከፈቱበትን ሰዓት በተመለከተ ቅሬታዎች ተሰንዝረዋል፤ በቀን አንዴ ወይም ሁለቴ የሚከፈት ሲሆን የሚቆየው ለአጭር ጊዜ ብቻ በመሆኑ ረዥም ሰልፎችን አስከትሎ ነበር፡፡

በቂ ዝናብ ያላቸው ማህበረሰቦች (9)

- በቂ ዝናብ ከሚያገኙ 9 ማህበረሰቦች፣ ሁለቱ ብቻ የመጠጥ ውሃን በተመለከተ ወቅትን ተከትሎ የሚከሰት ችግሮች የሉበንም ብለዋል፡፡
- በሁለት ማህበረሰቦች ውስጥ በተራራማ አካባቢዎች ከሚኖሩ ቤተሰቦች፣ 33 በመቶ ገደማ ንጹህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት አልነበራቸውም፡፡
- በኮርማርገፍያ ብዙ ምንጮች በበጋ ወቅት ደርቀው ነበር፤ ሁኔታው ተባብሶም ቤተሰቦች በቀን 20 ሊትር ውሃ ነበር የሚከፋፈላቸው፡፡
- በቱሩፌ በ2006 እና 2009 የወንዝ ውሃ የቧንቧ ውሃን በክሎ የአጣዳፊ ተቅማጥና ትውከት ወረርሽኝ እንዳስከተለ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኛ አረጋግጧል።
- በሶሞዶ ርቆ በተነጠለ መንደር፣ ሰዎች ውሃ ለመቅዳት ለአንድ ሰዓት ይጓዙ ነበር፡፡
- በአዳዶ በቅርቡ የአዳዶ ከተማንና ወረዳን በተራራ አካባቢ ከሚገኝ ምንጭ ጋር ለማገናኘት የተዘረጋው የቧንቧ መስመር፣ ክረምት ላይ በተከሰተ የመሬት መደርመስ ጉዳት የደረሰበት ሲሆን ከ3 ወራት በኋላም አልተጠገነም፤ በዚህም ሳቢያ ቤተሰቦችና የጤና ጣቢያው ንጽህናቸው ያልተጠበቀ ምንጮችና ወንዞችን ይጠቀሙ ነበር፡፡
- በግራር የመጠጥ ውሃ አቅርቦት አለመኖር፣ ለአብላጫዎቹ ቤተሰቦች (በእምድብር ከተማ አቅራቢያ ላልሆኑት) ትልቅ ችግር ነበር፡፡ ችግሩን ለመፍታት የቀረቡ ሁለት ዕቅዶች በወረዳው ውድቅ የተደረጉ ይመስላሉ፡፡

- በሁለት አካባቢዎች የሚገኙ ነዋሪዎች፣ ለአጎራባች ከተሞች የቧንቧ ውሃ ለማቅረብ በመሬታቸው ላይ በተገነቡ የውሃ ጣቢያዎች ደስተኛ አልነበሩም። በገጠር አካባቢዎች ንጹህ የመጠጥ ውሃ ባልነበረው ግራር፤ የቧንቧ መስመር ከምንጭ ጋር ተገናኝቶ፣ ለእምድብርና ወልቃይት ከተሞች ውሃ ይቀርብ ነበር። በሹምሸሃ ሁለት የውሃ ጉድጓዶች፣ የላሊበላን 50 በመቶ የውሃ ፍጆታ ይሸፍኑ ነበር። ይሄ ያስከተለው ችግር፣ ሹምሼሃ የቧንቧ ውሃ በራሽን እንድትከፋፈል አድርጓታል። የውሃ ጣቢያዎቹም በየሶስት ቀኑ አንዴ ነበር የሚከፈቱት።

ውስጣዊ ልዩነቶች፤ በ"ከተማ" መሠረተ ልማትና አገልግሎቶች አቅርቦት

በቀላሉ ለመድረስ አስቸጋሪ በሆኑ አካባቢዎች ለሚኖሩ ማህበረሰቦች ፣ የገጠር ከተማ መሰረተ ልማትና አገልግሎቶች አቅርቦት ደካማ ነበር። ወረዳው በውስጥ ለውስጥ መንገዶች ላይ የሚያደርገው ኢንቨስትመንት፣ ሰዎች የገጠር ከተማ ማዕከሎችን መሰረት ያደረጉ አገልግሎቶችን በአካል የሚያገኙበትን ሁኔታ ሊያሻሽለው ይችላል። በእርግጥ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ለሁሉም ወቅት ታልመው እስካልተገነቡ ድረስ፣ በክረምት ወቅት ችግሮች መፈጠራቸው አይቀርም።

ርቀው ለሚገኙ አካባቢዎች መሰረተ ልማትና አገልግሎቶች ላይ ከሚደረገው ኢንቨስትመንት ጎን ለጎን የ"ከተማ" አገልግሎቶችን ኢንቨስትመንት በማሳደግ፣ ርቀው በተነጠሉ አካባቢዎች የሚገኙ ነዋሪዎችን፣ የከተሜነትን ትሩፋቶች እንዲቋደሱ ማድረግ ይቻላል። ይሄም በፀሃይ ብርሃን የሚሰራ ሶላር /ነፋስ/ማይክሮ ሃይድል (መስመር የለሽ) ኤሌክትሪክ እንዲሁም በዘመነኛ የመገናኛ ቴክኖሎጂ የሚሰራጩና በሞባይል ስልክ ተደራሽ የሆኑ መረጃዎች (ከግብርና ልማት፣ ከእርሻ ውጭ የሆኑ ክህሎቶች፣ ከትምህርት፣ ከምግብ ሳይንስ፣ ከጤና አጠባበቅና ህክምና ወዘተ ጋር የተያያዙ)ላይ በሚደረግ የኢንቨስትመንት ሙከራ ሊፈተሽ ይችላል።

በተለይ የእርሻና የከብት እርባታ ምርታማነት ዝቅተኛ በሆኑባቸው ቦታዎች፣ ሦስተኛው ስትራቴጂ ፤ በጥቂት መንደሮች አልያ የክትመት ማዕከላት፣ በአገልግሎትና ከእርሻ ውጭ በሆኑ የሥራ ዘርፎች ላይ ኢንቨስት ማድረግ እንዲሁም ሰዎች መኖሪያቸውን እንዲቀይሩ ማስማማት ነው።

ለእያንዳንዱ ማህበረሰብ ተመራጩ የተቀናጀ ስትራቴጂ ተመሳሳይ ነው ማለት አይደለም። ማህበረሰቦች በመልክአ ምድር አቀማመጥ፣ በአሰፋፈር ጥንቅር፣ በእርሻ ወይም የቀንድ ከብት አቅምና በገበያ ተደራሽነት ረገድ ባላቸው ልዩነቶች ላይ ተመስርቶ ሊለያይ ይችላል። ትክክለኛውን ስትራቴጂ የመለየት ሥራ በወረዳ ደረጃ ቢከናወን ይመረጣል።

ውስጣዊ የከተማ መስፋፋትና ከእርሻ ውጭ የሆኑ ሥራዎች

ከአቅራቢያ ከተማ በጥቂት ርቀት ላይ የሚገኙ ማህበረሰቦች (6)

መሬት አልባ ወጣቶች፤ ጥሩ ውጫዊ የከተማ ትስስሮች በሌላቸው የገጠር ማህበረሰቦች ውስጥ እየኖሩ በገቢያቸው ስኬታማ እንዲሆኑ ከተፈለገ፣ እነዚህ ቦታዎች የበለጠ የ"ከተማ" ገጽታ መጎናጸፍ ይኖርባቸዋል። ወጣቶችን ከከተማ የኑሮ ዘይቤዎች ጋር ማስተሳሰር አስፈላጊ ነው። ከዚያም የበለጠ አስፈላጊው ግን ከእርሻ ውጭ የሆኑ ንግዶችንና የሥራ ዕድሎችን ማስፋፋት ነው። በርቀት የተነጠሉ ማህበረሰቦች፤ ወጣቶች ከእርሻ ውጭ በሆኑ ሥራዎች የመሳተፍ ዋነኛ ዕድላቸው

የሚመነጨው ከውስጣዊ የከተሞች መስፋፋት ነው፡፡ የዚህ መጠን በ6 ርቀው የተነጠሉ የWIDE ማህበረሰቦች ውስጥ ይለያያል፡-

- ቡና ላኪ በሆነውና ርቆ በተነጠለው አዳዶ ውስጥ፤ ከ10 ዓመት በላይ የዘለቀ የከተማ ማዕከል ነበር፡፡ ማዕከሉ ብዙም ባይስፋፋ፣ ከእርሻ ውጭ የሆኑ ሥራዎች ከማደጋቸውም በላይ በዓይነትም ጨምረው ነበር፡፡ ሆኖም ከእርሻ ውጭ የሆኑ ምርቶችና አገልግሎቶች ተፈላጊነታቸው ወቅት-ተኮር ነበር፡፡ የቡና ምርት በሚሰበሰብበት ወቅት ከፍተኛ ሲሆን በሌሎች ጊዜያት በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡
- ሁለት ለድርቅ ተጋላጭ የሆኑ ማህበረሰቦች፣ ውስጣዊ የከተማ መስፋፋት ሂደት ላይ ነበሩ፡፡ ይህም ሂደት ከእርሻ ውጭ የሆነ ፍላጎትና ኢንቨስትመንት፣ በምግብ ዋስትን እገዛ/ በድንገተኛ የምግብ እርዳት እና ከስደት በሚገኝ ገቢ ይደገፍ ነበር፡፡ በእርሻ የበለጠ ምርታማ በነበረው በአንደኛው ማህበረሰብ፣ ከእርሻ ውጭ ለሆነ ፍላጎትና ኢንቨስትመንት ገቢ የሚገኘው በአነስተኛ መጠን በመስኖ የሚመረቱ አትክልቶችን እንዲሁም እንቁላሎች፣ ቅቤና የደለቡ ከብቶችን ለተጎራባች ከተሞች ገበያ በመላክ ነበር፡፡

ማህበራዊ ዋስትና በስደት ገቢ ላይ የሚደረጉ ቅነሳዎች፣ በእነዚህ ማህበረሰቦች ከእርሻ ውጭ የሆኑ ሥራዎች ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳድራሉ፡፡

- አርብቶ አደር፣ ርቆ የተነጠለና ለድርቅ ተጋላጭ በሆነው ሉቃ፣ በቅርቡ ለሁሉም ወቅት የሚያገለግል መንገድ መገንባቱን ተከትሎ አንድ ገበያ፣ አንድ ካፌና ሦስት ሱቆች የተቋቋሙ ሲሆን ለአካባቢው የከብቶችና የሰሊጥ ንግድ መጨመርም ዕድሎችን ፈጥሯል፡፡
- በምግብ ዋስትን እገዛ ድጋፍ የመስኖ አትክልቶችን ያበቅል በነበረ፣ ራቅ ያለና ለድርቅ ተጋላጭ የሆነ አንድ ማህበረሰብ፣ ውስጣዊ የከተማ መስፋፋት ምልክቶች አልነበሩም። በአዋሽ ወንዝ ላይ ድልድይ መዘርጋት፣ አትክልትና አሸዋ ወደተጎራባች ከተሞች የመላክ ዕድል የሚያስፋፋ ሲሆን በቀበሌ ማዕከል ዙሪያ የከተማ መስፋፋት ሊፈጥር ይችላል፡፡
- በሌላ በጣም ራቅ ያለና ለድርቅ ተጋላጭ በሆነ ማህበረሰብ ውስጥ በቅርቡ አዲስ የቀበሌ ማዕከል ተሰይሟል፡፡ ሰባት ሱቆች ለወጣቶች ተሰጥቶ የነበረ ሲሆን ብድር እገዛ ግን አልተመቻቸላቸውም፡፡ ስለዚህም ለሸቀጦች መግዣያ ከቤተሰብ ገንዘብ መበደር የሚችሉ ታዳጊዎች ብቻ ነበሩ የንግድ ሥራ ውስጥ የሚገቡት፡፡ በመሆኑም ጥቅም ላይ ያልዋሉ ሱቆች ይነጠቁ ነበር፡፡ በቅጡ የተዋቀረ የአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት የድጋፍ ፕሮግራም፣ በቀበሌዎች ውስጥ እንዲህ ያሉ ነገሮችን ይፈቱ ዘንድ የአነስተኛ የፋይናንስ ድጋፍ ፕሮግራሞች አቅም አላቸው፡፡

የወረዳ ከተሞች ተጎራባች ማህበረሰቦች፣ ሌሎች ከተሞችና ትላልቅ ከተሞች የሚጎራበቱ ማህበረሰቦች (20-50,000)

ለድርቅ ተጋላጭ፣ የእርዳታ ጥገኛ ማህበረሰቦች (6)

አንድ የአርብቶ አደር ማህበረሰብ፣ ፈፅሞ በአካባቢው ከተማ እንዲስፋፋና ከእርሻ ውጭ የሆኑ ሥራዎች እንዲያድጉ ፍላጎት አላሳየም፡፡

- በገልቻ (ከረዩ) የቀበሌ ህንጻዎች ጥራት ዝቅተኛ የነበረ ሲሆን እምብዛም ጥቅም ላይ አልዋሉም፡፡ የመኖርያ ወይም የንግድ ህንጻዎች አልነበሩም፡፡ በአካባቢው ከነበረው ከእጅ ወደ አፍ የሆነ የንግድ እንቅስቃሴ ውጭ ብቸኛው ከእርሻ የተለየ ሥራ፣ ከአንድ ቦታ ለቤት ግንባታ የሚያገለግሉ ድንጋዮችን መሰብሰብ ነበር፡፡

ሁለት ለከተሞች ተጎራባች የሆኑ ማህበረሰቦች ውስጣዊ የከተሜነት ልማት አልነበራቸውም፡፡

- ዶ'አማ (ሩቅ፣ ለድርቅ ተጋላጭ፣ መስኖ) በቀበሌ ህንጻዎች ዙሪያ የከተማ ልማት አልነበረውም፤ ከእርሻ ውጭ የሆኑ ሥራዎች በአብዛኛው ንግድና የትራንስፖርት ዘርፍን ያካትቱ ነበር፡፡
- በአዜ ዴቦአ የከተማ ልማት አልነበረም፤ በ4 ኪ.ሜ ርቀት ላይ በሚገኘው የዞን ከተማ ከእርሻ ውጭ የሆኑ ጥቂት የሥራ ዕድሎች ነበሩ፡፡

ከተሞችን የተጎራበቱ ሁለት ማህበረሰቦችም በቀበሌ ህንጻዎች ዙሪያ ወደ ከተሜነት እየተስፋፉ ነበር፡፡

- ከላሊበላ ጋር የሚያገናኝ ዝቅተኛ የጥራት ደረጃ ያለው መንገድ በነበረው ሹምሸሃ፤ በቀበሌ ህንጻዎች ዙሪያ፣ የተወሰኑ ከእርሻ ውጭ የሆኑ የሥራ ዕድሎችን የፈጠረ አነስተኛ ከተማ ብቅ ብሎ ነበር፤ አንዳንድ ነዋሪዎችም በአየር ማረፊያ ውስጥ ተቀጥረው ነበር፡፡
- የአዬሌ ኬኬ (ለድርቅ ተጋላጭ፣ የመስኖ ጫት) የቀበሌ ማዕከል፣ በዋናው የሐረር -ድሬዳዋ መንገድ ላይ ይገኝ የነበረ ሲሆን የከተማ ቅጣይ ልማት ምልክቶች ነበሩ፤ በዚህ ሥፍራ እያደጉ የነበሩ ከእርሻ ውጭ የሆኑ ሥራዎች ንግድ ወይም ትራንስፖርትን ያካትታሉ፡፡

አንድ ማህበረሰብ፤ አንድ የከተማ አስተዳደር የከበበ ነበር፡፡

- የጋራ ጎዳ (ወላይታ) የቀበሌ ማዕከል፣ ከእርሻ ውጭ የሆኑ ሥራዎች ዕድገት ጋር በተያያዘ መስፋፋት የተነሳ ወደ ከተማ መስተዳድርነት ተቀይሯል፡፡

በምግብ ራሳቸውን የቻሉ ማህበረሰቦች (4)

ሦስት ማህበረሰቦች፤ የሰብል ምርቶች ወደ ከተሞች ገበያ ይልኩ የነበረ ሲሆን የእህል ንግድ ዋነኛ ከእርሻ ውጭ የሆነ የሥራ ዘርፍ ነበር፡፡

- በአዳ ዳዋታ (አርሲ) በአጭር ርቀት ላይ ጥሩና እየተስፋፉ ያሉ ከእርሻ ውጭ የሆኑ የሥራ ዕድሎች ነበሩ፤ ብቸኛው አካባቢያዊ ከእርሻ ውጭ የሆነ የሥራ ዘርፍ፣ ድንጋይ ማውጣት (ካባ) እና ድንጋይ መፍጨት ነበር፡፡
- በአዳ ሃሮ (ምዕራብ ሸዋ) አጎራባች ከተማ፣ አንዳንድ ከእርሻ ውጭ የሆኑ የሥራ ዕድሎች የነበሩ ሲሆን በቀበሌው ዙሪያ የነበሩት ግን ጥቂት ናቸው፤ እነሱም በአብዛኛው የትርፍ ሰዓት ሥራዎችና ከግብርና ምርት፣ ከትራንስፖርት ወይም ከቤት ግንባታ ጋር የተያያዙ ነበሩ፡፡

- በግራር (ጉራጌ) በንግድ ላይ የተሰማሩ ሰዎች አልነበሩም፡፡ በአጎራባች ከተማ አንዳንድ ከእርሻ ውጭ የሆኑ የሥራ ዕድሎች የነበሩ ሲሆን ወጣቶች "ከእርሻ ውጭ በሆኑ ትርፋማ ሥራዎች" መሳተፍ ይችሉ ዘንድ በገጠር አካባቢዎች የኤሌክትሪክና ውሃ አቅርቦት ጥያቄ ነበር፡፡
- የትመን (ምስራቅ ጎጃም) ትንሽ ከተማን ከብቦ የሚገኝ ሲሆን ነዋሪዎች ግን "ዝቅተኛ ደረጃ" ባላቸው ከእርሻ ውጭ በሆኑ ሥራዎችና በቀን ሥራ ላይ መሳተፍ አይፈልጉም ነበር፡፡

አነስተኛ ከተሞች፤ በዙሪያቸው ለሚገኙ መሬት አልባ የገጠር ወጣቶች፣ በቂ ከእርሻ ውጭ የሆኑ የሥራ ዕድሎችን አያቀርቡም፤ ለዚህ ዋነኛው እንቅፋት የመሬት አቅርቦት ችግር ነው፡፡ በገጠር ቀበሌዎች ክልል ውስጥ የሚከናወን ከእርሻ ውጭ የሆኑ የሥራ ዘርፎችን ከሚደግፉ የመሬት ፖሊሲዎች ጋር የተያያዘ "የከተማ መሠረተ ልማቶች" ኢንቨስትመንት፣ ጉልህ ለውጥ ሊያመጣ ይችላል፡፡

ለከተሞች አጎራባች የሆኑ ማህበረሰቦች (4 በምግብ ራሳቸውን የቻሉ)

ግንባታን ጨምሮ ከእርሻ ውጭ በሆኑ ሥራዎች ላይ ለመሰማራት የመጓዝ ዕድሎች፣ ለትላልቅ ከተሞች አጎራባች በሆኑ አራቱ ማህበረሰቦች ውስጥ እያደጉ ነበር፡፡

- በሁለቱ (ሻሸመኔ እና ደብረብርሃን አቅራቢያ) በጣም ጥቂት አካባቢያዊ ከእርሻ ውጭ የሆነ የሥራ ዘርፍ ነበር፡፡
- ምንም እንኳን የሥራ እንቅስቃሴዎች መሬት ባላቸው ወገኖች ብቻ የተወሰነ ቢሆንም ከጂማ ጋር አነስተኛ አዋሳኝ ድንበር ባለው በአንደኛው ማህበረሰብ፣ ለሁሉም ወቅት የሚያገለግል መንገድን ተከትሎ፣ ቅጥያ የከተማ መስፋፋት ሂደት እየተከናወነ ነበር፡፡
- አራተኛው ማህበረሰብ (ሲርባ)፣ የቢሾፍቱ - ሞጆ መንገድን ተከትሎ፣ "በጣም ፈጣን የከተማ መስፋፋት ሂደት" እና የኢንዱስትሪ መስፋፋት ትንቅንቅ ውስጥ ነበር፡፡

<u>የከተማ መስፋፋት ወደ ገጠር አካባቢዎች</u>

በከተማ ዳርቻ የሚካሄዱ ፈጣን የከተሜነት መስፋፋት ሂደቶች፣ የመልክአ ምድሮችን ገጽታ የሚቀይሩ ሲሆን ተደጋጋሚ የወሰን (ድንበር) ለውጦችም ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡ በኢትዮጵያ በ2000ዎቹ መጀመርያ ላይ የተወሰደው ለወረዳዎች ከፍተኛ ሃላፊነት የመስጠት እርምጃ፣ አዳዲስ የወረዳ ከተሞች መስተዳድር በፍጥነት እንዲስፋፉ ያደረገ ሲሆን ብዙዎቹም በ2010/13 "የኢኮኖሚ ከተሞች" (ማለትም የራሳቸውን ገቢ የፈጠሩ) ሆነዋል፡፡ በ2016 የኢትዮጵያ መንግስት ድረገጽ፣ 5ሺ የከተማና 10ሺ የገጠር ቀበሌዎችን የያዙ 800 ወረዳዎች መኖራቸውን አስታውቋል፡፡ ብሔራዊ የመንገድ ግንባታ ፕሮግራም፣ ለኢኮኖሚ ከተሞች መመስረትና ፈጣን ዕድገት አስተዋጽኦ ያደረገ ሲሆን ርቀው ለተነጠሉ የገጠር አካባቢዎችም አዳዲስ የገበያ ዕድሎችና የአገልግሎት አቅርቦቶችን ፈጥሯል፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ከመጣው ከገጠር ወደ ከተማ ፍልሰት ነባር ትናንሽና መካከለኛ ከተሞች እንዲሁም ትላልቅ ከተሞች በፍጥነት እያደጉ መጥተዋል (ማጣቀሻ፡- ፍልሰት)።

በWIDE ማህበረሰቦች ውስጥ የሚገኙ ብዙ ሰዎች፣ የአካባቢዎቻቸው የተወሰኑ ክፍሎች በአጎራባች ከተሞች መጠቃለልን ያልተቃወሙ ቢሆንም ከሂደቱ ጋር የተያያዙ በርካታ የተለያዩ ጉዳዮች ተነስተዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የሚከተሉት ይገኙባቸዋል፡-

- ለመተሃራ ተጎራባች በሆኑ አካባቢዎች (የገልቻ አርብቶ አደሮች) እና ቢሾፍቱ አቅራቢያ (ሲርባ) ለአንድ መሬት ሁለት ዕቅዶች ተይዘው ነበር፡፡ ገልቻን እየተስፋፋ ወዳለው መተሃራ የማካተት ዕቅድ እንደነበር የተነገረ ሲሆን ማህበረሰቡም የዓለም ባንክ የአርብቶ አደር ማህበረሰቦች ልማት ፕሮገራም (PCDP) ፕሮጀክት አካል የሆነ፣ ግዙፍ የመስኖ ፕሮጀክት እንደሚሰራለት ቃል ተገብቶለት ነበር፡፡ የሲርባ የተወሰነ ክፍል ለከተማነት የተመረጠ ቢሆንም ከመንገዱ በተቃራኒ በመንግስት የተጀመረ ግዙፍ የመስኖ ፕሮግራም በዝግታ እየተካሄደ ነበር፡፡
- የኩዬራ ከተማ ወደ ሻሸመኔ ሲካተት፣ ቱሩፌን ከዋናው መንገድ ጋር የሚያገናኘውን የአፈር መንገድ ጨምሮ ለኩዬራ አጎራባች የነበረ ጥቂት የቱሩፌ መሬት ወደ ከተማው ቀበሌ ተዛውሯል፤ ይሄ መንገድ በገጠር የመንግስት ሥራዎች መጠገኑ በመቅረቱ፣ በዝናብ ወቅት የተደራሽነት ችግር ፈጥሯል፡፡
- ሹምሾሃ፤ ከ2007 እስከ 2012 ባሉት ዓመታት፣ በላሊበላ ከተማ አስተዳደር ሥር ከነበሩ ሁለት የገጠር ቀበሌዎች አንዱ ነበር፤ የከተማ አስተዳደሩ የተሟላ የገጠር አገልግሎቶች ባለማቅረቡ፣ ነዋሪዎች ወደ ገጠር ወረዳ የመመለስ ጥያቄ አቅርበው ነበር፡፡
- አብዛኛው የኮርማገፍያ መሬት ለደብረ ብርሃን ከተማ አስተዳደር የተላለፈ ሲሆን የእርሻ መሬቱ በኢንቨስትመንት ይዞታ ውስጥ ታጥሮ ነበር፡፡ የኢንቨስትመንት ሂደቱ በጣም ያዘገመ ሲሆን አጥሩ፤ ገበሬዎች ምርታቸውን ለሽያጭ፣ በአህያ የሚያጓጉዙበትንና ከቀበሌው ወደ ከተማው ገበያ የሚወስደውን ነባር መንገድ ዘግቶት ነበር፡፡
- ትልቁን የጋራ ጎዶ ቀበሌ ወደ አንድ የከተማ አስተዳደርና ሁለት ትናንሽ ከተሞች ዳግም የማዋቀር ሥራ፣ በሽግግር ወቅት ችግሮች የታጀበ ነበር፤ ችግሮቹን ለመፍታትም ጥቂት ጊዜያት ወስዷል፡- ለምሳሌ የቀበሌ ቢሮዎች ለከተማ አስተዳደሩ ተሰጥተው ነበር፣ ግብር እና መዋጮዎችን መሰብሰብ ወደ ከተማ አስተዳደሩ በመተላለፉ፣ የገጠር ቀበሌው ምንም ዓይነት የገቢ ምንጮች አልነበሩትም፡፡ ትን ሿ ጋራ ጎዶ የጤና ጣቢያ አጥታለች፤ ምክንያቱም ጣቢያው ይገኝ የነበረው ወደ ቀበሌነት ደረጃ እንዲያድግ በተደረገ መለስተኛ ቀበሌ ውስጥ ነበር፡፡
- የ"የትመን ከተማ"ን ከበው የሚገኙት የየትመን አርሶ አደሮች፣ በገጠር መሬት ላይ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት እንዳይገነባ ያደረጉት የተቃውሞ ሰልፍ በብጥብጥ ነው የተጠናቀቀው፡፡ ይሄን ተከትሎ የገጠር - ከተማ ግንኙነቶችን ያካረሩ ሁኔታዎች ተከስተዋል፡፡ አንዳንድ የኤሌክትሪክ መስመር ያላቸው የከተማ ቤተሰቦች፣ በአቅራቢያ ለሚገኙ የገጠር ቤተሰቦች ቀጥለውላቸው የነበረውን መብራት የቆረጡ ሲሆን የ5ቱ ውሃ ጣቢያዎች (ምንጫቸው በገጠር መሬት ላይ የተቆፈረ የውሃ ጉድጓድ ነበር) የከተማ ሃላፊዎች፣ ለገጠር ተጠቃሚዎች የተመደቡትን ሁለት ጣቢያዎች ለመክፈት አሻፈረኝ ብለው ነበር፡፡

- በጣም አነስተኛ ንጹህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት የነበራቸው የግራር የገጠር ህዝቦች፣ ለእምድብርና ወልቃይት ከተሞች ውሃ በቧንቧ ለማድረስ፣ በመሬታቸው ላይ የውሃ ጉድጓድ ሲቆፈር ደስተኞች አልነበሩም።

የገጠር መሬትን ለከተማ ጥቅሞች ለማዋል ለወደፊት ከታቀዱ ወይም ከታሰቡ የመሬት ዝውውሮች ጋር የተያያዙ ጉዳዮችም ተነስተዋል፡-

- አንዱ ስጋት እርግጠኛ አለመሆን ነበር። ለምሳሌ መሬታቸው በቅርቡ ወደ ጂማ የተጠቃለለባቸው የሶሞዶ ገበሬዎች፤ ለጊዜው እርሻቸውን መቀጠል እንደሚችሉ ተነግሯቸው ነበር፤ ነገር ግን መሬታቸው መቼ እንደሚወሰድ ፍንጭ አልተሰጣቸውም።
- በቅርቡ የታተመው፣ ለጢቤ ከተማ መስተዳድር የተዘጋጀው የ10 ዓመት ዕቅድ፣ ከአዳ ሃሮ መለስተኛ ቀበሌዎች፤ የአንዱን የግጦሽ መሬት፣ ወደ አስተዳደሩ እንደሚያጠቃልል የሚጠቁም ሲሆን ይሄ ለአካባቢው ገበሬዎች ከፍተኛ ስጋት ውስጥ የሚከት ጉዳይ ነበር።
- መቼ ምን እንደሚሆን እርግጠኛ አለመሆን- በአዳ ዳዋታ፣ለጎንዴ ከተማ ተጎራባች የሆኑ የመለስተኛ ቀበሌ የተወሰኑ አካባቢዎች፣ ለከተማ መስፋፋት ተመርጠው ነበረ፤ ማህበረሰቡ መሬታቸውን ያጡ ሰዎች ካሣ እንደሚከፈላቸው ቢጠብቅም በምን መልኩ እንደሚሆን አልተነገረውም።
- ቀርሳ፤ በአዴሌ ኬኬ የሚገኙ ጥቂት መንደሮችን ለሃሮማያ አዴሌ ዐ1 ለማስተላለፍ ("የሃሮማያ ያልታቀደ የከተማ መስፋፋት" አካል ነው) እምቢተኛ መሆኑን ተከትሎ፣ በሃራማያና በቀርሳ ወረዳዎች ባለሥልጣናት መካከል የጥላቻ ስሜት ተፈጥሮ ነበር።

<u>የገጠር - ከተማ ፅምረት መደርጀት</u>

የገጠር-ከተማ ፅምረትመደርጀት፣ ኢኮኖሚን ለማዘመንና የኑሮ ደህንነትን ለመጠበቅ በተለያዩ መንገዶች አስተዋጽኦ ያደርጋል፡-

የገጠር-ከተማ ንግድ

- ለግብርና እና ኢንዱስትሪ ምርቶች ያለው የከተማ ፍላጎት፣ የገጠር ኢንቨስትመንትን በዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችና ግብአቶች ላይ የሚያነቃቃ ሲሆን የገጠር ነጋዴዎች ከከተማ ነጋዴዎች ጋር ትስስር እንዲፈጥሩም ዕድሎችን ይሰጣቸዋል።
- ከገጠር የሚላኩ ምርቶች ለከተማ ሸማቾች ርካሽ እህል፣ አትክልቶችና ፍራፍሬዎችን ሲያቀርቡ፣ ለከተማ አካባቢዎች ደግሞ የእንግዳ አቀባበል አገልግሎቶችንና እሴት የተጨመረበት ምርትን ይሰጣሉ።

የከተማ ጉዞና ፍልሰት (ማጣቀሻ፡- ፍልሰት)

- በከተማ ተሰርተው የተገኙ ገቢዎች፣ በገጠር አካባቢዎች ሥራ ላይ ሊውሉ ይችላሉ፤ ሰራተኞች ወደ ትውልድ ቀዬአቸው ሊያመጧቸው የሚችሉ አዳዲስ ከእርሻ የተለዩ ክህሎቶችን ይማራሉ።

- የገጠር ሰዎች፤ ከአዳዲስ የአስተሳሰብና ትግበራ መንገዶች ጋር ይተዋወቃሉ፡፡
- ከገጠር አካባቢዎች የመጡ ችግረኛ ስደተኞች፤ የከተማ ድህነትና ሌሎች የደህንነት አደጋዎች ይገጥማቸዋል፡፡

ኢንቨስትመንት

- ሃብታም የገጠር ቤተሰቦች፤ መዋዕለ ንዋያቸውን በከተማ መኖርያ ቤትና አንዳንዴ በንግድ ሥራዎች ላይ ያውላሉ፡፡
- የከተማ ነዋሪዎች፤ መዋዕለ ንዋያቸውን በገጠር እርሻና ገጠርን መሰረት ባደረጉ ከእርሻ ውጭ በሆኑ ሥራዎች ላይ ያፈሳሉ፡፡

ዘመናዊ የሰው ሃይል ልማት አገልግሎቶች ጥቅም በከተሞች

- ይሄ ወደ ተሻሻለ ደህንነትና የላቀ ጥራት ወዳለው የሰው ሃይል ሃብት ያመራል፡፡
- ለመንግስትና ለግል አገልግሎት ሰጪዎችም ደንበኞችን ያቀርባል፡፡

መንግስት ባከናወነው አገር አቀፍ የመንገድ ግንባታ ፕሮግራም፣ ከሶስቱ በቀር በ20ዎቹም ማህበረሰቦች በውጫዊ የመንገድ ትስስሮች ረገድ ከፍተኛ መሻሻሎች ታይተዋል፡፡ ሆኖም ማህበረሰቦች፣ ለተለያዩ ከተሞች ያላቸው የተደራሽነት መጠን ይለያያል፡፡

- በሰባት ለድርቅ ተጋላጭ በሆኑ ማህበረሰቦች - እህል፣ መደበኛ ሰብሎች፣ የቁም ከብቶች ወይም የመስኖ አትክልቶች/ፍራፍሬ (3 ማህበረሰቦች) ለአቅራቢያ ከተማ በአነስተኛ መጠን ብቻ ነበር የሚሸጠው፡፡
- በአንጻሩ፤ ቅርብ የተባሉት ሆስፒታሎች፣ በአብዛኛው በጣም ሩቅ ናቸው። እንደምሣሌ (ሉቃ- 63 ኪ.ሜ፤ ቆሮደጋጋ - 24 ኪ.ሜ፤ ዲንኪ - 43 ኪ.ሜ፤ ገብለን- 40 ደቂቃ በተሽከርካሪ፤ ጌልቻ- 82 ኪ.ሜ ከበድ ላሉ ህመሞች፤ ሃረሳው - 30 ኪ.ሜ) ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡
- በአራቱ ቡና ላኪ ማህበረሰቦች ውስጥ የሚገኙ ነጋዴዎች፣ ወደ አዲስ አበባ በሚያመሩ የንግድ መረቦች ውስጥ ተሳታፊ ነበሩ፤ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ጫት አምራቾች፣ ወደ ሳኡዲ አረቢያ ጫት ከሚልኩ ነጋዴዎች ጋር ትስስር ነበራቸው፡፡
- ስምንት ማህበረሰቦች፤ አዲስ አበባን ጨምሮ ወደተለያዩ ከተሞች የእህል ሰብሎች፣ ከብቶች እና/ወይም ባህር ዛፎች ይልኩ ነበር፤ በሁለት ማህበረሰቦች "ትላልቅ ነጋዴዎች" ከአዲስ አበባ ነጋዴዎች ጋር በቀጥታ የተሳሰሩ ነበሩ፡፡ በሌሎች ማህበረሰቦች፣ በአካባቢው ንቁ ከሆኑ "ትላልቅ ነጋዴዎች" ጋር የተሳሰሩ የአነስተኛ ነጋዴዎች ትስስር ነበር፡፡
- የከተማ ጉዞና ፍልሰት ጨምሯል፤ ግን በሁሉም ቦታ አይደለም፡፡
  - በ6 ማህበረሰቦች የከተማ ፍልሰት ይሄን ያህል አልነበረም፡፡
  - ከጉራጌ የከተማ ፍልሰት ለረዥም ዘመን የዘለቀ ነው፡፡
  - በ8 ማህበረሰቦች ውስጥ ወቅት-ተኮርም ሆነ መደበኛ የከተማ ፍልሰት እየጨመረ ነው፡፡

- ከ6 ማህበረሰቦች ለግንባታ ሥራ፣ ለከተማ መደበኛ ያልሆነ ዘርፍ ወይም መደበኛ የንግድ ተቋማት መጓዝ ጨምሮ ነበር፡፡ አምስቱ ከተሞች፡- ሻሸመኔ፣ ደብረብርሃን፣ ሃራማያ፣ ዱራሜ (የከምባታ ዞን ከተማ) እና ጎንዴ (በአርሲ የከተማ መስተዳድር) ነበሩ፡፡ የሲርባ ተጓጉች ወደ ሥራ የገቡ ሲሆን የቢሾፍቱ-ሞጆ መንገድን ተከትለው ከተሜነት እያስፋፉ ያሉ አካባቢዎች በቅርብ ርቀት ላይ ይገኛሉ፡፡

<u>ሁሉን አቀፍ ጉዳዮች</u>

የገጠር ከተሜነት መስፋፋት፤ ወደ ገጠር አካባቢዎች የከተማ መንሰራፋትና የገጠር - ከተማ ትስስሮች መደርጀት፣ በብዙዎቹ የዋይድ የገጠር ቀበሌዎች፣ ከእርሻ ውጭ ለሆኑ ሥራዎችና የንግድ ዕድሎች ዕድገት ወሳኝ ነበሩ፡፡

- መሃል ላይ ወይም መንገዶችን ተከትለው ከተሜነትን የሚያስፋፉ ቀበሌዎች- ይሄ ሂደት "ሁሉን በአንድ ላይ የሚያቀርቡ ሱቆች" በመክፈት፣ ሊፋጠን ይችላል፡
  - ገበያዎች ያሏቸውን ምርቶችና አገልግሎቶችን መለየት፤
  - ሥራ ፈጣሪዎችን ከብድር አገልግሎትና የሥልጠና ዕድሎች ጋር ማስተሳሰር፤
  - የመሬት አቅርቦትን ተደራሽ ለማድረግ፣ ከመንግስት ሃላፊዎችና ከማህበረሰቡ ጋር በትብብር መስራት፡፡
- በትናንሽና መካከለኛ ከተሞች፣ እሴት የሚጨምሩና የውጭ ምርቶችን በአገር ውስጥ ምርቶች የሚተኩ ትናንሽና መካከለኛ የንግድ ተቋማትን ለማስፋፋት፣ በመንግስትና በግል ዘርፉ የሚፈጠር አጋርነት፣ የአካባቢውን የሥራ ዕድሎች ሊያሳድግ ይችላል፡፡

በርካታ ርቀው የተነጠሉ የገጠር ማህበረሰቦች እዚህ ግባ የማይባል ውስጣዊ የገጠር ከተማ መስፋፋት ያላቸው ሲሆን ከአጎራባች ከተማ በአስቸጋሪ ርቀት ላይ ይገኛሉ፤ ከትላልቅ የከተማ ገበያዎችና ከከፍተኛ ደረጃ የጤናና የትምህርት ተቋማትም የራቁ ናቸው፡፡ በርካታ የተሻለ ትስስር ያላቸው ማህበረሰቦች፤ ርቀው የተነጠሉ አካባቢዎችን ይዘዋል፡፡ በከተሞችና እየከተሙ ባሉ የቀበሌ ማዕከሎች፣ በመገልገያዎችና አገልግሎቶች ዘርፍ የሚደረገው ቀጣይ ኢንቨስትመንት፣ በርቀት ሳቢያ ወደ ኋላ ለቀሩ አካባቢዎች ጥቅም አይሰጥም፡፡

መንግስት ርቀው የተነጠሉ የገጠር ነዋሪዎችን፣ በከተሜነት መስፋፋት ከሚገኙ ጠቀሜታዎች ከተወሰኑት ጋር የሚያስተሳስሩበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ፣ በቆጣሪ የማይሰራ የኤሌክትሪክ አማራጭና ዘመነኛ የመገኛኛ ቴክኖሎጂን ጨምሮ፣ ሌሎች ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች ጥቅም ላይ የሚውሉበትን መንገዶች መንግስት ሊመረምር ይገባል፡፡

የኑሮ ደረጃ ልዩነቶች

ኢ-እኩልነት እና የኑሮ ደረጃ ልዩነቶች በገጠር ማህበረሰቦች (2010-13)

WIDE የውይይት መነሻ አጭር መግለጫ ቁ. 2/...10[1]

ዋና ዋና ነጥቦች ከWIDE መረጃዎች

- ከዕድገትና እመርታ ጎን ለጎን በሃብት በደረጁ ቤተሰቦች ውስጥ የሃብት መደርጀትና በኑሮ መላቅ እየነላ መጥቷል። በመካከለኛ ገቢ ቤተሰቦችም ላይ እንዲሁ መሻሻል ታይቷል። ነገር ግን፤ d ከዚህ ተጠቃሚ መሆን አልቻሉም፤ ያጡ የነጡ ምስኪኖችም በችሮታና በምግብ እርዳታ በህይወትና በሞት መካከል ይገኛሉ።
- የልዩነቱ ምንጮች፡- እየጨመረ የመጣው የእርሻና የከብት ምርት፣ መስኖና የተለያዩ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች፣ ንግድ፣ የተሻሻሉ መንገዶችና የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲሁም ከግብርና ውጭ በሆኑ ሥራዎች መሳተፍና ባህር ማዶ ከተሰደዱ ቤተሰብ አባላት የሚላክ ገንዘብ ይገኙባቸዋል።
- ትልልቅ ለውጦችና ብዙ ልዩነቶች ተመዝግበዋል፡- በተለይ ለግብርና ምቹ በሆኑ፣ የገበያ አዝርዕት በሚያበቅሉ፣ የኢኮኖሚ ብዝሀነት ባላቸው፣ መስኖ ተጠቃሚ በሆኑና ለከተማ ቅርበት ባላቸው አካባቢዎች፣ በሀብታምና ደሀ መካከል ሰፊ ክፍተት እንዲፈጠር ምክንያት ሆነዋል።
- የWIDE ጥናት ክትትል ባደረገባቸው ማህበረሰቦች፤ የኑሮ ልዩነቶች በማህበረሰብ፣ በቤተሰብና በግለሰብ ደረጃ የሚጤኑ ሲሆን በዋናነት በፆታ፣ በእድሜ፣ በሀብትና በማህበረሰብ ውስጥ በሚሰጥ ደረጃ ላይ የተመሰረቱ ናቸው። በዚህ አጭር የጥናት መግለጫ፤ በስፋት የምናተኩረው በችግረኞች፣ በሴት በሚተዳደሩ ቤተሰቦች፣ በወጣቶችና ለችግር ተጋላጭ በሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ ነው። ሌሎች ተዳባይ የጥናት መግለጫዎች ደግሞ፤ ስኬታማ ግለሰቦችንና ሴቶችን የሚዳስሱ ይሆናል።

---

[1] ይህ አጭር የጥናት መግለጫ፤ በWIDE የውይይት መነሻ አጭር የጥናት መግለጫዎች ሁለተኛ ጥራዝ (ስብስብ) ውስጥ ከተካተቱት አስር መግለጫዎች አንዱ ነው። መግለጫው፤ በቴዎድሮስ ወ/ጊዮርጊስ እገዛ በአሉላ ፓንክረስት የተዘጋጀ ሲሆን በደሳለኝ ራህመቶ ተገምግሟል። አዘጋጁ፤ መግለጫዎቹ ይሰናዱ ዘንድ በገንዘብ ለደገፉት ለእንግሊዝ ዓለም አቀፍ የልማት ተቋም፣ ለአይሪሽ ኤይድና ለስዊድን ዓለምአቀፍ የልማት ኤጀንሲ ልባዊ ምስጋናውን ያቀርባል። በተጨማሪም የጥናት ሪፖርቱን በማርቀቅ ሂደት የተሳተፉና አጭር የጥናት መግለጫው የትኩረት አቅጣጫ እንዲሰላ እገዛ ያደረጉ ሌሎች የጥናት ቡድን አባላትና ባለሙያ ገምጋሚዎች፣ ለሥራው ለሰጡት ጊዜና ድጋፍ ያመሰግናል። ሌሎች ምስጋናና ዕውቅና የሚያሻቸውም አሉ፡- (1) ለዓመታት የጥናት መግለጫው የተዘጋጀበትን መረጃዎች ያሰባሰቡና ያደራጁ የጥናት መኮንኖችና ተቆጣጣሪዎች ሙሉ ጊዜያቸውን ሰጥተው ላበረከቱት አስተዋጽኦ፤ (2) በሶስት ዙሮች ለተካሄደው የWIDE ጥናት የገንዘብ ዕገዛ ላደረጉ የተለያዩ ድጋፍ ሰጪ ተቋማት፤ እና (3) በኢልምተ ሰብሳቢነትና በኢኮኖሚ ፖሊሲ ትንተና ክፍሉ በWIDE አጭር የጥናት መግለጫዎች ሁለተኛ ጥራዝ ላይ ለመወያየት መጋቢት 28 ቀን 2016 ዓ.ም በተዘጋጀው መድረክ ላይ የተሳተፉ ከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣናት፣ ላሳዩት ፍላጎትና ለከፈሉት የጊዜ መስዋዕትነት--- ምስጋና ይገባቸዋል። የጥናት መግለጫው፤ በከፍተኛ ደረጃ በተዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ፣ ከመንግስት ባለሥልጣናት ጋር በተደረገው ውይይት የተሰጡ አስተያየቶችን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ከለሳና ማሻሻያ ተደርጎበታል። አጭር የጥናት መግለጫው፤ የኢትዮጵያ የልማት ምርምር ተቋምን (ኢልምተ) ወይም የኢትዮጵያ መንግስትን አሊያም የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርጉለትን የልማት አጋሮች አመለካከትም ሆነ አቋም አይወክልም፤ ይልቁንም የፖሊስ ውይይት ለማነቃቃት የታለመ ነው። ሌሎች የጥራዝ ሁለት የውይይት መነሻ አጭር መግለጫዎችንና የጥናትና ምርምር ውጤቶችን በhttp://ethiopiawide.net/ ድረ-ገጽ ላይ ማግኘት ይቻላል።

- ድሀ ቤተሰቦች ኑሮን ለማሸነፍ የተለያዩ ትልሞችን ይጠቀማሉ፡፡ እነዚህ ትልሞች አብዛኛውን ጊዜ የጉልበት ሥራን፣ ከእርሻ የተለዩና የራቁ እንቅስቃሴዎችንና ተራ ንግዶችን ያካትታሉ፡፡ እነዚህ የቤተሰብ ክፍሎች፤ አደጋን ተከትሎ ለሚከሰት ድንገተኛ ችግር የበለጠ ተጋላጭ ናቸው፤ በአብዛኛው ለድህነት በሚዳርጉ ድርቅ፣ የከብቶች እልቂትና በሽታ በመሳሰሉት ይጠቃሉ፡፡ ተስፋቸውን የጣሉትም በጎረቤት ወይም በዘመድ አዝማዶቻቸው አለሁ ባይነትና በባህላዊ የመረዳጃ ተቋሞች (በተለይ እድሮች) ላይ ነው፡፡
- በሀብታምና ድሃው መካከል ያለው ግንኙነት ብዙ መልክ ያለው ሲሆን፤ የሥራ ቅጥር፣ የእኩል እርሻ፣ የእኩል እርቢ፣ ብድርና ችሮታን ያካትታል፡፡ ግንኙነቱ በአብዛኛው በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ ቢሆንም ሃብታሙ የበለጠ ተጠቃሚ ነው፡፡ በአንዳንድ ማህበረሰቦች በድርቅና ግሽበት የተነሳ ትብብሩ እያሽቆለቆለ መምጣቱን ማስረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በጥቂት ማህበረሰቦች ውስጥ ሀብታም ቤተሰቦች የራሳቸውን ምርት በማሳደግ ላይ ያተኮሩ ሲሆን ውስጣዊ ክፍፍል መጨመሩም ተመዝግቧል፡፡
  - ለድሃዎች ና ለችግር ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ማህበራዊ ዋስትናን ለማጎልበት፣ የሀብት አቅም ያላቸውን ጨምሮ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጥምረትን በመፍጠር፣ ባህላዊ የመረዳጃ ተቋማትን አሰራር ማስፋፋት ይኖርባቸዋል፡፡
- ብዙዎቹ ድሃ ቤተሰቦች መሰረታዊ የእርሻ ግብዓትን በተለይ የማዳበሪያ ወጪን ለመሸፈን አቅም ያጥራቸዋል፤ ይሄም እዳ ውስጥ ይዘፍቃቸዋል፡፡ በዚህም የተነሳ ተጨማሪ ለውጥ በሚያመጡ የኤክስቴንሽን ማዕቀፎች ውስጥ ለመሳተፍ እምብዛም ተንሣሽነት አያሳዩም፡፡
  - ከእርሻ ውጭ የሆኑ ሥራዎችን፣ ኤክስቴንሽንና የብድር አገልግሎትን እንዲሁም የገንዘብ ድጋፎችን የሚያስፋፉ፣ ከአቅምና ፍላጎታቸው ጋር የተጣጣሙ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞችን በመቅረጽ፣ የድሃዎች የኑሮ መተዳደሪያ ሊሻሻል ይችላል፡፡
- ለድሃ የሚደረግ ድጎማን ጨምሮ በአደጋ ለሚሞቱ ከብቶችና ለጤና አገልግሎት ማካካሻ የሚሰጡ የኢንሹራንስ ፕሮግራሞች የበለጠ ሊስፋፉ ይገባል፡፡ ከሴቶች የመሬት ባለቤትነት መብትና ከልጃገረዶች ትምህርት ጋር የተያያዙ የፆታ ግንኙነቶችን እንዲሁም ሴቶችና ህፃናትን ያማከለ የጤና አገልግሎትን በተመለከተ አዎንታዊ ለውጦች ተመዝግበዋል፡፡ የጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች መቀነስም የዚሁ አዎንታዊ ለውጥ አካል ናቸው፡፡
- የፆታ ሚናን በተመለከተ አዎንታዊ ለውጦች ቢመዘገቡም፣ አሁን ድረስ የቤት ውስጥ ስራዎችን በተለይ የመወጣት ሀላፊነት በልጃገረዶችና ሴቶች ላይ የተጣለ ነው፡፡ ከቤት ውስጥ ስራዎች ባሻገርም በንግድና በግብርና ላይ እኩሌታውን መሳተፍ አሁንም የሴቶቹ ተጨማሪ ሀላፊነት ነው፡፡
- ሴቶች እንደ አባወራ ሆነው የሚያስተዳድሩት ቤተሰብ በብዛት የተለመደ አይደለም፡፡ ብዙዎቹ በንግድ፣ በዕደጥበባትና በምግብ ማቀናበር ሥራዎች ላይ ነው የሚሠማሩት፡፡ ግና የሴት አባወራ ባለበት ቦታ ብዙ ጊዜ የግብርና ሥራ የሚሸፍንላቸው የሰው ጉልበት በማጣት ይቸገራሉ፡፡
  - የሴቶች ገቢ ማመንጪያ እንቅስቃሴዎችን ማስፋፋት፣ ዕድገትን ሊያነቃቃና ፆታዊ ሚዛንን ሊያሻሽል ይችላል፡፡

- ለሴቶች ቅርብ የሆነ የኤክስቴንሽንና የብድር አገልግሎትን የበለጠ ተደራሽ ማድረግ፣ ሴቶች የኑሮ መተዳደሪያቸውን የሚያሻሽሉበት እድሎችን ሊያነለብት ይችላል፡፡

- የመሬት አቅርቦት መቀነስና ተቀጥሮ የመስራት እድል ማጣት ወይም የሚመጥን አለመሆን፣ በትውልድ መካከል ውጥረት ፈጥሯል፡፡ የህብረት ሥራ ማህበራት ውስን ስኬት፣ አንዳንድ ወጣቶችን ወደ ተስፋ መቁረጥ እንዲገቡ አድርጓቸዋል፡፡ በትምህርት ወደ ለውጥ ጎዳና ቢገቡም፣ ህልማቸውን አለማስጨበጡ አንዳንዶችን ለስደት አነሳስቷቸዋል፡፡

- ምንም እንኳን፤ የስራ መነሻ ገንዘብና የብድር አቅርቦት፣ ድህ ለሆኑ ወጣት ወንዶችና ሴቶች ማነቆዎች ቢሆኑባቸውም ብዙዎቹ ወጣቶች፣ መጠነ ሰፊ በሆኑ እርሻ-ዘለል የሥራ ፈጠራ እንቅስቃሴዎች (በተለይ የኢኮኖሚ ብዝሀነትና ከፍተኛ የንግድ ትስስር ባሉባቸው አካባቢዎች) ላይ ተሰማርተዋል ፡፡ ፡፡

  - ወጣት ሴቶችን ጨምሮ ለገጠር ወጣቶች፣ የስራ ፈጠራ ፕሮግራሞች እንዲሁም የብድር አገልግሎትና ስልጠና በቀላሉ ተደራሽ መሆን ትልቅ ትኩረት መስጠት፣ የወጣቶችን የኑሮ መተዳደሪያ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

  - በተለይ ከግብርና ውጭ በሆኑ ሥራዎች ስኬት ከተቀዳጁ የህብረት ሥራ ማህበራት ትምህርት መቅሰምና የወጣቶች የሥራ ፈጠራ አቅምን ማጎልበት፣ ስደትን ከማለም የተለዩ አማራጮችን እንዲያገናዝቡ እድል ይሰጣቸዋል፡፡

- አልፎ አልፎ ወላጅ አልባ ህጻናትን ለመርዳት የለውጥ እንቅስቃሴ ከመኖሩ በስተቀር ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ቡድኖች በአብዛኛው የሚደገፉት በማህበረሰቡ ነው፡፡ አረጋዊያን እምብዛም ከዚህ ተጠቃሚ አይደሉም፡፡

- እንደ ኤች አይ ቪ/ ኤድስና የአእምሮ ህመም በመሰሉ ተጠቂ የሆኑ አንዳንድ የማህበረሰብ ክፍሎች በማህበረሰቡ መገለል ይደርስባቸዋል ፡፡

- የጉልበት ሰራተኞች፣ የእደ ጥበብ ባለሙያዎችና አንዳንድ ለማህበረሰቡ መጤ የሆኑ ንዑስ ቡድኖች መድሎ ይደረግባቸዋል፡፡

  - የአረጋውያን፣ የእጉዋለ ማውታን፣ የአካል ጉዳተኞች፣ የድሃዎች ፣ መድሎ የሚደረግባቸውና የተገለሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን ጨምሮ ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ቡድኖች የሚያጠቃልል የማህበረሰብ ዋስትና አገልግሎት ለመስጠት በማህበረሰቡ ደረጃ ወደታች ወርደው የሚተገብሩ ከማህበረሰባዊ ለውጥ አቀንቃኞች ማሠማራት ግድ ይላል።

- የማህበረሰብ ዋስትና ጥበቃን ስኬታማ ለማድረግ፣ አካባቢ አስተዳደር፣ የግሉ ዘርፍ፣ የሲቪል ማህበረሰብ፣መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ የማህበረሰብ መሪዎችና ባህላዊ ተቋማትን ጨምሮ ሌሎች በባለድርሻ አካላት መካከል የሚፈጠር የላቀ ትብብር ያሻል፡፡

<u>መግቢያ</u>

ይህ አጭር የጥናት መግለጫ፤ በ20 የገጠር ማህበረሰቦች ውስጥ የታየውን የሃብት አለመመጣጠንና የኑሮ ልዩነት ለማሳየት የWIDE ኢትዮጵያ መረጃዎችን ይጠቀማል፡፡ የኑሮ ልዩነቶች በማህበረሰብ፣ በቤተሰብና በግለሰብ ደረጃ የሚጤኑ ሲሆን በፆታ፣ እድሜ፣ ሀብትና በማህበረሰብ ውስጥ የሚሰጥ

ደረጃ ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ ይህ የጥናት ጽሁፍ በዋናነት፣ ከማህበረሰቡ እድገትና ለውጥ አንፃር ወደ ኋላ የቀሩ ድሃዎች ፣ በሴት (እማወራ) የሚተዳደሩ ቤተሰቦች፣ ወጣቶችና ለችግር ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የሚያተኩር ሲሆን፤ ሌሎች አባሪ የጥናት መግለጫዎች፤ ስኬታማ ግለሰቦች፣ ሥራ ፈጣሪዎች፣ የከተማ መስፋፋትና እድገት ላይ ያተኩራሉ (ማጣቀሻ፡- የገጠር ከተሜነት መስፋፋት፤ ስኬት እና ለውጥ)፡፡

በየማህበረሰቡና በማህበረሰቦች መካከል ኢ-እኩልነት የኑሮ ደረጃ ልዩነቶች

በWIDE የጥናት አካባቢዎች፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣ የኑሮ ልዩነትና ኢ-እኩልነት ተስተውሏል፡፡ የተሻለ ሀብት ያላቸው ቤተሰቦች፤ የእርሻና የከብት እርባታ ምርትን ለማሳደግ፣ በመስኖ፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች፣ ንግድ፣ የተሻሉ መንገዶችና ትራንስፖርት ተጠቃሚ ለመሆንና ከግብርና ውጭ ባሉ ሥራዎች ለመሳተፍ የሚያስችሉ አዳዲስ ዕድሎችን የመጠቀም የተሻለ ብልጫ አግኝተዋል፡፡ ለእርሻና ለገበያ አዝርዕት ምርት ይበልጥ ምቹ በሆኑ፣ ለከተማ አካባቢዎች ትስስርና ቅርበት ባላቸው እንዲሁም የኢኮኖሚ ብዝሃነት በሚታይባቸው ማህበረሰቦች የበለጠ ልዩነት የተመዘገበ ሲሆን፤ ይሄም በድህና ሀብታም መካከል ትልቅ ልዩነትን ፈጥሯል[2]፡፡ ነገር ግን፤ በምግብ ራሳቸውን ባልቻሉና በአርብቶአደር አካባቢዎችም እንዲሁ ጉልህ ልዩነት መፈጠሩ ተስተውሏል፡፡

ግብርና (ማለትም መስኖ፣ የገበያ አዝርዕት፣ ከብት እርባታና የወተት ተዋፅኦ ምርቶችን ጨምሮ) ዋነኛ የለውጥ አራማጅ ሞተር ነው፡፡ መስኖ፤ የገበያ አዝርዕትና አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ ሽንኮራ አገዳ ምስርና ድንች፣ ጥራጥሬ ፣ በአንዳንድ አካባቢ ደግሞ የቡና፣ ጫትና ባህር ዛፍ ምርትን ውጤታማ ያደርጋል፡፡ ዝናብን በመጠቀም የገበያ አዝርዕት ማምረት፣ በዋናነት ለጥራጥሬ እህሎች ምርት አመቺ በሆኑ አካባቢዎችም አስፈላጊ ነው፡፡ ዝናብ ሳይዘንብ ሊቀር እንደሚችል ግንዛቤ ውስጥ በማሣደር መስኖ ዝናብ አጠር በሆኑ አካባቢዎች የበለጠ አስፈላጊ ነው። የተዳቀሉ የጥራጥሬ እህሎችና ማዳበሪያ የገበያ ትስስሮችን አጠናክረውታል፡፡ ለግብርና የጥናትና ምርምር ተቋማት ቅርብ በሆኑ አካባቢዎች፣ የላቀ ምርት የሚሰጡ ወይም ድርቅን የመቋቋም ብቃት ያላቸው የዘር ዓይነቶች በስፋት የመተዋወቅ ዕድል አግኝተዋል፡፡

ሁለት የአርብቶአደር አካባቢዎች በእርሻ ስራ ላይ መሳተፍ ጀምረዋል፡፡ ኢኮኖሚያቸው በአብዛኛው ከብት በማርባት ላይ የተመሰረተ ቢሆንም፤ በገልቻ መስኖ በመጠቀም፣ በሉቃ ደግሞ በውሃ ማውረጃ ቦይ በመዘርጋት የእርሻ ሥራ ውስጥ ተሠማርተዋል፡፡ በብዙ አካባቢዎች የቀንድ ከብት ገበያ ለህልውናቸው ወሳኝ ሲሆን አንዳንድ ነጋዴዎችም በከብት ንግድ ሃብት አፍርተዋል ፡፡ በበርካታ አካባቢዎች ከብት ማደለብና የወተት ተዋፅኦዎችን ማምረት፣ ከአቅራቢያ ከተሞች ጋር ከተፈጠረ ትስስር ጋር ተዳምሮ፣ ቁልፍ የሃብት ልዩነት ምንጭ ሆኗል፡፡

ለእርሻ ምቹ በሆኑ፣ ጥሩ የገበያ ትስስርና የመንገድ አውታሮች ባላቸው አካባቢዎች፣ የገበያ አዝርዕት ንግድ ዋናው የልዩነት መንስኤ ነው፡፡ አንዳንድ ስኬታማ ነጋዴዎች ከእርሻ ወጥተው ወደ ሌላ ሥራ

[2] ይህ በ *Ethiopia Poverty Assessment 2014.* ውስጥ ከሚገኙ አሃዛዊ የጥናት ግኝቶች ጋር ይጣጣማል፡፡ World Bank Group. 2015. Washington, DC. © World Bank. https://openknowledge.worldbank.org/handle/10986/21323 License: CC BY. 3.0 IGO.

የገቡ ሲሆን፤ ሃብታም በሆኑ አካባቢዎች የሚገኙ ጥቂቶቹ ደግሞ መጓጓዣ (ሚኒባስና የጭነት መኪና) መግዛት እንዲሁም ወፍጮ ቤትና ሱቅ፣ የአትክልት መሸጫ መደብር፣ የመጠጥ ግሮሰሪና ሆቴል ማቋቋም ችለዋል፡፡

የአዳዲስ መንገዶች ዝርጋታ ወይም የነባሮቹ ዕድሳትም ለገጠሩ ኢኮኖሚ (ርቀው ለተነጠሉ አካባቢዎች ሳይቀር) መሻሻል የላቀ ድርሻ አለው፡፡ ባጃጅና ሞተር ብስክሌትን የመሳሰሉ የመጓጓዣ አማራጮች መስፋፋት፣ የማህበረሰብ ትስስርን ያሻሻለ ሲሆን አዳዲስ የስራ ዕድሎችንም ፈጥሯል፡፡ ከዚህም ባሻገር ሥራ ፈጣሪዎች በትራንስፖርት ዘርፍ መዋዕለ ንዋያቸውን እንዲያፈሱ አነሳስቷል፡፡

የነባር ከተሞች መስፋፋት የገጠሩ ኢኮኖሚ እንዲያንሰራራና እንዲያድግ ማነቃቂያ ሆኗል፡፡ የእርሻም ሆነ የከብት ምርት ገበያን ከመፍጠርም ባሻገር፣ በአገልግሎት ዘርፍ፣ በግንባታና በፋብሪካ ውስጥ የመስራት ዕድሎችን ከፍቷል፡፡ ይሄም በብዙ አካባቢዎች ለልዩነት መፈጠር ምክንያት ሆኗል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፤ በገጠር የሚኖሩ የተሻለ ሀብት ያፈሩ ቤተሰቦች፤ በአካባቢ ከተሞች (ርቀው በተነጠሉና በምግብ ራሳቸውን ባልቻሉ ማህበረሰቦችም ጭምር) መዋለ ነዋይ አፍስሰው መኖርያ ቤቶችን ቀልሰዋል፡፡

በመጨረሻም፤ ባህር ማዶ ከተሠደዱ የቤተሰብ አባሎች የሚላክ ገንዘብ፣ ለብዙዎቹ የገጠር አካባቢዎች ኑሮ መሻሻል ዋነኛው ምክኒያት ነው፡፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች ይሸው ከስደተኞች የሚላክ ገንዘብ፣ በትርፋማ ሥራዎች ላይ ሲውል አንዳንድ የገበሬ ቤተሰቦችን ከአብዛኞቹ የበለጠ ያበለጽጋቸዋል፡፡ እንደውም አንዳንዴ ገንዘባቸውን በአቅራቢያ ከተሞች ቤት ለመሥራት ወይም ለንግድ ሥራ ያውላሉ (ማጣቀሻ፡- ፍልሰት)፡፡

<u>የአየር ጠባይ ለውጥና የምርት ውድመት የሚያስከትለው ሊደጋ እና አንደምታዎች</u>

ዝናብ አጠር በሆኑ አካባቢዎች ፈርጀ ብዙ የአየር ጠባይ ለውጦች በአብዛኞቹ ቤተሰቦች ላይ ችግሮችን አስከትሏል፡፡ በእጅጉ የተጎዱት ግን በተለይ በጣም ድሃ የሆኑ ቤተሰቦች ናቸው፡፡ ይሄ የሚከሰተው በአብዛኛው በድርቅ አመታት ሲሆን አንዳንዴ ለአያሌ ከብቶች ሞት ምክንያት ይሆናል፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ፣ ጎርፍ፣ አውሎ ነፋስና ውርጭ የእህል ምርት ውድመትን አስከትሏል፡፡ በአንዳንድ አመታት እህል በሚያጠፉ ተባዮችና አረሞች መንስኤ ሰፊ ሽፋን ያላቸው የተለያዩ የአዝርዕት ምርቶች ተጎድተዋል፡፡ የእንስሳት በሽታም ከብቶችን፣ በጎችን፣ ፍየሎችንና ግመሎችን አጥቅቷል፡፡ ዝቅተኛ በሚባሉ የመልክአ ምድራዊ ቦታዎች ከዝናብ መጣል ጋር ተያያዥ የሆነ የወባ ወረርሽኝ ከባድ ችግር ሲሆን በጥቂት ቦታዎች የተቅማጥ በሽታ መከሰቱ ተነግሯል፡፡

ከአየር ጠባይ ጋር ተያያዥ የሆኑ አደጋዎችና የምርት ውድመቶች ዝናብ አጠር በሆኑና በዝቅተኛ ቦታዎች ይበልጥ የተለመዱና የከፉ መሆናቸው የታወቀ ነው፡፡ ሆኖም በትርፍ አምራችነት በሚታወቁና የገበያ አዝርዕት በሚያመርቱ አካባቢዎችም ችግሮች መኖራቸው ተነግሯል፡፡ የሚከሰተው የተፈጥሮ አደጋና የሚከሰትበት ጊዜ በአካባቢው ሁኔታዎች የሚወሰን ቢሆንም ሌሎች ጉዳዮችንም ይጨምራል፡፡ ከእነርሱም መካከል፡- የአደጋው መከሰት ተገማች አለመሆን፣ የዝናብ መቀነስ ወይም ዘግይቶ መምጣት፣የሙቀት መጨመር፣ የአፈር ለምነት ማሽቆልቆል፣ የአፈር

መሸርሸርና የደን መመንጠር፣ በአውሎ ነፋስ የሚከሰት የአዝርዕት ጥፋት እንዲሁም የአዝርዕትና የከብቶች በሽታዎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡

በሃብት የደረጁ ቤተሰቦች በአየር ጠባይ ለውጥ ሳቢያ የሚከሰት አደጋን የተሻለ የመቋቋም አቅም ያላቸው ሲሆን በአደጋው ማግስት የሚከተሉትን የረሀብ ወቅቶች ያለ ብዙ ስቃይ ያልፉታል፡፡ በአደጋው ያጡትን የከብት ሀብትና የኑሮ መተዳደርያ ዳግም ለመገንባትም ይችላሉ፡፡ ድሃ ቤተሰቦች ግን አደጋውን የመቋቋም አቅም ስለሌላቸው፣ለተከታዮቹ የረሃብ ወቅቶች ስቃይና መከራ ይጋለጣሉ፡፡ አብዛኛውን ጊዜም ብድርና ዕዳ ውስጥ ይዘፈቃሉ፡፡ ይሄ ደግሞ ከነበሩበትም የባሰ የድህነት አዘቅት ውስጥ ይከታቸዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ የተፈጥሮ አደጋና የምርት ውድመት፣ ከተደራራቢ የጤና እና የማህበረሰብ አደጋ ጋር በመቀናጀት በማህበረሰቦች ውስጥ ያለውን ልዩነት የበለጠ ያጎሉታል፡፡

<u>በቤተሰብ ደረጃ ያሉ ልዩነቶች</u>

የWIDE ጥናት ክትትል ባደረገባቸው አካባቢዎች ውስጥ ያሉ ቤተሰቦች፣ ባላቸው ጥሪት መነሻነት፣ ሀብታም፣ ድሃና ከድህነት ወለል በታች በሚሉ ሰፊ ዘርፎች ተከፋፍለዋል፡፡ የሀብትና የድህነት ፍረጃው እንደ የአካባቢው ሁኔታ ሊለያይ ይችላል፡፡ በዚህ ሦስት ምድብ መሰረት በቤተሰቦች መካከል ለታየው ልዩነት ዘርፈ ብዙ ምክንያቶች ቀርበዋል፡፡ ከቀረቡት ምክንያቶች መሀል የተፈጥሮ ሀብት ተጠቃሚነት ለምሳሌ መሬት (በተለይ በመስኖ የሚለማ መሬት)፣ የከብት ባለቤትነት፡- (ለእርሻ የሚሆኑ ጥማድ በሬዎች እንዲሁም ለንግድ የሚደልቡ ከብቶች) ይጠቀሳሉ፡፡ የሰው ጉልበትን የመጠቀም አቅምም የልዩነት ሌላው መንስኤ ነው፡፡ አቅም ያላቸው ቤተሰቦች በእርሻቸው ላይ በቀን፣ በወራት አሊያም በአመት አበል ከፍለው የሚያሰሯቸውን የጉልበት ሰራተኞች መቅጠር ይችላሉ፡፡ እንዲያውም ሃብታም ገበሬዎች፤ የደቦ እርሻ በሚኖርበት ወቅት ድሃ ገበሬዎችን በጉልበት ሰራተኞች እነሱን ወክለው እንዲሰሩ የሚልኩበት ሁኔታዎች በኮርማርጌፊያ፣ አዳ ዳዋታ ተስተውለዋል፡፡

የግብርና ግብዓቶች በተለይ ማዳበሪያን መጠቀም ዘርንም ሆነ ዝርያን ስለሚያሻሽል ዋነኛ የልዩነት ምክንያት ነው፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች (ለምሳሌ በየትመን አዝርዕት ለማብቀል ሰፊ ዳስ መስራት እንዲሁም በቱሩፌ በእጅ የሚሰራ የእህል መውቂያ መጠቀም) ልዩነት ፈጥረዋል፡፡ በተለይ በመስኖ የማልማት አቅም ባለበት አካባቢ ከገበያ አዝርዕት የሚገኝ ገቢ ሌላው ትልቁ የልዩነት መንስኤ ነው፡፡ በእርግጥ የገቢው መጠን እንደ አካባቢው አቅምና የገበያ ሁኔታ የሚወሰን ነው የሚሆነው፡፡

በቀበሌዎች ውስጥም ቢሆን ለመንገድ ያለው ቅርበት አልያም ለቀበሌ ማዕከሎች መቅረቡ የቤተሰቡን የሀብትና ድህነት አዝማሚያ ሊጠቁም ይችላል፡፡ ለመንገድ ወይም ለገበያ አሊያም ለቀበሌ ማዕከል አስተዳደር አካባቢዎች ቀረብ ብለው የሰፈሩ ቤተሰቦች ሱቅ ወይም ሌሎች የንግድ አገልግሎቶችን የመክፈት ዕድል ይኖራቸዋል (ማጣቀሻ፡- የገጠር ከተሜነት መስፋፋት)፡፡

አቅም ያላቸው ቤተሰቦች መገለጫዎች

አቅም ያላቸው ቤተሰቦች በአጠቃላይ ለመሬት ባላቸው የበለጠ አቅርቦትና በከፍተኛ የከብት ሃብት ይዞታቸው ይለያሉ፡፡ በተለይ ለእርሻና ለማደለብ የሚሆኑ በሬዎች እንዲሁም ዘመናዊ የግብርና

ምርት ማበልፀጊያ ግብዓቶችን መጠቀም፤ (ለምሳሌ፡- ማዳበሪያና የተሻሻሉ የእህል ዘሮችና የከብት ዝርያዎች) አይነተኛ መለያ ባህርያቸው ነው፡፡ የመስኖ አቅም ባላቸው አካባቢዎች የመስኖ ልማት ምርቶችን በመሸጥ የተሻለ ትርፍ ማግኘት ችለዋል፡፡ በሃብት የደረጁ ቤተሰቦች፤ አብዛኛውን ጊዜ የጉልበት ሰራተኞች በመቅጠር ወይም ተራ በተራ (በወንፈል) ከመሳተፍ ይልቅ ሰውን አደራጅተው በማሰራት (ደቦ) የሰው ሃይል አቅርቦታቸውን ያሳድጋሉ፡፡ የገበያ አዝርዕትን በመሸጥም ይበልጥ ከገበያ ጋር ትስስር ይፈጥራሉ፡፡

ብዙዎቹ የተሻለ ጥሪት የቋጠሩ ቤተሰቦች ከእርሻ እንዲሁም ከእርሻ ውጭ በሆኑ ዘርፎች የገቢ ምንጫቸውን በዓይነት አስፍተዋል፡፡ አንዳንዶች ከእርሻው ከእነአካቴው ወጥተው ሙሉ በሙሉ ወደ ንግድ አለም ማለትም ፣ትራንስፖርትና የአገልግሎት ዘርፎች ገብተዋል፡፡(see DB08:success). አያሌዎቹ ደግሞ ትልቅ ብድር ወስደው ራሳቸውም ገንዘብ አበዳሪ እስከመሆን ደርሰዋል፡፡ እነዚህ ብዙውን ጊዜ ትልልቅ እቁብ የሚጥሉና ከአንድ በላይ እድር ውስጥ አባል የሆኑ ናቸው፡፡

በሃብት የደረጀ ቤተሰብ የተሻለ መኖሪያ ቤት አለው፡፡ ቤቱ ባለቆርቆሮ ጣራ፣ የታጠረ ግቢ፣ ብዙ ክፍሎች ያሉት፣ የተለየ የከብቶቹ ማደሪያ የተሰራለት፣ የብቻው ኩሽና አንዳንዴም መጸዳጃ ቤትም ያለው ነው፡፡ ጥቂት ሃብታም ቤተሰቦች በአካባቢ ከተሞች ላይ ቤት መቀለሳቸው ይበልጥ እየጨመረ መጥቷል፡፡ በሃብት የደረጁ ቤተሰቦች፤ የተመጣጠነ ምግብ የሚያዘወትሩ ሲሆን ለድግስም ብዙ ወጪ ያወጣሉ፡፡ የእንስሳት ተዋፅኦም እንደአስፈላጊነቱ በዓል ሳይጠብቁ ይመገባሉ። አንዳንዶቹ በከተሞች የሚገኙ የግል የጤና አገልግሎት ተቋማት ተጠቃሚ ሲሆኑ፣ ልጆቻቸውንም መዋዕለ ህጻናትና ኮሌጅን ጨምሮ በግል ትምህርት ቤቶች ከፍለው ያስተምራሉ፡፡

የልሂቃን አፈጣጠር

ከማህበርሰቡ ፈንጠር ያለ ህይወት ያላቸው ሰዎች (በደምሣሣው ጉልህ ሰዎች ወይም ልሂቃን) አፈጣጠር በተሻሉ የምርት ማበልጸጊያዎች አቅም፣ጥራት ወይም ቅንጦት ባላቸው የመገልገያ እቃዎች፣ እንዲሁም የተሻሻሉ የግል የጤና እና የትምህርት አገልግሎት አጠቃቀማቸው ተለይተው ይወጣሉ፡፡ ልሂቃንን በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል፤ “ባህላዊ” እና “ዘመናዊ” በሚል፡፡ ባህላዊ ልሂቃን፤ ስልጣናቸውን በዋናነት የሚያገኙት መሬትንና የሰው ጉልበትን በመቆጣጠር እንዲሁም በከብቶች ሃብት ነው፡፡ ዘመናዊ ልሂቃን፤ በጣም በቅርቡ ብቅ ያሉ ሲሆን የበለጠ ስልጣን ያላቸው ናቸው፡፡ የስልጣን ሰገነትን መቆጣጠር የቻሉት፣ የንግድ ምህዳሩንና ሀብትን በእጃቸው በማስገባታቸው፣የተሻለ ትምህርት የመቅሰም ዕድል በማግኘታቸው፣የውጭ ትስስር በመፍጠራቸውና ፖለቲካውን መዘወር በመቻላቸው ነው፡፡ በከፊልም የሲቪል ሰርቪሱ በቀበሌዎች ደረጃ መስፋፋቱ ለልሂቃት መፈጠር አንዱ ምክንያት ነው፡፡ ከፍተኛ ሀብት፤ ልሂቃኑን በሃብት በደረጁ አካባቢዎች፣ የውሃ መሳቢያ ሞተርና ተሽከርካሪዎችን የመሳሰሉ የምርት ማበልጸጊያ እሴቶችን የመግዛት አቅም ብቻ አይደለም ያጎናጸፋቸው። እንዲሁም ድህነት በበረታባቸው አካባቢዎችም፣ በደቦ የሰው ጉልበት በማስተባበር የስራ ሃይል ማንቀሳቀስ ችለዋል፤ ወዝ አደሮችን በደሞዝ ከመቅጠር ጀምሮ፣ በቀላሉ የማይገኙ እንደ ፈረስና ግመል የመሳሰሉትን ጨምሮ ብዙ ከብቶች ላይ መዋዕለ ንዋያቸውን አፍስሰዋል፤ መኖሪያ ቤታቸውን አሻሽለዋል(ለምሳሌ የቆርቆሮ ጣራ ያለው ቤት ይሰራሉ)፤ በከተማ ውስጥም ቤት ይቀልሳሉ፡፡ የብረት አልጋ፣ ብርድልብስ፣ ከኤሌክትሮኒክ እቃዎች፡- እንደ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥንና

የሳተላይት ቴሌቪዥን፣ ከተሽከርካሪዎች ደግሞ ብስክሌት፣ ሞተር ብስክሌት ይገዛሉ፣ በጥቂት የገበያ አዝርዕት አብቃይ አካባቢዎችም የጭነት መኪናም ሸምተው ታይተዋል ። ልሂቃኑ በከተሞች የተሻሉ አገልግሎቶችን ማግኘት የቻሉ ሲሆን ልጆቻቸውን ለትምህርት ወደ ከተማ ይልካሉ። ልሂቃንነት ከፍተኛ ሀብትን የማዘዝ አቅም ብቻ ሳይሆን ተፅዕኖ የመፍጠር አቅምንም ይጨምራል። ይኽም በሚገኙበት የገጠር መንደር በመደበኛውና በኢ-መደበኛው ስልጣን ድርጅታዊ ውክልና ይኖራቸዋል።

በሀብታምና ድሀ መካከል ያለው ግንኙነት

በሃብታሙና ድሃው መካከል የሥራ ዕድል፣ እኩል እርሻ፣ የከብት እርባታ፣ ብድርና ችሮታን ጨምሮ ፈርጀ ብዙ መልኮች ያሉት ግንኙነት ነበር። የተደላደለ ኢኮኖሚ ባላቸው አካባቢዎች፣ ብዙ ሀብታም ገበሬዎች፣ ድሀ ግለሰቦችን በደሞዝ ይቀጥሯቸዋል። በሃብት የደረጁ ቤተሰቦች፤ አብዛኛውን ጊዜ በሬ ከሌላቸው ወይም በበሽታ ወይም እርጅና ምክንያት ከደከሙ ድሀ ገበሬዎች መሬት ላይ አምርተው በጋራ ለመጠቀም ውል ይገባሉ። አንዳንድ አቅም ያላቸው፣ ነገር ግን መሬት የሌላቸው ድሀ ገበሬዎች፣ የሃብታሙን ትርፍ መሬት አርሰው ከትርፉ ለመካፈል የሚዋዋሉ ሲሆን፤ ይሄን ውል የሚያደርጉትም ከድህነት ለመውጣት በማሰብ ነው። ብዙውን ጊዜ ስምምነቱ ለመሬት ባለቤቱ የሚያደላ ነው። የእኩል ከብት እርቢም ድሀና ሀብታሙን የሚያስተሳስር ውል ይፈጥራል። በተለይ ሀብታሙ ብዙ ከብት ኖሮት የማገድ አቅም ባጠረው ጊዜ ወይም የግጦሽ መሬት ሳይኖረው ሲቀርና ድሃው ለልጆቹ ወተት የሚፈልግ ከሆነ፣ ይሄንን የእኩል ከብት እርቢ ውል ይፈፅማል። አንዳንድ ሀብታም ገበሬዎች የማረሻ ጥማድ በሬ ለሌለው ድሀ ገበሬ በሬን በውሰት ይሰጣሉ፤ አልፎ አልፎም ገንዘብ ያበድራሉ፤ ግን የገንዘብ ብድሩ በአራጣ መሆኑ የተለመደ ነው። ጥቂት ሀብታም የገበሬ ቤተሰቦች ደግሞ ለድሀው ጎጆ መቀለሻ መሬትን ይፈቅዱና በአፀፋው ድሀው ገበሬ በእርሻ መሬታቸው ላይ በጉልበቱ እንዲሰራ ይዋዋላሉ።

ብዙዎቹ በሃብታምና ድሃ ቤተሰቦች መካከል የሚፈፀሙ ስምምነቶች በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ሆኖም አብዛኛውን ጊዜ የመሬቱ ባለቤቶቹ ወይም ጉልበት በርካሽ ዋጋ በማግኘት የበለጠ ተጠቃሚዎቹ ሃብታሞቹ ናቸው። ስለዚህ፤ ይህ የውል ትስስር እንደ ብዝበዛ መዋቅር ሊቆጠርም ይችላል። እንዲያም ሆኖ ሀብታም ቤተሰቦች ድሃዎች ችግር ሲገጥማቸው ችሮታ ያደረጉባቸው ወይም የደጎሙባቸው ጥቂት አጋጣሚዎች ታይተዋል። በተለይ ድህው የምግብ እጦት በገጠመው ጊዜ እጃቸውን ይዘረጋሉ። ለምሳሌ በሶሞዶ አንድ ድሀ የገበሬ ቤተሰብ ረሀብ በተከሰተ ወቅት ከሀብታም ገበሬ የእንሰት ምግብ እንደ ስጦታ ተበርክቶለታል። በአዳ ዳዋታ፣ አንድ ድሀ ሴት፣ ስኬታማ ከሆነ አንድ ነጋዴ፣ የቀብር ማስፈፀሚያ ወጪ ተሸፍኖላታል።

በቤተሰቦች መካከል ያለው ትብብር መቀነስ

በጥቂት አካባቢዎች የትብብር መንፈስ እያሽቆለቆለ መምጣቱ ተጠቁሟል። ሀብታም የገበሬ ቤተሰቦች፤ ትኩረታቸው በራሳቸው የምርት እድገትና የጉልበት ሰራተኛ መቅጠር ላይ ሆኗል። በተደጋጋሚ በሚመላለሰው የድርቅ አደጋ ምክንያት (በሃረሳው) ወይም የከብትና ወተት ዋጋ ማሻቀቡ፣ የጋራ የላም እርባታ ሥራ የማከናወን ፈቃደኝነትን እያጠፋው መጥቷል። የጉልበት ሥራ በእርሻ በሬ ውሰትና ጥማድ በሬም ጭምር የመለወጡ የልምድ አሰራርም (በኮርማርገፍያ)

ተዳክሟል፡፡ ጎጆ ተባብሮ የመቀለሱ ልምድም በአንዳንድ አካባቢዎች እየቀረ መምጣቱ ተስተውሏል፡፡ ለዚህም ምክኒያቱ የተሻለ ሀብት ያፈሩ ገበሬዎች የግንባታ ባለሞያ ቀጥረው ቤታቸውን ማሰራት በመጀመራቸው ነው (ግራር)፡፡ በሁለት አካባቢዎች የትብብር መንፈስ ለማሽቆልቆሉ ምክንያቱ በሙስሊምና በክርስቲያን መካከል ያለው ሀይማኖታዊ ልዩነት እየጎላ በመምጣቱ ነው ተብሏል፡፡ ይሄም በሙስሊሞችና ክርስትያኖች መካከል የነበሩ ዕድሮች ቀርተው በሙስሊም እምነት ተከታዮች ብቻ (ሶሞዶና አዳ ዳዋታ) የተለያዩ ዕድሮች እንዲመሰረቱ አድርጓል፡፡ በሦስት አካባቢዎች ፤ በሁለቱ (ገልቻ እና ቆሮደጋጋ) ለስራ ትብብር ከስደት ማህበረሰቡን የተቀላቀሉ ቤተሰቦችን እንዲገለሉ አግደዋል፡፡ በሦስተኛው መንደር ደግሞ የማህበረሰቡን አባላት ከተሰደዱበት ሲመለሱ አልቀበልም ብለዋቸዋል(ሹምሸሃ)፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች ድሀ ቤተሰቦች ቀበሌ በሚያደራጀው የአንድ ለአምስት መዋቅር ውስጥ እንዲገቡ መገደዳቸውን ጠቅሰዋል፤ ይህም በባህላዊውና በዘመናዊው የትብብር አሰራር መካከል ውድድር እየተፈጠረ መምጣቱን ጠቋሚ ነው፡፡ ባላቸው ከሞተባቸው በኋላ ውስን ትብብር የገጠማቸው የቤት እመቤቶች ያሉበት ሁኔታም ተስተውሏል (አዴሌ ኬኬ)፡፡

> ድሀ፣ እጅግ ድሀና ከድህነት ወለል በታች የሆኑ ቤተሰቦች፡- የኑሮ መተዳደሪያዎች፣ ድህነትና ድንገተኛ ችግር

ድሃ ቤተሰቦችን በጥቅሉ የሚገልፃቸው፡- አነስተኛ የመሬት ይዞታና አነስተኛ የከብት መጠን እንዲሁም ሌሎች የእሴት ውስንነት ናቸው፡፡ እነዚህ ውስንነቶች በግብርናው ዘርፍ ላይ ያላቸውን ተሳትፎ ይገድቡታል፡፡ ስለዚህም የመሬት አልያም ከብቶች አቅርቦት ለማግኘት ሲሉ የእኩል ማረስ ውል ውስጥ ይገባሉ፡፡ ውሉ ግን እነሱን ትርፋማ የሚያደርጋቸው አይደለም፡፡ ይህም ሲባል፣ በሌላ ሰው መሬት ላይ የእኩል ያርሳሉ ወይም የሀብታም ገበሬ እርሻ ወይም የባለሃብቱ ይዞታ ላይ በቀን ሰራተኝነት ይሰራሉ ማለት ነው፡፡ ይሄ ካልሆነ ስራ ፍለጋ ይሰደዳሉ (ማጣቀሻ፡- ፍልሰት)፡፡

የከብት እጦት፤ አብዛኛውን ጊዜ ድሃ የገበሬ ቤተሰቦች፤ መሬታቸውን የእኩል ለማሳረስ ወይም በሬ ለእርሻ ለመዋስ ለእነሱ በማይጠቅም ውል ውስጥ ይገባሉ፡፡ በዚህ ቤተሰብ ውስጥ ያሉ ሴቶች ብዙ ጊዜ ብዙ ትርፍ በማያስገኝ ንግድ፣ እንጨት ለቅሞ መሸጥ ወይም አረቄ ማውጣት ይሰማራሉ፡፡ አንዳንድ ህጻናት ለቤተሰባቸው ለመስራት፣ በእርሻ ለማገዝ፣ ብዙ ትርፍ በማያስገኝ ንግድ ለመጀመር ወይም ሥራ ለመቀጠር ወይም ለመሰደድ ትምህርታቸውን ያቋርጣሉ (ማጣቀሻ፡- ትምህርት)፡፡

እጅግ ድሀ፤ የሚባሉት ብዙውን ጊዜ ጭራሽ መሬት የሌላቸው ናቸው፡፡ ጥቂት ከብት ወይም ፈፅሞ ምንም ላይኖራቸው ይችላሉ፡፡ ስለዚህ ጉልበታቸውን ሸጠው ማደር አለባቸው፡፡ አንዳንዶች በሀብታሞች ቤት ውስጥ ተቀጥረው በጉልበት ያገለግላሉ፡፡

ከድህነት ወለል በታች፡- ያሉት ከጎረቤቶቻቸው፣ ዘመዶቻቸው፣ ማህበረሰቡና የሀይማኖት ተቋማት በሚቸሯቸው እርዳታ ተማምነው የሚኖሩ ናቸው፡፡ የኋላ ኋላ ድንማ ሲጓደል ለልመና መውጣታቸው ወይም በስደት ቀዬአቸውን ጥለው መሄዳቸው አይቀርም፡፡ እርሻን በተመለከተ በድህነትና በእድሜ /ፆታ እውነታዎች መካከል ጠንካራ ትስስር ይስተዋላል፡፡ ወጣቶች በጣም አሳሳቢ የሆነ የመሬት አልባነትና የሥራ አጥነት ወይም የማይመጥን ሥራ የመጋፈጥ ችግር ይገጥማቸዋል (ማጣቀሻ፡- ወጣቶች)፡፡

በድህነትና በችግር መቋቋም መካከል ግልፅ የሆነ ዝምድናም አለ፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ድህ ቤተሰብ የሚባለው ራሱ አንዳንዴ የሚፈጠረው ከእንዲህ ያለው የችግር መቋቋም አቅም እጦት ነው፡፡ በተለይ ሴት የቤተሰብ ኃላፊዎች ባል በሚሞትባቸው ወይም ትዳራቸው በፍቺ በሚፈርስባቸው ጊዜ አልያም በወጣት ባለትዳሮች ገና ከጅምሩ ሳይጠና አባወራ በጠና በሚታመም ወይንም ለአካል ጉዳተኝነት በሚጋለጥ ጊዜ ወይም የአልጋ ቁራኛ ከሆነ ችግሩን መቋቋም ሲያቅተው፣ ከዚህ ድንገተኛ ችግር ውስጥ ድህ ቤተሰብ ይፈጠራል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ፤ ቀደም ሲል የተደላደለ ኑሮ የነበረው ቤተሰብ፤ ድንገት ውድቀት ከገጠመው፣ ውድቀቱ ከፈጠረው ድንገተኛ ችግር ማንሰራራት ሲያቅተው፣ የድህነት አዘቅት ውስጥ ይገባል፡፡ ሦስተኛ፤ ድህ ቤተሰብ ችግር መቋቋም እጦት ተከትለው ለሚመጡ ሰበባ ሰበቦች የመጋለጥ ወይም የመጠቃት እድሉ ከፍተኛ ነው፡፡ ይህም የበለጠ ድህነት ውስጥ ይከተዋል፤ አንዳንዴም ከድህነት ወለል በታች ይሆናል፡፡

የምግብ ዋስትና በተረጋገጠባቸውና ባልተረጋገጠባቸው አካባቢዎች፣ በድሃ የኑሮ መተዳደሪያዎች መካከል አራት መሰረታዊ ልዩነቶች አሉ፡፡ አንደኛ፡- የምግብ ዋስትና ባልተረጋገጠባቸው አካባቢዎች ድህ ቤተሰቦች፤ በእጅጉ የሚተማመኑት በምግብ ዋስትና ድጋፍ ላይ ነው፤ አንዳንዶቹ ደግሞ ህይወትን ለማቆየት ይሰደዳሉ፡፡ ይሄ ብዙ ጊዜ በቀጥታ የኑሮ መተዳደርያ ዕድገትን ባያመጣም ያለ ብዙ የጥሪት መሟጠጥ የህልውና መቀጠልን ያረጋግጣል፡፡ ሁለተኛ፡- የምግብ ዋስትና በተረጋገጠባቸውና በተለይ የገበያ አዝርዕት አብቃይ በሆኑ አካባቢዎች፤ የሰብል ምርት ብዝሃነት በመኖሩ፤ የተሻለ ይዘት ያለው ምግብ ለማግኘትም ሆነ ዘርፈ ብዙ የምርት አማራጮችን ለገበያ ለማቅረብ ያስችላል፡፡ ሦስተኛ፡- በአንዳንድ የምግብ ዋስትና በተረጋገጠባቸው አካባቢዎች፤(ድሃ የማህበረሰብ ክፍሎችም ጭምር) ወደ ገበያ አዝርዕትና የወተት ተዋፅኦ አምራችነት የመለወጥ አዝማሚያ ተመዝግቧል፡፡ አራተኛ፡- በእነዚህ የምግብ ዋስትና በተረጋገጠባቸው አካባቢዎች፤ አብዛኛውን ጊዜ ከግብርና ውጭ በሆኑ ዘርፈ ብዙ ሥራዎችና ከባህር ማዶ ከሚላክ ገንዘብ በሚገኝ ገቢ ላይ ይበልጥ የመተማመን ሁኔታ ተስተውሏል፡፡ ከእነዚህ በመነሳት የምግብ ዋስትና በተረጋገጠባቸውና የገበያ አዝዕርት በሚያመርቱ አካባቢዎች የሚገኙ ድህ ቤተሰቦች፤ በህይወት የመቆየት ዕድል ብቻ ሳይሆን የኑሮ መተዳደሪያቸውን የማሳደግም ዘርፈ ብዙ አማራጮች እንዳሏቸው መደምደም እንችላለን፡፡

የድሃዎች ህልውና፡- ምግብ፣ ብድር፣ ትብብር እና ድጋፍ

ድህ ቤተሰቦች በአጠቃላይ እምብዛም በንጥረ ነገር ያልበለጸጉ ምግቦችን ነው የሚመገቡት፤በጣም አነስተኛ ስጋ፣ ወተትና እንቁላል፡፡ አንዳንዶች ዘይትና አታክልትን የመሳሰሉ የግዢ ምግቦችንም ቀንሰዋል፡፡ በጣም የባሰባቸው ድህ ከሚባሉት መሀል በተለይ ወቅትን ጠብቆ በሚመጣ የረሃብ ጊዜና ከአደጋ በኋላ በሚከሰት ድንገተኛ ችግር ውስጥ የሚመላለሱ ቤተሰቦች፤ ብዙ ጊዜ የሚመገቡትን ምግብና የአመጋገብ መጠን ይቀንሳሉ፡፡ አንዳንድ የድህ ቤተሰብ አባላት የሚመገቡትን የምግብ አይነት በሌላ ይለውጣሉ፤ ለምሳሌ ከጥራጥሬ እህሎች ወደ እንሰት (አዳዶ)፡፡ በድንገተኛ አደጋ ወቅት፤አንዳንድ ድህ ቤተሰቦች ከአነስተኛ ሽቃጮች የተገዛ ምግብንም እንኳን ይበላሉ (አዬሌ ኬኬ)፡፡

ድሃ ቤተሰቦች አብዛኛውን ጊዜ ከአነስተኛ የብድር ተቋማት ወይም ኢ-መደበኛ ከሆኑ ምንጮች፡- (ከዘመድ አዝማድ፣ጎረቤት ወይም ከአራጣ አበዳሪ) ገንዘብ ይበደራሉ፡፡ ከአነስተኛ የብድር ተቋማት የሚወስዱትን ብድር ብዙ ጊዜ ለከብት መግዣነት ያውሉታል፤ ከበድ ያለ ችግር ሲያጋጥማቸው ግን ለመድሃኒት መግዣ፣ ለልጆች ትምህርት ቤት ክፍያ ወይም ለስደት ወጪ መሸፈኛ ቅድሚያ በመስጠት ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡ አንዳንዱ ብድር ከምግብ ዋስትና ድጋፍ ጋር የተያያዘ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ድሃ ቤተሰቦች፣ ብድሩን እንደቸሮታ በመቁጠር ለመመለስ አሻፈረኝ ይላሉ፡፡ አንዳንዶቹ ድሃ ቤተሰቦች ለብድር አገልግሎት ብቁ የሚያደርገውን ፎርማሊቲ ሊያሟሉ ባለመቻላቸው ምክኒያት የብድር እድል ተጠቃሚ አይሆኑም፡፡ ስለዚህ ወደ አራጣ አበዳሪ ሄደው ከፍ ባለ የወለድ መጠን ለመበደር ይገደዳሉ፡፡ ድሃ ቤተሰቦች ብድራቸውን ሲከፍሉና የበለጠ ሲበደሩ የታዩባቸው ጥቂት አጋጣሚዎች አሉ፡፡ በሌላ በኩል ብድር ለመመለስ በጣም ሲቸገሩ ወይም ከዘመድ አዝማድ ተበድረው ከማህበር የተበደሩትን ገንዘብ ለመመለስ የተገደዱባቸው አጋጣሚዎችም ተከስተዋል(ገብለን)፡፡ ስለዚህ ድሃ ቤተሰቦች በብድር ምክኒያት የሚመጡ መዘዞችን በመፍራት፣ በአጠቃላይ ብድር ለመውሰድ ፍቃደኛ አይደሉም፡፡

ድሃ ቤተሰቦች አብዛኛውን ጊዜ ሰጥቶ የመቀበል የትብብር ውልን (ወንፈል) ይመርጣሉ፡፡ የትብብር ውሉን ከጎረቤት ወይም ከዘመዶቻቸው ጋር ሊገቡ ይችላሉ፡፡ አንዳንዶች ከሀብታም ገበሬዎች ጋር በቡድን ስራን የመወጣት ውል (ደቦ) ይዋዋላሉ፡፡ በቡድን ላከናወኑት ስራ በምላሹ የምግብ ፍጆታቸው ይሸፈንላቸዋል፡፡ የግብርና የቀን ስራ ለማከናወን ውል የሚገቡም አሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ከዘመዶቻቸው ወይም ከጎረቤቶቻቸው የማረሻ በሬ ይዋሱና፣ ያዋሷቸውን ሰዎች መሬት በማረስ ብድራቸውን ይከፍላሉ፡፡

ከሞላ ጎደል ሁሉም ድሃ ቤተሰቦች የእድር አባላት ናቸው፡፡ ግን አንዳንድ ጊዜ የቀብር ማስፈጸሚያ ወጪ፣ በዕድሮች ከሚከፈለው ገንዘብ የበለጠ ይሆናል፡፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች እድሮች ከብት ላጣ ቤተሰብ፣ የድንማ ክፍያ ያከናውናሉ፡፡ በጥቂት አካባቢዎች እድሮች ለአባላቶቻቸው የብድር አገልግሎትም ይሰጣሉ፡፡ የተወሰኑት ድሃ የገበሬ ቤተሰቦች፤ በውጭ ወይም ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚኖሩ ልጆቻቸው በሚላክላቸው ገንዘብ ወይ በሚያመጡላቸው ስጦታ ተማምነው የሚኖሩ ናቸው፡፡

ድሃ ቤተሰቦች የምግብ እጥረት አደጋ በተጋረጠባቸው ወቅት ይበልጥ የሚተማመኑት ዘመዶቻቸው ወይም ጎረቤቶቻቸው የሚለግሷቸውን እርዳታ ነው፡፡ አንዳንዶች፤ ከጎረቤቶቻቸው እህል ይበደሩና ከአጨዳ ወቅት በኋላ ይመልሳሉ ወይም ያበደራቸውን ሰው ከብት ይጠብቃሉ፡፡ በህመም ወቅት ከጎረቤትና ከዘመድ አዝማድ የሚገኝ እርዳታ ወሳኝ ሚና አለው፡፡ በጥቂት አካባቢዎች ቤተ ክርስቲያናትም ለድሃዎች እርዳታ ይለግሳሉ፡፡ የምግብ ዋስትና ባልተረጋገጠባቸው አካባቢዎች፣ የምግብ ዋስትና ድጋፍ፣ ዋናውን የምግብ እጥረት አደጋ መቋቋሚያ አቅም በማቅረብ ይታወቃል፡፡ ሆኖም አንዳንድ ጊዜ ሰዎች አበል በሌለው የማህበረሰብ ሥራ ላይ ለመሳተፍ እንደሚያቅማሙ ተጠቁሟል፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች፤ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ለድሃ የገበሬ ቤተሰቦች የገንዘብ ብድር ወይም ከብቶችና ለልጆቻቸው የመማሪያ ቁሳቁስ ማሟላትን የሚያካትት ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡ አንዳንድ ድሃ ቤተሰቦች፤ ከማህበረሰብ መዋጮዎችና ታክስ ነፃ ይደረጋሉ ወይም ንፁህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ያለክፍያ እንዲያገኙ ይፈቀድላቸዋል (ገልቻ)፡፡

የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት ለድሃዎች

አንዳንድ ድሃ ቤተሰቦች ከኤክስቴንሽን አገልግሎቶች ተጠቃሚ ሆነዋል፡፡ ምንም እንኳን እንደ ምርጥ ዘርና ማዳበሪያ የመሳሰሉ የግብርና መሰረታዊ ግብዓቶች ተሰጥተዋቸው ወደ ምርት የተሰማሩ ቢሆንም፤ ብዙ ድሀ ገበሬዎች የምርጥ ዘሩንና የማዳበሪያውን ዋጋ የመክፈል አቅም እንደሌላቸው በምሬት ተናግረዋል፡፡ ሌሎች ደግሞ ለምርጥ ዘሩ እንጂ ለማዳበሪያው የመክፈል አቅም የለንም ብለዋል፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች ማዳበሪያው የሚቀርበው በህብረት ሥራ ማህበራት በኩል ቢሆንም አንዳንዶች ከገበያ መግዛትን ይመርጣሉ፡፡ በጥቂት አካባቢዎች የማዳበሪያ አቅርቦቱ ከምግብ ዋስትና ድጋፍ ጋር የተያያዘ ሲሆን ገበሬዎች ማዳበሪያ እንዲወስዱ ይገደዳሉ፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች ጥቂት ድሃ የገበሬ ቤተሰቦች ከተዳቀለው ከብቶች ተጠቃሚ ቢሆኑም፣ ከብቶቹ ግን ድርቅና በሽታ የመቋቋም አቅም የሌላቸው መሆኑ ስጋት ፈጥሯል፡፡

በሴት እማወራ የሚተዳደሩ ቤተሰቦች

በሴት ኃላፊነት የሚተዳደሩ ቤተሰቦች የተለመዱ አይደሉም፡፡ በዚህ መደበኛ ባልሆነ ምድብ ስር የሚካተቱ የቤተሰብ አይነቶች ሁሉም እጅግ ድሃ አሊያም ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ከድሃ ቤተሰብ ጋር የሚያመሳስል የአቅም ማነስና የችግር አይነት በእነሱም ላይ አይስተዋልም ማለት አይደለም፡፡ በጥቅሉ በሴት የሚተዳደሩ ቤተሰቦች ላይ ከባድ ስራን የማከናወን የጉልበት እጥረት ይታያል፡፡ እነዚህ ሴቶች የደረሱ ወንድ ልጆች ከሌሏቸው ወይም ሴት ልጆቻቸው በጋብቻ ሌላ ወንድን ወደ ቤተሰቡ ስበው ማስጠጋት ካልቻሉ ይህ በወንድ ጉልበት የሚሸፈን ስራ ይስተጓጎላል፡፡ ሴት የቤተሰብ ኃላፊዎች፤ እርሻን በተመለከተ የስራ ክፍፍል ላይ በትብብር ማሳረስ፣ ጥማድ በሬ በውሰት ማምጣት ወይም የጉልበት ሰራተኛ ቀጥሮ ማሰራት ይችላሉ፤ ግን ይህንን ማድረግ የሚችሉት የገንዘብ አቅም ካላቸው ብቻ ነው፡፡

በሴት ኃላፊነት የሚተዳደር ቤተሰብ በትዳር መፍረስ ወይም በአባወራ ሞት የሚፈጠር ነው፡፡ የባል ሞት ወይም የጋብቻ መፍረስ ብዙውን ጊዜ የቤተሰብ የሀብት መሸርሸር ያስከትላል፡፡ ብዙ ባላቸውን ያጡ ሴቶች፤ የባለቤታቸው መታመምና የማታ ማታ መሞት፣ በህክምና ወጪ የቤተሰቡን ጥሪት እንደሚያሟጥጠውና ከሞተ በኋላ የቀብር ማስፈጸሚያ ወጪ፣ ቤተሰቡን የድህነት አዘቅት ውስጥ እንደሚከተው በምሬት ተናግረዋል፡፡

አንዳንድ ስኬታማ በሴት የሚተዳደሩ ቤተሰቦች፤ መሬት የወረሱ ወይም ከፍቺ በኋላ ያገኙ ሲሆን በግብርና ኤክስቴንሽን የተሰጣቸውን ምክርና ግብአቶች ተጠቅመዋል፤ የጉልበት ሰራተኞች መቅጠርና ብድር ማግኘትም ችለዋል፡፡ ሌሎች ደግሞ መጠጥ በመሸጥና ከብት በማድለብ ይተዳደራሉ፡፡ ጥቂቶች ደግሞ በከተማ ቤት ያላቸው ወይም ከባህር ማዶ የሚላክ ገንዘብ እየደጎማቸው የሚኖሩ ናቸው (ማጣቀሻ፡- ሴቶች እና ስኬት)፡፡

ድሀ የቤተሰብ ኃላፊ ሴቶች

ድሃ የቤተሰብ ኃላፊነት የተጣለባቸው ሴቶች ከመሬት፣ የጉልበት አቅምና ከጥማድ በሬ ጋር የተያያዙ ችግሮች ይገጥማቸዋል፡፡ ዘርፈ ብዙ ህልውናን የማቆያ ትልሞች አላቸው፡፡ አንዳንዶች መሬታቸውን በጋራ የሚያሳርሱ ሲሆን ሌሎች መሬት አልባዎች ደግሞ በጉልበታቸው ሰርተው ለመኖር ይጥራሉ፡፡

አንዳንዶች ከልጆቻቸው ወይም ከአማቻቸው ድጋፍን ለማግኘት ይሞክራሉ፡፡ ሌሎች ደግሞ ጥማድ በሬ ከዘመድ አዝማድ በመዋስ ወይም የጉልበት ሰራተኛ በመቅጠር የእርሻውን ግዴታ ይወጣሉ፡፡ ብዙዎቹ ዘርፈ ብዙ ኑሮን የማሸነፊያ ትልሞች ይጠቀማሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል ብዙ ትርፍ የማያስገኝ ንግድ፣ እንጨት ለቅሞ መሸጥ፣ ምግብ ማዘጋጀት ወይም የአልኮል መጠጦችን መጥመቅ፣ ጥጥ ፈትሎ ለገበያ ማቅረብ፣ ልብስ ማጠብ፣ ውሃ ማመላለስ፣ ሳር ማጨድ ወይም ኩበት ጠፍጥፎ ለገበያ ማሰናዳት ይገኙበታል፡፡ ጥቂቶች፤ ልጆቻቸው ከሳኡዲ አረቢያ ወይም ሱዳን በሚልኩላቸው ገንዘብ ይጠቀማሉ፡፡ የምግብ ዋስትና ባልተረጋገጠባቸው አካባቢዎች አብዛኞቹ፤ ከምግብ ዋስትና ድጋፍ ወይም የምግብ እርዳታ በሚገኝ ድንማ ላይ የሚተማመኑ ሲሆን፤ ይህም የምግብ እጥረት ለመቋቋም ወሳኝ ነው፡፡

ጥቂቶቹ ከግብርና ልማት ሠራተኞች (Development Agents) ምክር የሚያገኙ ሲሆን ማዳበሪያና ምርጥ ዘር የመሳሰሉ የግብርና ግብዓቶችን ይጠቀማሉ፡፡ ሆኖም ብዙዎቹ የኤክስቴንሽን ድጋፍ ያልተቀበሉ ሲሆን ግብዓቶችን የመግዣ አቅም የላቸውም፡፡ ጥቂቶች ብድር ያገኙ ሲሆን፤ ሌሎች ለብድር ብቁ ያልሆኑ ወይም ብድሩን ከከፈሉ በኋላ ግብአቶችን የመውሰድ ፍላጎት የሌላቸውም ነበሩ፡፡ አያሌዎቹ ሰብልን በበረዶ ወይም ከብትን በበሽታ የማጣት አደጋን ተከትሎ በሚከሰት አቅም እጦት ሳቢያ ወደ ድህነት አዘቅት የገቡ ናቸው፡፡ ጥቂቶቹ፤ እጅግ ድሃ መሆናቸው በግልጽ የሚታይ ሲሆን፤ በቂ ምግብም ሆነ መጠለያ የሌላቸውና ልጆቻቸውን ት/ቤት መላክ የተሣናቸው ናቸው፡፡

ብዙዎቹ ድሀ የቤተሰብ ኃላፊ ሴቶች፤ የምግባቸውን መጠንና ጥራት ቀንሰው የሚመገቡ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ዘወትር በርሀብ የሚሰቃዩ ናቸው፡፡ በጥቂት አካባቢዎች የሚኖሩበት ቤት እንኳን የራሳቸው ያልሆነ፣ የቤት ኪራይም የመክፈያ አቅም የሚያጥራቸው ድሃ ቤተሰቦች እንዳሉ ተስተውሏል፡፡ አንዳንዶቹ ሥራ ለማገዝ ትምህርታቸውን ያቋረጡ ልጆች ያላቸው ናቸው፡፡ ብዙዎች ችግራቸውን ለመቅረፍ የሚተማመኑት በእድሮች ሲሆን፤ አንዳንዶች የቤተሰብ እድርና የሴቶች እድርም ውስጥ አሉበት፡፡ ጥቂቶች ግን አባል ለመሆን የገንዘብ አቅም ያጥራቸዋል፡፡ አንዳንዶች መንግስታዊ ካልሆነ ድርጅት ብድርን ጨምሮ ድጋፍ ያገኛሉ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ህልውናቸው የተመሰረተው በቸሮታ ላይ ሲሆን ለምግብ ሆነ ለጉልበት ድጋፍ ተገን የሚያደርጉት ጎረቤቶቻቸውን ነው፡፡ ቤተሰብ የሚያስተዳድሩ በእድሜ የገፉ ሴቶች፤አንዳንድ ጊዜ የሴት የልጅ ልጆቻቸው እገዛ የሚያገኙ ሲሆን ውሃ በመቅዳትና ምግብ በማብሰል ይረዷቸዋል፡፡ በጥቂት አካባቢዎች፤ አንዳንድ እጅግ ድሃ የሆኑ ሴቶች ከምግብ ዋስትና ድጋፍ ሥራ (ገበለን) ወይም ከአስገዳጅ የማህበረሰብ መዋጮዎችና ታክስ ነጻ የሚደረጉ ሲሆን (አዴሌ ኬኬ፣ ግራር) አንዳንዶች ነጻ የውሃ አቅርቦት ይፈቀድላቸዋል (ገልቻ)፡፡

<u>በግለሰብ ደረጃ ያሉ ልዩነቶች</u>

በሁሉም አካባቢዎች ለወጣት ወንዶችና ወጣት ሴቶች ያሉ እድሎችም ሆኑ ማነቆዎች በእጅጉ ይለያያሉ፡፡ ለከተማ ቅርበትና የገበያ ትስስር ያላቸው አካባቢዎች የተሻሉ አማራጮች ያላቸው ናቸው (ማጣቀሻ፡- ወጣቶች)፡፡

ወጣት ወንዶች

ወጣት ወንዶች በሁሉም አካባቢዎች እየጎላ የመጣ የመሬት አቅርቦት ችግር ተጋርጦባቸዋል። የወጣት ስራ አጥነትና በቀደመው ትውልድ ላይ ጥገኛ የመሆን አዝማሚያ የተለመደ አሳሳቢ ጉዳይ ነው። ሻል ያለ ሀብት ካለው ቤተሰብ የወጡ ወጣቶች፣ ከወላጆቻቸው የሚታረስ መሬት ያገኛሉ። ደሀ ቤተሰቦች ግን አብዛኛውን ጊዜ ለልጆቻቸው የሚያካፍሉት መሬት አይኖራቸውም። አንዳንድ ወጣቶች በእኩል የማረስ ወይም የሰው መሬት የማረስ ውል ውስጥ ይገባሉ።

ቢሆንም አንዳንድ ወጣቶች ትምህርት በማግኘታቸው ምክንያት የማረስ ፍላጎትም ሆነ የእርሻ ክህሎት የሌላቸው ሲሆን ሥራም አላገኙም። የአስረኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተናን ማለፍ ያልቻሉ ወጣቶች ብዙውን ጊዜ ቤት ቀርተው ወላጆቻቸውን የማገዝ እጣ ፈንታ ይገጥማቸዋል። አንዳንዶች በዚህ ደስተኛ አይደሉም። መደበኛ የሆነ ቅጥር ለማግኘት ብዙውን ጊዜ ከቀዬ መሰደድ የግድ ቢሆንም፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ላጠናቀቁም እንኳን በቂ የሥራ ዕድል የለም። በእርግጥ ጥቂቶቹ የልማት ሠራተኛ መሆን ወይም የመምህርነት ሥራ ማግኘት ችለዋል። ብዙዎች በከብት ንግድ፣ በግብርና ምርት ወይም ብዙ ትርፍ በማያስገኝ ንግድ ውስጥ የሚሳተፉ ሲሆን ከድሃ ቤተሰብ ለወጡ ወጣቶች ግን በእነዚህ ዘርፎች መሰማራት የሚታሰብ አይደለም። የመነሻ ገንዘብና የብድር አቅርቦት ችግር ይገጥማቸዋል። ነገር ግን በግብርና ላይ ተሠማርቶ የመሥራት ዕድሎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፉ መጥተዋል። በቡና ለቀማ፣ በእቃ ጫኝና አውራጅነት፣ ምርትን በመጠበቅ፣ በከተሞች ደላላ በመሆን ወይም በፋብሪካዎችና በግንባታ ስራዎች ላይ የመሳተፍ አማራጮች ተፈጥረዋል። በአንዳንድ ሁኔታዎች የደሞዝ ሥራ አማራጮች እየተሻሻሉ በመምጣታቸው ወጣቱ እስካሁን መሰደድ አላስፈለገውም (ሃረሳው)። በትራንስፖርቱ ዘርፍም፣ በሞተር ብስክሌትና በጋሪ አልፎ አልፎ ሥራ አልጠፋም፤ እንዲሁም በሱቆችና ሌሎች ንግዶች (ለምሳሌ፡- የሳተላይት ቴሌቪዥን ኪራይ) ይስተዋላሉ። ከሃገር ውጪ የስደት የሥራ ዕድሎች አብዛኛውን ጊዜ የሚገኙት በአረብ ሀገራት ሲሆን እሱም በተለይ ለሴቶች እንጂ ለወንዶች እምብዛም አይገኝም (DB07: mobility)።

ወጣቶችን፤ በወጣቶች የህብረት ሥራ ማህበራት ለማደራጀት ሙከራ ተደርጓል። ነገር ግን አብዛኞቹ የግብርና የህብረት ሥራ ማህበራት በዘርፈ ብዙ ምክንያቶች የተነሳ ስኬታም ሊሆኑ አልቻሉም። በአመራር ድክመትና ቅንጅት መፍጠር አለመቻል፣ በብድር አቅርቦትና የፋይናንስ አስተዳደር ወይም በባለሀብቶችና ግለሰቦች መካከል ያለ ፉክክር ከሚጠቀሱት ችግሮች ዋናዎቹ ናቸው። ሆኖም አንዳንድ ወጣቶች በመስኖ ልማትና የተፈጥሮ ደን ጥበቃ ቡድኖች ውስጥ ተሳትፈው የተሻለ ውጤት አስመዝግበዋል። በአሸዋና ድንጋይ ምርት ላይ የተሰማሩ ወጣቶች ግን ከሁሉም በበለጠ ስኬታማ ሆነዋል (ማጣቀሻ፡- ወጣቶች)። በአንዳንድ አካባቢዎች፤ ወጣቶች መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ብደር አግኝተዋል ወይም የገቢ-መፍጠሪያ ሥራዎች ውስጥ እንዲሳተፉ ድጋፍ ተደርጎላቸዋል።

ወጣት ሴቶች

በአጠቃላይ ወጣት ሴቶች በቀጥታ መሬት የማግኘት ወይም የመሬት ባለቤት የመሆን እድል ማግኘት አልቻሉም። ምክንያቱም በባህላዊ የፆታ ሚና እና ወላጆች ለወጣት ወንዶች ማድላት ናቸው። ቢሆንም በፍቺ ወይም ባል ሲሞት የሴቶች የመሬት ወራሽነትና ባለመብትነት በመሬት-መብት ህግ መሰረት ተደንግጎላቸዋል። በተግባር ግን አሁንም ሴቶች የመሬት ወራሽ ሆነው ለመሥራት፣

በማህበረሰቡ ሽማግሌዎችም ሆነ አንዳንዴ በቀበሌ አመራር ዘንድ ፍጹም በሆነ ተቀባይነት አይስተናገዱም፡፡ ይሄም የመነጨው በባላቸው ባህላዊ አስተዳዳሪነት ሥር በመኖራቸውና ለማረስ የወንድ ጉልበትና ጥማድ በሬዎች ባለመኖራቸው ሲሆን በአጠቃላይ ሃላፊነት ተቀብለው ለመወጣት አቅም ያንሳቸዋል ከሚል ጥርጣሬ ነው፡፡ ቢሆንም አንዳንድ ሴቶች በፍቺ ወቅት የሚገባቸውን መሬት ተካፍለው በመውሰድ፣ የእኩል እርሻ ወይም ሰራተኛ ቀጥረው ማሳረስ ችለዋል(ማጣቀሻ፡- ወጣቶች እና ሴቶች)፡፡

ወጣት ሴቶች በራሳቸው ቤተሰብ ለመመስረት ባህሉ አይፈቅድላቸውም፤ ከጋብቻ ውጭ ያሉ እድሎች ደግሞ ውስን ይሆኑባቸዋል፡፡ በአብዛኛው እንቅስቃሴያቸው በቤት አካባቢ የተገደበ ነው፡፡ ት/ቤት የሚገቡ ልጃገረዶች ብዛት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣ ሲሆን አንዳንዶች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውንና ከዚያም በላይ ገፍተው ይቀጥላሉ (ማጣቀሻ፡- ትምህርት)፡፡ ነገር ግን መደበኛ ስራ የማግኘት ዕድል ከነጭራሹ የለም ሊባል ይችላል፡፡ ቢሆንም ጥቂቶች፤ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች፣ የልማት ሠራትኞች፣ የእንስሳት ሃኪሞች፣ መምህራን እንዲሁም በአንድ አካባቢ የአነስተኛ ብድር ተቋማት ወኪሎች ለመሆን ችለዋል፡፡ የማህበረሰቡም መልካም አርአያ ሆነዋል (ማጣቀሻ፡- ሴቶች)፡፡ በበርካታ አካባቢዎች፣ ወጣት ሴቶች፤ በአበባ እርሻዎች፣ በቡና መፈልፈያ ማዕከሎች፣ በፋብሪካዎች ወይም በጥናት ተቋማት ውስጥ በደመወዝ ተቀጥረው የመስራት እድል አግኝተዋል፡፡

ሆኖም አብዛኞቹ ወጣት ሴቶች፤ ገቢ-አመንጪ በሆኑ ሥራዎች ላይ ተሳትፈዋል፡፡ እነዚህ ሥራዎችም ተራ ሸቀጦችን፡- ስኳር፣ ጨውና ዘይት የመሳሰሉትን መነገድ፣ የከብት ተዋፅኦዎችን በተለይ ቅቤ፣ ወተትና እንቁላል መሸጥ፤ ከብት የማድለብ ተግባር ላይ መሳተፍ፤ የከብት ድርቆሽ መሸጥ፤ ምግብና የአልኮል መጠጥ ማዘጋጀትና መሸጥ፤ የገበያ አዝርዕት፡- (እንደ ቡና እና ጫት የመሳሰሉትን) መነገድ ወይም ሻይ ቤትና ምግብ ቤት መክፈት ወይም የተከፈተበት ውስጥ መስራትን ይጨምራሉ፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች ወጣት ሴቶች፤ የንግድ ሥራቸውን እንዳያስፋፉና በሌሎች ገቢ-አመንጪ እንቅስቃሴዎች ላይ እንዳይሳተፉ ማነቆ የሆነባቸው የብድር አቅርቦት አለመኖር መሆኑን ጠቁመዋል (ማጣቀሻ፡- ሴቶች)፡፡

በብዙ አካባቢዎች ለሚገኙ ወጣት ሴቶች፤ ወደ ከተማ ፈልሶ በአብዛኛው በአገልግሎት ዘርፍ ላይ መሥራትና ወደ አረብ አገራት ተሰድዶ፣ በቤት ሰራተኝነት መሰማራት ዋነኛ ህልማቸው ነው፡፡ ስኬታማ ስደተኞች የሚባሉት፤ በዋናነት ወደ ባህር ማዶ ተሻግረው፣ ገንዘብ ወደ ሀገር ቤት የላኩና ከዚያም የኑሮ መተዳደሪያ አማራጮቻቸውንና ደረጃቸውን ለማሻሻል የሚያውሉት ደህና ጥሪት ይዘው የተመለሱት ናቸው፡፡ ምንም እንኳን ስደት እንዳይበረታታ የሚያደርጉ ፖሊሲዎች ቢፀድቁም ወይም ስደት አደጋ እንዳለው ቢታወቅም ብዙዎች ባህር ማዶ ለመሰደድ ማለማቸውን ቀጥለዋል (ማጣቀሻ፡- ፍልሰት)፡፡

<u>ትውልድ እና የዕታ ግንኙነቶች</u>

በጊዜ ሂደትና በመሬት እጥረት፣ በመሬት ይዞታ ማነስ ምክንያት በቀድሞዎቹ ትውልድ አባላትና በወጣቱ መካከል ውጥረት ነግሷል፡፡ ወጣቶቹ ማግባት፣ የራሳቸውን ቤት መቀለስና የኑሮ መተዳደሪያቸውን በግል መመስረት ይሻሉ፡፡ በዚህም ምክንያት በነባሩና የቀድሞው ትውልድ የመሬት ባለቤቶችና መሬት አልባ በሆኑት የወጣቱ ትውልድ አባሎች መሀል እያደገ የመጣ ልዩነት

ይስተዋላል፡፡ ለግብርና የሚሆን መሬት እደላና የባለቤትነት ማረጋገጫ፣ ለተራዘመ ጊዜ በሊዝ መልክ መስጠት፣ የገበሬ ልሂቃንን ቀጣይ እጣ ፈንታ ወደማስተማመን የሚያመራ እርምጃ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ሂደት በሁሉም አካባቢዎች የተከናወነ ቢሆንም፤ በሃብት በደረጁና የበለጠ ትስስር በፈጠሩ አካባቢዎች፣ ልሂቃኑ ምርታቸውን እንዲያነለብቱና እንዲያሰፉ እንዲሁም ከዘርፈ ብዙ ምንጮች ገቢ እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታ አግኝተዋል ::

የመሬት ይዞታ ባለቤትነቱ በቀድሞው ትውልድ ቤተሰቦች ብቻ ሲከማች፣ ወጣቶች ለወላጆቻቸው በመስራታቸው አንዳንዴ ቅሬታና ተስፋ መቁረጥ ማንፀባረቃቸው አልቀረም፡፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ ይህ ቅሬታ ገንፍሎ በጎረቤታሞች መሀል ያለ ግንኙነትን ሲያሻክር፤ አሊያም በቀበሌ አመራሮች በኩል ሲንፀባረቅ ተስተውሏል፡፡

በፆታ ግንኙነቶች ረገድ አንዳንድ አዎንታዊ ለውጦች ተመዝግበዋል (ማጣቀሻ፡- ሴቶች)፡፡ በፍቺ ወቅት የሴቶች መሬት የመካፈል መብት ተሻሽሏል፤ በእርግጥ የንብረት ክፍፍሉ አንዳንዴ በፖለቲካ ግንኙነትና ለወንዱ በሚያደሉ ሽማግሌዎች ሚና ይወሰናል፡፡ በተጨማሪም መሬት በድጋሚ በሚከፋፈልበት ወቅት አብዛኛውን ጊዜ ሴቶች አይካተቱም፡፡ ለዚህ ቀበሌው የሚያቀርበው ምክኒያት፤ “ሴቶች መሬት ለማረስ አቅም የላቸውም” የሚል ነው፡፡(ኮርማርገፍያ) በሁሉም አካባቢዎች የፆታ ኢ-ፍትሃዊነት የቀነሰ ሲሆን በአብዛኛው ከለውጥ እርምጃዎች ጋር የተያያዘ ነው፡፡ እነዚህ እርምጃዎች፡- የሴቶች የመሬት መብት፣ የልጃገረዶች ትምህርት መስፋፋት፣ሴቶችና ህፃናትን ማዕከል ያደረገ የጤና አገልግሎት ማዕቀፎችና የለውጥ እንቅስቃሴዎች፣ የሴቶች ጥቃትንና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለመከላከል የተወሰዱ እርምጃዎችን ያካትታሉ፡፡ በእርግጥ እነዚህ እርምጃዎች በወንዶች በኩል ቅዋሜ አስነስተዋል፡፡

በወጣት ሴቶችና ወላጆቻቸው መካከልም ውጥረት ተፈጥሯል፡፡ በተለይ ጋብቻን በተመለከተ በሚወሰኑ ውሳኔዎች ዙርያ፣ በባል ምርጫና መቼ ጋብቻው ይፈጸም የሚሉት ጉዳዮች የቅራኔ መንስኤ ናቸው፡፡ መጪውን ዘመናቸውን ለማረጋገጥና ወላጆች፤ አብዛኛውን ጊዜ የሴት ልጆቻቸውን ጋብቻ ቀደም ብለው ማሰናዳት ይፈልጋሉ፤ በደቡብ አንዳንድ አካባቢዎች ከጥሎሽ የሚገኝ ጥቅምን ለማግኘት ሲሉ ለሴት ለጆቻቸው ትዳር ምርጫ ላይ ጣልቃ ይገባሉ፡፡ ወጣቶቹ ሴቶች በወላጆቻቸው የሚታቀደውን የለጋ እድሜ ጋብቻም አሻፈረኝ በማለት የራሳቸውን የትዳር ጓደኛ የመምረጥ ፍላጎት አላቸው፡፡ በብዙ አካባቢዎች፤ በትምህርት፣በሚዲያ ቅስቀሳና በቤተ ክርስቲያን ቡድኖች ሚና ወጣት ሴቶች፣ በምርጫቸው የፈለጉትን ማግባት እንደቻሉ ምልክቶች ታይተዋል (ማጣቀሻ፡- ወጣቶች)፡፡

በደሞዝ ተቀጥሮ የመስራትና ከባህር ማዶ ከሚላክ ገንዘብ ገቢ የማግኘት ዕድሎች፣ የወጣት ሴቶችን የመደራደር አቅም አሳድገውታል፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች፤ ቀደም ባሉ ጊዜያት “የወንዶች" የስራ ድርሻ ተብለው የሚወሰዱ ተግባራት፣ የቀንና የኮንትራት ሰራተኛ እንዲሁም ንግድን ጨምሮ በሴቶች መያዝ ጀምሯል፡፡ ነገር ግን፤ በኢኮኖሚው ለውጥ ምክንያት በፊት የሴቶች ድርሻ የነበሩ የስራ ዘርፎች ለምሳሌ የወተት ተዋፅኦን መሸጥ የመሳሰሉትን ወንዶች ተረክበዋል (ማጣቀሻ፡- ሴቶች)፡፡ በቤት ውስጥ አካባቢ የወንዶች ሚና ላይ መጠነኛ ለውጥ ተስተውሏል፤ አንዳንዶች ውሃ ይቀዳሉ፤የማገዶ እንጨት ይለቅማሉ ወይም ጽዳትና ምግብ ማሰናዳት ላይ ይሳተፋሉ፡፡

<u>ለችግር ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችና እና ድጋፍ</u>

የምግብ ዋስትና ያልተረጋገጠባቸው አካባቢዎች ከምግብ ዋስትና ድጋፍ በስተቀር፣ ለአብዛኞቹ ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ቡድኖች ውስጥ የሚፈረጁ ግለሰቦች፤ የሚደገፉት በአብዛኛው በጎረቤቶች በዘመድ አዝማዶችና በጓደኞች ነው፡፡ ሃዘን ሲደርስና በህመም ወቅት ዋናውን ድጋፍ የሚያደርጉት እድሮች ናቸው፡፡ ነገር ግን የሚሰጡት እርዳታ ብዙውን ጊዜ የተጎጂውን ወጪ የሚሸፍን አይደለም፡፡ ጉዳት የደረሰበትን ቤተሰብም ዳግም እንዲያንሰራራ አያደርግም፡፡

በሁሉም አካባቢዎች የአካል ጉዳተኝነትና በሽታ (ማየት የተሳናቸው፣ መስማት የተሳናቸው፣ የሚጥል በሽታ ያለባቸው ወዘተ) ያለባቸው ጥቂት ሰዎች አሉ፡፡ ኤችአይቪ/ኤድስ እና የአእምሮ ቀውስ በብዙ አካባቢዎች ያልተጠቆሙ ሲሆን፤ በአንዳንድ አካባቢዎች በግልፅ ወደ ውይይት አልቀረቡም፡፡ በጥቂት አካባቢዎች የአካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች በማህበረሰቡ መገለል ይደርስባቸዋል፡፡ ከተከሰተው መገለል ውስጥ ከኤድስ ቫይረስ በደማቸው የሚገኝ በሦስት አካባቢዎች የአካል ጉዳት ያለባቸው አባላት ቤት እንዳይከራዩ የመከልከሉ ሁኔታ ተጠቃሽ ምሳሌ ነው፡፡ የሀይማኖት ተቋማትም በጥቂት አካባቢዎች ድጋፍ ሰጥተዋል፡፡

ወላጆቻቸውን ያጡ ህጻናትንና አረጋዊያንን የተመለከቱ ችግሮች በተደጋጋሚ ውይይት ቢደረግባቸውም ተቋማዊ ድጋፍ ያለው ግን በአንዳንድ አካባቢዎች ብቻ ነው፤ እሱም ወላጆቻቸውን ላጡ ህጻናት ብቻ ነው፡፡ ወላጆቻቸውን ያጡ ልጃገረዶች በአሳዳጊዎቻቸው ግፊት በለጋነት እንደሚዳሩ የተጠቆመ ሲሆን፤ ጥቃት እንደደረሰባቸውም ተነግሯል(ሹምሽሃ፣ ዶአ'ማ)፡፡ የሚደረግላቸው እገዛ ከብዙ በጥቂቱ ፡- የመማሪያ ቁሳቁስ፣ ገቢ-አመንጪ ሥራዎች፣ ተቋማዊ ወይም ማህበረሰብ ተኮር ጉዲፈቻን ይጨምራል፡፡ በአንጻሩ አረጋዊያኑ ለእርዳታ በእጅጉ የሚተማመኑት የቅርብ ዘመዶቻቸውንና ጎረቤቶቻቸውን ነው፡፡ በእርግጥ በጥቂት አካባቢዎች መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ሀይማኖታዊ መሰረት ያላቸው ተቋማት፤ ለአረጋዊያኑ አልፎ አልፎ ድጋፍ ሲያደርጉ ተስተውሏል፡፡

በድህነት ምክንያት በሰው ቤት ውስጥ በደሞዝ ተቀጥረው ለመስራት የሚገደዱት ሌሎች የችግር ሰለባ ናቸው፡፡ በሁሉም አካባቢዎች የተሻለ ሀብት ያላቸው የገበሬ ቤተሰቦች በእርሻ ላይ እና በቤት ውስጥ እንዲሰሩላቸው የጉልበት ሠራተኞች ለተወሰነ ወቅት ወይም በቋሚነት ይቀጥራሉ፡፡ ወንዶቹ ተቀጣሪዎች በእርሻ ላይ፣ ሴቶቹ በቤት ውስጥ ሥራ ይሰማራሉ፡፡ ልጆችም ከደሀ ቤተሰብ የመጡ ከሆነ ይቀጠራሉ፡፡ ወንዶቹ ልጆች ከብት ያግዳሉ፣ ሴቶች ቤት ውስጥ ያገለግላሉ፡፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች ቀጣሪው እንደ በጎ አድራጊ አባት ይሆንና፣ ተቀጣሪው ራሱን የሚችልበትን መቋቋሚያ ይሰጠዋል፤ ይድረዋል፡፡ ቢሆንም ብዙውን ጊዜ ተቀጣሪ ሆነው የመቅረታቸው አዝማሚያ ያመዝናል ፡፡ ይህ በተዛባ እኩልነት ላይ የተመሰረተ የቀጣሪና ተቀጣሪ ግንኙነት አንዳንዴ በወላጆች ብቻ ሳይሆን በልጆቻቸውም ህይወት ተደግሞ ይቀጥላል፡፡ አንዳንድ ሴት የቤት ሰራተኞች ደግሞ የወሲባዊ ትንኮሳ ሰለባ ይሆናሉ፡፡

በብዙ አካባቢዎች፤ የእደ ጥበብ ሞያ ያላቸው (ሸክላ ሰሪዎች፣ ቆዳ ሰራተኞች፣ ቀጥቃጮች) በባህል በመጣ አስተሳሰብ ምክንያት በማህበረሰቡ ውስጥ የሚጠሉም የሚገለሉም ሲሆን መድልዎም

ይደርስባቸዋል።[3] ይህ ሁኔታ በደቡብ ኢትዮጵያ በተለይ ጎልቶ ቢስተዋልም የመቀነስ ነገር ግን አለ። በአንዳንድ አካባቢዎች እንደተስተዋለው የእጅ ሞያ ባለቤቶች ቁጥር እያነሰ ነው። በአንዳንድ አጋጣሚዎች እነዚህ ባለሞያዎች ወደ ማህበረሰቡ ተቋሞች እንዳይገቡ ይታገዳሉ፣ በተጨማሪ ጥቃትም እንደሚደርስባቸው ተጠቅሷል። በአንድ አጋጣሚ እኚህ የማህበረሰቡ አባሎች በሀይማኖታዊ ስነ ስርዓት ላይ እንዳይሳተፉ በመታገዳቸው ለመንግስት አቤቱታ ማቅረባቸው ይጠቀሳል (ሹምሸሃ)። ነገር ግን በአንዳንድ የደቡብ ክልል አካባቢዎች የፕሮቴስታንት የሀይማኖት ተቋም ይህንን ነባር ሁኔታ ለመቀልበስና የእጅ ሞያ ባለቤቶቹን የማህበረሰብ የተቀባይነት ደረጃ ለማሻሻል ሚና ተጫውቷል።

ከሌለ ቦታ ፈልሰው የመጡ ሰዎች፤ አብዛኛውን ጊዜ በተቀላቀሉት ማህበረሰብ ውስጥ የጥቅም ተቋዳሽ መሆን አይችሉም፣ ይገለላሉ። ግን በአንዳንድ ሁኔታዎች መጤ የሆኑ ክፍሎች፤ አዲስ የፈጠራ መንገዶችን አስተዋውቀው ብልጽግናን አምጥተዋል። (ማጣቀሻ፡- ለውጥ) በሌላ በኩል ግን ፈልሰው ወደ ማህበረሰቡ የመጡ ቡድኖች ብዝበዛና መገለልን ጨምሮ ለመድሎ ሲጋለጡ ይታያል። በቱሩፌ መንደር ከንባታዎች፤ የደርግ መንግስት ሲወድቅ ከመኖሪያቸው እንዲባረሩ ተደርገዋል። እዚያው መቅረት የቻሉ አብዛኞቹ ስደተኞች ግን መሬቱን እንዲይዙ ፈቃድና ምዝገባ ተደርጎላቸዋል። ነገር ግን በቅርብ ፈልሰው የመጡት በቆዩት የሚጨቆኑ ታችኛው መደብ የመሆን እጣ ደርሷቸዋል። በቆሮደጋጋ በስደት የመጡ ሰራተኞች በጉስቁልና ላይ ይገኛሉ። አገልግሎት ላይ እንዳይሳተፉ ከመታገድ ባሻገር በቦታው ላይ ለሚቀሰቀሱ ግጭቶች መንስኤ ተደርገውም የመቆጣጠር እጣ ፈንታ ደርሷቸዋል። በገልቻ በስደት የመጡት የምግብ ዋስትን እገዛ እርዳታ እንዲያገኙ ፈቃድ አልተሰጣቸውም።

[3] *በኢትዮጵያ የተገለሉ የማህበረሰብ ክፍሎች ይመልከቱ፡- The Excluded Minorities of Ethiopia,* Dena Freeman and Alula Pankhurst eds (2003), London: Hurst.

የወጣትነት ሽግግሮች

ከወጣትነት ወደ አዋቂነት በገጠር ማህበረሰቦች ያሉ ሽግግሮች (2010-13)

WIDE የውይይት መነሻ አጭር መግለጫ ቁ. 3/...10[1]

<u>ዋና ዋና ነጥቦች - ከWIDE የጥናት መረጃዎች</u>

- የታዳጊ ወጣቶች ወደ ጉልምስና ሽግግር፣ ፋይዳ ባለው የፅንሰ ሐሳብ ግንዛቤ፣ ፆታን ባገናዘቡ 15 ሽግግሮች ሊፈረጅ ይችላል። ፈርጆቹም፤ 6 ግላዊ ሽግግሮች (ማለትም፣ ጉርምስና፣ ግርዛት፣ የወሲብ ጅማሮ፣ የስራ ክህሎት፣ ትምህርት፣ ማንነት)፤ 3 የስራ ሽግግሮች (ማለትም፣ የቤት ውስጥ ስራ፣ ገቢ ማስገኛ ስራ፣ የኢኮኖሚ ራስ-ገዝነት)፤ 3 የቤተሰብ ሽግግሮች፡ (ማለትም፣ ጋብቻ፣ ቤተሰብ ምስረታ፣ ልጅ መውለድ)፤ 3 ማህበረሰባዊ ሽግግሮች፡ (ማለትም፣ ማህበራዊ ትስስር፣ ማህበረሰብ በቀል ድርጅቶች፣ ዜግነት) ናቸው።
- የልጃገረዶች ወደ ጉልምስና ሽግግር፣ ከወንድ ልጆች ሽግግር ቀድሞ የመከሰት አዝማሚያ አለው። ይሁን እንጂ፣ ግርዛትና ያለእድሜ ጋብቻን የመሰሉ አንዳንድ ሽግግሮች የሚፈፀሙበት ጊዜና አኳሃን ላይ፣ የየባህሉ ዘዬና ዝንባሌ፣ ጉልህ ተፅእኖ አለው።
- ወጣቶች ሲባል፣ ወጣት ወንዶች እንደማለት ተደርጎ ስለሚታሰብ፣ ያለእድሜ ጋብቻን በሚመለከት ካልሆነ በቀር፣ ለወጣት ሴቶች የሚሰጣቸው ትኩረት አነስተኛ ነው።
  - ለወጣት ሴቶች የምርታማነት ሚና እና ለወጣት ወንዶች የተዋልዶ ሚና፣ እንዲሁም ጥንዶች ራሳቸውን ችለው ለሚመሰርቱት ራስገዝ ኑሮ ተጨማሪ ትኩረት መስጠት ጠቃሚ ይሆናል።
  - የወጣቶችን ሽግግር ለማሻሻል ያለሙ የለውጥ እንቅስቃሴዎች፣ ለወጣቶች የምርታማነት እና የተዋልዶ ጉዳዮች፣ እንዲሁም ለባህል ነክ እሴቶች ምላሽ መስጠት ይጠበቅባቸዋል።
- የልጃገረዶችን ሽግግር የሚመለከቱ የለውጥ እንቅስቃሴዎች፣ በህፃናት ጋብቻ ላይ እና የሴት ልጅ ግርዛትን በማስቆም ላይ ያተኩራሉ።

---

[1] ይህ አጭር የጥናት መግለጫ፤ በWIDE የውይይት መነሻ አጭር የጥናት መግለጫዎች ሁለተኛ ጥራዝ (ስብስብ) ውስጥ ከተካተቱት አስር መግለጫዎች አንዱ ነው፡፡ መግለጫው፤ በናታን ንጉሴ እገዛ በአሉላ ፓንክረስት የተዘጋጀ ሲሆን በደሳለኝ ራህማቶ ተገምግሟል፡፡ አዘጋጁ፤ መግለጫዎቹ ይሰናዱ ዘንድ በገንዘብ ለደገፉት ለእንግሊዝ ዓለም አቀፍ የልማት ተቋም ፣ ለአይሪሽ ኤይድና ለስዊድን ዓለምአቀፍ የልማት ኤጀንሲ ልባዊ ምስጋናውን ያቀርባል፡፡ በተጨማሪም የጥናት ሪፖርቱን በማርቀቅ ሂደት የተሳተፉና አጭር የጥናት መግለጫው የትኩረት አቅጣጫ እንዲሰላ እገዛ ያደረጉ ሌሎች የጥናት ቡድን አባላትና ባለሙያ ገምጋሚዎች፣ለሥራው ለሰጡት ጊዜና ድጋፍ ያመሰግናል፡፡
ሌሎች ምስጋናና ዕውቅና የሚያሻቸውም አሉ፡- (1) ለዓመታት የጥናት መግለጫው የተዘጋጀበትን መረጃዎች ያሰባሰቡና ያደራጁ የጥናት መኮንኖችና ተቆጣጣሪዎች ሙሉ ጊዜያቸውን ሰጥተው ላበረከቱት አስተዋጽኦ፤ (2) በሶስት ዙሮች ለተካሄደው የWIDE ጥናት የገንዘብ ዕገዛ ላደረጉ የተለያዩ ድጋፍ ሰጪ ተቋማት፤ እና (3) በኢልምተ ሰብሳቢነትና በኢኮኖሚ ፖሊሲ ትንተና ክፍሉ በWIDE አጭር የጥናት መግለጫዎች ሁለተኛ ጥራዝ ላይ ለመወያየት መጋቢት 28 ቀን 2016 ዓ.ም በተዘጋጀው መድረክ ላይ የተሳተፉ ከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣናት፣ ላሳዩት ፍላጎትና ለከፈሉት የጊዜ መስዋዕትነት--- ምስጋና ይገባቸዋል፡፡ የጥናት መግለጫው፤ በከፍተኛ ደረጃ በተዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ፣ ከመንግስት ባለሥልጣናት ጋር በተደረገው ውይይት የተሰጡ አስተያየቶችን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ከለሳና ማሻሻያ ተደርጎበታል፡፡ አጭር የጥናት መግለጫው፤ የኢትዮጵያ የልማት ምርምር ተቋምን (ኢልምተ) ወይም የኢትዮጵያ መንግስትን አሊያም የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርጉለትን የልማት አጋሮች አመለካከትም ሆነ አቋም አይወክልም፤ ይልቁንም የፖሊስ ውይይት ለማነቃቃት የታለመ ነው፡፡ ሌሎች የጥራዝ ሁለት የውይይት መነሻ አጭር መግለጫዎችንና የጥናትና ምርምር ውጤቶችን በhttp://ethiopiawide.net/ ድረ-ገጽ ላይ ማግኘት ይቻላል፡፡

- የለውጥ እንቅስቃሴዎች፣ ብዙውን ጊዜ፣ ነባራዊ ሁኔታን ከነሰበቡ በመገንዘብ የለውጥ አስፈላጊነትን አስረድቶ ከማሳመን ይልቅ፣ እንዲሁም የጫና ለውጥ የሚያመጣቸውን መዘዞች በማስቀረት ፋንታ፣ ክልከላን እያስቀደሙ ገደብ መጫንን ያዘወትራሉ።
- በአንዳንድ ማህበረሰቦች ውስጥ፣ ከወላጆችና ከታዳጊዎች በኩል፣ እምቢታዎች ታይተዋል። በአብዛኞቹ ማህበረሰቦች ውስጥ፣ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን፣ ያለእድሜ ጋብቻ አሁንም እንደቀጠለ ነው። በአንዳንድ ማህበረሰቦች፣ የሴት ልጅ ግርዛት አሁንም በስውር እየተፈፀመና በዚህም ሳቢያ ተጨማሪ አደጋዎችን እያስከተለነው።
  - የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስወገድ ያለሙ የለውጥ እንቅስቃሴዎች፣ የባለድርሻ አካላትን ተሳትፎ ማስተባበር፤ እንዲሁም ከማህበረሰብና ከባህላዊ መሪዎች፣ ከወላጆች፣ ከትምህርት ቤቶች፣ ከጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች፣ በተለይም ከልጃገረዶችና ከወንድ ልጆች ጋር አካሄዱን ማቀናጀት ይኖርበታል።
  - የሕፃናት ጋብቻን ለማስቆም የታሰቡ የለውጥ እርምጃዎች፣ የግዴታ ጋብቻን በሚያስወግድ የፈቃደኝነት ጋብቻ ላይ ማተኮር አለባቸው። የልደት ምዝገባን ማስፋፋትም፣ የልጃገረዶች እድሜ ላይ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን ሊፈታ ይችላል።
  - አደግ ያሉ ወጣት ልጃገረዶች፣ የወሊድ መቆጣጠሪያ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዳይሆኑ የሚገጥማቸው ችግር፣ ላልተፈለገ እርግዝናና ብዙውን ጊዜም ለአደገኛ ውርጃ የሚገፋፋ ችግር እንደመሆኑ፣ ጉዳዩ እንደገና መታየትና መሻሻል ይገባዋል። የወለዱትን ሕፃን የማሳደግ አቅም ለሌላቸው፣ ለአካለ መጠን አለመድረሳቸውን ያገናዘበ ልዩ ድጋፍ እንዲያገኙ የሚያደርግ፣ እንዲሁም የልጅ ማሳደጊያ ድጎማን የሚያበረታታ ማሻሻያ ያስፈልጋል።
  - ከ16-18 ዓመት የሆናቸው ወጣቶች የሚጋቡበት ሁኔታ በተመለከተ፣ ፣ በብዙ አገራት ህጋዊ እንደመሆኑና፣ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ በፍትህ ሚኒስቴር ፈቃድ እድል እንደመከፈቱ፣ በሚመለከታቸው አካላት ቁጥጥርና ክትትል ስር፣ በልዩ ሁኔታ የጋብቻ ፈቃድ የሚያገኙበት አኳሃን ወደፊት መፍጠር ይቻላል።
  - ጠለፋን አስመልክቶ በተደነገጉ ሕጎች ተግባራዊ ሲደረጉ፣ 'ከፈቃደኝነት ጠለፋ' እና በመፈቃቀድ ከሚከወን ጋብቻ ተለይቶ መታወቅ አለበት። ወጣት ጥንዶች፣ በወላጆች ከሚጫንባቸው ጋብቻ ለማምለጥ እና የጥሎሽ ወጪዎችን ለማስቀረት፣ እንዲሁም በራሳቸው ምርጫ ለመመራት ሲሉ፣ የመፈቃቀድ ጋብቻን ወይም 'የፈቃደኝነት ጠለፋን' ይጠቀማሉ።
- የስነወሲብ ትምህርትን የማስጀመር፣ የልጃገረዶች መፀዳጃ ቤቶችን የማዘጋጀት፣ እንዲሁም በአንዳንድ አካባቢዎችም የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁስንም ጭምር የማቅረብ ውጥኖች ታይተዋል። ይሁን እንጂ፤ ወጣት ልጃገረዶችንና ወንድ ልጆችን በሰፊው በሚመለከቱ መሰረታዊ የተዋልዶ ጤና ጉዳዮች ዙሪያ የነበረው ትኩረት አነስተኛ ነው።
  - የወጣት ልጃገረዶች የምግብ ፍላጎት፣ የብቻ መፀዳጃ ቤት ፣ የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁስ ብሎም በወላጆችና በትምህርት ቤቶች በኩል የሚቀርብ የስነወሲብ ትምህርት ከዚህ ቀደም

የተደረጉና ውጤት ያስመዘገቡ ሙከራዎችን መመርኮዝ ይገባዋል፤ ወደፊት ቀዳሚ ትኩረት እንዲያገኙም ማድረግ ያስፈልጋል።

- የታዳጊ ወጣቶች የስነወሲብ ጤና ፡ - የወሊድ መቆጣጠሪያ ተጠቃሚነትን የሚያጎላ፣ ቅድመ-ጋብቻ እርግዝና የሚገጥማቸውንና ልጅ የሚያሳድጉትን የሚደግፍ፣ የአደገኛ ውርጃ ችግሮችን የሚቀርፍ፣ ልጅ የማሳደግ ፈተናዎችን የሚያቃልል፣ እንዲሁም ወጣት ወንዶችን፣ ወላጆችንና ወጣት ሴቶችን የሚያሳትፍ መሆን አለበት።

- ወጣት ልጃገረዶች ላይ የሚጋረጡ ዋና ዋና ጉዳዮች ፡ - በብልት ትልተላ/በግርዛት እና በሕፃናት ጋብቻና በተዋልዶ ጤና ላይ ብቻ ታጥረው የሚቀሩ አይደሉም። ይህንን አልፈው የሚሻገሩና፣ ይልቁንም ከትምህርትና ከስልጠና፣ ከስራ እድልና ከስራ ፈጠራ ቢዝነስ፣ እንዲሁም ከፍልሰትና ከስደት ጋር ይያያዛሉ።

- የልጃገረዶች ትምህርት እንዲስፋፋ፣ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ላይ ማበረታቻ አግኝቷል። ይሁን እንጂ፣ አደግ ላሉ ወጣት ልጃገረዶች፣ የስልጠናና የክህሎት ማጠናከሪያ አማራጮችን ለማስፋፋት የተሰጠው ትኩረት ውስን ነው።

  - በስልጠናና በስራ እድል አማካኝነት ያለእድሜ ጋብቻን የሚያስቀሩ አማራጮች እንዲስፋፉ ማድረግ ይገባል።

  - በወጣት ሴቶች የምርታማነት ሚና ዙሪያ፣ አማራጮችን የማስፋፋት ጉዳይ፣ ተጨማሪ ትኩረት ማግኘት አለበት። ትኩረት ከሚያሻቸው መካከልም፣ በብድር አቅርቦት በኩል ተጠቃሚነታቸውን ማስፋፋት፣ በወጣትና በሴት የሕብረት ስራ ማህበራት ውስጥ ተሳትፏቸውን ማሳደግ፣ እንዲሁም የቢዝነስና የስራ ፈጠራ እንቅስቃሴያቸውን ማበረታታት፣ ይጠቀሳሉ።

- የወጣቶች የስራ ዓለም ሽግግር፣ በመሬት ጥበት እና በስራ እጥረት/እጦት ሳቢያ ችግር ይገጥመዋል። ይሁን እንጂ፣ ወጣቶች በዘርፈ ብዙ የገቢ ምንጭ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ይሣተፋሉ።

- በእርሻ-ዘለል መስክ የተሰማሩ የወጣት ሕብረት ስራ ማህበራት፣ በእርሻ ዘርፍ ከተሰማሩት ማህበራት የተሻለ ስኬት አሳይተዋል። ብዙ የወጣት ሕብረት ስራ ማህበራት፣ የብድር፣ የስልጠና፣ የአመራር፣ የአስተዳደር፣ እና የውድድር ተግዳሮቶች ገጥመዋቸዋል።

- የወጣቶች ማህበረሰባዊ ሽግግሮች፣ የተፈጥሮ ሐብት በቀድሞ ትውልድ የተያዘ በመሆኑ እንዲሁም በስራ እድልና በገቢ ምንጭ እጥረት ሳቢያ የሚገቱበት ሁኔታ ይስተዋላል።

- ወጣቶች በአንዳንዶቹ አካባቢዎች፣ ይበልጥ በሐይማኖት ውስጥ እየገቡ፣ ከማህበራዊ ጉዳዮች ራሳቸውን አግልለዋል።

- የወጣት ማህበራትና ድርጅቶች፣ የኢኮኖሚ እድልን ከማስፋፋት ይልቅ በፖለቲካ ቅስቀሳ ላይ ያተኮሩ ብዙም የረባ ሚና የሌላቸው ተቋማት ናቸው የሚል አመለካከት በሰፊው ይታያል።

- ነባር ወግና ልማድን የማበረታታት እጦት ወጣት ሴቶች በወጣቶች ማህበርም ይሁን በማህበረሰባዊ ጉዳይ እንዳይሳተፉ ትልቅ ተፅኖ ያሣድራሉ።

- ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት፣ ወደ ገጠር አካባቢዎች፣ በአነስተኛ ከተሞችና የቀበሌ ማእከላት አማካኝነት መስፋፋት አለባቸው። በግለሰብና በቡድን የሚከናወኑ የስራ ፈጠራ ጥረቶችም ሊበረታቱ ይገባል።
- በገጠር አካባቢዎች በእርሻ-ዘለል የህብረት ስራ ማህበራት ዘንድ የታየው ሻል ያለ ስኬት፣ በሌሎችም ዘንድ መደገምና መበራከት አለበት።
- በኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የወጣቶችን የተደራጀ ተሳትፎ ማበረታታት እንዲሁም የሴቶችን ተሳትፎ በመደገፍ ማስፋፋት፣ በማህበረሰብ ጉዳዮች ውስጥ የወጣቶችን ሚና ሊያሻሽል ይችላል።

መግቢያ

ይህ የጥናት መግለጫ፣ በ2010-13 በሃያ የገጠር ማህበረሰቦች ውስጥ የተከሰቱ የወጣት ሽግግሮችን ለማሳየት፣ የኢትዮጵያ WIDE ጥናትን እንደ ዳራ ይጠቀማል። ግላዊ፣ የቤተሰብ፣ የስራ እና ማህበረሰባዊ በሚሉ 4 ዘርፍ ከተመደቡት 15 ሽግግሮች መካከል፣ የጥናት መግለጫው በተለይ የለውጥ እንቅስቃሴ የተካሄደባቸው ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር ሲሆን፤ በዚህ መድበል ተጣማሪ በሆኑ ሌሎች የጥናት መግለጫዎች ላልተዳሰሱ ጉዳዮች ሰፋ ያለ ቦታ ይሰጣል።

የወጣቶችን ሽግግር መገንዘብ

ወጣቶች ማለት፣ በአመዛኙ ወጣት ወንዶች እንደማለት ተደርጎ ስለሚታሰብ፣ ለወጣት ሴቶች የሚሰጣቸው ትኩረት አነስተኛ ነው። ለወጣቶች የሚካሄዱ የለውጥ እንቅስቃሴዎች፣ ለወጣት ሴቶች ሲሆን በተዋልዶ ጉዳይ ላይ ሲያጠነጥን፣ ለወጣት ወንዶች ደግሞ በምርታማነት ጉዳይ ላይ ያተኩራል። ብዙውን ጊዜም፤ የወጣት ሴቶችን የምርታማነት ሚናና የወጣት ወንዶችን የተዋልዶ ሚና ይዘነጋሉ። ከዚህም በተጨማሪ፣ የወጣቶች ሽግግር፣ ወጣት ወንዶች እና ወጣት ሴቶችን ለየብቻ እየነጣጠለ የሚያይ ሆኗል። ብዙውን ጊዜም፣ ጥንዶች ተጣምረው የሚመሰርቱትን የአብሮነት ኑሮ እና የሚፈጥሩትን አዲስ ቤተሰብ ጭምር ባቀፈ መንገድ፣ ከዖታ አንፃር አይተነተንም።

- ለወጣት ሴቶች የምርታማነት ሚናና ለወጣት ወንዶች የተዋልዶ ሚና፣ እንዲሁም ጥንዶች ራሳቸውን ችለው ለሚመሰርቱት የራሳቸው ኑሮ ተጨማሪ ትኩረት መስጠት ጠቃሚ ይሆናል።

የወጣቶች የጉልምስና ሽግግርን፣ የዖታና የእድሜ ገፅታ ባላቸው፣ ግላዊ፣ ማኅበራዊ እና ማህበረሰባዊ ፈርጆች ከፋፍሎና መልክ ሰጥቶ መገንዘብ ይቻላል። በለውጥ እንቅስቃሴዎችና በወጣቶች ሽግግር መካከል ጥልፍልፍ መስተጋብሮች አሉ፤ አንዳንዶቹ ርቱዕ/ቀጥተኛ፣ አንዳንዶቹ ኢ-ርቱዕ/ተዘዋዋሪ ወይ ደግሞ አባሪ ናቸው። የለውጥ እንቅስቃሴ፣ ከፈፃሚው አካል፣ ከስፍራው እና ካቀፋቸው ተግባራት አንፃር ሊተነተን ይችላል።

የጉልምስና መዳረሻዎች፣ አስራ አምስት ግላዊና ማህበራዊ ሽግግሮችን ወይም በዓይነትና በቆይታ የተዛነቁ የድንበር ኬላዎችን ያቀፉ ናቸው። ስድስት ግላዊ ሽግግሮች አሉ፡ 1) አካለ መጠን መድረስና ጉርምስና፤ 2) የወጣቶች ግርዛት (በአንዳንድ ባህሎች ያለ፣ በሌሎች ግን የሌለ)፤ 3) የወሲብ ጅማሮ፤

4) የስራ ክህሎት መያዝ፤ 5) መደበኛ ትምህርት ማጠናቀቅ፤ እና 6) ግላዊ/ማህበራዊ ማንነት መገንባት። ሦስት ሥራ-ነክ ሽግግሮች አሉ፡- ነ) የቤት ስራ ሙያዎችን መጨበጥ፤ 2) የ'ገቢ' ምንጭ ስራ ትልሞች፤ 3) በኢኮኖሚ ራስን መቻል። ሁለት ዓይነት መልክ ካላቸው ማህበራዊ ሽግግሮች መካከል፣ ሦስት ቤተሰብ-ነክ ሽግግሮች አሉ፡ ነ) ጋብቻ መፈፀም፤ 2) ራስን ችሎ የቤተሰብ ኑሮ መመስረት፤ እና 3) ልጆችን መውለድ ናችወ፡፡ ሦስቱ ማህበረሰባዊ ሽግግሮች ደግሞ፡- ነ) በማህበራዊ ትስስር ልውውጦች ውስጥ፤ 2) በማህበረሰብ-በቀል ተቋማት ውስጥ፤ እና 3) የየአካባቢው ሃይማኖታዊና የፖለቲካ 'የዜግነት' ጉዳዮች ውስጥ መሳተፍን ይመለከታሉ። እያንዳንዱ ሽግግር፣ በዕታና በእድሜ የሚለያዩ፣ የየራሱ የድንበር ኬላዎችንና መዳረሻ አምባዎችን የያዘ ነው። አብዛኞቹ ከወጣትነት ወደ ጉልምስና የሚደረጉ ሽግግሮች፣ ከወንዶች በፊት በሴቶች ቀድመው መከሰታቸው፣ በባህል የተለመደ ነው።

በሽግግሮች ላይ ድርሻ ያላቸው ለውጦች፣ በገጠር ማህበረሰቦች ውስጥ ከማዘመን ሂደት ጋር አብረው ከተከሰቱት ሰፋፊ የእመርታ ለውጦች ጋር የተዛመዱ ናቸው። ከእነዚህም መካከል፣ በጉልህ በሚታይ የመንግስት የኢንቨስትመንት እድገት አማካኝነት፣ የተወሰነ የእርዳታ ገንዘብም ታክሎበት፣ በመሰረተልማት፣ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ ልማት፣ በማህበራዊ ዋስትና፣ በዕታ እኩልነት እና በከባቢያዊ የአስተዳደር መዋቅር መስኮች የተከሰቱ ለውጦች ይጠቀሳሉ። ለልማት ከተካሄዱ የለውጥ እንቅስቃሴዎች እርምጃዎች መካከል ከፊሎቹ፣ አንዳች የሽግግር ዓይነት ላይ አነጣጥረው ለውጥ ለማምጣት የተቀረፁ ናቸው፤ ለምሳሌ፣ የጋብቻ እድሜ ወለል ወደ 18 ዓመት ከፍ የተደረገበት ውሳኔን እና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ለሁሉም የማዳረስ ዘመቻን መጥቀስ ይቻላል። ከወጣቶች ጋር በቀጥታ ያልተዛመዱ አላማዎችን ለማሳካት የተቀረፁ፣ ለአብነትም የመሬት ይዞታን የማጠናከር እና የወሊድ መቆጣጠሪያ አገልግሎት አቅርቦትን የማጠናከር እንቅስቃሴዎች፣ በወጣቶች የሽግግር ጉዞ ላይ ያልተጠበቀ ውጤትና ተፅእኖ አምጥተዋል። የለውጥ እንቅስቃሴዎች፣ በየአካባቢው ከተንሰራፉ ባህላዊ ወጎችና እሴቶች ጋር በየጊዜው ግጭት ውስጥ ስለሚገቡ፣ ሚዛን የጠበቀ የለውጥ ብልሃት ያስፈልጋል (ማጣቀሻ፡- እናቶችና ጨቅላ ህጻናት)፡፡

- የወጣቶችን ሽግግር ለማሻሻል ያለሙ የለውጥ እንቅስቃሴዎች፣ ለወጣቶች የምርታማነት እና የተዋልዶ ጉዳዮች፣ እንዲሁም ለባህል ነክ እሴቶች የመፍትሄ ምላሽ መስጠት ይጠበቅባቸዋል።

በወጣቶች ሽግግር እና በለውጥ እንቅስቃሴ መካከል ያሉ ግንኙነት፣ "ከላይ ታች" እና "ከታች ላይ" ከተሰኙት አካሄዶች አንፃር ሊታይ ይችላል። በመጀመሪያው አካሄድ እይታ፣ ትምህርት፣ ጤና፣ ግብርና፣ የምግብ ዋስትናና ድህነት ቅነሳን የመሳሰሉ በጥቅል የተፈረጁ የየዘርፉ የለውጥ እንቅስቃሴዎች፣ ከዋና ዋናዎቹ የሽግግር ፈርጆች ጋር የሚዛመዱበትን አቅጣጫ ከተመለከተ በኋላ፤ እያንዳንዱን ሽግግር እያጤነ፣ ከምን ዓይነት የለውጥ እንቅስቃሴ ጋር ግንኙነት እንደሚኖራቸው ይፈትሻል። የለውጥ እንቅስቃሴዎች፣ በግል፣ በስራ እና በቤተሰብ የሽግግር መስኮች ዘንድ በርከት የማለታቸውን ያህል፣ ለማህበረሰብ የሽግግር መስኮች የሚሰጡት ትኩረት አነስተኛ ነው። ትልልቆቹ የለውጥ እንቅስቃሴ ትኩረቶች፣ ትምህርትን በማጠናቀቅ ላይ እንዲሁም ሴቶችን በተመለከተ፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በተለይም የሴት ልጅ ግርዛትንና የብልት ትልተላን፣ የህፃናት ጋብቻንም በመከላከል ላይ ያነጣጠሩ ናቸው።

ግለዊ ሽግግሮች

በዚህ የመግለጫው ክፍል፣ ጉርምስና፣ ግርዛት እና የወሲብ ጅማሮ ላይ እናተኩራለን። እነዚህ ትኩረቶች፣ የእናትና የጨቅላ ጤናን በሚመለከተው የጥናት መግለጫ ውስጥ በጥልቀት ተዳስሰዋል (ማጣቀሻ፡- እናቶችና ጨቅላ ህጻናት)። የትምህርት ሽግግሮችም፣ በሌላ የጥናት መግለጫ ተካትተዋል (ማጣቀሻ፡- ትምህርት)።

ጉርምስና (አካለ መጠን)

ከጉርምስና ተዛማጅ ጉዳዮች መካከል፣ በእድገት ለመመንደግ መሟላት የሚገባው የምግብ ፍላጎት አንዱ ሲሆን፣ በዚህ ረገድ የምግብ ዋስትና ፕሮግራምና ደራሽ እርዳታ ጠቃሚ ሚና ሊኖራቸው ይችላል። በትምህርት ቤት ውስጥ ለልጃገረዶች የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁስና መፀዳጃ ቤት አቅርቦት፤ እንዲሁም በወላጆችና በትምህርት ቤቶች በኩል የሚሰናዳ የስነወሲብ ትምህርት አቅርቦት፣ የጉርምስና ተዛማጅ ጉዳዮች ናቸው። በትምህርት ቤቶች በኩል፣ የንፅህና ቁሳቁስ ለልጃገረዶች የቀረበው፣ በአራት አካባቢዎች ብቻ ነው። ይህም የድንገተኛ ጊዜ አቅርቦትን፣ እንዲሁም ልጃገረዶች ወርሃዊ መዋጮ እየከፈሉ በመምህራንና በልጃገረዶች ክለቦች አማካኝነት የሚካሄደውን የቁሳቁስ ስርጭትን ይጨምራል።

- በእስካሁኖቹ ፍቱን ተሞክሮዎች ላይ በመመርኮዝ፣ የወጣት ልጃገረዶች የምግብ ፍላጎት፣ ለብቻ ተለይቶ የተዘጋጀ መፀዳጃ ቤት፣ የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁስ አቅርቦት፣ እንዲሁም በወላጆችና በትምህርት ቤቶች በኩል የሚቀርብ የስነወሲብ ትምህርት፤ ወደፊት ቀዳሚ ትኩረት እንዲያገኙ ማድረግ ያስፈልጋል።

ግርዛት/ የሴት ልጅ ግርዛት

የፖሊሲ አላማዎች በሴት ልጅ ግርዛት ላይ ቢያተኩሩም፣ የወንድ እና የሴት ልጅ ግርዛት፣ በአብዛኞቹ የኢትዮጵያ አካባቢዎች በሰፊው የተለመደ ድርጊት ነው። የወንዶች ግርዛት የማይካሄድባቸው ሁለት የደቡብ ክልል የገጠር መንደሮች አሉ (አዳዶ እና ሉቃ)። በሰሜን አካባቢዎች፣ የወንዶች ግርዛት የሚከናወነው፣ በልደት ሰሞናት፣ ገና በጨቅላ እድሜ ነው። በኦሮሞ ህብረተሰቦች፣ በተለምዶ ከገዳ ስርዓት የእድሜ መደብ ጋር ተያይዞ፣ በእድሜ በሚበላለጡ ልጅና ጎልማሳ ወንዶች ላይ በአንድ ጊዜ ግርዛት ይከናወል። ወንዶች በጨቅላ እድሜያቸው በጤና ጣቢያ የማስገረዝ ልምድ እንዲፈጠርና እንዲስፋፋ የሚረዱ የለውጥ እንቅስቃሴዎች፣ ለኤችአይቪ ያጋልጣል ተብሎ የሚገመተውን የቡድን ግርዛት ለማስቀረት፣ ለዚህም ሰዎችን ለማሳመንና በጤና ጣቢያ አገልግሎት አዲስ ልምድ ለማስጀመር የሚደረጉ ጥረቶችን ያካትታል። በለውጥ እንቅስቃሴዎች ሳቢያ የመጡት ምላሾች ለተወሰኑ ለውጦች መነሻ ሆነዋል። ግን ቅሬታና እምቢታ ግን አልተለየውም። በየቤቱ የሚከናወነው ግርዛት በአብዛኛው አልተቋረጠም። በሌላ አንፃር ደግሞ፣ ለዓመታት ዘግይቶ የሚደረግ ግርዛት እየቀነሰ መጥቷል።

የሴት ልጅ ግርዛት ፣ ጨርሶ እንዲጠፋ በተካሄደበት ዘመቻ የሴት ልጅ ብልት ትልተላ የሚል ስያሜ የተሰጠው ልማድ፣ በአብዛኛው የኢትዮጵያ አካባቢ፣ በአውራ ባህላዊ ሥርዓቶች ውስጥ ጉልህ ቦታ ይዞ፣ ሁሌም የሚጠቀስ ነባር ወግና ልማድ ነው። WIDE ከሚከታተላቸው 20ዎቹ አካባቢዎች

መካከል፣ የሴት ልጅ ግርዛት እንደባህል የማይካሄድባቸው በደቡብ ክልል የሚገኙት ሁለት አካባቢዎች ናቸው (አዳዶ እና ሉቃ)። በትግራይ፣ በህወሐት ዘመን ተወግዷል። የግርዛት ጊዜ ይለያያል። በአማራ ክልል አካባቢዎች፣ በጨቅላ እድሜ፣ በልደት ሳምንት ገደማ ነው (ከ7 እስከ ፲፬ ባሉት ቀናት)። በሌሎች አካባቢዎች ደግሞ፣ የጋብቻ አይቀሬ የዋዜማ ቅድመዝግጅት እንደሆነ ተቆጥሮ በጉርምስና እድሜ ወይም ከዚያ በፊት ባሉት ዓመታት ይከናወናል። የሴት ልጅ ግርዛት ሲከለከል፣ በሁለት አካባቢዎች (በአዜ ደቦዓ እና በአዳ ሃሮ)፣ ከክልከላው ለማምለጥ በፈለጉ ነዋሪዎች አማካኝነት፣ ከተለመደው እድሜ በፊት ግርዛት እንደተከናወነ ተመልክቷል። በሌላ አካባቢ ደግሞ የጋብቻ ጊዜ ጋር ተያይዞ፣ ከተለመደው እድሜ የዘገየ ግርዛት ተከናውኗል (በጋራ ጎዶ)።

ከድርጊቱ ጀርባ ያሉ መነሻ ሃሳቦችና ስሜቶች፣ በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡ አንዱ ሃሣብ ፅዳት፣ ንፅህና፣ ነውር፣ ውርደትና ውበት ተብለው የሚነሱ ባህላዊ ዝንባሌዎችና ሲሆን፤ በሌላ በኩልም፤ ያተገረዘች ሴት፣ ጋብቻ፣ ወሲብ፣ እርግዝናና ወሊድ ላይ ችግር እንደሚገጥማት፣ ስድብና መገለልም እንደሚደርስባት የሚጠቁሙ፣ ማህበራዊ መነሻ ያላቸው ሃሳቦችና ስሜቶች አሉ። ሴቶችን በቁጥጥር ስር ማስገባት ከሚል ሰፊ እምነት ጋር ተያይዞ የሚገኘው ሌላኛው ማህበራዊ መነሻ ሃሳብና ስሜት፣ ግርዛት የሴቶችን የወሲብ ስሜት በመገደብ ከጋብቻ በፊትና ከጋብቻ ውጭ የሚፈፀም ወሲብን ይከላከላል የሚል ነው።

የሴት ልጅ ግርዛትን ለመከላከል፣ የአራት ወገን አካላት የየራሳቸውን የለውጥ ሚና ከውነዋል፤ እነርሱም፡- ፩)መንግስት ፤ 2) መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና አለማቀፍ ተቋማት፤ 3) ሐይማኖታዊ ቡድኖች፤ እና 4) ከባቢያዊ ድርጅቶችና ተቋማት ናቸው። ከለውጥ እንቅስቃሴዎች መካከልም፤ ፩) የሴቶች ጉዳይ ቢሮዎችን፣ ትምህርት ቤቶችን እና የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችን ያቀፉ የግንዛቤ ማሳደጊያ ዘመቻዎች፤ 2) ማስጠንቀቂያን ወይም በተግባር ገራገሮችንና ወላጆችን መክሰስንም የሚያካትቱ የሕግ አውጪና የፍርድ ቤት እርምጃዎች፤ እና 3) ያልተገረዙ ልጃገረዶችን በአርአያነት አድምቆ የማሳየት ጥረቶች ይጠቀሳሉ።

የለውጥ እንቅስቃሴዎች ያገኙት ምላሽ እንደየሁኔታው ይለያያል። ምላሾችን የመቅረፅ ድርሻና ተፅእኖ ያላቸው ጉዳዮች፡- ፩) የግርዛት ልማድ በባህል ውስጥ የተንሰራፋበትና የገነነበት መጠን፤ 2) የለወጥ እንቅስቃሴዎች ዓይነት፣ ለስኬታቸው የተካሄደው የጥረት ልክ፣ እንዲሁም የአቅጣጫዎች ቅንጅት፤ 3) በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ዙሪያ፣ የየአካባቢው አቅጣጫ፤ 4) ክልከላውን በመቃወም፣ የባህል፣ የብሔረሰብ ወይም የሃይማኖት ማንነቶችና አርማዎች የተስተጋቡ መሆን አለመሆናቸው፤ 5) ከሌሎች የለውጥ እንቅስቃሴዎች ትስስርና ከሌሎች ለውጦች ግንኙነት መኖር አለመኖሩ፤ እንዲሁም 6) በጥናቱ ወቅት የተስተዋለ የየአካባቢው የትስስር መጠን፣ እጦትና ርቀት ናቸው። የቀነሰበትን ልክና የለውጡን መጠን አገናዝቦ መረዳት፣ ጥልፍልፍ የበዛበት ስራ ነው። በሁለቱ የትግራይ ክልል አካባቢዎች፣ የሴት ልጅ ግርዛት፣ በህወሃት ዘመን ተወግዷል። በአራቱ የአማራ ክልል አካባቢዎች፣ ሴት ልጅ ግርዛት እንደ አውራ ባህላዊ ስርዓት ገነን ያለ ልማድ ሲሆን፣ በተወሰነ ደረጃ ከቀጠለው የእምቢታ ምላሽ ጋር፣ ተግባራዊ የተደረገው ክልከላም የበለጠ ትኩረት እያገኘ መጥቷል። ከአምስቱ የደቡብ ክልል አካባቢዎች መካከል በሁለቱ፣ የሴት ልጅ ግርዛት አይካሄድም። በሦስት አካባቢዎች ግን፣ በባህል የተያዘ ጉልህ ልማድ ነው። በፕሮቴስታንት ቤተእምነቶች እና መንግታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ዘንድ ጠንካራ የለውጥ እንቅስቃሴዎች ታይተዋል። የተወሰነ አደባባይ ያልወጣ እምቢታም

ነበር። ከስምንቱ የኦሮሚያ ክልል አካባቢዎች መካከል በሁለቱ፣ የክልከላው ጠንካራ ተግባራዊነት ቀርቷል፤ በአደባባይ የሚታይም ሆነ የማይታይ እምቢታ ቢኖርም። በሌላ በኩል፣ በሦስት አካባቢዎች፣ አደባባይ ያልወጣ የተወሰነ የእምቢታ ምላሽ ቢኖርም፣ በቅጡ የተቀናበሩ ጠንካራ ዘመቻዎች እየተካሄዱ፣ የሴት ልጅ ግርዛት በጉልህ ቀንሷል።

- የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስወገድ ያለሙ የለውጥ እንቅስቃሴዎች፣ የባለድርሻ ተሳትፎን ማስተባበር፣ እንዲሁም ከማህበረሰብና ከባህላዊ መሪዎች፣ ከወላጆች፣ ከትምህርት ቤቶች፣ ከጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች፣ በተለይም ከልጃገረዶችና ከወንድ ልጆች ጋር አቅጣጫዎቹን ማቀናጀት ይኖርበታል።
- የተለያዩ አቅጣጫዎችን ያዋሃደ እንቅስቃሴ የላቀ ውጤታማነት ሊኖረው ይችላል። ከአስገዳጅ ጫና ይልቅ፣ አስረድቶ ማሳመን ላይ ማተኮርም፣ የሴት ልጅ ግርዛት በድብቅ እንዳይቀጥል ሊከላከል ይችላል።

የወሲብ ጅማሮ

ቅድመ-ጋብቻ ወሲብ በባሕል ተቀባይነት ያገኘው በአንድ አካባቢ ብቻ ነው (በሉቃ)። ነገር ግን፣ ቅድመ-ጋብቻ እርግዝናና ወሊድ አይነኬ ነውር ነው። የተወለደው ሕፃን እየተጣለ ለሞት የሚዳረግበት "ሚንጊ[2]" የተሰኘው ይሄው ልማድ፣ በተለይ ቤተክርስትያናትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እየተቃወሙት ተዳክሟል። በሌሎች አካባቢዎች፣ ቅድመ-ጋብቻ ወሲብን የመታገስ አዝማሚያ የሚጨምረው፣ ለሴቶች ሳይሆን ለወንዶች ሲሆን ነው። ድግንግልናን ማጣት የልጃገረዶችን የጋብቻ እድል ያበላሻል የሚል ስጋት ገንኖ የሚታይ በመሆኑም፣ የተጠለፉ ልጃገረዶች ጠላፊያቸውን እንዲያገቡ አስገዳጅ ጫና ለማሳረፍ ምክንያት ሆኗል። ቢሆንም ግን፣ በወንድ ልጆችም ሆነ በልጃገረዶች ዘንድ ቅድመ-ጋብቻ ወሲብ መኖሩን የሚያሳዩ መረጃዎች አሉ። በሌላ በኩልም፣ ቅድመ-ጋብቻ ወሲብ የማይፈልጉና ያልፈፀሙ በአስራዎቹ እድሜ ክልል የሚገኙ ወንድ ልጆችና ልጃገረዶችም አሉ። ከበርካታ መነሻ ምክንያቶች መካከልም፤ አይናፋርነት፣ በትምህርት ላይ ለማተኮር መፈለግ፣ የተደላደለ ኑሮ እስኪያገኙ ድረስ ለመቆየት፣ በወላጆች የሚመረጥ አጋር፣ ወይም በተለይ በደቡብ አካባቢ በፕሮቴስታንት ቤተእምነቶችን ጨምሮ ሐይማኖታዊ ግዝት ይገኙበታል። ወጣቶች ለመጀመሪያ ጊዜ በጋብቻቸው ምሽት ወሲብ የሚፈፁሙበት አጋጣሚዎችም አሉ።

የተዋልዶ ጤና ትምህርት፣ በትምህርት ቤቶችና በጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች በኩል ይቀርባል። የወሊድ መቆጣጠሪያ አቅርቦት፣ የማግኘት እድልና ተጠቃሚነት እንደየአካባቢው በጉልህ የሚለያይ ቢሆንም፣ ከአንድ አካባቢ በስተቀር፣ የወሊድ መቆጣጠሪያን በቀላሉ የማግኘት እድል፣ በተለይ በአስራዎቹ እድሜ ላሉ ልጃገረዶች ብርቅ ነው። የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችም ብዙውን ጊዜ ላላገቡ ሴቶች የወሊድ መቆጣጠሪያ መስጠት አይፈልጉም። በስምንት አካባቢዎች ቅድመ-ጋብቻ እርግዝና መጨመሩን የሚጠቁሙ መረጃዎች ተመልክተዋል። በ3 አካባቢዎች ቅጠላቅጠልን የመሳሰሉ ባህላዊ ዘዴዎችን በመጠቀም ወይም ክኒኖችን በገፍ በመዋጥ ውርጃዎች መከናወናቸውን የሚያሳዩ መረጃዎች አሉ፤ በውርጃዎቹ ምክንያት የደረሱ ጉዳቶችና የሞት አደጋዎችም ተዘግበዋል። በጤና አገልግሎት ውስጥ ፅንስ የማቋረጥ አገልግሎት መቅረብ አለመቅረቡ፣ ከቦታ ቦታ ይለያያል።

[2] በደቡብ አሞ፣ ከጋብቻ ውጭ የተወለዱ ህጻናት የሚጣሉበት ልማዳዊ ሥርዓት

የገንዘብ አቅም ያላቸው ሴቶች ወደ ከተማ በተለይም ወደ ግል ክሊኒኮች እንደሚሄዱ ተነግሯል (ማጣቀሻ፡- እናቶችና ጨቅላ ህጻናት)፡፡ በ1997 ዓ.ም የወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ እንደደነገገው፣ የአስገደዶ መድፈር ድርጊት በሚኖርበት ጊዜ ወይም፣ ልጃገረዷ በአካላዊ ወይም በአእምሯዊ አቅም ጉድለት ሳቢያ ልጅ ማሳደግ የማትችል በምትሆንበት ጊዜ ካልሆነ በቀር፣ ውርጃ ሕገወጥ ነው።

- የታዳጊ ወጣቶች የስነወሲብ ጤና፣ የወሊድ መቆጣጠሪያ ተጠቃሚነትን የሚያጎላ፣ ቅድመ-ጋብቻ እርግዝና የሚገጥማቸውንና ልጅ የሚያሳድጉትን የሚደግፍ፣ እንዲሁም ወጣት ወንዶችን፣ ወላጆችንና ወጣት ሴቶችን የሚያሳትፍ መሆን አለበት።
- አደገኛ ውርጃዎች፣ በተለይ የወሊድ መቆጣጠሪያ ለማግኘት ባልቻሉ ታዳጊ ወጣቶች እንደሚፈፀሙ በመረጃ ከመረጋገጡ አኳያ፣ ሕፃን የማሳደግ አቅም የሌላቸው ታዳጊ ወጣቶች፣ ፅንስ ማቋረጥ እንዲችሉ የተለየ ፈቃድ በሚሰጥ መልኩ የሕግ ድንጋጌዎቹ እንዲሻሻሉ እንደገና መታየት ይገባቸዋል።
- በትምህርት፣ በስልጠናና በስራ እድል አማካኝነት ያለእድሜ ጋብቻን የሚያስቀሩ አማራጮች እንዲስፋፉ ማድረግ ይገባል።

በድህነትም ሆነ በሌላ ምክንያት፣ ተቀባይነት ያላቸው የጋብቻ ስርዓቶችን ለማሟላት ያልቻለ ወይም ለማሟላት ያልፈለገ ወጣት ወንድ፣ ሚስት ለማግኘት የሚፈፅመው ልማዳዊ ድርጊት ጠለፋ ነው። ጠለፋ በአብዛኞቹ አካባቢዎች እንደቀነሰ ተነግሯል። ለዚህም፣ ትምህርት ቤትና የውሃ ምንጭ በቅርበት የማግኘት እድል መሻሻሉ፣ እንዲሁም ከከባድ ቅጣት ማስፈራሪያ ጋር የአገር ሽማግሌዎች በግልግል ከማስታረቅ መቆጠባቸው፣ የየራሳቸው ድርሻ አላቸው። ምንም እንኳ፣ ከአምስት ባላነሱ አካባቢዎች፣ ጠለፋ ድራሹ ጠፍቷል ማለት እንደሚቻል ቢነገርም፣ በሌሎች ስድስት አካባቢዎች ግን፣ በመረጃነት ከሚታዩ የቅርብ ጊዜ ጥቂት ድርጊቶች ጋር፣ አሁንም አሳሳቢ አደጋ እንደሆነ ይታሰባል።

ጠለፋን ለማስቆም የተካሄዱ የለውጥ እንቅስቃሴዎች፣ በቤተሰብ ህግ እና በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የተደገፉ ሲሆኑ፣ በበርካታ ቦታዎችም የቅጣት እርምጃዎች ይጠቀሱላቸዋል። ይሁን እንጂ፣ አብዛኛው የቅጣት ውሳኔ የገንዘብ ቅጣትን ብቻ የያዘና በሕግ ከተፈቀደው እጅጉን ያነሰ፣ የአስተዳደር አካላትም ስራዬ ብለው ሳይከታተሉት የሚቀር ይሆናል። ከጠለፋ በኋላ ጉዳዩን በጋብቻ ለመቋጨት የሚደረጉ የአገር ሽማግሌዎች ግፊቶችና በጅምር የሚቋረጡ የፍርድቤት ጉዳዮችም ታይተዋል።

'የፈቃደኝነት ጠለፋ' ወይም ኩብለላ፣ 'የመፈቃቀድ' ጋብቻ በሚል ስያሜ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፣ ከስምንት ባላነሱ አካባቢዎች እየጨመረ የመጣ ይመስላል። በኦሮሞ አካባቢዎች፣ በተለይ ለድሃ ወንዶች የጥሎሽ ክፍያን የሚያስቀር ዘዴ ተደርጎ ይታያል። ከጠለፋ በኋላ፣ ለእርቅ የሚደረገው ወጪ አነስ ያለ ነው። አንዳንዴም፣ ልጃገረዶች ያለፍላጎታቸው በወላጅ ከሚጫንባቸውን ጋብቻ የሚያመልጡበት መንገድ ነው። ነገር ግን፣ የአራት አካባቢዎች አስተዳዳሪዎች እና ወላጆች፣ የፈቃደኝነት ጠለፋ እንደሚያሳስባቸው፤ ልጃገረዶች ትምህርት እንዲያቋርጡና በአነስተኛ ስጦታ ተማልለው ወደ ጋብቻ እንዲገቡ ሊገፋፉቸው እንደሚችል ጠቁመዋል።

- የጠለፋ ሕጎች ተግባራዊ ሲደረጉ፣ 'ከፈቃደኝነት ጠለፋ' እና በመፈቃቀድ ከሚከወን ጋብቻ ተለይቶ መታወቅ አለበት። ወጣት ጥንዶች፣ ወላጆቻቸው ከሚጭኑባቸው ጋብቻ ለማምለጥ

እና የጥሎሽ ወጪዎችን ለማስቀረት፣ እንዲሁም በራሳቸው ምርጫ ለመመራት ሲሉ፣ የመፈቃቀድ ጋብቻን ወይም 'የፈቃደኝነት ጠለፋን' ይጠቀማሉ።

የስራ ሽግግሮች

ከስራ ሽግግሮች መካከል የሚካተቱት፣ በአመዛኙ ወጣት ሴቶች እንደሚያደርጉት የቤት ውስጥ ሙያዎችን መጨበጥ፤ በወንዶችና በሴቶች ዘንድ የገቢ ምንጭ እና የምርታማ ስራ ትልሞችን መያዝ፣ እንዲሁም ጥንዶች ከወላጆቻቸው ኑሮ ውጭ የገዛ ራሳቸውን ኑሮ እየመሰረቱ በኢኮኖሚ ራስ-ገዝ መሆን ናቸው።

የቤት ውስጥ ሙያዎችን መጨበጥ

ዘልማዳዊው የስራ ክፍፍል፣ አብዛኛውን የቤት ውስጥና የተዋልዶ ስራ፣ ለልጃገረዶችና ለሴቶች ይመድባል። የሃላፊነቶች ሽክም የሚበዛውና በተለይ የእንክብካቤ ስራ የሚበረታው፣ የድሃ ቤተሰብ ልጃገረዶች ላይ ነው። በበርካታ ዝናብ አጠር አካባቢዎች፣ ልጃገረዶች ውሃ ለመቅዳት ረዥም መንገድ ይጓዛሉ። የልጃገረዶች የቤት ውስጥ ስራ፣ ብዙውን ጊዜ ከትምህርት ሰዓት በኋላና በእረፍት ቀናት ሁሉ ጠምዶ ይይዛቸዋል። ታናናሽ እህትና ወንድማቸውን የመንከባከብ ሃላፊነትም፣ ከትምህርት እንዲያረፍዱ ያስገድዳቸዋል። ልጃገረዶች፣ በመኖሪያ ግቢ ውስጥ የሚከናወኑ የፅዳትና የምግብ ዝግጅት፣ የልብስ አጠባና የልጅ እንክብካቤ ሃላፊነቶችን፤ ከመኖሪያ ውጭም፣ እንጨት ለቅመው፣ ውሃ ቀድተው የማምጣት፣ ወፍጮ ቤትና ገበያ የመመላለስ ሃላፊነቶችን ጨምሮ፣ ዘርፈ ብዙ የቤት ስራዎችን ይሸፍናሉ። በብዙዎቹ አካባቢዎች፣ በቤተሰብ እርሻም ፣ በተለይ በአረም እና በአጨዳ ወቅት ልጃገረዶች ይሰራሉ። እንደቤተሰብ የኑሮ ደረጃ፣ ደህየት ባሉት ዘንድ ጥቃቅን የሸቀጥ ንግድ የሚሰሩ፣ ደህና ደርጀት ባሉት ዘንድ ደግሞ በቤተሰብ ቢዝነስ ውስጥ የሚሰሩም አሉ። አንዳንዴም፣ ከእናቶቻቸው ጋር መጠጥ ጠምቀው ይሸጣሉ። የወፍጮ ቤቶች መበራከት፣ በእጅ እህል ለሚፈጩ ልጃገረዶችና ወጣት ሴቶች፣ ስራ እንደቀነሰላቸው ተጠቅሷል።

በፆታዊ የስራ ክፍፍል ዙሪያ፣ በተለይ በትርፍ አምራች አካባቢዎች፣ ጥቃቅን ለውጦች ታይተዋል። በባህል ከሞላ ጎደል ልጃገረዶች የሚሰሯቸው፣ እንጨት መልቀምና ውሃ መቅዳት፣ ወደ ወፍጮ ቤት ወይም ወደ ገበያ እህል መውሰድና ሌሎች ከመኖሪያ ውጭ የሚካሄዱ መሰል ስራዎች፣ በወንድ ልጆች ሲከናወኑ ይታያል። ልብስ የሚያጥቡ፣ ቤት የሚያፀዱ፣ ምግብ የሚያዘጋጁ፣ አረቄ በማዘጋጀት ጭምር ስራ የሚያግዙ ወንድ ልጆች ቢኖሩም፤ በመኖሪያ ግቢ ውስጥ በሚካሄዱ ስራዎች ላይ፤ የወንድ ልጆች ተሳትፎ እምብዛም ነው።

የገቢ ምንጭ ስራ ትልሞችና የምርታማነት ሚናዎች

በብዙ አካባቢዎች፣ ገና ከአስር ዓመት እድሜ ብዙም ከፍ ሳይሉ ጭምር፣ የገቢ ምንጭን ከትምህርት ጋር ማጣመር የሚጀምሩ ወንድ ልጆችና ልጃገረዶች ተበራክተዋል። አደግ ያሉት ልጆችና ወጣቶችም፣ ወደ ቅጥር ስራ ይበልጥ እየገቡ፣ ከቤት ውስጥ ስራ በተጨማሪ የገቢ ምንጭን ከትምህርት ጋር የማፈራረቅ ጫና እየበረታባቸው መጥቷል (ማጣቀሻ፡- ትምህርት) ከጊዜ ወደ ጊዜ የእርሻ-ዘለል

ስራዎች ፋይዳ እየጨመረ ነው፤ በተለይም የተሻለ የገበያ ትስስርና የከተማ ቅርበት ባላቸው አካባቢዎች ጎልቶ ይታያል።

በወጣት ወንዶች ከሚካሄዱ አነስተኛ የቢዝነስ እንቅስቃሴዎች መካከል፤ የእህል፣ የእንሰሳት፣ የቡና፣ የጫት ንግዶች፤ እንዲሁም የእንጨት፣ የከሰልና የሳር ምርትና ሽያጭ፤ የልብስ፣ የመድሃኒት፣ የፀረ-ተባይ ሽያጭ፤ የጋሪና የሞተርሳይክል የትራንስፖርት አገልግሎት፣ የእርሻ ምርት ድለላ፤ በተጨማሪም ጫማ መጥረግና የቴኒስ መጫወቻ ጠረጴዛ ማከራየት ይገኙበታል። መነሻ ገንዘብና የወላጆች ድጋፍ ማግኘት የቻሉ አንዳንድ ቀልጣፋና ታታሪ ወጣት ወንዶች፣ የላቀ ትርፋማነት ባላቸውና እንደ ወፍጮ ቤትና ሱቅ፣ ሻይ ቤትና ካፊቴሪያ በመሳሰሉ ሥራዎች ተሰማርተዋል። ድህነት በባሰባቸው ቤተሰቦች ዘንድ ግን፣ ወጣት ወንዶች መነሻ ገንዘብ ስለማያገኙ ወይም ቤተሰብ የመደገፍ ሃላፊነት ስለሚሸከሙ፣ በቢዝነስ የመሰማራት እድላቸው፣ ብዙውን ጊዜ አነስተኛ ነው።

ወጣት ወንዶች፣ እዚያው በያሉበት አካባቢ የስራ እድል የሚያገኙበት አጋጣሚ ኢምንት ነው። ብዙውን ጊዜ፣ በፍልሰት ወደ ከተሞች መግባትን ይጠይቃል። ጥቂቶቹ፣ በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ ወይም በአስተማሪነት ወይም የልማት ሠራተኞች (በግብርና ቢሮ/ በቀበሌ አስተዳደር) ሆነው ተቀጥረዋል ወይም ስራ አግኝተዋል። በመንገድ ግንባታ፣ በውሃ ልማት፣ በፋብሪካ ተከላ (ለምሳሌ የቢራ ፋብሪካ በኮርማርገፊያ፣ የዱቄት ፋብሪካ በአዳ ዳዋታ) አማካኝነት የሚፈጠሩ፣ የቀን ስራ እድሎችም አሉ። ይሁን እንጂ፣ የስራ እድሎች በስፋት የሚታዩት፣ የከባድ መኪና ጫኝና አውራጅነት፣ የሾፌር ረዳትነትን፣ የቤት ግንባታ ሰራተኛነትን በመሳሰሉ፣ መደበኛ ያልሆኑ የስራ ዘርፎች ነው። ብዙውን ጊዜ፣ ወደ ቀን ስራ የመግባት ጫና የሚበረታው፤ ገቢ የማግኘትና ቤተሰብ የመርዳት ሸክም ያለባቸው፣ የድሃ ቤተሰብ ወጣት ወንዶች ላይ ነው።

የወጣት ሴቶች ዋና የገቢ ምንጭ፣ ጥቃቅን የንግድ እንቅስቃሴዎች፣ በተለይም የእህል፣ የአትክልትና ፍራፍሬ፣ የእስንሰሳት (በአብዛኛውም የዶሮ)፣ የምግብ፣ የአልኮል መጠጥና የቡና ንግድ ስራዎች ናቸው። በጥቂት ቦታዎች፣ በሃብት ሻል ያሉ ቤተሰብ ያላቸው ወጣት ሴቶች፣ ፀጉር ቤት የመሳሰሉ የንግድ ሥራዎች አቋቁመዋል። የደሃ ቤተሰብ ልጃገረዶች፣ በጥቃቅን ንግድ፣ የአልኮል መጠጥ ጠምቀው በመሸጥ ወይም በቀን ስራ የገቢ ምንጭ የማግኘትና ቤተሰባቸውን የመርዳት ጫና ይበረታባቸዋል።

ወጣት ሴቶች፣ በመደበኛ ዘርፎች የመቀጠር ወይም ስራ የማግኘት እድላቸው ሲበዛ ኢምንት ነው። በእርግጥ፣ በአበባ እርሻዎች መስክ፣ ከወጣት ወንዶች ይልቅ ወጣት ሴቶች ተመራጭ ሆነዋል። በአንድ አካባቢ ደግሞ፣ ብዙ ወጣት ሴቶች የቡና ማጠቢያ ፋብሪካ ውስጥ ይሰራሉ (በአዜ ደቦኣ)። የቀን ስራም ሆነ የቅጥር ስራ ለማግኘት ብዙውን ጊዜ ሴቶች በፍልሰት ወደ አቅራቢያ ከተማ ወይም ወደ ክልል ከተማ፣ ወደ ትልልቅ ከተሞች ወይም ወደ ውጭ አገር ይሄዳሉ። በአመዛኙም፣ በቤት ሰራተኛነት፣ በአገልግሎት ዘርፍ በቡና ቤቶች ወይም በግንባታ ስራ ለመቀጠር ነው የሚፈልሱት (ማጣቀሻ፡- ፍልሰት)።

- በወጣት ሴቶች የምርታማነት ሚና ዙሪያ፣ አማራጮችን የማስፋፋት ጉዳይ፣ ተጨማሪ ትኩረት ማግኘት አለበት። ትኩረት ከሚያሻቸው መካከልም፣ በብድር አቅርቦት በኩል ተጠቃሚነታቸውን ማስፋፋት፣ በወጣትና በሴት የሕብረት ስራ ማህበራት ውስጥ

ተሳትፏቸውን ማሳደግ፣ እንዲሁም የንግድና የስራ ፈጠራ እንቅስቃሴያቸውን ማበረታታት ይጠቀሳሉ።

በኢኮኖሚ ራስን መቻል (በኢኮኖሚ ራስ-ገዝ መሆን)

የኢኮኖሚ ራስገዝነት፣ ብዙውን ጊዜ ከወላጆች የኑሮ ደረጃ እና በተለይም ከመሬት ይዞታ ጋር ይተሳሰራል። የመሬት እጥረትና እጦት፣ የወጣት ወንዶች ዋና ፈተና እንደሆነ በሁሉም አካባቢዎች በተደጋጋሚ ይጠቀሳል። እየተጣበበ ከመጣው የመሬት ይዞታ ጋር፣ ከወላጆች መሬት ማግኘትም ይበልጥ አስቸጋሪ እየሆነ፣ በትውልዶች መሃል ውጥረትን እና በልጆች መሃል ተቀናቃኝነትን እያባባሰ ነው።

የወጣት ሴቶች የመሬት ይዞታ፣ በአመዛኙ ሲታይ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፣ በመሬት ይዞታ ምስክር ወረቀት ውስጥ የሚስቶች ስም እንዲካተት ከመደረጉ ባሻገር ብዙም ያለፈ አይደለም። ከጋብቻ ፍቺ በኋላ፣ ሴቶች የመሬት ድርሻ ያገኙበት አጋጣሚ አለ። ይሁን እንጂ፣ አንዳንዶቹ ሚዛናዊ የመሬት ድርሻ ለማግኘት አልቻሉም። ይህም የሚሆነው፤ በፍቺ ሽምጋዮች የፆታ አድልዎ ምክንያት፣ አንዳንዴም በቀበሌ አስተዳደር ሳቢያ ሲሆን፤ ከተወለዱበት አካባቢ ርቀው ባል አግብተው የነበሩና በእርሻ የሚሰማራ የቀን ሰራተኛ ያጡ ሴቶች፣ ተገቢ የመሬት ድርሻ የማያገኙበት ጊዜ አለ።

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ለሚቀጥሉ ጥቂት ወጣት ወንዶችና ከጥቂትም ጥቂት የሆኑ ወጣት ሴቶች፣ ስራ ተቀጥረው በኢኮኖሚ ራሳቸውን ለመቻል፣ ትምህርት አንድ አማራጭ መንገድ ይሆናቸዋል። ይሁን እንጂ፣ በትምህርት መቀጠል፣ ብዙውን ጊዜ የወላጆችን ድጋፍ ስለሚጠይቅ፣ አልፎ አልፎ፣ የኢኮኖሚ ራስገዝነትንና ጋብቻን የሚያዘገይ፣ ለድሃ ቤተሰብ ወጣቶችም አስቸጋሪ ይሆናል። ችግሩ ተደራራቢ የሚሆነው ደግሞ፣ ብዙ ወጣት ወንዶች ትምህርት ከጨረሱ በኋላም ስራ ለማግኘት አለመቻላቸው ነው።

ወጣት ወንዶች፣ መሬት በማግኘት ወይም በቀን ስራ ራሳቸውን ሲችሉ፣ ወጣት ሴቶች ራሳቸውን የሚችሉበት ዋነኛ መንገድ ግን፣ ጋብቻ ነው። ይሁን እንጂ፣ ወጣት ሴቶች በወላጆቻቸው ስር ሆነው፣ በትዳር ውስጥ (ፈት ካልሆኑ በቀር)፣ በእርሻ ዘለል ስራዎች፣ በጥቃቅን ንግድ፣ በምግብና በመጠጥ ዝግጅት፣ በቀን ስራ ገቢ ያገኛሉ። የተሟላ የኢኮኖሚ ራስገዝነት ሲዘገይ፣ የወጣት ወንዶችና የወጣት ሴቶች የጋብቻ ዝግጁነትን ያደናቅፋል። ይህም፣ በወጣት ሴቶች ላይ በሚያሳድረው ጫና፣ በእድሜ ከገፉ ወንዶች በኩል የሚመጡ የጋብቻ ጥያቄዎችን እንዲቀበሉ ይገፋፋቸዋል።

<u>የወጣቶች የስራ ሽግግሮችን የሚያበረታቱ ጉዳዮችና የለውጥ እንቅስቃሴዎች</u>

ወጣት ወንዶችን የሚመለከቱ ዋና ዋና ጉዳዮች፣ የመሬትና የስራ እጦት/እጥረት ናቸው። ውስን የሆነው መሬት በቀደምት ትውልዶች ስር መሆኑ፣ በትውልዶች ጎራ እና በልጆች መሃል ውጥረትን አስከትሏል። ወጣት ወንዶች፣ በባህል እንደተለመደው፣ የራሳቸውን ኑሮ ለመጀመር እየተሳናቸው፣ በዚህም ሰበብ ጋብቻና ቤተሰብ ምስረታ የሚዘገይበት አጋጣሚ እየተፈጠረ፤ ወጣት ወንዶችና ሴቶች፣ በወላጆቻቸው ስር ሲሰሩ ወይም ከአካባቢያቸው ሲፈልሱ ይታያል። የመሬት እጦት ክፉኛ የሚበረታባቸው፣ የድሃ ቤተሰብ ወጣት ወንዶች፣ በኪራይ መሬት ለመስራት ይገደዳሉ፤ ለቀን ስራ ወይም ለፍልሰት ይዳረጋሉ (ማጣቀሻ፡- ኢ-እኩልነት፤ እና ፍልሰት)።

የመማር እድል ያገኙ ብዙ ወጣቶች ወንዶች ስራ ለማግኘት አለመቻላቸውን ተከትሎ፣ በትምህርት የመተማመን ስሜትን የመሸርሸርና ፋይዳውን የመጠራጠር አዝማሚያ ተፈጥሯል። በጥቂት ቦታዎች ሃሳባቸውን የገለፁት አንዳንድ የማህበረሰብ አባላት፣ የተማሩ ወጣት ወንዶች በእርሻ ስራ የመሰማራት ፍላጎት እንደሌላቸው ጠቁመዋል። ወጣቶች በአቅራቢያቸው የሚያወላዳ የስራ እድል የማያገኙበት የአማራጭ እጥረት አሳሳቢ እንደሆነባቸው አንዳንድ የህብረተሰብ አባላት የገለፁባቸው ጥቂት አካባቢዎችም አሉ። ስጋታቸውን ሲያስረዱም፣ “ያለስራ ቦዝኖ መቀመጥ” የአልኮል መጠጥና የጫት ሱስን፣ ወይም ስርቆትና ሁከት መፍጠርን ጨምሮ “በመጥፎ ልማድ መጠመድ” በማለት ይጠቅሳሉ።

የወጣቶች የስራ ማህበራት እንዲስፋፉ የማበረታታት እንቅስቃሴ በብዙዎቹ አካባቢዎች አለ። ይሁን እንጂ፣ በበርካታ አካባቢዎች፣ የስራ ማህበራት እየሰሩ አይደለም፤ ወይም ፈርሰዋል። በአንዳንድ አካባቢዎችም፣ ለማህበራት ተመድቦ የነበረ መሬት በቀበሌ ተወስዶ ለኢንቨስተሮች ተመድቧል። የወጣቶች የስራ ማህበራት የተደራጁት፣ ለፈርጀ ብዙ የስራ አይነቶች ሲሆን፤ ከእነዚህም መካከል፣ የግብርና ስራ፣ በተለይም የመስኖ እርሻ፣ የእርሻ ምርት የመጫንና የማውረድ፣ የእንስሳት ማድለቢያና የእንስሳት ንግድ፣ የአሸዋ አቅርቦትና የድንጋይ ወፍጮ ስራ፣ ደኖችን እና ተራራማ ተዳፋት ቦታዎችን የማልማትና የመጠበቅ ስራ፣ የእጣንና የማር ምርት መስኮች ይጠቀሳሉ። በጥቂት ቦታዎች፣ የስራ ማህበራት ለሻይ ቤትና ለካፊቴሪያ፣ ለሱቁችና ለንግድ፣ ለእደጥበባትና ለብረታብረት ስራ፣ ለእንጨት ስራና ለቤት ግንባታ በአነስተኛ ከተሞች ውስጥ በስራ ማህበራት ተደራጅተዋል።

በአንዳንድ ቦታዎች፣ በነዋሪዎች መካከል ውጥረቶች ተፈጥረዋል። በአንድ በኩል፣ የወል መሬቶችን ለእርሻ ለመጠቀም የሚፈልጉ ወጣቶች አሉ። ነባር የወል የግጦሽ መሬት እንዳይነካ የሚከላከሉ የአንጋፋ ትውልድ ሰዎች በበኩላቸው፣ የወጣቶች የስራ ማህበራት መሬት ወስደው የረባ ነገር ይሰራሉ የሚል እምነት የላቸውም። አብዛኞቹ የእርሻ ስራ ማህበራት፣ ስኬታማ አይደሉም። አንዳንዶቹም ወደ ሌላ ስራ ዞረዋል። ይሁን እንጂ፣ አንዳንድ የመስኖ እርሻ ማህበራት፣ ደህና ሰርተዋል። ከሌሎች የላቀ የትርፋማነት ስኬት ያሳዩ የስራ ማህበራት፣ በአነስተኛ ከተሞች የተደራጁ፣ የአሸዋና የድንጋይ አቅርቦት፣ እንዲሁም የድንጋይ ንጣፍ ምርት ማህበራት ናቸው።

በወጣቶች የስራ ማህበራት ዙሪያ፣ ፈርጀ ብዙ ችግሮች አሉ፤ ከእነዚህም መካከል፣ ከስራ አስተዳደርና ከአመራር ጋር የተያያዙ ችግሮች፣ ያለፈቃድ ከሚሰሩ ግለሰቦች የሚመጣ ውድድር፣ እንዲሁም የገበያ አቅም እና የቅንጅት ችግሮች ይጠቀሳሉ። መንግስት አንዳንዴ ስልጠናዎችን፣ የውሃ ሞተር ’ ለመሳሰሉ መሳሪያዎች ዱቤ እና ብድር ይሰጣል። በእርግጥ፣ ብድር መመለስ ላይ ብዙውን ጊዜ ችግር አለ። ብድር ሳይመለስ እየቀረና እየዘገየም፣ አዳዲስ የስራ ማህበራትን የማደራጀት እድል ይደናቀፋል። በአንዳንድ አካባቢዎች፣ ወጣቶች ራሳቸውን በስራ ማህበራት እንዲያደራጁ መንግስት ድጋፍ አይሰጠንም የሚሉ ቅሬታዎች አሉ። ወጣት ሴቶችም፣ በአንዳንድ ቦታዎች፣ እንድንሳተፍ አልተደረገም የሚል ቅሬታ አላቸው። በወጣት የስራ ማህበራት ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ፣ በጣም አነስተኛ ነው። ምንም እንኳ፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በሚደግፏቸው የሴቶች የስራ ማህበራት ውስጥ የሚሳተፉ አንዳንድ ወጣት ሴቶች ቢኖሩም፣ ለወጣት ሴቶች ታስበው የተደራጁ የስራ ማህበራት የሉም (ማጣቀሻ፡- ሴቶች)።

- ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት፣ ወደ ገጠር አካባቢዎች፣ በአነስተኛ ከተሞችና የቀበሌ ማእከላት አማካኝነት መስፋፋት አለባቸው። ወጣት ወንዶችና ሴቶች፣ በግለሰብና በቡድን የሚከናወኑት የስራ ፈጠራ ጥረትም ሊበረታታ ይገባል።
- ገጠር አካባቢዎች በእርሻ-ዘለል የስራ ማህበራት ዘንድ የታየው ሻል ያለ ስኬት፣ በሌሎችም ዘንድ መደገምና መበራከት አለበት።
- በኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የወጣቶችን የተደራጀ ተሳትፎ ማበረታታት እንዲሁም የሴቶችን ተሳትፎ እየደገፉ ማስፋፋት፣ በማህበረሰብ ጉዳዮች ውስጥ የወጣቶችን ሚና ሊያሻሽል ይችላል።

<u>ቤተሰብ-ነክ ሽግግሮች</u>

ከሦስቱ ቤተሰባዊ ሽግሮች መካከል፣ በዛ ባሉ የለውጥ እርምጃዎች የተካሄዱበትና በፖሊሲም ሰፋ ያለ ቦታ የተሰጠው የጋብቻ ሽግግር ላይ እናተኩራለን። ራስን ችሎ ኑሮ የመመስረት ጉዳይ፣ ከሞላጎደል በስራ ሽግግሮች ስር እንደተዳሰሰው፣ አዳጋች እየሆነ ነው፤ ምክንያቶቹም፣ የመሬት እጥረትና ከወላጆች ወይም ከአንጋፋ ትውልድ ስር ያልተላቀቀ ጥገኝነት፣ ለትምህርት የሚውለው ጊዜ መርዘም፣ እና የስራ እጦት ናቸው። ልጆችን የማፍራት ጉዳይ፣ በሌላ የጥናት መግለጫ ተካትቷል (ማጣቀሻ፡- እናቶችና ጨቅላ ህጻናት)።

የሕፃናትና ያለእድሜ ጋብቻ እና የትዳር አጋር ምርጫ

ባህላዊ ጋብቻ፣ ከብሔር-ብሔረሰብ፣ ከየአካባቢውና ከየቀዬው ባህሎች፣ እንዲሁም ከሃይማኖታዊ አመለካከቶች ጋር ተይይዞ፣ መልከ-ብዙ ስርዓትና ወግ አለው። በታዳጊነት እድሜ አጋማሽና ከዚያ ወዲያ ባሉት አመታት የሚፈፀም የልጃገረዶች ጋብቻ፣ ከአንዳንድ የደቡብ ክልል አካባቢዎች በስተቀር፣ በመላ ኢትዮጵያ የተለመደ ነው። ልጅህን ለልጄ በማለት ወላጆች ለጋብቻ የሚዋዋሉበት ልማድ በነበረበት ከአማራ ክልል በስተቀር፣ አስር አመት ሳይሞላቸው ወይም በለጋ የታዳጊነት እድሜ ላይ የሚከናወን የልጃገረዶች ጋብቻ፣ ብዙም አልተለመደም። ይሁን እንጂ፣ ያለእድሜ ጋብቻ በተለመደበት ማህበረሰብና አካባቢ ውስጥም፣ የሁሉም ቤተሰብ እና የሁሉም ልጆች ውሳኔ አንድ አይነት አይደለም። ከቤተሰብ ቤተሰብም ይለያል። ያለእድሜ ጋብቻ፣ እንደየሁኔታው በኑሮ ከመደርጀት ጋር፣ በሌላ ሁኔታ ደግሞ ከድህነት ጋር የመዳበል አዝማማያዎች ይታዩበታል። አንዳንዴም፣ ትምህርት ከማቋረጥ ጋር፣ ያለእድሜ ጋብቻ አብሮ የሚታይበት ጊዜ አለ፤ ይህም ከድህነት ጋር ሊዛመድ ይችላል (ማጣቀሻ፡- ትምህርት)። የአካባቢ ርቀትና ያለእድሜ ጋብቻ ላይ ከወጡ ክልከላዎች የማምለጥ አቅምም፣ ከሚጠቀሱ ግፊቶች መሃል ናቸው። በተጨማሪም፣ በወላጅ ይሁንታ አልያም የወላጅን ፍላጎት በመጣስ፣ ያለእድሜ ጋብቻ የሚፈፅሙና አልፎ አልፎም የሚኮበልሉ አንዳንድ ልጃገረዶችና ወንድ ልጆች አሉ።

የዘልማድ ጋብቻ፣ ክሽምግልና ጋር በወላጆች ምርጫ የሚወሰንና የሚፈፀም ስለሆነ፣ ወጣቶቹ ጥንዶች በምርጫና በውሳኔ ውስጥ ቦታ የላቸውም ማለት ይቻላል። የጋብቻ የእድሜ ወለል ወደ 18 ዓመት ከፍ ለማድረግ የተወጠኑ ለውጦች፣ በቤተሰብ ሕግ እና በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ አማካኝነት

ተተግብረዋል። በወንጀልነት በተፈረጁት ያለእድሜ ጋብቻ እና ጠለፋ ላይ፣ በ2005 ፅኑ ቅጣት ተጥሎባቸዋል።

ያለእድሜ ከሚፈፀም ጋብቻ ጀርባ ያሉ ሃሳቦች፣ በአመዛኙ ሳያገቡ የሚቆዩ ልጃገረዶች ለአደጋዎች ይጋለጣሉ ከሚሉ ሃሳቦች ጋር የተያያዙ ናቸው፤ ከአደጋዎቹም መካከል፣ ጠለፋ፣ ቅድመ-ጋብቻ ወሲብ፣ ድንግልናን ማጣት፣ የልጅነት እርግዝና፣ ውርጃ፣ ከጋብቻ ውጭ ልጅ ማሳደግ ይጠቀሳሉ። ልጃገረዶችና ወንድ ልጆች፣ ዛሬ ባለው የትምህርት ቤት አውድ፣ በለጋ እድሜ ትውውቅና ቅርርብ እየጀመሩ ነው። በዚህም፣ ከጋብቻ የቀደመ ወሲብና እርግዝና እየተፈጠረ፣ "ችግር ውስጥ ይገባሉ"፣ ከዚያም "ሸክም ይሆናሉ፤ እድሜያቸው ሳይጠና ለአባለዘር በሽታ ይጋለጣሉ" በማለት ወላጆች ይፈራሉ። ከጋብቻ በፊት ወሲብ የጀመሩ ልጃገረዶች፣ "ጥሩ የትዳር አጋር አታገኝም፣ እድሜዋ እየገፋ የጋብቻ እድል ታጣለች" የሚሉ ስጋቶችም ይታያሉ። አንዳንድ ልጃገረዶች፣ ትምህርት አቋርጠው ሲወጡ፣ የሚሰሩት ነገር ስለማይኖራቸው፣ ያለእድሜያቸው ወደ ጋብቻ ለመግባት ይፈልጋሉ የሚል ሃሳብም አለ።

በአብዛኞቹ አካባቢዎች፣ ያለእድሜ ጋብቻ በንፅፅር መቀነሱን የሚያሳዩ መረጃዎች አሉ። ፈርጀብዙ ገባር መንስኤዎቹም፣ የሕግ ተግባራዊነት፣ የወላጆችና የልጆች ትምህርት፣ የስራ እና የፍልሰት ምኞቶች፣ በወጣቱ ትውልድና በሴቶች አቅም ዙሪያ የተከሰቱ የአቅጣጫ ለውጦች፣ እንዲሁም ከመሬት እጥረት፣ ከስራ እድል እጦት፣ ከኑሮ መወደድ ጋር የተያያዙ፤ ራስ-ገዝ ኑሮ በመመስረት ረገድ ወጣቶችን ከሚፈታተኑ እንቅፋቶች ጋር የተሳሰሩ የኢኮኖሚ ችግሮች ናቸው። አስተማማኝ የኢኮኖሚ መደላድል ሳይኖር የሚፈፀም ያለእድሜ ጋብቻ እንደሚያሳስብና ብዙም ሳይቆይ ለፍቺ እንደሚዳርግ በመግለፅ በበርካታ አካባቢዎች ስጋቶች ተሰንዝረዋል።

ያለእድሜ ጋብቻ ቢቀንስም እንኳ፣ ያለእድሜ ጋብቻ እንዳልተቋረጠ በብዙ አካባቢዎች በሰፊው ተወስቷል። አደግ ያሉ ልጃገረዶች ለአካለ መጠን ደርሰዋል ብለው ብዙ ወላጆች የሚያምኑ እንደመሆናቸውም፣ ክልከላዎችን የሚቃረን የማህበረሰብ እምቢታ አለመቋረጡም ተነግሯል። በወጣቱ ትውልድ አማካኝነት፣ ማለትም ወጣት ሴቶችና ወንዶች በራሳቸው ምርጫ እየወሰኑ፣ በየጊዜው ያለእድሜ ጋብቻ ይፈፅማሉ። እንዲያውም፣ በሦስት አካባቢዎች ያለእድሜ ጋብቻ እየተበራከተ መምጣቱ በአንዳንዶች ተጠቁሟል።

ያለእድሜ ጋብቻን ለማስቆም የተወጠኑ የለውጥ እንቅስቃሴዎች፣ በሴቶችና ሕፃናት ጉዳይ ቢሮዎች አማካኝነት የሚካሄዱ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን፣ በትምህርት ቤት ውስጥ በልጃገረዶች ክበብና አንዳንዴም 'በድንግሎች' ክበብ አማካኝነት፣ ወይም ከጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ጋር በትብብር የሚቀርብ ትምህርት፣ በልጃገረዶች የእድሜ ማረጋገጫ የህክምና ምርመራ አማካኝነት፣ ያለእድሜ ጋብቻ ላይ የተሳተፉ ወላጆችንና ሽምጋዮችን በመክሰስ ፍርድ ቤት ማቅረብና እስራትን ጭምር ያካትታሉ። የለውጥ እንቅስቃሴዎች መጠንና ስፋት ላይ ድርሻ ካላቸው ጉዳዮች መካከል፤ ክልላዊ ፖሊሲና መመሪያ፣ የችግሩ አሳሳቢነት ላይ የሚታይ የአመለካከት አዝማሚያ፣ ጥናቱ እንደተካሄደበት የጊዜ ልዩነት ይጠቀሳሉ።

ከሞላ ጎደል በሁሉም አካባቢ፣ የለውጥ እንቅስቃሴዎች የተካሄዱት በመንግስት ነው። በእርግጥ፣ በሁለት አካባቢዎች መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በተለይ በትምህርት ቤቶች ውስጥ በስልጠና

ተሳትፈዋል (ገልቻ እና ሶሞዶ)። በአንድ አካባቢም፣ ወረዳው እምነት የሚጣልባቸው ልማዳዊ ድርጅቶችን ለማሳተፍ አቅዷል (ጋራ ጎዶ)። የተለያዩ ክልላዊና አካባቢያዊ አዝማሚያዎች ጉልህ ናቸው። በአንድ የትግራይ ክልል አካባቢ፣ ጉዳዩ መፍትሄ እንዳገኘ ተነግሯል (በገብለን)፤ በሌላ የክልሉ አካባቢ ግን፣ አሁንም ችግሩ እንዳለ ተጠቅሷል (በሃረሳው)። በአማራ ክልል፣ ያለእድሜ ጋብቻ ፈታኝ ችግር ነው ተብሎ የሚታሰብ ሲሆን፣ በአንዳንድ አካባቢዎች የተካሄዱ መረር ያሉ የለውጥ እንቅስቃሴዎች፣ ሽምጋዮችንና ወላጆችን ማስፈራራትንና የመቅጣት አጋጣሚዎችን ያካተቱ ናቸው። በኦሮሚያ ክልል፣ ያለእድሜ ጋብቻ ከሌሎቹ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የከፋ እንዳልሆነ በማሰብ፣ ለጠለፋና ለሴት ልጅ ግርዛት ችግሮች ቅድሚያ ትኩረት ተሰጥቷል። በደቡብ ክልልም፣ ጠለፋና የሴት ልጅ ግርዛት ዋና ችግር ተደርገው ይታያሉ።

በተጨባጭ፣ በአብዛኞቹ አካባቢዎች ሲካሄዱ የቆዩ የለውጥ እርምጃዎች፣ ግንዛቤን በማስጨበጥ ላይ የተወሰኑ ናቸው። የየአካባቢው ባለስልጣናትም ብዙውን ጊዜ፣ ያለእድሜ ጋብቻ ላይ ክልከላ በመጫን ቅራኔን መፍጠር አይፈልጉም። በወላጆችና በልጃገረዷ መካከል ስምምነት ካለ፣ ምንም ማድረግ አንችልም የሚል መከራከሪያም ያቀርባሉ። ምስክሮች ለፍርድ ቤት ቃላቸውን ለመስጠት እንደሚፈሩና፣ በአንድ አካባቢም ሃላፊዎች ሙስና እንደሚፈፅሙ ጭምር የሚጠቁሙ አቤቱታዎች አሉ። ይሁን እንጂ፣ በስድስት አካባቢዎች፣ የሴቶች ጉዳይ መስሪያ ቤቶችን፣ መምህራንን፣ ፖሊስን እና ፍርድቤትን ያካተቱ የሕግ እርምጃዎች ተወስደዋል (ሁለት በአማራ ክልል፣ አንድ በትግራይ ክልል፣ እና ሦስት በኦሮሚያ ክልል)። የልጃገረዶች የእድሜ ምርመራ መካሄዱ በሦስት ቦታዎች የተጠቀሰ ሲሆን (በአማራ ክልልና በትግራይ ክልል)፣ በአንድ አካባቢም ከጋብቻ የእድሜ ወለል አልፋችኋል የሚል ማረጋገጫ በልጃገረዶች ክንድ ላይ መለያ ማህተም እንዲለጠፍ ተደርጓል። በአንድ አካባቢ፣ የ13 አመት ልጃገረድ ወላጅ እናት ለአንድ አመት፣ አባቷ ደግሞ ለሦስት አመት እንዲታሰሩ ተደርገዋል (ሹምሽሃ)።

- የልጃገረዶች እድሜ አከራካሪ መሆኑ ሲታይ፣ ዋናው መነሻ ችግር ተብሎ ሊጠቀስ የሚችለው የልደት ምዝገባና ምስክር ወረቀት አለመኖሩ ነውና፣ ይህንን ችግር መፍታት ያሻል።

ክልከላውን በተመለከተ በሚታዩ የእምቢተኝነት ምላሾች መካከል፣ በአደባባይ ክልከላው ተቀብሎ ልማዳዊውን ድርጊት በድብቅ መቀጠል፣ የልጃገረዶችን እድሜ አግንኖ መከራከር፣ ሌላ ድግስ አስመስሎ ጋብቻ መሰረግ፣ ወይም ከመምህራን ጣልቃ ገብነት ለማምለጥ ጋብቻውን በክረምት ማድረግ፣ የእድሜ ምርመራ በሚካሄድባቸው አካባቢዎችም ታላላቅ እህቶችን ማስመርመር ይጠቀሳሉ። በአንድ አካባቢ፣ ያለእድሜ ጋብቻ በወላጆች የሚወጠንበት ሽምግልናና ስምምነት አሁንም የተወሰነ ያህል የሚታይ ቢሆንም፣ ጋብቻ የሚፈፀመው ልጅቱ 18 ዓመት ሲሞላቸው ነው (በየትመን)።

የፖሊሲ ርዕሰ ጉዳይ እና ትኩረት፣ በጋብቻ እድሜ ዙሪያ ቢያጠነጥኑም፣ ይበልጥ መሰረታዊ የሆነው ጥያቄ፣ በጋብቻ አጋር ምርጫ ዙሪያ የውሳኔ ሰጪነት ጉዳይ ላይ እና በወላጆች የተወጠነ ጋብቻ የሚፈፀመው ያለ ልጃገረዷ ፈቃድ መሆኑ ላይ ነው። በደቡብ አካባቢዎች፣ ዘልማዳዊው የጥሎሽ ክፍያ፣ ወጣት ወንዶች የወላጆች ውሳኔ ጥገኛ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። በእርግጥ፣ ከቀን ስራ እና ከፍልሰት ጋር በተያያዘ፣ ብዙውን ጊዜ ወጣት ወንዶች የጥሎሽ ክፍያውን በከፊል ይሸፍናሉ።

ይሁን እንጂ፣ በጋብቻ አጋር ምርጫዎች ላይ ጉልህ ለውጥ ታይቷል። ወጣት ወንዶች፣ ወጣት ሴቶችም ጭምር፣ የየራሳቸውን አጋር በመምረጥ ረገድ ከጊዜ ወደ ጊዜ ድርሻቸው እየጨመረ፤ እንዲሁም በጥንዶች መፈቃቀድ የሚፈፀም ጋብቻ እየተለመደ የመጣበት በጉልህ የሚታይ ለውጥ አለ። በወላጆች በሚወጠኑ ጋብቻዎችም እንኳ፣ ሴት ልጃቸውን ማማከርና ፈቀደኝነቷን መጠየቅ በብዙዎቹ አካባቢዎች ተለምዷል። በእርግጥ፣ ልጃገረዶች ይሁንታቸውን እንዲገልፁ ብዙ ጫና ይመጣባቸዋል። እንዲያም ሆኖ፣ የራሳቸውን ምርጫ የሚወስኑ ልጃገረዶች በብዙዎቹ አካባቢዎች እየተበራከቱ ናቸው። የቀን ስራ እና የንግድ እንቅስቃሴያቸውም፣ የራሳቸውን ምርጫ የመወሰን ድርሻቸውን አስፍቶላቸዋል። በተማሩ ጥንዶች ዘንድ፣ እንዲሁም በፕሮቴስታንት ቤተእምነት በተሰባሰቡት ዘንድ፣ የራሳቸውን ምርጫ የመወሰን ልምድ ሰፋ ብሎ ይታያል። ይሁን እንጂ፣ አንዳንዴ ወላጆች የሴት ልጃቸውን ምርጫ ይቃወማሉ፤ የትምህርት ቤት ወጪ ለመከልከል ጭምር ይዝታሉ (ዶአማ)።

- 18 ዓመት ሳይሞላቸው ለመጋባት የሚፈልጉ አንዳንድ ወጣት ጥንዶች ከመኖራቸው አንፃር፣ በበርካታ አገራት ሕጋዊ እንደመሆኑና በ2000 በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግም በፍትህ ሚኒስቴር ፈቃድ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ እድል የሚሰጥ ከመሆኑ አኳያም፣ የሴቶች ጉዳይ ቢሮ፣ ፍርድቤትና ሌሎች የሚመለከታቸው ተቋማት ከሚያደርጉት ተገቢ ክትትልና ቁጥጥር ጋር፣ 16-18 ዓመት የሆናቸው ወጣቶች ልዩ የጋብቻ ፈቃድ የሚያገኙበት ሁኔታ እንዲፈጠር ማሰብ ይቻላል።

ማህበረሰባዊ ሽግግሮች

የወጣቶች የማህበራዊ ትስስር ተሳትፎ ላይ ያሉ መረጃዎች አነስ ያሉ ናቸው። የወጣት ድርጅቶችና በማህበረሰብ ተወጥነው በተዋቀሩ ድርጅቶች ውስጥ፣ ወጣቶች ያላቸው ተሳትፎን የሚመለከት መረጃ ደግሞ ውስን ነው። በሃይማኖት ውስጥ ግን፣ የወጣቶች ተሳትፎ እየጨመረ መምጣቱን የሚያሳዩ ምልክቶች በብዙ አካባቢዎች አሉ። አንዳንድ ወጣቶች፣ በተለይ በሃብት ሻል ያሉ ወጣት ወንዶች፣ በእቁብ ማህበራት ገብተው ይቆጥባሉ።

በሦስቱ የወጣት ድርጅትቶች፣ ማለትም በወጣት ማህበራት፣ ሊጎች እና ፌደሬሽኖች መካከል ያለው ልዩነት፣ የአመራሮቻቸው ተወራራሽነት ተጨምሮበት፣ አንዳንዴ ግልፅ አይደለም። የወጣት ማህበራት፣ ረዘም ያለ ታሪክ አላቸው፤ ነገር ግን ብዙ ወጣት አይሳተፍባቸውም። የወጣት ድርጅቶች የአባላት ብዛት ላይ፣ ጉልህ ልዩነቶች አሉ። በአንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ እንቅስቃሴ አያካሂዱም፤ ወይም ከነጭራሹ የሉም።

የወጣት ማህበራት፣ የስራና ኢኮኖሚ እድሎችን አይፈጥሩም በሚል፣ ብዙ ወጣት በማህበራት ላይ ያን ያህልም እምነት አያሳድርም፤ አልያም እምነቱ ተሸርሽሯል። የወጣት ማህበራት ደግሞ፣ በብድርና በስልጠና እጦት፣ እንዲሁም በወረዳ ድጋፍ እጥረት ሳቢያ፣ አቅማቸው የተገደበ ነው። የወጣት ሊጎች፣ የኢህአዴግ መዋቅር አካል ሲሆኑ፣ ፌደሬሽኖች በአመዛኙ የወጣት ማህበራትንና የወጣት ሊጎችን የፖለቲካ እንቅስቃሴ የሚያስተባብሩና አነስ ባሉ የአባላት ቁጥር እንደ አመራር ሆነው ይሰራሉ። የወጣት ማህበራት፣ ሊጎችና ፌደሬሽኖች፣ በየራሳቸው ሊኖራቸው በሚችል የተለያየ ሚና ዙሪያ፣ በአመራሮች ዘንድ ጭምር የረባ ግንዛቤ የለም።

የወጣት ድርጅቶች ውስጥ የወጣት ሴቶች ተሳትፎ፣ በጣም ውስን ነው። ቁጥራቸውም፣ ከወጣት ወንዶች ብዛት ጋር ሲታይ፣ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። በአመራር ቦታ ድርሻቸውም፣ አናሳ ነው። በአንዳንድ ቦታዎች፣ ወጣት ሴቶች፣ ሻል ያለ እንቅስቃሴና ገንዘብ አቅም ወዳላቸው የሴት ማህበራት መግባትን ይመርጣሉ። በእርግጥ ብዙ ጊዜ፣ የሴት ማህበራት፣ በአመዛኙ ያገቡ ሴቶችን ያቀፉ ናቸው።

በማህበራት ውስጥ ካለው አናሳ ተሳትፎ በተቃራኒ፣ በሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የወጣቶች ተሳትፎ ከፍ ያለ ነው። በተለይ ወጣቶች ወደ ፕሮቴስታንት ቤተክርስትያናት እንዲቀላቀሉ የሚጋብዙ ሁኔታዎችና፤ በምዕመን ሰበካ ጉባኤ ውስጥም የድርሻቸውን ሚና ሲጫወቱ ይታያል። በእርግጥ፣ ወጣቶች፣ እንደ ሰንበት ትምህርት ቤት በመሳሰሉ የኦርቶዶክስ ቤተክርስትያናት እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንዲሁም በአንዳንድ አካባቢዎች በመስጊድ ግንባታ ላይ አስተዋፅኦ በማበርከትና በመሳሰሉ የሙስሊም ህብረተሰብ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ይሳተፋሉ።

በማህበረሰባዊ ጉዳዮች ውስጥ የወጣቶች ተሳትፎ፣ ውስን እንዲሆን ያደረጉ ምክንያቶችን በተመለከተ፣ መሬት የሌላቸው ወጣቶች፣ በእርሻ ማሳ ለሚካሄድ የተፈጥሮ ጥበቃ ስራና ለመሰል የማህበረሰብ እንቅስቃሴ የሚሰጡት ትኩረት አነስተኛ መሆኑ፣ እንዲሁም የወጣቶች ውሳኔ ሰጪነት በቤተሰብ አባወራ ስር መሆኑ፣ በከፊልም ቢሆን በመንስኤነት ተጠቅሰዋል። ይሁን እንጂ፣ አንዳንድ ወጣት ወንዶች በቀበሌ አመራርነት፣ በልማት ኮሚቴ እና በሌሎች መንግስታዊ ወይም ህዝባዊ ስራዎችና በበጎፈቃድ ስራዎች፣ ለምሳሌ በመንገድ ጥገና፣ በምንጭ ጠረጋ፣ አንዳንዶችም ሚሊሺያ በመሆን ይሳተፋሉ።

የወጣት ሴቶች ተሳትፎ ይበልጥ የተገታው በቤት ውስጥ ሃላፊነት፣ በዶታ ኡድልዎ፣ በፍላጎት እጥረትና በማበረታቻ እጦት እንደሆነ ተገልጿል። የወጣት ሴቶች ተሳትፎ ከወጣት ወንዶች በባሰ ሁኔታ አናሳ ቢሆንም፣ እንደ ብርቅ በሚታይ ሁኔታ፣ በጤና ዘማችነት፣ በጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኝነት፣ በልማት ኤጀንትነትና በአስተማሪነት ጥቂት ወጣት ሴቶች የስራና የሃላፊነት ቦታ ይዘዋል።

ትምህርት

ትምህርት በገጠር ኢትዮጵያ (2010-13)፡- ራዕይና ጥርጣሬ

WIDE የውይይት መነሻ አጭር መግለጫ ቁ. 4/...10[1]

ዋና ዋና ነጥቦች ከWIDE መረጃዎች

- በገጠር ኢትዮጵያ ከትምህርት ጋር በተያያዘ የባህል ለውጥ ተካሂዷል። ከ1995 ወዲህ የWIDE ጥናት ክትትል ባደረገባቸው ማህበረሰቦች ውስጥ የታየው መሻሻል ለዚህ ምስክር ነው (ለምሳሌ በ1995፣ ት/ቤት የገባች አንድም ልጃገረድ ያልነበረው ማህበረሰብ፤ በ2010 በርካታ ሴት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን አስመርቋል) መንግስት ለትምህርት ቅድሚያ በመስጠት ረገድ ያሳየው ቁርጠኝነትም ሌላው ማሳያ ነው።
- ይሄ በጎ አካሄድ ግን ስጋት የገጠመው ይመስላል። በ1995፤ ትምህርት በግብርና ለሚተዳደሩ ማህበረሰቦች የሚሰጠውን ፋይዳ በተመለከተ ጥርጣሬ ሰፍኖ ነበር። በ2003፤ ትምህርት ወደተሻለ ህይወት እንደሚያደርስ መንገድ የሚታለም ሆነ። በ2010-13፣ በዋናነት የቀለም ትምህርት ስኬት ለመቀዳጀት የተቃኘ፣ ከፍተኛ ፍላጎትና ራዕይ፣ ተመልሶ ከመጣው ጥርጣሬ ጋር አብረው ዘልቀዋል። የትምህርት ጥራት ዝቅተኛ ነው ተብሎ ይታሰባል። እንደ ነገሩ የተማሩ በርካታ የገጠር ወጣቶች፣ ፈተና ከወደቁ በኋላ ትምህርት የመቀጠል ዕድል የላቸውም፤ ሥራ የማግኘት ተስፋቸውም የመነመነ ነው።
- ከቀለም ትምህርት ውጭ ለሆኑ ሙያዎች ዋጋ መስጠት፣ ለዚህ ችግር ምላሽ ለመስጠትና የመንግስት የገጠር ሥራ ፈጠራን እንዲሁም የኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ ግቦችን ለማሳካት ወሳኝ ነው። ከግንዛቤ ውስጥ ከሚገቡ አማራጮች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል፡-
  - በመንግስት ፖሊሲ በታቀደው መሰረት፣ መደበኛ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና (ቴሙትሥ)፣ ልዩ ትኩረት በመስጠት ጥራትን ማጠናከር፤
  - ኢ-መደበኛ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠናን በከፍተኛ ደረጃ ማስፋፋት እንዲሁም ዓላማዬ ብሎ የቅድሚያ ትኩረት መስጠት፤

---

[1] ይህ አጭር የጥናት መግለጫ፤ በWIDE የውይይት መነሻ አጭር የጥናት መግለጫዎች ሁለተኛ ጥራዝ (ስብስብ) ውስጥ ከተካተቱት አስር መግለጫዎች አንዱ ነው። መግለጫው፤ በካትሪን ዶም የተዘጋጀ ሲሆን በስጦታው ይማም ተገምግሟል። አዘጋጅዋ፤ መግለጫዎቹ ይሰናዱ ዘንድ በገንዘብ ለደገፉት ለእንግሊዝ ዓለም አቀፍ የልማት ተቋም፣ ለአይሪሽ ኤይድና ለስዊድን ዓለምአቀፍ የልማት ኤጀንሲ ልባዊ ምስጋናዋን ታቀርባለች። በተጨማሪም የጥናት ሪፖርቱን በማርቀቅ ሂደት የተሳተፉና አጭር የጥናት መግለጫው የትኩረት አቅጣጫ እንዲሰላ እገዛ ያደረጉ ሌሎች የጥናት ቡድን አባላትና ባለሙያ ገምጋሚዎች፣ ለሥራው ለሰጡት ጊዜና ድጋፍ ታመስግናለች። ሌሎች ምስጋናና ዕውቅና የሚያሻቸውም አሉ፡- (1) ለዓመታት የጥናት መግለጫው የተዘጋጀበትን መረጃዎች ያሰባሰቡና ያደራጁ የጥናት መኮንኖችና ተቆጣጣሪዎች ሙሉ ጊዜያቸውን ሰጥተው ላበረከቱት አስተዋጽኦ፤ (2) በሶስት ዙሮች ለተካሄደው የWIDE ጥናት የገንዘብ ዕገዛ ላደረጉ የተለያዩ ድጋፍ ሰጪ ተቋማት፤ እና (3) በኢልምተ ሰብሳቢነትና በኢኮኖሚ ፖሊሲ ትንተና ክፍሉ በWIDE አጭር የጥናት መግለጫዎች ሁለተኛ ጥራዝ ላይ ለመወያየት መጋቢት 28 ቀን 2016 ዓ.ም በተዘጋጀው መድረክ ላይ የተሳተፉ ከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣናት፣ ላሳዩት ፍላጎትና ለከፈሉት የጊዜ መስዋዕትነት--- ምስጋና ይገባቸዋል። የጥናት መግለጫው፤ በከፍተኛ ደረጃ በተዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ፣ ከመንግስት ባለሥልጣናት ጋር በተደረገው ውይይት የተሰጡ አስተያየቶችን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ከለሳና ማሻሻያ ተደርጎበታል። አጭር የጥናት መግለጫው፤ የኢትዮጵያ የልማት ምርምር ተቋምን (ኢልምተ) ወይም የኢትዮጵያ መንግስትን አሊያም የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርጉለትን የልማት አጋሮች አመለካከትም ሆነ አቋም አይወክልም፤ ይልቁንም የፖሊስ ውይይት ለማነቃቃት የታለመ ነው። ሌሎች የጥራዝ ሁለት የውይይት መነሻ አጭር መግለጫዎችንና የጥናትና ምርምር ውጤቶችን በhttp://ethiopiawide.net/ ድረ-ገጽ ላይ ማግኘት ይቻላል።

- ለህብረተሰቡ አመለካከት ቀጥተኛ ምላሽ መስጠት፤ ለምሳሌ፡- በሚዲያ ዘመቻ እንዲሁም በአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ዘርፈ ብዙ የተግባር ክህሎት አማራጮችን በማካተት፡፡

- ሁሉን የሚያካትት ትምህርት ወደ ሁሉን አቀፍ ዕድገት የሚያደርስ መንገድ ነው፤ ቁልፍ የመንግስት ግብ ነው፡፡በአብዛኞቹ ማህበረሰቦች ማነቆው ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ወደ ሁለተኛ ደረጃ ተቀይሯል፡፡ ሆኖም በተደራሽነትና ስኬት ረገድ በየማህበረሰቡ ልዩነቶች አሉ - በአርብቶ አደርና በአንዳንድ ራቅ ያሉ ማህበረሰቦች፣ በእጅጉ ዝቅ ያለ ነው፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ጥራት፣ የወረደ ነው ተብሎ ይታሰባል፡፡ ተነጥለው በርቀት የሚገኙ፣ አነስተኛ ወይም አዲስ ት/ቤቶች ከጥራት ጋር በተያያዘ ዝቅ ያሉ ናቸው (ለምሳሌ፡- በህንጻዎችና ብቃት ባላቸው መምህራን)፡፡

- ተደራሽነትና ስኬት፣ በየማህበረሰቦቹ ውስጥ ባሉ የህብረተሰብ ክፍሎች መካከልም በእጅጉ ይለያያል፡፡ ልዩነቱ፤ ከቅድመ መጀመሪያና የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ይጀምርና፣ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ይብሳል፤ ድሃ/ለጥቃት ተጋላጭ የሆኑ ህጻናት/ታዳጊዎች ትምህርት ለመማር ይቸገራሉ/አይችሉም፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ትምህርትና ሥራን ስለሚያጣምሩ ፣ በርካቶቹ ትምህርታቸውን የሚከታተሉት ወጣ ገባ እያሉ ነው፡፡

- የገጠር ኢትዮጵያ ሰፊ ብዝሃነት ያለው ሲሆን ልዩነቶች ይበልጥ እየጎሉ መጥተዋል፤ በዚህ አውድ ውስጥ ሁሉን አቀፍ የትምህርት ተደራሽነትን እውን ለማድረግ፣ ሁሉንም በአንድ አቅጣጫ ብቻ መቃኘት ከሚለው አካሄድ መውጣትን ይጠይቃል፡፡ ከዚህ በታች የቀረቡትን ጨምሮ፣ ከአካባቢያዊ አውድና ግለሰባዊ ሁኔታ ጋር እንደ አመቺነቱ የሚዛመዱ የተለያዩ አማራጮችን ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ይቻላል፡-

  - ለችግረኛ አካባቢዎች/ትምህርት ቤቶች ይበልጥ የተነጣጠረ፣ ሁሉን አቀፍ ድጋፍ መስጠት፤ ለምሳሌ ዳጎስ ያለ የገንዘብ ድጋፍ ለችግረኛ ት/ቤቶች፤ የውጣ ውረድ ካሣ - በአርብቶ አደር ወይም ራቅ ያሉ ት/ቤቶች ለሚያስተምሩ መምህራን የበረሃ አበል ማሠብ፤ የት/ቤት ምገባ/ማበረታቻ ፕሮግራሞች - በምግብ ዋስትና ባልተረጋገጠባቸው አካባቢዎች ማካተት ይጠቀሣሉ፡፡

  - ለመንግስት የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት በቂ ውጤት ያመጡ፣ ነገር ግን ቀጥተኛ ያልሆኑ ወጪዎችን የመክፈል አቅም ለሌላቸው ችግረኛ ብሩህ ወጣቶች ነጻ የትምህርት ዕድል ፕሮግራሞች መንደፍ፡፡

  - ችግረኛ/ለጥቃት ተጋላጭ ህጻናትን ወይም ቤተሰቦቻቸውን፣ ከማናቸውም ዓይነት የት/ቤት መዋጮ ነጻ ማድረግና ለት/ቤቶቹ ገንዘቡን መተካት፤ ለምሳሌ፡- ከላይ እንደተጠቆመው ዳጎስ ባለ የገንዘብ ድጋፍ፡፡

- ትምህርትን ይበልጥ አመቺ ማድረግ፣ ሁሉ-አቀፍነትን የበለጠ ለማቀላጠፍ ትልቅ ሚና ይኖረዋል፡፡ ዘርፈ ብዙ የትምህርት/ሥልጠና ሥርዓት ተደራሽነትን ማረጋገጥና ሁለቱን የሚያገናኝ ድልድይ መፍጠር፣ በገጠር ኢትዮጵያ የሚታየውን የተለያዩ የትምህርት-እና-ሥራ

ጉዞዎች የተሻለ ያስተናግዳል። ከግንዛቤ ውስጥ ከሚገቡ አማራጮች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡-

- የማህበረሰቡ ምርጫ በሆነበት ሥፍራ የፈረቃ ትምህርትን መቀጠል እንዲሁም የህጻናት/ወጣት ቡድኖችን በሚጠቅም ቦታ (ጥራት ያለው) አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት መስጠት፤
- ት/ቤቶች፤ የትምህርት መርሃ ግብራቸውን የማህበረሰቡን ወቅት-ተኮር/ሳምንታዊ ልማዶች (ለምሳሌ፡- የሰብል ምርት መሰብሰቢያ ወቅትና የገበያ ቀናት) ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ እንዲያሻሽሉት ማበረታታት፤
- የማታ ክፍለ ጊዜ ትምህርቶችን በሁሉም ደረጃዎች የበለጠ ማስፋፋት እንዲሁም የቀንና የማታ ትምህርት ሽግግሮችን ማቅለል፤
- የትምህርት ኮርሶችን ማሻሻል እንዲሁም ትምህርት አቋርጦ መልሶ መጀመር እንዲቻል መመሪያዎችን ቀለል ማድረግ፤
- የርቀት ትምህርትን በገንዘብ መደገፍ/ማስፋፋት።

- ብዙዎቹ እነዚህ ሃሳቦች የኢትዮጵያ መንግስት ፖሊሲ አካል ሆነዋል፤ (ለምሳሌ፡- የትምህርት ሚኒስቴር "ሰማያዊ መጽሐፍ")[2]። ሆኖም የወረዳ የትምህርት ሃላፊዎች እነዚህን ለማስፈጸም ተጨማሪ ድጋፍ ሊያስፈልጋቸው ይችላል። ጥራትን ለማሻሻልና አመቺነትን ለማሳደግ በታለሙ እርምጃዎች መካከል ጥምረት መኖሩን ለማረጋገጥ፣ መንግስት ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች ላይ ሊመረኮዝ ይችላል[3]።
- የልጃገረዶች ትምህርት መሻሻል አሳይቷል፤ ነባር ማህበራዊ ልማዶችንና ድርጊቶችን በአበረታች ሁኔታ በመጋፈጥ። ሆኖም በዚህም ረገድ ከማህበረሰብ ማህበረሰብ ልዩነቶች ይታያሉ። አያሌ ከጾታ ጋር የተዛመዱ ፈተናዎች (የቤት ውስጥ ሥራዎች፣ የት/ቤት የንጽህና ችግር፣ ያለ ዕድሜ ጋብቻ፣ የወላጆች ያለ ዕድሜ/ያልተፈለገ እርግዝናን መፍራት) ልጃገረዶች ከፍ ባሉ የትምህርት ክፍሎች እንዳይሳተፉ ይገድባሉ።
- ት/ቤቶችን ለልጃገረዶች ምቹ ማድረግና ያለ ዕድሜ ጋብቻን መከላከል፣ ጥቂቶቹን ችግሮች ይፈታቸዋል። የወጣት ሴቶችን የትምህርት ዕድሎች የበለጠ ለማሳደግ፣ መንግስት ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባ ጉዳዮች አሉ፡-
  - ለሴትና ወንድ ተማሪዎች ጥንቃቄ የተሞላበት፣ በቂ፣ ዕድሜና ባህልን ከግምት ውስጥ ያስገባ የጾታ ምክር በመለገስ፣ ወጣት ሴቶች ካልተፈለገ እርግዝና እንዲጠበቁ ማድረግ።
  - ጋብቻና እርግዝና በሚከሰቱ ወቅትም፣ ወጣት ሴቶችን ከት/ቤት የሚያግዱ መሆን የለባቸውም፤ ያገቡ ወጣት ሴቶችና ያላገቡ እናቶች ተመልሰው ትምህርት ቤት መግባት

[2] *የትምህርት አመራር አደረጃጀት፣የማህበረሰብ ተሳትፎና የፋይናንስ መመሪያ* (ትምህርት ሚኒስቴር፤2002 -) "ሰማያዊው መጽሐፍ" በሚልም ይታወቃል።

[3] እንደየ አካባቢው ሁኔታ ተጣጥመው የተቀረጹና የተመሩ አሰራሮች ይበልጥ ወጥ ከሆኑት ለምን እንደሚልቁ ፣ "ያንኑ አሰራር መደጋገም" ጥራትን እንደማያሳድግም፣ አያሌ ምሳሌዎችን፣ (ከሌሎች ሥራዎች በተጨማሪ) Lant Pritchett "*The rebirth of education – Schooling ain't learning*",ዓለም አቀፍ የልማት ማዕከል፤2013፤ ይመልከቱ።

እንዲችሉ፣ ለት/ቤቶችና ማህበረሰቦች ቀጥተኛ መመሪያ መስጠት፤ የፖሊሲ ጉዳይ መሆኑንም ግልጽ ማድረግ፡፡

- በማህበረሰቡ ውስጥ የሚሰሩ በአርአያነት የሚታዩ ባለሙያ (professional) ሴቶች ፤ ልጃገረዶችን/ወጣት ሴቶችንና ወላጆቻቸውን ያነቃቃሉ፡፡ ስለዚህም በየአካባቢው ለመንግስት የሥራ መደቦች፣ ቅድሚያ ለሴቶች መስጠት፣ የሴቶችን ትምህርት ለማስፋፋት የሚወሰዱ እርምጃዎችን ውጤታማነት ለማጠናከር ያግዛል፡፡

<u>መግቢያ</u>

"ማህበራዊ ለውጥ ለማምጣት ትልቁ ሃብት የወጣቶች ትምህርት ነው፤ እናም ትምህርታቸው ከንቱ ሆኖ እንዳይቀርና ህብረተሰቡ እንዲያድግ ከተፈለገ፣ እኒህ ወጣቶች የሃላፊነት ቦታዎች ሊሰጣቸው ይገባል" (ዶናልድ ሌቪን፤ 1961)፡፡

መንግስት ለትምህርት ትኩረት በመስጠት ረገድ ያሳየው ቁርጠኝነት በሌቪን ሃሳብ እንደሚስማማ ማረጋገጫ ነው፡፡ ይህ አጭር የጥናት መግለጫ፤ በኢትዮጵያ 20 ማህበረሰቦች ውስጥ በትምህርት ዕድሎች፣ ስኬቶች፣ አመለካከቶችና ተስፋዎች ረገድ፤ ማህበረሰቦቹ ለመጀመሪያ ጊዜ በWIDE በተጠኑበት በ1995 እና 2010-13 መካከል የታዩ ለውጦችን የሚዳስስ ሲሆን (መግቢያውን ይመልከቱ) መንግስት በኢትዮጵያ ትራንስፎርሜሽን ለማምጣት ባስቀመጠው ግብ፣ የትምህርትን ሚና የበለጠ ለማጠናከር እንደ ሃሳብ መነሻነት ያገለግላል፡፡

<u>በራዕይና በጥርጣሬ መሃል - ትምህርት ለምኔ...</u>

የWIDE ጥናት፤ ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት፣ በገጠር ኢትዮጵያ፣ በትምህርት ላይ የታየውን አስገራሚ የአመለካከት ለውጥ ጉዞ ይሰንዳል፡፡

በ1995 የተደበላለቀ አመለካከት ነው የታየው፡፡ መሰረተ ትምህርትና የቁጥር ክህሎት ጠቃሚ እንደሆኑ ይታሰብ ነበር፡፡ ግማሽ በሚሆነው ማህበረሰብ ዘንድ ትምህርት፤ ዕውቀትንና አስተሳሰብን ያሰፋል ተብሎ ቢታመንም ለገበሬ ወይም ለገበሬ ሚስት የዕለት ተዕለት ተጨባጭ ኑሮ ያለው ፋይዳ ሙግት ፈጥሯል፡፡ በሦስት ማህበረሰቦች፤ የተማሩ ሰዎች እርሻ ጥለው ይሄዳሉ የሚል ፍራቻ ተንጸባርቋል፡፡ በሌሎች ሦስት ማህበረሰቦች፤ አንዳንድ ሰዎች ትምህርትን ሙሉ በሙሉ ተቃውመዋል፡፡ (በዲንኪ፣ አንድ ተደማጭነት ያለው ገበሬ፣ ትምህርት፤ "የግብርና ሥራዎችን ያዳክማል" ሲል፤ በሹምሸሃ፣ "ህጻናትን ከቤተሰቦቻቸው ይለያል"፤ በአዴሌ ኬኬ፣ "ማንነትንና ባህላዊ የአኗኗር ዘይቤን ያዛባል" -- ተብሏል)፡፡ ስዕሉ ለልጃገረዶች የጨፈገገ ነበር፡፡ ትምህርት ከእርሻ ለተለዩ ሥራዎች ጠቃሚ ሊሆን እንደሚችል ቢታሰብም በአንዳንድ ቦታዎች አሉ ለማለት የሚያስደፍር አልነበረም፡፡

በ2003፣ በግለሰብ ህልምና ራዕይም ሆነ (ከእርሻ ህይወት መውጣትን ጨምሮ) በማህበረሰብ ልማት አንጻር ትምህርት ወደ ከፍተኛ ተስፋ ተለውጦ ነበር፡፡ ሆኖም በ6 ማህበረሰቦች ከትምህርት ከፍተኛ ወጪና ፋይዳ ጋር የተዛመዱ ሃይለኛ ስጋቶች ተነስተዋል፡፡ ለምሳሌ በገብለን (ምስራቅ ትግራይ)፣ አንዳንድ ሰዎች፤ የድህረ 10ኛ ክፍል ትምህርት ደኅና ኑሮ የሚመሩ ብቻ የሚያገኙት ዕድል መሆኑን በመጠቆም፣ "ይሄማ ወደ ንጉሱ ሥርዓት ይመልሰናል" ብለዋል፡፡ በአዳ ሃሮ (ምዕራብ ሸዋ) ቃለ

ምልልስ የተደረገላቸው ተጠያቂዎች ደግሞ፤ ተማሪዎች የእርሻ ሙያም ሆነ ለመንግስት ሥራ የሚያስፈልግ ትምህርት አለመቅሰማቸውን ገልጸዋል፤ በዚህም የተነሳ ቤተሰብ ከተማሩ ልጆች ተስፋ የሚያደርገው ድጋፍ የማይጨበጥ ጉም ሆኗል፡፡

በ2010-13 በትምህርት ተደራሽነትና ስኬታማነት ረገድ ትልቅ (በማህበረሰቦች መካከል ልዩነት ቢኖርም) የመሻሻል ውጤት የታየ ሲሆን ይሄም የትምህርት ፋይዳን በተመለከተ የባህል ለውጥ መምጣቱን ያጠናክራል፡፡ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት እንዲዳረስ መንግስት ያከናወነው የግንዛቤ ማሳደጊያና የቅስቀሳ ጥረት፤ የአገልግሎት አሰጣጥን ያስፋፋ ሲሆን ዘርፈ ብዙ የማዘመን እንቅስቃሴዎች፣ ትምህርትን ከሌሎች አካባቢያዊ የዝመና እንቅስቃሴ ገጽታዎች ጋር ትስስር እንዲፈጥር አድርገውታል (ለምሳሌ፡- የ"ዘመናዊ ወላጆች" ሴቶችን እንዲሁም ወንዶች ልጆቻቸውን ማስተማር፤ የተማሩ ወጣቶች "ዘመናዊ ሃሳቦች"ን ለምሳሌ፡- በምርጫ ማግባት፣ ንጽህናን መጠበቅ፣ በጤና ተቋማት ወሊድ መፈጸም ወዘተ ለመቀበል የበለጠ ክፍት ናቸው ተብሏል)፡፡

ሆኖም ግን ይሄ በጎ እንቅስቃሴ ስጋት የገጠመው ይመስላል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃና ከዚያ በላይ የተማሩ ወጣቶች ሥራ አጥ መሆናቸው፣ በ1995 በአራት ማህበረሰቦች፣ በ2003 በስድስት ማህበረሰቦች፣ እንደ ችግር የተቆጠረ ሲሆን በ2010-13 ትልቅ ስጋት ፈጥሯል፡፡ በአራቱም ክልሎች፣ በ15ቱም ማህበረሰቦች፣ በጣም ርቀው ከተነጠሉት አንስቶ (ለምሳሌ ገብለን) እስከ የከተማ ዳርቻ (ሻሸመኔ አቅራቢያ ያለው ቱርፌ፣ ሃሮማያ አቅራቢያ የሚገኘው አዴሌ ኬኬ) በርካታ ሰዎች፤ አያሌ ቁጥር ያላቸው እንደነገሩ የተማሩ የገጠር ወጣቶች (ለምሳሌ፡- ፈተና ከወደቁ በኋላ ተስፋ የቆረጡ የ8ኛ ክፍልና የመንግስት ተቋም የሚያስገባ በቂ ውጤት ያላመጡ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች እንዲሁም ከየክፍሉ ትምህርት ያቋረጡ) ያለ ተጨማሪ የትምህርት ዕድልና የሥራ ተስፋ በባዶ መቅረታቸው አሳስቧቸዋል፡፡

የተለያዩ አመለካከቶች ተስተውለዋል፡፡ ማህበረ ኢኮኖሚያዊ ልዩነቶች ባላቸው አያሌ ማህበረሰቦች፣ ለትምህርት የነበረው ቁርጠኝነት ከፍተኛ ነው፤ ነገር ግን የሚባለው ዝቅተኛ ጥራት፣ ለውድቀትና ለሥራ አጥነት እንደዳረገ ይታሰባል፡፡ እናም ለብዙዎች እውነታው ከሚጠበቁት ጋር አልተጣጣመም፡፡ በዚህም የተነሳ ህልምና ራዕይ፣ ከአለመተማመን ጋር ጎን ለጎን ዘለቁ፡፡ እኒህም በኢኮኖሚ የደረጁትን ጊራር/ጉራጌ ("በማህበረሰቡ ውስጥ ፕሮፌሰሮች፣ ዶክተሮችና ባለ ዲግሪዎች ይኖራሉ" ነገር ግን የተማሩ ወጣቶች ሥራ ሳያገኙ ሲቀሩ፤ "ለማህበረሰቡ አደጋ" ነው) ሶሞዶ/ጂማ እና ኡዳ ሃሮ/ምዕራብ ሸዋ፤ እንዲሁም ዝናብ አጠር የሆኑትን የምስራቅ ትግራይ ሃረሳውና ገብሌን፣ የከምባታ አዘ ደቦአን ያካትታሉ ("ከሁለት ዓመት ወዲህ፣ ለአካባቢው አያሌ ምሩቃን፣ የሥራ ዕድል የለም፤ ወጣቱ ትውልድ፣ ሥራ ፍለጋ፣ አገሩን ጥሎ ከመውጣት ውጭ ምን ያድርግ?")፡፡

በሌላኛው ጥግ ትምህርት የመማር ቁርጠኝነት ከጥርጣሬ ያልወጣባቸውና ከትምህርት የሚጠበቁት ተስፋ ገና ጨቅላ የሆነባቸው ማህበረሰቦች አሉ - በተለይም ርቀው በተነጠሉት ሉቃ/ጸማይ፣ ዲንኪ/ሰሜን ሸዋ እና ቆሮደጋጋ/አርሲ፡፡ ሌሎች ማህበረሰቦች፤ በመሃል ላይ ሲሆኑ በአብዛኞቹ ግን ከዝቅተኛ ጥራት፣ ከስኬት እጦትና ከሥራ አጥነት ጋር የተዛመዱ ሥጋቶች እየጨመሩ ነበር፡፡

በተጨማሪም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና (ቴሙትሥ) የመከታተል ፋይዳን በተመለከተ አለመተማመን ሰፍኗል፡፡ በ2010፣ ቴሙትሥ እንደ አንድ አማራጭ ቢቆጠርም በብዙዎቹ

ማህበረሰቦች የተደራሽነት ችግር ነበር። በ2011/12 እና በ2013 ዝቅተኛ ጥራት ወይም ውስን ፋይዳ (በብቃት ያልሰለጠኑ መምህራን፣ የማሽኖች/መሣሪያዎች እጥረት፣ በቂ ያልሆነ የተግባር ልምምድ፣ የአማራጮች መጥበብ) እንዲሁም የቴሙትሥ ምሩቃን ሥራ አለማግኘት፣ ከፍተኛ ሥጋት ፈጥሯል። በሶሞዶ የተደላደለ ቤተሰብ እንዳላት ወጣት ሴት፣ ጥቂት የተለዩ በስተቀር፣ በአጠቃላይ የወላጆችና ወጣቶች ህልምና ራዕይ፣ ወደ ዩኒቨርሲቲ ትምህርት የተቃኘ ሲሆን ቴሙትሥ እንደ ሁለተኛ ምርጥ አማራጭ የሚቆጠር ነበር። በ2010፣ የብቃት ማረጋገጫና ምዘና፣ ተጨማሪ ፈተናን ጋርጧል፤ ብዙዎችም ማለፍ እንዳልቻሉ የተነገረ ሲሆን ይሄም ከፍተኛ ቅሬታን ፈጥሯል - ለምሳሌ፡- በአዳ ሃሮ።

<u>"ትምህርት ለምኔ" የሚለውን ጥያቄ መመለስ</u>

ከቀለም ትምህርት ውጭ የሆኑ ሙያዎችንና ኑሮዎችን ማከበር፤ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የታለመውን የኢኮኖሚ እመርታና በተለይም የመንግስት የገጠር የሥራ ፈጠራና የኢንዱስትሪ ማስፋፋት ፖሊሲ ግቦችን ለማሳካት ወሳኝ ነው። ይሄም ከላይ የተጠቀሱት በርካታ የገጠር ወጣቶች፣ ተጨማሪ ትምህርት መቀጠል የሚችሉባቸውን መንገዶች መክፈትን ይጠይቃል።

አምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ዕቅድ (ESDP5, 2015/16-2019/20) በየወረዳው ቢያንስ አንድ ቴሙትሥ እንደሚቋቋም ይገልጻል። ሆኖም ቴሙትሥ ጠቃሚ ነው ተብሎ የሚታሰበው ጥራቱና ፋይዳው ተሻሽሎ ሲታይ ብቻ ነው። በተጨማሪም በአሁኑ ወቅት ኢ-መደበኛ/መደበኛ ያልሆኑ ቴሙትሥ በአብዛኛው መንግስታዊ ባልሆኑ ተዋንያን ላይ የተመሰረቱ (በWIDE ወረዳዎች) እምብዛም የሉም፤ በግል ኮሌጆች ሲቀርብ ደግሞ ለብዙዎች በጣም ውድ ነው። የመንግስት ቴሙትሥ ተቋማት፣ ኢ-መደበኛ አማራጮችን ማስፋፋት ያለባቸው ቢሆንም ከመደበኛው ቴሙትሥ ጋር እየታገሉ በመሆኑ አልሆነላቸውም። ይሄ የሚጠቁመው፡-

- ከመነሻው የቴሙትሥ ተቋማትን በብቁ ባለሙያዎችና በበቂ መሳሪያዎች ማደራጀት ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። ይሄም የራሳቸውን በቂ ገቢ ለማመንጨት የተሻለ አቅም ያጎናጽፋቸዋል (በቴሙትሥ ስትራቴጂ ላይ በታቀደው መሰረት) ከዚያም ጥራት ያለው ሥልጠና ሊሰጡ ይችላሉ።
- ኢ-መደበኛ/መደበኛ ያልሆኑ ቴሙትሥ በከፍተኛ ደረጃ ማስፋፋት- ለቅድመ 8ኛ ክፍልና ለቅድመ 10ኛ ክፍል እንዲሁም የ10ኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ወስደው ለመደበኛው የድህረ 10ኛ ክፍል ሥልጠና የሚያበቃ ውጤት ላላመጡ ተማሪዎች በእጅጉ የሚፈለጉትን አማራጮች ይከፍታል። መንግስት ጠንካራ የመሪነቱን ድርሻ ከሚወስድባቸው ጉዳዮች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል፡-
  - በመንግስት የቴሙትሥ ተቋማት፣ ሆነ ብሎ ለኢ-መደበኛ አማራጮች ትኩረት መስጠት
  - በቴሙትሥ ሥልጠና እና በገጠር የወጣቶች ሥራ ፈጠራ ፕሮግራሞች መካከል ትስስሮችን ማጠናከር፡- ለምሳሌ ማንበብና መጻፍ/የሂሳብ ትምህርት፣የቴክኒክና ቢዝነስ ክህሎት ሥልጠና እንዲሁም በአካባቢው ተፈላጊነት ባላቸውና ተለይተው በታወቁ የሥራ ዘርፎች የተግባር ልምምድ--- በጥምረት በሚሰጡ አካባቢ-በቀል ፕሮግራሞች መንደፍ።

- ክልላዊና አገር አቀፍ የሰው ሃይል ፍላጎት መረጃ የሚሰጡ፣ የወረዳ የሰው ሃይል ሃብት ገበያ ማዕከላትን ማቋቋም፣ የቴሙትሥ ተመራቂዎችን ሥራ በመፈለግ ረገድ ሊያግዝ ይችላል።

WIDE ክትትል ባደረገባቸው ማህበረሰቦች ውስጥ የተስተዋለው ለቴሙትሥ የተቀዛቀዘ ፍላጎት፤ በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ዕቅድ (ESDP5) ላይ ከሰፈረው፤ "ባለፉት ዓመታት በቴሙትሥ ሥርዓት ላይ የተከናወኑ ዘርፈ ብዙ ለውጦች ለህብረተሰቡ በአግባቡ አልተብራሩም" የሚል ጥልቅ ትንተና ጋር የሚጣጣም ነው። የስልጠና ጥራቱንና ፋይዳውን ማጠናከር፣ የቴሙትሥ ምሩቃን ሥራ የማግኘት ዕድላቸውን በእጅጉ ያሳድጋል። ይሄም ቀስ በቀስ ለግንዛቤና አመለካከት ለውጥ አስተዋጽኦ ያደርጋል። መንግስት ለህብረተሰብ አመለካከቶች ቀጥተኛ ምላሽ መስጠትን ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል። ለምሳሌ፡-

- በአንደኛ ደረጃና በሁለተኛ ደረጃ ስርዓተ ትምህርትና በማስተማር/መማር ሂደት ለኑሮ ክህሎቶች ከፍተኛ ትኩረት መስጠት። ሥርዓቱን አሁን ከሚታየው ከሞላ ጎደል ሙሉ በሙሉ በቀለም ትምህርት ላይ ያተኮረ አካሄድ ማስተካከል፣ የህጻናትና ወላጆችን ተስፋ ወደ አንድ ወገን ያዘነበለ ብቻ እንዳይሆን ለማድረግ ያግዛል።
- የመደበኛና የኢ-መደበኛ/መደበኛ ያልሆኑ የቴሙትሥ ትምህርቶችና እነዚህን መማር የሚያስገኙትን የሥራ ዓይነቶች በተመለከተ በጎ ገጽታቸውን የሚያሳድጉ የሚዲያ ቅስቀሳዎች ማከናወን። ሁሉም ሰው የዩኒቨርሲቲ ወይም የመደበኛ ቴሙትሥ ምሩቅ መሆን የለበትም። በእርግጥም WIDE በጥናቱ ያረጋገጠው የገጠር የኢኗኗር ደረጃ ለውጦች (ማጣቀሻ፡- ኢ-እኩልነት፤ እና ስኬት) የሰለጠኑ ቴክኒሺያኖች የውሃ ፓምፖችን፣ የእህል ወፍጮዎችን፣ የሞባይል ስልኮችን፣ የኤሌክትሪክ መስመሮችን ወዘተ የመጠገን አቅም እንዳላቸው ያሳየ ሲሆን፤ ዘርፉ ይበልጥ ክብርና ዋጋ ሊሰጠው ይገባል።

<u>በ2010-13 ተደራሽነት - በጣም ኢፍትሃዊ፤ ግን በማህበረሰቦች መካከል አለመመጣጠን ይታያል</u>

በ2010-13 የመዋዕለ ህጻናት ትምህርት አገልግሎት እንደ ቅርብ ጊዜ የመንግስት ፖሊሲ ቀስ በቀስ በተለያዩ ሞዳሊቲዎች እያደገ ነው ። በ2011/12 እና 2013 በWIDE በተጠኑ 12 ማህበረሰቦች፤ የመዋዕለ ህጻናት ትምህርት የመከታተል ፍላጎት ነበር፤ ሆኖም የተመዝጋቢዎች ቁጥር አነስተኛ መሆኑ አልቀረም። በስምንት ማህበረሰቦች አገልግሎቱ ከእነአካቴው አልነበረም። በከተማ ዳርቻ በሚገኙ ማኅበረሰቦች (ለምሳሌ ግራርና ሲርባ) ጥቂት በኑሮ የተደላደሉ ቤተሰቦች፤ ልጆቻቸውን በግል መዋዕለ ህጻናት ውስጥ አስገብተዋል።

በ1995 በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት አገልግሎትና ተደራሽነት ረገድ የነበሩት ልዩነቶች፤ በ2010-13 ተጽዕኖ ማሳደራቸውን ቀጥለዋል። አንዳንድ ማህበረሰቦች ከዝቅተኛ ተደራሽነት ተነስተው በፍጥነት የተመጣጠኑ ሲሆን ሌሎቹ አልሆነላቸውም (ለምሳሌ፡- ገብለን ከቆሮደጋጋ ጋር ሲነጻጸር) የተሟላ የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት የሌላቸው ሰባት ማህበረሰቦች ነበሩ። የአንደኛ ደረጃ ምዝገባ ቢያንስ በስምንት የተለያዩ ማህበረሰቦች በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሯል፡- ጋራ ጎዶ፣ ዶማና አዜ ዴቦአ (በዋናነት ፕሮቴስታንትና መጀመሪያ ላይ የተሻለ አገልግሎት የተሰጣቸው)፤ አዳዶ (ፕሮቴስታንት)፤ ሹምሸሃ፣ ኮርማርገፍያና አዴሌ ኬኬ (የከተማ ዳርቻ) እና በትግራይ ገብለን እንደ ምሣሌ ይጠቀሣሉ። አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት በነበረባቸው ማህበረሰቦች ቆሟል (ያለ በቂ ግልጽ ምክንያት)-

የአርብቶ አደር አካባቢዎች ከሆኑት ሉቃና ገልቻ በስተቀር፤ በእነዚህም አካባቢዎች ቢሆን የወደፊት ዕጣ ፈንታው እርግጠኛ አይደለም፡፡

የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት አገልግሎትና ተደራሽነት በአብዛኛው ተሻሽሏል፡፡ ነገር ግን በአምስት ማህበረሰቦች ብቻ ነበር ተማሪዎች የ9ኛና 10ኛ ክፍል ትምህርታቸውን በአካባቢያቸው ወይም በአቅራቢያ መከታተል የሚችሉት፡፡ በ1995 የትምህርት አገልግሎት በቅጡ ባልደረሳቸው ማህበረሰቦች፤ የታየው መሻሻል ከሌሎቹ አንጻር ያልተመጣጠነ ሲሆን ለበርካታ ተማሪዎች አሁንም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን መከታተል ፈተና መሆኑ አልቀረም (በተለይ ከድሃ ቤተሰቦች ለወጡና ለልጃገረዶች)፡፡ ይህም በርቀት፣ በወጪ ምክንያቶችና- ለልጃገረዶች ደግሞ በደህንነት ፍራቻ የተነሳ ነው፡፡ በሁለቱ የአርብቶ አደር ማህበረሰቦች፤ አሁንም የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ገቢዎች ቁጥር በጣም አነስተኛ ነው፡፡

በ2010-13 ከሦስቱ ማህበረሰቦች በቀር በሁሉም የመሰናዶ ትምህርትን (ከ11ኛ-12ኛ ክፍል) ለመከታተል ከቤተሰብ መነጠል የግድ ነበር፡፡ በሰባት ወረዳዎች ውስጥም የመንግስት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አልነበረም፡፡ እናም በአንደኛው ጥግ በበርካታ ማህበረሰቦች ውስጥ በአንጻራዊነት የድህረ 10ኛ ክፍል ትምህርት የተከታተሉ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሰዎች የሚገኙ ሲሆን በሌላኛው ጥግ በ2010 ራቅ ባሉት ዲንኪና ቆሮደጋጋ እንዲሁም በ2011/12 በሉቃ የድህረ 10ኛ ክፍል ትምህርት ተመዝጋቢዎች ቁጥር በጣም አነስተኛ ነበር፡፡

በአጠቃላይ በአብዛኞቹ ማህበረሰቦች በ1995 በአንደኛ ደረጃ ትምህርት በአገልግሎት አሰጣጥና በተደራሽነት ረገድ የነበረው ማነቆ ወደ 9ኛ ክፍል ተሻግሯል፤ በድኅረ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትም ተጨማሪ ችግሮች ተከስተዋል፡፡ በከተማ ዳርቻ ላይ የሚገኙ ማህበረሰቦች የተጠቀሙ ሲሆን አንዳንድ ርቀው የተነጠሉ ማህበረሰቦችም ጥሩ ነበሩ፡፡ በሦስቱ በጣም ርቀዉ በተነጠሉ ማህበረሰቦች፤ የሁለተኛ ደረጃና የከፍተኛ ትምህርት ተደራሽነት በእጅጉ የተገደበ እንደሆነ ቀጥሏል፡፡ በሁሉም ክልሎች ፈጣን የመሻሻል ውጤት ተመዝግቧል፡፡ ሁለቱ የአርብቶ አደር ማህበረሰቦች ዝቅተኛ የትምህርት ስኬት አሳይተዋል፤ ምንም እንኳን ብዙም ያልራቀውና በዘመናዊ የዓለም ኢኮኖሚ የተከበበው ገልቻ፤ ከሉቃ የተሻለ ውጤት ማስመዝገብ ቢችልም፡፡

የት/ቤቶች ውጭያዊ ድጋፍ (በለጋሾች፣መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ሃይማኖትን መሰረት ያደረጉ ድርጅቶች) ወጥነት ይጎድለዋል - በማህበረሰቡ በሚገኙበት ቦታ አንጻር፣ በተደራሽነትና በድጋፍ ዓይነት፡፡ በአብዛኛው የተለመዱት የድጋፍ ዓይነቶች፤ በመሰረተ ልማትና ድሃ ወይም ለችግር ተጋላጭ የሆኑ ህጻናት ላይ የሚያተኩሩ ናቸው፡፡ የመጀመሪያው በሰዓቱ የሚቀርብ ነበር፤ ሁለተኛው ደግሞ በበርካታ አጋጣሚዎች ዘላቂነት አልነበረውም፡፡ የሚሰጠው ድጋፍም ሆነ ድጋፉ የሚቆምበት መንገድ ተገማች ወይም ከወረዳ ሃላፊዎች ጋር በቅንጅት የሚከናወን አይመስልም፡፡ በአምስቱ ርቀው የተነጠሉ ማህበረሰቦች ደግሞ ከእነአካቴው ድጋፍ የሚባል የለም፡፡ የተማሪዎች ምገባ ለምሳሌ፡- በሃረሳው (ምስራቅ ትግራይ)፣ እንዲሁም በሉቃ/ጸማይ ለልጃገረዶች የምግብ ዘይት መስጠት የመሳሰሉ የማትጊያ ፕሮግራሞች ውጤታማ ቢሆኑም ለለጋሽ የድጋፍ ቅነሳ የተጋለጡ ናቸው ተብሏል። ይህ ሁኔታ በሃረሳው ታይቷል።

<u>የትምህርት ጥራት በ2010-13 - አሳሳቢና ያልተመጣጠነ</u>

በሁሉም ማህበረሰቦች በአንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ከትምህርት ጥራት መውረድ (በተለይ ከከተማ ት/ቤቶች ጋር ሲነጻጸር) ጋር በተያያዘ ፈርጀ ብዙ "እጥረቶች" ወይም ችግሮች የተጠቀሱ ሲሆን ይሄም በፈንታው የወጣቶችን ሥራ የማግኘት ተስፋ የመነመነ አድርጎታል፡፡ በጥቂት ማህበረሰቦች እንግሊዝኛ መማር ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነበር፡፡ ቢያንስ በአምስት ማህበረሰቦች ውስጥ የተማሪዎች በአንድ ዓመት ሁለት ክፍሎችን ማለፍ ቀርቷል ወይም ሙሉ በሙሉ አይተገበርም፡፡ ለዚህም ምክንያቱ ተማሪዎች አስፈላጊውን ዕውቀት ሳይቀስሙ ያልፉና በኋላ ላይ ይወድቃሉ ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡ አሃዳዊ የማስተማር ፖሊሲም (አንድ አስተማሪ ከመጀመሪያው ዓመት አንስቶ እስከሚቀጥሉት አራት ክፍሎች በተመሳሳይ የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ህጻናትን የሚከታተልበት) አልተወደደም፡፡ ምክንያቱም ለህጻናት መጀመርያ ላይ "መጥፎ አስተማሪ" ከገጠማቸው ለአራት አመታት የተሻለ መምህር የሚያገኙበት ዕድል ስለማይኖር ነው፡፡ በሁሉም ት/ቤቶች (ከዶኦማ/ጋሞ በስተቀር) ህጻናት ግማሽ ቀን ብቻ ነው የሚማሩት፡- በዚህ መንገድ ትምህርትና ሥራን አጣምረው ያካሂዳሉ፡፡ ይሄ በአንዳንድ አካባቢዎች አይቀሬ መሆኑ በግልጽ የተነገረ ሲሆን በሁሉም ማህበረሰቦች በስፋት የሚታወቅ እውነታ/ከስተት ነው፡፡

ከመሠረተ ልማት ጋር በተገናኘ የዕድሳት ወጪዎችን መሸፈን ብዙ ጊዜ ፈተና ቢሆንም ነባር ት/ቤቶች የተሻሉ ናቸው፡፡ በዘጠኝ ማህበረሰቦች፤ አሁንም የት/ቤት የውሃ አቅርቦት አሳሳቢ መሆኑ አልቀረም፡፡ የመምህራን እጥረት (በ11 አጋጣሚዎች ተስተውሏል) በከተማ ዳርቻ ለሚገኙ ወይም የተሻለ ትስስር ለፈጠሩ ማህበረሰቦች እምብዛም እንደ ችግር የማይነሳ ቢሆንም፤ በዚህም ብዙ ጊዜ የሚታወኩት አነስተኛና በጣም ርቀው የተነጠሉ ት/ቤቶች ናቸው፡፡ ከመምህራን ጋር የተያያዙ ችግሮች በስፋት የተለመዱ ሲሆን ከብቃት ማነስ እስከ ከባድ የሥራ ጫና እንዲሁም በቂ ያልሆነ ማትጊያና ከት/ቤት አዘወትሮ መቅረት ወይም ማርፈድ የመሳሰሉ ጉዳዮችን ያካልላል - አስተማሪዎች በከተማ እንጂ በማህበረሰቡ ውስጥ የማይኖሩባቸው በከተማ ዳርቻ የሚገኙ ማህበረሰቦችን ጨምሮ፡፡ ሌሎች ችግሮች በመማርያ/ማስተማርያ ቁሶች አቅርቦት፣ በአስተማሪ ሙያዊ ሥልጠና እና በአንድ ክፍል ውስጥ ባሉ ተማሪዎች ብዛት ዙሪያ ያጠነጥናሉ፡፡

በአጠቃላይ የWIDE መረጃ እንደሚጠቁመው፤ ከጥራት ጋር ለተዛመዱ ጉዳዮች በሙሉ ት/ቤቶች ተመጣጣኝ ባልሆነ ሁኔታ የተነኩ ሲሆን በአብዛኛው አነስተኛ፣ አዲስ ወይም በጣም ርቀው የተነጠሉ ት/ቤቶች ደካማ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ይህም የሚጠቁመው ትምህርት ቤት ማስፋፋት እንደ መንግስት የቅድሚያ ትኩረት የሚከናወን ቢሆንም የሚያስፈልገውን የገንዘብ አቅም ማሰባሰብ በመንግስትም ሆነ በማህበረሰቦች በኩል አስቸጋሪ ሆኖ መገኘቱን ነው፡፡

ለጥራት ችግሮች ምላሽ ለመስጠት ፈርጀ ብዙ እርምጃዎች ተጠቅሰዋል - በአብዛኛው ቀላል የማይባል የማህበረሰብ ጊዜን/የገንዘብ መዋጮን/የዓይነት ድጋፍን የሚጠይቁ ናቸው፡፡ በስድስት ት/ቤቶች በማስተማርያ/መማርያ ቁሶች ረገድ መሻሻል ተስተውሏል፡፡ በስምንት ት/ቤቶች ደግሞ የት/ቤት የገንዘብ ድጋፍ ከመንግስት ወይም ከለጋሾች መገኘቱ ተጠቅሷል፡፡ ብዙ ት/ቤቶች የራሳቸው የገቢ ምንጭ ያላቸው ሲሆን በአብዛኛው ከወላጅ/ማህበረሰብ መዋጮ ጎን ለጎን ከፊል መሬታቸውን በመጠቀም የሚያገኙት ነው፡፡ የት/ቤት መሠረተ ልማት እንቅስቃሴዎች በስፋት የተለመዱ ሲሆን የማህበረሰብ ድጋፍን ሙሉ በሙሉ ያሳትፋሉ፡፡ በማስተማር/መማር ሂደቱ ላይ ያነጣጠሩ ዘርፈ ብዙ

እርምጃዎች ተወስደዋል (የመምህራን አቅም ማጎልበቻ፣ የት/ቤት ቁጥጥር፣ የልዩ ፍላጎት ትምህርት እንዲሁም የተማሪዎችና መምህራን የ1ለ5 ጥምረት አሰራር) ነገር ግን ውጤታማነታቸውን የሚያሳይ በቂ ማስረጃ አልተገኘም፡፡ በአንዳንድ ት/ቤቶች ወላጆች ወይም የት/ቤት ሠራተኞች ከጥራት ጋር የተያያዙ ችግሮች አሳሳቢ መሆናቸው መቀጠሉን የሚገልጽ ስሜት አንጸባርቀዋል፡፡

በመንግስት ፖሊሲ መሰረት ወላጆች በት/ቤት ጉዳዮች ውስጥ መሳተፍ ይጠበቅባቸዋል - በተለይ ከክፍል ለመቅረትና ለጥራት ችግሮች ምላሽ ለማፈላለግ ይረዳሉ። ምንም እንኳን በእንቅስቃሴያቸው ደረጃና በውጤታማነታቸው ረገድ ብዙ ልዩነት ቢታይም በአንዳንድ ማህበረሰቦች የወላጆች-መምህራን ማህበራት ዘርፈ ብዙ ሃላፊነቶች እንዳሏቸው ወይም ተጽዕኖ ፈጣሪ እንደሆኑ ይነገራል።

በአጠቃላይ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ምን ያህል ጥሩ ነው የሚለውን በተመለከተ፣ በማህበረሰቦችና በት/ቤቶች መካከል በግልጽ የሚታዩ አለመመጣጠኖች (ልዩነቶች) ተመዝግበዋል፡፡ ፈርጀ ብዙ በሆኑ ጉዳዮች መነሻነት ሳቢያ፣ የጥራት መውረድ፣ በሁሉም ዘንድ የናኘ ችግር ተደርጎ የሚቆጠር ሲሆን ይሄ ደግሞ በፊናው በፈተና ስኬታማ አለመሆንን እንዲሁም የሥራ ቅጥር ውስንነትን ያስከትላል፡፡ የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል የተወሰዱ እርምጃዎችን ስንመለከት፣ አንድም በቂ አይደሉም አሊያም ደግሞ ችግሩን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመፍታት በበቂ ሁኔታ አልተተገበሩም፡፡

<u>ማን ት/ቤት ተገኘ፤ ማን አልተገኘም ፤ ለምን?</u>

ከድሃ/ተጋላጭ ቤተሰቦች ለሚወጡ ህጻናት ትምህርት መከታተል በእጅጉ አስቸጋሪ ነው፡፡ ህጻናቱ ጨርሶ ላይመዘገቡ ወይም ዘግይተው ትምህርት ሊጀምሩ፣ በመደበኛ መንገድ ትምህርታቸውን ላይከታተሉና ለማጥናት በቂ ጊዜ ላይኖራቸው ይችላል፡፡ ይሄ ደግሞ ለዝቅተኛ የትምህርት ውጤት ይዳርጋቸዋል - ለምሳሌ፡- ዘግይተው ትምህርት በመጀመራቸው ወይም ለቤተሰባቸው ወይም ለራሳቸው መሥራት ስለሚኖርባቸው በዝቅተኛ ውጤት ትምህርታቸውን ያቋርጣሉ፤ ወይም ሊያጠኑ በሚሞክሩበት ምቹ ያልሆነ ከባቢ የተነሳ በፈተና የመውደቅ ዕድላቸው ከፍተኛ ይሆናል (ማጣቀሻ፡- ኢ-እኩልነት)፡፡

በሁሉም ማህበረሰቦች ውስጥ ለህጻናት ወይም ታዳጊዎች ትምህርት፣ ድህነት ከመዋዕለ ህጻናት ትምህርት ጀምሮ መሰናክል ሆኖባቸዋል ተብሏል፡፡ በአንደኛ ደረጃ፣ የት/ቤት የጽህፈት መሳሪያዎች የግል ወጪ በተለይ በዓመቱ የችግር ወቅት (ቅድመ የሰብል አዝመራ ስብሰባ) ቀላል የማይባል ሸክም ነው፡፡ በዚህም የተነሳ በሃረሳው ችግረኛ ህጻናት እስከርቢቶ ከጠፋባቸው ይቀጣሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የማህበረሰብ መዋጮ መርህ፣ ከክፍያ ነጻ ፖሊሲ ጋር አብረው ስለሚተገበሩ፣ ከግማሽ በላይ በሚሆኑ ማህበረሰቦች፣ የሆነ ዓይነት የት/ቤት ክፍያ አይቀሬ ነው፡፡ የድህረ-አንደኛ ደረጃ ትምህርት ለመከታተል፣ ወጪው በእጅጉ ከፍተኛ ሆኗል - ምክንያቱም በአብዛኛው ተማሪዎች፣ ከቤተሰባቸው ርቀው ስለሚኖሩ ነው፡፡

በትምህርት ዕድሎች ረገድ በዘጠኝ በእጅጉ የተለያዩ ማህበረሰቦች ውስጥ በሃብታምና በድሃ ህጻናት መካከል ልዩነቶች (በሥራ ዕድልም እንዲሁ) ተጠቁሟል፡፡ በWIDE ቃለ-ምልልስ የተደረገላቸው መላሾች እንደጠቆሙት፤ ብሩህ፣ ነገር ግን ችግረኛ የሆኑ ተማሪዎች፣ የመንግስት ዩኒቨርሲቲ ለመግባት

የሚያበቃቸው ውጤት አምጥተውም ትምህርታቸውን ሊያቆሙ ይችላሉ፡፡ ቤተሰቦቻቸው በተሻለ የኑሮ ደረጃ ላይ የሆኑ ልጆች ግን ችሎታ ቢኖራቸውም ባይኖራቸውም ትምህርታቸውን ይቀጥላሉ፤ ምክንያቱም ቤተሰቦቻቸው ለግል ትምህርት የመክፈል አቅም ያላቸው በመሆኑ፡፡ ከላይ እንደተገለጸው፤ የተሻለ የኑሮ ደረጃ ከሚመሩ ቤተሰቦች የወጡ ልጆች፤ የመዋዕለ ህጻናት ከመከታተል የሚገኙ ጠቀሜታዎችን የማጣጣም የላቀ ዕድል እንዳላቸው የሚያሳዩ ማስረጃዎችም አሉ፡፡

ትምህርት የመማር ዕድላቸው አነስተኛ የሆነና ትምህርታቸውን በጊዜ የማቆም ወይም በተደጋጋሚ የማቋረጥ ከፍተኛ ዕድል ያላቸው ህጻናት፣ ለአደጋ ተጋላጭ በሆኑ ቡድኖች ውስጥ የሚፈረጁ ሲሆኑ ከእነሱም መካከል በዕድሜ የገፉ፣በህጻን ወይም በአንድ ወላጅ የሚመሩ ቤተሰቦች፣ ወላጆቻቸውን በሞት ያጡ፣ የእንጀራ ልጆች፣ የጉልበት ሥራ ላይ የተሰማሩ ሰዎች ልጆች፣ ቤተሰቦቻቸው ለገቢ የሚያሰሯቸው ወይም የቤተሰቡን የገቢ ጫና እንዲያቃልሉ የተገደዱ ህጻናት ይገኙባቸዋል፡፡ እኒህ ቤተሰቦች፣ ማን ትምህርት ቤት እንደሚሄድ ለመወሰን፣ ከህጻናቱ መካከል መምረጥ ይኖርባቸዋል፡፡

በበርካታ ማህበረሰቦች፣ ከወጪ ጋር የተዛመዱ ችግሮችን ለመፍታት የተወሰዱ እርምጃዎች አሉ፡፡ ነገር ግን በቂ የሚባሉ አይደሉም፡፡ መንግስት ለችግረኛ ህጻናት የት/ቤት ቁሳቁሶችን እንደሚሰጥ በአምስት ማህበረሰቦች ብቻ ተጠቅሷል፡፡ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት፣ በዘጠኝ ማህበረሰቦች ውስጥ ድጋፍ እንደሚሰጥ ቢገለጽም በሁለቱ የአገልግሎት ጊዜውን ጨርሷል፡፡ ይበልጥ ጉልህ እንቅስቃሴ የሚያደርገው (ያለ ግልጽ ምክንያት) በሦስት ማህበረሰቦች ብቻ ነው፡፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ በኑሮ የተደላደሉ ግለሰቦች፣ ነገዶች፣ እድሮችና ቤ/ክርስትያናት ጥቂት ህጻናትን ይረዳሉ፡፡ የምግብ ዋስትና ድጋፍ ሃብቶችን ለተረጂ ቤተሰቦች ማስተላለፉ፣ በአምስት ማህበረሰቦች ረድቷል ተብሏል፡፡ ስድስት ማህበረሰቦች (ሁለቱን የምስራቅ ትግራይ አካባቢዎች ጨምሮ) የየራሳቸውን አካባቢ በቀል የድጋፍ ሥርዓት የመሰረቱ ሲሆን በአብዛኛው የችግረኛ ቤተሰብ ልጆችን ከሙሉ ወይም ከፊል የት/ቤት ክፍያ ነጻ ያደርጋሉ፡፡

በአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ትምህርትን እያስተጓጎሉ መከታተል በስፋት የተለመደ ሲሆን ለዚህም ምክንያቱ ከማህበረሰብም ከቤተሰብም ጋር የተያያዘ ነው፡፡ (ለምሳሌ፡- የገበያ ቀናት፣ በማህበረሰብ ደረጃ የስደት መስፋፋት ወይም መጨመር፣ የቤተሰብን ገቢ ለመደጎም መሥራት፣ ድህነት ወይም በቤተሰብ ደረጃ የሚከሰት ዱብዳ አደጋ፣ ረሃብ) በርካታ ትምህርት ከጊዜ ጊዜ አቋርጦ የመጀመር ሂደቶችም ተስተውለዋል፤ ማለትም ህጻናት/ወጣቶች ከት/ቤት ትምህርት አቋርጠው ከወጡ ከረዥም ጊዜ በኋላ (አንዳንዴም ከብዙ ዓመታት)ተመልሰው የሚገቡበት ሁኔታ፡፡

ትምህርትን እያስተጓጎሉ መከታተል፤ ህጻናት/ወጣቶች ትምህርትንና ሥራን አጣምረው ለማስኬድ ሲሞክሩ፣ ከሚገጥሟቸው ችግሮች የተነሳም ሊከሰት ይችላል፡፡ አብዛኞቹ ልጆች በቤተሰብ እርሻ ላይ ወይም በቤት ውስጥ ይሰራሉ - ይሄ በኢትዮጵያ ነባር ማህበራዊ ልማድ ነው፡፡ በተጨማሪም በ11 ማህበረሰቦች ውስጥ ህጻናት/ወጣቶች ለቤተሰባቸው፣ ለራሳቸው ወይም ለሁለቱም ገቢ ለማግኘት ሲሉ ሥራ እንደሚሰሩ ተጠቅሷል፡፡ ይሄ በአብዛኛው በችግር አስገዳጅነት የሚወሰን ነው፡፡ (ብዙ ጊዜም የህጻኑን ትምህርት ለመደገፍ ይውላል) ምንም እንኳን በጥቂት አጋጣሚዎች የምርጫ ጉዳይ ቢሆንም፡፡ ህጻናት የሥራ ልምድን የመሳሰሉ የረዥም ጊዜ ጠቀሜታዎችን ለማግኘት በሚል በሥራ ላይ እንደሚሰማሩ ተናግረዋል - እንደ በጎ ቅድመ ጥንቃቄ ማለት ነው፡፡ አንዳንድ የሥራ ዓይነቶች፣ ከትምህርት ጋር አጣምሮ ለማስኬድ ቀለል የሚሉ ሲሆን ሁሉም ህጻናት ግን የሚሰማሩበትን ሥራ

የመምረጥ ዕድል አያገኙም፡፡ የቤት ውስጥ ሥራዎች አሁንም የልጃገረዶችና የወጣት ሴቶች ዕዳ መሆናቸው አልቀረም (ማጣቀሻ፡- ወጣቶች፤ እና ሴቶች)፡፡ ክፍያ ካለው ሥራም የበለጠ ሸክም ሊሆን ይችላል፡፡ አንዲት ልጃገረድ ከኮርማርገፍያ (ሰሜን ሸዋ) እንደገለጸችው ከት/ቤት የመቅረት ችግርም ያስከትላል፤ ለዚያውም ያለምንም የገቢ ማካካሻ፡፡

በዚህም የተነሳ በ2010 - 13 WIDE በተከታተላቸው ማህበረሰቦች፤ ከት/ቤት ውጭ የሆኑ ህጻናት (ዘግይቶ ጀማሪዎች፣ ያቋረጡ ወይም ከእነአካቴው ያልገቡ) እንዲሁም በመደበኛነት የማይከታተሉ የማይገኙ፣ መሰረታዊ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ፖሊሲን ለማስፈጸም ተግዳሮት መሆናቸው አልቀረም፡፡ የተለያዩ ውጣ ውረድ የበዛባቸው የትምህርት ጉዞዎች፤ የቤተሰብ ውሳኔዎች፣ የግለሰብ ሁኔታዎች እንዲሁም ህጻናቱ/ወጣቶቹ በራሳቸው የሚወስኗቸው ውሳኔዎች ጥምር ውጤቶች ናቸው፡፡

ከትምህርት የመቅረት ችግሮችን ለመፍታት የተለያዩ ጥረቶችና እርምጃዎች መደረጋቸው ተጠቅሷል፡፡ በማህበረሰቡ ዓይነት ላይ ተሞርኩዞ፤ የት/ቤት ሰራተኞች፣ የቀበሌ ሃላፊዎች፣ ልዩ ኮሚቴዎች፣ የገጠው ፓርቲ ሴሎች፣ የልማት ቡድኖችና ነለ5 አደረጃጀቶች፤ ወላጆችን ወይም ተማሪዎችን በጊዜ ት/ቤት እንዲመዘገቡና ትምህርታቸውን ሳያስተጓጉሉ እንዲከታተሉ የማሳመን ሃላፊነት ተጥሎባቸው ነበር፡፡ እነዚህ ጥረቶች ምን ያህል ውጤታማ እንደሆኑ ግልጽ አይደለም፡፡ በአንዳንድ ማህበረሰቦች፣ የተከበሩ ዕውቅ ግለሰቦች ሚናቸውን ተጫውተዋል (ለምሳሌ፡- በግራር በእጅጉ የተከበሩ የጉራጌ ጎሳ መሪ፣ በሉቃ/ጸማይ የአገር ሽማግሌዎች፣ በአዬሌ ኬኬ/ምስራቅ ሀረርጌ የሃይማኖት መሪዎች)

በስድስት ማህበረሰቦች፣ በከፍተኛ የሰብል ምርት መሰብሰቢያ (አዝመራ) ወቅት፣ ት/ቤቶች መርሃ ግብራቸውን በማሻሻል ለሳምንት ወይም ሁለት ሳምንት ትምህርት ይዘጋሉ፡፡ ኋላ ላይ በሳምንቱ መጨረሻ ቀናት ላይ የማካካሻ ትምህርት ይሠጣሉ፡፡ ይሄ ግን ለምሳሌ፡- ረዘም ያለ የቡና መልቀሚያ ጊዜ በሚያስፈልጋቸው የሶሞዶና አዳዶ አካባቢዎች ወይም በመስኖ የሚለማ ጫት፣ በተደጋጋሚ በሚሰበሰብበት አዬሌ ኬኬ ሊሰራ አይችልም፡፡ ማንኛውም የመርሃ ግብር ማስተካከያ፣ በዓመቱ የተወሰነ ወቅት ላይ የሚሰጡ የመምህራን "አቅም ማጎልበቻ ትምህርቶች"ን ማቻቻል ይኖርባቸዋል፡፡

<u>ሁሉን አቀፍ ትምህርት - ለሁሉን አቀፍ ዕድገት</u>

ሁሉን አቀፍ ትምህርት፤ ሁሉን አቀፍ ዕድገትን እውን ማድረጊያ ጥርጊያ መንገድ ነው፤ የሚለው ቁልፍ የመንግስት ግብ ነው፡፡ ሆኖም በተለያዩ ማህበረሰቦችና የማህበረ ኢኮኖሚያዊ የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል የተፈጠሩትን የኑሮ ደረጃ ልዩነቶች ምላሽ ለመሥጠት የበለጠ ፈታኝ ሆኗል፡፡ ለምን ቢሉ --- የገጠር ኢትዮጵያ ሰፊ ብዝሃነት ያለው ህብረተሰብ ልዩነቶች ይበልጥ እየጎሉ መጥተዋል (ማጣቀሻ፡- ኢ-እኩልነት)፡፡ በዚህ ድባብ ውስጥ ለሁሉም አንድ ወጥ የአካሄድ አቅጣጫ ይበቃል ተብሎ አይታሰብም፡፡ ከአካባቢያዊ አውድና ግለሰባዊ ሁኔታ ጋር እንደ አመቺነቱ ለሚዛመዱ የተለያዩ አማራጮች ትኩረት ሊሰጥ ይገባል፡፡

የ5ኛው ትምህርት ዘርፍ ልማት ዕቅድ (ESDP5) የኑሮ ደረጃ ልዩነቶችን ለመፍታት ያለሙ እርምጃዎችን አካትቶ ይዟል (ለታዳጊ ክልሎችና ለአርብቶአደር፣ ለከፊል አርብቶአደር እንዲሁም ተበታትነው ለሰፈሩና ለድንገተኛ አደጋ ለተጋለጡ አካባቢዎች - ልዩ ድጋፍ፤ "ለአደጋ ተጋላጭ ለሆኑ፣ ለድሃና ለተዘነጉ ህጻናት"-የከፍተኛ የአንደኛ ደረጃና የሁለተኛ ደረጃ ነጻ የትምህርት ዕድል፤ ድሃና

ዝቅተኛ ገቢ ካለው ቤተሰብ ለወጡ ህጻናት - የትምህርት መሣሪያዎች፣ የተማሪዎች ምገባና የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ) እነዚህን እርምጃዎች ለማጎልበት መንግስት ለተገለሉ አካባቢዎችና ት/ቤቶች ተጨማሪ ድጋፍና አቅም ለመስጠት የታለሙ ፈርጀ-ብዙ አማራጮችን ከግምት ውስጥ ሊያስገባ ይችላል፡፡ ከእነዚህም መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡-

- ችግር ለበረታባቸው ት/ቤቶች ዳጎስ ያለ የገንዘብ ድጋፍ መስጠት፡- ወቅታዊው፣ የተመዘገቡ ተማሪዎች ብዛት ላይ የተመሰረተ የድጋፍ አሰጣጥ ቀመር፣ አካባቢያዊ እውነታዎችን ከግምት ውስጥ ያስገባ አይደለም፤ ይህም ከተማሪዎቹ ቁጥር የበለጠ ጥራት ያለው ትምህርት መስጠት የቱን ያህል አስቸጋሪ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ አነስተኛ/ርቀው የተነጠሉ ት/ቤቶች፣ ድህነት በበረታባቸው አካባቢዎች የሚገኙ ወይም የተለየ ችግር ያለባቸው ት/ቤቶች (ለምሳሌ፡- የአርብቶአደር ህይወት) ከፍተኛ ፈተናዎችን ይጋፈጣሉ፡፡ ነገር ግን በተሻለ አቋም ላይ ከሚገኙት/ጠንካራ ትስስር ካላቸው እንዲሁም በኑሮ የተደራጁ ማህበረሰቦች ውስጥ ከሚገኙ ት/ቤቶች ጋር ተመሳሳይ የሆነ ድጋፍ ነው የሚያገኙት፡፡ ስለዚህ ቀመሩን ማሻሻል የግድ ይላል፡፡ ለምሳሌ፡- የተገለሉ ት/ቤቶች የነፍስ ወከፍ ድርሻን ማሳደግ የሚገጥማቸውን ተጨማሪ ፈተናዎች ለማሸነፍ ያግዛቸዋል፡፡
- የበለጠ ፈታኝ በሆኑ አካባቢዎች ለሚሰሩ መምህራን ተጨማሪ ድጋፍና ማበረታቻዎች ማድረግ፡- በ5ኛው ትምህርት ዘርፍ ልማት ዕቅድ (ESDP5) ትንተና መሰረት፤ የመምህራንን ክህሎት በማጎልበት ላይ ማተኮር በቂ አይደለም፤ ይሄም "የመምህርነት ሙያ በምርጫ የሚገባበት ሙያ እንዲሆን የሚያደርግ ስትራቴጂ" መቅረጽን ይጠይቃል - "በመምህራን ፍላጎቶች ላይ ትኩረት" በማድረግ፡፡
- የት/ቤት ምገባ/ማበረታቻ ፕሮግራሞች፡- የምግብ ዋስትና ባልተረጋገጠባቸው አካባቢዎችና ተደራሽነት ለሌላቸው ማህበረሰቦች፡፡

ትምህርትን የበለጠ ሁሉን አቀፍ እንዲሆን ማድረግ፣ አንዳንድ ህጻናትን/ወጣቶችን እንዳይማሩ የሚያግዱ የተለያዩ ግለሰባዊ ማነቆዎችን ለመፍታት ትኩረት መስጠትንም ይጠይቃል፡፡ መንግስት የገንዘብ ማነቆዎችን ለመፍታት በገንዘብና በዓይነት የሚደረጉ የድጋፍ ዓይነቶችን ከግንዛቤ ውስጥ ሊያስገባ ይችላል፡፡ ለምሳሌ፡-

- የመንግስት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋም ወይም ዩኒቨርሲቲ ለመግባት ብቁ ለሆኑ ግና ለትራንስፖርት፣ መጻህፍት ወዘተ ወጪ ለመሸፈን አቅም ለሌላቸው ወጣቶች ከሁለተኛ ደረጃ በላይ ነጻ የትምህርት ዕድል መስጠት፡፡
- ድሃ/ተጋላጭ ቤተሰቦች፣ ከክፍያና ሌሎች መዋጮዎች (የዓይነትም ሆነ የጉልበትን ጨምሮ) ነጻ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤ ለአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች፤ ለዚህም ለት/ቤቶችና ማህበረሰቦች፣ ልዩ መመሪያ ማውጣት፡፡ ልክ በመንግስት የጤና ወጪ ፕሮግራም እንደሚደረገው ሁሉ ት/ቤቶች ላጡት ገቢ፣ ዳጎስ ባለ የገንዘብ ድጋፍ፣መካካስ ይገባቸዋል፡፡

ትምህርትን ከአካባቢያዊ ሁኔታ ጋር ተጣጥሞ ለተዛመደ መፍትሄ ይበልጥ ተስማሚና ክፍት ማድረግ፣ እነዚህን የገንዘብ ድጋፍ እርምጃዎች ያጎለብታቸዋል፤ በተለይ በህጻናት/ችግረኛ ወጣቶች/ተጋላጭ ቤተሰብ ያላቸው ዘንድ በስፋት የተለመዱትን ቀጥተኛ ያልሆኑ (በማስተጓጎልና በማቋረጥ የታጀቡ)

የትምህርት ጉዞዎች ለማስተናገድ ዕድል በመስጠት፡፡ ከግንዛቤ ውስጥ የሚገቡ አማራጮች ተከታዮቹን ያካትታሉ፡-

- የማህበረሰቡ ምርጫ በሆኑባቸው አካባቢዎች፣ የፈረቃ ትምህርትን መቀጠል እንዲሁም የህጻናት ቡድኖችን በግልጽ ጠቃሚ በሚሆኑባቸው ቦታዎች አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት መስጠት (ለምሳሌ፡- በግራር ለሠራተኛ ህጻናት)፤
- ት/ቤቶች የትምህርት መርሃ ግብራቸውን፣ ከማህበረሰቡ ወቅት-ተኮር/ሳምንታዊ ልማዶች (ለምሳሌ፡- ዋና የሰብል ምርት መሰብሰቢያ ወቅትና ትላልቅ የገበያ ቀናት) ጋር አጣጥመው እንዲያሻሽሉት ማበረታታት፤
- የማታ ክፍለ ጊዜ ትምህርቶችን በሁሉም ደረጃዎች የበለጠ ማስፋፋት እንዲሁም የቀንና የማታ ትምህርት ሽግግሮችን ማቅለል፤
- የርቀት ትምህርት ተደራሽነትን በገንዘብ መደገፍ/ማስፋፋት (ተደራሽ ባልሆኑ አካባቢዎች አገልግሎትን ለማስፋፋት፣ በመረጃና በዘመነኛ የመገናኛ ቴክኖሎጂ የታገዘ መፍትሄ፣ እንደ ሰፊ የመንግስት-መር እንቅስቃሴ አካል መያዝ (ማጣቀሻ፡- የገጠር ከተሜነት መስፋፋት)፡፡
- የትምህርት ኮርሶችን ማሻሻል እንዲሁም አስተዳደራዊ ደንቦችን ማቅለል፤ ይሄም ወጣቶች ሥራና ትምህርትን በቀላሉ ማፈራረቅ ያስችላቸዋል፡፡

ይህ የመጨረሻው የእርምጃዎች ዝርዝር፤ በተለይ በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና እንዲሁም በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ሊተገበር የሚችል ሲሆን የሁለተኛ ደረጃና የአንደኛ ደረጃም ተማሪዎች ጭምር፣ ከዓመታት ማቋረጥ በኋላ ተመልሰው ት/ቤት መግባት የሚችሉበትን ሁኔታ ቀለል ማድረግም ትልቅ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው፡፡ ይሄ የቀድሞ ትምህርታቸውን ያለ ጥቅም ያስቀሩ የነበሩ አያሌ ወጣቶችን ዳግም ወደ ት/ቤት እንዲገቡ ለመሳብ የሚያግዝ ሲሆን ወጣት ስደተኞች ወይም ተመላሾችም (ማጣቀሻ፡- ፍልሰት) የትምህርት ስኬታቸውን (በስደት ወቅት ወይም በኋላ) ለማበልጸግ ያስችላቸዋል፡፡

እኒህ ብዙዎቹ እርምጃዎች፣ የኢትዮጵያ መንግስት ፖሊሲ አካል ሆነዋል፡፡ ለምሳሌ፣ የትምህርት ሚኒስቴር "ሰማያዊ መጽሐፍ" (2002)፤ ት/ቤቶች፣ የትምህርት መርሃ ግብራቸውን ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥመው እንዲያሻሽሉ እንዲሁም የወረዳ ሃላፊዎች ለት/ቤቶች የገንዘብ ድጋፍ ለመመደብ የሚያስችል መስፈርት እንዲያወጡ ያበረታታል፡፡ ሆኖም የትምህርት ሃላፊዎች እንዲህ ያሉ እርምጃዎችን ለመተግበር ተጨማሪ ድጋፍ ሊፈልጉ ይችላሉ፡፡ መንግስት በትምህርት ሥርዓቱ ውስጥ የላቀ ተለዋዋጭነት እንዴት የተሻለ ትምህርትን እንደሚያጠናክር የሚያሳይ ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን - እንደ ከፍተኛ የጥራት መመዘኛ ሊቀምር ይችላል ::

<u>የጾታ እኩልነት - የመሻሻል ውጤቶችና ቀርነቶች</u>

በአብዛኞቹ ማህበረሰቦች የመጣው ለውጥ በግልጽ የሚታይ ሲሆን ባለፉት አሥር ዓመታት፣ ለልጃገረዶች ትምህርት የነበረው አመለካከት በከፍተኛ ሁኔታ ተሻሽሏል ተብሏል፡፡ ነገር ግን ከማህበረሰብ ማህበረሰብ ትልቅ ልዩነቶች መታየታቸው አልቀረም፡፡ ለምሳሌ በ1995፣ ት/ቤት ባልነበረው ጌብለን፤ በ2010 ከአካባቢው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎችና ተመራቂዎች መካከል ልጃገረዶች ይገኙበታል፡፡ በሌላ በኩል በቆሮደጋጋ፣ በዚያው ዓመት፣ 10ኛ ክፍል ያጠናቀቀች ልጃገረድ ስለመኖሯ ማንም የሚያውቅ የለም፡፡ በአጠቃላይ፤ በአራት ማህበረሰቦች (ሁለቱን አርብቶአደሮች ጨምሮ)፣ ልጃገረዶች አሁንም አያሌ ፈተናዎችን መጋፈጣቸው አልቀረም፡፡ በአራቱ በጣም የተለያዩ የአማራ ብሄረሰቦች፣ ሁኔታው ቀላል አልነበረም፡፡ በሁለቱ የምስራቅ ትግራይና በሁለቱ ከተማ ዳርቻ በሚገኙ ማህበረሰቦች፣ የልጃገረዶች ትምህርት ከፍተኛ መሻሻል አሳይቷል፡፡

በብዙ ማህበረሰቦች፣ የት/ቤቶች ቅርብ መሆን (የአንደኛ ደረጃና በአንዳንድ ሁኔታዎች ከ9ኛ-10ኛ) እንዲሁም የመንግስት አጠቃላይ የማበረታቻ ድጋፍ ፖሊሲ፣ እገዛ አድርገዋል፡፡ የልጃገረዶችን ትምህርት ለማሻሻል ታልመው ከተወሰዱ የተለዩ እርምጃዎች መካከል፡- ልዩ ኮሚቴዎች ማቋቋም፣ የተሞክሮ ልውውጥ ፕሮግራም ማዘጋጀት፣ ልዩ የትምህርት እገዛ፣ የወር አበባ ማየት ለጀመሩ ልጃገረዶች፣ ድጋፍ ማድረግና ለቤተሰቦች ማትጊያ መስጠት (ለምሳሌ በሉቃ፣ ከት/ቤት ለማይቀሩ ልጃገረዶች ዘይት ይሰጣል) ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በእርግጥ እንዲህ ያለው ማበረታቻ በአንድ ወይም ጥቂት ማህበረሰቦች ውስጥ ብቻ ነው የታየው፡፡ ትልቅ ድጋፍ የታየው በአዜ ዴቦአ ብቻ ሲሆን በጾታ እኩልነት ላይ ሰፊ እንቅስቃሴ የሚያደርግ አንድ የከምባታ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት፤ ጠና ያሉ ልጃገረዶችና ወጣት ሴቶች ላይ አተኩሮ ሰፊ ድጋፍ ይሰጣል፡፡ ያለ ዕድሜ ጋብቻን በመቃወም፣ በስኬት ታሪኮች የታጀቡ ንቅናቄዎች በስፋት ተደርገዋል (አስተማሪዎች ቤተሰቦችን አንቅተዋል፤ ከድርጊታቸው አስቁመዋል፤ ልጃገረዶች ለፖሊስ ወይም ለወረዳው የሴቶች ቢሮ አመልክተዋል)፡፡ የመከላከል - ማምለጫ ስልቶችም ታይተዋል፡፡ ለምሳሌ፡- በገልቻ፣ በከረምት ት/ቤት ሲዘጋ፣ ልጃገረዶችን ባል የሚያጋቡ ቤተሰቦች (ማጣቀሻ፡- ወጣቶች)፡፡

የልጃገረዶች ትምህርት፣ ነባር ማህበረሰባዊ ልማዶችንና ድርጊቶችን በተለያዩ መንገዶች ለመጋፈጥ አግዟል፡፡ የተማሩ ልጃገረዶች በቤት ውስጥ ሥራ የሚፈጠር ጫናን በጀ ብለው አይቀበሉም ተብሏል፡፡ ከፈቃዳቸው ውጭ የሚመቻች ጋብቻንና የሴት ልጅ ግርዛትንም ይቃወማሉ (ለምሳሌ በአዜ ዴቦአ)፡፡ የተማሩ ሴቶች፤ የትዳር አጋራቸውን ራሳቸው እንዲመርጡ ወይም ከጋብቻ በፊት መተዳደሪያ ገቢ እንዲኖራቸውም ይሻሉ፡፡ እኒህ ዓይነቶቹ ተመራጭ ሚስቶች ይሆናሉ ተብሏል፤ ምክንያቱም የትዳር ህይወታቸውን ለማሻሻል፣ ባላቸውን የመርዳት የተሻለ አቅም ይኖራቸዋል፡፡ ሴቶች በህብረተሰቡ ውስጥ የነበራቸውን ቦታና ሚና በተመለከተ ለታየው የግንዛቤ ለውጥ አስተዋጽኦ ካደረጉ ጉዳዮች አንዱ የልጃገረዶች የትምህርት ስኬት ነው ተብሏል፡፡ ለማህበረሰቡ አርአያ የሆኑ የተማሩ ሠራተኛ ሴቶች፤ አንዳንዴ ከድሃ ቤተሰብ የወጡ ቢሆንም ክብርና አድናቆት ያገኛሉ፡፡ ልጃገረዶች ትምህርት "ዘመናዊ ህይወት"ን እውን ማድረጊያ መንገድ እንደሆነ በማሰብ ያልሙታል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ብዙዎቹ፣ ገበሬ ማግባት እንደማይፈልጉ ተናግረዋል (ማጣቀሻ፡- ሴቶች)፡፡

ወጣት ወንዶችንም ይሸው ተመሳሳይ ምክንያቶች ተግዳሮት ሆኖባቸዋል (አይሳካልንም፣ ሥራ አናገኝም የሚል ፍራቻና ለስደት መማለል) እንዲሁም የወግ አጥባቂዎች ልጃገረዶችን የማስተማር ፋይዳውን መሞገት እና ሌሎች በርካታ ተጨማሪ ፈተናዎች፡፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ ታዳጊ ወንዶች ይበልጥ ለእርሻ ሥራ ትምህርታቸውን የሚያቋርጡ ሲሆን ልጃገረዶች ተጨማሪውን የት/ቤት ወይም የቤት ውስጥ ሥራዎች ይጋፈጣሉ፤ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በቤተሰብ ውስጥ ዱብዕዳ አደጋ ቢከሰት፣ ከትምህርት ጋር ከእነአካቴው ለመቆራረጥ የበለጠ ተጋላጭ ይመስላሉ፡፡ የወር አበባ ማየት የጀመሩ ልጃገረዶች፣ በት/ቤት የውሃ እጦት፣ በመጸዳጃ ቤት ችግርና ድጋፍ ያለማግኘት የተነሳ ከትምህርት ገበታቸው ይርቃሉ፡፡ ያለ ዕድሜ ጋብቻ፣ በተለይ ድህነት ለበረታባቸው ታዳጊ ሴቶች፣ አሁንም ከባድ ፈተና መሆኑ አልቀረም (ማጣቀሻ፡- ወጣቶች፤ ኢ-እኩልነት፤ እና እናቶችና ጨቅላ ህጻናት)፡፡ ያረገዙ ልጃገረዶች፣ ሙሉ በሙሉ ትምህርት ያቋርጣሉ፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ በዝቅተኛ ክፍሎች፣ የልጃገረዶች ተሳትፎ ጥሩ ቢሆንም፣ ከፍ እያለ ሲሄድ ግን ቀስ በቀስ ይቀንሳል - በአንዳንድ ማህበረሰቦች ደግሞ በተለየ ፍጥነት ይቀንሳል፡፡

ሆኖም ለውጥ እየመጣ መሆኑን የሚያጠናክሩ ሁኔታዎች ተከስተዋል፡፡ በጥቂት የተለያየ ባህልና አኗኗር ባላቸው ማህበረሰቦች ውስጥ (ቆሮደጋጋ/አርሲ፣ አዴሌ ኬኬ/ምስራቅ ሐረርጌ፣ ሹምሽሃ/ሰሜን ወሎና ዶአማ/ጋሞ) ታዳጊ ሴቶች ከጋብቻ ወይም ከወሊድ በኋላ ያቋረጡትን ትምህርት ለመቀጠል ወደ ት/ቤት ተመልሰው ገብተዋል፡፡ እንዲህ ያሉ ክስተቶች እምብዛም አያጋጥሙም፡፡ ነገር ግን በአብዛኛው፣ ቢያንስ የቤተሰባቸው ጥቂት አባላት ድጋፍ ያላቸው፣ የእነዚህ ታዳጊ ሴቶች ቁርጠኝነት፣ ተስፋ ፈንጣቂ ምልክት ነው፡፡

<u>መሻሻልን ማነልበት. . .</u>

በትምህርት የጾታ እኩልነትን የማስፈን ተጨማሪ መሻሻሎች በ5ኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም ESDP5 አጀንዳ ውስጥ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቷቸዋል፡፡ ጾታ ተኮር ጥቃትና ማስፈራራትን ለመቀነስ የት/ቤቶችን የሥነምግባር ደንብ መከታተልና ማስፈጸም፣ በሁሉም ት/ቤቶች ንጹህ የመጠጥ ውሃና በቂ፣ ጾታ-ተኮር፣ የንጽህና መጠበቂያ አገልግሎቶች እንዲሁም የዩኒቨርሲቲና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተማሪዎች የጤና ምክር የሚያገኙባቸው የተለዩ ክፍሎች መኖራቸውን ማረጋገጥን በመሳሰሉ እርምጃዎች፡፡ ከዚህ በታች የቀረቡት ሃሳቦች ከዚህ የጥናት ጽሁፍ ትንተና እንዲሁም (ማጣቀሻ፡- ወጣቶች፤ እናቶችና ጨቅላ ህጻናት፤ እና ሴቶች) የወጡ ሲሆን እነዚህን እርምጃዎች ይበልጥ ለማበርታት ወይም ለማበልጸግ ያለሙ ናቸው፡፡

በመጀመሪያ፤ ያለ ዕድሜ ጋብቻን ለመከላከል የታቀደ ነገር የለም፤ በተጨማሪም በ5ኛው የትምህርት ዘርፍ ዕድገት ፕሮግራም (ESDP5) ጨርሶ አልተጠቀሰም፡፡ የተጠቀሱትን እርምጃዎች ለማጠናከር ዕድል ይኖር ይሆናል፡፡ ለምሳሌ፡- ከሰሩትም ሆነ ካልሰሩት ተሞክሮዎች ይበልጥ በተደራጀ ሁኔታ መማር፡፡ ከንጹህ ውሃና በቂ የመጸዳጃ ክፍሎች ጋር የተዛመዱ የ5ኛው ትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም (ESDP5) እርምጃዎችን ለማበልጸግ፣ የወር አበባ ለሚያዩ ልጃገረዶች የንጽህና መጠበቂያዎችን ተደራሽ ማድረግና ስለአጠቃቀማቸው ምክር መስጠትን የተመለከቱ በጥቅል የተቀመጡ እርምጃዎች ከግንዛቤ ውስጥ መግባት ይኖርባቸዋል፡፡

በርካታ ተደጋጋፊ እርምጃዎች የወጣት ሴቶችን፣ የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት የመከታተል ዕድል፣ የበለጠ ሊያሳድጉት ይችላሉ፡፡ በተለይም፤ መንግስት የሚከተሉትን ከግንዛቤ ውስጥ ሊያስገባ ይችላል፡-

- ለተማሪዎች (ለወንዶችም ለሴቶችም) ተመጣጣኝ፣ ዕድሜና ባህልን ከግምት ውስጥ ያስገባ የሥነ ጾታ ምክር መለገስ፣ እንዲሁም ስለ ወሊድ መቆጣጠሪያ ምክርና የት እንደሚገኝ መረጃ መስጠት፣ ወጣት ሴቶችን ካልተፈለገ እርግዝና የተሻለ ለመጠበቅ፣ ለአስተማሪዎችና ለጤና ሠራተኞች በቂ መመሪያና ማጣቀሻ መጻህፍት፤
- ት/ቤቶች ያገቡ ወጣት ሴቶችና ያላገቡ እናቶችን መልሰው እንዲቀበሉ (እንዲያስገቡ) መመሪያ ማወጣት - ያለዕድሜ ጋብቻና ያልተፈለገ እርግዝና፣ ለመጪዎቹ ጥቂት ጊዜያት አብሮን የሚዘልቅ እውነታ መሆኑን በመገንዘብ፡፡ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወጣት ሴቶችን ከት/ቤት ውጭ ማድረግ ፋይዳ ቢስ ማዕቀብ ሲሆን ለሌሎች "መጥፎ ተጽዕኖ" ይሆናሉ የሚለውም የተሳሳተ ሃሳብ ነው፡፡ ምክንያቱም አብዛኛውን ጊዜ፣ ሌሎች ተማሪዎች የት/ቤት ጓደኛቸው፣ ወደ ት/ቤት ተመልሳ ባትመጣም እንኳን የሆነችውን ያውቃሉ፡፡
- ት/ቤቶች የህጻናት መንከባከብያ ማዕከላትን እንዲያቋቁሙ ማበረታታት- ትላልቅ እህቶችና ወጣት እናቶች ትምህርታቸውን መከታተል እንዲችሉ- ለምሳሌ፡- ከፍ ያለ የገንዘብ ድጋፍ በመስጠት፣ ማዕከላቱ ያላቸው ት/ቤቶች እንዲያስተዳድሯቸው መርዳት፡፡
- በአካባቢ ያሉ የመንግስት የሥራ መደቦችን ለሴቶች ቅድሚያ መስጠት- ለምሳሌ፤ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች እንዲሁም መምህራን፣ የግብርና የልማት ሠራተኞች የእንስሳት ሃኪሞች፣ የቀበሌ ሥራ አስኪያጆች ወዘተ-- ለማህበረሰቡ የባለሙያ ሴቶች አርአያ እንዲሆኑና የመንግስትን የሴቶችን ትምህርት የማስፋፋት እርምጃዎች ለማጎልበት፡፡

Mother and infant in Korodegaga

የእናቶችና የጨቅላዎች ጤንነት

በኢትዮጵያ የገጠር አካባቢዎች በእናቶችና በጨቅላ ህጻናት ጤንነትና ደህንነት ዙሪያ የታዩ ለውጦች (2003-13)

WIDE የውይይት መነሻ አጭር መግለጫ ቁ.5/...10

ዋና ዋና - ከWIDE የጥናት መረጃዎች

- ከእርግዝና ጀምሮ፣ ጨቅላ ሕፃን እስኪጠና ድረስ ያለው ልዩ ጊዜ፣ ለ15 ወራት ይዘልቃል። እናትና ጨቅላ፣ በዚህ ወቅት በርካታ አደጋዎች ይገጥሟቸዋል። አደጋዎቹ ሕይወትን ሊያሳጡ፤ ወይም ቶሎ ለማይድን (ለቁራኛ) የጤና ጠንቅ ሊዳርጉ ይችላሉ። በገጠር ማኅበረሰቦች ውስጥ፣ በእናቶችና በጨቅላ ሕፃናት ጤንነትና ደህንነት መስክ፣ ተጠቃሽ የመሻሻል ለውጦች እንደተመዘገቡ፣ በWIDE የተደራጁት የ2003 እና የ2010/13 የጥናት መረጃዎች፣ በንፅፅር ያሳያሉ። ለውጦቹም፣ በመንግስት መሪነት ከሚካሄዱ ፈርጀ ብዙ የማዘመን እንቅስቃሴዎች ጋር ይያያዛሉ።
- ይሁን እንጂ፣ እናትና ጨቅላ፣ በ2010/13 ጭምር፣ ከበርካታ አደጋዎች ጋር መጋፈጣቸው አልቀረም። በተለይ፣ በሩቅ ቦታና በዝናብ አጠር አካባቢ የሚኖሩ ሴቶች፣ በድህነት የሚቸገሩና አባወራ በሌለበት ቤተሰብ ውስጥ ያሉ ሴቶች፣ እንዲሁም ታዳጊ ወጣት ሴቶች ላይ አደጋው ይበረታል። አደጋን የሚያባብሱ ሌሎች ገባር ሰበቦችም አሉ፤ ከእነዚህም መካከል፡- ከዓመቱ ወቅቶች ጋር የሚፈራረቅ ጫና፣ የመጠጥ ውኃ የጥራት ጉድለትና እጥረት፣ እንዲሁም የሴቶች የስራ ሸክም ተጠቃሾች ናቸው።
- ከቅድመ እርግዝና ክስተቶች ጋር የተዛመዱ አደጋዎች፡- WIDE የሚከታተላቸው ሃያዎቹ ማኅበረሰቦች፣ የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎችን ለማስፋፋት፤ የሴት ልጅ ግርዛትን፣ የወሲብ ጥቃትንና ጠለፋን ለመቀነስ፤ እንዲሁም የጋብቻ የእድሜ ወለልን ለመገደብ የተካሄዱ የለውጥ እንቅስቃሴዎችን አስተናግደዋል። እንደየአካባቢው የባህል ሁኔታም፤ የለውጥ እንቅስቃሴዎችን

---

[1] ይህ አጭር የጥናት መግለጫ፤ በWIDE የውይይት መነሻ አጭር የጥናት መግለጫዎች ሁለተኛ ጥራዝ (ስብስብ) ውስጥ ከተካተቱት አስር መግለጫዎች አንዱ ነው፡፡ መግለጫው፤ በፊሊፓ ቤቫን የተዘጋጀ ሲሆን በሄለን አንደሚካኤል ተገምግሟል፡፡ አዘጋጅዋ፤ መግለጫዎቹ ይሰናዱ ዘንድ በገንዘብ ለደገፉት ለእንግሊዝ ዓለም አቀፍ የልማት ተቋም፣ ለአይሪሽ ኤይድና ለስዊድን ዓለምአቀፍ የልማት ኤጀንሲ ልባዊ ምስጋናዋን ታቀርባለች፡፡ በተጨማሪም የጥናት ሪፖርቱን በማርቀቅ ሂደት የተሳተፉና አጭር የጥናት መግለጫው የትኩረት አቅጣጫ እንዲሰላ እገዛ ያደረጉ ሌሎች የጥናት ቡድን አባላትና ባለሙያ ገምጋሚዎች፣ ለሥራው ለሰጡት ጊዜና ድጋፍ ታመሰግናለች፡፡ ሌሎች ምስጋናና ዕውቅና የሚያሻቸውም አሉ፡- (1) ለዓመታት የጥናት መግለጫው የተዘጋጀበትን መረጃዎች ያሰባሰቡና ያደራጁ የጥናት መኮንኖችና ተቆጣጣሪዎች ሙሉ ጊዜያቸውን ሰጥተው ላበረከቱት አስተዋጽኦ፤ (2) በሶስት ዙሮች ለተካሄደው የWIDE ጥናት የገንዘብ ዕገዛ ላደረጉ የተለያዩ ድጋፍ ሰጪ ተቋማት፤ እና (3) በኢልምኖ ሰብሳቢነትና በኢኮኖሚ ፖሊሲ ትንተና ክፍሉ በWIDE አጭር የጥናት መግለጫዎች ሁለተኛ ጥራዝ ላይ ለመወያየት መጋቢት 28 ቀን 2016 ዓ.ም በተዘጋጀው መድረክ ላይ የተሳተፉ ከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣናት፣ ላሳዩት ፍላጎትና ለከፈሉት የጊዜ መስዋዕትነት--- ምስጋና ይገባቸዋል፡፡ የጥናት መግለጫው፤ በከፍተኛ ደረጃ በተዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ፣ ከመንግስት ባለሥልጣናት ጋር በተደረገው ውይይት የተሰጡ አስተያየቶችን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ከለሳና ማሻሻያ ተደርጎበታል፡፡ አጭር የጥናት መግለጫው፤ የኢትዮጵያ የልማት ምርምር ተቋምን (ኢልምኖ) ወይም የኢትዮጵያ መንግስትን አሊያም የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርጉለትን የልማት ኤጋሮች አመለካከትም ሆነ አቋም አይወክልም፤ ይልቁንም የፖሊስ ውይይት ለማነቃቃት የታለመ ነው፡፡ ሌሎች የጥራዝ ሁለት የውይይት መነሻ አጭር መግለጫዎችንና የጥናትና ምርምር ውጤቶችን በhttp://ethiopiawide.net/ ድረ-ገጽ ላይ ማግኘት ይቻላል፡፡

በይሁንታ ተቀብለው የመተግበር፣ ከፈቃደኝነት ርቀው የማፈግፈግ፣ እንዲሁም በእምቢታ የመከላከል ምርጫዎችን ያቀላቀለ የተለያየ ምላሽ ሰጥተዋል።

- ከጋብቻ በፊት ማርገዝ፣ በከፊሎቹ ማኅበረሰቦች 'አስነዋሪ' ድርጊት ነው። ይሄም በድብቅ ለሚካሄድ የውርጃ ተግባር በር ይክፍታል። የጋብቻ የእድሜ ወለልን (በ18 ዓመት) ለመገደብ የወጣው ሕግ፣ በየትኛውም ማኅበረሰብ ውስጥ ተግባራዊ አልሆነም።
  - ስር የሰደዱ የዘልማድ እምነቶችን ሸርሽሮ ማሸነፍ፣ ብልሃትን ይጠይቃል። በአንድ በኩል፣ ባላሰለሰ ጥረት የማግባባት መንገድ፣ በሌላ በኩል ደግሞ፣ የሕጎች ተግባራዊነት ላይ የተመረኮዙ የቅጣት ማስጠንቀቂዎችን የመጠቀም መንገድ፣ ሚዛን ጠብቀው በጥበብ እንዲቀናጁ የሚያደርግ መላ ያስፈልጋል። የቅጣት ማስጠንቀቂያዎችን አለመጠን መንዛት፣ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዲደበቁ እንጂ እንዲቀንሱ አያደርግም።
- ሳያገቡና 18 ዓመት ሳይሞላቸው ከትዳር በፊት የወሲብ ግንኙነት የሚያደርጉ ሴቶች፤ የወሊድ መቆጣጠሪያ የማግኘት እድላቸው አናሳ ነው:: በዚህም ሳቢያ ላልተፈለገ እርግዝና፣ እንዲሁም ውርጃ ይዳረጋሉ::
  - ታዳጊና ወጣት ተኮር የስነተዋልዶ አገልግሎት፣ በአገር አቀፍ ደረጃ፣ ተቋማዊ ሥርዓት ከተዘረጋለትና ውጤታማ ተግባራዊነት ከታከለበት፤ ያልተፈለገ እርግዝና፣ ፅንስን በዘልማድ የማቋረጥ አደጋ እንዲሁም ከ18 ዓመት በታች የሚከናወን ጋብቻ ይቀንሳል።
- <u>እርግዝና</u>፡- የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች፣ በአግባቡ አሟልቶ መመገብ፣ ከከባድ ስራ መቆጠብ፣ እረፍት መውሰድና ንፅህና መጠበቅ እንደሚያስፈልግ ለሴቶች ምክር ቢሰጡም፤ ብዙ ሴቶች በጀ ብለው ለመተግበር አልቻሉም ወይም አልፈለጉም። በ2014 መለስተኛ የኢትዮጵያ ስነሕዝብና ጤና ዳሰሳ ስሌት መሰረት፣ 54% ሴት የገጠር ነዋሪዎች፣ የቅድመ-ወሊድ አገልግሎት አግኝተዋል።
- WIDE በሚከታተላቸው ማኅበረሰቦች ውስጥ፣ አስፈላጊ የቅድመ-ወሊድ ምርመራዎችን ከሚያጓድሉ የአቅርቦት መሰናክሎች መካከል፣ የመሳሪያ እጥረት፣ የጤና ማዕከላት ርቀትና ብቃት የጎደለው መስተንግዶ ይገኙበታል። ብዙ ሴቶች፣ በተለይም ድሃ እና ራቅ ባለ ሥፍራ የሚኖሩ ሴቶች፣ የቅድመ-ወሊድ አገልግሎት የማግኘት ፍላጎትና ግፊት አልነበራቸውም። ሊወሰዱ ከሚችሉ እርምጃዎች መካከልም የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡-
  - የቅድመ-ወሊድ የምርመራ መሳሪያዎችንና ስልጠናዎችን ለሁሉም የኤክስቴንሽን ሰራተኞች በማሟላት፣ አገልግሎቱን ይበልጥ ለተጠቃሚዎች ማዳረስ።
  - ለድሃ ሴቶች፣ የጤና ተቋምና የትራንስፖርት ወጪዎችን መሸፈን።
- ወሊድ፡- በ2014 በገጠር የሚኖሩ 91% ሴቶች፣ ልጅ የወለዱት ያለ ሙያተኛ ድጋፍ ነው (የኢትዮጵያ ስነሕዝብና ጤና ዳሰሳ/EDHS)።
- WIDE በሚከታተላቸው ማኅበረሰቦች ውስጥ፣ ሙያተኛ የወሊድ ድጋፍ እንዳይዳረስ የሚገቱ ትልልቆቹ የአቅርቦት መሰናክሎች፣ የጤና ማዕከላት ርቀትና የውስጥ ለውስጥ መንገድ ችግር፣ የሰራተኞችና የመድሃኒት እጥረት፣ የአምቡላንስ አገልግሎት እጦት፣ እንዲሁም የሆስፒታልና

የትራንስፖርት ወጪዎች ናቸው። አገልግሎት የማግኘት ፍላጎትን ከሚገቱ መሰናክሎች መካከልም፣ የምን ቸገረኝ ዝንባሌ አንዱ ነው። በተለይ በቅድመ-ወሊድ ክትትል ወቅት፣ አሳሳቢ የጤና እክል ካልታየ፣ የወሊድ ድጋፍ አያስፈልገኝም ወደሚል ስሜት ያዘነብላሉ። ወንድ ባለሙያዎች ከወሊድ አጠገብ ቢገኙ እንደ ነውር መቆጠሩ፣ እንዲሁም ከወሊድ በኋላ ስድስት ሰዓት ሳይሞላት ደጅ መውጣት በባህል መከልከሉ፣ የአገልግሎት ፍላጎትን ይገታሉ።

- ዘመናዊ የወሊድ አገልግሎትን ወደሚያሟላ ሥርዓት የሚደረግ ሽግግር፣ ዘገምተኛ ሂደት ነው።
- የጤና ተቋማትን በመሳሪያና በሰራተኛ ለማደራጀት፣ እንዲሁም የውስጥ ለውስጥ መንገዶችን ለመስራት በቀጣይነት የሚወጣ ገንዘብ፣ በሙያተኛ የታገዘ ወሊድ ይስፋፋ ዘንድ፣ የአገልግሎት አቅርቦትን ያሻሽላል። የአገልግሎት አሰጣጥ ላይ፣ የሴቶች ባህላዊ እምነቶችንና ውሳኔዎችን በትኩረት ማጤንም፣ የአገልግሎት ፍላጎትን ለማሳደግ ያግዛል። እስከዚያ ድረስ ግን...

- በአቅርቦት ጉድለት፣ በቦታ ርቀት፣ በድህነት እና በግል ውሳኔዎች ሳቢያ፣ ብዙ ነፍሰጡሮች በቀጣዮቹ የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎሜሽን ዕቅድ)፤ ዓመታት፣ በጤና ጣቢያ እና በሆስፒታል የወሊድ አገልግሎት ሳያገኙ ይቀራሉ። ለእነዚህ ሴቶች...
  - ከመደበኛው አገልግሎት ባለፈ፣ ወደ ማኅበረሰቡ ይበልጥ በመቅረብ የድጋፍ እጅ መዘርጋት፤ ለምሳሌም ቤት ውስጥ የሚከናወን ወሊድ፣ ጤናማና ንፁህ እንዲሆን የሙያ እገዛ ማቅረብ፤
    - የሪፈራል ሥርዓቱን አሰራር በማሻሻል፣ አደጋ ላይ ለሚወድቁ ነፍሰጡሮች እንዲደርስላቸው ማድረግ፤
    - ደረጃቸው በተሻሻሉ የጤና ኬላዎች ውስጥ፣ በባለዲፕሎማ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች የሚቀርብ የወሊድ አገልግሎትን መልሶ ማስጀመር (ሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎሜሽን ዕቅድ)፤
    - በጤናማና በንፁህ ወሊድ ዙሪያ፣ እንዲሁም በድንገተኛ አደጋ የድጋፍ አሰጣጥ ዘዴ ላይ ያተኮሩ ስልጠናዎችን በቀጣይነት ለመስጠት፣ ከጤና ልማት ሠራዊት ውስጥ ሴቶችን በአግባቡ መመልመል፤
    - የቤት ውስጥ ወሊድን የማገዝ አጋጣሚ ይኖራቸዋል ተብለው የሚገመቱ ሴቶች በሙሉ፣ ስለ ጤናማና ስለ ንፁህ ወሊድ እንዲያውቁ፣ ለድንገተኛ አደጋም የድጋፍ አሰጣጥ 'ሀሁ'ን እንዲገነዘቡ፣ በጤና ልማት ሠራዊት አማካኝነት ማስተማር ይቻላል። ይህም፣ ዘመነኛ የመገናኛ ቴክኖሎጂን በመጠቀም፣ ሊሳለጥ የሚችል ነው።
  - ከዋና መስመር ያልተዘረጋ ኤሌክትሪክ - በፀሐይ ወይም በነፋስ ኃይል እና በጥቃቅን ግድብ አማካኝነት የሚመነጭ ኤሌክትሪክ በመጠቀም፤ ሞባይል ስልክ አገልግሎቶችን ማዳበር በጤናማ ወሊድ ላይ ያተኮረ አገልግሎትን ለመጠቀም፤ እንዲሁም በድንገተኛ አደጋ ወቅት ከሙያተኛ የወሊድ አማካሪዎች ጋር ለመገናኘት ያስችላል።

- የአገልግሎት ተደራሽነት፣ ድህነትና የቦታ ርቀት፡- ድህነት የጠናባቸው ብዙ ሴቶች፣ ወሊድ ነክ አገልግሎቶችን በክፍያ የመጠቀም አቅም የላቸውም። ክፍያው፣ የሌሎች ሴቶችንም አቅም ይፈታተናል።
  - መንግስት፣ ለሁሉም ነፍሰጡሮችና ለሁሉም ሕፃናት ጤንነት እንዲሁም ደህንነት ሙሉ ሃላፊነት መውሰድ ይኖርበታል። በቅጡ የተቋቋመ የሴቶች የወሊድ መብት፣ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡
    - ቅድመ-ወሊድና ድህረ-ወሊድ የጤና አገልግሎት፣ በተቻለ መጠን በአቅራቢያቸው ማግኘት፤ እና በመመሪያ የፀደቀ በቂ የወሊድ ፈቃድ የጊዜ መጠን።
    - በቅድመ-ወሊድ ምርመራ የጤና ችግር ለተገኘባቸው ሁሉ፤ ወይም በምጥ ጊዜ ለድንገተኛ አደጋ ለተጋለጡ ሁሉ የባለሙያ የወሊድ አገልግሎት ወይም የማህፀን ሐኪም ድጋፍ በነፃ ማግኘት።
    - ወንዶች፣ ከነፍሰጡርና ከምታጠባ እናት ጋር በተያያዘ፣ የአመጋገብ፣ የንፁህ ውኃ፣ የስራ ጫና፣ ከባድ እቃ የማንሳት፣ የእረፍት፣ ቅድመና ድህረ የወሊድ አገልግሎት ጉዳዮች ዙሪያ አስፈላጊ ዕውቀት እንዲቀስሙ ማድረግ።
- ድርቅ፡- WIDE ከሚከታተላቸው ማኅበረሰቦች መካከል አስሩ፣ ከ2003 እስከ 2011 ድረስ ለሁለት ዓመት ወይም ከዚያ በላይ በከባድ ድርቅ ተጠቅተዋል። እነዚህ ሁሉ፣ ከ2005 ወዲህ የምግብ ዋስትና ድጋፍ እና ደራሽ የምግብ እርዳታ አግኝተዋል። ቢሆንም፣ በሁለት ማኅበረሰቦች ውስጥ፣ በ2008 እና በ2010 የሰው ሕይወት ጠፍቷል።
  - በድርቅ ወቅት፣ ለነፍሰጡርና ለሚያጠቡ እናቶች ተጨማሪ የአልሚ ምግብ ፕሮግራም፣ የጡት ወተት ላጡ ጨቅላዎችም ደራሽ የሕፃናት ወተት ማቅረብ፣ ነፍስ አድን ተግባራት ናቸው።

<u>መግቢያ</u>

ከእርግዝና ጀምሮ ጨቅላ ሕፃን እስኪጠና ድረስ ያለው ልዩ ጊዜ፣ ለ15 ወራት ገደማ (ለ450 ቀናት) ይዘልቃል፡ 9 የእርግዝና ወራት፣ ወሊድ እና 6 ወራት የጨቅላ ሕፃን እድገት (በተመራጩ የጡት ወተት)። በዚህ የጊዜ ማዕቀፍ ውስጥ፣ እናትና ልጅ፣ በጥንድና በነጠላ፣ ከበርካታ አደጋዎች ጋር ይጋፈጣሉ።

- በማህፀን ውስጥ፣ በወሊድ ጊዜና በመጀመሪያዎቹ ስድስት የሕይወቱ ወራት ውስጥ፣ ጨቅላውን የሚያጋጥሙት ክስተቶች፣ በአካልና በስነልቦና የረዥም ጊዜ ውጤቶችንና መዘዞችን ሊያስከትሉ ይችላሉ።
- ነፍሰጡር ሴት፣ በእርግዝና ወራትና በወሊድ ጊዜ፣ ከዚያም በጣሙን የሷ ጥገኛ የሆነውን ጨቅላ ለማሳደግ የምታሳልፋቸው የመጀመሪያዎቹ ሳምንታትና ወራት ውስጥ፣ በሰውነቷና በአእምሮዋ ላይ የሚያጋጥሙ ክስተቶች፣ በአካልም ሆነ በስነልቦና የረዥም ጊዜ ውጤቶችንና መዘዞችን ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡ ይኸውም በግል በሷ ላይ፣ እንዲሁም ከልጇ ጋር ባላት ቁርኝትና ብሎም በቤተሰቧ ላይ ሊደርስ ይችላል።

በእርግዝና ዋዜማ፣ ሴቷ የነበራት የምርጫና የውሳኔ ድርሻ፣ የኋላ ኋላ በእርግዝና ማግስት ለሚኖራት መነሻ ብርታትና የጉዞ ፅናት ትርጉም አለው። ከቅድመ እርግዝና አብይ ጉዳዮች መካከል ዋና ዋናዎቹ፣ የሴት ልጅ ግርዛት፣ የወሊድ መቆጣጠሪያ አጠቃቀም፣ የወሲብ ጥቃት፣ ጠለፋ፣ ወሲብ የጀመረችበት እድሜ፣ ከዚህም ጋር የጋብቻ እድሜ፣ በዋናነት ይጠቀሳሉ።

የጥናት መግለጫው፤ በ2003 እና በ2010 በቅርበትና በጥልቀት የተሰናዱ አይነተኛ የጥናት መረጃዎችን በመጠቀም፡-

- ከ2003 እስከ 2013 ድረስ ባሉት ዓመታት፣ የእናቶችና የጨቅላ ሕፃናት ጤናና ደህንነት እንዲሻሻል ያደረጉ መንስኤዎችን ነቅሶ ያወጣል።
- ነፍሰጡሮችና ወላድ ሴቶች ላይ የሚያጋጥሙ ጠቅላላ አደጋዎችን በተመለከተ፣ WIDE በሚከታተላቸው በሃያዎቹ ማኅበረሰቦች ዘንድ፣ በእያንዳንዱ ማኅበረሰብ ውስጥ እና በማኅበረሰቦች መካከል የሚታዩ ልዩነቶችን ይገልጻል። በ450 የሂደቱ ቀናት ከዳር እስከ ዳር የዘለቁ አምስት የአደጋ ገባር መንስኤዎች ላይ፣ የWIDE3 ግኝቶችን ይገልጻል።
- የአደጋ መንስኤዎች፣ ከአራት የሂደቱ እርከኖች ጋር ባላቸው ትስስር ዙሪያ፣ ማለትም ቅድመ-እርግዝና፣ እርግዝና፣ ወሊድ እና የጨቅላው ሕፃን የመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራት እድገት ጋር ባላቸው ጉድኝት ዙሪያ፣ የWIDE3 ግኝቶችን ይገልጻል።

<u>የእናትና የጨቅላ ጤንነትን እንዲሁም ደህንነትን ከ2003 እሰከ 2013 ድረሰ ያሻሻሉ መንስኤዎች</u>

WIDE በሚከታተላቸው ማኅበረሰቦች ውስጥ ተመዝግበው የተደራጁ የ2003 እና የ2010/13 የጥናት መረጃዎች፣ አፊሴላዊውን የስታትስቲክስ መረጃ የሚረጋግጡ ናቸው። በገጠር እናቶችና ጨቅላ ሕፃናት ጤንነትና ደህንነት ላይ፣ በተለይ ከ2005 ወዲህ፣ ትልልቅ የመሻሻል ውጤቶች በስፋት እንደተመዘገቡ፣ ጥናታዊው መረጃ ይመሰክራል። እነዚህ የመሻሻል ውጤቶች፣ ከፈርጀ ብዙ የማዘመን ሂደቶች መስተጋብር የመነጩና፣ በዋና ዋና ዘርፎች መንግስት ከዘረጋቸው የለውጥ እንቅስቃሴዎች ጋር የተዛመዱ ናቸው::

- የነዋሪዎች ጥሪትና ገቢ እየጨመረ መጥቷል። ይህም፣ ከግብርና መዘመን ጋርና እርሻ-ዘለል የስራ መስኮች ከማደጋቸው ጋር የተጎዳኘ፤ የመንግስት የለውጥ እንቅስቃሴና ስራ ፈጣሪ የገጠር ነዋሪዎች የሚደርጉት ጥረት በድምር ያስገኙት ውጤት ነው።
- የገጠር መሰረተ ልማትን ለማዘመን፣ መንግስትና ማኅበረሰብ፣ የውስጥ ለውስጥና አገናኝ መንገዶችን በማሻሻል፤ እንዲሁም የጤና ኬላዎችን፣ ትምህርት ቤቶችንና የቀበሌ ቢሮዎችን በመገንባት ረገድ በጋራ ሰርተዋል።
- ኮሙኒኬሽን በፍጥነት እየተሻሻለ፣ ትምህርት እየተስፋፋ፣ የከተማ ግንኙነት እየደረጀ በመምጣቱ፣ እንዲሁም በግንዛቤ ማዳበሪያ የመንግስት ፕሮግራሞች አማካኝነት፣ ዘመናዊ ሃሳቦች ወደ ገጠር እየደረሱ፣ ቀስ በቀስም የማኅበረሰብ አኗኗርና ልማድ እየተለወጠ መጥቷል። ።
- በማኅበረሰብ ውስጥ የሴቶች ደረጃና ማዕረግ ላይ የመሻሻል ለውጥ እውን የሆነው፤ መንግስት የሴቶችን መብት ለመጠበቅ ካወጣው ሕግና የፆታ አድልዎን ለመቀነስ

ከሚያካሂዳቸው ሌሎች ፕሮግራሞች ጋር፣ እንዲሁም ከትምህርት መስፋፋት፣ ከወሊድ ቁጥጥር ተጠቃሚነት ማደግና ይህን ተከትሎ ከሚቀንሰው የወሊድ መጠን፣ እንዲሁም የሴቶች እጅ ወደ ገበያ ይበልጥ እየገባ፣ ገንዘብም ወደ እጃቸው እየገባ የኢኮኖሚ ተሳትፏቸው ከማደጉ ጋር ተያይዞ ነው።

- መንግስት፣ የለጋሾች ገንዘብ ታክሎበት፣ አናሳ ምርትና በድርቅ ለተጎዱ ማኅበረሰቦች፣ የምግብ ዋስትና ፕሮግራምና ደራሽ የምግብ እርዳታ አቅርቧል።
- መንግስት፣ የለጋሾች ገንዘብ ታክሎበት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም እየተሳተፉ፣ ከማኅበረሰብ የገንዘብና የጉልበት አስተዋፅኦ ጋር፣ የንፁሕ ውኃ ተደራሽነት እንዲጨምር አድርጓል።
- በሺህ የሚቆጠሩ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች፣ በገጠር ማኅበረሰቦች ዘንድ፣ የግልና የአካባቢ ንፅሕናን ለማሻሻል፣ በየቦታውም በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር፣ እንዲሁም የጤና ትምህርት፣ የቤተሰብና የስነተዋልዶ የጤና አገልግሎት ለማቅረብ ጥረዋል።
- ዘመናዊ የሕክምናና የስነተዋልዶ ጤና አገልግሎት፣ በመንግስት፣ በግል ክሊኒኮችና ለትርፍ ባልተቋቋሙ ድርጅቶች እየቀረበ ተደራሽነቱ ጨምሯል።

<u>በእናትና በጨቅላ ሕፃናት ጤናና ደህንነት ላይ የሚታዩ ልዩነቶች በ2013</u>

WIDE በሚከታተላቸው ማኅበረሰቦች መካከል፣ በሃብት፣ በምግብ ዋስትና፣ በርቀት፣ በአሰፋፈር ሁኔታ፣ በመንግስት አገልግሎት ተደራሽነት ረገድ፣ ልዩነቶች ይታያሉ። እነዚህ ልዩነቶችም፣ ከእርግዝና፣ ከወሊድና ከጨቅላው የመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራት እድገት ጋር የተጎዳኙ አደጋዎችን የማባባስ አልያም የማቃለል ተፅእኖ አላቸው።

- አደጋዎቹ የሚብሱት፣ ድህነት በበረታባቸው ዝናብ አጠር አካባቢዎች፣ እንዲሁም ርቀው ተነጥለው በሚኖሩ ማኅበረሰቦች ላይ ነው።

በማኅበረሰብ ውስጥም ልዩነቶች አሉ፡-

- ከመአከሉ ራቅ ብለው በዳር የሚገኙ የማኅበረሰቡ አካባቢዎች ላይ፣ አደጋው ይጨምራል።
- ድሃ ሴቶች፣ ጥላ ከለላ አባወራ በሌለበት ቤተሰብ ውስጥ የሚኖሩ ሴቶች፣ ከጋብቻ ውጭ ሳያስቡት የሚያረግዙ ሴቶች፣ እና የቤት ሰራተኛ ሴቶች ላይ፣ አደጋው ይበዛል።

<u>በ450ዎቹ ቀናት ጎልተው የዘለቁ ጉዳዮች - በ2013</u>

ርቀውና ተነጥለው የሚኖሩ - በውስጥ ለውስጥና በአገናኝ መንገድ ጉድለት እንዲሁም የከተማ ቅርበት በማጣት

የእናትና የጨቅላ አገልግሎቶችን የመጠቀም እድል፣ በከፊል የሚወሰነው፣ ከመኖሪያ ሰፈር ወደ ጤና ኬላ፣ ወደ ጤና ጣቢያ ወይም ወደ ሆስፒታል ለመድረስ ባለው የአመቺነት ልክ ነው። በሌላ መልኩ ሲታይም፣ የመኖሪያ ሰፈር፣ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችና የጤና በጎ ፈቃደኞች ለሚያካሂዱት የቤት

ለቤት ጉብኝት ባለው የአመቺነት መጠን፣ በአገልግሎት ተጠቃሚነትም ላይ ተፅእኖ አለው። በሃያዎቹ የማኅበረሰብ አካባቢዎች የሚገኙ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች በሙሉ፣ በበጋ ወቅት ብቻ የሚያገለግሉ ናቸው። በዝናብ ወቅት ግን፣ መንገዶቹ መኪና አያስገቡም፣ ለእግረኛም አስቸጋሪ ናቸው። በሁለት ማኅበረሰቦች ውስጥ፣ በበጋ ወቅት መኪና ማስገባት የሚችሉ ቦታዎች አሉ። በሰባት ማኅበረሰቦችም፣ ለመኪናና ለእግረኛ እንቅስቃሴ የሚያመቹ የመንገድ ማሻሻያዎች ተሰርተዋል። ቀሪዎቹ አስራ አንድ ማኅበረሰቦች ግን፣ ከቁጥር የሚገባና በወጉ የተሰራ የረባ መንገድ ስለሌላቸው፣ በበጋ ወቅት ሳይቀር፣ የአገልግሎት ተደራሽነታቸው ተገድቧል፤ በተለይ ወደ ዳር ወጣ ያሉ ነዋሪዎች፣ ከአገልግሎት ጋር ተራርቀዋል።

ድህነት

በቂ ምግብ የማጣት እና ያለ ፋታ በከባድ ስራ የመጠመድ አደጋ የሚብሰው፣ በድሃ ነፍሰጡሮችና እናቶች ላይ ነው። ይህም፣ ማህፀን ውስጥ በሚያድገው ፅንስ ላይና የጡት ወተት በሚያሻው ጨቅላ ሕፃን ላይ፣ የጤናና የደህንነት መዘዞችን ያስከትላል። ድሃ ሴቶች፣ የቅድመ-ወሊድ ክትትል አጠቃቀማቸው አነስተኛ ነው። ከእርግዝና ጋር የተወሳሰበ የጤና ችግር እንደተፈጠረባቸው ቢታወቅ እንኳ፣ ጤና ጣቢያ ወይም ሆስፒታል ለመመላለስ፣ የትራንስፖርትና የምግብ ወጪው፣ የአገልግሎትና የመድሃኒት ክፍያ ታክሎበት፣ አቅማቸውን የሚገዳደርና የማይሞከር ይሆንባቸዋል።

- ድህነት የጠናባቸው ሴቶች፣ ያለ ተጨማሪ የገንዘብ ድጋፍ፣ በመንግስት የሚቀርበውን ወሊድ ነክ አገልግሎት መጠቀም አይችሉም።

ድርቅ

ድርቅ፣ በነፍሰጡሮችና በፅንሳቸው ላይ፣ እንዲሁም ስድስት ወር ያልሞላው ጨቅላ ልጃቸውን በሚያጠቡ እናቶች ላይ ያስከተለው የከፋ ጥፋትና ስብራት፣ ዘርዘር ተደርጎ፣ በ2003 የWIDE ጥናት ተሰንዷል። ከደረሱት ጥፋቶች መካከልም፣ የእናት ህልፈት፣ የጨቅላ ሞት፣ እናቶችን ለቁራኛ የጤና ጠንቅ የሚዳርግ የአካልና የአእምሮ ጉዳት፣ የጨቅላ ሕፃናትን የወደፊት የአካልና የአእምሮ እድገት ለሳንካ የሚያጋልጥ ፅኑ የምግብ እጦት ይገኙበታል።

WIDE ከሚከታተላቸው ማኅበረሰቦች መካከል አስሩ፣ ከ2003 እስከ 2011 ድረስ፣ ለሁለት ዓመታትና ከዚያ በላይ በከባድ ድርቅ ተጠቅተዋል። እነዚህም በሙሉ፣ ከ2005 ገደማ ወዲህ፣ የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ድጋፍ (በስምንት አካባቢዎች) ወይም ደራሽ የምግብ እርዳታ፤ ወይም ሁሉንም አይነት ድጋፍና እርዳታ አግኝተዋል። ቢሆንም ግን፣ በደቡብ ክልል በሚገኙ ሁለት ማኅበረሰቦች (በ2008 እና በ2010) እንዲሁም በምስራቅ ትግራይ በሚገኝ በአንድ ማኅበረሰብ (በ2008) ህይወታቸውን ያጡ ሰዎች እንዳሉ ተዘግቧል።

- በድርቅ ወቅት፣ ነፍሰጡሮችንና የሚያጠቡ እናቶችን፣ በአልሚ ምግብ ፕሮግራም መደገፍ፣ እንዲሁም የጡት ወተት ላጡ ጨቅላዎች ደራሽ የሕፃናት ወተት ማቅረብ፣ ሕይወትን የሚታደጉ ነፍስ አድን ተግባራት ናቸው።

የወቅት ፍርርቆሽ

ከዓመቱ ወቅቶች የትኛው ለወሊድ ተመራጭ እንደሆነ፣ በ2003 የተጠየቁ ነዋሪዎች የሰጡት ምላሽ፣ እንደየአካባቢያቸውና እንደየመተዳደሪያቸው ቢለያይም፤ ሁሉም የሚጋሯቸው ታሳቢዎች አሉ። እነርሱም ጎተራ ሲሞላ፣ ኪስ አበጥ ሲል፣ ውሃ እንደልብ ሲሆን፣ ተስማሚ አየር ሲኖር እንዲሁም ወባ የማይነሳበት ጊዜ ናቸው። እነዚህ ወቅቶች፣ በሴቶች ትከሻ ላይ የእርሻ ስራ የማይከብድበት ወቅት አይነተኞቹ እንደሆኑ አስረድተዋል።

እስከ 2010-13 ድረስ በነበረው የኢኮኖሚ እድገት፣ ማኅበረሰቦቹ ኑሯቸውን የሚያሻሽል ትርጉም ያለው ለውጥ አግኝተዋል። የመስኖ ተጠቃሚነትም (በ13 ማኅበረሰቦች)፣ የኪስ መራቆት ችግርን ቀለል ለማድረግ፣ ወቅቶችን ተከትሎ የሚፈራረቅባቸውን የገቢ ምንጭ ውጣውረድ ለማረጋጋት ረድቷል። በእርግጥ፣ የመስኖ ተጠቃሚነት፣ ከነባሩ የእርሻ ወቅት ውጭ፣ ለሴቶች ተጨማሪ የእርሻ ስራና ተደራቢ ጫና አምጥቷል። የንፁሕ ውኃ ተደራሽነት በብዙ ማኅበረሰቦች ተሻሽሏል። የወባ ችግርም፣ የመከላከያ እርምጃዎች በተካሄዱባቸውና የመድሃኒት አቅርቦት በተዳረሰባቸው አካባቢዎች ቀንሷል።

ንፁህ ውኃ

የንፁህ ውኃ ተደራሽነት በአብዛኞቹ አካባቢዎች ቢሻሻልም፣ በ2013ም ጭምር የወረዳ የውኃ ፕሮግራሞች፣ በተለያዩ ችግሮች ከመዘፈቅ አልተላቀቁም።

- በሦስት አካባቢዎች የመጠጥ ውኃው ንፁህ አይደለም (ዲንኪ፣ አማራ፤ ገልቻ፣ ኦሮሚያ፣ ቆሮደጋጋ፣ ኦሮሚያ)። የተወሰኑ የንፁህ ውኃ ጣቢያዎች በተሰራላቸው አምስት አካባቢዎች ውስጥም ቢሆን፣ አብዛኛው ነዋሪ፣ የመጠጥ ውኃ የሚቀዳው፣ ከወንዝ፣ ከወራጅ ውኃ፣ ከኩሬና ንፅህናቸው ካልተጠበቁ ምንጮች ነው።
- በሰባት አካባቢዎች፣ የንፁህ ውኃ ጣቢያ እና ንፅህናው ያልተጠበቀ ውኃ፣ ጥቅም ላይ ሲውል ይታያል። በሁለት አካባቢዎች፣ ንፁህ ውኃ በ'ራሽን' ይከፋፈላል።
- በአምስት አካባቢዎች፣ ሁሉም ነዋሪ የንፁህ ውኃ ተጠቃሚ መሆን ችሏል፤ በአንደኛው አካባቢ የገንዘብ አቅም የሌላቸው ነዋሪዎች፣ የወንዝ ውኃ የሚጠቀሙ ቢሆንም። በንፁህ ውኃ ተጠቃሚነት ሻል ብለው የሚታዩት አብዛኞቹ አካባቢዎች፣ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ድጋፍ ያገኙ ናቸው።
- አንዳንዶቹ የውኃ ጣቢያዎች አይሰሩም። የመለዋወጫ እቃ እጥረትና የቧንቧ ባለሙያ እጦት፣ የተለመዱ ችግሮች ናቸው።

የሴቶች ስራ

ሴት የምታከናውነው ስራ፣ ከቤተሰብ ብዛትና የኑሮ ደረጃ፣ እንዲሁም ከዓመታዊው የወቅቶች ፍርርቆሽ ጋር ይያያዛል። ከእነዚህ ስራዎችም መካከል፣ የቤተሰብ አስተዳደርና የቤት ውስጥ ስራ፣ የልጆች እንክብካቤና የምግብ ዝግጅት፣ ገቢያ መሄድ፣ እንጨት መልቀምና ውሃ መቅዳት፣ የቤተሰብ

ማሳ ላይና በግብርና የቀን ስራ መሰማራት፣ የእንስሳት እንክብካቤ፣ እርሻ-ዘለል ስራዎች፣ የምግብ ዋስትና ስራ (በአንዳንድ ማህበረሰቦች) እና የማህበራዊ ትስስር ግንኙነቶችን መወጣት ይገኙበታል።

በመጀመሪያዎቹ ሦስት የእርገዝና ወራት፣ ነፍሰጡር ሴቶች ለአካል ዝለት የተጋለጡ ናቸው። በእርግዝና ወቅት፣ በተለይ ደግሞ በኋለኞቹ ወራት ላይ፣ ከባድ እቃ ማንሳት አልያም መሸከም የለባቸውም። ሆኖም ግን ብዙ ሴቶች ባለባቸው የሥራ ጫና ምክንያት፤ በጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች እንዲያርፉና ከባድ ነገር እንዳያነሱ የሚሰጣቸውን ምክር መተግበር አይችሉም፡፡

የየአካባቢው ብዙ ወንዶች፣ በከባድ ስራ ወይም ጠምዶ በሚይዝ ስራ ሳቢያ በወላዶች ላይ የሚመጣውን አደጋ አልተገነዘቡም። በዚህም ሴቶች፣ ሚስት ከመሆናቸው አንፃር ብቻ ሳይሆን ከማህበረሰብ አባልነታቸው አንፃርም ተፅእኖ ያድርባቸዋል።

- ለምሳሌ፣ በአንድ አካባቢ፣ ሦስት ሴቶች በማህበረሰብ ስራ ላይ በገጠማቸው ከባድ ሽክም ሳቢያ ፅንስ እንደተጨናገፈባቸው ተነግሯል።
- የምግብ ዋስትና ፕሮግራም በሚካሄድባቸው አብዛኞቹ አካባቢዎች፣ ነፍሰጡርና የሚያጠቡ ሴቶች፣ የምግብ ዋስትና ሕዝባዊ ስራዎች ላይ ከባድ ጫና እንዳይደርስባቸው የሚከላከል በግልፅ የተደነገገ መመሪያ የለም።

ወላዶች ተገቢ ባልሆነ የስራ ጫና በሚገጥማቸው አደጋ ዙሪያ፣ ለወንዶች ስልጠና መስጠት፣ በጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ውስጥ መካተት አለበት። በማህበረሰብ በሚሰናዳ የጉልበት ስራ ላይም፣ ለነፍሰጡርና ለሚያጠቡ ሴቶች የእረፍት ፈቃድ መስጠት ይገባል።

<u>የቅድመ - እርግዝና ጉዳዮች</u>

ወሊድ እና የወሊድ መቆጣጠሪያ

በኢትዮጵያ ህዝብና ጤና ቆጠራ (EDHS) ጥናት መሰረት፤ በ2014 ከገጠር ነዋሪ ባለትዳር ሴቶች መካከል፣ 38.4% ያህሉ የወሊድ መቆጣጠሪያ ተጠቅመዋል። የWIDE3 ጥናታዊ መረጃ፤ የወሊድ መቆጣጠሪያ አጠቃቀም፣ እንደየማኅበረሰቡ ዓይነት ልዩነት እንደሚታይበት ይጠቁማል።

- በ5 ማኅበረሰቦች ውስጥ፣ የወሊድ መቆጣጠሪያ አጠቃቀም በንጽጽር ከሌሎች ያንሳል። ሦስቱ ርቀው የሚኖሩ ማኅበረሰቦች ናቸው (ከተለያየ ሃይማኖት ጋር)። በሌሎቹ ዘንድ የአጥባቂ ሙስሊሞች ቅዋሜ ይታያል። የባሎች ተቃውሞና በጤና ኬላ የወሊድ መከላከያ አቅርቦት አስተማማኝ አለመሆን (2010)፣ ተጠቃሚነትን የሚቀንሱ ሁለት ምክንያቶች እንደነበሩ ሴቶች ይጠቅሳሉ።
- በስድስት ማኅበረሰቦች፣ ጉልህ የተጠቃሚነት ለውጥ ተፈጥሯል። የለውጡ ምክንያቶችም ልጆች ሳይበዙ በእንክብካቤ ማሳደግ እና "ለኑሮ ማሰብ" የሚሉ ናቸው። በአራቱ አካባቢዎች አንዳንድ ወንዶች መቃወማቸው ባይቀርም፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የወሊድ መቆጣጠሪያ መርፌ በመምጣቱ፣ ሴቶች በምስጢር ሊጠቀሙበት ይችላሉ።
- በቀሪዎቹ ዘጠኝ አካባቢዎች፣ የወሊድ መቆጣጠሪያ ተጠቃሚነት፤ 50% ወይም ከዚያ በላይ ነው።

- ለከተማ በቀረቡ አንዳንድ ማኅበረሰቦች ውስጥ፣ በአስራዎቹ ዕድሜ የሚገኙ ታዳጊ ወጣቶች፣ በቀላሉ የወሊድ መቆጣጠሪያ የማግኘት እድል አላቸው። ራቅ ያለ አንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ደግሞ ከጤና ኬላ ያገኛሉ። በሌሎች ማኅበረሰቦች፣ ከጋብቻ በፊት ወሲብ መፈጸም "ነውር" መሆኑ፣ ለታዳጊዎች ሁኔታውን አስቸጋሪ አድርጎባቸዋል።

የሴት ልጅ ግርዛት

የ WIDE3 መረጃዎች፤ የሴት ግርዛት ከማኅበረሰብ ማኅበረሰብ ጉልህ ልዩነት እንዳለው ያሳያሉ።

- በአራት ማኅበረሰቦች ጨርሶ ግርዛት የለም።
- በሌላ አምስተኛ ማኅበረሰብ ደግሞ፣ ከሞላ ጎደል ቀርቷል የሚባል ነው።
- በአራት ማኅበረሰቦች ልማድ፣ ሴት ልጅ የምትገረዘው በተወለደች በ7 ቀኗ ነው። ርቆ በሚገኝ አንድ አካባቢ፣ የሴት ልጅ ግርዛት ክልከላ ተቀባይነት አላገኘም፤ የመከልከል እርምጃም አልተወሰደም። ክልከላ ተግባራዊ በሆነባቸው ሌሎች ሦስት አካባቢዎች፣ የሴት ልጅ ግርዛት ቀንሷል። አንዳንዶች በድብቅ አንዳንዴም "ከትክክለኛው ቀን ውጭ" ያደርጉታል።
- በሦስት ማኅበረሰቦች ወግ፤ የሴት ግርዛት የሚፈጸመው በዘልማዳዊ ጋብቻ ዋዜማ ነው።
  - በሁለት የአርሲ አካባቢዎች፤ ክልከላ ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን፣ ዘልማዳዊ ጋብቻ እየቀነሰ የፈቃደኝነት ጋብቻ እየጨመረ መምጣቱም ተደማምሮ፣ የሴት ግርዛት በእጅጉ ቀንሷል።
  - በጋሞጎፋ አካባቢ የሴት ግርዛት ዕድሜ ዝቅ የተደረገ ሲሆን፣ ማኅበረሰቡ ክልከላውን ተቃውሞታል፤ ክልከላውን የማስፈጸም እርምጃም አልተወሰደም።
- በስምንት ማኅበረሰቦች፤ ግርዛት የሚፈጸመው ልጃገረዶች ወሲብ ለመፈጸም ዝግጁ ከመሆናቸው ጥቂት ቀደም ብሎ ነው።
  - በሁለቱ ማኅበረሰቦች፤ ክልከላው ተቃውሞ ገጥሞታል፤ የመከልከል እርምጃ አልተወሰደም።
  - በሌሎች ሁለት ቦታዎች እርምጃ ባይወሰድም፣ ልማዳዊ ድርጊቱ ግን እየቀነሰ ነበር።
  - በአንደኛው፣ በግንዛቤ መስፋፋትና በቅጣት ፍራቻ፣ ልማዳዊው ድርጊት ቀንሷል።
  - የሴት ልጅ ግርዛት ትልቅ ልማዳዊ ሥርዓት በሆነባቸው ሦስት ማኅበረሰቦች ውስጥ፣ የሴት ልጅ ግርዛት ለመከልከል የተወሰዱ ጠንካራ እርምጃዎች፣ ድርጊቱ በድብቅ እንዲካሄድ አድርገዋል። በዚህም የተነሳ፣ ትክክለኛ መረጃ ማግኘት አልተቻለም።

ሴቶች ጋብቻና ወሲብ የሚፈፅሙበት እድሜ

ለአቅመ ወሲብ የደረሰች ወይም የወሲብ ግንኙት የጀመረች ልጃገረድ፣ ጋብቻ ስትፈፅም ተቀባይነት ያለው ወግ እንደሚሆን በሰፊው ይታመናል። የጋብቻ የእድሜ ወለል 18 ዓመት መሆኑ በጣም በዛ (ዘገየ) ብለው የሚያስቡት፣ ገና በ16 ዓመትም ለአቅመ ወሲብ ይደረሳል በማለት ነው። እንዲህ

የፈጠነው፣ አመጋገብ ስለተሻሻለ ነው ተብሏል። ከጋብቻ በፊት እርግዝና እንዳይከሰት ወላጆች ይሰጋሉ።

18 ዓመት ያልሞላቸው ልጃገረዶች ጋብቻ የሚፈፅሙበት ምክንያት፣ በግል ምርጫና ውሳኔ፣ ትምህርት ቤት ውስጥ ስኬት በማጣት ወይም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ለመቀጠል የገንዘብ አቅም ማጣት፣ ቤት ውስጥ ከሚጫንባቸው ቅጥ የለሽ ሃላፊነት ለማምለጥ፣ ወይም ከአስቸጋሪ የእንጀራ እናት ለመሸሽ የሚሉ መንስኤዎችን ያካትታል። በኑሮ ደህና የተደላደሉ ቤተሰቦች ውስጥ፣ በወላጆች ውሳኔ "ለባል የተዳሩ" አንዳንድ ልጃገረዶች አሉ።

የተማሪ ልጃገረድ ያለእድሜ ባል ሊያገቡ ሲሉ፣ የሴቶች ጉዳይ ፅ/ቤት ያስቆማቸው ጋብቻዎች አሉ። ባብዛኛውም እንደ ምክንያት የቀረበውም፣ የልጃገረዲ እድሜ ለጋብቻ አልደረሰም በማለት ሳይሆን፣ በትምህርቷ መቀጠል ትፈልጋለች በሚል ነው።

- በትግራይ እና በአማራ ክልል በሚገኙ ማኅበረሰቦች ውስጥ፣ ልጃገረዶችን በታዳጊነታቸው ለባል ለመዳር የሚፈልጉ ወላጆች፣ የልጆቻቸውን እድሜ በመደበቅ ይዋሻሉ። በአንድ የትግራይ ክልል ወረዳ፣ ልጃገረድን ያለእድሜዋ የሚድሩ ወላጆች የ800 ብር እና የ6 ዓመት እስራት እንድሚደርስባቸው ማስጠንቀቂያ ተሰራጭቷል። በሁለት የአማራ ክልል አካባቢዎች ምንም አልተደረገም፤ በሁለት ሌሎች የክልሉ አካባቢዎች ደግሞ ልጃገረዶች ከጋብቻ በፊት ለእድሜ ምርመራ ይላካሉ፤ ነገር ግን ከ18 ዓመት በታች፣ ያለእድሜ የሚፈፀም ጋብቻ መቀጠሉ አልቀረም።
- ገና በለጋ እድሜ የሚደረግ ጋብቻ፣ በኦሮሚያ እና በደቡብ ክልል አርሶአደር አካባቢዎች ውስጥ የተለመደ አይደለም። ያለእድሜ ጋብቻን የሚከለክለው ሕግ ተግባራዊ ሲሆንም አይታይም። ትምህርት በመስፋፋቱና በየአካባቢው እየጨመረ በመጣው የኢኮኖሚ ተሳትፎ፣ እንዲሁም ወደ ከተማና ወደ ውጭ አገር በሚደረግ ፍልሰት የተነሳ፣ ብዙ ወጣት ሴቶች ጋብቻቸውን ያዘገያሉ።
- በሁለት አርብቶ አደር አካባቢዎች፣ የ12 ዓመት ልጃገረዶች ለአቅመ ጋብቻ እንደደረሱ ተደርገው ይቆጠራሉ።

የወሲብ ጥቃትና ጠለፋ እርግዝናን ሲያስከትል

የወሲብ ጥቃትና የጠለፋ ድርጊት፣ በሁሉም አካባቢዎች ቀንሷል። ነገር ግን ከቦታ ቦታ ልዩነቶች አሉ።

- ጠለፋ በአራት ማኅበረሰቦች፣ ድራሹ ጠፍቷል ተብሏል። በአንድ የአርቢዎች ወረዳ ደግሞ፣ አሳሳቢ የማይሆንበት ደረጃ ላይ እንደደረሰ ተወስቷል።
- በከንባታ በሚገኘው አካባቢ፣ መንግስታዊ ባልሆነ ድርጅት አማካኝነት ወደ ፍርድ ቤት በቀረበ ክስ፣ በጥፋተኛው ላይ የ15 ዓመት እስራት መፈረዱ፣ ጠለፋን ለማስወገድ እንደረዳ ተነግሯል።
- በአንድ የትግራይና በሦስት የአማራ ክልል አካባቢዎች የሚኖሩ ልጃገረዶች፣ እንደ ድሮ ባይሆንም፣ ለጠለፋ አደጋ ይጋለጣሉ።

- በብዙ የኦሮሚያ ክልል አካባቢዎች ጠለፋ፤ ያለ ጥሎሽ ለማግባት የሚደረግ ልማድ ነበር። በሁሉም አካባቢዎች ጠለፋ ቀንሷል። ግን በሴቷ ስምምነት የሚፈጸም የ"ፈቃደኝነት ጠለፋ" ጨምሯል።
- በመንግስት እርምጃ አማካኝነት፣ በሦስት የደቡብ ማኅበረሰቦች ጠለፋ ቀንሷል። በሌላ አንድ ማኅበረሰብም ቀንሷል፤ አሳሳቢ ችግር መሆኑ ግን አልቀረም።
- በ11 ማኅበረሰቦች፣ የወሲብ ጥቃት አሁንም አሳሳቢ ችግር ነው። የህጉ አፈጻጸም ደካማ ነው። ያገቡ ሴቶች ላይ የሚፈፀሙ የወሲብ ጥቃቶች መኖራቸው በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ተዘግቧል።
- በሌሎች ማኅበረሰቦች፣ በመንግስት እርምጃና በቅጣት ፍራቻ የተነሳ፣ የወሲብ ጥቃት እንደቀነሰ ተጠቅሷል።
- ድሃና ለጥቃት የተጋለጡ ሴቶች ላይ፣ ለወሲብ ጥቃት የመጋለጥ አደጋ ይጨምራል፤ ፍትህ ማግኘት እድል ደግሞ የላቸውም።

የመንግስት እርምጃዎች

ስር የሰደዱ የዘልማድ እምነቶችን ሸርሽሮ ማሸነፍ፣ ብልሃትን ይጠይቃል። ያላሰለሰ የማግባባት ጥረትን፣ እንዲሁም በሕጎች ተግባራዊነት የተደገፈ የቅጣት ማስጠንቀቂያን፣ በጥበብ ሚዛን ጠብቆ ያዋሃደ ዘዴ ያስፈልጋል። የቅጣት ማስጠንቀቂያዎችን አለመጠን መንዛት፣ ልማዳዊ ድርጊቶች እንዲደበቁ እንጂ እንዲቀንሱ አያደርግም።

<u>የእርግዝና ጉዳዮች</u>

እርግዝና - ከጋብቻ ውጭ

ከጋብቻ ውጭ የማርገዝ ጉዳይን በተመለከተ ከማኅበረሰብ ማኅበረሰብ፣ የተለያዩ የአመለካከት አዝማሚያዎች ይታያሉ።

- በሰባት ማኅበረሰቦች ጉዳዩ አልተነሳም፤ በጥያቄም አልቀረበም።
- ከተማ አቅራቢያ በሚገኙ ሌሎች አራት ማኅበረሰቦች ውስጥ፣ ያላገቡ እናቶች ከልጆቻቸው ጋር እዚያው ማኅበረሰብ ውስጥ መኖር ይችላሉ።
- በስድስት ማኅበረሰቦች፣ ከጋብቻ ውጭ ማርገዝ "ነውር" ነው። በዚህም፣ ሴቶች ጽንስ ያቋርጣሉ (ብዙውን ጊዜ በዘልማድ ዘዴ)፤ አካባቢውን ለቀው ይሄዳሉ፤ ወይም ልጃቸውን ለሞት አሳልፈው ይሰጣሉ። በአንድ ማኅበረሰብ፣ ከጋብቻ በፊት የወሊድ መቆጣጠሪያ መጠቀም አስነዋሪ ነው።
- ጌዴኦ በሚገኘው ማኅበረሰብ፣ ከጋብቻ የቀደመ የወሲብ አጋጣሚ ኢምንት ነው (ከጋብቻ በፊት የሚፈፀም ወሲብ የተለመደ አይደለም)። ያረገዘች ልጃገረድ፣ ፅንሱን ታቋርጣለች፣ ወይም አካባቢውን ጥላ ትሄዳለች፤ አልያም ታገባለች።

- በፀማይ የአርቢዎች አካባቢ፣ ቅድመ ጋብቻ ወሲብ (ከጋብቻ በፊት የሚፈፀም ወሲብ) የባሕል ተቀባይነት አለው። ነገር ግን፣ ያረገዙ ልጃገረዶች፣ የዘልማድ ውርጃ ነው የሚጠብቃቸው። ምክንያቱም፣ ሕፃኑ ከተወለደ፣ ሚንጊ ተብሎ ሊገደል ይችላል። ልጃገረዲቱም፣ ተዋርዳ ትገለላለች።

ፅንስ ማቋረጥ

እዚህም ላይ፣ ከማኅበረሰብ ማኅበረሰብ፣ ጎላ ያሉ ልዩነቶች አሉ።

- በአራት ማኅበረሰቦች፣ የፅንስ ማቋረጥ ዘመናዊ አገልግሎት ማግኘት እንደሚቻል ተጠቅሷል። ዘልማዳዊ ውርጃ ግን፣ ስሙ አልተነሳም (በተግባር አልተከሰተም ማለት ግን አይደለም)።
- በአማራ ክልል በሚገኙ አራቱ ማኅበረሰቦችና በሌሎች ሦስት ማኅበረሰቦች፣ ከዘልማዳዊው ውርጃ ጎን ለጎን፣ የገንዘብ አቅም ያላቸው ሴቶች በየአጋጣሚው አልፎ አልፎ ዘመናዊ የፅንስ ማቋረጥ አገልግሎትን እንደሚጠቀሙ ተገልጿል።
- በአምስት ማኅበረሰቦች፣ የዘልማድ ውርጃ አለ። ዘመናዊ አገልግሎት ግን ጨርሶ አልተጠቀሰም።
- በፀማይ የአርቢዎች አካባቢ፣ ፅንስ የማቋረጥ ዘመናዊ አገልግሎት፣ ሕገወጥ ነው ተብሎ ይታመናል።
- በሦስት ማኅበረሰቦች፣ በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት፣ ከቁጥር የሚገባ ፅንስ የማቋረጥ ድርጊት የለም፡ በወሊድ መቆጣጠሪያ ምክንያት፣ 'ትልቅ ነውር' በሚል ልማድ ሳቢያ፣ ብዙ ልጆች ወልዶ ቤተሰብ ማብዛት ተፈላጊ ነው በሚል እምነት የተነሳ።
- ያላገቡ ልጃገረዶች፣ ፅንስ ለማቋረጥ፣ ብዙውን ጊዜ የዘልማድ 'አዋቂዎች' ዘንድ ይሄዳሉ። የዘልማድ ቅጠላቅጠልና ስራስር ይሞክራሉ። ወይም፣ እንደ አምፒሲሊን የመሳሰሉ ክኒኖችን በገፍ ይውጣሉ። በጀርም ተመርዘው ለበሽታ እንዲሁም ለሞት ሲዳረጉ ታይቷል። በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ፣ ፅንስ ያቋረጡ አንዳንድ ሴቶች፣ ፅንስ የተጨናገፈባቸው በማስመሰል፣ ባል እንዳያውቅ ያደረጉበት ጊዜ አለ።

ሳያገቡና 18 ዓመት ሳይሞላቸው የወሲብ ግንኙነት የሚያደርጉ ሴቶች፤ በወሊድ መቆጣጠሪያ እጥረት፣ ይህን ተከትሎም ባልተፈለገ እርግዝና፣ እንዲሁም ፅንስ ለማቋረጥ የዘልማድ ዘዴ በመጠቀም ሳቢያ የሚፈጠር የችግር ጓዝ ይገጥማቸዋል።

- ታዳጊና ወጣት ተኮር የስነተዋልዶ አገልግሎት፣ በአገር አቀፍ ደረጃ በቅጡ ተቋማዊ ከተደረገና ውጤታማ ተግባራዊነት ከታከለበት፤ ያልተፈለገ እርግዝና፣ ፅንስን በዘልማድ የማቋረጥ አደጋ እንዲሁም ከ18 ዓመት በታች የሚከናወን ጋብቻ ሊቀንስ ይችላል።

ነፍሰጡርነት

በ2003 በቃለምልልስ የተሳተፉ ሴቶች፣ ከነፍሰጡርነት ጋር የተዛመዱ በርካታ ችግሮችን ዘርዝረዋል።

- ከተጠቀሱት ችግሮች መካከልም፤ የስቃይ፣ የሕመምና የሠውነት መዛል ስሜቶች፣ ለእርጉዝ የማይሆኑ የስራ ውጣውረዶች፣ ጭንቀት፣ እንዲሁም ከእግዝና ጋር የተጎዳኙ ሕመሞች ይገኙበታል።
- በእርግዝና ወቅት የተከሰተ የምግብ እጦት፣ ከዛሬም አልፎ ለነገ ችግር የሚፈጥር፣ በእናት እና በጨቅላዋ ላይ የተጫነ እዳ ይሆናል።
  - ነፍሰጡር ሴቶች፣ ከሌሎች የባሰ የስቃይ ስሜትና የስነልቦና ችግር ይደርስባቸዋል። ይበልጥ ለአደጋ እየተጋለጡ ለስጋትና ለሰቀቀን ይዳረጋሉ። ጉልበት ተንጠፍጥፎ ያለቀ ያህል፣ በአቅመቢስነትና በዝለት ስሜት፣ መላወስ እስኪሳናቸው ድረስ ጫናው ይበረታባቸዋል። ለወሊድ ችግር፣ ለቁራኛ የአካል ጉዳት፣ ለሞትም ጭምር ይዳረጋሉ።
  - በወሊድና ከዚያ በኋላ፣ በሕፃኑ ላይ ከሚገጥሙት ችግሮች መካከል፡- ከክብደት በታችና ጤና የራቀው፣ በወጉ መመገብና ማደግ የተሳነው፣ ዘወትር ለበሽታ የተጋለጠ፣ በአእምሮም ዘገምተኛ፣ የቆዳ ችግሮች የተደራረቡትና ነጋ ጠባ የሚያለቅስ ሕፃን ሊሆን ይችላል፤ ከዚህም አልፎ ለሞት ሊዳረግ ይችላል።

ቅድመ-ወሊድ አገልግሎት

የ2014ቱ የኢትዮጵያ ህዝብና ጤና ቆጠራ (EDHS) ስሌት፣ 35% ያህል የገጠር ሴቶች ከብቁ ባለሙያ የቅድመ-ወሊድ አገልግሎት እንዳገኙና፣ 19% ያህሉ ደግሞ በጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች እንደተስተናገዱ ይገልፃል። በWIDE3 ጥናት ላይ፣ የቅድመ-ወሊድ አገልግሎት ላይ ያተኮሩ ጥያቄዎች አልተዳሰሱም። አገልግሎቱን ለማስፋፋት ከ2010 እስከ 2013 በመንግስት የተካሄደውን ዘመቻ ከነውጤቱ የሚያካትትና የለውጥ ሂደቱን ለማገናዘብ የሚያስችልም አይደለም። በ2013 የተጠኑት ከፊሎቹ ማኅበረሰቦች ደግሞ፣ ቀደም ብለው ከተጠኑት ማኅበረሰቦች በኑሮ ደረጃ ከፍ ያሉ ናቸው።

በ2011 መገባደጃ ላይ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች በአጠቃላይ የቅድመ-ወሊድ ምክር መስጠት ጀምረው ነበር። ለነፍሰጡሮች የሚሰጡት ምክርም፣ የተሟላና ያላደረ ትኩስ ምግብ እንዲበሉ፣ ከከባድ ስራ እንዲርቁ፣ እረፍት እንዲወስዱ፣ የግልና የአካባቢ ንፅህናቸውን እንዲጠብቁ የሚገፋፉ ነው። የአዮዲን፣ የአይረን እና የክትባት ጉዳዮችም መነሳታቸው አልቀረም። አንዲት የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኛ፣ የማዳመጫ መሳሪያ (stethoscope)፣ የደም ግፊት መለኪያ እና የክብደት ሚዛን ስላልነበራት፣ ሴቶችን ወደ ጤና ጣቢያ ማስተላለፍ ነበረባት፤ አንዳንዶቹ ሴቶች ግን ወደ ጤና ጣቢያ የመሄድ ፍላጎት አልነበራቸውም። እቅድና ኮታ የሚሟላት ጫና የተሸከሙ አንዳንድ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችና የወረዳ ሃላፊዎች፣ ትልልቅ የስኬት ቁጥሮችን እየጠቀሱ ቢናገሩም፣ ከማኅበረሰብ አባላትና ነዋሪዎች ንግግር ጋር ቁጥሮቹ አይጣጣሙም።

በኑሮ ደረጃ ሻል ያሉ ስድስት ማኅበረሰቦች ውስጥ በ2013 ከተካሄደው ጥናት የተገኙ ውሱን መረጃዎች እንደሚያሳዩት፣ የቅድመ-ወሊድ አገልግሎት የሚቀርበው በተለያየ መንገድ ነው :- በጤና ጣቢያ፣ በጤና ኬላ እና በቤት ለቤት ጉብኝት። አገልግሎቱ በዝርዝር፣ ምን እንደሚያካትት ግን

አይታወቅም። በአጠቃላይ የጤና ልማት ሠራዊት ምንነት ላይም፣ ቅጥ ያለው የጋራ ግንዛቤ አልነበረም።

WIDE በሚከታተላቸው ማኅበረሰቦች፣ አስፈላጊ የቅድመ-ወሊድ ምርመራዎችን ከሚያጓድሉ የአቅርቦት መሰናክሎች መካከል፣ የመሳሪያ እጥረት፣ የጤና ማዕከላት ርቀት እና መጥፎ መስተንግዶ ይገኙበታል። ብዙ ሴቶችም፣ በተለይ በድህነት የሚቸገሩና ርቀው የሚኖሩ ሴቶች፣ አገልግሎቱን በመሻት የሚያሳድሩት ግፊት የለም። ሊወሰዱ ከሚችሉ እርምጃዎች መካከልም፣ የሚከተሉት ይጠቀሳሉ።

- አገልግሎቱን ይበልጥ ለማዳረስ፣ የቅድመ-ወሊድ የምርመራ መሳሪያንና ስልጠናን ለሁሉም የኤክስቴንሽን ሰራተኞች ማሟላት፤
- ለድሃ ሴቶች፣ የጤና ተቋምና የትራንስፖርት ወጪዎችን መሸፈን::

<u>የወሊድ ጉዳዮች</u>

የወሊድ ሰሞን የጨቅላ ሕፃናት ሞት

በ2003 በቃለምልልስ የተሳተፉ ሴቶች፣ በወሊድ ወቅት ጨቅላ ህፃናትን ለሞት የሚዳርጉ የተለያዩ መንስኤዎችን ዘርዝረዋል። ከእነዚህም መንስኤዎች መካከል፣ ነፍሰጡሯ ላይ የሚደርስ የአካል ጉዳትና ጫና (ተደናቅፋ ከወደቀች፣ ከባድ እቃ ካነሳችና ከተሸከመች፣ በባል ከተደበደበች ወይም የወሲብ ግንኙነት ላይ ሃይል ከበዛባት)፣ የምግብ እጥረት፣ የእርግዝና ጊዜ ሕመም፣ የድህረ-ወሊድ አገልግሎት ጉድለት፣ በእርግዝና ወቅት መድሃኒትና ጎጂ ንጥረነገሮች መጠቀም፣ የወሊድና የውርጃ ጠባሳ፣ በወሊድ ጊዜ የሚከሰት ችግር፣ ያለጊዜው የሚመጣ ወሊድ፣ በዘር ሐረግ የሚተላለፍ ችግር፣ የፈጣሪ ፈቃድ፣ ጥንቆላ፣ እና ሌሎች የአጉል እምነት ሰበቦች ተጠቅሰዋል። በWIDE3፣ የጨቅላ ሕፃናትን ሞት የሚመለከት መረጃ የለም።

የ2011ቱ የኢትዮጵያ ህዝብና ጤና ቆጠራ (EDHS) እንደሚያመለክተው፣ የወሊድ ሰሞን የሕፃናት ሞት (ገና ሲወለዱ ወይም በተወለዱ በሰባት ቀናት ውስጥ የሚሞቱ ሕፃናት ቁጥር፣ በገጠርና በከተማ) ለአምስት ዓመታት ተመሳሳይ እንደነበረ ያመለክታል። ከዚህ ጋር ሲነጻጸር፣ በ2005 የገጠር አካባቢዎች የተመዘገበው የወሊድ ሰሞን የሕፃናት ሞት መጠን፣ ያነሰ ነው። ለሰባት ወርና ከዚያ በላይ በዘለቁ 1000 እርግዝዎች ውስጥ፣ በወሊድ ሰሞን የተከሰተው የጨቅላ ሕፃናት የሞት መጠን 37 ነበር።

የመባቻ ወር የጨቅላ ሕፃናት ሞት፣ (በተወለዱ በወር ውስጥ፣ በገጠርና በከተማ)፣ ከ2005 እስከ 2011 ባሉት አምስት ዓመታት፣ ብዙም አልተለወጠም (39 ከ1000 የነበረው የሞት ምጣኔ፣ 37 ከ1000 ሆኗል)። በ2014 የዓለም ጤና ድርጅት እንዳሰላው፣ ያለጊዜው የመጣ ወሊድ (37%)፣ በጀርም የመመረዝ ሕመም (28%)፣ በወሊድ ጊዜ የመታፈን አደጋ (24%)፣ ሕፃናትን በተወለዱ በአንድ ወር ውስጥ ለሕልፈት የሚዳርጉና በብዛት የሚያጋጥሙ ዋና መንስኤዎች ናቸው። በዚህ ረገድ፣ የወባ፣ የኩፍኝ፣ የኤችአይቪ፣ የተቅማጥና የሳምባ ምች የነበራቸው ድርሻ፣ ከ2005 ወዲህ ቀንሷል።

የእናቶች ሞት

በWIDE3 ጥናት ውስጥ፣ ከጥቂት የገጠመኝ ትውስታዎች በቀር፣ በእናቶች ሞት ዙሪያ መረጃ የለም። ከ2011 በፊት በነበሩት 7 ዓመታት፣ ሕይወት ያለው ሕፃን ለመገላገል ከበቁት 100,000 ወሊዶች ውስጥ፣ የእናቶች ሞት መጠን 676 እንደነበረ በ2011ቱ የኢትዮጵያ ህዝብና ጤና ቆጠራ ተገልጿል (EDHS 2011)። ለ2013 በተሰራ ሌላ የጥናት ስሌት ደግሞ፣ ከ100,000 ሕያው ወሊዶች ውስጥ፣ የእናቶች ሞት መጠን 497 ሆኗል (Lancet 2014)። ውርጃ፣ የእርግዝና ወቅት የደም ግፊት፣ የደም መፍሰስ፣ የጀርም ብክለት፣ 'ለእናቶች ሞት በመንስኤነት የሚፈረጁ ናቸው፤ ይህም ችግሮቹን ለመፍታት ተቋሚዊ የጤና አገልግሎት የግድ እንደሆነ ያመለክታል' (የጤና ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ [HSTP] 2015-2019: 9)።

የወሊድ ዓይነትና ቦታ

በገጠር የጤና ተቋማት ውስጥ የሚከናወን ወሊድ በፍጥነት እየጨመረ፣ ከ2011 እስከ 2014 ድረስ፣ ከ4.1% ወደ 10.3% እንዳደገ የየኢትዮጵያ ህዝብና ጤና ቆጠራ መረጃ አሳይቷል። በሰለጠነ ሙያተኛ የታገዘ ወሊድ፣ ከ4% ወደ 9.1% ጨምሯል። ከእነዚህም አብዛኞቹ በከተማ አቅራቢያ የሚኖሩና፣ በኑሮ ደህና የተደላደሉ ሴቶች ናቸው፡ 'በሰለጠነ የጤና ባለሙያ የታገዘ ወሊድ ላይ ለተመዘገበው የመቶኛ እድገት፣ ትልቁን ድርሻ ያበረከተው፣ በኑሮ በደረጁ የከተማ አካባቢዎች የተፈጠረው የመሻሻል ለውጥ ነው' (የጤና ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ፣ 2015-19: 57)። የአሃዛዊው መረጃ ግልባጭ፣ በ2014 የገጠር ሴቶች 90.9% ያህል ልጃቸውን የወለዱት ያለሙያተኛ ድጋፍ እንደሆነ የሚያሳይ ነው። ከእነዚህም መካከል አብዛኞቹ፣ በቤተሰብ አባላት፣ በጎረቤት ወይም በልምድ አዋላጅ ድጋፍ፣ ቤት ውስጥ የወለዱ ናቸው። 5.7% ያህሉ ደግሞ ለብቻቸው ሆነው ወልደዋል።

ወሊድን በተመለከተ፣ በWIDE3 ጥናት ውስጥ ዳጎስ ያለ መረጃ አናገኝም። በ2013 ጥናት በተካሄደባቸውና በኑሮ ደርጀት ባሉት አካባቢዎች፣ ሁሉም ወሊዶች በጤና ጣቢያ ወይም በሆስፒታል መከናወን አለባቸው የሚለው የመንግስት ፖሊሲ ተግባራዊ መሆን መጀመሩን የሚጠቁሙ ምልክቶች ታይተዋል። ለምሳሌ ያህልም፣ ለወሊድ በሚመች ድባብ የተዘጋጀ አንድ ጤና ጣቢያን፣ አንዳንድ የአምቡላንስ ወይም ባህላዊ የአምቡላንስ አገልግሎቶችን፣ ነፍሰጡሮች በጤና ጣቢያ እንዲወልዱ ምክር የሚሰጡ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞችን፣ በየቤቱ ለሚያዋልዱ የልምድ አዋላጆች የተላለፉ ማስጠንቀቂያዎችን መጥቀስ ይቻላል። ይሁን እንጂ፣ በሙያተኛ የተደገፈ የወሊድ አገልግሎት በስፋት እንዳይዳረስ የሚገቱ የአቅርቦት መሰናክሎች አሉ። ከእነዚህም መካከል፡- የጤና ማዕከላት ርቀትና የውስጥ ለውስጥ መንገድ ችግር፣ የሰራተኞች እና የመድሃኒት እጥረት፣ የአምቡላንስ አገልግሎት እጦት፣ እንዲሁም የሆስፒታልና የትራንስፖርት ወጪዎች ይገኙበታል።

ከዚህም በተጨማሪ፣ በ2013 ጥናት በተካሄደባቸው፣ በኑሮና በመገናኛ አውታር ደህና የደረጁ ማኅበረሰቦች ውስጥም ሳይቀር፣ ብዙ ሴቶች በጤና ጣቢያ መውለድን አይመርጡም። ለምን እንደሆነ ሲናገሩም፣ ጤና ጣቢያዎች ጥራት የራቃቸው በመሆናቸው፣ ሙያተኛ ስለሚያጥራቸው ወይም ወንዶች ብቻ በመሆናቸው፣ በትራንስፖርትና በመድሃኒት ወጪ ሳቢያ፣ በጥሪ የሚመጣ አምቡላንስ ስለሌለ ወይም ብርቅ ስለሆነ፣ ከተገኘም እንኳ ከወሊድ በኋላ ወደ ቤት መልሶ ስለማያደርስ፣ ከወሊድ በኋላ ስድስት ሰዓት ሳይሞላት ደጅ መውጣት በባህል ስለማይፈቀድ፣ በቅድመ-ወሊድ

ክትትል አሳሳቢ የጤና እክል ካልታየ የወሊድ ድጋፍ ስለማያስፈልግ፣ የሚሉ የተለያዩ ምክንያቶችን አቅርበዋል።

- ዘመናዊ የወሊድ አገልግሎትን ወደሚያሟላ ሥርዓት የሚደረግ ሽግግር፣ ዘገምተኛ ሂደት ነው።
- የጤና ተቋማትን በመሳሪያና በሰራተኛ ለማደራጀት፣ እንዲሁም የውስጥ ለውስጥ መንገዶችን ለመስራት በቀጣይነት የሚወጣ ገንዘብ፣ በሙያተኛ የታገዘ ወሊድ ይስፋፋ ዘንድ፣ የአገልግሎት አቅርቦትን ያሻሽላል። የአገልግሎት አሰጣጥ ላይ፣ የሴቶች ባህላዊ እምነቶችንና ውሳኔዎችን በትኩረት ማጤንም፣ የአገልግሎት ፍላጎትን ለማሳደግ ያግዛል። እስከዚያ ድረስ ግን...

በአቅርቦት ጉድለት፣ በቦታ ርቀት፣ በድህነት እና በግል ውሳኔዎች ሳቢያ፣ ብዙ ነፍሰጡሮች በቀጣዮቹ የሁለተኛው የዕድገትና ተራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዓመታት፣ በጤና ጣቢያ እና በሆስፒታል የወሊድ አገልግሎት ሳያገኙ ይቀራሉ። ለእነዚህ ሴቶች...

- ከመደበኛው አገልግሎት ባለፈ፣ ወደ ማኅበረሰቡ ይበልጥ በመቅረብ የድጋፍ እጅ መዘርጋት፤ ለምሳሌም ቤት ውስጥ የሚከናወን ወሊድ፣ ጤናማና ንፁህ እንዲሆን የሙያ እገዛ ማቅረብ፡
  - የሪፈራል ሥርዓቱን አሰራር በማሻሻል፣ አደጋ ላይ ለሚወድቁ ነፍሰጡሮች እንዲደርስላቸው ማድረግ፤
  - ደረጃቸው በተሻሻሉ የጤና ኬላዎች ውስጥ፣ በባለዲፕሎማ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች የሚቀርብ የወሊድ አገልግሎትን መልሶ ማስጀመር (የሁለተኛው የዕድገትና ተራንስፎርሜሽን ዕቅድ)፤
  - በጤናማና በንፁህ ወሊድ ዙሪያ፣ እንዲሁም በድንገተኛ አደጋ የድጋፍ አሰጣጥ ዘዴ ላይ ያተኮሩ ስልጠናዎችን በቀጣይነት ለመስጠት፣ ከጤና ልማት ሠራዊት ውስጥ ሴቶችን በአግባቡ መመልመል፤
  - የቤት ውስጥ ወሊድን የማገዝ አጋጣሚ ይኖራቸዋል ተብለው የሚገመቱ ሴቶች በሙሉ፣ ስለ ጤናማና ስለ ንፁህ ወሊድ እንዲያውቁ፣ ለድንገተኛ አደጋም የድጋፍ አሰጣጥ 'ሀሁ'ን እንዲገነዘቡ፣ በጤና ልማት ሠራዊት አማካኝነት ማስተማር ይቻላል። ይህም፣ የዘመነና የመገኛኛ ቴክኖሎጂን በመጠቀም፣ ሊሳለጥ የሚችል ነው።
- ከዋና መስመር ያልተዘረጋ ኤሌክትሪክ - በፀሐይ ወይም በነፋስ ኃይል እና በጥቃቅን ግድብ አማካኝነት የሚመነጭ ኤሌክትሪክ፤ ልዩ ልዩ ሞባይል ስልክ አገልግሎቶችን (ለምሳሌም በጤናማ ወሊድ ላይ ያተኮረ አገልግሎትን[2]) ለመጠቀም፤ እንዲሁም በድንገተኛ አደጋ ወቅት ከሙያተኛ የወሊድ አማካሪዎች ጋር ለመገናኘት ያስችላል።

[2] ለምሳሌ በኢትዮጵያ የተሞከረውን http://www.maternity.dk/en/The%20Safe%20Delivery%20App ይመልከቱ።

የድህረ-ወሊድ ጉዳዮች

የድህረ-ወሊድ አገልግሎት

WIDE3 የተመለከታቸው ማኅበረሰቦች፣ በተለያየ መልክ፣ የቪታሚን ኤና የክትባት፣ የሚያጠቡ እናቶችም የአልሚ ምግብ አቅርቦት መኖሩን ተናግረዋል። ከወሊድ በኋላ ጊዜ ሳይሰጡ ቶሎ በሥራ እንዳይጠመዱ እና ልጃቸው ለስድስት ወር የጡት ወተት ብቻ እንዲመግቡ የሚያስረዳ ትምህርት መሰጠቱንም ገልፀዋል። የእናቶች ምግብን፣ የሕፃናት ንፅሕናን፣ ደህና አለባበስን፣ ሕፃናትን ለሕክምና መውሰድን፣ ሴትና ወንድ ሕፃናት አለማበላለጥን በተመለከተ የተሰጡ ትምህርቶችንም ጠቅሰዋል። በእነዚህ ጉዳዮች ዙሪያ፣ እናቶች ምን ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው በቅጡ እንዲታወቅ፣ በተለይ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ባደረጉት ጥረት የተነሳ፣ ሰፊ ግንዛሬ ተፈጥሯል። ነገር ግን፣ ሁሉም ሴቶች የተማሩትን ነገር በተግባር ይፈፅማሉ ማለት አይደለም። አንዳንዶቹ በስራ ተጠምደው ፋታ ያጣሉ፤ አንዳንዶቹ ፍላጎት የላቸውም፤ አንዳንዶቹ ድህነት ከብዷቸዋል። በሁለት አካባቢዎች (ምናልባትም በሌሎች አካባቢዎች ጭምር)፣ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች፣ በምግብ እጥረት የተጎዱ ሕፃናትን ለመመዝገብ፣ ቤት ለቤት እየዞሩ ይጎበኛሉ። በሃርረሳው፣ ሴቶች ለ10 ወራት፣ ከምግብ ዋስትና የስራ ሃላፊነት እረፍት ያገኛሉ።

የጨቅላ ሕፃናት ሕመም

በ2003 እጅጉን ተዘውትረው የተጠቀሱ የጨቅላ ሕፃናት ሕመሞች፣ ተቅማጥ፣ ትውከት፣ የምግብ እጥረት እና ወባ ነበሩ። በንፁሕ ውኃ፣ በተሻሻለ ምድጃና ማድቤት፣ በኢኮኖሚ እድገት፣ በምግብ እርዳታ፣ እንዲሁም በወባ መከላከያና ሕክምና እርምጃዎች አማካኝነት፣ የእነዚያ ሁሉ ሕመሞች ክስተት እንደቀነሰ መናገር ይቻላል። በWIDE3 ጥናት ውስጥ፣ በጨቅላ ሕፃን ሕመም ላይ ያተኮረ መረጃ የለም። የገንዘብ አቅም ያላቸውና ወደ ጤና ጣቢያ ቀረብ ብለው የሚገኙ ነዋሪዎች፣ ጨቅላ ሕፃን ሲታመም ወደ ሕክምና መውሰድን እያዘወተሩ እንደሆነ የሚያሳዩ መረጃዎች ግን አሉ።

የአገልግሎት ተደራሽነት

ድህነት የጠናባቸው ብዙ ሴቶች፣ ወሊድ ነክ አገልግሎቶችን በክፍያ የመጠቀም አቅም የላቸውም። ርቀው የሚኖሩ ሲሆን ደግሞ፣ ወሊድ ነክ አገልግሎቶችን ማግኘት ለሁሉም ሴቶች አስቸጋሪ ይሆናል። ሌሎች ሴቶችም፣ አገልግሎት እንዳያገኙ የሚገድብ ብዙ ዓይነት መሰናክል ይገጥማቸዋል፣ ለምሳሌ ትብብር የሚነፍግ ባል ይጠቀሳል።

- መንግስት፣ ለሁሉም ነፍሰጡሮችና ለሁሉም ሕፃናት ጤንነት እንዲሁም ደህንነት ሙሉ ሃላፊነት መውሰድ ይኖርበታል። በቅጡ የተቋቋመ የሴቶች የወሊድ መብት፣ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡
  - ቅድመ-ወሊድና ድህረ-ወሊድ የጤና አገልግሎት፣ በተቻለ መጠን በአቅራቢያቸው ማግኘት፤ እንደመመሪያ የተዘጋጀ የወሊድ ፈቃድ የጊዜ መጠን።

- በቅድመ-ወሊድ ምርመራ የጤና ችግር ለተገኘባቸው ሁሉ፤ ወይም በምጥ ጊዜ ለድንገተኛ አደጋ ለተጋለጡ ሁሉ የባለሙያ የወሊድ አገልግሎት ወይም የማህፀን ሐኪም ድጋፍ በነፃ ማግኘት ።
- ወንዶች፣ ከነፍሰጡርና ከምታጠባ እናት ጋር በተያያዘ፣ የአመጋገብ፣ የንፁህ ውኃ፣ የስራ ጫና፣ ከባድ እቃ የማንሳት፣ የእረፍት፣ ቅድመና ድህረ የወሊድ አገልግሎት ጉዳዮች ዙሪያ ንቃት እንዲያገኙ ማድረግ።

የሴቶችና ልጃገረዶች ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ

የሴቶችና ልጃገረዶች ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ በገጠር ኢትዮጵያ ማህበረሰቦች (2010-13)

WIDE የውይይት መነሻ አጭር መግለጫ ቁ. 6/...1ø

ዋና ዋና ነጥቦች ከWIDE መረጃዎች

- የሴቶች እና ልጃገረዶች በገጠር ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ ያደገ ሲሆን በዓይነትም ተስፋፍቷል፤ እርሻም ሆነ እርሻ ዘለል ዘርፎች ትላልቅ ኢኮኖሚያዊ አማራጮችን ፈጥረዋል፡፡ ነገር ግን ይበልጥ በኢኮኖሚው ላይ ያተኮሩ የለውጥ እርምጃዎችና ሰፊ ፍትሃዊ የቅጥር ከባቢ እንዲፈጠር የሚያበረታቱ መልዕክቶች አንጻር የታዩት ድክመቶች፣ ሊመጣ ይችል የነበረውን ለውጥ ወይም መሻሻል ገድበውታል፡፡
- ሰፊ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች፣ ለሴቶች እና ልጃገረዶች የሥራ ዕድሎችን ያሰፋሉ (የፋብሪካዎች ሥራ፣ ሰፋፊ የንግድ እንቅስቃሴዎች፣ ከመስኖ ልማት ጋር የተገናኘ የጉልበት ሥራ) የሚጠቀሱ የሥራ አይነቶች ናቸው፡፡ ነገር ግን የቅጥር ኢፍትሃዊነት ጥያቄ በግልጽ የሚታይ ነው፤ በአንዳንድ የኢንዱስትሪ አካባቢዎችና የቀን ሥራ ላይ የደሞዝ ክፍያ አለመመጣጠኖችን (ወይም ዝቅተኛነትን) ጨምሮ ህፃናትን የመንከባከብ ወይም (ተያያዥ) ኃላፊነት ያለባቸው ተቀጥረው የሚሰሩ ወይም መቀጠር የሚሹ ሴቶች የሚገጥሟቸው ማነቆዎች በርካታ ናቸው፡፡ በሌላ በኩል፤ በሴት የሚተዳደሩ ቤተሰቦች ምርታማነት አብዛኛውን ጊዜ የጉልበት ሠራተኛ ለመቅጠር በሚወጣው ወጪ ይገደባል (መሬታቸውን የእኩል የማሳረስ አማራጭ ደግሞ የችግር ተጋላጭነታቸውን ይጨምረዋል)፡፡
- እየሰፋ ከመጣው ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ፣ የሰራተኞችንም ሆነ የአሰሪዎችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣ ፍትሃዊ የሥራ ቅጥርን/ተደራሽነትን ተፈጻሚ ማድረግ ይጠይቃል፡፡ በ2009 ብሔራዊ የሥራ ቅጥር ፖሊሲና ስትራቴጂ እንዲሁም በ2003 የሥራ ህግ ላይ የተቀመጠውን ማጤን ያሻል)፡፡ ለምሳሌ ያህል በተጨማሪ ከሚያካትታቸው ጉዳዮች፤ የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

---

[1] ይህ አጭር የጥናት መግለጫ፤ በWIDE የውይይት መነሻ አጭር የጥናት መግለጫዎች ሁለተኛ ጥራዝ (ስብስብ) ውስጥ ከተካተቱት አስር መግለጫዎች አንዱ ነው፡፡ መግለጫው፤ በሊሊ ላቭሌይና ካትሪን ዶም የተዘጋጀ ሲሆን በእመቤት ሙሉጌታ ተገምግሟል፡፡ አዘጋጆቹ፤ መግለጫዎቹ ይሰናዱ ዘንድ በገንዘብ ለደገፉት ለእንግሊዝ ዓለም አቀፍ የልማት ተቋም፣ ለአይሪሽ ኤይድና ለስዊድን ዓለምአቀፍ የልማት ኤጀንሲ ልባዊ ምስጋናቸውን ያቀርባሉ፡፡ በተጨማሪም የጥናት ሪፖርቱን በማርቀቅ ሂደት የተሳተፉና አጭር የጥናት መግለጫው የትኩረት አቅጣጫ እንዲሰላ እገዛ ያደረጉ ሌሎች የጥናት ቡድን አባላትና ባለሙያ ገምጋሚዎች፣ ለሥራው ለሰጡት ጊዜና ድጋፍ ያመሰግናሉ፡፡ ሌሎች ምስጋናና ዕውቅና የሚያሻቸውም አሉ፡- (1) ለዓመታት የጥናት መግለጫው የተዘጋጀበትን መረጃዎች ያሰባሰቡና ያደራጁ የጥናት መኮንኖችና ተቆጣጣሪዎች ሙሉ ጊዜያቸውን ሰጥተው ላበረከቱት አስተዋጽኦ፤ (2) በሶስት ዙሮች ለተካሄደው የWIDE ጥናት የገንዘብ ዕገዛ ላደረጉ የተለያዩ ድጋፍ ሰጪ ተቋማት፤ እና (3) በኢልምተ ሰብሳቢነትና በኢኮኖሚ ፖሊሲ ትንተና ክፍሉ በWIDE አጭር የጥናት መግለጫዎች ሁለተኛ ጥራዝ ላይ ለመወያየት መጋቢት 28 ቀን 2016 ዓ.ም በተዘጋጀው መድረክ ላይ የተሳተፉ ከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣናት፣ ላሳዩት ፍላጎትና ለከፈሉት የጊዜ መስዋዕትነት--- ምስጋና ይገባቸዋል፡፡ የጥናት መግለጫው፤ በከፍተኛ ደረጃ በተዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ፣ ከመንግስት ባለሥልጣናት ጋር በተደረገው ውይይት የተሰጡ አስተያየቶችን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ከለሳና ማሻሻያ ተደርጎበታል፡፡ አጭር የጥናት መግለጫው፤ የኢትዮጵያ የልማት ምርምር ተቋምን (ኢልምተ) ወይም የኢትዮጵያ መንግስትን አሊያም የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርጉለትን የልማት አጋሮች አመለካከትም ሆነ አቋም አይወክልም፤ ይልቁንም የፖሊስ ውይይት ለማነቃቃት የታለመ ነው፡፡ ሌሎች የጥራዝ ሁለት የውይይት መነሻ አጭር መግለጫዎችንና የጥናትና ምርምር ውጤቶችን በhttp://ethiopiawide.net/ ድረ-ገጽ ላይ ማግኘት ይቻላል፡፡

- ለሴቶችና ለወንዶች፣ ለተመሳሳይ ሥራ ተመሳሳይ ክፍያን ተግባራዊ ማድረግ፤
- የህፃናት እንክብካቤ አገልግሎት አማራጮች እንዲሁም የወሊድ መብቶች፣ በመሰረታዊ የሥራ ሁኔታ ቁጥጥር ውስጥ መካተታቸውን ማረጋገጥ፤
- የቅጥር መብቶች ግንዛቤን ማስፋፋት፤ሴቶች (እንዲሁም ወንዶች) የበለጠ መብታቸውን ለማስከበር እንዲችሉና ከብዝበዛ ነጻ በሆነ በእኩል ሁኔታ ለቅጥር የመደራደር አቅማቸውን ማጠናከር፤
- ነባር ፕሮግራሞችን ማሳደግ፣ ባለሃብቶች፣ የሴቶችን ቅጥር የሚያሻሽል ተጨማሪ እርምጃ እንዲወስዱ ያበረታታቸዋል።

- ሴቶች የሚሳተፉበትን የሥራ ዘርፍ በመወሰን ረገድ መነሻ ካፒታል፣ገንዘብ፣ንብረቶችና የግለሰብ ወይም ቤተሰብ ሃብት ቁልፍ ሚና አላቸው። መሬት ወይም መነሻ ካፒታል የሌላቸው ሴቶች፤ ውጤታማ ባልሆኑ፣ ‹ከእጅ ወደ አፍ› እንቅስቃሴዎች ውስጥ ይጠመዳሉ ወይም ደግሞ መደበኛ አሊያም መደበኛ ያልሆነ ድጋፍ ጥገኛ ይሆናሉ። በሌላ በኩል፤ በሀብት የደረጁ ሴቶች፣ በተሰማሩባቸው ዘርፎች፤ ለምሳሌ፡- የንግድ ድርጅቶችን በማስተዳደር ወይም ሰፋ ባለ ንግድ ላይ በመሰማራት፣ ስኬታማ መሆናቸውን ይገልጻሉ።
- የብድር አቅርቦት፤ አንዳንድ ሴቶች፣ ገቢ-አመንጪ የሆኑ ሥራዎችን እንዲጀምሩ ያግዛቸዋል። ሆኖም ግን ለኪሳራ የሚዳርግ፣ እጥረት ያለበትና ተደራሽነቱ ውስን ነው ተብሎ ይታሰባል፤ አንዳንዶችንም ለባሰ የኢኮኖሚ ማሽቆልቆል ዳርጓቸዋል። ለድሃ ወይም በጣም ድሃ ለሆኑ ሴቶችና ቤተሰቦች፣ የምግብ ዋስትና ድጋፍ ቀጥተኛ እገዛ፣ የምግብ ፍጆታ ጥያቄያቸውን ለማሟላት በጣም ወሳኝ ነው። ነገር ግን ይሄ ድጋፍ ብቻውን ድህነትን ለማሸነፍ እንደሚያስችላቸው የሚጠቁም መረጃ አልተገኘም።
- እንደ ሰፊ የማህበረሰብ ዋስትና እንቅስቃሴና የኢኮኖሚ ተሳትፎ ፖሊሲዎችን ማስፋፊያ አካል፣ መንግስት በተለይ ድህነት የበረታባቸው ሴቶችን ለመደገፍ የሚያግዙ ፕሮግራሞችን ከግምት ውስጥ ሊያስገባ ይችላል። ለምሳሌ፡-
  - በአግባቡ የታለመ “የካፒታል ማነቃቂያ” መስጠት (በገንዘብ ድጋፍ/በቂ መጠን ባለው የንብረት ዝውውር፤ ከበቂ ስልጠና፣ ዝግጅትና ክትትል ጎን ለጎን)፤በጣም ድሃ ለሆኑ ሴቶች፣ ብድር መውሰድ አዋጭ ወደሚሆንበት ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ያስችላቸዋል[2]።
- ምንም እንኳ ሴቶችን ወይም ልጃገረዶችን እንዲያካትቱ የሚደግፉ የፖሊሲ ማዕቀፎች ቢኖሩም ወንዶችንም ሆነ ሴቶችን ያለሙ የኑሮ መተዳደሪያ የለውጥ እርምጃዎች ቢኖሩም ሴቶችን ወይም ልጃገረዶችን ሲያካትቱ አይስተዋልም። ሴት አርሶ አደሮችና ያገቡ ሴቶች፤ ብዙውን ጊዜ በተለያዩ ምክንያቶች፣ በግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎቶች መርሃ ግብር አይሸፈኑም። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ወጣት ሴቶች ብዙ ጊዜ በወጣት ማህበራት የለውጥ እርምጃዎች ይዘነጋሉ።

[2] በትግራይ በ CGAP-Ford ፋውንዴሽን የምረቃ ፕሮግራም፣ የተተገበረው የሙከራ ፕሮግራም፣እነዚህ ዕቅዶች በአግባቡ ተነጣጥረው ሲታለሙና በበቂ ድጋፍ ሲታጀቡ፣ "የምግብ ዋስትና ድጋፍን በስልት ለማሳደግ" እና "ከድህነት መውጫ መንገድ" ለመከፈት ያላቸውን አቅም አጉልቶ ያሳያል (Sengupta, A. (2012): Pathways out of the Productive Safety Net Programme: Lessons from Graduation Pilot in Ethiopia: Working Paper. CGAP/Ford Foundation. June 2012. ሪፖርት ይመልከቱ)።

ከእርሻ ውጭ የሆኑ አማራጮችን የሚደግፉ የመንግስት የለውጥ እርምጃዎች ባለመኖራቸው ተስፋ መቁረጥ ተከስቷል።

- መንግሥት፤ የለውጥ እንቅስቃሴዎች ለወንዶችም ለሴቶችም በተጨባጭ መድረሳቸውን የሚያረጋግጡ እርምጃዎችን ከግንዛቤ ውስጥ ሊያስገባ ይችላል፤ በተለይም፡-
  - በወንድ የሚተዳደሩ ቤተሰቦች ውስጥ የሚገኙ ሚስቶችን ጨምሮ፣ የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት መርሃ ግብር ለሴቶች እንዲደርሱ ማድረግ፤ ነገር ግን የሴቶች ተብለው ከሚታወቁ የኢኮኖሚ ዘርፎች ውጭ ያሉትንም የሚያካትት ድጋፍ መስጠት፤
  - የወጣቶች የህብረት ሥራ ማህበራትና ሌሎች የወጣት የኑሮ መተዳደርያ የለውጥ እርምጃዎች፤ የወጣት ሴቶች የተለዩ ጥያቄዎች፣ ፍላጎቶችና ገደቦችን ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፤
  - በገጠር አካባቢዎች አነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት እንዲስፋፉና ለሴቶችም ለወንዶችም እንዲደርሱ ድጋፍ ማድረግ።
- የፆታ እኩልነትን የማስፈን ሰፊ እርምጃ፤ በሴቶች አቅም ዙሪያ የነበረውን ግንዛቤ በተመለከተ፣ በማህበረሰባዊ ልማዶች ላይ ተፅዕኖ ይፈጥራል። እርስ በእርስ በመደጋገፍ ሂደትም፣ በኢኮኖሚ ስኬታማ የሆኑ ሴቶች፣ በአመለካከት ላይ ሰፊ ለውጦችን ለማምጣት ከፍተኛ ተጽዕኖ ያላቸው ሲሆን ሌሎች ሴቶች ወይም ልጃገረዶች ለራሳቸው ይቻላል ብለው በሚያስቡት ላይም ተፅዕኖ ያሳድራል። ይሁን እንጂ የሴቶችን ወይም ልጃገረዶችን የኑሮ መተዳደሪያ በቀጥታ ለመደገፍ "በቂ አልተሰራም" የሚል ስሜት ይንፀባረቃል። የመንግስት የለውጥ እርምጃዎች በሚኖሩበት ወቅትም ውጤታማነታቸው ውስን ነው (ለምሳሌ፡- የሴቶች የህብረት ሥራ ማህበራት አቅም እንዳላቸው ቢያሳዩም፣ ውስን በሆነ የመንቀሳቀሻ አቅም፣ በደካማ አመራርና አነስተኛ የምርት ሽያጭ የተነሳ ይንገዳገዳሉ)።
- ሥራ ክፍፍልና በውሳኔ ሰጪነት ላይ ያሉ የወንድ ስጋቶች ወይም አትራፊ በሆኑ ንግዶች ላይ የሚታይ ፉክክርን ጨምሮ ቀላል የማይባሉ ማህበረሰባዊ ማነቆዎች አሁንም ቀጥለዋል ። ሴቶች "ብዙ እንደሚሰሩ" (የአምራችነትና የሥነ ተዋልዶ ኃላፊነቶች) ይገልጻሉ፤ ነገር ግን በገቢ ላይ ቀጥተኛ ውሳኔ ሰጪነት እንዳላቸው የሚያሳይ በቂ ማስረጃ የለም።
- በኢኮኖሚያዊ ተሳትፎና በተለወጡ ማህበራዊ ልማዶችና አመለካከቶች እንዲሁም የእኩልነት ቀጣይ ማህበረሰባዊ እንቅፋቶችን ለማሸነፍ፣ እርስ እርስ ተደጋጋፊ ሂደቶችን አዎንታዊ በሆነ መልኩ የሚያጠናክሩ እርምጃዎች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡-
  - የሴቶች ወይም ልጃገረዶች ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎን ለመደገፍ የታለሙ፣ ከአካባቢያዊ ነባራዊ ሁኔታ አንጻር የተቃኙ የለውጥ እርምጃዎችን ማጠናከር (ለምሳሌ፡- ለሴቶች የህብረት ሥራ ማህበራት በቂ ድጋፍ ማድረግ የሚጨምር)፤
  - የፆታ እኩልነትን የሚያንፀባርቁ መልዕክቶች፤ወንዶችንም ሴቶችንም በአግባቡ ማሳተፋቸውን ማረጋገጥ፤ ለምሳሌ የፆታ እኩልነትን የሚያንፀባርቁ መልዕክቶች፤ “ተጨባጭ ህይወት” ላይ ያነጣጠሩ በማድረግና "የተጨባጭ ህይወት" ስጋቶችን ለመቅረፍ

መሞከር፡፡ እነዚህ መልዕክቶች በተለይ ወንዶች የሚያነሷቸው ጉዳዮች ላይ ማነጣጠር ይገባቸዋል፡፡

- በማህበረሰቦች ውስጥ ያሉ አርአያ የሆኑ ሴቶችን ተፅዕኖ ማስፋት (ከዘርፈ ብዙ የኢኮኖሚ/ሙያ ዘርፎች እንዲሁም በገጠር አካባቢዎች ከሚገኙ ሴቶችና ልጃገረዶች ጋር የጋራ የሆኑ ተሞክሮዎችን መለዋወጥ) ይሄንንም ይበልጥ በታለመና ውጤታማ በሆነ የግለሰቦች አጭር ታሪክ አማካኝነት ማከናወን (ለምሳሌ፡- ሴቶች በት/ቤቶች ንግግር እንዲያደርጉ በመጋበዝ፣ የሚዲያ ክበቦች አዎንታዊ የሴቶች የኑሮ ውጣውረድ እንዲያነሱ ማበረታታት፤ መደበኛ ያልሆኑ የማህበረሰብ ቡድኖች ለ“ስኬት” ዕውቅና እንዲሰጡና እንዲያስተዋውቁ ማነሳሳት ይጠቀሳሉ)፡፡

<u>መግቢያ</u>

በWIDE መጀመሪያ ላይ በ1995፣ በመቀጠልም በ2010-13 (መግቢያ) ጥናት ከተደረገባቸው 20 የኢትዮጵያ የገጠር ማህበረሰቦች ከተሰበሰበው መረጃ፣የተሰራው ትንተና ላይ መሰረት በማድረግ፣ይሄ አጭር መግለጫ የሚከተሉትን ይጠቁማል፡- 1) የሴቶች ወይም ልጃገረዶች ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ ማደጉንና በዘርፍም መስፋቱን፤ 2) በማህበረሰብ - ደረጃ (ኢኮኖሚያዊና ማህበረሰባዊ) እና በግለሰብ - ደረጃ (ለምሳሌ፡- ማህበረሰባዊ ቦታ) የተፈጠሩ ልዩ ጥምረት የኢኮኖሚ ተሳትፎን እንደሚወስኑ፤ በአብዛኛው በሰፊ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች፣ እንዲሁም የግለሰብ ወይም ቤተሰብ ሃብት ወይም የመነሻ ካፒታል ተደራሽነት፤ አዳዲስ ኢኮኖሚያዊ አማራጮችን መፍጠሩን፤ 3) የኑሮ መተዳደሪያዎችን ለመደገፍ የሚተገበሩ የመንግስት የለውጥ እርምጃዎች ደካማነት፣ዕድገት መሆን ያለበትን ያህል ተሟጥጦ ጥቅም ላይ አለመዋሉን፤ 4) የሴቶች ወይም ልጃገረዶች ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ፣ እርስ በእርስ ለሚደጋገፉ ማህበረሰባዊ የአመለካከት ለውጥ አስተዋጽኦና ተጽዕኖ ማድረጉን፡፡

መረጃው፤ የፖሊሲ አንደምታዎች መነሻ የሚፈጥር ሲሆን መንግስት፤ የሴቶችን ወይም ልጃገረዶችን ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ የበለጠ ለማጠናከር ከግንዛቤ ውስጥ ሊያስገባቸው የሚችሉ አማራጮችን ያቀርባል - ሁለቱም ደግሞ ሰፊ የጾታ እኩልነት የማስፈን እርምጃና የሴቶችን አቅም የማጎልበት ግቦችን እንዲሁም እውን ለማድረግ የሚያልመውን የኢትዮጵያ ትራንስፎርሜሽንን ለማሳካት ያግዛሉ፡፡

<u>የኢኮኖሚ አማራጮችን ማስፋት፡ የለውጥ አዝማሚያዎች</u>

የእርሻም ሆነ ከእርሻ ውጭ የሆኑ ዘርፎች ለኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ ትልቅ አማራጮችን ፈጥረዋል፡፡ ሴቶች በግብርናው ዘርፍ ትርጉም ባለው መልኩ መሳተፋቸውን የቀጠሉ ሲሆን ከ2010-13 ባሉት ጊዜያት፣ ለሴቶች የእርሻ የጉልበት ሥራ ማከናወን በጣም የተለመደ ነበር (በ2010-13 በ12 ማህበረሰቦች፣ በ1995 በ3 ማህበረሰቦች መኖሩ ተነግሯል)፡፡ በ1995 መኖራቸው ያልተነገረ የአካባቢ ኢንዱስትሪ (ለምሳሌ፡- የፋብሪካዎች/የአበባ እርሻዎች ሥራ) የቅጥር ዕድሎች፣ በ2010-13 ትርጉም ባለው መልኩ ተፈጥረዋል፡፡

የአነስተኛ ወይም ጥቃቅን ንግዶች እንቅስቃሴ፣ ከሞላ ጎደል በሁሉም ማህበረሰቦች የተገለጹ ሲሆን ሴቶች በሰፋፊ ንግዶች ላይ የሚያደርጉት ተሳትፎ እያደገ መጥቷል (በ6 ማህበረሰቦች የተመዘገበ ሲሆን በ1995 ግን ሁሉም ሰፋፊ ንግዶች የሚከናወኑት በወንዶች ነበር)። የመንገድ ዳር ንግድ በጥቂት ማህበረሰቦች ብቅ ብቅ ያሉ ሲሆን ሴቶች እንደ ሻይ ቤቶች፣ ምግብ ቤቶች፤ መጠጥ ቤቶች፣ ጥቂት የፀጉር/የውበት ሳሎኖች ያሉ አነስተኛ የንግድ ድርጅቶችን በመምራት በስፋት ተሳትፈዋል)። በ2010-13 የአልኮል መጠጦችን ማምረት መስፋፋቱን የቀጠለ ሲሆን በ13 ማህበረሰቦች፣ ሴቶች መሳተፋቸው ተነግሯል (በ1995 ከነበረው 11 አንጻር)። በ1995 እና በ2010-13፣አንዳንዶች ከዚህ ምርት ተጠቃሽ ገቢ አግኝተዋል (ለምሳሌ፡- ቱሩፌ፣ የትመንና ኮርማርገፍያ ይጠቀሣሉ)። ነገር ግን በአራት የደቡብ ማህበረሰቦች፤ ይሄ እንቅስቃሴ በ2010-13 የቆመ ሲሆን ለውጡ በአካባቢው ከተጀመረው የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ጋር የተገናኘ ሊሆን እንደሚችል ይገመታል። ምክንያቱም እምነቱ 2010-13፣ በሴቶች የህብረት ስራ ማህበራት ውስጥ መሳተፍ ይበልጥ የተስፋፋበት ወቅት ነው። በበርካታ የእርዳታ ጥገኛ ማህበረሰቦች ውስጥ፤ ሴቶች ወይም ልጃገረዶች በመንግስት ወይም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ምግብ ወይም ገንዘብ ለሥራ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳትፈዋል። በ1995፣ የሴቶች ሥራ ፍለጋ፣ ወደ ከተሞችና ባህር ማዶ መጓዝ፣ በ3 ማህበረሰቦች ውስጥ ብቻ የተጠቀሰ ሲሆን በ2010-13፣ በአብዛኞቹ ማህበረሰቦች ታይቷል (ማጣቀሻ፡- ፍልሰት)።

ከግራር በስተቀር ጥጥ መፍተልና ዕደጥበባትን የመሳሰሉ ባህላዊ ስራዎች የቀነሱ ይመስላሉ። በዚህ ማህበረሰብ ቀደም ሲል የሸክላ ሥራ ተቃውሞ ቢገጥመውም፣ በ1995 ዳግም ብቅ ያለ ሲሆን በ2010 መስፋፋት ችሏል። ይሄ ዘርፍ በተለይ ለድሃ ልጃገረዶችና ሴቶች ጠቅሟል። የዘርፉ መቀነስ የተከሰተው፣ ሴቶችና ልጃገረዶች ከ1995 ይልቅ በ2010-13፣ በሌሎች ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በመሳተፋቸው ሊሆን ይችላል። በተለይ ደግሞ የተሻለ የግንኙነት ትስስር በፈጠሩ አልያም ይበልጥ ከተሜነት ባላቸው ማህበረሰቦች ይህ ሁኔታ ተንፀባርቋል። ከውጭ የሚገቡ ቁሶች፣ ሴቶች በባህላዊ መንገድ የሚያመርቱትን መተካታቸውም ለዘርፉ መቀነስ በምክንያትነት ሊጠቀስ ይችላል።

በአጠቃላይ እየሰፋ ከመጣው ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ ጎን ለጎንም፣ የሥራ ዕድል አለመኖርን የሚጠቁሙ ሁኔታዎች እንደነበሩ ተነግሯል። በከፍተኛ መጠን የጨመረው ሥራ ፈላጊ ስደተኛ፣ የአካባቢ የሥራ ዕድል አማራጮች ውስንነትን የሚጠቁም ሲሆን የመሬት እጥረት የወጣቶችን የሥራ ዕድሎች መገደቡ ተነግሯል፤ ለምሳሌ፡- በገብለን፣ ግራር፣ አዜ ዴቦአ። የኢንዱስትሪዎች መዘጋትም በግለሰቦች የቅጥር ሁኔታ ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ ይፈጥራል፤ ለምሳሌ፡- በገልቻ የተዘጋው የብረታ ብረት ሪሳይክሊንግ ፋብሪካ ተጠቃሽ ነው።

<u>ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ፡ ወሳኝ ቁልፍ ጉዳዮች</u>

የእያንዳንዷ ሴት ወይም ልጃገረድ ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ፤ በማህበረሰብ ደረጃ ባሉ የኢኮኖሚ ጉዳዮች፣ በማህበረሰባዊ ልማዶችና በእነዚህ ላይ በሚፈጠሩ ለውጦች እንዲሁም በማህበረሰብ ውስጥ በሚሰጥ ደረጃና በተወሰኑ ንብረቶችና ጥሪቶች አቅርቦት፣ ልዩ ጥምረት የሚወሰን ነው። የWIDE መረጃ፤ እነዚህ የተለያዩ በርካታ ጉዳዮች፣ እንዴት ዘርፈ ብዙ የግለሰብ ተሞክሮዎችን እንደፈጠሩ በጥልቀት ያብራራል።

የማህበረሰብ አውድና የሰፊ መሰረተ ልማት ግንባታዎች ፋይዳ

ሰፊ የማህበረሰብ አውድ፤ ለሴቶች በሚኖሩት የገቢ ማግኛ አማራጮች ላይ ወሳኝ ሚና አለው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ከኢንቨስትመንቶች ጋር የተገናኙ ሲሆን የሚገኙትም ባደጉ ወይም ጥሩ መንገዶች ባላቸው፣ ከገበያ ማዕከሎች ጋር በቅጡ በተሳሰሩ፣ ወይም በንፅፅር ሰፊና በፍጥነት እያደጉ በሚገኙ የከተማ ማዕከሎች አቅራቢያ በሚኖሩ ማህበረሰቦች ውስጥ ነው (ማጣቀሻ፡- የገጠር ከተሜነት መስፋፋት)፡፡

መዋቅራዊ ለውጥ፤ የሴቶች ወይም የልጃገረዶች ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎን በማሳደግ ረገድ ወሳን ሚና ይጫወታል፡፡ የመስኖ ወይም አዳዲስ የገበያ ሰብሎች ምርት መስፋፋትና መጀመር፣በአንዳንድ የተጠቀሱት አካባቢዎች፣ የቀን ሥራ ዕድሎችን (ከገልቻ በቀር በቆሮደጋጋ፣ አዴሌ ኬኬ፣ ዶአማ፣ ሃረሳው፣ ሹምሽሃ፤ በየትመን እየተፈጠረ ነው)፤ ወይም ለሴቶች የንግድ አማራጮችን ፈጥረዋል (ለምሳሌ፡- የሶሞዶ ከፍተኛ መጠን ያለው የቡና ንግድ) ሊጠቀስ ይችላል፡፡

የኢንዱስትሪ መስፋፋት ቀስ በቀስ እያደገ ሲሆን ለሴቶችና ልጃገረዶች አዳዲስ ዕድሎችን ፈጥሯል፡፡ በእርግጥ በሁሉም ቦታ በተመሳሳይ መጠን አይደለም፡፡ እንዲህ ዓይነት ዕድሎች ከውስጣዊ የአካባቢ/አቅራቢያ ኢንቨስትመንት ጋር የተቆራኙ ሲሆን በዋናነት የሚገኙትም ለከተማ ማዕከሎች ቀረብ በሚሉና ጥሩ የመንገድ ተደራሽነት ባላቸው አካባቢዎች ነው (ለምሳሌ ያህል፡- ሀበሻ ቢራ ፋብሪካ፣ የግል የወተት ተዋፅኦ ምርት፤ በኮርማርገፍያ ውስጥ/አቅራቢያ የሽሮ ማቀነባበሪያ ፋብሪካዎች፤ ሌሎች ምሳሌዎች ደግሞ በአዳ ዳዋታ፤ ቱሩፊ፣ ሲርባ ይጠቀሳሉ)፡፡ ከኢንዱስትሪ ጋር የተገናኙ ዕድሎች በጣም ርቀው በተነጠሉ ወይም ተደራሽነታቸው አስቸጋሪ በሆኑ ማህበረሰቦች ውስጥ ከተለዩ፤ እንደ ቡና ምርት ካሉ ሁኔታዎች ጋር የተያያዙ ካልሆነ በስተቀር እምብዛም አይገኙም፡፡ ይሄም ግን የራሱ ባህሪ አለው፤ ለምሳሌ፡- የግል የቡና እርሻዎች ባሉት አዜ ዴቦአ (ለሴቶች ከእርሻ ውጭ የሆነ ከፍተኛ የሥራ ዕድል ይሰጣል) በአንፃሩ ጋራ ጎዶ፤ ርቀው የሚገኙ ናቸው፡፡ በሶሞዶ ደግሞ (የተሻለ ትስስር ቢኖረውም) ምንም የለም ::

በተለያዩ የማህበረሰብ የከተማ መስፋፋት ዓይነቶችና ሴቶችና ልጃገረዶች በሚያከናውኗቸው የሥራ ዘርፎች አንፃራዊ ፋይዳ መካከል ትስስሮች አሉ፡፡ ለምሳሌ፡- በዲንኪና ቆሮደጋጋ፤በአነስተኛ ንግዶች ላይ የተሰማሩ ሴቶች የሉም፤ እኒህ በ2010 ላይ፣ ምንም ዓይነት የከተማ መስፋፋት ያልተጀመረባቸው ሁለቱ ብቸኛ ማህበረሰቦች ናቸው፡፡ አነስተኛ ንግዶችን የሚያካሂዱ ሴቶች ውስጣዊ የከተማ መስፋፋት ባላቸው ማህበረሰቦች የሚገኙ ሲሆን ከትላልቅ የከተማ ማዕከሎች (ለምሳሌ ገብለን) በእጅጉ ርቀው ላሉ አካባቢዎች፣ ከፍተኛ የከተማ አገልግሎት ፍላጎት ምላሽ ሊሰጥ ይችላል፡፡ እኒህ ሴቶች በከተማ ዳርቻ ባሉ ማዕከሎችም የሚገኙ ሲሆን (ላሊበላ አቅራቢያ ባለው ሹምሽሃ፣ ሻሸመኔ አቅራቢያ ባለው ቱሩፊ) ነዋሪዎች በመለስተኛ ከተሞች ያሉ አገልግሎቶችን በአካባቢያቸው ማግኘታቸው ምቹ ሆኖላቸው ይሆናል፡፡ ምግብና መጠጦችን ለሽያጭ ማሰናዳትም መለስተኛ ከተማ አቅራቢያ ወይም በመጠኑ ሰፋ ያለ የከተማ ማዕከል ባላቸው ማህበረሰቦች ዘንድ ይበልጥ የተለመደ ነው፡፡(በቱሩፊ የሚዘጋጀው ለከተማ ፍጆታ መሆኑ በግልጽ ተነግሯል)፡፡

በኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦትና ሴቶች በሚያከናውኗቸው የተወሰኑ ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች መካከልም ትስስሮች አሉ፡፡ አነስተኛ የንግድ እንቅስቃሴዎች ተስፋፍተዋል በሚባሉባቸው ማህበረሰቦች፣

የኤሌክትሪክ ኃይል ያለ ሲሆን ኤሌክትሪክ ጨርሶ በሌለባቸው ሰባት ማህበረሰቦች እንዲህ ያሉ የንግድ ስራዎች አልተጠቀሱም፡፡ የኤሌክትሪክ መኖር የቴክኖሎጂ ውጤቶች አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ያስቻለ ሲሆን (ለምሳሌ፡- የእህል ወፍጮ) ሴቶች በሌሎች እንቅስቃሴዎች ላይ የሚያጠፉትን ጊዜ ቀንሶላቸዋል፡፡ ይሄም በኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ ላይ የራሱ ተፅዕኖ ይኖረዋል፡፡

የመሬት እጥረትና እያደገ የመጣው መሬት አልባነት፣ ከወጣት ሴቶች የበለጠ በተለይ በወጣት ወንዶች የኢኮኖሚ አማራጮች ላይ ተፅዕኖ ማድረጉን ቀጥሏል፡፡ ነገር ግን በሴቶችም ላይ ቢሆን በተዘዋዋሪ ቀጥተኛ ያልሆነ ተፅዕኖ ማሳደሩ አልቀረም፡፡ ምክንያቱም የወጣት ወንዶችን የጋብቻ ጊዜ ያዘገየዋል፡፡ በዚህም የተነሳ አንዳንድ ሴቶች ስራ ፍለጋ ይሰደዳሉ (ማጣቀሻ፡- ወጣቶች፤ እና (ማጣቀሻ፡- ፍልሰት)፡፡

የግለሰብ ሁኔታ፡ ሀብትና የመነሻ ካፒታል አቅርቦት ወሳኝ ጉዳዮች

በተለያዩ ምክንያቶች በግለሰቦች መካከል የሚደረገው መስተጋብር ውስብስብ ነው (ማጣቀሻ፡- ኢ-እኩልነት፤ እና ስኬት) ለሚከናወኑት የሥራ ዘርፎች ዓይነት እንዲሁም ብዝሃነትና አንጻራዊ ስኬት ሃብት ወይም የካፒታል አቅም ወሳኝ ሚና አለው፡፡ ድሃ ሴቶች በአብዛኛው በኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ላይ የሚሳተፉት የኑሮ ችግራቸውን ለማሸነፍ ነው፡፡ (ለምሳሌ፡- በሹምሽሃ የተለያዩ ነገሮችን ለመሥራት ይሞክራሉ፤ በኡዳ ሃሮ ደግሞ የንግድ እንቅስቃሴዎች ላይ ይሳተፋሉ) ድሃ ሴቶች (ከሰፋፊ ንግዶች በስተቀር በሁሉም) ዘርፈ ብዙ በሆኑ ሥራዎች ላይ እንደሚሳተፉ ተነግሯል፤ በሌላ በኩል እጅግ ድሆቹ ያላቸው አማራጭ ውስን ሲሆን ብዙ ጊዜ ኑሮአቸው ሴፍቲ ኔትን ጨምሮ በሌሎች መደበኛና መደበኛ ያልሆኑ ድጋፎች ላይ የተመሰረተ ነው፤ (ልመናን ጨምሮ ማለት ነው፤ ለምሳሌ፡- በዲንኪና ገብለን)፡፡ በተደላደለ የኢኮኖሚ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ሴቶች በአብዛኛው ገቢ መሻት አይጠበቅባቸውም፡፡ ቢሆንም አንዳንድ ሃብታም መሰረት ያላቸው ሴቶች፤ ዘርፈ ብዙ በሆኑ የንግድ እንቅስቃሴዎች ላይ ይሳተፋሉ፡፡ ይሄም በመነሻ ካፒታል አቅርቦት ይቀላጠፍላቸዋል፡፡ በንግድ ዘርፎች በሚሳተፉ ወቅት ደግሞ ጉልህ ስኬት ያስመዘግባሉ (ማጣቀሻ፡- ስኬት)፡፡

ስለዚህም በሀብት የደረጁ ሴቶች መዋዕለ ንዋያቸውን ገቢ አመንጪ በሆኑ እንደ ሰፋፊ ንግድ፣ አነስተኛ የንግድ ድርጅቶች ባሉ ሥራዎች ላይ ያፈሳሉ፡፡ ሃብት መፍጠር በቻሉ ቡድኖች ውስጥ ሁሉ ትናንሽ ንግዶች ጠቃሚዎች መሆናቸው አይታበልም፡፡ ነገር ግን ከፍተኛ የገበያ ዋጋ ያላቸው እንደ ቡና፣ ሰብል፣ ወተት/ቅቤ ያሉ ምርቶች በብዛት የሚነገዱት በሃብታም ሴቶች ነው፡፡ (ዝቅተኛ ዋጋ ያላቸው ምርቶች (ሳር/እንጨት/ኩበት) ደግሞ እጅግ ድሀ በሆኑ ሴቶች ይነገዳል፡፡ ሰፋፊ ንግዶች እጅግ በበለጸጉ ሴቶች ብቻ ነው የሚካሄዱት፡፡ ምክንያቱም ምርቶችን ከጅምላ አከፋፋዮች ለመግዛት በቂ የመነሻ ካፒታል ይፈልጋል (ለምሳሌ፡- በጋራ ጎዶ አንዲት የሀብታም ሚስት፤ ጤፍ በቆሎና ቡና እየገዛች ትነግዳለች)፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ገበያ በሌለበት ወይም በተቀዛቀዘበት ወቅት ለመቋቋም የሚያስችል አስተማማኝ የገንዘብ አቅም፤ እንዲሁም እንደ መሬት ያሉ ጥሪቶችና ለሽያጭ የሚሆኑ ምርቶችን ለማብቀል የሚያስፈልጉ ግብአቶች ሊኖሩ ይገባል (በሲርባ የሀብታም ገበሬዎች ሚስቶች እህል ይሸጣሉ)፡፡

እጅግ ድሃ ወይም ያጡ የነጡና ድሃ የሆኑ ሴቶች፤ አብዛኛውን ጊዜ “ከእጅ ወደ አፍ” በሆኑ ዘርፎች ውስጥ ይሳተፋሉ (ለምሳሌ፡- ሳር ወይም የማገዶ እንጨት ንግድ)፡፡ መሬት የሌላቸው ወይም መሬት

ቢኖራቸውም ጉልበት የሌላቸው ድሃ ሴቶች፤ ብዙውን ጊዜ በእርሻና እርሻ - ዘለል በሆኑ ዘርፎች፣ በቀን ሥራ ወይም ደሞዝ በሚያስገኙ የጉልበት ስራዎች ላይ ይሰማራሉ፡፡ ምግብ ለሥራ ወይም የምግብ ዋስትና ድጋፍ ጋር የተያያዘ የጉልበት ሥራ አተገባበር ግልፅ አይደለም፡፡ አንዳንድ በሀብት የደረጁ ሴቶች የሚሳተፉ ሲሆን በጉልበት ሥራ መሳተፍ ያልቻሉ ሌሎች ያጡ የነጡ ድሃዎች /አረጋውያን ወይም ሴቶች የድጋፍ አቅርቦት እንደማያገኙ ተነግሯል፡፡ ምንም እንኳን በወጉ ባይዘገብም በሰዎች መኖርያ ቤት በሰራተኝነት ተቀጥሮ መስራት የተጠቀሰው ድሃ ወይም በጣም ድሃ የሆነ የቤተሰብ መሰረት ባላቸው ሴቶች/ልጃገረዶች ዘንድ ብቻ ነው (ሳይዘገብ ቀርቶ ቢሆንም)፡፡

አንዲት ሴት በቤተሰቡ ውስጥ ያላት ቦታና ደረጃ በምትሰማራባቸው የሥራ ዘርፎች ላይ የተወሰነ ተፅዕኖ ቢኖረውም ይሄ በፊናው በቤተሰቡ ሀብትና አቅም ላይ በእጅጉ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ በኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ለመሳተፍ የንብረት ባለቤትነት ወይም ተደራሽነት ወሳኝ ሲሆን (ለምሳሌ፡- መጠጥ በመሸጥ የምትተዳደር አንዲት የግራር ሴት፤ ከሴፍቲ ኔት ጥማድ በፊና ላም አግኝታለች)፡፡ የንብረት ባለቤት አለመሆን ደግሞ ከፍተኛ እንቅፋት ወይም ማነቆ ነው፡፡ የካፒታል አቅርቦትና አስተማማኝ የገንዘብ አቅም ስለሚኖራቸው፣ በንግድ ሥራ ላይ መሰማራት በአብዛኛው የባለጠጋ ሚስት በሆኑ ሴቶች ወይም ዘመድ አዝማድ ዘንድ የተለመደ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- በአዜ ዴቦአ፤ አንዲት የስኬታማ አርሶ አደር ሚስት የቤተሰቡን ገንዘብ የሸቀጣ ሸቀጥ ሱቅ ወይም የውበት ሳሎን ለመክፈት ተጠቅማበታለች፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ በራስ የግብርና ሥራዎች ላይ መሳተፍ እንዲሁም የቤተሰቡን ገቢ መደገፍ በአብዛኛው በሀብታም ወይም ስኬታማና መካከለኛ ገቢ ባላቸው የገበሬ ወይም ነጋዴ ሚስቶች የሚከናወን ነው (ለምሳሌ፡- በሃረሳው፤ የሀብታም ገበሬ ሚስት በቤተሰቡ የመስኖ ልማት ወይም የከብት እርባታ ላይ ትሳተፋለች)፡፡ በሌላ በኩል የድሃ ገበሬ ሚስቶች በአብዛኛው በቤት ውስጥ ስራዎች ከመሳተፍ ጎን ለጎን ጥቃቅን ንግድ/የቀን ስራ በመሳሰሉ ፈርጀ ብዙ ስራዎች ላይ ይሰማራሉ (ወዘተ)፡፡ በእርግጥ ለቤተሰቡ ገቢ ለማምጣት በራሳቸው በቂ አይደሉም፡፡ ሴቶች ለቤተሰቡ በሚያደርጉት የገቢ አስተዋፅኦ ላይ የመወሰን ሥልጣን ይኑራቸው አይኑራቸው ሁሌም በግልፅ ይታወቃል ማለት አይደለም (ለምሳሌ፡- በኮርማርገፍያና አዳ ሃሮ ገቢን በአብዛኛው የሚቆጣጠሩት ወንዶች ናቸው)፡፡

መሬት በተለይ በቤተሰብ የኑሮ ደረጃ ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ መሬትም ሆነ ማንኛውም ዓይነት መነሻ ካፒታል የሌላቸው ሴቶች አብዛኛውን ጊዜ ውጤታማ ባልሆኑ ዝቅተኛ ስራዎች ውስጥ ይጠመዳሉ፡፡ የሰው ጉልበትም እንዲሁ ወሳኝ ነው - በተለይ በሴት ለሚተዳደሩ ቤተሰቦች፡፡ መሬት እያላቸው የሰው ጉልበት የሌላቸው አንዳንድ ሴቶች፤ መሬታቸውን "ለእኩል ጥቅም የሚያሳርሱ" ሲሆን (አንዳንዶቹን ላልተገባ የመሬት ባለቤትነት ውዝግብ ዳርጓቸዋል፤ ለምሳሌ፡- በቱሩፊ) መሬት የሌላቸው ሴት የቤተሰብ አስተዳዳሪዎች በሚሳተፉባቸው ተመሳሳይ ስራዎች ውስጥም ይሳተፋሉ (የቀን ስራ፣ ጥቃቅን ንግድ፣ የምግብ ዋስትና ድጋፍ/ምግብ ለሥራ የጉልበት ሥራ) የሰው ጉልበት ከቤተሰብ ለሚያገኙ ወይም ለእኩል ጥቅም ከማሳረስ ይልቅ የጉልበት ሰራተኛ የሚቀጥሩ ሴቶች (ወጪው ከፍተኛ ስለሚሆን) ሁልጊዜ ይቀናቸዋል ማለት አይደለም (ለምሳሌ በአዴሌ ኬኬ፣አንዲት ሴት የጉልበት ወጪ ለመሸፈን ንብረቶቿን መሸጥ ነበረባት)፡፡

<u>ሁሉን አካታች ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎን ማረጋገጥ</u>

ከላይ በግልፅ እንደሰፈረው፤ ሰፊ የማህበረሰብ የመሰረተ ልማት ግንባታ ለሴቶች ወይም ልጃገረዶች የኢኮኖሚ አማራጮችን አስፍቷል፡፡ ቢሆንም ከስራ ቅጥር ጋር የተገናኙ የፍትሃዊነት ችግሮች በግልጽ ይታያሉ፡፡ ሴቶች በኢንዱስትሪ የሥራ ቅጥርና በቀን ሥራ፣ ከወንዶች ያነሰ ክፍያ እንደሚከፈላቸው ጠቁመዋል (ለምሳሌ፡- በዶኣማ ሴቶች ለተመሳሳይ የመስኖ ልማት ስራዎች ለወንዶች ከሚከፈላቸው የወቅቱ ተመን በግማሽ ያነሰ ተከፍሏቸዋል፤ በሃረሳው ሴቶች ለመስኖ ስራ በቀን ከ30-40 ብር ሲከፈላቸው፣ወንዶች ከ50-60 ብር ተከፍሏቸዋል፤ በአዜ ዴቦአ የቡና መፈልፈያ ማዕከል እንዲሁ ልጃገረዶች ከወንዶች ያነሰ ይከፈላቸዋል)፡፡

ሴቶችን ያለመ አካባቢ-በቀል የኢንዱስትሪ የሥራ ቅጥር፣ በተወሰኑ ማህበረሰቦች ጉልህ ተጽዕኖ እንደፈጠረ ተነግሯል(ለምሳሌ፡- በኡዳ ዳዋታ፣ የልዩ ድጋፍ ፖሊሲ፣ 10ኛ ክፍል የጨረሱና የመጀመሪያ ዲግሪ የያዙ ሴቶችን አበረታቷል)፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ፤ ሌሎች ኢንቨስትመንቶች ደግሞ ወንዶችን ጠቅመዋል (ለምሳሌ፡- በሲርባ፣ አንድ የቻይና ኮንስትራክሽን ኩባንያ፣ በአብዛኛው ወንዶችን ነው የቀጠረው)፡፡ በሌላ በኩል ከፍ ያሉ የስራ ቦታዎች (ሥራ አስኪያጅች ወዘተ ...) እምብዛም ለሴቶች አይሰጡም (ለምሳሌ፡- ወንድ የቡና እርሻ ሥራ አስኪያጅ - በጋራ ጎዶ፤ ወንድ የችግኝ ማፍያ ኃላፊ - በዲንኪ፤ ወንድ የቡና አምራቾች ዩኒየን ሥራ አስኪያጅ - በአዳዶ)፡፡

ሥራ ፍለጋ ቀዬን ጥሎ ከመጓዝ ጎን ለጎን፣ በአካባቢ-በቀል ኢንዱስትሪ ውስጥ መቀጠር በወጣት ልጃገረዶች/ሴቶች ተደጋግሞ ተጠቅሷል፡፡ እነዚህን ዕድሎች መጠቀም (በአንዳንድ አጋጣሚዎች በቀጥታ) ከወጣት ሴቶች ነፃነት መሻት፣ ከህልምና ራዕይ መለወጥ (ከእርሻ/አካባቢ-በቀል የኑሮ መተዳደሪያዎች ውጭ) እንዲሁም ከከፍተኛ የትምህርት ደረጃ ጋር የተቆራኘ ነው፡፡ (ማጣቀሻ፡- ትምህርት፤ ፍልሰት፤ እና ወጣቶች)፡፡ ሆኖም ቤተሰብ ላላቸው ወይም ሃላፊነት ለተሸከሙ ሴቶች ይሄ እምብዛም የማይቻል ወይም አመቺ አለመሆኑን ዘገባዎች ይጠቁማሉ፡፡ (ለምሳሌ፡- በቱሩፊ፣ አንዲት ሴት፣ ህፃን ልጇን ከማሳደግ ጎን ለጎን፣በሥራዋ ለመቀጠል ታግላለች፤ በዲንኪ፣ ታዳጊ ልጃገረድ ያላት እናት፣ የ‹ከተማ› ሥራ ማግኘት አልቻለችም)፡፡

እየሰፋ ከመጣው ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ፣ የሰራተኞችንም ሆነ የአሰሪዎችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፤ (በ2009 በወጣው ብሄራዊ የሥራ ቅጥር ፖሊሲና ስትራቴጂ እንዲሁም በ2003 በታወጀው የሥራ ህግ ላይ የተቀመጡትን ጨምሮ) ፍትሃዊ የሥራ ቅጥር/ተደራሽነትን መተግበር ይጠይቃል፡፡ የፖሊሲ ትኩረቶች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡-

- ለሴቶችና ለወንዶች፤ ለእኩል ሥራ እኩል ክፍያን ተግባራዊ ማድረግ፤
- የህፃናት እንክብካቤ አገልግሎት አማራጮች እንዲሁም የወሊድ መብቶች በመሰረታዊ የሥራ ሁኔታ ቁጥጥር ውስጥ መካተቱን ማረጋገጥ፤ (ህፃናት ላላቸው ወይም ሊወልዱ ለተዘጋጁ ሴቶች አማራጮችን መስጠት የስራ ቅጥር ዋስትና የሚያጎናፅፍ ሲሆን ሴቶች እንዳይገለሉ እገዛ ያደርጋል)፡፡
- የቅጥር መብቶች ግንዛቤን ማስፋፋት፤ (ለምሳሌ፡- በታለሙ መልዕክቶች አማካኝነት) ሴቶች (እንዲሁም ወንዶች) የተሻለ መብታቸውን ማስከበር እንዲችሉና ከብዝበዛ ነጻ በሆነ እኩል ሜዳ ላይ ለቅጥር የመደራደር አቅማቸውን ለማጠናከር ያግዛል፡፡

- ነባር አሰራሮችን (ጅምሮችን) ማሳደግ፣ባለሃብቶች የሴቶችን ቅጥር ለማስፋፋት ተጨማሪ እርምጃ እንዲወስዱ ያበረታታቸዋል፡፡

<u>የሴቶችን የኑሮ መተዳደሪያዎች መደገፍ፡- ከመሻሻል ጎን ለጎን ያልተቀረፉ እንከኖች</u>

በሁሉም ማህበረሰቦች ከኑሮ መተዳደሪያ ጋር የተዛመዱ የተለያዩ የለውጥ እርምጃዎች መወሰዳቸው ተመዝግቧል፡፡ እነዚህ የለውጥ እርምጃዎች የግድ ሴቶችን ታላሚ ያደረጉ ባይሆኑም በመርህ ደረጃ ለሴቶችም ተደራሽነት ያላቸው ናቸው፡፡ ግማሽ ያህል በሚሆኑ ማህበረሰቦች ደግሞ ሴቶች-ተኮር የኑሮ መተዳደሪያ የለውጥ እርምጃዎች ተተግብረዋል፡፡

አብዛኛውን ጊዜ ሴቶች ወይም ልጃገረዶች በተጨባጭ፣ የኑሮ መተዳደሪያን ለመደገፍ በሚተገበሩ አጠቃላይ የመንግስት የለውጥ እርምጃዎች አይታቀፉም፡፡ ይሄን ተከትሎም ለሴቶች ወይም ልጃገረዶች “በቂ አልተሰራም” የሚል ጠንካራ ትችት ይሰነዘራል (ለምሳሌ፡- በገብለን፣ በመንግስት አሰራር «የቁርጠኝነት ማነስ» ሳቢያ፤ በኡዳሃሮ፣ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች፤ ‹ከከፍተኛ ባለሥልጣናት ያቀዷቸውን ንድፈ ሃሳቦች ቢደጋግሙም፣ ጠንካራ ሴቶችን የሚያነቃቁ ተጨባጭ ፕሮግራሞች ግን የሉም›) የመንግስት የለውጥ እርምጃዎች በሚኖሩ ወቅትም ውጤታማነታቸውን የሚገድቡ ችግሮች አይጠፉም፤ ለምሳሌ፡- (ነ)በበቂ ሁኔታ ተደራሽ አለመሆን እና (2) የለውጥ እርምጃዎቹ የራሳቸው ውስንነቶች (ለምሳሌ፡- የብድር እጥረት ወይም በቂ ክትትል ያለመኖር)፡፡

ሴት አርሶ አደሮች በፖሊሲ ደረጃ እንዲካተቱ ቢገለፅም፣ አብዛኛውን ጊዜ በግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት መርሃ ግብር ይዘነጋሉ፡፡ የWIDE ጥናት ክትትል ባደረገባቸው ማህበረሰቦች እንደታየው፣ አብዛኛውን ጊዜ ምክርና ግብአቶች የሚቃኙት ሞዴል አርሶ አደሮችን (በአብዛኛው ወንዶች) ለመደገፍ ነው፤ በዚህም የተነሳ ለአብላጫዎቹ ሴቶች ተደራሽ አይደሉም (ለምሳሌ፡- በዶአማ፣ አዳ ዳዋታ፣ ግራር)፡፡ ከዚህ በተጨማሪም፣ ባለትዳር ሴቶች በራሳቸው የኤክስቴንሽን አገልግሎት መርሃ ግብር ያግኙ አያግኙ በግልጽ አይታወቅም፡፡ የልማት ሠራተኞች ከቤተሰብ አስተዳዳሪዎች (ሃላፊዎች) ጋር የመስራት ዝንባሌ አላቸው (ብዙ ጊዜ ወንዶች ይሆናሉ)፡፡ ይሄም ለምሳሌ፡- በኮርማርገፍያ፣ አዳ ዳዋታና ግራር ተጠቅሷል፡፡ ሴቶች (በአብዛኛው ባል የሞተባቸውና ትዳር ያፈረሱ) ከግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት መርሃ ግብር፣ ምክር ማግኘታቸውንና መጠቀማቸውን (ለምሳሌ፡- በሲርባ) ወይም በልዩ ፕሮጀክቶች መሳተፋቸውን (ለምሳሌ፡- በቆሮደጋጋ 53 የሴት አባወራዎች፤ በመስኖ የለማ መሬት አግኝተዋል) የሚያሳዩ አብነቶች ተሰንደዋል፡፡ ቢሆንም ሴቶች የሚያገኙት ምክርና ድጋፍ አብዛኛውን ጊዜ የሴት ተብለው በተፈረጁ የሥራ ዘርፎች ላይ ብቻ የተገደቡ ናቸው (ለምሳሌ፡- በሶሞዶ፣ ሴቶች በዶሮና እንቁላል ምርት ላይ እንዲሰማሩ ይበረታታሉ፤ በኮርማርገፍያ፣ ለአትክልት ልማት የሚጠቅሙ ምክሮችና ግብአቶች ያገኛሉ)፡፡ እነዚህ አማራጮች ለአንዳንድ ሴቶች ተጨባጭ ጠቀሜታ አምጥተው ይሆናል፤ ነገር ግን የሌሎችን ፍላጎት ደግሞ እንዳላሟሉ የሚጠቁሙ ማስረጃዎች አሉ - ብዙ ጊዜ የወጣቶችን እና/ወይም ይበልጥ የተማሩትን (ለምሳሌ፡- በሶሞዶ)፡፡ በዚህም ሳቢያ፣ የሴት ተብለው በተፈረጁ እንቅስቃሴዎች ላይ ብቻ ማተኮር፤ ነባሩን ፆታ-ተኮር የኢኮኖሚ ዘርፍ ክፍፍል ለመገዳደር አልቻለም፡፡

ሴቶች በምግብ ዋስትና ድጋፍ ሥራ ላይ የመሳተፍ እኩል ዕድል ተሰጥቷቸዋል ተብሏል፡፡ እንዲያም ሆኖ የሴቶችን ተጨባጭ ሁኔታ ያላገናዘቡ የሥራ ጫና ችግሮች በተጨማሪ፣ የማህበረሰብ ሥራ ተሳትፎ ሴቶች ጥቅማቸውን የሚጋፉ አማራጮችን እንዲወስዱ ያስገድዳቸዋል፡፡ ለምሳሌ፡- በሃረሳው አንዲት ድሃ ሴት፣ እርሻዋን በአግባቡ ለማረም በቂ ጊዜ ባለማግኘቷ ምርቷ ቀንሶበታል፤ ለእርሻ ማሳዋ ጊዜ ሰጥታ መስራት ደግሞ የምግብ ዋስትና ድጋፍ አባልነቷን ያሳጣታል፡፡ የምግብ ዋስትና ድጋፍ ብቻውን ቤተሰቦች ወይም ሴቶች ድህነትን ማሸነፍ እንዳስቻላቸው የሚጠቁም ማስረጃ አልተገኘም፡፡

በአብዛኛው የወጣቶች የኑሮ መተዳደሪያን ለመደገፍ የሚወሰዱ የመንግስት የለውጥ እርምጃዎች ወጣት ሴቶችን የሚዘነጉ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ወጣት ሴቶችን በሚያካትቱባቸው ጥቂት አጋጣሚዎች ደግሞ፣ ሃላፊዎች ምን ያህል ወጣት ሴቶች በለውጥ እርምጃ መርሃ ግብሩ እንደሚሳተፉ አያውቁም፡፡ እንዲህ ያሉት እንቅስቃሴዎች አንድም በዘልማድ የ«ወንድ» ተብለው ይታሰባሉ (ለምሳሌ፡- በገብለን፣ ንብ ማነብ) አሊያም ሴቶች ስለ ጉዳዩ በቂ ግንዛቤ አይኖራቸውም ወይም እንዲሳተፉ አይበረታቱም (ለምሳሌ፡- በብዙ ማህበረሰቦች፣ የድንጋይ ካባ ወይም የደን የህብረት ሥራ ማህበራት ወንድ በበላይነት የሚቆጣጠራቸው ናቸው)፡፡ የገንዘብ ቁጠባ መስፈርትም፣ ወጣት ሴቶች በለውጥ እርምጃዎች ውስጥ እንዳይሳተፉ እንቅፋት ሆኖባቸዋል (ለምሳሌ፡-በአዳዶ)፡፡ ከከተማ አካባቢዎች በተለየ (በአዳዶ እንደተገለጸው) እርሻ-ዘለል ለሆኑ የሥራ ዘርፎች የሚሰጠው ድጋፍ አናሳ ነው፡፡ ይሄም ወጣቶችን ለተስፋ መቁረጥ ይዳርጋል (በተለይ፤በዲንኪ፣ ሶሞዶ፣ ኮርማርገፍያ፣ አዳ ዳዋታና አዳ ሃሮ እንደተገለፀው)፡፡ በግራር ብዙ ሴቶች ለተሰማሩበት የሸክላ ሥራ ምንም ድጋፍ እንደማይደረግ ቅሬታቸውን ተናግረዋል፡፡

በዘጠኝ ማህበረሰቦች፣ የሴቶች የህብረት ሥራ ማህበራት እንዳሉ የታወቀ ሲሆን ሁሉም በመንግሥት ወይም መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ድጋፍ የተቋቋሙ ናቸው፡፡ ጥቂቶቹ አቅማቸውን ቢያሳዩም (ለምሳሌ፡- በገልቻ፣ የቁጠባና የብድር ህብረት ሥራ ማህበር ለግለሰቦች ብድር በመስጠት ስኬት ማስመዝገቡ ተነግሯል) አብዛኞቹ ግን በትግል ላይ ናቸው፡፡ ከሚጠቀሱ ማነቆዎች መካከልም፡- ከምርት ሽያጭ ወይም ግብአት አቅርቦት ጋር የተያያዙ ችግሮች (ለምሳሌ፡- በጋራ ጋዶ፣ የጥጥ ፈታዮች የህብረት ሥራ ማህበር፤ በሹምሸሃ፣ የተሻሻለ ምድጃ የህብረት ሥራ ማህበር)፣ በአባላት መካከል የሚፈጠር አለመተማመን፣ የድጋፍ እጥረት (የገንዘብ፣ የክትትልና የቴክኒክ ድጋፍን ጨምሮ)፣ የአመራር ክህሎት ማነስ፤ እንዲሁም በአንዳንድ አጋጣሚዎች የቀበሌ አመራር ደካማ እገዛ ይገኙባቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከአባልነት ጋር የተያያዘ የዝምድና አሰራርም እንደ ችግር ተጠቅሷል፡፡

ወጣትና ትዳር ያልመሰረቱ ሴቶች እንዴት የህብረት ሥራ ማህበራትን በቀላሉ መቀላቀል እንደሚችሉ (ለምሳሌ፡- በየትመን የጥጥ ፈታዮች የህብረት ሥራ ማህበርን በዕድሜ የገፉ ሴቶች እስኪቀላቀሉት ድረስ ለወጣቶች ተብሎ የተቋቋመ እንደነበር ተነግሯል) ወይም አባል መሆን እንደማይችሉ በግልፅ የሚታወቅ ነገር የለም፡፡ ነገር ግን በሁሉም ማህበረሰቦች፣ በህብረት ሥራ ማህበራት ውስጥ የሚሳተፉ አብዛኞቹ ሴቶች ያገቡ ወይም ባል የሞተባቸው አሊያም ትዳር የፈረሰባቸው ናቸው፡፡ ይሄም ወጣትና ያላገቡ ሴቶች፣ በአዋቂም ሆነ በወጣቶች የለውጥ እርምጃዎች ውስጥ ተዘንግተዋል በሚለው አመለካከት ዙሪያ አሳሳቢ ችግር መኖሩን ጠቋሚ ነው (ማጣቀሻ፡- ወጣቶች)፡፡

የብድር አገልግሎት ፕሮግራሞች ለሴቶች ተደራሽነታቸው (በአጠቃላይም ሆነ ሴቶች ላይ ያተኮሩ) እንደጨመረ ተነግሯል (ለምሳሌ፡- ገብለን፣ አዬሌ ኬኬ፣ ሃረሳው)፡፡ በአንዳንድ አጋጣሚዎች፣ ብድር ሴቶችን መነሻ ካፒታል እንዲያገኙ አስችሏቸዋል (ለምሳሌ፡- በገብለን፣ አንዲት ሀብታም ሚስት ሱቅ ከፍታለች፤ በአዬሌ ኬኬ፣ አንዲት ድሃ ሴት ለሽያጭ የሚሆን በግ መግዛት የቻለች ሲሆን ብድሩን ለጥቃቅን ንግድ የሚሆኑ ምርቶች ላይ አውላለች)፡፡ ቢሆንም ይሄ ሁልጊዜ የሚገኝ አማራጭ ነው ማለት አይደለም (ለምሳሌ፡- በአዳዶ፣ አንዲት ድሃና መሬት የሌላት ሴት የቤተሰብ አስተዳዳሪ፣ ለብድር ዋስትና የሚሆን ንብረት ስለሌላት፣ ዝቅተኛ ክፍያ በሚያስገኝ ከእንስት ምርት ጋር በተገናኘ የጉልበት ሥራ ላይ ተጠምዳለች)፡፡ አንዳንዴ ደግሞ ሴቶች ሌሎች ጥቅሞችን ላለማጣት ሲሉ ብድር የመውሰድ ጫና ውስጥ እንደሚገቡ ተነግሯል (ለምሳሌ፡- በገብለን)፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ ግን የብድር ተደራሽነት ውስን ሲሆን ያለውን ፍላጎትም የሚሸፍን አይደለም፡፡ ይሄ ደግሞ የሴቶችን ኑሮ አሉታዊ በሆነ መንገድ የሚያውክ ሲሆን ተፅዕኖ የመፍጠር አቅማቸውንም ይገድበዋል - ለምሳሌ በቱሩፌና አዜ ዴቦአ እንደተገለፀው፡፡ ብድር ለውድቀት የሚዳርግበት፣ ትርፍ የማያስገኝበት ወይም የኢኮኖሚ ማሽቆልቆል የሚያስከትልበት ሁኔታም ያጋጥማል (ለምሳሌ፡- በገብለን፣ አንዲት ድሃ የቤተሰብ አስተዳዳሪ፤ በብድር ባገኘችው ገንዘብ የገዛቻት ላም ሞታባታለች፤ በቆሮደጋጋ፣ የሰብል እህል ምርታማ አለመሆን ሴቶች ዕዳቸውን መክፈል እንዳይችሉ አድርጓቸዋል)፡፡

ከዚህ በተጨማሪም፣ ብድሩን መመለስ አዳጋች ሊሆን ይችላል ወይም ትርፋማ ባልሆነ ኢንቨስትመንት ላይ ይውላል፤ አሊያም ባሎች እንዳሻቸው ይጠቀሙበታል (ለምሳሌ፡- ቱሩፌ) የሚሉ ስጋቶችም እንዳሉ ተመዝግቧል፡፡

በአብዛኞቹ ሁኔታዎች፣ በማህበረሰብ ደረጃ፣ የሴቶች ወይም ልጃገረዶች ተጨባጭ ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ ከመንግስት የለውጥ እርምጃዎች ጋር ቁርኝት የለውም፡፡ ጥቂት ሴቶች፣ ካፒታል በሚጠይቅ ሥራ ላይ የመሳተፍ አቅማቸውን (ችሎታቸውን) ከተለየ የለውጥ እርምጃ ጋር አቆራኝተውታል፡፡ ለምሳሌ፡- በሲርባ ስኬታማ ትዳር ያላት ሚስት፣ ከአሮሚያ ብድርና ቁጠባ ማህበር ለመነሻ በወሰደችው ብድር በተለያዩ የንግድ ዘርፎች ላይ ተሰማርታለች (DBO8: success)፡፡ ነገር ግን ለሴቶች የኑሮ መተዳደሪያ ምንም ድጋፍ በሌላቸው ወይም በጣም ውስን ድጋፍ ባላቸው በርካታ ማህበረሰቦች (ለምሳሌ በገብለን፣ ሃረሳው፣ ጋራ ጎዶ፣ አዳዶ፣ ኡዳ ዳዋታ) ሴቶች መነሻ ካፒታል በሚጠይቁ የንግድ ስራዎች ላይ ተሰማርተው ይታያሉ፡፡

<u>ሴቶችን የበለጠ መደረስ ...</u>

ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎን ማስፋፋት፣ የኑሮ ልዩነትን የመቀነስና ለችግር ተጋላጭ ግለሰቦችን ከድህነት የማውጣት ሰፊ የቁርጠኝነት እንቅስቃሴ አካል ነው፡፡ የWIDE መረጃ እንደሚጠቁመው፤ ኢኮኖሚያዊ ደረጃቸው ሴቶች ገቢ በሚያስገኙ ሥራዎች የመሳተፍ አቅማቸውን የሚቀርጽ ሲሆን ብድር ለብዙዎች ከድህነት መውጫያ መንገድ አልፈጠረላቸውም፡፡ ሴቶች በአብዛኛው ሁኔታ የኑሮ መተዳደሪያቸውን ለመደገፍ በታለሙ የለውጥ እርምጃዎች ውስጥ አልተካተቱም፡፡ በተገለፀው ሰፊ የድህነት ቅነሳ ግብና በ2014 የማህበራዊ ዋስትና ፖሊሲ መሰረት፣ መንግስት የመነሻ ካፒታል አቅርቦትን (ተደራሽነትን) እውን ለማድረግ የሚረዱ አማራጭ/አጋዥ ዘዴዎችን ከግምት ውስጥ ሊያስገባ ይችላል፡፡ ለምሳሌ፡-

- በአግባቡ የታለመ “የካፒታል ማነቃቂያ” መስጠት (በገንዘብ ድጋፍ/በቂ መጠን ባለው የንብረት ዝውውር፤ ከበቂ ስልጠና፣ ዝግጅትና ክትትል ጎን ለጎን) በጣም ድሃ ለሆኑ ሴቶች ብድር መውሰድ አዋጭ ወደሚሆንበት ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ያስችላቸዋል።

የመንግስት የለውጥ እርምጃዎችን የሚያጠናክሩ ሌሎች እርምጃዎች፣ የማህበራዊ ዋስትና ግቦችን እውን ለማድረግ አስተዋፅኦ የሚያበረክቱ ሲሆን የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎም የበለጠ ያሳድጉታል - በተለይ የኑሮ መተዳደሪያን ለመደገፍ የሚወሰዱ እርምጃዎች ወንዶችንም ሴቶችንም በተጨባጭ ማካተታቸውን ለማረጋገጥ የታለሙ እርምጃዎች። ለምሳሌ፦

- በወንድ የሚተዳደሩ ቤተሰቦች ውስጥ የሚገኙ ሴቶችን ጨምሮ የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎቶች ለሴቶች እንዲደርሱ ማድረግ፤ በተጨማሪም ሴት ተኮር ተብለው ከሚገለፁት እንቅስቃሴዎች ከምክር ባሻገር ማካተት ይገባዋል።
- የወጣቶች የህብረት ሥራ ማህበራትና ሌሎች የወጣት የኑሮ መተዳደርያ የለውጥ እርምጃዎች፤ ለወጣት ሴቶች የተለዩ ፍላጎቶች፣ ጥቅሞችና ማነቆዎች የተሻለ ትኩረት መስጠት ይኖርባቸዋል፤
- በገጠር አካባቢዎች ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋሞች እንዲስፋፉና ለሴቶችም ለወንዶችም እንዲደርሱ ድጋፍ ማድረግ።

<u>የፆታ እኩልነት እርምጃ ውጤታማ ነው፤ ግን “እንቅፋቶች” ቀጥለዋል</u>

በስፋት የተካሄደው የፆታ እኩልነትን የማስፈን እርምጃ፣ ሴቶችን ወይም ልጃገረዶችን በተመለከተ ነባር አመለካከቶችን በመለወጥ ረገድ አስተዋፅኦ ማድረጉን የሚጠቁሙ ማስረጃዎች አሉ። ይኸውም በተለወጡ ማህበራዊ ልማዶችና በሴቶች ወይም ልጃገረዶች ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ መካከል በሚደረጉ እርስ በእርስ ተደጋጋፊ ሂደቶችን የሚመለከት ነው። ነገር ግን ማህበረሰባዊ እንቅፋቶች አሁንም ቀጥለዋል። እነዚህ እንቅፋቶች በሥራ ክፍፍልና በውሳኔ ሰጪነት ላይ ያሉ የወንድ ስጋቶችንና አትራፊ በሆኑ ንግዶች ላይ ያለውን ፉክክር ያካትታሉ።

የመንግስት የለውጥ እርምጃዎች ለሴቶች መብቶች

ፍትሃዊ የጤና እና የትምህርት አገልግሎቶች አቅርቦትን የሚደግፉ የመንግስት የለውጥ እርምጃዎችና ሴቶች እነዚህን የማግኘት መብታቸው በሁሉም ማህበረሰቦች እድገትና መሻሻል አሳይተዋል (ማጣቀሻ፦ ትምህርት፤ እና እናቶችና ጨቅላ ህጻናት)። በመርህ ደረጃ፣ የትምህርትና የጤና አገልግሎቶች ከፍተኛ ተደራሽነት፣ ለሴቶች ወይም ልጃገረዶች የኢኮኖሚ ተሳትፎ አዎንታዊ አስተዋፅኦ እንደሚያደርግ ይጠበቃል። የዚህ ውጤት በግለሰብ ደረጃ ታይቷል (ለምሳሌ፦ በጥቂት ማህበረሰቦች፣ ልጃገረዶች በባለሙያነት ተቀጥረዋል፤ ወደዚህ ዓይነት ህይወት የመግባት ብዙ ፍላጎትም ታይቷል፤ እንዲሁም ሴቶች የጤና መታወክ በእጅጉ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደሆነ ጠቁመዋል)። በበርካታ ማህበረሰቦች ከተስተዋለው ከፍተኛ የትምህርት /ተስፋ/ ሥራ አጥነት/ስደት ትስስር በስተቀር በማህበረሰብ ደረጃ የታየ አዝማሚያ የለም (ማጣቀሻ፦ ትምህርት፤ ወጣቶች፤ እናፍልሰት)። አንዳንድ ሴቶች፣ የተደራሽነት እንቅፋቶችን (የወንድ ተቃውሞን ጨምሮ) የገለጹ ሲሆን ኢኮኖሚያዊ ዓላማዎችን ለማሳካት፣ የቤተሰብ ዕቅድ ጥቅም ላይ የዋለባቸው አጋጣሚዎች አሉ

(ለምሳሌ፡- በአዜ ዴቦአ፣ አንዲት ሴት፣ ያልተፈለገ እርግዝና በማስወገዷ፣ ንግዷን መቀጠል እንደቻለች ተነግሯል፤ በሃረሳው ደግሞ ወጣት ወንዶችና ሴቶች፣ ቀድሞ በኢኮኖሚ ለመደላደል በማቀድ፣ የመጀመሪያ ልጃቸውን የመውለጃ ጊዜ ማዘግየታቸው ተጠቁሟል)።

ይበልጥ በስፋት፣ የሴቶችን የመሬት ባለቤትነት፣ የውርስና የፍቺ መብቶችን የሚያሻሽሉ መንግስት - መር ፕሮግራሞችና ህጎች፣ የማበረታቻ እርምጃ አጋጣሚዎችን ጨምሮ በሁሉም ማህበረሰቦች መተግበራቸውን የሚጠቁሙ ምልክቶች ታይተዋል። (ለምሳሌ፡- በሃረሳው፣ ዳግም የመሬት ማከፋፈል)። ነገር ግን ስኬቶች ከማህበረሰብ ማህበረሰብ ይለያያሉ። ልዩነቱ የመነጨው የተለያየ ደረጃዎች ባላቸው የወንድ ቅዋሜና በተለይ ሽማግሌዎቹ በሚይዙት አቋም እንዲሁም በቀበሌና በወረዳ ደረጃ ባሉ የሴት አመራሮች ብቃትና ቁርጠኝነት ነው። ወንድ የገነነባቸው እንደ ፍርድ ቤትና ፖሊስ ጣቢያ ያሉ ተቋማትም የሚያደርጉት የድጋፍ መጠን ለልዩነቱ የድርሻውን ያበረክታል። ወጣቶች፤ የትዳር አጋራቸውን የመምረጥ መብታቸው ይበልጥ ተቀባይነት እያገኘ መጥቷል፤ ነገር ግን በሁሉም ቦታ አይደለም (ለምሳሌ፡- ገልቻ)። በጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ላይ የተወሰዱት እርምጃዎች፤ ያለዕድሜ ጋብቻን፣ ጠለፋን፣ አስገድዶ መድፈርንና ባሏ ከሞተባት ሴት ውርስ ጋር የተያያዙ ችግሮችን ቀንሰዋል። እኒህን የሚቃወሙ ሴቶች በቤተሰቦቻቸው እገዛ ተደርጎላቸዋል። ሆኖም እነዚህ ልማዶች በምንም ዓይነት መንገድ ከእነአካቴው አልጠፉም። የሴት ብልት ትልተላ፣ ህገ ወጥ በመሆኑ፣ በእርግጥም መቅረት አለመቅረቱን አሊያም ነባር ባህላዊ ልማድ በነበሩባቸው ማህበረሰቦች አሁንም እየተፈጸመ መሆኑን ለማወቅ አስቸጋሪ አድርጎታል። እገዳውን በአፍ መቃወም ግን በሦስት አካባቢዎች ተስተውሏል (ማጣቀሻ፡- ወጣቶች፤ እና እናቶችና ጨቅላ ህጻናት)። የሴቶችን ፖለቲካዊ ተሳትፎ ለማሳደግ የታለሙ እርጃዎች፣ በአንዳንድ ማህበረሰቦች፣ በሙሉ ልብና ቁርጠኝነት አልተተገበሩም (ለምሳሌ፡- በዶአማ፣ 4 ሴት የቀበሌ ም/ቤት አባላት ብቻ ነበሩ፤ የቀበሌ የሴቶች ማህበራትም የአቅም ችግር አለባቸው)። በቦታቸው ያሉት የተወሰኑትም ቢሆኑ ውጤታማነታቸው አጠራጣሪ ነው። በአጠቃላይ፣ በሁሉም ማህበረሰቦች ውስጥ አብዛኞቹ ሴቶች፣ በፖለቲካው ንቁ ተሳታፊዎች አይደሉም።

ሴቶች በግለሰብ ደረጃ መብቶቻቸውን ለማስከበር ድፍረት፣ ጊዜና ከሽማግሌዎች ወይም ፍርድ ቤቶች ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል። ድሃ ሴቶችና በሴቶች የሚተዳደሩ ቤተሰቦች፣ ይህን ለማድረግ ሲሞክሩ ብዙውን ጊዜ የተለያዩ ችግሮች ይገጥማቸዋል። እንዲያም ሆኖ የፆታ እኩልነት የማስፈን እርምጃዎች፣ ሴቶች ቀስ በቀስ በራስ መተማመን እንዲያዳብሩ ረድተዋቸዋል። ከዚህም ባሻገር አመለካከቶችን በመለወጥ ረገድ አስተዋጽኦ አድርገዋል።

አመለካከቶች - ተሳትፎን ያቀላጥፉሉም፤ ይገድባሉም

በአንድ በኩል የማህበራዊ ልማዶች ለውጥ ከሞላ ጎደል በሁሉም ማህበረሰቦች ውስጥ በግልፅ የተስተዋለ ሲሆን ሴቶች ሊሳተፉባቸው የሚችሉ የሥራ ዓይነቶች ላይ ወሳኝ ሚና አላቸው። ይህ ሴቶችን እንደ ‹ደካማ› አድርጎ የመቁጠር አመለካከት ላይ የተፈጠረ ለውጥን ይጨምራል (ለምሳሌ፡- በአዳ ሃሮ፣ ሴቶች አሁን ነጻ በሆነ የራሳቸው እንቅስቃሴዎች የመሳተፍ አቅም እንዳላቸው ተደርገው ነው የሚታሰቡት)። በሥራ ክፍፍል ረገድ ለመጣው የአመለካከት ለውጥ ማሳያው፣ አንዳንድ ወንዶች የቤት ውስጥ ስራዎችን መጋራታቸው (በጣም አልፎ አልፎ) ሲሆን ሴቶች ከቤት ውጭ

የበለጠ ሚና መውሰድ እየተለመደ መጥቷል፡፡ በጥቅሉ የሴቶች የሥራ ጫና ጨምሯል፡፡ የሹምሽሃ ሴቶች እንደገለፁት፤ “አሁን ሁሉንም ነገር ነው የሚሰሩት” (ይህንን ሲሉ ምርታማውንም ሆነ የሥነ ተዋልዶውን ሥራ ለማለት ነው)፡፡ በጋብቻና በኢኮኖሚ ራስን በመቻል ዙሪያ የነበረው ህልምና ራዕይ መለወጡን ወይም እየተለወጠ መሆኑን ጠቋሚ ነገሮች አሉ (ለምሳሌ፡- በኮርማርገፍያ፣ የሴቶች ስደት “ሌላ ዓይነት ቤተሰብ” ፈጥሯል ተብሏል)፡፡ የልጃገረዶች ትምህርት አስፈላጊነትም ላይ የአመለካከት ለውጥ ተፈጥሯል፤ ትኩረትም ይሰጠው ጀምሯል (ለምሳሌ፡- በሶሞዶና ሲርባ በኑሮ የተደራጁ ሀብታም ቤተሰቦች፤ ለሴት ልጆቻቸው የጥናት ጊዜ ለመስጠት የቤቱን ሥራ የሚያከናውን ሰራተኛ ይቀጥራሉ)፡፡ በሌላ በኩል፤ ሴቶች በኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች የሚቀዳጁት ስኬትና ተግተው መስራታቸው በአንዳንድ አጋጣሚዎች የአመለካከት ለውጥ አስከትሏል፡፡ ለምሳሌ፡- በኮርማርገፍያ፣ አንዳንድ በሴት የሚተዳደሩ ቤተሰቦች፣ በወንድ ከሚተዳደሩት የበለጠ ስኬታማ ለመሆን ችለዋል፡፡

ሆኖም ይሄ ቁርኝት ግልጽ የሆነ አይደለም፡፡ አንዳንድ ማህበረሰቦች የወግ አጥባቂነት አመለካከትን የመቀነስ ለውጥ ቢያሳዩም ሴቶች የሚሳተፉባቸው የኢኮኖሚ ዘርፎች ግን ውስን እንደሆኑ ቀጥለዋል (ለምሳሌ፡- ሃረሳውና ገብለን)፡፡ በሌላ በኩል፤ ሴቶች በተጨባጭ ዘርፈ ብዙ በሆኑ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በሚሳተፉባቸው ሌሎች ማህበረሰቦች ደግሞ ከሴቶች ደረጃ አንጻር ማህበራዊ ለውጡ ውስን መሆኑ ተነግሯል (ለምሳሌ፡- ጋራ ጎዶ)፡፡ ወንዶች፤ የተወሰኑ “ይበልጥ አትራፊ” የሆኑ የንግድ ዘርፎችን በበላይነት መቆጣጠራቸውን ቀጥለውበታል፡፡ ለምሳሌ፡- ዋናውን የገበያ አዝርዕት ንግድ በአብዛኛው የሚያካሂዱት ወንዶች ናቸው (ለምሳሌ፡- በአዳዶ ወንዶች ብቻ ይቆጣጠሩታል)፡፡ ይሄ ብቻም አይደለም፡፡ አዲስ የንግድ ዘርፎችም ይበልጥ ትርፋማ እየሆኑ ሲመጡ ወንዶች ይረከቡታል (ለምሳሌ፡-በኮርማርገፍያ፣ የወተት ምርት/ንግድ /በአዬሌ ኬኬ፣ ቀድሞ በ‹ሴት› ይመራ የነበረ ዘርፍ ነው)፡፡

ባህልና ሃይማኖት ከሴቶች ወይም ልጃገረዶች ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ ጋር ረቂቅ በሆኑ መንገዶች መስተጋብር በመፍጠር ለአብነት የሚበቁ ለውጦችን አስከትለዋል (ለምሳሌ፡- በአዜ ዴቦአ፣ የከምባታ ሴቶች በነባር ባህላዊ ልማድ መሰረት፣ ከቤት አይወጡም ነበር፤ አሁን ግን ሥራ ፍለጋ ይሰደዳሉ)፡፡ በተለያዩ ልማዶች መካከል ፉክክርም ታይቷል (ለምሳሌ፡- የፕሮቴስታንት አማኞች በሚበዙበት አዳዶ፤ ሴቶች ቤት ውስጥ እንዲቀመጡ የሚያደርገው ነባር ባህላዊ ልማድ፤ የኢኮኖሚ ስኬትን ከሚሰብከው የፕሮቴስታንት እሴት የበለጠ ተፅዕኖ ፈጣሪ ሆኗል)፡፡ ወንዶችም የሴቶች በኢኮኖሚው መሳተፍ ስጋት እንደፈጠረባቸው ገልፀዋል፡፡ ለምሳሌ፡- ከቤት ውስጥ ሃላፊነታቸው ጋር እንደሚጋጭ ወይም የቤት ውስጥ ጉዳያቸውን ችላ እንዲሉ እንደሚያደርጋቸው አሊያም ከትክክለኛው ባህሪ እንዲያፈነግጡ ሊያደርጋቸው እንደሚችል ጠቁመዋል (ለምሳሌ፡- በዶአማ፣ አንድ ገበሬ፤ ሚስቱ በእርሻ የጉልበት ሥራ ላይ ከተሰማሯች መጥፎ ባህሪ ታመጣለች የሚል ስጋት ነበረው)፡፡ በሌላ በኩል፤ ሴቶች በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ከመሳተፍ ወደ ኋላ የሚሉት ከቤት መውጣት የለብንም በሚለው ነባር አመለካከት ብቻ ሳይሆን ባለቤቶቻቸው ፈቃደኛ ስለማይሆኑ ነው ተብሏል (ለምሳሌ፡-ግራር)፡፡ በተቃራኒው ደግሞ ሴቶች፣ የወንዱ ስጋት ሴቶች በማህበረሰቡ ውስጥ ከሚኖራቸው የደረጃ ለውጥ ጋር የተገናኘ መሆኑን ተገንዝበዋል (ለምሳሌ፡- በሲርባ፣ በዋናነት በሰብል ንግድ ላይ የተሰማሩ ሴቶች እንደጠቆሙት፤ ወንዶች «ሴቶች ነፃ ከተለቀቁ በጣም ሃይለኛ ይሆናሉ» ብለው ይፈራሉ)፡፡

<u>ትራንሰፎርሜሽንን መምራት፡- የአርኣያዎችና የህልም ፋይዳ</u>

የWIDE ጥናት መረጃ፣ አዎንታዊ ኡደት መኖሩን የሚጠቁም ማስረጃ ያቀርባል፡፡ ዓይነተኛ በሆነ መንገድ በኢኮኖሚው ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉ ወይም ስኬታማ የሆኑ የተወሰኑ አርአያ ሴቶችና ልጃገረዶች መኖር፤ ሴቶችን በሚመለከት ከተፈጠረው ሰፊ የአመለካከት ለውጥ እንዲሁም ከሴቶችና ልጃገረዶች እያደገ የመጣ ህልምና ተስፋ ጋር በመጣመር፣ ሴቶችና ልጃገረዶች የሚያከናውኗቸው ወይም ለራሳቸው ይቻላል ብለው የሚያስቧቸው የሥራ ዘርፎች ላይ የወሳኝነት ሚና ይጫወታሉ፡፡ ነባር ልማዳዊ ሚናዎችንና አመለካከቶችን የተጋፈጡ ሴቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ፡- ሴቶች የወንድ ጥገኛ መሆን እንደሌለባቸው በተግባር እንዳሳየችው፣ የዲንኪ ሴት የወረዳ ምክር ቤት አባል ወይም ደግሞ እንደ ሶሞዶዋ ሀብታም ሴት ነጋዴ ዓይነት ሰዎች ይገኛሉ፡፡ ይህቺ ሴት፣ መጀመሪያ ላይ በኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ እንዳትሳተፍ ባለቤቷ ጫና ቢያሳድርባትም የአካባቢ ሽማግሌዎችን ድጋፍ አግኝታ፣ ስኬታማ ነጋዴ ልትሆን በቅታለች (ማጣቀሻ፡- ስኬት)፡፡ እነዚህ ሴቶች በጣም ጥቂት ናቸው፤ ነገር ግን እንዲህ ዓይነት አርአያዎችና ሌሎች የተማሩ አልያም በኢኮኖሚ ስኬታማ የሆኑ ወይም ራሳቸውን የቻሉ ሴቶች፣ ትርጉም ያለው ተፅዕኖ እንደሚፈጥሩ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

ልጃገረዶች ወይም ወጣት ሴቶች አብዛኛውን ጊዜ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ነፃነትንና ‹የተሻለ ህይወት›ን ለማግኘት ይጥራሉ፡፡ ይሄ ደግሞ ብዙውን ጊዜ ከትምህርት ጋር ይገናኛል፡፡ ይሁን እንጂ ምንም እንኳን እያደገ የመጣው ከፍተኛ ተስፋና ተጨባጩ የወጣቶች የሥራ አጥነት ደረጃ፣ በትምህርት ላይ ያለመተማመን ስሜትን እንደሚፈጥር ተስተውሏል፡፡ የተሻለ የሚያልሙ ሴቶች ስደትን የሚወስዱት እንደ አማራጭ ሆኗል፡፡ ምክንያቱም የሚሰደዱት የሆኑ አማራጮችን አልመው ሳይሆን የተሻለ ጥቅም ይገኝበታል በሚል ድፍን ተስፋ ነው፡፡ ይሄም መዘዋወርን ለተሻለ ህይወት፣ እንደ አንድ እርምጃ ከመቁጠር ሰፊ ህልም ጋር ይገናኛል፡፡ ከዚህ አንጻርም በርካታ ልጃገረዶች፣ በማህበረሰባቸው ውስጥ መቀመጥን አይሹም (ማጣቀሻ፡- ትምህርት፤ እና ፍልሰት)፡፡

ወጣት ልጃገረዶች ወይም ሴቶች በአጠቃላይ ሊሆኑ የሚሹትን ሲያስቡ የበለጠ ከፍ አድርገው ነው (ብዙዎች በህክምና እና ምህንድስና ዘርፍ መማርና መስራት ነው የሚፈልጉት)፡፡ በሌላ በኩል፤ በዕድሜ ገፋ ያሉት ሴቶች፣ አብዛኛውን ጊዜ በትምህርት ያልዘለቁ ሲሆኑ በ “ተጨባጭ ህይወት” የተጠመዱና የቤተሰብ ኃላፊነት የተሸከሙ ናቸው፡፡ እነዚህ ሴቶች፣ መተዳደሪያ ገቢን ለማግኘት ያሉትን ማነቆዎች የበለጠ ያውቃሉ፤ ስለዚህም በሃረሳውና፣ በጋራ ጎዶ እንደታየው የሸቀጣሸቀጥ ሱቆች ወይም ምግብ ቤት ለመክፈት፣ በገልቻ እንደታየው በመስኖ እርሻ ሥራ ላይ ለመሰማራት) ወይም ጋራ ጎዶ እንደታየው ነባር ንግዳቸውን ለማስፋፋት ያልማሉ፡፡

ወጣቶች ሴቶች ወይም ልጃገረዶች በሚያልሙትና በተጨባጭ በአካባቢያቸው ባለው የሥራ ዕድል መካከል ከፍተኛ ልዩነት አለ፡፡ አንዳንዶች የመጀመሪያ ህልማቸው እውን ባይሆን ሁለተኛ ዕቅድ ይኖራቸዋል፤ ቀጣይ የትምህርት ዕድል ከሌላቸው አብዛኛውን ጊዜ ስደት ወይም ገቢ በሚያመነጩ እንቅስቃሴዎች ላይ መሳተፍ ነው የሚሆነው፡፡ ለምሳሌ በአዳ ሃሮ - ስደት፣ በኮርማርገፍያ - የዶሮ እርባታ እንዲሁም በሹምሸሃና አዬሌ ኬኬ - የሸቀጣ ሸቀጥ ሱቆች መክፈትን የመሳሰሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ (ማጣቀሻ፡- ትምህርት)፡፡

አብዛኞቹ እነዚህ ይበልጥ ተጨባጭ የሆኑ ተስፋዎች፣ ከእርሻ ዘርፍ ውጭ የተቃኙ ናቸው፡፡ በጣም ጥቂት ሴቶች ወይም ልጃገረዶች ብቻ ናቸው በእርሻ ወይም ከእርሻ ጋር በተገናኙ ሥራዎች ላይ ለመሰማራት የሚፈልጉት፡፡ ይሄም በወጣት ወንዶችም ሆነ ሴቶች ዘንድ የሚታይ ይበልጥ አጠቃላይ የሆነ አዝማሚያን የሚያንፀባርቅ ነው፡፡ ነገር ግን ሌላ ተጨማሪ እውነታም አለ፡፡ ይኸውም ሴቶች ራሳቸውን እንደ “እርሻ ሥራ አስኪያጆች” ወይም ሃላፊዎች አለማየታቸው ነው - መሬቱ የራሳቸው ንብረት ቢሆንም አሊያም ደግሞ ከባለቤታቸው ጋር ቢያስተዳድሩትም ለውጥ የለውም (ማጣቀሻ፡- ትምህርት፤ እና ወጣቶች)፡፡

<u>መሻሻልን ለማጎልበት - ልማዶችና ተሰፋዎች ላይ ተፅዕኖ ማድረግ</u>

በኢኮኖሚውና በማህበረሰባዊ አውድ ላይ የሚከሰቱ ለውጦች በአንድ የተወሰነ ማህበረሰብ ውስጥ እርስ በርስ የሚፈጥሩት መስተጋብር፣ በፊናው የሴቶችንና ልጃገረዶችን የኢኮኖሚ ተሳትፎ ይፈጥራል፡፡ ለምሳሌ፡- በኡዳ ሃሮ፣ ከሴቶች ጥንካሬ ጋር በተያያዘ የተፈጠረው የአመለካከት ለውጥና የአካባቢው ኢኮኖሚያዊ ዕድገት፣ ለሴቶች ሰፋ ያሉ የንግድ አማራጮች መከፈት አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡ ከትምህርት በሚገኘው ውጤት ላይ ከተፈጠረ ከፍተኛ ያለመተማመን ስሜትና ቁጥራቸው እየጨመረ ከሚገኝ ወጣት ሴቶች ለሥራ መሰደድ ጎን ለጎን የልጃገረዶች ትምህርት መሻሻል አሳይቷል፡፡ ይሄም በፊናው፣ በሴቶች ላይ ተጨማሪ የአመለካከት ለውጥን አስከትሏል፤ ለምሳሌ፡- ወጣት ሴቶች የኢኮኖሚ ነፃነት በመሻት የሚያደርጉት ስደት “ብልህነት የተመላበት ኢኮኖሚያዊ እርምጃ” በሚል ነው የተገለፀው፡፡ በተቃራኒው በሹምሽሃ፣ በንፅፅር በሴቶች ዘንድ ከፍተኛ ደረጃ ያለው ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ቢኖርም፣ ጠንካራውን የአማራ ብሄረሰብ ወግ አጥባቂነት ለመገዳደር በቂ ሆኖ የተገኘ አይመስልም፡፡ ለብዙ ወላጆች፣ አሁንም ድረስ ሴት ልጅን በቶሎ መዳር፣ ከሌሎች አማራጮች የበለጠ ቅድምያ የሚሰጠው ትልቅ ጉዳይ ነው፡፡

ሰፊ ለውጦችና ዕድገቶች ቢመዘገቡም አመለካከቶችና የማህበረሰብ ልማዶች፣ ለሴቶች ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ እንቅፋቶች ሆነው ቀጥለዋል፡፡ በኢኮኖሚያዊ ተሳትፎና አመለካከቶችን በመለወጥ እንዲሁም ለፆታ እኩልነት መስፈን መሰናክል የሆኑ ቀጣይ ማህበረሰባዊ እንቅፋቶችን በማሸነፍ መካከል ያለውን ሁለትዮሽ የለውጥ ሂደትን ማጠናከር፣ ለሰፊው የፆታ እኩልነት ግቦች በአዎንታዊነት አስተዋፅኦ ያደርጋል (የኢትዮጵያ ሴቶች ብሄራዊ ፖሊሲ ላይ በተቀመጠው መሰረት) በተጨማሪም በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (GTP2) ላይ በታቀደው መሰረት፣ የሴቶችን በአገሪቱ ትራንስፎርሜሽን ላይ የተሟላና ፍትሃዊ ተሳታፊነት ያረጋግጣል፡፡ የሴቶችን ተሳትፎ የሚያሳድጉ እርምጃዎች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡-

- የሴቶችን ወይም ልጃገረዶችን ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ ለማገዝ የታለመ እንደአካባቢው የተቀረፀ የለውጥ እርምጃን ማጠናከር (ለምሳሌ፡- ለሴቶች የህብረት ሥራ ማህበራት የተሟላ በቂ ድጋፍ ማድረግን) በማህበረሰብ ውስጥ የሴቶችን ልዩ ፍላጎቶች ከግምት ውስጥ ያስገባ ድጋፍ መቅረፅ፤ ሴቶች በሥራ ገበያ ውስጥ የሚያደርጉትን ውጤታማ ተሳትፎ ለማገዝ የሚደረጉ የመንግስት የለውጥ እርምጃዎችን አቅም ያሳድጋል፡፡
- የፆታ እኩልነትን የሚያንፀባርቁ መልዕክቶች፤ ወንዶችንም ሴቶችንም በአግባቡ ማሳተፋቸውን ማረጋገጥ፤ (ለምሳሌ የፆታ እኩልነትን የሚያንፀባርቁ መልዕክቶች

“የተጨባጭ ህይወት” ሁኔታዎች ላይ ያነጣጠሩ በማድረግና በተለይ በወንዶች የሚነሱትን "የተጨባጭ ህይወት" ስጋቶችን በመቅረፍ)፡፡ የፆታ እኩልነትን ለማስፈን የሚደረጉ ጥረቶች አብዛኛውን ጊዜ ወንዶችን አያሳትፉም፤ ነገር ግን ወንዶችን በውይይት ለማሳተፍ ወይም በስጋቶች ዙሪያ (እና ከራሳቸው ተሳትፎ አንፃር ለሴቶች ለውጡ ምን ማለት እንደሆነ) ውይይት ለመፍጠር፣ ጥንቃቄ የተመላበትና በቅጡ የታለመ መድረክ ያስፈልጋል፡፡

- በማህበረሰቦች ውስጥ አርአያ የሆኑ ሴቶችን ተፅዕኖ ማስፋት (ከፈርጀ ብዙ የኢኮኖሚ ዘርፎች/ ሙያዎች እንዲሁም ከገጠር ማህበረሰብ፣ ሴቶችና ልጃገረዶች ጋር የጋራ የሆኑ ተሞክሮዎች) ይሄንንም ይበልጥ በታለመና ውጤታማ በሆነ የግለሰቦች አጭር ታሪክ አማካኝነት ማከናወን (ለምሳሌ፡- ሴቶች በት/ቤቶች ንግግር እንዲያደርጉ በመጋበዝ፣ የሚዲያ ክለቦች አዎንታዊ የሴቶች ጉዞዎችን እንዲያነሱ በማበረታታት፤ መደበኛ ያልሆኑ የማህበረሰብ ቡድኖች ለ“ስኬት” ዕውቅና እንዲሰጡና እንዲያስተዋውቁ ማነሳሳት)፡፡

የሥራ ፍለጋ ፍልሰት

በገጠር ማህበረሰቦች ለሥራ ፍለጋ የሚደረግ ፍልሰት (2010-13)

WIDE የውይይት መነሻ አጭር መግለጫ ቁ. 7/...10[1]

ዋና ዋና ነጥቦች ከWIDE መረጃዎች፡-

- በተገኙት ሰፊ መረጃዎች መሠረት፤ ለሥራ መዘዋወር መጀመሪያ የተከሰተው ከልማት ጋር ተያይዞ ነው[2]፤ በ2010-13 ጥናቱ የሚከተሉት ድምዳሜዎች ላይ ደርሷል፡-
  - በጣም የተስፋፋና ይበልጥ ውስብስብ ፍልሰት በWIDE ማኅበረሰቦች፤ ብዙ ሰዎች በተለይ በርካታ ሴቶችና ወጣቶች ሥራ ፍለጋ ይፈልሳሉ፤ ለተለያዩ የቆይታ ጊዜያትና ወደ ተለያዩ መዳረሻዎች (ከተሞች፣ፋብሪካዎች፣ ሌሎች የገጠር አካባቢዎች፤በኢትዮጵያና ከኢትዮጵያ ውጭ - ይሄ እስከ ጥቅምት 2013 ድረስ በህጋዊ መንገድ ይካሄድ ነበር)፤
  - ይህ የማህበረሰቦች የዕድገት ውጤት ነው፤ ሰዎች በውስጣቸው የተፈጠረውን የተሻለ የመሻት ህልምና ራዕይ ለማሳካት (በአርአያነት በሚታዩ ቀደምት ስኬታማ ስደተኞች ላይ ይንጸባረቃል) እንዲሁም ለኑሮ ማነቆዎች ምላሽ ለመስጠት ከቦታ ቦታ ይዘዋወራሉ - በተለይም ለወጣቶች መሬት አልባነትና ሥራ አጥነት፤
  - የፍልሰት ተሞክሮዎች የተቀላቀሉ ውጤቶች አሉት፤ የከፋ ጉዳት ያጋጥማል፤ ነገር ግን ስኬታማ ስደተኞች በአካባቢያቸው ኢኮኖሚ ላይ መዋዕለ ንዋያቸውን ሲያፈሱ፣ የስደተኛ ቤተሰቦች የኑሮ ደህንነትና ማህበራዊ ዋስትና ይጎለብታል፤ ነባር ማህበራዊ ልማዶች እንዲለወጡ አስተዋጽኦ ያደርጋል (ለምሳሌ፡- የሴቶች ማህበራዊ ደረጃ መለወጥ)፤ እንዲሁም በመሬትና የሥራ ዕድል እጥረት ሳቢያ የሚከሰተው ውጥረት ይረግባል፤

---

[1] ይህ አጭር የጥናት መግለጫ፤ በWIDE የውይይት መነሻ አጭር የጥናት መግለጫዎች ሁለተኛ ጥራዝ (ስብስብ) ውስጥ ከተካተቱት አስር መግለጫዎች አንዱ ነው፡፡ መግለጫው፤ በካትሪን ዶም የተዘጋጀ ሲሆን በአስናቀ ከፍአለ ተገምግሟል፡፡ አዘጋጁዋ፤ መግለጫዎቹ ይሰናዱ ዘንድ በገንዘብ ለደገፉት ለእንግሊዝ ዓለም አቀፍ ልማት ተቋም፣ ለአይሪሽ ኤይድና ለስዊድን ዓለምአቀፍ ልማት ድርጅት ልባዊ ምስጋናዋን ታቀርባለች፡፡ በተጨማሪም የጥናት ሪፖርቱን በማርቀቅ ሂደት የተሳተፉና አጭር የጥናት መግለጫው የትኩረት አቅጣጫ እንዲሰላ እገዛ ያደረጉ ሌሎች የጥናት ቡድን አባላትና ባለሙያ ገምጋሚዎች፣ ለሥራው ለሰጡት ጊዜና ድጋፍ ታመሰግናለች፡፡ ሌሎች ምስጋናና ዕውቅና የሚያሻቸውም አሉ፡- (1) ለዓመታት የጥናት መግለጫው የተዘጋጀበትን መረጃዎች ያሰባሰቡና ያደራጁ የጥናት መኮንኖችና ተቆጣጣሪዎች ሙሉ ጊዜያቸውን ሰጥተው ላበረከቱት አስተዋጽኦ፤ (2) በሶስት ዙሮች ለተካሄደው የWIDE ጥናት የገንዘብ ዕገዛ ላደረጉ የተለያዩ ድጋፍ ሰጪ ተቋማት፤ እና (3) በኢልምተ ሰብሳቢነትና በኢኮኖሚ ፖሊሲ ትንተና ክፍሉ በWIDE አጭር የጥናት መግለጫዎች ሁለተኛ ጥራዝ ላይ ለመወያየት መጋቢት 28 ቀን 2016 ዓ.ም በተዘጋጀው መድረክ ላይ የተሳተፉ ከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣናት፣ ላሳዩት ፍላጎትና ለከፈሉት የጊዜ መስዋዕትነት--- ምስጋና ይገባቸዋል፡፡ የጥናት መግለጫው፤ በከፍተኛ ደረጃ በተዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ፣ ከመንግስት ባለሥልጣናት ጋር በተደረገው ውይይት የተሰጡ አስተያየቶችን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ከለሳና ማሻሻያ ተደርጎበታል፡፡ አጭር የጥናት መግለጫው፤ የኢትዮጵያ የልማት ምርምር ተቋምን (ኢልምተ) ወይም የኢትዮጵያ መንግስትን አሊያም የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርጉለትን የልማት አጋሮች አመለካከትም ሆነ አቋም አይወክልም፤ ይልቁንም የፖሊስ ውይይት ለማነቃቃት የታለመ ነው፡፡ ሌሎች የጥራዝ ሁለት የውይይት መነሻ አጭር መግለጫዎችንና የጥናትና ምርምር ውጤቶችን በhttp://ethiopiawide.net/ ድረ-ገጽ ላይ ማግኘት ይቻላል፡፡

[2] ከሌመንስ (2014)፤ "*Does development reduce migration?*" በሚለው ጥናቱ እንደገለጸው፤"አንድ ዘለግ ያለ ጽሁፍና የቅርብ ጊዜ መረጃ፣ ጨርሶ የተለየ ነገር ይጠቁማል፤ "በሰዎች እንቅስቃሴ ሽግግር" ሂደት፣ አገራት ከፍተኛ- መካከለኛ ገቢ ላይ እስከሚደርሱ ድረስ፣ ስደት በጥቅሉ ከኢኮኖሚ ዕድገት ጋር የሚጨምር ይሆናል፤ ከዚያ በኋላ ብቻ ነው የሚቀንሰው"፡፡

- ...ከሥራ ጋር የተዛመደ የገጠር ፍልሰት፣ ለገጠር አካባቢያዊ ዕድገት አስተዋጽኦ ሊያበረክት እንደሚችል ጥናቱ ይጠቁማል፡፡ ይህን አቅም ለማጠናከር መንግስት የሚከተሉትን ከግንዛቤ ውስጥ ሊያስገባ ይችላል፡-
  - የስደት አደጋዎችንና ጥቅሞችን ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ የስደት ፖሊሲን ማሻሻል፤ እንዲሁም ሁሉም ባለድርሻ አካላት፣ የመጀመርያውን እንዲከላከሉና ሁለተኛውን እንዲያነለብቱ አቅጣጫ መስጠት፤
  - በኢትዮጵያ የስደት ፖሊሲና አመራር (እያደገ የሚሄድና ውስብስብ) እንዲጠናከር ለማገዝ፤ ተቋማዊ የትንተና አቅምን መፍጠር፤
- ከስደት የሚላክ ገንዘብ አጠቃቀምን ለማሻሻል ያለሙ እርምጃዎች፣ ከገጠር ፍልሰት የሚገኙ ውጤቶችን ያጎለብታሉ፡፡ ለምሳሌ፡-
  - የገንዘብ ዝውውርና የባንክ አገልግሎት አማራጮችን የበለጠ ምቹ ማድረግ (በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በታሰበው መሠረት በገጠር አካባቢዎች የባንክ አገልግሎቶችን ማስፋፋት)፤
  - ከስደተኞች የሚላክ ገንዘብ ወይም ቁጠባ፤ ለመድን ዋስትና ፕሮግራሞችና ለብድር መያዣነት እንዲውል ማበረታታት፤
  - ከቀዬአቸው የፈለሱ የጉራጌ ተወላጆች የልማት ባህልን በመከተል፤ የባህር ማዶ ስደተኞች ወይም ተመላሾች፣ በትውልድ አካባቢያቸው፣ የመሰረተ ልማት ግንባታዎችን የሚደግፉባቸውን መንገዶች መቅረጽ (ለምሳሌ፡- "የአካባቢ የልማት ትስስሮች/ ቦንድ")
- ለከተማ/ኢንዱስትሪ ሥራ መፍለስ፣ ለገጠር ማህበረሰብ ይበልጥ አስፈላጊ እየሆነ መጥቷል፡፡ ሆኖም ብዙ ጊዜ ደህንነቱ ያልተጠበቀ ህይወት ያስከትላል፤ በዝባዥ ለሆነ የሥራ ሁኔታ ያጋልጣል (በተለይ ወደ ከተሞች ለሚፈልሱ ሴቶች)፤ በዚያ ላይ ገቢውም እዚህ ግባ የሚባል አይደለም (ያውም ከተገኘ)፤
- የከተማ/ኢንዱስትሪ ፍልሰት ተሞክሮን ማሻሻል፣ የመንግስት የኢንዱስትሪንና የአነስተኛ ከተሞች የልማት ማስፋፋት ፖሊሲ ግቦችን ያጠናክራል፡፡ ይሄን ሊያግዙ ከሚችሉ የተወሰኑ እርምጃዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡-
  - የስደተኞች መታወቂያ ወረቀትና የማህበራዊ አገልግሎት ተደራሽነትን ምቹ ማድረግ እንዲሁም ክፍት የሥራ ቦታዎችን የተመለከቱ መረጃዎች መስጠት፣
  - አነስተኛ የሥራ ሁኔታን ማስፈጸም፤ የአሰሪዎችን ሃላፊነቶች ግልጽ ማድረግና መከታተል፡፡
- እነዚህን እርምጃዎች በትናንሽ ከተሞች/የአካባቢ ፋብሪካዎች መተግበር፣ ወደ ትላልቅ ከተሞች የሚደረገውን ፍልሰት ሊቀንስ ይችላል፤ ምክንያቱም ብዙዎች ወደ ማህበረሰባቸው መጓዝ ወይም ዘወትር መመላለስ በሚያስችላቸው የመኖርያቸው አቅራቢያ መስራትን ይመርጣሉ፡፡
- በገጠር ኢትዮጵያ ሰዎች ህገ ወጥ ስደት የሚያስከትለውን አደጋዎች ያውቃሉ፡፡ እንዲያም ሆኖ በተጨባጭ የደረሱ ጉዳቶች መኖራቸው እየታወቀ፣ ብዙ ጊዜ ህገ ወጥ ስደት ተመራጭ ነው፤ ምክንያቱም ህጋዊው የባህር ማዶ የስራ ቅጥር ሂደት (በሚኖር ጊዜ) ውድና "የተሻለ አይደለም"

ተብሎ ይታሰባል፡፡ በዚያ ላይ በህጋዊ መንገድ የሚጓዙቱ እራሳቸው፣ በቂ ዝግጅት የማያደርጉና አስተማማኝ ዋስትና የሌላቸው ናቸው፡፡

- ለወጣት ወንዶች (አብዛኞቹ ህጋዊ የባህር ማዶ የሥራ ዕድሎች ለቤት ውስጥ ሥራ እንደመሆኑ) እና ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ወገኖች (ብዙ ጊዜ ለስደት ጉዞ የሚያስፈልገው ወጪ የሚሸፈነው ጥሪት-በሚያሟጥጡ መንገዶች ነው) ህገ ወጥ ስደት እንደ ብቸኛ አማራጭ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡
- በቅርቡ የተሻሻለውን የባህር ማዶ የሥራ ቅጥር፣ ህጋዊ ማዕቀፍ በማጎልበትና ህገ ወጥ ስደትን ለማስቀረት እየተደረጉ ካሉ ጥረቶች ጎን ለጎን፣ መንግስት ህጋዊ የስደት ጉዞ የበለጠ ተመራጭ የሚሆንበትን መንገድ ማጤን ይኖርበታል፡፡ ለምሳሌ፡-
  - የተሟላና ግልጽ መረጃ በስፋት መኖሩን ማረጋገጥ (ለምሳሌ፡- በማህበራዊ ሚዲያና በመንግስት ቢሮዎች)፤
  - ህጋዊ የስደት ጉዞን የበለጠ ተደራሽ፣ ክፍያው ኪስ የማይጎዳና ጊዜ የማይወስድ ማድረግ (ለምሳሌ፡- የስደት ጉዳዮች አስተዳደርን ከማዕከላዊነት ማውጣት)፤
  - በባህር ማዶ ለሚገኙ ስደተኛ ሰራተኞች፣ አስተማማኝ ዋስትና ለመስጠት የሚያስፈልገውን የሰው ሃይል መመደብ፤
  - በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ የስደት ተጓጉች፣ ወጪያቸውን ለመሸፈን የሚያስችሉ መደበኛ የድጋፍ አማራጮችን መፍጠር፤
  - ለወጣት ወንዶች የሥራ ዕድሎችን መክፈት፤ ለምሳሌ፡- ዘርፈ ብዙ የሥራ ዓይነቶችን የሚያካትት የሁለትዮሽ ስምምነትና ወደ በርካታ መዳረሻዎች የሚደረግ የስደት ጉዞን ህጋዊ ማድረግ፡፡
- ሴቶች በከፍተኛ መጠን ከጨመረው ፍልሰታቸው፣ ሙሉ በሙሉ ተጠቃሚ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ይሄን ከሚያግዙ እርምጃዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙባቸዋል፡-
  - የኢንዱስትሪ አሰሪዎች፤ "ለተመሳሳይ ሥራ ተመሳሳይ ክፍያ" የሚለውን መርህ መተግበራቸውን ማረጋገጥ፤
  - በተለይ ከቤት ውስጥና ከእንግዳ አቀባበል የሥራ ቅጥር ጋር የተገናኙ ዝቅተኛ የሥራ መስፈርቶች ተፈጻሚነት ላይ ማተኮር፤
  - ሴቶች በስደት ከሚልኩት ገንዘብ ተጠቃሚ የመሆን መብታቸውን ማስከበር፤ ለምሳሌ፡- ወጣት ሴቶች፤ ከቤተሰባቸው ውጭ በግላቸው የሚጠቀሙበት የባንክ አገልግሎትና ለቁጠባ የሚያተጓቸው የብድር ፕሮግራሞችን ምቹ ማድረግ፡፡

መግቢያ

ጥቂት ወይም በብዛት፣ ለብቻ፣ ተመላላሽ ወይም ተደጋጋሚ፣ ጊዜያዊ ወይም ዘላቂ፣ በፍቃደኝነት ወይም በግፊት የሚደረጉ ከቦታ ቦታ ዝውውሮችን ጨምሮ ዘርፈ ብዙ የሰዎች እንቅስቃሴ ይካሄዳል፡፡ ዝውውሮቹ በተለያዩ ምክንያቶች ይከሰታሉ - ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወይም ፖለቲካዊ (ወቅትን የተከተለ ሥራ፣ የኑሮ መተዳደሪያዎች ብዝሃነት፣ የፖለቲካ አለመረጋጋት፣ የጎሳ ግጭት፣ የተፈጥሮ አደጋዎች፣ ማህበረሰባዊ ስጋቶች፣ የጋብቻ ዕቅዶችን ጨምሮ)በእነዚህ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ተደራራቢ ሰበቦች፡፡ ይህ አጭር መግለጫ፤ ከኑሮ መተዳደሪያ ጋር በተዛመዱ ምክንያቶች፣ የትውልድ ቀዬአቸውን፣ የገጠር ማህበረሰብ፣ ትተው የሄዱ ግለሰቦች ተሞክሮዎች ላይ የሚያነጣጥር ይሆናል፡፡

ለሥራ መዘዋወር - ማን፣ የትና ለምን ያህል ጊዜ

የWIDE ጥናት ክትትል ባደረገባቸው ማህበረሰቦች፣ ሥራ ፍለጋ ከቦታ ቦታ መዘዋወር አዲስ ክስተት አይደለም፡፡ ከ1995 እስከ 2010/13 ባሉት ጊዜያት ግን ማነው የሚጓዘው፣ የትና ለምን ያህል ጊዜ ከሚለው አንጻር አዳዲስ አዝማሚያዎች ተፈጥረዋል፡፡ ወደ ሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች፣ የግብርና ሥራ ፍልሰት (ከቀዬአቸው ውጭ ባለ መሬት ላይ ለመቀጠር የሚጓዙ ሰዎች)፤ ከአዲስ/ግዙፍ የከተማ ወይም ኢንዱስትሪ ፍልሰት (የተለያየ ደረጃ ወዳላቸው የከተማ አካባቢዎች ወይም የኢንዱስትሪ መንደሮች - የአበባ እርሻ፣ የወርቅ ማውጫ፣ የኢንዱስትሪ ዞኖች፣ የአካባቢ ፋብሪካዎች-የሚጓዙ ሰዎች) እና ከባህር ማዶ የሥራ ስደት (ከፍተኛ ቁጥር ያለው ህዝብ ያካተተ) ጋር ተዛንቀው ዘልቀዋል፡፡ የፍልሰት ተሞክሮዎች በእጅጉ የተለያየ የቆይታ ጊዜያት ያላቸው ሲሆን ለምሳሌ፡- በአቅራቢያ ከተሞች ወይም ፋብሪካዎች ለተወሰነ ሥራ ለጥቂት ሳምንታት፣ ጥቂት ወራት ወይም የተወሰነ ወቅት እንዲሁም በርካታ ዓመታት እስከ መቆየት ይዘልቃል፡፡

ሥራ ፍለጋ ወደ ከተማ አካባቢዎች ወይም ፋብሪካዎች መጓዝ፣ ለሥራ ባህር ማዶ የመሻገር ያህል ትልቅ ቦታ አለው፤ ጉዳዩ በሁሉም ማህበረሰቦች የተነሳ ሲሆን በ12ቱ ትልቅ ቦታ እንዳለው ተስተውሏል[3]፡፡ በብዙ አካባቢዎች (ለምሳሌ፡- ጋራ ጎዶ/ወላይታ፣ አዳዶ/ጌዲኦ) ለወቅታዊ የከተማ/ኢንዱስትሪ ሥራ መፍለስ፤ ወቅታዊ የግብርና ፍልሰትን በከፊል ተክቶታል፡፡ በመስክ ጥናቱ ወቅት (በአብዛኛው፣ መንግስት በጥቅምት 2013፣ በህጋዊ የባህር ማዶ የሥራ ጉዞ ላይ ጊዜያዊ እገዳ ከመጣሉ በፊት የተከናወነ ነው)፤ የውጭ አገር መዳረሻዎች በዋናነት የባህረ ሰላጤ አገራት፣ ሱዳንና ለአዜ ዴቦአ (ከምባታ) ደቡብ አፍሪካ ነበሩ፡፡ ፍልሰቱ ህጋዊና ህገወጥ ስደትን ያካተተ ሲሆን ከማህበረሰብ ማህበረሰብ ይለያያል፡፡ በሰባት በእጅጉ የተለያዩ ማህበረሰቦች፤ ከወቅታዊ የገጠር ፍልሰት በተጨማሪ፣ ወደተለያዩ የከተማ/ኢንዱስትሪና ባህር ማዶ መዳረሻዎች የሚደረጉ ከፍተኛ ፍሰቶች ጎን ለጎን ዘልቀዋል፡፡

ከቀዬአቸው ወጥተው የሚሰሩ ሴቶች ቁጥር የጎላ ዕድገት አሳይቷል (ለምሳሌ፡- በ2013፤ በአዳ ዳዋታ/አርሲና በአዳሃሮ/ምዕራብ ሸዋ፤ ከወንዶች ይልቅ ሴቶች በብዛት ተሰደዋል) አያሌ የቅርብ ጊዜ

[3] *'RurbanAfrica – African rural-city connections'* research project የሚለውን ይመልከቱ (http://rurbanafrica.ku.dk/).

ስደተኞችም ወጣቶች ናቸው (ለምሳሌ፡- በ2010፤ በገብለን/ምስራቅ ትግራይ፣ ከ185 የወጣት ማህበር አባላት 56ቱ ቀዬአቸውን ትተው ሄደዋል)፡፡

<u>ሰዎች ለምን ይዘዋወራሉ</u>

ሰዎች የትውልድ ቀዬአቸውን ትተው የሚወጡት በፈርጀ ብዙ ምክንያቶች ነው፡፡ መጠኑ ከግለሰብ ግለሰብ ቢለያይም አብዛኛውን ጊዜ ከውሳኔ ላይ የሚደረሰው ገፊ በሆኑና ሳቢ በሆኑ ተጽዕኖዎች ላይ ተመስርቶ ነው፡፡ ሰዎች ህይወትን እንደ ማቆያ/ኑሮን ማሸነፊያ ትልምና ለተሻለ መጪ ህይወት እንደ ዋስትና በመቁጠር አካባቢያቸውን ትተው ይወጣሉ፡፡ በስደት ውሳኔ ላይ ህልምን ማሳካት ከበፊት ጊዜ የበለጠ ትልቅ ሚና ተጫውቷል፡፡ ለምሳሌ፡- በኡዳ ሃሮ ሰዎች ስለ ስደተኞች *"ህልም"* ጠቅሰዋል፡፡ አንዳንድ ሰዎች መጀመሪያ ላይ በጫና (አስገዳጅ ሁኔታ)ይሰደዳሉ፤ ይሄ ግን በኋላ ላይ ወደ ኢንቨስትመንት ይለወጣል፡፡ የሃረሳው (ምስራቅ ትግራይ፤ 2011) አባት ጥሩ አብነት ነው፡፡ በስድስት ዓመታትውስጥ ሦስት ጊዜ ወደ ሳኡዲ አረቢያ ተጉዟል፡፡ መጀመሪያ ላይ የራሱንና የወንድ ልጁን ዕዳ ለመክፈል ነበር፤ በኋላ ግን ለቤተሰብ ገንዘብ ከመላኩም ባሻገር በባንክ የቁጠባ ሂሳብ ከፍቷል፤ ጥሩ ቤትም መገንባት ችሏል፡፡

የስደት ውሳኔ አብዛኛውን ጊዜ ከጋራ የቤተሰብ ውሳኔ ይመነጫል፤ ወይም ከስደተኛው ኤጀንሲ እንዲሁም ከቤተሰብ፣ከዕድሜ አቻዎች ወይም የማህበረሰብ ጫና ተዕዕኖ እንደሚኖራቸው ሊዘነጋ አይገባም፡፡ ቤተሰብን የመርዳት አቅም ማጎልበት፣ በብዙ የስደት ውሳኔዎች ላይ ትልቅ ሚና ይጫወታል፡፡ ለምሳሌ፡- በአዜ ዴቦአ፣ አንዲት በአካባቢው የቡና እርሻ ላይ የምትሰራ ወጣት፣ ወደ አረብ አገር ለመሰደድ የምትሻው፣ *"እዚህ የምታገኘው ገንዘብ በቂ አለመሆኑን በመጠቆም የራሷንና የቤተሰቧን ህይወት ለመለወጥ"* እንደሆነ ገልጻለች፡፡በሶሞዶ (ጂማ አቅራቢያ) አንድ ገበሬ ስለ ስደት አስረግጦ ሲናገር፤ *"እኒያ ስደተኞች፤ ችግረኛ ቤተሰቦቻቸውን መርዳትና የራሳቸውን ህይወት መለወጥ ችለዋል--- ስደት እንደ ሥራ ዕድልም ያገለግላል፡፡ ስደት ባይኖር ኖሮ ቀበሌው ያንን ሁሉ ሥራ አጥ ወጣት የት ያደርገው ነበር?"* ብሏል፡፡

በኢኮኖሚ ስኬታማና በቂ ትስስር በፈጠሩ እንደ ኡዳ ዳዋታ (በአዳማ-አሰላ መንገድ)፣ ሶሞዳ (በጂማ አቅራቢያ) እና ሲርባ (በቢሾፍቱ-ሞጆ መንገድ) በመሳሰሉ ማህበረሰቦችም ሆነ እንደ ሃረሳው ድህነት በበረታባቸው/በቅጡ ባልተሳሰሩ ማህበረሰቦች ውስጥ፤ ከፍተኛ የሰዎች ዝውውር ታይቷል፡፡ ስለዚህ፣ የአካባቢው ኢኮኖሚ በጤናማ ሁኔታ እያደገ ባለበትም ወቅት ጭምር፣ በአካባቢው ያሉት የሥራ አማራጮች በጣም ውስን ይሆናሉ አሊያም ይበልጥ የተማሩ የሚባሉ ወጣቶችን ህልምና ፍላጎት አይመጥኑም (ለምሳሌ፡- በሃረሳው *"ለወጣቱ የሚመጥን የሥራ ዕድል የለም"*)፡፡

ለበርካታ ወጣት ወንዶች ለኑሮ በቂ ሃብትና ከዚያም በላይ ያላቸውን ሰዎች ጭምር፤ ህልምና ራዕይ ከመሬት አልባነት ዕጣ ፈንታ ጋር ተዳምረው እንዲሁም የወጣት ወንዶችና ሴቶች ሥራ አጥነት፤ ስደትን ትክክለኛ አማራጭ አድርጎታል ፡፡ ለምሳሌ፣ በሲርባ አንድ በኑሮው የተደላደለ ገበሬ፤ አንዷ ሴት ልጁ፣ 10ኛ ክፍል ከጨረሰች በኋላ ሥራ ባለማግኘቷ፣ ወደ ዱባይ ተሰድዳ እየሰራች መሆኑን አስረድቷል፡፡ ገበሬውና ቤተሰቡ ከልጅቱ ገንዘብ አይፈልጉም፤ ህይወቷን እንድታሻሽል ብቻ ነው የሚሹት፡፡ በሃረሳውና ሌሎች ማህበረሰቦች፤ የመንግስት ሠራተኞችም ሳይቀሩ (ለምሳሌ፡- መምህራን) ተሰድደዋል፡፡

ለረዥም ዘመን የዘለቁ ነባር ወይም ዘመነኛ የስደት ልማዶችም የራሳቸው ተጽዕኖ አላቸው፡፡ በግራር (የጉራጌ ወደ ከተማ የመፍለስ ልማድ)፣ አዜ ዴቦአ (በጥቂት ዓመት ውስጥ "ልማድ" የሆነው የከምባታ/ሃዲያ ወደ ደቡብ አፍሪካ መሰደድ)፣ሃረሳው (በአፋር በኩል ከሳኡዲ አረቢያ ጋር የንግድ ግንኙነቶችን መስፋፋት) እንዲሁም አዴሌ ኬኬ/ምሥራቅ ሐረርጌ (ለሴቶች ከቤት ውስጥ ሥራ፣ ለወንዶች ከጫት ንግድ ጋር የተያያዘ፣ ወደ ጅቡቲ የሚደረግ ልማዳዊ፣ ከወቅት ጋር የተያያዘ ስደት፤ ጥቂቶች ወደ የመንና ሳኡዲ ጉዞ የሚቀጥሉበት) ለምሣሌ ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

በትምህርትና በመደበኛ ሥራ የተሻለ ኑሮ ከሚመሩ ጥቂቶች ጎን ለጎን፣ ያለ ብዙ ትምህርት ስኬት የተቀዳጁ ደፋር ስደተኞች፤ ትምህርታቸውን ገና በማለዳ በማቋረጣቸው ወይም በመውደቃቸው ሥራ የማግኘት ተስፋቸው ለተዳፈነ አያሌ ወጣቶች፣ አዲስ አርአያ ሆነዋል (ማጣቀሻ፡- ትምህርት፤ እና ወጣቶች)፡፡ ለምሳሌ፡- አርአያዋ አንዲት የስደት ተመላሽ መሆኗን የገለጸች የ13 ዓመት የሶሞዶ ታዳጊ፤ *"ለመሰደድ የምፈልግበት ምክንያት 10ኛ ክፍልን ስጨርስ፣ ውጤቴ ሥራ ለማግኘት በቂ ላይሆን ይችላል ብዬ ስለምፈራ ነው"* ብላለች፡፡ በሃርሬሳው አንድ የችግረኛ ቤተሰብ ልጅ፣ የመንግስት ዩኒቨርሲቲ ለመግባት የሚያበቃ ውጤት ቢያመጣም፣ ቤተሰቡ ወጪውን ሊሸፍኑለት አልቻሉም፤ በዚህም የተነሳ "ተስፋ ቆርጦ" ወደ ሳኡዲ ተሰድዷል፡፡

<u>የስደት አደጋዎችና ጥቅሞች ተመጣጣኝነት</u>

ከትውልድ ቀዬ ወጥቶ የመሰደድ አደጋዎችና ጥቅሞች ተመጣጣኝነትን አስመልክቶ የተለያዩ ሰዎች በጣም የተለያዩ አመለካከቶችን ያንጸባርቃሉ፡፡ የወረዳ ሃላፊዎች፣ አብዛኛውን ጊዜ ስኬታማ ያልሆነ ስደት፣ አደጋዎችና ጉዳቶችን አጉልተው ይናገራሉ፤ በጣም የተለመደ ክስተት አድርገውም ያቀርቡታል፡፡ ስደት እንደ *"ኣዲሰ ሃጂ ልማድ"* ነው የተገለጸው(በሶሞዶ)፤ ለስደተኞቹና ቤተሰቦቻቸው መከራን ያመጣ፣ ለማህበረሰቡ ትኩስ ሃይል ያለውን ወጣት ያሳጣና በእጅጉ ወደ ኋላ ለተጓተተ ዕድገት የዳረገ ነው ተብሏል፡፡ መንግስት ለወጣቶች አካባቢያዊ የኢኮኖሚአማራጮችን ለመፍጠር የሚያደርጋቸው ጥረቶች ትኩረት ተሰጥቷቸዋል፤ ለምሳሌ "የገጠር ወጣቶች የሥራ ፈጠራ ፕሮጀክት" (አዳዶ/ጌዲኦ)፣ የሴቶች የቁጠባና የዶሮ እርባታ ቡድኖች (ሶሞዶ) ወዘተ፡፡

ቢሆንም ወደ አረብ አገራት የሚሰደዱ ወጣት ሴቶችን እንደ "ጀግኖች" ለሚቆጥሩ (በኮርማርገፍያ/ሰሜን ሸዋ) ወይም ስደታቸውን እንደ *"ብልሀ ኢኮኖሚያዊ እርምጃ"* ለሚጠቅሱ ሰዎች (በኡዳ ሃሮ)፣ አካባቢያዊ የኢኮኖሚ አማራጮች፤ ሌላ ቦታ ተሰርቶ ከሚገኝ ከፍተኛ ጠቀሜታ ጋር ጨርሶ አይመጣጠንም፡፡ ሰዎች ስደት የሚያስከትለውን አደጋ ጠንቅቀው ያውቁታል፡፡ በWIDE ቃለ ምልልስ የተደረገላቸው ብዙዎቹም፣ በተጨባጭ ያጋጠሙ የአደጋ ታሪኮችን ተናግረዋል (ለምሳሌ፡- ብዝበዛ፣አካላዊና ሥነልቦናዊ ጥቃቶችና ሞት)፡፡ ሌሎች ችግሮች ተብለው የተጠቀሱት፡- ከፍተኛ ወጪ፣ የሥራ አለመኖርና መጥፋት ናቸው፡፡ ነገር ግን ስኬታማ ስደት፤ በግለሰብ፣ በቤተሰብና በማህበረሰብ ደረጃ መጥቀሙን የሚያሳዩ በቂ ማስረጃዎችም አሉ፡፡ በዚህም የተነሳ ብዙዎች፤ የስደት በጎ ጎኖች፣ ከክፉ ጎኖቹ ይልቃሉ ብለው ያስባሉ፡፡

ሙስሊም በሚበዛባቸው ጥቂት ማህበረሰቦች፣ ወደ ባህር ማዶ የተሻገሩ ስደተኞች፣ ለሃይማኖት አክራሪነት የተዳረጉበት ሁኔታ አለ (ለምሳሌ፡- በኡዳ ሃሮ፣ ስደተኞች "አዲስ የሙስሊም ባህል" አምጥተዋል፤ *"የዚህ ዓይነት አክራሪ ሃይማኖት አሰራጭተዋል"* ተብሏል)፡፡ ስደት በአብዛኛው

ከዘመናዊ ሃሳቦች ጋር የተያያዘና ከስኬት፣ ብልጽግና፣ *"ዘመናዊ የአኗኗር ዘይቤ"፣ "ሥልጡን ባህሎች"* (አልባሳት፣ ቤቶች፣ የምግብ አበሳሰል) እንዲሁም አዳዲስ የንግድ ሃሳቦች ወዘተ--- ጋር የተገናኘ ነው፡፡ አንደኛው የጥናት መኮንን ስለ አዳዶ ሲናገር፤ *"በዕድሜ የገፉ ሰዎች ሰደትን እንደ ድህነት ምልክት ሲቆጥሩት፤ ወጣቱ ትውልድ እንደ አንድ የገቢ ማመንጪያ መንገድ ይመለከተዋል"* ብሏል፡፡

በአንዳንድ ማህበረሰቦች ውስጥ "የስደት ባህል" እንደሚፈጠር የሚጠቁሙ ምልክቶች ታይተዋል - በፍጥነት የመስፋፋት ተጽዕኖ፣ "ተፎካካሪ ስደት" (በሶሞዶ) እንዲሁም ተደጋጋሚ የስደት ምልልስ ክስተት የሚሉትም ተጠቅሰዋል፡፡ በህዳር 2013፣ WIDE በጎበኛቸው ማህበረሰቦች፤ በባህርማዶ ስደት ላይ ለተጣለው እገዳ እምብዛም ድጋፍ አልነበረም፡- ወጣቶችና ቤተሰቦቻቸው፤ የሥራ አጥነት ችግርን ያባብሰዋል ሲሉ የሞገቱ ሲሆን መንግስት *"ህይወታቸውን እንዲይለውጡ"* የመከልከል መብት እንደሌለውም ተከራክረዋል፡፡ በየአካባቢው የሥራ ዕድሎችን መፍጠር ባለመቻሉም፣ በስደት ጉዞ ላይ የጣለውን *"እገዳ ማንሳት"* እንዳለበት አስረግጠው ይናገሩ ነበር[4]፡፡

በኑሮ መተዳደሪያዎች ላይ ያሳረፈው ተጽዕኖ

በአብዛኞቹ ማህበረሰቦች ከትውልድ ቀዬ መሰደድ፣ እየጨመረ ከመጣው በመሬት እጥረት ሳቢያ የሚፈጠር ውጥረት ጥቂት እፎይታን መስጠቱ በግልጽ ይታወቃል፡፡ በእርግጥም ቀደም ሲል እንደተገለጸው፤ ስደት በከፊል ለመሬት እጥረትና በአጠቃላይ፣ ለኑሮ መተዳደሪያ አማራጮች እጥረት ምላሽ ሰጥቷል፡፡ ከስደተኞች የሚላክ ገንዘብና ቁጠባ፣ ከኑሮ መተዳደርያ ጋር የተዛመዱ ኢንቨስትመንቶችንም እውን አድርጓል፡፡ እነዚህ የገቢ ምንጮች በግብርና ዘርፍ ላይ ውለዋል፡፡ ለምሳሌ ከብቶች ለመግዛት (ማረሻ በሬዎች ወይም የሚደልቡ)፣ የእርሻ መሳሪያዎች ወይም ግብአቶች እንዲሁም ተጨማሪ መሬት ለመከራየት (ለምሳሌ፡- በቱሩፌ፣ ሃረሳው፣ አዜ ዴቦአ፣ ኮርማርጌፍያ፣ ሲርባ፣ አዳ ሃሮና አዳ ዳዋታ)

የስደት ተመላሾች ወይም የስደተኞች ዘመዶች ከእርሻ ውጭ በሆነ ዘርፍ ላይም መዋዕለ ንዋያቸውን አፍስሰዋል፤ ይሄም የአካባቢውን ኢኮኖሚ በዓይነት ለማስፋትና (ማጣቀሻ፡- ስኬት)፡፡ የገጠር ከተሜነት መስፋፋት በሚለው አጭር መግለጫ ላይ እንደተገለጸው፤የገጠር-ከተማ ትስስሮችን ለማደርጀት አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡ ለምሳሌ፡- በአዜ ዴቦአና በሶሞዶ የስደት ተመላሾች፤ መዋዕለ ንዋያቸውን በከባድ መኪኖችና ሚኒባሶች ላይ አፍስሰዋል፤ በአዳዶ በባጃጆች፤ በአዜ ዴቦአ እና በግራር አቅራቢያ ባሉ ከተሞች፡- በሆቴሎች እንዲሁም የተለያዩ መጠን ባላቸው ሱቆች፣ የእህል ወፍጮዎች፣ ንግድ፣ ካፌዎች ወይም ምግብ ቤቶች፣ የውበት ሳሎኖች ወዘተ--በየቦታው ጥቂት ኢንቨስት አድርገዋል፡፡ እንዲያም ሆኖ ግን ከእርሻ በተለዩ ዘርፎች ላይ መዋዕለ ንዋያቸውን ማፍሰስ የሚፈልጉ ስኬታማ የስደት ተመላሾች፤ የገበያ በቅጡ ተደራሽ አለመሆንና የመጠን ውስንነትን የመሳሰሉ መዋቅራዊ ማነቆዎች እንደገጠማቸው ተጠቅሷል፡፡

[4] እነዚህ "የስደት ባህል" አዝማሚያዎች፣ ከWIDE3 የመጨረሻ የመስክ ሥራ በኋላ፣ በ2013 ማብቂያ ላይ በተከሰቱ ሁነቶች (በተለይ መንግስት በዓለም አቀፍ ስደት ላይ የጣለው እገዳና የሳኡዲ መንግስት በኢትዮጵያውያን ሠራተኞች ላይ የወሰደው የጅምላ ማባረር እርምጃ) ተቀይረው እንደሆነ ለማወቅ፣ ተጨማሪ የመስክ ጥናትን ይጠይቃል፡፡

በአንዳንድ ማህበረሰቦች ከተስተዋሉ አዎንታዊ ተጽዕኖዎች መካከል፡- ወንዶች በሌሉባቸው ቤተሰቦች ብዙ ዕለታዊ/ኮንትራት የግብርና ሥራ መኖር፤ ጥሪቶችን ከመሸጥ ይልቅ ዕዳን የመክፈል አቅም ማዳበር፤ እንዲሁም ስደተኞች ይዘውት የመጡት አዳዲስ ክህሎቶች (በጣም አልፎ አልፎ) እና የንግድ ሥራ ሃሳቦች ይገኙባቸዋል (ለምሳሌ፡- በሶሞዶ ስደተኞች የሚሰማሩባቸውን ሥራዎች ቀድመው የሚያጠኑ ሲሆን በዚህም መንገድ በአካባቢው ማህበረሰብ ላይ ተጽዕኖ ያሳርፋሉ ተብሏል)።

ስደተኞች ሳይሳካላቸው ሲቀር ወይም ሲሞቱ አሊያም የስደት ወጪን ለመሸፈን ጥሪት ክፉኛ ሲሟጠጥ፣ በቤተሰቦች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል። ቢሆንም በአምስት ማህበረሰቦች (አዳ ሃሮ፣ ሶሞዶ፣ አዳ ዳዋታ፣ አዘ ዴቦአ እና ጋራ ጎዳ) ስደት፤ ኢኮኖሚውን ከሚያንቀሳቅሱት ዋነኛ ሞተሮች አንዱ ነው። ውስጥ አዋቂ ምንጮች እንደገመቱት፤ ለኢኮኖሚው ከ10-25 በመቶ ድረስ አስተዋጽኦ ያደርጋል (በጋራ ጎዶ፣ ወደ ከተማ/ኢንዱስትሪ አካባቢዎች የሚደረጉ ፍልሰቶችን ጨምሮ ማለት ነው)።

<u>በሰዎች ልማት ላይ ያሳረፈው ተጽዕኖ</u>

ስኬታማ ስደተኞች ባሉባቸው ቤተሰቦች፤ ግልጽ የኑሮ ደህንነት ውጤቶች ተመዝግበዋል። በአብዛኛው የተለመዱት በተሻሉ የመኖርያ ቤቶችና የአኗኗር ደረጃዎች ላይ የሚደረጉ ኢንቨስትመንቶች ናቸው። በአመጋገብ (በአዘ ዴቦአ፤ የስደተኞች ቤተሰቦች "ወተት እንደ ውሃ ይጠጣሉ" ተብሏል) በአለባበስ እንዲሁም ለአብዛኛው የገጠር ማህበረሰብ ተደራሽ ያልሆኑ የጤና አገልግሎቶችን በክፍያ ተጠቃሚ በመሆን ረገድ ጉልህ መሻሻሎች መምጣታቸው ተጠቅሷል። ለምሳሌ፡- የሲርባ ወጣት፣ ለ10 ዓመታት በዓይነስውርነት የኖሩ አባቷ፣ በአዲስ አበባ ከፍተኛ ህክምና ማግኘት እንዲችሉ አድርጋለች። *"እሷ የህክምና፣የትራንስፖርትና የመኖርያ ወጪዎችን ሙሉ በሙሉ ባትሸፍን ኖሮ ---- ይህንን እንኳን በውኔ በህልሜም አላሰበው ነበር"* ብለዋል አባቷ።

በስደትና በትምህርት መካከል ያለው መስተጋብር ውስብስብ ነው። ቀደም ሲል እንደተገለጸው፤ መውደቅ (ወይም የመውደቅ ፍራቻ) በትምህርት-ከዚያም-በሥራ ጉዞ፣ ለስደት የሚገፋፋ የተለመደ ምክንያት ነው። በአንዳንድ ማህበረሰቦች፤ ይሄና የቀደሙ ስኬታማ ስደተኞች ተጽዕኖ፣ ትምህርታቸውን አቋርጠው የሚወጡ ወጣቶች (መቀጠል የሚችሉ ቢሆኑም እንኳን) ቁጥር እንዲጨምር ማድረጉ ተነግሯል (በWIDE,ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ግለሰቦች፤ *"በፍጥነት የመሰፋፋት ተጽዕኖ"*ን ገልጸዋል፤ ለምሳሌ፡- በሃረሳው፣ አዘዴቦአ፣ ሲርባ፣ ሶሞዶና አዳዶ)። ለትምህርት ወደ ከተማ ሄደው በዚያው የቀሩ ወጣቶችም አሉ።

በሌላ በኩል፤ ሥራና ትምህርትን አጣምረው ለማስኬድ የሚጥሩ የከተማ ፍልሰተኞች ነበሩ (ለምሳሌ በሲርባና ኮርማርገፍያ ተጠቅሰዋል)። ከአዳዶ የፈለሱ ጥቂት ወጣቶች፣ የት/ቤት ወጪያቸውን የሸፈኑት፣ ከወርቅ ቁፋሮ ሥራቸው ሲመለሱ ነው። በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ ከስደተኞች የሚላክ ገንዘብ፣ የህጻናትን ወይም የወንድም እህቶችን የት/ቤት ወጪ ለመሸፈን ይውላል። ለምሳሌ፡- በሶሞዶ አንዲት የቤተሰቡ አስተዳዳሪ፣ ስኬታማ ሴት፤ ከወንድ ልጇ የሚላከላትን ገንዘብ፣ ሴት ልጇን ለማስተማር የተጠቀመችበት ሲሆን አሁን እሷ በወረዳው የውሃ ቢሮ ውስጥ ተቀጥራለች።

<u>በማህበራዊ ልማት ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ</u>

ስደት በቤተሰቦች መዋቅር ላይ ውስብስብ ተጽዕኖዎችን ያሳድራል - በተለይ ወጣት ወንዶች ወይም ሴቶች አሊያም ሁለቱም ተጋብተው መኖር ከጀመሩ በኋላ ሲሰደዱ፡፡ ከስደት መልስ ሁለቱም የየራሳቸውን የኑሮ መተዳደርያና የየራሳቸውን አዲስ ቤተሰብ እንደሚመሰርቱ ተነግሯል፡፡ ከአካባቢያዊና ማህበረሰባዊ ልማዶች ያፈነገጡ ብዙ ቤተሰቦችም ይፈጠራሉ (ለምሳሌ፡- በርካታ በእማወራዎች የሚተዳደሩ ቤተሰቦች፤ ባል በስደት ሌላ ቦታ ሆኖ ከወላጆቻቸው ጋር የሚኖሩ ያገቡ ወጣት ሴቶች፤ እናታቸው በመሰደዷ ከአያቶቻቸው ጋር የሚኖሩ ህጻናት፤ የስደት ተሞክሮን ወይም የስደት ውሳኔን ተከትሎ የሚከሰት ፍቺ ወዘተ)፡፡

ስደት በወላጆችና በልጆች ግንኙነት ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ሁለትዮሽ ነው፡፡ በአንድ በኩል የስደት ውሳኔ፣ ውጥረት የሚፈጥርበት ሁኔታ አለ፡፡ በአስተማሪነት ደሞዝ ያጠራቀሟትን ገንዘብ አውጥተው፣ ወደ ደቡብ አፍሪካ ካልላኩኝ፣ "ሞቼ እገኛለሁ" ብሎ አባቱን ሌት ተቀን ያስቸገረው፣ የአዜ ዴቦአ ወጣት አንድ ምሣሌ ነው፡፡ በሌላ በኩል ስደት በመሬት አቅርቦት ዙሪያ ያለውን ውጥረት ያረግባል (ለምሳሌ በኮርማርገፍያ፣ የተደላደለ ኑሮ ያላቸው ቤተሰቦች፤ ወጣቶች ወደ ከተሞች ሄደው ሥራ እንዲፈልጉ ገንዘብ ይሰጧቸዋል፤ በኡዳ ሃሮ፣ አንድ ወጣት፤ ችግረኛ አባቱ መሬት እንደማይሰጡት ግልጽ ሲያደርጉለት፣ ወደ አምቦ በመፍለስ፣ በሆቴል ውስጥ ተቀጥሮ፣ ደህና ኑሮ መስርቷል)፡፡

ስደት በየአካባቢው የማህበራዊ ደህንነት ዋስትና ሥርዓቶች ላይም የሁለትዮሽ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡ ወጣቶች በሚሰደዱበት ወቅት በአቅም የደከሙ ወላጆቻቸውን በጉልበት ሥራ የሚያግዝ ይጠፋል፡፡ ነገር ግን ወጣቶች፤ ቤተሰቦቻቸውን የመደገፍ አቅም ለማግኘት፣ እንደ መጀመሪያ አማራጭ የሚወስዱትም ስደትን ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ የስደት ህይወታቸው ስኬታማ ሲሆንም ቤተሰባቸውን ይረዳሉ፡፡ ቀደም ብሎ እንደተገለጸውም፤ ለብዙዎቹ የስደት ውሳኔዎች ዋነኛ ምክንያቱ ይሄ ህልምና ራዕይ ነው፡፡

ስደት በሴቶች ላይም ከፍተኛ ተጽዕኖ አለው፡፡ የሴቶች በከፍተኛ መጠን መፍለስና መሰደድ፣ እንደ አዜ ዴቦአ (ከምባታ) እና ኮርማርጌፊያ (ሰሜን ሸዋ) ባሉ ወግ አጥባቂ ማህበረሰቦች ውስጥ ጉልህ ለውጥ መምጣቱን ያንጸባርቃል፡፡ ይበልጥ በስፋት ሲታይ፣ ስኬታማ ስደት፤ ለሴቶች ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ አቅም መጎልበት ዋነኛው ምክንያት ነው፡፡ አንዲት ስኬታማና በዕድሜ የገፉ እንስት የቤተሰብ አስተዳዳሪ ከኮርማርገፍያ እንደተናገሩት፤ *"ሴቶች በኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውሳኔ ሰጪ የሚሆኑበት፣ ከተለመደው የተለየ ዓይነት ቤተሰብ ይመሰረታል-----አንድ ሰው የበለጠ ገንዘብ ባለው ቁጥር የመወሰን አቅሙም ይጨምራል"* ሆኖም በሶሞዶ እንደታየው፣ በዝባዥ የሚሆንበት አጋጣሚም ይኖራል፡፡ ቤተሰቦቻቸው ወይም ባሎቻቸው ባህር ማዶ የሚልኳቸው ወጣት ሴቶች፣ ብዙ ጊዜ ከስደት መልስ ለራሳቸው እዚህ ግባ የሚባል ጥሪት አይተርፋቸውም፡፡ በብዙ የከተማ ፍልሰትም እንዲሁ ነው(ከዚህ በታች ይመልከቱ)፡፡

<u>የገጠር ልማትን ለማጠናከር የሰዎች ዝውውርን ማነልበት</u>

ከአካባቢያዊ ሁኔታ ጋር የተጣጣሙ የተሻሉ አማራጮችና ማነቆዎች መኖራቸው የማይካድ ቢሆንም፣ በኢትዮጵያ የገጠር ማህበረሰቦች የታየው ከፍተኛ የሰዎች ዝውውር (ስደትና ፍልሰት) የዕድገታቸው ውጤት መሆኑን የWIDE ጥናት አረጋግጧል፡፡ ይሄ ዕድገት በውስጣቸው የፈጠረባቸውን የበለጠ የመሻት ህልምና ራዕያቸውን ለማሳካትም ቀዬአቸውን ጥለው ይፈልሳሉ፡፡ ስኬታማ የሆነ ስደት ጠቃሚ ሊሆን እንደሚችል ማስረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በየአካባቢው ባለው የተፈጥሮ ሃብትና የሥራ ገበያ እጥረት ሳቢያ የሚፈጠሩ ውጥረቶችን አርግቧል፡፡ ወጣቱ ትውልድ፤ ከስደት አገር ሰርቶ በሚልከው ገንዘብ፣ ለማህበራዊ ደህንነት ዋስትናና ለቤተሰቡ የኑሮ ደህንነት መሻሻል አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ስደተኞች የሚልኩትና የሚቆጥቡት ገንዘብ፤ ለቀዬአቸው ኢንቨስትመንት ከመዋሉም ባሻገር የየአካባቢውን ኢኮኖሚያዊ አማራጮች አሳድጓል፡፡ በበርካታ ማህበረሰቦችም፤ ከሥራ ጋር የተዛመደ ከፍተኛ የሴቶች ፍልሰት፣ በጾታ አመለካከትና ግምት ላይ አዎንታዊ ለውጦችን አምጥቷል፡፡

የገጠር ኢትዮጵያ ዕድገት በቀጠለ ቁጥር፣ ከሥራ ጋር የተዛመዱ የተለያዩ ፍልሰቶችምመጨመራቸው ይቀጥላል፡፡ ይህም የገጠር ኢኮኖሚያዊ አማራጮችን ለማስፋፋትና የተሻለ ለማድረግ እየተከናወነ ከሚገኘው መንግስት-መር ልማት ጎን ለጎን፣ ለገጠር አካባቢያዊ ዕድገት አንድ ግብአት ሊሆን ይችላል፡፡ ለዚህም፤ መንግስት ለሚከተሉት ነጥቦች ትኩረት መስጠት ይኖርበታል፡-

- ስደት የሚያስከትላቸውን አደጋዎችና ጥቅሞች ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ የስደት ፖሊሲን ማሻሻል፤ እንዲሁም ባለድርሻ አካላት የመጀመርያውን እንዲከላከሉና ሁለተኛውን እንዲያጎለብቱ አቅጣጫ መስጠት፡፡
- የስደት ፖሊሲና አስተዳደርን ለማጠናከር ይቻል ዘንድ፣ በኢትዮጵያ ያለውን ፍልሰትና ውስብስብነቱን እንዲሁም በጊዜ ሂደት ያሳየውን ዕድገት የመተንተን ተቋማዊ አቅምን መፍጠር፡፡

ከስደት የሚላክ ገንዘብ ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ በማሳደግ፣ ከገጠር ፍልሰት የሚገኙ ጥቅሞችን አንጠፍጥፎ ሥራ ላይ ለማዋል አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የተለያዩ እርምጃዎችን ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ይቻላል፡-

- ወጣቶች ለስደት የሚነሳሱት በከፊል ቤተሰባቸውን ለመርዳት ባላቸው የሃላፊነት ስሜት ሲሆን በብዙ ሁኔታዎችም የትውልድ አካባቢያቸውን የማህበራዊ ደህንነት ዋስትና አጠናክረዋል፡፡ ይሄ እንቅስቃሴ፣ መንግስት በገጠር አካባቢዎች የባንክ አገልግሎትን ለማስፋፋት ባስቀመጠው ግብ መሰረት፤ ስደተኞች በአገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ኪስ የማይነዳ ምቹ የባንክ አገልግሎት እንዲሁም የገንዘብ ዝውውር አማራጮች እንዲያገኙ በማድረግ፣ የበለጠ ሊጎለብት ይችላል፡፡
- ስደተኞችና ቤተሰቦቻቸው ገንዘባቸውን በቀዳሚነት የሚያውሉት፣ የኑሮ ደህንነትና የሰው ዕድገትን በሚያሻሽሉ ጉዳዮች ላይ ነው፡፡ መንግስት ይህ በጎ አዝማሚያ የሚጠናከርበትን መንገድ ሊያጤን ይችላል፤ ለምሳሌ፡- ከሚልኩት ወይም ከሚቆጥቡት ገንዘብ ውስጥ የተወሰነውን ለጤና ኢንሹራንስና ሌሎች የኢንሹራንስ ፕሮግራሞች ወይም እንደ ብድር መያዣነት እንዲያውሉት ማበረታታት፡፡

ስደተኞች የሚልኩትንና የሚቆጥቡትን ገንዘብ እንዲያሳድጉ የሚያበረታቱ እርምጃዎች፤ (ለምሳሌ፡- ከላይ እንደተገለጸው፣ የተሻለ የባንክ አገልግሎትና የገንዘብ ዝውውር አማራጮች፣ ለቁጠባ ሂሳብ ከፍተኛ ወለድ መክፈል) ብዙዎች ገንዘባቸውን በኑሮ ደህንነት ላይ ከማዋል ጎን ለጎን፣ ጥቅም በሚያስገኙ ትርፋማ ኢንቨስትመንቶች ላይ ለማዋል ትኩረት እንዲሰጡ ያደርጋቸዋል፡፡ የወረዳ ሃላፊዎች፤ በተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች፣ ጥቅም በሚያስገኙ ትርፋማ ኢንቨስትመንቶች ዙሪያ ምክር ሊለግሱ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፡- ገበያ ባላቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች ዙርያ ለሥራ ፈጣሪዎች ምክር የሚሰጥ፣ ከብድር አገልግሎትና ሥልጠና ጋር የሚያስተሳስር፣መሥሪያ ቦታ [መሬት] እንዲያገኙ የሚያግዝ የምክር አገልግሎት ማመቻቸት (ማጣቀሻ፡- የገጠር ከተሜነት መስፋፋት)፡፡

- በጉራጌ ወደ ከተማ የፈለሱ ተወላጆች፣ የትውልድ አካባቢያቸውን ልማት በገንዘብ የሚደግፉበትን ባህል በመከተል፣ መንግስት፤ የባህርማዶ ስደተኞች ወይም ተመላሾች፣ የአካባቢያቸውን የመሰረተ ልማት ግንባታዎች የሚደግፉበትን መንገዶች ሊቀይስ ይችላል፡፡ በዚህም ሂደት፣ ስደተኞች በትውልድ ቀዬአቸው መዋዕለ ንዋያቸውን ለማፍሰስ ሲፈልጉ የሚገጥማቸውን መዋቅራዊ ማነቆዎች ያስወግዳል፡፡ በእጅጉ የሚፈለገውን ለመሰረተ ልማት ግንባታ የሚውል ገንዘብ ለማሰባሰብ፣ ከዳያስፖራ ቦንድ ጋር ተመሳሳይነት ያለውን "የአካባቢ ልማት ቦንድ" መፈተሽ ይቻላል፡፡ በአሰራሩ ሃቀኝነትና ውጤታማነት ላይ መተማመንና እርግጠኝነት መፍጠር ግን ይጠይቃል፡፡

ስደት እንደ ሌላው ኢኮኖሚያዊ አማራጭ፣ የሴቶች አቅምን በማጎልበትና ለራሳቸውም ሆነ ለቤተሰቦቻቸው አስተማማኝ ውጤት በመፍጠር ረገድ ሙሉ በሙሉ አስተዋጽኦ ማድረጉን ማረጋገጥ፣ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ይሄ፤ መንግስት የጾታ እኩልነትን ለማስፋፋት በሚያስተላልፈው መልዕክት ትኩረት ሊሰጠው ይችላል (ማጣቀሻ፡- ሴቶች)፡፡ መንግስት፤ ወጣት ሴቶች በግላቸው የባንክ አገልግሎት ተጠቃሚ የሚሆኑባቸውን መንገዶች ሊያመቻች ይችላል፤ በዚህም ገንዘባቸውን ያለ ቤተሰብ ጣልቃ-ገብነት፣ በስማቸው በተከፈተ የባንክ ሂሳብ ያስገባሉ፡፡ ሌሎች ከግንዛቤ ውስጥ መግባት የሚሹ የማትጊያ እርምጃዎችም ከግንዛቤ ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ፤ ለምሳሌ፡- የገንዘብ ቁጠባቸውን ለማበረታታት ወለዱ አነስተኛ የሆነ ብድር ማመቻቸት፣ ከስደት መልስ የራሳቸውን የንግድ ሥራ ለማቋቋም ያነሳሳቸዋል፡፡

በመዳረሻ አገራት ያሉ የሥራ ዕድሎችን በተመለከተ የተሻለ መረጃና ዝግጅት፣ ይበልጥ የተሳለጠና ለስደተኞች ምቹ የሆነ የአስተዳደር ሥርዓትና ተገቢነት ያላቸው የህግ ማዕቀፎችን ማጠናከር ወይም ማስፈጸም፤ የስደት ውጤትን የበለጠ ያጎለብተዋል፡፡ ቀጣዩ ክፍል፤ ይህንን ርዕሰ ጉዳይ፣ ከWIDE ማስረጃዎች፡- 1) የከተማና ኢንዱስትሪ ፍልሰት፤ እና 2) የባህር ማዶ ስደት አንጻር ይመለከተዋል፡፡

የከተማ/ኢንዱስትሪ ተሞክሮዎች

የWIDE መረጃ እንደሚጠቁመው፤ የከተማ/ኢንዱስትሪ ሥራ ፍለጋ ወይም ግዙፍ የግብርና ፕሮጀክቶች ውስጥ (የሆቴል መስተንግዶል አገልግሎት፣ ኮብልስቶን ማንጠፍ፣ የግንባታ ሥራዎች፣ የተለያዩ ዓይነቶችና መጠኖች ያሏቸው ፋብሪካዎች፣ የወርቅ ማምረቻ፣ የአበባ እርሻዎች፣ መተማና ሁመራ የሰሊጥ እርሻዎች፣ የሸንኮራ አገዳ እርሻዎች) ለመቀጠር የሚፈልሱ ሰዎች፤ ብዙ ጊዜ ካሉበት አደገኛ ሁኔታ ጋር የተገናኙ የተለያዩ ችግሮችን ይጋፈጣሉ፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ሥራ ፍለጋ ፈተና ነው፤

በተለይ ብዙዎች እቅድ እና ማረፊያ ሣያመቻቹ በሚጓዙባቸው የከተማ አካባቢዎች ለችግር ይጋለጣሉ፡፡ ሌላው ፈተና የኑሮ ውድነት ነው፤ ምክንያቱም ፍልሰተኞች ከቤተሰባቸው መሶብ ቆርሰው (ተካፍለው) የሚበሉበት ዕድል አይኖርምና፡፡

ወደ ከተማ አካባቢዎች የሚፈልሱ ወንዶች፣ ከሴቶች የተሻለ የሚዋጣላቸው ይመስላሉ፡፡ ሴቶች ብዙ ጊዜ ዝቅተኛ ክፍያን ጨምሮ ለተለያዩ ብዝበዛዎችና ለጥቃት ከሚያጋልጡ ሥራዎች (ለምሳሌ፡- የቤት ሰራተኝነት፣ የቡና ቤት፣ ካፌ ወይም ምግብ ቤት አስተናጋጅነት ወይም ሴተኛ አዳሪነት) ጋር ይጋፈጣሉ፡፡ በተመሳሳይ፤ በብዙ ማህበረሰቦች፤ የከተማ ፍልሰት ለሴቶች ጠቃሚ አይደለም ተብሎ ይታሰባል፡፡ አንዲት የኦዳ ሃሮ ወጣት ሴት እንዳብራራችው፤ *"የተሻለ ህይወት ፍለጋ ወደ ከተሞች የፈለሱ አብዛኞቹ ልጃገረዶች ሰኬታማ አይደሉም (ወደ አካባቢያቸው ሲመለሱ)አንዳንዴ ልጅ ስለሚወልዱ በእድጉ ተጎጂ ይሆናሉ፤ ምክንያቱም በቤተሰብም ሆነ በማህበረሰብ ደረጃ ቀድሞ የነበራቸውን ክብር ያጣሉ፡፡ የቤት ሠራተኞች በአገሪቱ ውስጥ እምብዛም አይከበሩም፤ ገንዘብ ለቤተሰብ አይልኩም፤ ከቀዬአቸው ሲወጡ የለበሷትን ልብስ እንኳን አይቀይሩም"፡፡*

በኢንዱስትሪ የሥራ ዘርፎች ውስጥ ከተቀጠሩት መካከል ሴቶችም ይገኙበታል - ምናልባት እንደ ተመራጭ ሥራ ተቆጥሮ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን የተሻለ ደሞዝ የሚከፈላቸው አይመስሉም፡፡ ለምሳሌ በፊንጫ ወይም አዲስ አበባ ፋብሪካዎች ውስጥ የሚሰሩ ጥቂት ወጣት ሴቶች ባሉበት አዳ ሃሮ፤ እንዲሁም በአሰላ ፋብሪካዎች የሚሰሩ አንዳንድ ሴቶች በሚገኙበት አዳ ዳዋታ፤ ይሄ ከውጭ አገር ስደት በእድጉ ያነሰ ጥቅም እንዳለው ተደርጎ ነው የሚቆጠረው፡፡ መሠረታዊ የሥራ ሁኔታም እንደ ችግር የሚነሱበት አጋጣሚዎች አሉ (ለምሳሌ፡- ከሲርባ አንድ ወጣት ሴት በአበባ እርሻ እና ከገብሌን አንድ ወጣት ወንድ፣ በመድሃኒት ፋብሪካ ውስጥ ከሰሩ በኋላ የከፋ ራስ ምታት ይዟቸዋል)፡፡

በአጠቃላይ የከተማ ፍልሰተኞች በትውልድ ቀዬአቸው ቤተሰባቸውን መደገፍ አልቻሉም ተብሏል፡፡ ለምሳሌ፡- በጋራ ጎዶ (ወላይታ) አንድ ችግረኛ ገበሬ፤ ወደ ሃዋሳ የፈለሰ ወንድ ልጁ ገንዘብ እንደማይልክለት ጠቁሞ፤ ለዚህም ምክንያቱ ቤተሰቡን ከመደገፉ በፊት የግል ህይወቱን በገንዘብ መደገፍ ስላለበት ነው ብሏል፡፡ በኮርማርገፍያ ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ግለሰቦችም፤ "በኢትዮጵያ ውስጥ አብዛኞቹ ፍልሰተኞች ቤተሰባቸውን ለመደገፍ የሚያስችል ብዙ ገንዘብ *አያገኙም*፤ "ያሉ ሲሆን "በአረብ አገራት የሚገኙ ብዙዎቹ ሴቶች ግን ሥራ በጀመሩ በአራት ወራት ጊዜ ውስጥ ገንዘብ ይልካሉ፤ ከዚያም ለወላጆቻቸው ባለ ቆርቆሮ ጣራ መኖሪያ ቤት ይሰራሉ" በማለት አብራርተዋል፡፡

<u>የከተማ/ኢንዱስትሪ ተሞክሮዎችን ማሻሻል</u>

በከተማ/ኢንዱስትሪ አካባቢዎች ሥራ የሚፈልጉ ሰዎችን መርዳት፣ የእነሱንና ቤተሰቦቻቸውን ውጤት ሊያሻሽል የሚችል ሲሆን የመንግስት የኢንዱስትሪ ልማት ግቦችንም ያጠናክራል፡፡ ይህ ፈርጀ ብዙ እርምጃዎችን ሊያካትት ይችላል፤ ለምሳሌ፡-

- ፍልሰተኞች የመታወቂያ ወረቀት የሚያገኙበትን መንገድ ምቹና ቀላል ማድረግ፤ የማህበራዊ አገልግሎቶች ተደራሽነት እንዳላቸው ለማረጋገጥ፤

- በአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት ለስደተኞች የክህሎትና የሥራ ፈጠራ ሥልጠና እና ብድር ማመቻቸት፤
- ፍልሰተኞች፤ ክፍት የሥራ ዕድሎችን፣ ተመጣጣኝ ማደርያ፣ የጤና አገልግሎቶች፣ የክህሎት ሥልጠና እና የብድር ዕድሎችን በተመለከተ መረጃ በቀላሉ እንዲያገኙ ማድረግ--(ለምሳሌ፡- ውክልና በተሰጠው ሃላፊነት የሚሰማው ቀበሌ/መስተዳድር ቢሮ አማካኝነት፤ በተለይ ፍልሰት በሚበዙባቸው አካባቢዎች ወኪል በማቆም እገዛ መስጠት)፡፡

ሦስት ጉዳዮች ልዩ ትኩረት ይሻሉ

- መንግስት በኢንዱስትሪ ወይም ግዙፍ የግብርና ማቀናበሪያ ፋብሪካዎች ውስጥ የጉልበት ብዝበዛን ለመቀነስ፣ መሠረታዊ የሥራ ሁኔታን የተመለከቱ ጉዳዮችን ለመፈተሽ የቅድሚያ ትኩረት ሊሰጠው ይችላል፡፡ የሥራ ህጎችና ደንቦችን ለማስፈጸም፣ የአሰሪዎች ሃላፊነቶች በግልጽ ተዘርዝረው ሊቀመጡ፣ ሊታወቁና ክትትል ሊደረግባቸው ይገባል (ለምሳሌ፡- የደህንነት መስፈርቶች በሥራ ላይ፣ ደሞዝ፣ ትራንስፖርት፣ ጥሩ መኖርያ ቤት)፡፡

የከተማ/ኢንዱስትሪ አካባቢዎች ፍልሰት፣ ለሴቶች ከአደጋ ነጻና አስተማማኝ ሊደረግ ይገባል- ብዙዎቹ፤ በኢትዮጵያ ሌሎች ቦታዎች የመሥራት አማራጭ ዋጋ ያለው መስሎ ከተሰማቸው፣ ከአገር ውጭ መጓዝን ላይመርጡ ይችላሉ፡፡ ወቅታዊውን በሴት ፍልሰተኞች ላይ ጎልቶ የሚታይ ብዝበዛ ለማስቆም፣ የቤት ሠራተኝነትና የእንግዳ አቀባበል አገልግሎት ቅጥር፣ መሠረታዊ የሥራ ሁኔታ ላይ ልዩ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ፍልሰተኛ ሴቶችን ከጉዳት መከላከያ ተጨማሪ መንገዶችም ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ (ለምሳሌ፡- የከተማ መጠለያዎች ወዘተ) (ማጣቀሻ፡- ሴቶች)

ብዙ ሰዎች ለአካባቢያቸው ቀረብ ባሉ ቦታዎች ሥራ ማግኘትን ሊመርጡ ይችላሉ (ማጣቀሻ፡- የገጠር ከተሜነት መስፋፋት)፡፡ ይሄንን ይበልጥ ማራኪና ሳቢ ማድረግ፣ የሰዎች ክምችት ወደ ትላልቅ ከተሞች እንዳይጎርፍ ለመከላከልም ያግዛል፡፡ ይሄ በአነስተኛ ከተሞችና የአካባቢ ፋብሪካዎች ለሚገኙ ፍልሰተኞች፣ የኑሮና የሥራ ሁኔታዎች ትኩረት መስጠትን ይጠይቃል፣ የወረዳ/መስተዳድር የሠራተኛ ጉዳይ ቢሮዎች የአመራር አቅምን ማጠናከር፤ እንዲሁም የአካባቢና አቅራቢያ የሥራ መረጃዎች ማደራጃ ሥርዓት መቅረጽና በገጠር ማህበረሰቦች ውስጥ በስፋት ማሰራጨት፡፡

<u>የባህር ማዶ ጉዞ ተሞክሮዎች</u>

የWIDE መረጃ በአብዛኛው የተሰበሰበው፣ መንግስት በጥቅምት 2013፣ በህጋዊ የአረብ አገራት የሥራ ጉዞ ላይ፣ ጊዜያዊ እገዳ ለመጣል ከመወሰኑ በፊት ነው፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰውም፤ የባህር ማዶ ስደት በስፋት የሚታዩባቸው ማህበረሰቦች ነበሩ፡፡ በዚህም የተነሳ አደጋዎቹ በቅጡ የሚታወቁ ይመስላሉ፡፡ ሰዎች የመንግስትን የግንዛቤ ማስጨበጫ መልዕክቶች አድምጠዋል፤ ስኬታማ ያልሆኑ የስደት ታሪኮችን ከአካባቢያቸው ወይም ከሚዲያው አግኝተዋል፤ ወይም በግላቸው ስኬታማ ያልሆኑ ስደተኞችን ያውቃሉ፤ አሊያም ራሳቸው ስኬታማ አልነበሩም፡፡ ነገር ግን ይሄ ሁሉ እያንዳንዱን ሰው ከመሰደድ አልገታውም፡፡ ለምሳሌ፡- የሲርባ የስደት ተመላሽ፤ ከዱባይ የ3 ዓመት ቆይታ በኋላ ወደ አገሯ ብትመለስም፤ ዳግም ወደ ባህሬንለመጓዝ የቪዛ ሂደት ላይ ነበረች፡፡ ብዙ ሴቶች *"በቀጣሪዎቻቸው ጥቃት ይፈጸምባቸዋል"* ወይም *"ድንገት ይሰወራሉ"* ያለችው የስደት ተመላሽዋ፤

"ግን ደግሞ ብዙ ወጣት ሴቶች ዳንስ ያለ ገንዘብ የሚያገኙበት ማለፊያ ዕድል ነው" ብላለች፡፡ እናም *"እዚህ ሥራ ፈቶ ከመቀመጥ ተሰድዶ መስራት ይሻላል"* ባይ ናት፡፡ ከአገር ውጭ የመጓዝ ስኬት፤ *"የራሰን ህይወት ለመለወጥ"* እንደ ተመራጭ መንገድ ይታሰባል፡፡ ለምሳሌ የኮርማርገፍያ የልማት ቡድን መሪ የሆነች አንዲት ሴት፤ *"በቀን ሺ ጊዜ እጅን በሳሙና መታጠብ እያለ፣ እቦት መጠፍጠፍ ምን አመጣው?"* ስትል ጠይቃለች፡፡

በሌላ በኩል፤ እጩ ስደተኞች፤ ህጋዊውን የስደት ጉዞ በተመለከተ ግልጽና የተሟላ መረጃ የላቸውም፤ ይሄም ደላሎች ጣልቃ ገብተው የመረጃ ክፍተቱን እንዲሞሉ ይፈቅድላቸዋል፡፡ ደላሎች፤ ስደተኞችን በህገወጥ ጉዞዎች ከአገር እንደሚያስወጡም ተጠቅሷል፡፡ሆኖም የስደተኞች ከአገር የመውጣት ውሳኔን በተመለከተ፣ ደላሎች ቢያንስ በሚዲያና በህዝብ ውይይት ላይ ተደጋግሞ የተነገረላቸውን ያህል ትልቅ ቦታ ያላቸው አይመስሉም፡፡ በአጠቃላይ በአካባቢያዊ ውይይቶች ላይ ህገወጥ ዝውውር የሚለው ሃሳብ አልተነሳም፡፡ ለምሳሌ አብዛኛው ስደት ህገወጥ በነበረበት ሃረሳው፤ ህብረተሰቡ ስለ "ስደት" እንጂ ስለ "ህገ ወጥ ዝውውር" አያወራም፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ይሄን ቃል የሚጠቀሙበት የመንግስት ባለሥልጣናት ወይም ሚዲያው ነው፡፡ በሶሞዶና በኡዳ ሃሮ ነዋሪዎች፤ ለህጋዊ ስደት "ጎዳንሳ ሴራ (ቀቤሳ)" በሚል የኦሮምኛ አገላለጽ ይጠቀማሉ፡፡ (ቀጥተኛ ትርጉሙ- "በህጋዊ መንገዶች ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ" የሚል ነው) በአንጻሩ፣ ፈቃድ በሌላቸው ደላሎች አማካኝነት የሚደረግ ስደት "ጎዳንሳ ሴራ ኣላ" በሚል ይገለጻል፡፡ (ከህጋዊ መንገዶች ውጭ መንቀሳቀስ)፡፡ ሆኖም ግን የኋለኛውም እንኳን፣ በህጋዊው መስመር ያልተጓዙ ነገር ግን መሰደድን የመረጡ ሰዎችን የሚመለከት ነው፡፡

በጉዞ ወቅት ከሚያጋጥሙ ከፍተኛ አደጋዎች በተጨማሪ፣ ሰነድ አልባ ዓለም አቀፍ ስደተኞች፣ በህገ ወጥነታቸው ሳቢያ በህግ ተይዘው ወደ አገራቸው ለመመለስ የተጋለጡ ናቸው፡፡ ይሄ ከተባለ ዘንዳ፤ በአንዳንድ ሁኔታዎች፣ ህጋዊ ስደተኞችም፣ አግባብ ላልሆነ አያያዝ ተጋላጭ ይመስላሉ፡፡ እናም በርካታ ቁጥር ያላቸው የስደት ተመላሾች፤ ለተመደቡበት ሥራ ዝግጁ ሳይሆኑ በመቅረታቸውና ችግሮች በሚያጋጥሙበት ወቅት የሚተማመኑበት የደህንነት ዋስትና ባለመኖሩ የተነሳ፣የሚሰማቸውን የአቅመቢስነት ስሜት ገልጸዋል፡፡ አንዲት የኡዳ ሃሮ ወጣት፣ ሁኔታውን ከፊሊፒንሶች ጋር ታነጻጽረዋለች፡- *"ፊሊፒንሶች ከብሔራዊ ኤጀንሲያቸው ምክርና ሥልጠና ሰለሚያገኙ፣ የቅጥር ኮንትራታቸው በጣም አሰተማማኝ ነው"* ሌላዋ ከኡዳ ዳዋታ ደግሞ፤ "ወኪሎቹ ትልቅ ችግር አለባቸው" ስትል ትወቅሳለች፡፡ ሴቶቹ አንድ ችግር ሲጠቁሙ፤ "ዝም እንዲሉ" ይነግሯቸዋል፡፡ እነዚህ ሴቶች በራሳቸው እርምጃ ለመውሰድ ሲሞክሩ ደግሞ *"ቦታቸውን ለመቀየር ሰለሚምክሩ የተለየ ችግር ሊገጥማቸው ይችላል"* (ሠራተኛዋን ከቀጣሪዋ ጋር የማስተሳሰር - የከፋላ ሥርዓትን ይጠቁማል)፡፡

በአጠቃላይ የስደት አዝማሚያዎች፣ ለወጣት ወንዶችና ወጣት ሴቶች በእጅጉ የተለያዩ ናቸው፡፡ ለወጣት ሴቶች፣ ሁለቱም በነበሩበት ማህበረሰቦች ውስጥ፣ ከከተማ ፍልሰት ይልቅ የባህርማዶ ስደት፣ እንደ ተሻለ አማራጭ ይታሰባል፡፡ ለወጣት ወንዶች፣ በአጠቃላይ ወደ ባህርማዶ የሚደረግ ስደት፣ በህገወጥ መንገድ የሚከናወን ነበር፡፡ ስለዚህም በእጅጉ ለአደጋ የተጋለጠ ነው፡፡ ለዚህም ምክንያቱ የአረብ አገራት ህጋዊ ስደት፣ አብዛኞቹ ዕድሎች ለቤት ሰራተኞች በመሆኑ ነው፡፡ ወደ ደቡብ አፍሪካ የሚደረግ ስደት በሙሉ ህገወጥ ነበር፡፡

ከስኬታማ የባህር ማዶ ስደት የሚገኘው ገቢ፣ ብዙ ጊዜ ከሌሎች ዓይነት ስደቶች በእጅጉ የላቀ ነው፡፡ ተስፋና ጉጉቱም ታዲያ እንደዚያው የላቀ ነው፡፡ ሆኖም የስደት ወጪን መሸፈን ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ እጩ ስደተኞችና ቤተሰቦቻቸው፤ ቤተሰቡን በእጅጉ የሚያደኸዩና ለችግር የሚያጋልጡ ትልሞችን ይጠቀማሉ፡፡ የጥሪት ክፍተቱ ከስደት በሚላክ ገንዘብ እስኪሟላ ድረስ መከራው ይቀጥላል - ይሄም ስደቱ ምናልባት በስኬት ከተጠናቀቀ ነው፡፡ በሶሞዶ፣ ቤተሰቦች፤ ቢያንስ አንድ ልጅ ባህር ማዶ ለመላክ እህል ወይም ከብቶች ይሸጣሉ አሊያም ገንዘብ ይበደራሉ፡፡ በአዜ ዴቦአ "ሌሎች ወላጆች እንደሚያደርጉት" ሁሉ፤ አንድ ቤተሰብ የወንድ ልጃቸውን የደቡብ አፍሪካ ጉዞ ለመሸፈን፣ ሁለት በሬዎቻቸውንና በመሬታቸው ላይ ያሉትን ባህርዛፎች በሙሉ ሸጠዋል፡፡

በብዙ ሁኔታዎች፣ ድህነት የበረታባቸው ሰዎች (ከስኬታማ ስደት የበለጠ ተጠቃሚዎቹ) መጀመሪያ ላይ ይበልጥ ለአደጋ በሚያጋልጠው፣ ነገር ግን ክፍያው አነስተኛ በሚባለው መንገድ ነው የሚሰደዱት። ምኞታቸው ወደፊት ወደተሻሉ አገራት ለመጓዝ የሚያስችል ጥሪት በመቋጠር፤ ምናልባትም በህጋዊው መንገድ ተሰደው የተሻለ ክፍያ ለማግኘት ነው፡፡ ለምሳሌ ይሄ፣ በሶሞዶ የተለመደ ነው፡፡ ወጣት ሴቶች መጀመርያ በህገወጥ መንገድ ወደ ሱዳን ይሰደዳሉ፤ ጥሪት ከቋጠሩ በኋላ ወደ አረብ አገራት ይሻገራሉ፡፡

<u>የባህርማዶ የሥራ ቅጥርን ማሻሻል</u>

አዲሱ የስደተኞች ህገ ወጥ ዝውውርና ድንበር ማሻገር መከላከያና መቆጣጠርያ አዋጅ እንዲሁም የባህር ማዶ የሥራ ቅጥር የተሻሻለው አዋጅ፣ በሃምሌና ታህሳስ 2015፣ እንደ ቅደም ተከተላቸው ጸድቀዋል፡፡ ይሄንን ለማጎልበትና የባህር ማዶ የሥራ ቅጥርን ለብዙ ሰዎች ተመራጭ ለማድረግ፣ መንግስት ህጋዊ የስደተኞች ጉዞ የበለጠ ተፈላጊ የሚሆንበትን መንገድ ማጤን ይኖርበታል፡፡

ምንም እንኳን ለስደት የተዘጋጁ ወጣቶችና ወላጆቻቸው፣ አደጋዎቹን ጠንቅቀው የሚያውቁ ቢሆንም ህገወጥ ስደትን ለመቆጣጠር የሚደረጉ ጥረቶች ያስፈልጋሉ፡፡ የሚከተሉት እርምጃዎች እኒህን ጥረቶች የሚያበለጽጓቸው ሲሆን ከሁለት ዓመት በላይ፣ ባህር ማዶ ሥራ ፍለጋ ለመጓዝ ለወሰኑ ሰዎች የነበረው ብቸኛው አማራጭ ህገ ወጥ ስደት ከመሆኑ አንጻር ተፈላጊነታቸው አጠያያቂ አይደለም፡-

- የባህር ማዶ የሥራ ቅጥርን የተመለከቱ ጉዳዮችን በመምራትም ሆነ መረጃ በመስጠት ለሚሳተፉ ወገኖች ሁሉ ግልጽ የአሰራር መመሪያ መቅረጽ፡፡ በተሻሻለው የህግና ቁጥጥር ማዕቀፍ መሰረት፣ በሁሉም ደረጃዎች ላይ ያሉ የመንግስት መዋቅሮች፣ ግዳጅ የሌለበት፣ አስተማማኝና ህጋዊ ጉዞን የሚደግፉበትን መንገድ ጨምሮ ግልጽነት ለመስጠት ከላይ የተጠቀሰው የስደት ፖሊሲ፣ ተገቢ ማዕቀፍ ይሆናል፡፡
- ባህርማዶ በህጋዊ መንገድ ሥራ ለመቀጠር ያለውን ሂደትም ሆነ የህገ ወጥ ስደት አደጋዎችን አስመልክቶ በቂ መረጃ መኖሩን ማረጋገጥ፡፡ በዚህም ባህርማዶ ተሻግረው ለመስራት የሚሹ ወገኖች፣ ህልማቸውን ዕውን የሚያደርጉበት ህጋዊ አማራጭ መኖሩን ያውቃሉ፣ አሰራሩንና ጥቅሞቹን ይገነዘባሉ እንዲሁም ለአደጋ የሚያጋልጡና ሁልጊዜ ቀና ያልሆኑ ደላሎች ላይ መውደቅ እንደሌለባቸው ይረዳሉ፡፡ እኒህንና ሌሎች ተያያዥ መረጃዎችን (በተለይ በመዳረሻ አገሮች ላይ ያተኮሩ፣ የሥራ ዕድሎችና ተያያዥ መስፈርቶች፣ የድጋፍ ፕሮግራሞችና

ሥልጠናዎች-[በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ወይም በሌሎች መንገዶች]፣ የሥራ ውል ዓይነቶች፣ የኤጀንሲዎችና ቀጣሪዎች ሃላፊነቶች እንዲሁም የሰራተኞች መብቶች ወዘተ-) ከመንግስት ቢሮዎች ጎን ለጎን ማህበራዊ ድረገጾችን የመሳሰሉ ሚዲያዎችን በመጠቀም መስጠት ይቻላል፡፡

- ህጋዊ የስደት ጉዞን በቀላሉ ተደራሽ፣ አነስተኛ ክፍያ ጊዜ የማይፈጅ ማድረግ። በተለይ ህጋዊ አማራጭ ከእነአካቴው ቆሞ ከነበረበት ከሁለት ዓመት በኋላ "ህገ ወጥ ስደት ይበልጥ ፈጣንና ክፍያውም አነስተኛ ነው" የሚለውን በስፋት የተሰራጨ አመለካከት ለማክሸፍ ያግዛል፡፡ ለዚህም፣ መንግስት፣ የስደት አስተዳደር የበለጠ ከማዕከላዊነት የሚወጣበትን መንገድ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ለምሳሌ፡- ለስደት ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች፣ የሚመለከተው የፌደራል መ/ቤት ቅርንጫፍ ቢሮዎችን በብዛት መክፈት፤ የወረዳ አስተዳደሮች ሃላፊነትን ግልጽ ማድረግ (ለምሳሌ፡- አስፈላጊ ሰነዶች መሟላታቸውን ማረጋገጥ ሊሆን ይችላል) እንዲሁም እነዚህ ቢሮዎች፣ በበቂ ሰራተኞች የተደራጁ መሆናቸውን ማረጋገጥ፡፡
- ስደተኞች ከጉዞ በፊት በቂ ዝግጅት ማድረጋቸውን ማረጋገጥ፡፡ ይሄም ለተወሰኑ ሥራዎች ከሚያስፈልጉ የክህሎት ሥልጠናዎች ጎን ለጎን፣ በመዳረሻቸው አገር የስደተኞች መብትንና የሚገኙ ድጋፎችን የተመለከቱ ዝርዝር መረጃዎች እንዲሁም ገቢያቸውን ለማስተዳደር የሚረዳቸው ከገንዘብ ጋር የተያያዘ ሥልጠናን ሊያካትት ይችላል፡፡
- ስደተኞች በመዳረሻ አገራት የተሻለ ጥበቃና ድጋፍ ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፡፡ የመጀመሪያው እርምጃ፣ የተሻሻለውን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልገውን የሰው ሃይል መመደብ ነው፤ ለምሳሌ፡- በመዳረሻ አገራት በሚገኙ የኢትዮጵያ ኤምባሲዎች ውስጥ የሥራ አታሼዎች መመደብ፡፡ ኤምባሲዎች፤ በስደተኞች መካከል ማህበራዊ ትስስር እንዲፈጠር ድጋፍ ማድረግ እንዲሁም ከቀጣሪዎቻቸው ጋር ለተጋጩ ሠራተኞች፣ (ኤጀንሲዎች ችግሩን እስኪፈቱ ድረስ) መጠለያ መስጠት ይችላሉ፡፡

የባህርማዶ ህጋዊ የሥራ ቅጥርን መልሶ በመተግበር ሂደት፣ ሦስት ዓይነት ለስደት የተዘጋጁ ቡድኖች ልዩ ትኩረት ይሻሉ፡፡

- አንደኛ፤ መንግስት በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ እጩ ስደተኞች፤ የስደት ወጪያቸውን ለመሸፈን የሚያስችላቸው የብድር አማራጮች መፍጠርን ሊያጤነው ይችላል፡፡ ይሄም ስደተኞችና ቤተሰቦቻቸው፣ ጎጂ አካሄዶችን እንዳይከተሉ ይታደጋቸዋል፤ ለምሳሌ፡- የቤተሰባቸውን ምርታማ ጥሪቶች ከማሟጠጥ ወይም ርካሽ ነው በሚል ህገ ወጥ ስደትን ከመምረጥ ይታደጋቸዋል፡፡
- ሁለተኛ፤ ወጣት ወንዶች በህጋዊ መንገድ፣ ባህርማዶ የመስራት ዕድሎች ሊሰጣቸው ይገባል፤ለምሳሌ፡-የሁለትዮሽ ስምምነቶች፣ ለወንዶችም ለሴቶችም ክፍት የሆኑ የሥራ ዓይነቶችን (ኮንስትራክሽን፣ ትራንስፖርት ወዘተ--) እንዲያካትቱ በማድረግ፡፡ በርከት ወዳሉ አገራት ለሥራ መጓዝን ህጋዊ ማድረግ የሚቻልበትን መንገድ መፈተሽም ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡
- ሦስተኛ፤ መንግስት "ዕድሜያቸው ላልደረሰ ስደተኞች" (ከ18 ዓመት በታች ለሆኑ) ልዩ ትኩረት መስጠትይገባዋል፡፡ እንዲሁም፣ በተሻሻለው አዋጅ ውስጥ የተካተቱ፣ ከዕድሜ፣

ትምህርትና ሙያዊ ብቃት ጋር የተዛመዱ መስፈርቶች፣ ቅድመ ሁኔታዎቹን የማያሟሉ (ጥናታችን እንደሚያሳየው፤ በገጠር ማህበረሰቦች፣ ቁጥራቸው ብዙ ነው) ከ8 ዓመት በታች የሆኑ ወይም 8ኛ ክፍል ያልደረሱ በርካታ ታዳጊዎች፣ በህገ ወጥ መንገድ መሰደዳቸውን እንዲቀጥሉ በማያደርግ ሁኔታ፣ እንዴት ተፈጻሚ እንደሚሆኑ ማጤንም ይኖርበታል፡፡ የክህሎት ሥልጠናና ከ10ኛ ክፍል በፊት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አማራጮችን የበለጠ ለማሳደግና በገጠር የቀበሌ ማዕከላት፣ ጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ተቋማት እንዲመሰረቱ ድጋፍ ለማድረግ ያለሙ እርምጃዎች (በሌሎች በርካታ የጥናት መግለጫዎች ተጠቅሰዋል)፣ ለእነዚህ ወገኖች አማራጮችን በመክፈት ረገድ ሚናቸው ቀላል አይደለም፡፡

ኢኮኖሚያዊ ሰኬት

ዋና ዋና ነጥቦች ከWIDE የጥናት መረጃዎች

- የWIDE ጥናት እንደሚጠቁመው፤ የኢኮኖሚ ስኬት የሚመነጨው በመንግስት እርምጃዎችና በሌሎች ያልተናነሰ ሚና ባላቸው ቁልፍ ጉዳዮች መስተጋብር ነው፡፡ እነርሱም፡- የራስ ተነሳሽነት፣ የተወሰነ መጠን መነሻ ካፒታልና ሰፊ የአጋጣሚ ክስተቶች ናቸው፡፡ በቀላሉ ሊተው በማይችል ደረጃ፣ የWIDE የገጠር ማህበረሰቦች (ከ1995 ወዲህ)፣ በአጠቃላይ የለውጥ ሂደት ከፍ ብሏል፡፡ በአዋጭነት አውድ የኢኮኖሚ ስኬታማነት፣ የመልካም አርአያዎችን ፈለግ በመከተል እውን ሊደረግ ይችላል፡፡
- በአንድ በኩል፣ የኢኮኖሚ ስኬት እድሎች፣ በተለያዩ የገጠር ማህበረሰቦች ይለያያል፡፡ የመሰረተ ልማት የዕድገት ደረጃም ወሳኝነት አለው፡፡ በሌላ በኩል፣ የግለሰብ ስኬት ሰፊ የመሰራጨት ተጽዕኖ ያለው ሲሆን ተጨማሪ አካባቢያዊ የኢኮኖሚ እድሎችንም ይከፍታል፡፡
- ከዚህ መረጃ በመነሳት፣ ሊተኮርባቸው የሚገቡ ቁልፍ ፖሊሲዎች የሚከተሉት ናቸው፡-
  - የኢኮኖሚ ስኬታማነት በመንግስት ወጥ የሆነ እርምጃ፣ ከአንዱ ግለሰብ ወደ ሌላው ሊደገም አይችልም፡፡
  - ለቡድኖችና ማህበራት ከሚሰጥ ትኩረት ጎን ለጎን የግለሰብ ተነሳሽነቶችን መደገፍ፣ ጠንካራ የገጠር ልማት ውጤቶችን ለመፍጠር አስተዋጽኦ ሊያበረክት ይችላል፡፡
  - ለአካባቢያዊ የኢኮኖሚ ሁኔታዎች የታለሙ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች፣ የአካባቢ በቀል ሥራ ፈጣሪዎችን ውጤት ያሳድጋል፡፡

[1] ይህ አጭር የጥናት መግለጫ፤ በWIDE የውይይት መነሻ አጭር የጥናት መግለጫዎች ሁለተኛ ጥራዝ (ስብስብ) ውስጥ ከተካተቱት አስር መግለጫዎች አንዱ ነው፡፡ መግለጫው፤ በተፈራ ጎሹና በካትሪን ዶም ጋር በጋራ የተዘጋጀ ሲሆን በኢዛና አምደወርቅ ተገምግሟል፡፡ አዘጋጆቹ፤ መግለጫዎቹ ይሰናዱ ዘንድ በገንዘብ ለደገፉት ለእንግሊዝ ዓለም አቀፍ የልማት ተቋም፣ ለአይሪሽ ኤይድና ለስዊድን ዓለምአቀፍ የልማት ኤጀንሲ ልባዊ ምስጋናቸውን ያቀርባሉ፡፡ በተጨማሪም የጥናት ሪፖርቱን በማርቀቅ ሂደት የተሳተፉና አጭር የጥናት መግለጫው የትኩረት አቅጣጫ እንዲሰላ እገዛ ያደረጉ ሌሎች የጥናት ቡድን አባላትና ባለሙያ ገምጋሚዎች፣ ለሥራው ለሰጡት ጊዜና ድጋፍ ያመሰግናሉ፡፡ ሌሎች ምስጋናና ዕውቅና የሚያሻቸውም አሉ፡- (1) ለዓመታት የጥናት መግለጫው የተዘጋጀበትን መረጃዎች ያሰባሰቡና ያደራጁ የጥናት መኮንኖችና ተቆጣጣሪዎች ሙሉ ጊዜያቸውን ሰጥተው ላበረከቱት አስተዋጽኦ፤ (2) በሶስት ዙሮች ለተካሄደው የWIDE ጥናት የገንዘብ ዕገዛ ላደረጉ የተለያዩ ድጋፍ ሰጪ ተቋማት፤ እና (3) በኢልምተ ሰብሳቢነትና በኢኮኖሚ ፖሊሲ ትንተና ክፍሉ በWIDE አጭር የጥናት መግለጫዎች ሁለተኛ ጥራዝ ላይ ለመወያየት መጋቢት 28 ቀን 2016 ዓ.ም በተዘጋጀው መድረክ ላይ የተሳተፉ ከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣናት፣ ላሳዩት ፍላጎትና ለከፈሉት የጊዜ መስዋዕትነት--- ምስጋና ይገባቸዋል፡፡ የጥናት መግለጫው፤ በከፍተኛ ደረጃ በተዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ፣ ከመንግስት ባለሥልጣናት ጋር በተደረገው ውይይት የተሰጡ አስተያየቶችን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ከለሳና ማሻሻያ ተደርጎበታል፡፡ አጭር የጥናት መግለጫው፤ የኢትዮጵያ የልማት ምርምር ተቋምን (ኢልምተ) ወይም የኢትዮጵያ መንግስትን አሊያም የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርጉለትን የልማት አጋሮች አመለካከትም ሆነ አቋም አይወክልም፤ ይልቁንም የፖሊስ ውይይት ለማነቃቃት የታለመ ነው፡፡ ሌሎች የጥራዝ ሁለት የውይይት መነሻ አጭር መግለጫዎችንና የጥናትና ምርምር ውጤቶችን በhttp://ethiopiawide.net/ ድረ-ገጽ ላይ ማግኘት ይቻላል፡፡

- የWIDE ጥናት፤ የተለያዩ አስደናቂ ታሪክ ያላቸው ስኬታማ ግለሰቦችን (ወጣት ወይም ሽማግሌ ወንዶች፣ ወጣት ሴቶች፣ ያገቡ ሴቶች፣ ሴት የቤተሰብ ኃላፊዎች፣ ገበሬዎች፣ ነጋዴዎችና የቢዝነስ ሰዎች) አግኝቷል።
- ይህ የሚያመለክተው፣ የላቀ ጥምረት ያለው አካባቢያዊ የገጠር ኢኮኖሚ በመፈጠር ላይ መሆኑን ነው። ከዚህ ውስጥም ፈርጀ ብዙ የኢኮኖሚ ስኬት ሊፈጠር ይችላል። በተለይ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው፡-
  - የእርሻና አካባቢያዊ የንግድ ወይም ቢዝነስ ስኬት፣ እርስ በርስ ሊደጋገፉ ይችላሉ፤
  - የገጠር ዕድገት በተለይ ለአካባቢ ነጋዴዎችና ለግብርና ምርት ማቀነባበሪያ ኢንቨስትመንት የላቀ ድጋፍ በማድረግ፤ ሁሉንም አካባቢያዊ የገበያ ትስስሮች ቁርኝት በማጠናከር ሊጎለብት ይችላል።
  - የግብር አሰባሰብና የንግድ ቁጥጥር እንዲሁም አፈጻጸማቸውን ግልፅነትና ወጥነት ማሻሻል፣ አካባቢያዊ የንግድና ቢዝነስ እንቅስቃሴዎችን በማበረታታት ረገድ ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረክታል። እነዚህም ከሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ፖሊሲ ጋር የሚጣጣሙ ሲሆን የWIDE ጥናት በፍጥነት እንዲተገበሩ ይጠቁማል።
- የመንግስት የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት በአጠቃላይ ለስኬታማ ገበሬዎች ቁልፍ አስተዋጽኦ አበርክቷል። ይሄንን የበለጠ ለማጠናከርም፡-
  - አርሶአደሮች የግብርና ግብአቶችን በአግባቡ እንዳያገኙ የሚያደርጉ የገንዘብ ማነቆዎችን መፍታት እና የኤክስቴንሽን አገልግሎቶችን ከአካባቢያዊ አውድ አንጻር መቅረጽ - ለምሳሌ፡- ለባህላዊ ሰብሎች ከሚሰጠው ወቅታዊ ትኩረት ጎን ለጎን አማራጭ የገበያ አዝርዕቶችን ማብቀል የሚሹ ወይም በመስኖ ልማት ላይ የተሰማሩ አርሶ አደሮችን ያለመ ድጋፍ መስጠት፤
  - የመስኖ ልማት ለስኬት ወሳኝ መሆኑን የበለጠ እውቅና መስጠት፤ በተለይ ነባር የመስኖ መሰረተ ልማቶችን እንዲጠገኑ በማድረግና ተጨማሪ የመስኖ መሰረተ ልማቶችን በመገንባት። ይሄም የመስኖ ልማት አካባቢዎችን ለማስፋፋት የሚያግዝ የግል ኢንቨስትመንትን ያሳድጋል፤
  - በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ላይ በታሰበው መሠረት፤ ለቀንድ ከብት ኤክስቴንሽን አገልግሎትና ጥራት ላለው የእንስሳት ህክምና ተደራሽነት መስፋፋት ከፍተኛ ትኩረት መስጠት፣ የከብት ርባታ እንደ አንድ የኢኮኖሚ ስኬት ምንጭ እያደገ ለመጣው ሚናው ምላሽ ይሰጣል።
- የገንዘብ መነሻ ካፒታል፣ ለገበሬዎችም ሆነ ለነጋዴዎችና የቢዝነስ ሰዎች ሌላው ቁልፍ ጉዳይ ነው። ነገር ግን፤ በአቅርቦት ማነቆዎች፣ አስቸጋሪ አሰራሮች፣ የተጋነኑ የማስያዣ መስፈርቶች፣ የብድር ማነስ) መደበኛ የብድር አገልግሎት ማግኘት ብዙውን ጊዜ አዳጋች ነው። ይኼንን ችግር ለመፍታት መንግስት የሚከተሉትን ከግንዛቤ ውስጥ ሊያስገባ ይችላል፡-
  - አነስተኛ የገንዘብ ተቋማት ለንግድ አመቺ የሆነ አቀራረብን እንዲቀርፁ ማበረታታት፤ እንዲሁም

- ለገጠሩ ማህበረሰብ ስኬታማ ግለሰቦች፣ አዲስ አይነት የማስያዣ አማራጮችን በመፍጠር፣ የባንክ አገልግሎት ተጠቃሚነታቸውን ማሳደግ[2] (ለምሳሌ፡- ከፍ ያለ ዋጋ ያላቸውን የግለሰቡን ንብረቶች እንደ ቤት ወይ መሬት ካርታ አስይዞ መበደር ማስቻል)፤ ይሄንን መንግስት በገጠር አካባቢዎች የባንክ አገልግሎትንና "ዘመናዊ የመኖርያ ቤቶች"ን ለማስፋፋት ባስቀመጠው ግብ መሰረት ማከናወን ይቻላል[3]::

- ስኬታማ ለሆኑ አርሶ አደሮች ተጨማሪ መሬትን ማግኘት፣ ለበለጠ ዕድገት ቁልፍ ሚና አለው:: ግን ይኼ የአካባቢ ውዝግብን ሊፈጥር ይችላል፡-
  - ህጋዊ በሆነ መንገድ መሬት መግዛትና መለወጥ የሚቻልባቸውን መንገዶች የሚያመቻቹ ተቋማዊ አሰራሮች ማጠናከር ይህን የሚያቀላጥፍ ሲሆን ደካማ የሆኑ የማህበረሰቡን አባላት መብትም ይጠብቃል:: በማህበረሰቡ መሀል የሚፈጠረውን ውጥረትም ለማርገብ ይረዳል:: ለምሳሌ፡- የመሬት ግዢና ሽያጭን መፍቀድ በሌላ ጎን ደግሞ መሬት ለሌላቸው ወጣት የማህበረሰብ ክፍሎች ወይም ለከተማ መስፋፋት የመሬት አቅርቦትን ማቀላጠፍ::

- በብዙዎቹ ሁኔታዎች አስተማማኝ የኢኮኖሚ ስኬቶች ገና መሰረት አልጣሉም:: ስኬታማ ግለሰቦች፤ አደጋዎችን የሚቋቋሙት በእርሻ ወይም ከእርሻ ውጭ ባሉ የተለያዩ ዘርፎች እንቅስቃሴያቸውን በማስፋት ነው:: ለብዙዎቹም እርሻ፣ የኢኮኖሚ ዘርፋቸውን በዓይነት ለማስፋት መነሻ መሰረት ሆኗቸዋል::

- ስለዚህም ኢኮኖሚን በተለያዩ ዘርፎች ማስፋፋት፣ አደጋን የመቋቋም አቅምንና ዘላቂነትን ያጎለብታል:: ይሄም የሚጠቁመው፡-
  - በተወሰኑ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች (ለምሳሌ፡- ለአርሶ አደሮች አንድ አዝርዕት ብቻ ማብቀልን) ላይ አተኩሮ የሚከናወን የማስፋፋት ሥራ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልገዋል::
  - የተለያዩ የመድን ዋስትና አገልግሎቶችን ተደራሽ ማድረግ (ለምሳሌ፡- የከብቶች፣ የጤና ወዘተ) የኢኮኖሚ ስኬትን ለመቀዳጀት የበለጠ አስተዋፅኦ ያበረክታል::
  - የስኬታማ ሥራ ፈጣሪ ግለሰቦችን የእይታ አድማስ ማስፋት፣ ስኬታቸውን አስተማማኝና ዘላቂነት ያለው ለማድረግ ይረዳቸዋል::

[2] የቀድሞው ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ፤ በህዳር 2005 በተካሄደው የግብርና እና የገጠር ፋይናንስ ዓለምአቀፍ ጉባኤ ላይ ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር፤ በገጠር አካባቢዎች የግለሰቦች የባንክ አገልግሎት ተጠቃሚነት ያለውን ፋይዳ አስረግጠው ገልጸዋል (http://nextbillion.net/news/thiopia-meles/).

[3] የገጠር የመኖሪያ ቤቶች ልማት በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ላይ የመንግስት ግብ ሆኖ ተቀምጧል፤ የከተማ መኖሪያ ቤቶች ልማትን ከማስፋፋት ጎን ለጎን (http://www.ena.gov.et/en/index.php/economy/item/816-ministry-plans-to-construct-over-2-4-million-houses-in-gtp-ii ይመልከቱ)

መግቢያ

ይህ አጭር የጥናት መግለጫ፤ በገጠር ኢትዮጵያ ሥራ ፈጣሪ ግለሰቦች የአስተሳሰባቸውን ሙሉ አቅም በተገኘው ግብዓት ላይ በማዋል፣ በአካባቢው ማህበረሰቦች አውድ (ይበልጥ በሰፊው ያለው ሁኔታ በሌሎች የጥናት መግለጫዎችና የWIDE ሰነዶች ተገልጧል) በተገኘው ለውጥ ሳቢያ የተፈጠሩ ዕድሎችን ሳያባክኑ በመጠቀም እንዴት ስኬታማ እንደሆኑ ያሳያል፡፡ በዚህም የጥናት መግለጫው፤ ሥራ ፈጣሪዎችን የከተማ ማህበረሰብ አባላት ብቻ አድርጎ ማሰብ ስህተት መሆኑን ይጠቁማል - ይህም በኢትዮጵያ የገጠርና የከተማ ክፍሎች መካከል ተሰምሮ የኖረው መስመር እየደበዘዘ መምጣቱን ከሚያሳዩ አያሌ ምልክቶች አንዱ ሲሆን በርካታ የፖሊሲ አንደምታዎችንም የያዘ ነው (ማጣቀሻ፡- የገጠር ከተሜነት መስፋፋት)፡፡

ይህ አጭር የጥናት መግለጫ፤ በ70 ስኬታማ ግለሰቦች ታሪክ ላይ በመመስረት የWIDE ኢትዮጵያን የጥናት መረጃዎች በመጠቀም፣ በ20 የተለያዩ የገጠር ማህበረሰቦች የተመዘገቡ የኢኮኖሚ ስኬት ዕይታዎችን ያቀርባል[4]፡፡ የጥናት መግለጫው፤ የኢኮኖሚ ስኬት ብዙውን ጊዜ የተለያዩ መሰረታዊ ምክንያቶች ሁለንተናዊ ትስስር ውጤት መሆኑን አጉልቶ ለማሳየት ይሞክራል፡፡ እነዚህ መሰረታዊ ምክንያቶች መንግስትን ቢጨምሩም ከመንግስት ተግባራት አልፈው የሚሄዱ ይገኙበታል፡፡ አጭር የጥናት መግለጫው፤ መልከ ብዙ የሆነውን የስኬታማ ግለሰቦች ታሪክ በዖታ፣ በእድሜና በሥራ ዓይነት ከፋፍሎ በቁንፅል የሚያሳይ ሲሆን ይህም ይበልጥ ውስብስብ አካባቢያዊ የገጠር ኢኮኖሚ በመፈጠር ላይ መሆኑን ማስረጃ ነው ሲል ይሞግታል፡፡ ከነዚህም በተጨማሪ በተለያየ የገጠር ኢኮኖሚ አውድ ውስጥ የግለሰቦች ስኬት ከስኬታማዎቹ ግለሰቦች አልፎ የሚሻገር ተጽዕኖ እንደሚፈጥር ለማሳየት ይሞክራል፡፡ ስለሆነም ሥራ ፈጣሪ ግለሰቦችን መንግስት በማህበራት መልክ ከሚያደርጋቸው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ጎን ለጎን መደገፉ አስፈላጊ እንደሆነ ይጠቁማል፡፡ አጭር የጥናት መግለጫው፤ የመንግስት ተግባራት ለኢኮኖሚ ስኬታማነት ያላቸውን አስተዋፅኦ የሚቃኝ ሲሆን እነዚህ ተግባራት አካባቢያዊ የኢኮኖሚ ውጤቶችን የበለጠ ለማሻሻል ሊጠናከሩ የሚችሉባቸውን አማራጮችም ይዳስሳል፡፡ WIDE ጥናት ባደረገባቸው ማህበረሰቦች ውስጥ የተገኙ ዘላቂና አስተማማኝ የስኬት ጉዞዎችን በማጎሳትም፣ በዚህ ረገድ እንዴት የኢኮኖሚ ዘርፍ ዓይነቶችን ማስፋት ወሳኝ ስትራቴጂ እንደሆነ ያብራራል፡፡

የኢኮኖሚ ስኬት- የተለያዩ ጉዳዮች ጥምር ውጤት

ጥናት ከተደረገባቸው ሰባ እጅግ የተለያዩ ግለሰቦች ታሪክ መረዳት እንደተቻለው፤ የኢኮኖሚ ስኬታማነት የብዙ ጉዳዮች ጥምር ውጤት ነው፡፡ የመንግስት እርምጃ (በቀጣይ ክፍል እንደሚብራራው) ከግል ተነሳሽነት፣ ከሰፊ የአጋጣሚ ለውጦችና ከመነሻ ካፒታል ጋር መስተጋብር መፍጠራቸውን ማየት ይቻላል፡፡

[4] ለአጭር መግለጫው የተጠኑት አጫጭር ታሪኮች፣ ስልታዊ በሆነ መንገድ የተመረጡ የተለያዩ የኢኮኖሚ ስኬት ናሙናዎችን አይወክሉም፤ ስኬት የተተረጎመው እንደ የአካባቢው ሁኔታ ነው፡፡ ሆኖም እነዚህ ግለሰቦች ንቁ ተሳታፊ እንደሆኑበት የWIDE ማህበረሰቦች ሁሉ፣ የስኬታማ ግለሰቦች መግለጫዎቹ፣ መጠነ ሰፊ ልዩነቶችን ያቀፉ የተለያዩ የኢኮኖሚ ስኬት ዓይነተኛ ምሳሌዎች ተብለው የተመረጡ ናቸው፡፡ ይህና መረጃዎችን ለመተንተን ጥቅም ላይ የዋለው አብነት-ተኮር የጥናት ስልት፣ አይታዎቻችንና የደረስንባቸው ድምዳሜዎች/ጥቆማዎች፣ ሰፊውን የገጠር ኢትዮጵያ እውነታ የሚያንጸባርቁ ናቸው ለማለት ያስደፍረናል፡፡

የራስ ተነሳሽነት ለግለሰቡ ስኬት ወሳኝ ነው። የራስ ተነሳሽነት፤ አንዳንዶች የበለጠ እንዲያልሙ፣ አእምሮአቸውን በማንቃት በትጋት እንዲሰሩና በአቅማቸው ያለውን አማራጭና ግብዓቶች አሟጠው ተጠቅመው፣ ከሌሎች ተነሳሽነታቸው ደካማ ከሆኑ ግለሰቦች የበለጠ ስኬታማ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። ይህም ሌሎች ግለሰቦች ሊያገኙት የሚያዳግታቸውን የገንዘብ ወይም ማህበራዊ ካፒታል እና ለሁሉም በእኩል የቀረቡ ግብአቶችን (ለምሳሌ፡- በአገራዊ አውድ ለውጦችና በመንግስት የለውጥ እርምጃዎች ሳቢያ የሚፈጠሩ መልካም አጋጣሚዎች) ይጨምራል።

ከሁሉም አስገራሚዎቹ ደግሞ ከገጠማቸው መከራ የራስ ተነሳሽነታቸውን ተጠቅመው ከግል ውድቀታቸውና መሰል ጋሬጣዎች ስኬትን ተቀዳጅተው መላቀቅ የቻሉት ግለሰቦች ናቸው። በምስራቅ ሐረርጌ (አዴሌ ኬኬ) የምትኖረዋ ፊደል ያልቆጠረች ወጣት ነጋዴ ለዚህ ጥሩ አብነት ናት። ይቺ ወጣት፣ ሁለተኛ ትዳሯን ከፈታች በኋላ ሱቅ ከፍታ በመነገድ ልጇን ማሳደግ ችላለች። ልጇን ከማሳደግም ባሻገር ባጠራቀመችው ገንዘብ፣ በ2012 ዓ.ም የራሷን መኖሪያ ቤትም ገንብታለች።

የተለያዩ በአጋጣሚ የሚፈጠሩ ለውጦች ለምሳሌ፡- እንደ አየር ጠባይ አደጋ፣ ግሽበትና የማህበረሰቡ መስተጋብርም ለግለሰቡ ስኬት ወሳኝ ናቸው። የአየር ጠባይ ለውጥ አደጋ አሉታዊ ውጤቶች፣ የስኬት ጉዞዎችን ወደ ኋላ የጎተቱባቸው ብዙ አጋጣሚዎች አሉ። ለምሳሌ፡- በምስራቅ ትግራይ (ገብለን)፣ አንድ አርሶ አደር በ2008/9 በተከሰተው ድርቅ ሳቢያ በርካታ የቀንድ ከብቱን ያጣ ሲሆን የቤተሰቡን ሀብት ወደ ቀድሞ ቦታው ለመመለስ በጣም ተግቶ መስራት ነበረበት።

የዋጋ ግሽበት አዎንታዊም አሉታዊም ጎኖች አሉት። የሁለቱ ጥምረት ለአንዳንዶች ጠቃሚ ሲሆን ለሌሎች ደግሞ አስከፊ ነው። በርካታ አርሶአደሮች እንደገለጹት፤ ስኬታማ ሊሆኑ የቻሉት በተለያዩ ጥምር ሁኔታዎች ነው። በአብዛኛው በኤክስቴንሽን አገልግሎት በተደገፈ ምርታማነት፣ በገበያ ፍላጎት መጨመር (በተለይ በመስፋፋት ላይ ከሚገኙ የከተማ አካባቢዎች ብዙም ያልራቁ ማህበረሰቦች) እና ለእርሻ ወይም ለከብት ምርታቸው ከፍተኛ ገንዘብ የሚከፍላቸው ሲያገኙ። ግን አንዳንዶች እንደጠቆሙት፤ ግሽበት፣ የምርት ግብአቶችና የቤት አስቤዛዎችን ዋጋ በማናር የስኬት ጉዟቸውን አደናቅፎባቸዋል። ነጋዴዎች የዋጋ ግሽበትን በተመለከተ ጥሩ አመለካከት የላቸውም። ለምሳሌ በምስራቅ ሸዋ (ገልቻ) የምትገኝ አንዲት ነጋዴ እንዳብራራችው፤ የዋጋ ግሽበት የደንበኞቿን የመሸመት አቅም የሚያዳክም ሲሆን የንግድ እንቅስቃሴና ገቢንም ያቀዛቅዛል። የሰብል ምርት ዋጋ መዋዠቅ ለስኬት ጥሩ ቢመስልም እድገትን ወደ ኋላ ሊጎትት ይችላል። ለምሳሌ፡- በአዳዶ (ጌዴኦ) ከ2011 ወዲህ፣ የቡና ዋጋ በዓለም አቀፍ ገበያ መውደቅ ትላልቅ ቡና አምራቾችን ጎድቷቸዋል፤ ወይም በሰሜን ሸዋ (ዲንኪ) በመስኖ ልማት ስኬታማ የሆኑ አርሶ አደሮች በሽንኩርት ዋጋ መውጣትና መውረድ ተጎድተዋል።

ይበልጥ ተጨባጭ ባይሆንም በእኩል ደረጃ ተጽዕኖ የፈጠረ ትልቅ ለውጥም በWIDE ማህበረሰቦች ተመዝግቧል። ይህ በጥቅሉ ከፍተኛ የሆነ የህብረተሰብ መስተጋብር፤ *"የ1990ዎቹ ውድቀትን የሚሰብኩ የአስተሳሰብ ባህሎች በተሰፈኝነት የአስተሳሰብ ባህሎች መተካታቸው ነው"*[5]። ይህ የአስተሳሰብ አዝማሚያ በሌላ ማህበረሰብ-ተኮር ጥናት የተጠናከረ ሲሆን እንዴት "የራስን ህይወት

[5] Bevan et al, 2014, *Long Term Perspective on Development Impacts in Rural Ethiopia – WIDE3 Stage 3 – Six Communities with Agricutural Potential: Short Summary*

መለወጥ" እንደ አንድ ወጥ መርህ የሚቀነቀን ሐረግ ሊሆን እንደቻለ ይጠቅሳል[6]። ተነሳሽነትና ክህሎት ያላቸውን የማህበረሰቡን አካላት ለማንቀሳቀሻ የሚሆን ግብዓትም ከዚህ አስተሳሰብ ተገኝቷል። በማህበረሰቡ ዘንድ ስኬት የሚደገፍና የሚቀናበት ጉዳይ ሲሆን ቀላሉ ተግባር ስኬታማ መሆን ነው። ስለዚህም፤ ለምሳሌ በምስራቅ ሐረርጌ (አዴሌ ኬኬ) አንዲት ስኬታማ የወተት ነጋዴ፤ ሁለት ጊዜ አግብታ ብትፈታም በርካታ ወንዶች ለጋብቻ የጠየቋት በስኬታማነቷ የተነሳ እንደሆነ አሌ አይባልም (ነጋዴዋ የሁሉንም ጥያቄ አልተቀበለችም)።

የተወሰነ ዓይነት መነሻ ካፒታል መመደብ መቻል ለስኬት መሰረታዊ ቅድመ ሁኔታ ነው። ለገበሬዎች ይህ ማለት፤ ለመነሻ "በቂ" መሬትና የሰው ጉልበት ማግኘት ሲሆን ከላይ ለተጠቀሱት ቁልፍ ነጥቦች ምስጋና ይግባቸውና (ማለትም፡- የተሻለ የማምረት አቅም፣ የገበያ ፍላጎት መጨመርና ከፍተኛ የምርት ዋጋ) ... ተጨማሪ መሬት መግዛትና የሰው ጉልበት መቅጠር ችለዋል። ለምሳሌ፡- በወላይታ (ጋራ ጎዶ) አንድ ገበሬ የራሱን 2 ሄክታር (ከአካባቢው አማካይ በእጅጉ የሚበልጥ) እና በእኩል የሚያርሰው ተጨማሪ መሬት ሊያገኝ ችሏል።

የገንዘብ ካፒታል ለገበሬዎችም፣ ለነጋዴዎችም ሆነ ለቢዝነስ ሰዎች በአጠቃላይ ወሳኝ ጉዳይ ነው። ይህ የመነሻ ገንዘብ (ካፒታል) ምንጩ የተለያየ ነው። ከነዚህም መሃል መደበኛ የብድር አገልግሎት፣ ኢ-መደበኛ ብድሮች፣ እቁብ ወይም ከባህር ማዶ ስደት የሚላክ ወይም የተጠራቀመ የስደት ገንዘብ ይጠቀሣሉ። በርካታ ግለሰቦች በጣም አነስተኛ በሆነ መነሻ ገንዘብ ነገር ግን የዘመድ ድጋፍን ጨምሮ ሌሎች ግብአቶችን በመጠቀም ስኬታማ መሆን ችለዋል። ለዚህ እንደ አይነተኛ አስገራሚ ምሳሌ ተደርጋ የምትጠቀሰው በመካከለኛ ዕድሜ ላይ የምትገኘው የሲርባ (በምስራቅ ሸዋ፤ በሞጆና በቢሾፍቱ መካከል የሚገኝ) ነዋሪ ናት። ይህች ሴት፤ የዛሬ 15 ዓመት በ100 ብር የመነሻ ካፒታልና በባለቤቷ ድጋፍ ለአካባቢው የመጀመሪያው የሆነ የሸቀጣ ሸቀጥ ሱቅ የከፈተች ሲሆን በ2013 ዘርፈ ብዙ በሆኑ የእርሻና ከእርሻ ውጭ የሆኑ ዘርፎች ተሰማርታ፣ ሰባት ሰራተኞችን ለመቅጠር ችላለች። ከገንዘብ ባሻገር የራሷ መኪና እና በቢሾፍቱ ከተማ የገነባችው የመኖሪያ ቤትን የመሰሉ ቋሚ ንብረቶችንም አፍርታለች። በቀጣይም እዚያው ቢሾፍቱ ከተማ ላይ ሱፐርማርኬት ለመክፈት አቅዳለች።

በእርግጥ፤ ለብዙዎቹ ማህበረሰባዊ እሴት ወሳኝ ጉዳይ ነው። አብዛኞቹ ስኬታማ ሴት የቤተሰብ አስተዳዳሪዎች፤ የዘመድ አዝማድ፣ የቤተሰብ አባል፣ የጓደኛና ሌሎችን ድጋፍና ማበረታቻ ተጠቅመዋል። ለምሳሌ፡- በሉቃ (ጸማይ) ከፊል አርብቶ አደር የሆነች ስኬታማ ሴት፤ ሰሊጥ ለገበያ የምታመርት ሲሆን ወደ ከብት ማድለብ በመግባት የሥራ ዘርፏን ለማስፋት አቅዳለች። ይህች ሴት ታዲያ የጉልበት ድጋፍና ምክር ያገኘችው ከጎረቤቶቿና ከአካባቢው አስተዳዳሪዎች ነው። የስራ ክፍፍልና በተለያዩ የቤተሰብ አባላት መካከል የሚደረግ ትብብርም ወሳኝ ነው። ለምሳሌ፡- በዲንኪ አንድ ትልቅና ስኬታማ የእርሻ ይዞታ ባለው ቤተሰብ ይህ ሁኔታ ተስተውሏል። እምብዛም ያልተለመደው የሲርባ ወጣት ጥንድ ነጋዴዎች አብነት ነው። እነዚህ ወጣት ጥንዶች፤ ሆቴል/ካፌ/ምግብ ቤት የሚያስተዳድሩ ሲሆን በሚኒባሳቸው ለአበባ እርሻዎች የትራንስፖርት

[6]Svein Ege, forthcoming, *The New Economy: Agricultural Transformation in North Shäwa, Ethiopia.*

አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ ንግድ ነክ ጉዳዮችን ከቀበሌ ንግድ ቢሮ ወይም ኢንዱስትሪ ቢሮ ጋር የምትነጋገረው ሚስትየዋ ናት፡፡

በነጋዴዎች መካከል የሚደረግ ትብብርም ለስኬት ቁልፍ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- በጋሞ (ዶአማ) አንድ ወጣት የሙዝና በቆሎ ነጋዴ ከንግድ ባልደረቦቹ ጋር ገንዘብ የሚበዳደሩበት ሁኔታ አለ - እንደ ፍላጎታቸውና እንዳላቸው ገንዘብ፡፡ በርካታ ስኬታማ ግለሰቦች ባለሙት የንግድ ዘርፍ ከመሰማራታቸው በፊት ቀድመው በተቋቋሙ የሌሎች ሰዎች ንግድ ውስጥ የመስራት ዕድል ያገኙ ሲሆን ይሄም ሥለ ሥራው ትምህርት እንዲቀስሙና የተወሰነ መነሻ ካፒታል እንዲቋጥሩ አስችሏቸዋል፡፡ ለምሳሌ፡- በሃረሳው (ምስራቅ ትግራይ) አንድ ወጣት የቆዳና ሌጦ ነጋዴ፤ ወደ ሥራው የገባው መጀመሪያ ለሌሎች የቆዳና ሌጦ ነጋዴዎች አህያ በመምራት ነበር፡፡ በ2011 የራሱን ንግድ ጀምሯል፡፡ በአዴሌ ኬኬ አንድ ወጣት ገበሬ የእርሻ ሥራ የጀመረው በአባቱ መሬትና ከጓደኛው ጋር አንድ የውሃ መሳቢያ ፓምፕ በጋራ በመጠቀም ሲሆን በ2012 ተጨማሪ መሬት ተከራይቶ፣ ለራሱ ከማረሱም ባሻገር የግሉን የውሃ መሳቢያ ፓምፕ ለመግዛት በቅቷል፡፡ ለውጥ ላይ የሚያተኩረው አጭር ጽሁፍ በመማር ሂደት የማህበረሰባዊ እሴት አስፈላጊነትን አስረግጦ ይገልጻል፡፡)

የWIDE ጥናት ከትትል ባደረገባቸው ማህበረሰቦች፤ አብዛኞቹ በኢኮኖሚ ስኬታማ የሆኑ ግለሰቦች ከአካባቢው የፖለቲካ አመራር ጋር ግንኙነት ወይም አባልነት የሌላቸው ናቸው፡፡ በጥናቱ ከተካተቱት ማህበረሰቦች አንድ - ሦስተኛዎቹ ከአካባቢ የፖለቲካ ስልጣን ወይም መሪዎች ጋር ግንኙነት ያላቸው እንደሆኑ ታውቋል፡፡ ነገር ግን በፖለቲካ አመራር ውስጥ አለመሳተፍም በራስ የግል ሥራ ላይ ለማተኮር ሆን ተብሎ የሚቀየስ ስትራቴጂ የሚሆንበት አጋጣሚም እንዳለ ተስተውሏል፡፡ አንዳንድ ሞዴል አርሶአደሮች የምርት ግብአትና ምክር የማግኘት ጥቅም እንዳላቸው ያምናሉ፡፡ ግን ምክሩና ግብዓቱ ከስኬት በፊት የተሰጠ ወይስ በኋላ ግልፅ ሆኖ አልተቀመጠም፡፡ ወይስ ሞዴል አርሶአደሮች ተብለው መሰየማቸው ከመነሻ ባስመዘገቡት ስኬት በኋላ የተቸራቸው ይሆን፡፡ በአግባቡ ግንኙነት የመፍጠር ትልቁ ነገር ጠቃሚ የሆኑ የመንግስት የለውጥ እርምጃዎችን የተመለከቱ መረጃዎችን በቀላሉ ማግኘት ነው (ማጣቀሻ፡- ለውጥ)፡፡

ከላይ ከቀረቡት ቁልፍ ጉዳዮች መካከል የመንግስት እርምጃዎችና ትላልቅ የአጋጣሚ ለውጦች በመርህ ደረጃ በማህበረሰቦች ውስጥ እያንዳንዱ ዘንድ የሚደርሱ ናቸው፡፡ ነገር ግን የራስ ተነሳሽነትና ግፊት የግለሰቡ ባህርይ ወይም ማንነት መገለጫ ነው፡፡ የመነሻ ካፒታል ማግኘት ደግሞ እንደ ግለሰቡ የህይወት ሁኔታ የሚወሰን ነው፡፡ ወሳኙ ነገር እነዚህ ጉዳዮች ሲጣመሩ የሚሰጡት ውጤት ነው፡፡ ይህ "ጥምር" ውጤት የሚጠቁመው፡-

- ወጥ እና ተመሳሳይ በሆነ የመንግስት እርምጃ፤ በአንድ ግለሰብ ላይ የተገኘን ስኬት በሌሎችም ላይ በተመሳሳይ መንገድ መድገም እንደማይቻል ነው፡፡ ኢ-እኩልነት በሚለው ጽሁፍ እንደታየው፤ በዚህ አጭር የጥናት መግለጫ ውስጥ ከትትል የተደረገባቸው ስኬታማ ግለሰቦችን ተጠቃሚ ያደረገ የመንግስት እርምጃ፣ ምንም ዓይነት መነሻ ካፒታል ያልነበራቸው ወይም የግል ተነሳሽነታቸው በችግርና መከራ ሳቢያ የነጠፈባቸው ዘንድ ተደራሽ አልሆነም፡፡ ስኬትን ለመድገም ከግለሰብ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር ተጣጥመው የተቀረጹ የመንግስት የለውጥ እርምጃዎችን ይጠይቃል፡፡

<u>የግለሰቦች ስኬት በማህበረሰቡ አውድ እንደሚቀረፅ ማህበረሰባዊ አውድንም ይቀርጻል</u>

የተለያዩ ዓይነት ማህበረሰቦች የተለያዩ የስኬት ዕድሎችን ያቀርባሉ፡፡ ለምሳሌ፡- ስኬታማ የንግድ ሰዎች የከተማ መስፋፋት በተደረጉባቸው ቦታዎች የበለጠ ይገኛሉ (ማጣቀሻ፡- የገጠር ከተሜነት መስፋፋት)፡፡ ይህ ሊሆን የሚችለው በንፅፅር ሰፊ እና በመንሰራፋት ላይ ከሚገኙ የከተማ አካባቢዎች ጋር ጠንካራ ትስስሮች በመፍጠር ነው፡፡ (ይህንን የሚያሳዩ ምሳሌዎች፣ ጂማ አቅራቢያ በሶሞዶ የሚገኙ ጥቂት የንግድ ሰዎችን የሚያካትት ሲሆን በተለያዩ የአገልግሎት/የንግድ ዘርፎች ላይ ተሰማርተዋል፤ ቀደም ብለው የተጠቀሱት የሲብራ ጥንድ ወጣቶችም ተጠቃሽ ናቸው) ወይም እንደ ገልቻ ውስጣዊ ወይም የመንገድ ዳር የከተማ መስፋፋት ያላቸው (ጥቂት ወጣት የሸቀጣ ሸቀጥ ሱቅ ባለቤቶች ይኼንን አዝማሚያ ተጠቅመውበታል)፡፡ ከፍተኛ የግብርና ምርታማነት አቅም ባላቸው ማህበረሰቦች፣ ስኬታማ ግለሰቦች ገበሬ የመሆን እድላቸው ከፍ ያለ ሲሆን ነጋዴዎች የገበሬውን ምርት ለገበያ ያመቻቻሉ፤ በተለይ እንደ ኡዳ ሃሮ (ምዕራብ ሸዋ) ፣ ኮርማርገፍያ (ሰሜን ሸዋ) እና ኡዳ ዳዋታ (አርሲ) በመሳሰሉ ከትላልቅ ከተሞች ርቀው በሚገኙ ማህበረሰቦች፡፡

በተቃራኒው፤ የአንዳንድ ግለሰቦች ስኬታማ መሆን ከእነሱ ተርፎ ሌሎችን የማዳረስ አዝማሚያ አለው፡፡ የተወሰኑት ሌሎች ሰዎችን ቀጥረዋል፤ ለምሳሌ፡- በትልልቅ የቡና አምራች ወይም ጫት አብቃዮች እርሻ ላይ እንዲሁም ሰፋፊ የእርሻ መሬት ወይም የመስኖ ልማት ባላቸው ገበሬዎች ዘንድ ተቀጥረው ይሰራሉ (ቆሮደጋጋ/አርሲ)፡፡ አልያም ደግሞ በሶሞዶ እና ሲርባ ጥንዶቹ እንዳደረጉት፣ በንግድ ድርጅቶቻቸው ውስጥ ይሰራሉ፡፡ ስኬታማ ግለሰቦች የስራ ዕድል የሚፈጠርበት ሰንሰለት ማዕከሎች ናቸው (ወይም የአካባቢው የገበያ ትስስሮች)፡፡ ብዙውን ጊዜ ስኬታማ ገበሬ ከመሆን ነው የሚጀምሩት፡፡ ለምሳሌ፡- በኡዳ ሃሮ በጣት የሚቆጠሩ ገበሬዎች ስኬታማ በመሆናቸው፣ ማህበረሰብ በቀል የሆነ የነጋዴ መደብ እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል፡፡ ከዚህ የነጋዴ መደብ ውስጥ አንዳንዶቹ በጅምላ ከገበሬዎች ምርት ገዝተው ውጭ ላሉ ነጋዴዎች የሚሸጡ ሲሆኑ ገበሬዎች ገበያ በመፈለግ የሚያጠፉትን ጊዜ አድኖላቸዋል፡፡ ከገጠር የውስጥ ለውስጥ መንገዶች መሻሻል ጋር ተያይዞ የጋሪ ፈረስ እንደ አዲስ አትራፊ የንግድ እንቅስቃሴ ብቅ እንዲል አድርጎታል፡፡ በ2013፣ ከ160 በላይ ጋሪዎች በዋናነት ሸቀጥን ወደ ገበያ ከማመላለስ በተጨማሪ ነጋዴዎችን ወይም እህልን ከመውቂያ ስፍራ ወደ ገበያ ለማድረስ አገልግለዋል፡፡ ምርትን ለመጫንና ለማውረድ የሚያስፈልግ የሰው ጉልበት፣ ሌላው ስኬት የፈጠራቸው ዕድሎች አካል ነው፡፡

ከዚህ እኩል ዋናው ጉዳይ ደግሞ የአርአያነት ምሳሌ የሚሆኑ ግለሰቦች በማህበረሰባቸው ውስጥ መፈጠራቸው ነው፡፡ እኒህ ግለሰቦች ደግሞ ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረው፣ መንግስት በይፋ ከሰየማቸው “ሞዴሎች" መሃል አይደሉም (ማጣቀሻ፡- ለውጥ፤ እና ሴቶች)፡፡

ስኬታማ ግለሰቦች የመሰረተ ልማት ግንባታን እንደ ልዩ የስኬት ቁልፍ ጉዳይ እምብዛም አይጠቅሱትም፡፡ ነገር ግን መረጃው በግልጽ እንደሚጠቁመው፡- የተሻለ የመንገድ ዝርጋታ፣ የስልክ መስመር፣ የኤሌክትሪክ ኃይል ሽፋን፣ የመጋቢ መንገዶች መሻሻል ወዘተ-- ቀደም ሲል ለተጠቀሰው ጥቅል መሻሻል አንቀሳቃሽ ሞተር ሲሆኑ ለግለሰብ ሥራ ፈጣሪነት ስኬት አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡

በሁሉም ማህበረሰቦች፣ የመሰረተ ልማት ግንባታ፣ አካባቢያዊ የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማምጣት ወሳኝ እንደሆነ ታምኖበታል፡፡ በተቃራኒው፤ በተለይ የአንዳንድ ወሳኝ መሰረተ ልማት አለመኖር የኢኮኖሚ

ስኬትን የሚገድብ ማነቆ እንደሆነ ተለይቷል፡፡ የመንገድ ግንባታ እጦት በተደጋጋሚ የተጠቀሰ ሲሆን በሁሉም ማህበረሰቦች፣ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ችግር መኖሩ ታውቋል (ማጣቀሻ፡- የገጠር ከተሜነት መስፋፋት)፡፡ የሚለውን ይመልከቱ) በዚህም የተነሳ ተደራሽነታቸው አስቸጋሪ በሆኑ የእርሻ ማሳዎች ምርት ወደ ገበያ የሚወጣበት አማራጭ ጠፍቶ በተቀመጠበት የበሰበሰበት አጋጣሚዎች አሉ (ለምሳሌ፡- የካሮት ምርት በኮርማርገፍያ)፡፡ በአንዳንድ ማህበረሰቦች ደግሞ ከአጎራባች ማህበረሰቦች ጋር የሚያገናኙ አስተማማኝ መንገዶች የሉም፡፡ ለምሳሌ፡- ይሄ በአዳዶ (ጌዲኦ) ለትላልቅ ቡና አምራቾችና ለአካባቢው ነጋዴዎች ተግዳሮት ፈጥሮባቸዋል፤ በቆሮደጋጋ ገበሬዎች በመስኖ ያለሙትን ምርት ወደ ገበያ ለማድረስ እንቅፋት ሆኖባቸዋል፡፡

ከላይ የቀረቡት እይታዎች የሚጠቁሙት፡-

- መንግስት ከሚደግፋቸው የተደራጁ የቡድን ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ጎን ለጎን የግለሰብ ተነሳሽነቶችን መደገፉ ሰፊ መሰረት ላለው የገጠር ማህበረሰቦች ዕድገት አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡
- ለውጥ ላይ በሚያተኩረው ጽሁፍ እንደተመለከተው፣ «አርአያን የመከተል» አዝማሚያን መጠቀም መደበኛ ላልሆኑ የማህበረሰብ እውቀት ስርጸት ሂደቶች ትኩረት መስጠትና ማበረታታትን ይጠይቃል፡፡
- መንግስት የቅድሚያ ትኩረት በሰጠው መሰረት፤ የመሰረተ ልማት ግንባታን ማፋጠን የሚኖረው ቁልፍ ሚና ይቀጥላል፡፡ ይህ አካባቢ በቀል ሥራ ፈጣሪዎችን ለመደገፍ ያለው አቅም በተለይ ለአካባቢያዊ የኢኮኖሚ ሁኔታዎች ተስማሚ ኢንቨስትመንትን በማለም የበለጠ ሊጎለብት ይችላል፡፡

የበለጠ ቀጥተኛ የድጋፍ እርምጃዎችም ከግንዛቤ ውስጥ መግባት አለባቸው፡፡ ከዚህ በታች የተጠቀሱት የተወሰኑት ነጥቦች የመንግስት ወቅታዊ ወይም የታቀደ የገጠር ልማት አጀንዳ ላይ የሚያጠነጥኑ ናቸው፡፡ በዚህ አጭር የጥናት መግለጫ ላይ የቀረቡ ሃሳቦች፤ አስፈላጊነታቸውን ለማስረገጥና ትኩረት የሚሹ አንዳንድ ጉዳዮችን ለማጉላት የሚያልሙ ናቸው፡፡

<u>ባለብዙ መልክ ከሆኑ ኢኮኖሚዎች የተገኙ ዘርፈ ብዙ የስኬት ተሞክሮዎች</u>

በተለያዩ አውዶች ውስጥ እንደቀረበው፤ ስኬታማ ግለሰቦች ከዕድሜ፣ ጾታና የሥራ ዘርፍ አንጻር ሰፊ ብዝኃነት ያለው ታሪኮችን የሚያንጸባርቁ ናቸው፡፡ ወጣት ወይም በእድሜ የገፉ፣ ገበሬ ወይንም ነጋዴዎች፣ ወንዶች ወይም ሴቶች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ አንዳንዶቹ ባለትዳር ናቸው፡፡ በመሆኑም የባሎቻቸው ድጋፍ ብዙውን ጊዜ ለስኬታቸው ቁልፍ ነው፡፡ ነገር ግን ሴቶች ላይ በሚያተኩረው ጽሁፍ ውስጥ እንደተገለጸው ቤተሰባቸውን የሚያስተዳድሩ ስኬታማ ሴቶችም አሉ፡፡ ምንም እንኳን መረጃው ትምህርት በኢኮኖሚ ስኬት ያለውን ሚና ለመፈተሽ ባይፈቅድም፣ አንዳንድ በኢኮኖሚ ስኬታማ የሆኑ ግለሰቦች ያልተማሩ መሆናቸው ሊጤን የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ ቀደም ሲል የተጠቀሰችው በወተት ንግድ ስኬታማ የሆነችው የአዴሌ ኬኬ ሃብታም ሴት ለዚህ ጥሩ አብነት ትሆናለች፡፡ ይህቺ ሴት ከወረዳው ቢሮ ባገኘችው ከወለድ ነጻ የሆነ የ500 ብር ብድር የንግድ ሥራዋን የጀመረች ሲሆን በ2011፣ ባጠራቀመችው ገንዘብ፣ ሚኒባስ ለመግዛትና የጅምላ ማከፋፈያ ሱቅ ለመክፈት ማቀዷ ተጠቅሶላታል፡፡

የኢኮኖሚ ስኬት በመቀዳጀት ምሳሌ ለመሆን የበቁ ጥንዶችም አሉ፡፡ ስኬታቸው በከፊል በትብብር የመስራታቸው ውጤት ነው፡፡ ቀደም ሲል የተጠቀሱት የሲርባ እና ገልቻ ጥንዶች እንደምሣሌ መጥቀስ ይቻላል፡፡ ሌሎች በምሳሌነት የሚጠቀሱት ደግሞ በመካከለኛ የእድሜ እርከን ላይ የሚገኙ የሶሞዶ (ጅማ አቅራቢያ) ጥንድ የንግድ ሰዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ጥንዶች መሬታቸውን ለእኩል የሚያሳርሱ ሲሆን ከብቶቻቸውንም ለእኩል ያረባሉ፡፡ ገቢያቸውን የሚያገኙት ከእርሻ ውጭ አስፍተው በሚንቀሳቀሱባቸው ዘርፎች ሲሆን ሚስትየው የሸቀጣ ሸቀጥ ሱቅ፣ የግብርና ሰብሎች ንግድ (በዋናነት ቡና እና በቆሎ) ላይ ስትሰማራ፣ ባልየው የእህል ወፍጮ በመትከልና በመጠገን እንዲሁም በትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፍ ላይ ተሰማርቶ ይሰራል፡፡ ከዚህም ባሻገር ሰባት የራሳቸውን የእህል ወፍጮ በጋራ ያስተዳድራሉ፡፡

ይሄ ብዝሃነት ያለው የህይወት ታሪኮችና ተሞክሮዎች የበለጠ ውስብስብ የሆነ የገጠር ኢኮኖሚ መፈጠሩን የሚተርክ ሲሆን ዘርፉ ብዙ የኢኮኖሚ ስኬቶች ሊፈጠሩ እንደሚችሉና እርስ በርስ እንደሚደጋገፉ ይጠቁማል፡፡ የኦዳ ሃሮ የታሪክ መስመር (ልዩ ባይሆንም) ስኬታማ ገበሬዎች አካባቢው ያፈራቸው ነጋዴዎችና የንግድ አለም ሰዎች የስኬት እድሎችን እንደሚፈጥሩና ከእነዚህ ስኬታማ ግለሰቦች መኖር መልሰው ተጠቃሚ ሊሆኑ እንደሚችሉ ያሳያል፡፡ ይህ በፊናው የሚጠቁመን፡-

- የገጠር ልማት ውጤቶች የወረዳ ዕቅድን የአካባቢ የገበያ ሰንሰለት መዘርጋት ላይ በማተኮር አካባቢ ላፈራቸው ነጋዴዎችና ለግብርና ምርት ማቀነባበሪያ አካባቢያዊ ኢንቨስትመንት የላቀ ድጋፍ በማድረግ ሊሻሻል ይችላል፡፡ (በተጨማሪም የገጠር ከተሜነት መስፋፋት የተሰኘው አጭር ጽሁፍ "ሁሉን በአንድ ጣራ ኪዮስክ" ማቋቋም መዋዕለ-ንዋያቸውን ለማፍሰስ ፈቃደኛ የሆኑ የገጠር ሥራ ፈጣሪዎችን ይረዳል የሚለውን የሚጠቁም ሃሳብ ይመልከቱ)፡፡

<u>የመንግስት እርምጃዎች፡- መደገፍ፣ ማገድ፣ ስኬትን ችላ ማለት</u>

ምንም እንኳን የተሰባጠረ ቢሆንም፣ የኢኮኖሚ ስኬታማነትን በተመለከተ ይህ አጭር የጥናት መግለጫ፣ ከመንግስት እርምጃዎች ጋር የተያያዙ አንዳንድ ቁልፍ ጉዳዮችን ለመጠቃቀስ ሞክሯል፡፡ እነዚህ የተጠቀሱት ጉዳዮች ለብዙዎች ወሳኝ መሆናቸው ታይቷል፡፡ በአንዳንድ አጋጣሚዎች የመንግስት እርምጃ፤ በቀጥታ የኑሮ መተዳደሪያዎችን ለማሻሻል የታቀደ ሲሆን በጥቅሉም በኢኮኖሚ ስኬታማ በሆኑ ግለሰቦች ጉዞ ላይ አዎንታዊ ውጤት ፈጥሯል (ለምሳሌ፡- በግብርና ኤክስቴንሽን መርሀ ግብር አገልግሎት)፡፡ ሌሎች ቁልፍ ጉዳዮች ለኢኮኖሚ ስኬት ወሳኝ ይመስላሉ፤ ሆኖም የመንግስት እርምጃ በአንድአንድ ሁኔታዎች የተጠበቀውን ያህል ውጤት አላሳየም፡፡ (ለምሳሌ፡- የከብት እርባታ፣ መስኖ፣ "አማራጭ የገበያ አዝርዕት" እና የብድር አገልግሎት ተደራሽነት)፡፡ ከቀረጥና ሌሎች ቁጥጥሮች ጋር በተያያዘ የመንግስት እርምጃ በጥቅሉ አሉታዊ ውጤት እንዳለው ተደርጎ ይታሰባል፡፡ በመጨረሻም፤ ስደት ለኢኮኖሚ ስኬት ከፍተኛ ሚና እንዳለው በመንግስት ችላ ተብሏል (ማጣቀሻ፡- ፍልሰት)፡፡

የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት፡- ስኬታማ ገበሬዎች ተብለው ከሚታወቁት ውስጥ ብዙዎቹ ወይም ሁሉም እንደጠቆሙት፤ ከልማት ሰራተኞች ከመንግስት የስልጠና ፕሮግራሞች የተገኙ የግብርና ኤክስቴንሽን የለውጥ እርምጃዎች፣ ድጋፎችና ምክሮች ጠቅመዋቸዋል፡፡ ከሌሎች ገበሬዎች

ጋር ያደረጉት የልምድ ልውውጥም እንዲሁ፡፡ ነገር ግን፤ ከተወሰኑ ግብአቶች ጥራት፣ ብዛት፣ ወቅታዊነትና ተስማሚነት ጋር የተያያዙ ችግሮችም በብዛት ተጠቅሰዋል (ለምሳሌ፡- ተስማሚ ያልሆነ ምርጥ የበቆሎ ዘር፣ አንድ የአዳዶ ስኬታማ ቡና አምራች፣ በግድ እንዲጠቀም ተደርጓል)፡፡ የግብርና ልማት ሰራተኞች የሙያ ብቃት ደካማ መሆንም በችግርነት ይጠቀሳል፡፡ በጣም ተደጋግሞ የሚሰማው ትችት የግብርና ግብዓቶች የዋጋ ውድነት ሲሆን፤ ይሄም ስኬታማ ገበሬዎች ግብዓቱን በተሰጠው መመሪያ "መጠን" እንዳይጠቀሙ እንቅፋት ሆኖባቸዋል፡፡

መሰናዮ፡- WIDE የጥናት ክትትል ባደረገባቸው ብዙዎቹ ማህበረሰቦች፤ መስኖ የገበሬዎችን ምርታማነት በከፍተኛ መጠን በማሳደግ ረገድ ትልቅ ሚና ተጫውቷል (በተጨማሪም የገጠር ከተሜነት መስፋፋት የሚለውን አጭር ጽሁፍ ይመልከቱ)፡፡ የመስኖ ተደራሽነት ያላቸው ብዙዎቹ ገበሬዎች፣ የመስኖ ልማት መሬታቸውን ለማሳደግ መዋዕለ ንዋያቸውን አፍሰዋል ወይም ለማፍሰስ አቅደዋል፡፡ ቢሆንም ብዙዎቹ እንደጠቀሱት፤ አስተማማኝ ወይም ከፍተኛ የውሃ አቅርቦት ለማግኘት የሚያስፈልገው ወጪ ከፍተኛ መሆን ትልቅ ማነቆ ነው፤ መንግስት ደግሞ በዚህ ረገድ ምንም ተግባር አላከናወነም፡፡ በበርካታ ማህበረሰቦች የመስኖ እርሻ አጀማመር ከመንግስት እርምጃ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፡፡ ለምሳሌ፡- የሶሞዶ ገበሬዎች፣ በመስኖ ማልማትን የቀሰሙት ልምድ ካላቸው የውጭ ሰዎች ነው፡፡ የአዬሌ ኬኬ ገበሬዎች ደግሞ በአካባቢው ዋናውን መንገድ የገነቡት የቻይና ተቋራጮች፣ ውሃ ያገኙበትን መንገድ በመቅሰም ለመስኖ ልማት ተጠቅመውበታል (ማጣቀሻ፡- ለውጥ)፡፡

ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ‹ተለዋጭ› አዝርዕቶች ፡- ለአያሌ ገበሬዎች ስኬት ቁልፉ ምክንያት ከፍተኛ ዋጋ ያላቸውን ‹ተለዋጭ› አዝርዕቶች ማብቀላቸው ነው፡፡ እነዚህ አዝርዕቶች በገበያ ላይ ከፍተኛ ወይም እያሻቀበ የሚሄድ ዋጋ የሚያወጡ ሲሆኑ እኒህ ግለሰቦች ይህንን ሲረዱ ለገበያው ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት ይሄን አዝርዕት የሚያለሙበትን መሬት እያሰፉ መጡ፡፡ ይህ ሁኔታ - በአንዳንድ አጋጣሚዎች ያለምንም የመንግስት ድጋፍ መከናወኑ ተስተውሏል፡፡ ለምሳሌ፡- የባህር ዛፍ ተክል (በኮርማርገፍያ፣ አንድ ስኬታማ ገበሬ ነዐዐሺ ብር ግምት ያላቸው ነዐሺ ዛፎች አብቅሏል)፡፡ ሌላው ጫት ነው (በአዬሌ ኬኬ ከማህበረሰቡ ደረጃ በጣም ከፍ ያለ ሀብት ይታፈስበታል)፡፡ በሌሎች ሁኔታዎች አዳዲስ አዝዕርቶችን መሞከር የሚፈልጉ ገበሬዎች ከኤክስቴንሽን አገልግሎት ተስማሚ ዘሮችን ቢያገኙም ልዩ የምክር አገልግሎት ግን አልነበረም፡፡ ለምሳሌ፡- አንዳንድ ግለሰቦች በሉቃ ሰሊጥን፣ በዶአማ ደግሞ ቅመማ ቅመምን እንደ ገበያ አዝርዕት ማብቀል ጀምረዋል፡፡

የከብት እርባታ እንቅስቃሴ፡- በአያሌ ማህበረሰቦች ከብት ማርባት ተጠቃሚ የሚያደርግ የንግድ እንቅስቃሴ እየሆነ መጥቷል፤ እንደ ባህላዊ የገንዘብ ቁጠባ ዘዴ ከማገልገሉ በተጨማሪ ማለት ነው፡፡ ከብት ማደለብም እንዲሁ ተጠቃሚ የሚያደርግ ዘርፍ ሆኗል፤ አንዳንድ ስኬታማ ግለሰቦችም በስፋት ተያይዘውታል፤ "የእኩል ማደለብ"ን ጨምሮ፡፡ በአዜ ዴቦአ (ከምባታ) አንድ ግንባር ቀደም የሆነ ነጋዴ፣ በዚሁ መንገድ በአንድ ጊዜ እስከ 20 የሚደርሱ በሬዎችን ገዝቶ ያደልባል፡፡ ሌላው ትልቁ ከከብት እርባታ ጋር የተያያዘው እንቅስቃሴ ደግሞ ቀደም ሲል እንደተጠቀሰችው፣ የአዬሌ ኬኬ የወተት ነጋዴ ሁሉ የወተት ላሞችን ማርባትና ወተትና የወተት ተዋፅኦዎችን እያመረቱ ለገበያ ማቅረብ ነው፡፡ ይሄ ለራሳቸው ለገበሬዎቹና ለነጋዴዎች ጥሩ ገቢን ያመጣል፡፡ ሆኖም፤ የከብት

እርባታ ለኪሳራ ሊዳርግም ይችላል፤ በተለይ ዝናብ አጠር በሆኑ ማህበረሰቦች፡፡ ከብቶችን ማጣት ለከፍተኛ ውድቀት ሊዳርግ ይችላል፡፡ ቀደም ሲል የተጠቀሰው የገብለን ገበሬ ጥሩ ምሳሌ ነው፡፡

የሚከተሉት እርምጃዎች፤ የግብርና ኤክስቴንሽን አገልግሎት አዎንታዊ ውጤቶችን የሚያጎለብቱ ሲሆን የመስኖና የከብት እርባታ እንቅስቃሴዎች አቅምንም ያሳድጋሉ፡-

- የግብርና ግብአቶችን አቅርቦት የሚገድበውን የገንዘብ ማነቆ መፍታት፡- ይሄ ማነቆ ስኬታማ ገበሬዎችን ጭምር የሚገዳደር ሲሆን፤ የገንዘብ ማነቆው መፈታት በቂ የግብአቶች አጠቃቀምን የሚያረጋግጥና ምርትን የበለጠ የሚያሳድግ ይሆናል፡፡

የኤክስቴንሽን አገልግሎቶችን ከአካባቢያዊ አውድ አንፃር መቅረጽ፤ አማራጭ አዝርዕትን ለማብቀል ፍላጎት ያላቸውን ግለሰቦች የተሻለ ያግዛል፡፡ የባህላዊ ሰብሎችን ምርት ለማሳደግ አሁን ከሚደረገው ድጋፍ ጎን ለጎን የዘር አቅርቦትና ምክር፣ በመስኖ ከሚያለሙ ገበሬዎች ፍላጎት አንጻር የተቃኘ ማድረግም ጠቃሚ ነው፡፡ የመገናኛ ግንኙነት ቴክኖሎጂን መሰረት ያደረገ መፍትሄና በባለሞያ የታገዘ የምክር አገልግሎት እንደ መንግስት መር የተግባር እርምጃ ሆኖ ሊቀርብ ይችላል፤ በገጠር ከተሜነት መስፋፋት በሚለው አጭር ጽሁፍ እንደተጠቆመው፡፡

የመስኖ አገልግሎቱን ለማስፋትና ለማሳደግ መንግስት ግንባር ቀደም ሆኖ የሚመራበት ሰፊ አማራጭ አለ፡፡ በተለይ ዘላቂ የውሃ አቅርቦት በሚያስፈልግባቸው አካባቢዎች በግለሰቦች አቅም ችግሩ ምላሽ ሊሰጠው አይችልም፡፡ ነባር የመስኖ መሰረተ ልማቶችን መጠገን፣ አግባብ በሆኑ ቦታዎች የጠብታ መስኖን ማበረታታት፣ (ማጣቀሻ፡- የገጠር ከተሜነት መስፋፋት) እንዲሁም የመስኖ መሰረተ ልማቶችን ለመገንባት ተጨማሪ እርምጃዎችን መውሰድ ሁሉ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

- የከብት እርባታ ኤክስቴንሽን መርሀ ግብር ላይ የበለጠ ማተኮር የከብት እርባታ እንቅስቃሴዎችን ይበልጥ ትርፋማ ያደርጋል፡፡ አሁን የተያዘውን የከብት ዝርያ የማዳቀልና የተዳቀሉ ምርጥ ዘሮችን አቅርቦት ማሳደግ፤ ዘመናዊ የከብት እርባታ ዘዴዎችን ግንዛቤ የበለጠ ማሳደግ፤ እንዲሁም ጥራት ያለው የእንስሳት ህክምናን ማስፋፋትና የበለጠ ተደራሽ ማድረግ፡፡ ይሄ ከግለሰቦች አቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች የሚከሰቱ የከብቶች ሞትን ለመቅረፍ፣ ከከብቶች ኢንሹራንስ ትልሞች ጋር ሊተጋገዝ ይችላል፡፡

ቀደም ብሎ እንደተገለጸው፤ ስኬታማ ለሆኑ ገበሬዎች በቂ መሬት እንዲያገኙ ማድረግ፤ ምርታቸውን እንዲያስፋፉና የበለጠ እንዲያድጉ ወሳኝ ነው፡፡

በህጋዊ መንገድ መሬት ለመሸጥና ለመለወጥ የሚያስችሉ ተቋማዊ አሰራሮችን ማጠናከር ይሄን ያቀላጥፈዋል፡፡ በሌላ በኩል፤ በማህበረሰቡ ውስጥ ደካማ የሆኑትን አካላትም ከአደጋ ይጠብቃሉ፡፡ በአግባቡ ለሚሰራ የመሬት ኪራይ ገበያ አስፈላጊ ከሆኑ ሥርዓቶችና ደንቦች ባሻገርም የአካባቢ ባለሥልጣናት ከመሬት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ግጭቶችን መፍታት እንዲችሉ ለማገዝም ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ለምሳሌ፡- በስኬታማ ግለሰቦች የሚለማ የተጨማሪ መሬት ጥያቄና መሬት አልባ ለሆኑ ወጣቶች በሚሰጥ መሬት መሀል የሚነሳ ውጥረትን ለማርገብ መዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ፤ ከከተማ መስፋፋትና ከገጠር መሬት ጋር ተያይዞ የሚከሰት ውጥረትን ለማቅለልም ዝግጁነት ያሻል (ማጣቀሻ፡- የገጠር ከተሜነት መስፋፋት)፡፡

የብድር አቅርቦት፦ በርካታ ገበሬዎች፣ ነጋዴዎችና የንግድ ዓለም ሰዎች፤ በመነሻ ካፒታልነት የብድር አቅርቦት ማግኘታቸው፣ ለስኬታቸው ቁልፍ ሚና መጫወቱን ጠቁመዋል። አንዳንዶቹ መደበኛ ከሆነ የገንዘብ ተቋም ብድር የወሰዱ ሲሆን ይሄ ብዙ ጊዜ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የመንግስትን ድጋፍ ይጠይቃል። ብዙዎች ግን ከመደበኛው የገንዘብ ተቋም ብድር ለማግኘት ከፍተኛ ችግር እንደገጠማቸው ገልጸዋል (ለዚህም ከሚቀርቡ ምክንያቶች መካከል ለማስያዣ የሚጠየቁት መጠን ከአቅማቸው በላይ መሆን፣ ብድር የመጠየቂያው አሰራር ውስብስብና አድካሚ መሆን ይጠቀሳሉ)። በሌላ መልኩ ደግሞ ብድሩ የማይረባ (በጣም አነስተኛ) እንደሆነ ጠቁመዋል። በዚህም የተነሳ ብዙዎች መደበኛ ያልሆኑ የብድር አገልግሎቶችን ለመጠቀም ተገደዋል። ለምሳሌ፦ ቀደም ሲል የተጠቀሰው ከነጋዴ ጓደኞቹ ጋር ገንዘብ የሚበዳደረው የዶአማ ወጣት ነጋዴ ሊጠቀስ ይችላል። እቁቦች፤ ታማኝነትን መሰረት ባደረገው ባህሪያቸው፤ ከወለድ ነጻ በመሆናቸውና በግትር አቋም የታጠሩ ባለመሆናቸው የተወደሱ ሲሆን አይነተኛ የመነሻ ካፒታል ምንጭ በመሆንም ትልቅ ሚና ተጫውተዋል። ለምሳሌ፦ ቀደም ሲል የተጠቀሱት የሲርባ ወጣት ጥንድ ነጋዴዎች በሳምንት 2ሺ ብር ከሚጥሉት ዕቁብ በደረሳቸው 200ሺ ብር ካፊቴሪያ በመክፈት የንግድ እንቅስቃሴያቸውን ማስፋት ችለዋል። ከዚያም በመቀጠል ሌላ የ400ሺ ብር ዕቁብ መጣል ጀምረዋል።

ይህ የሚጠቁመው፤ በመደበኛ የብድር አገልግሎት አማካኝነት በቂ የመነሻ ካፒታል ተደራሽነትን ለማሳደግ ለሚሹ ወገኖች ክፍተት መኖሩን ነው - መንግስት በገጠር አካባቢዎች የባንክ አገልግሎቶችን ለማስፋፋት ከቀረጸው ግብ ጋር በሚጣጣም መልኩ። መንግሥት የሚከተሉትን ከግምት ውስጥ ሊያስገባ ይችላል፦

- ለንግድ አመቺ የሆኑ አቀራረቦችን እንዲቀርጹ አነስተኛ የገንዘብ ተቋማትን ማበረታታት ያሻል። ለምሳሌ፦ ቢሮክራሲውን ረገብ ማድረግ፣ የቢዝነስ ፕሮፖዛሎችን ከተቀመጠው የብድር ጣሪያዎች ጋር ከማወዳደር ይልቅ በብቃታቸው መመዘን እንዲሁም የብድር ማስያዣ መስፈርቶችን እንደ የሁኔታው መቅረጽ የሚያስችሉ መንገዶችን መፈለግ።
- በገጠር ማህበረሰቦች የስኬታማ ግለሰቦችን የባንክ ተጠቃሚነት የሚያሳድግ አዳዲስ የብድር ማስያዣ እሴቶችን መፍጠር - ለምሳሌ፦ መንግስት በቅርቡ ይፋ ባደረገው በገጠር አካባቢዎች "ዘመናዊ ቤቶች"ን የመገንባት ግብ መሰረት ከፍ ላሉ እሴቶች መስሪያ የሆኑ ግብዓቶችንና ቤት በቀዬው እንዲያገኝ ማገዝ።

ሰደት፦ የWIDE ጥናት ከትትል ባደረገባቸው ማህበረሰቦች፣ በርካታ ግለሰቦች ለስኬት የበቁት በስደት እንደሆነ ይናገራሉ። አንዳንዶቹም በስደት ሰርተው ያጠራቀሙትን ገንዘብ እንደ መነሻ ካፒታል ተጠቅመውበታል - በአዜ ዴቦአ ሆቴልና የጭነት መኪና እንዳለው ስኬታማ ነጋዴ። ይሄ ሰው ከደቡብ አፍሪካ ስደት የተመለሰው 1.4 ሚሊዮን ብር ይዞ ነው። ሌሎች ደግሞ ከባህር ማዶ ዘመዶቻቸው የሚልኩላቸውን ገንዘብ ጥበብ በተሞላበት መንገድ በንግድ ሥራ ላይ አውለውታል። ለምሳሌ፦ በግራር (ጉራጌ) አንድ ስኬታማ ገበሬ/ነጋዴ፣ ሴት ልጆቹ የሚልኩለትን ገንዘብ፣ ከራሱ ገቢ ጋር በማጣመር ልኳንዳ ቤት ከፍቷል።

- ፍልሰት ላይ በሚያተኩረው አጭር ጽሁፍ ውስጥ የበለጠ ተብራርቶ እንደቀረበው፤ መንግስት የዜጎች ስደት፣ ለኢትዮጵያ የገጠር ማህበረሰቦች ዕድገት ያለውን አዎንታዊ ሚና ከግምት ውስጥ በማስገባት እርምጃዎችን ሊወስድ ይችላል። ይሄም ሌሎች ብዙ የገጠር

ስደተኞች ስኬታማ እንዲሆኑና በዚህ መንገድ ለትውልድ ቀዬአቸው የሚያበረክቱትን አስተዋጽኦ ማሳደግ እንዲችሉ በር ይከፍታል።

ግብር እና የንግድ ቁጥጥሮች፡- ከግብርና ከንግድ ቁጥጥር ጋር የተያያዙ የመንግስት እርምጃዎች ብዙውን ጊዜ ለኢኮኖሚ ስኬታማነት መሰናክል መሆናቸው ይነሳል። በአብዛኞቹ ማህበረሰቦች ስኬታማ ግለሰቦች፣ በተለይ ነጋዴዎችና የንግዱ ዓለም ሰዎች የግብር አሰባሰብ አሰራሩን ግልፅነት የሌለው አድርገው ይመለከቱታል። ምክንያቱም በምን መሰረት የግብሩ መጠን አንዳንድ ጊዜ ቋሚ እንደሚሆንና ሌላ ጊዜ ደግሞ እንደሚቀየር አይረዱትም። የግብር ስርዓቱ ለምን ወጥ እንዳልሆነም አይገባቸውም። ለምሳሌ፡- በሶሞዶ ግብር ከፋይ የሆኑ የሱቅ ባለቤቶች፤ በስፋት ቡና የሚነግዱ የሀገሩ ሰዎች ቀረጥ እንደማይከፍሉ ጠቁመዋል፤ በኡዳ ሀሮ ደግሞ ፈቃድ ያላቸው የእህል ነጋዴዎች፣ ፈቃድ ከሌላቸው ጋር የመፎካከር ዕጣ ፈንታ እንደገጠማቸው ተናግረዋል።

- የንግድ ፈቃድንና የግብር ልኬትን በተመለከተ ግልፅነትና ወጥነት ያለው አሰራር መዘርጋት አካባቢያዊ ንግድንና የንግድ እንቅስቃሴን ለማበረታታት ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል። እነዚህ ከሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎሜሽን ዕቅድ ፖሊሲ ጋር የሚስማሙ ሲሆኑ ከላይ የቀረቡት ማስረጃዎች በአፋጣኝ መተግበር እንዳለባቸው ይጠቁማሉ።

<u>መቋቋም፣ ዘላቂነትና የኢኮኖሚ ብዝሃነት</u>

አንዳንድ ግለሰቦች ዘላቂ የስኬት መሰረት የፈጠሩ ይመስላሉ (ለምሳሌ፡- ከስደት የተመለሰው የአዜ ዴቦአ ወጣትና የሶሞዳ ጥንድ የንግድ ሰዎች)። ግን በብዙ አጋጣሚዎች፣ በተለይ የምግብ ዋስትና ባላረጋገጡና ከፊል አርብቶአደር በሆኑ ማህበረሰቦች፣ ስኬታቸው ከባድ የተፈጥሮ አደጋን መቋቋም ይችል እንደሆነ ግልፅ አይደለም። ለምሳሌ፡- በሲርባ፣ አንዲት አዛውንት የቤተሰብና እርሻ አስተዳዳሪ፤ ወንድ ልጇንና የረዥም ጊዜ የእርሻ ሰራተኛዋን በሞት ባጣችበት ዓመት መጨረሻ ላይ የእህል ጎተራዋ በእሳት ወድሞባታል። ለብዙዎቹ በዝናብ ላይ ለሚተማመኑ ስኬታማ አርሶአደሮች፣ ከምርት የሚያገኙት ገቢ፣ ምርቱን ለማምረት ካወጡት ወጪ በምን ያህል የበለጠ ወይም ያነሰ መሆኑን የሚወስንላቸው የአየር ጠባይ ሁኔታው ነው። ከሰብል ምርት ዋጋ መዋዠቅ ወይም መቀነስ አሊያም ኪሳራ አንጻር የሚነሱ የዘላቂነት ጥያቄዎችም አሉ።

ሁሉም ስኬታማ ግለሰቦች፤ አደጋን ለመቋቋምና ለዘላቂነት ጥያቄዎች የሰጡት ምላሽ የኢኮኖሚ ዘርፎችን በዓይነት ማስፋት ነው። አርሶ አደሮች፤ የተለያዩ ዓይነት ሰብሎችን ከማምረት ባሻገር የመሬቱን መጠን ለእያንዳንዱ ሰብል አመቺ እንዴት ሊሆን እንደሚችል በመወሰን (ለምሳሌ፡- ከሰብሉ ምርት ከሚጠብቁት ዋጋ ወይም ትርፋማ ከሆነ የእርሻ አመት በኋላ ተጨማሪ ሌላ አዝርዕትን ለመሞከር በአቀዱት አንፃር፤ ለምሳሌ፡- በሶሞዶ አንድ ትልቅ ቡና አምራች፣ የበለጠ ብዙ ጫት ማምረት እንደጀመረው ማለት ነው። ነጋዴዎችም የሚነግዱትን የምርት ዓይነት አስፋፍተዋል። ለምሳሌ፡- በዶአማ አንድ የሙዝ፣ የበቆሎና የከብት ነጋዴ፣ ከወትሮው ንግዱ በተጨማሪ የሸቀጣ ሸቀጥ መደብር ለመክፈት እቅድ ነድፏል። የንግድ ሰዎች በአያሌ የተለያዩ የንግድ እንቅስቃሴዎች ላይ መዋዕለ ንዋያቸውን አፍሰዋል። ቀደም ሲል እንደተጠቀሱት የሶሞዶ ጥንድ የንግድ ሰዎች ምሣሌነታቸው የሚዘነጋ አይደለም።

በጣም የተለመደው ሂደት፣ አንድ አርሶ አደር፣ በአንድ ወይም በበርካታ ከእርሻ ውጭ በሆኑ ዘርፎች ላይ መዋዕለ ንዋዩን ሲያፈስ ስኬታማ መሆኑ (በአበጀና ኢዛና ጥናት ውስጥም ይገኛል፤2011)[7] እርሻ በሁሉም ማህበረሰቦች፣ ለስኬት የመነሻ መሰረት እንደሆነ ያሳያል። በአዳዶ፣ አንድ ትልቅ ቡና አምራች እንዲሁም ከብት የሚያደልብ፣ የሸቀጣሸቀጥ ሱቅ የከፈተ፣ ዳቦ ቤትና ሻይ ቤት/ምግብ ቤት ያለው ገበሬ እንዳስረዳው፡- በዘርፈ-ብዙ እንቅስቃሴዎች ላይ መሳተፍ ግለሰቡ ከአንዱ ዘርፍ ያገኘውን ገቢ ሌላኛውን ለማጠንከር፣ ለማስፋፋት ወይም በተጨማሪ አዲስ ዘርፍ ላይ ለመሳተፍ ያስችለዋል። በአብዛኛው የሚጠቀሱ የኢኮኖሚ ዘርፍ ዓይነቶችን የማስፋፊያ ጥርጊያዎች፡- የግብርና ምርቶች ንግድ፣ ወፍጮ ቤቶች ወይም ሱቆች፣ ትራንስፖርት/የእንግዳ አቀባበል አገልግሎቶችና ለኪራይ የሚሆኑ ክፍሎችና ቤቶች በማህበረሰቡ ቀዬ ውስጥ ወይም በአቅራቢያው በሚገኝ ከተማ ውስጥ መገንባትን የመሳሰሉት ናቸው።

እነዚህ መረጃዎች ወደ ሚከተሉትን ነጥቦች ያመራሉ፡-

- መጀመሪያ፤ የኢኮኖሚ ዘርፍ ዓይነቶችን ማስፋት የግለሰብ ኢኮኖሚያዊ ስኬትን የአደጋ ተቋቋሚነትና ዘላቂነት በማጎልበት ረገድ ያለውን ሚና ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፣ የተወሰኑ የኢኮኖሚ ዘርፎች ብቻ ተለይተው እንዲስፋፉ ወይም እንዲተዋወቁ ሲደረግ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። በአንድ ሰብል ላይ የሚተማመኑ ገበሬዎች፤ ከፍተኛ የገቢያ ዋጋ ያላቸው ሰብሎችም ጭምር፣ ኪሳራ ሊያመጡባቸው ይችላሉ። ለነጋዴዎች፣ የአንድ ምርት የገበያ መቀዛቀዝ፣ በሌሎች ምርቶች የተሻለ ገበያ ሊካካስ ይችላል። መንግስት፤ በዓይነተ-ብዙ የኢኮኖሚ ዘርፎች ላይ መንቀሳቀስ ያሉትን በርካታ ጥቅሞች ይበልጥ በተሟላ መልኩ በመገንዘብ፣ ከግለሰቦች ምርጫ አንፃር ምላሽ መስጠትና በአሁኑ የገጠር ኢትዮጵያ ማህበረሰቦች፣ ይህን የበለጠ ለመደገፍ በሚያስችለው መልኩ ፖሊሲውን ሊቃኝ ይገባዋል።
- የስኬታማ ጉዞዎች ዘላቂነትና ተቋቋሚነት፣ የተፈጥሮ አደጋዎችን (ለምሳሌ፡- የከብት ሞት እና የጤና እክሎች) የሚታደጉ የተለያዩ የመድን ዋስትና ትልሞችን በመፍጠር ሊጎለብት ይችላል (ባህላዊ የመድን ዋስትና ተቋሞችን፡- ለምሳሌ፡- እድር፣ የከብት እድር)። ኢ-እኩልነት በሚለው አጭር ጽሁፍ ላይ እንደተገለጸው፤ እንዲህ መሰሎቹን የኢንሹራንስ ትልሞች ማስፋፋት፣ የገጠር ማህበረሰቦች ድሃና ለችግር ተጋላጭ አባላትን ለመታደግ ይጠቅማል። ከዚህ በላይ በማህበረሰቡ ውስጥ በሀብት ላይ ካሉት ለድሆቹ በማድላት የማካካሻ እና የባህላዊ የመረዳጃ መንገዶችንም ያጎለብታል።
- ስኬታማ ግለሰቦች ሊሰማሩባቸው የሚያቅዷቸውን ኢንቨስትመንቶች አድማስ ማስፋት፣ ስኬታቸውን ለማጠናከር ያግዛቸዋል። የገጠር ከተሜነት መስፋፋት የሚለው አጭር ጽሁፍ እንደሚጠቁመው፤ ይሄን ማድረጊያ አንዱ መንገድ፤ ለገበያ አዋጭ የሆኑ ምርቶችን ወይም አገልግሎቶችን በተመለከተ ምክር የሚለግሱ፣ ሥራ ፈጣሪዎችን ከሥልጠናና የብድር ዕድሎች ጋር የሚያስተሳስሩ፣ የመሬት አቅርቦት ችግሮችን ለመፍታት የሚያግዙ፣ "ሁሉን አገልግሎት በአንድ ጣራ ሥር" የሚያቀርቡ አካባቢያዊ ኪዮስኮችን ማቋቋም ነው።

[7] Abeje Berhanu and Ezana Amdework, 2011, *Peasant Entrepreneurship and Rural Poverty Reduction: the case of Model farmers in Bure Woreda, West Gojjam Zone.* Forum for Social Studies monograph No.8. Forum for Social Studies, Addis Ababa.

- ከላይ የቀረቡት ማስረጃዎች፣ የግለሰብ እንቅስቃሴዎችን መደገፍ ያለውን ፋይዳ ያሳያሉ፡፡ ነገር ግን፤ አንዳንድ የኢንቨስትመንት ዘርፎች በጣም ስኬታማ ከሆኑ ግለሰቦችም አቅም በላይ ናቸው፡፡ በእንዲህ ያሉት ሁኔታዎች፣የህብረት ሥራ ማህበራት ጠቃሚ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ - ለምሳሌ፡- በትላልቅ ማሽኖች የሚከናወኑ የእርሻ ሥራዎችን በማገዝና በምርት ማቀነባበር እንቅስቃሴዎች ላይ በቀጥታ በመሳተፍ፡፡ ነገር ግን፤ (ኢ-እኩልነት፤ ሴቶች፤ እና ለውጥ በሚሉት ጽሁፎች ላይም *ተጠቅሷል)* የWIDE ጥናት መረጃ እንደሚጠቁመው፤ የህብረት ሥራ ማህበራት የግለሰብ እንቅስቃሴዎችን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመደገፍና ለማስፋፋት ይችሉ ዘንድ አስፈላጊነታቸው አሌ ለማይባለው የአስተዳደር አቅም ግንባታና የቁጥጥር መንገዶች ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል፡፡

<u>ስኬታማ ግለሰቦች እንዴት ነው ኢንቨስት የሚያደርጉት?</u>

አብዛኞቹ ስኬታማ ግለሰቦች፤ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎቻቸውን ለማጠንከር ወይም በዓይነት ለማስፋፋት ብቻ ሳይሆን የአኗኗር ደረጃቸውን ለማሻሻል ኢንቨስት ያደርጋሉ፡፡ የዚህም መገለጫ (የተሻሉ መኖሪያ ቤቶች፣ በተሟሉ ቁሳቁሶች የተደራጀ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፡- በሶሞዳ፣ ጥንድ የንግድ ሰዎች ዘመናዊ ቪላ ቤት) ሰርተዋል፡፡ በብዙዎቹ ላይ እንደታየው፣ ኢንቨስትመንታቸው ከከተማ ጋር ቁርኝት ያለው ነው፡፡ ምክንያቱም - በከተማ ላይ መገንባት ንግድ ለመክፈት ወይም ለማከራየት አልያም ልጆቻቸውን ለማስተማር እና ይሄንን የመሳሰሉ ተግባሮችን በአንድ ላይ ለማከናወን ያግዛል፡፡ ለምሳሌ፡- የአዜ ዴቦአ ስኬታማ ገበሬ በዱራሜ ትልቅ ህንፃ ገንብቷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ስኬታማ ግለሰቦች፤ በልጆቻቸው ወይም በራሳቸው ትምህርት ላይ ኢንቨስት ያደርጋሉ ወይም ለማድረግ ያቅዳሉ፡፡ ለምሳሌ፡- አንድ የጋራ ጋዶ ስኬታማ ገበሬ፤ ልጆቹ በሙሉ የትምህርት እድል እንዲያገኙ ካደረገ በኋላ፣ እሱ ራሱ በሂሳብ አያያዝ ትምህርት ዲፕሎማ ለማግኘት በመማር ላይ ይገኛል፡፡

አርአያዎች (ሞዴሎች)

የመልካም አስተዳደ
ር፡ ባህሪያቱ (Characteri
stics of Good Goverance)
1- ተሳትፏዊ/Participatory/
2- የጋራ መግባባት/Consensus/
3- ቶሎ ምላሽ መስጠት/Responsiven
ess/
4- ግልፀኝነት/Transparency/
5- ተጠያቂነት/Accountability/
6- ፍትሀዊነት/Fairness or equit
able & Incluesvei
7- የህግ የበላይነትን መከተል/The
Rule of Law/
8- ቀልጣፋነትና ውጤታማነት
/Efficientive/

የትራንስፎርሜሽን አርኢያዎች (ሞዴሎች) እና እውነታዎች

የWIDE የውይይት መነሻ አጭር መግለጫ ቁ. 9/...10[1]

ዋና ዋና ነጥቦች ከWIDE የጥናት መረጃዎች

- የWIDE ጥናት፤ በእጅጉ የተነቃቃ መንግስት መር የገጠር ትራንስፎርሜሽን ጉዞን ይሰንዳል። ይህም ብቻ አይደለም፤ በቀበሌና በንዑስ ቀበሌ ደረጃዎች በቁጥር ላይ ከተመሰረቱ ግቦች በተጓዳኝ፣ ለዓይነተኛ ሂደት በቂ ትኩረት በመስጠት፣ ከትራንስፎርሜሽን የሚገኙ ውጤቶችን ማሻሻል እንደሚቻልም ጥናቱ ይጠቁማል።
- በቀበሌና "በልማት ቡድን" አመራሮች ላይ ተደራራቢ ሃላፊነቶችና ከባድ የስራ ጫናዎች መኖራቸው፣ የWIDE ጥናት ባካተታቸው አካባቢዎች የሚከናወኑ የልማት የለውጥ እርምጃዎችን ጥራት ሲያጓድሉ የታዩ ተደጋጋሚ ክስተቶች ናቸው። ይህ አዝማሚያ አንዳንዴ ደግሞ ማህበረሰቡ በፍትሃዊነት ወይም አካትችነት ላይ ያለውን አመኔታ እንዲያጣ የሚያደርግ አሉታዊ ተጽዕኖ ሲፈጥርም ታይቷል።
- ውጤቶችን ለማሻሻል፣ የቀበሌ አመራሮች፣ የእያንዳንዱን ማህበረሰብ የተለዩ ፍላጎቶች በቅርበትና በቀጣይነት ታሳሚ የሚያደርጉ ዕቅዶችንና ማዕቀፎችን እንዲቀርጹ የበለጠ እገዛ ሊደረግላቸው ይገባል።
- የኢትዮጵያ መንግስት፣ በወረዳና በቀበሌ ደረጃ በሚገኙት ሶስቱ የመንግስት አካላት መካከል ያሉ ግንኙነቶችን ጠቃሚ በሆነ መልኩ በመገምገም፣ የህግ አውጪውንና የህዝብ ተወካዮችን መዋቅሮች ነጻነት፣ አካባቢያዊ ተደራሽነትና ለዜጎች ያላቸውን ተግባራዊ ጠቀሜታ ለማጎልበት የሚያስችሉ መንገዶችን ሊቀይስ ይችላል።
- በቀበሌ ሊቀመንበሮችና በአስፈጻሚ አካላት መካከል ያሉ ግንኙነቶችም፣ ተጠያቂነትን ለማጎልበትና የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን ለመከታተል በሚደረግ ጥረት ውስጥ እንደ አንድ ወሳኝ የጅማሬ ምዕራፍ ይታያል።

---

[1] ይህ አጭር የጥናት መግለጫ፤ በWIDE የውይይት መነሻ አጭር የጥናት መግለጫዎች ሁለተኛ ጥራዝ (ስብስብ) ውስጥ ከተካተቱት አስር መግለጫዎች አንዱ ነው። መግለጫው፤ በሣራ ሾን በ2014 ዓ.ም ነው የተዘጋጀው። አዘጋጇ፤ መግለጫው በዓለም ባንክ J-GAM ትረስት ፈንድ አማካኝነት ለተደረገለት የገንዘብ ድጋፍ ልባዊ ምስጋናዋን ታቀርባለች። በተጨማሪም የጥናት ሪፖርቱን በማርቀቅ ሂደት የተሳተፉና አጭር የጥናት መግለጫው የትኩረት አቅጣጫ እንዲሰላ እገዛ ያደረጉ ሌሎች የጥናት ቡድን አባላትና ባለሙያ ገምጋሚዎች፣ ለሥራው ለሰጡት ጊዜና ድጋፍ ጥልቅ ምስጋናዋን ትገልጻለች። ሌሎች ምስጋናና ዕውቅና የሚያሻቸውም አሉ፦ (1) ለዓመታት የጥናት መግለጫው የተዘጋጀበትን መረጃዎች ያሰባሰቡና ያደራጁ የጥናት መኮንኖችና ተቆጣጣሪዎች ሙሉ ጊዜያቸውን ሰጥተው ላበረከቱት አስተዋጽኦ፤ (2) በሶስት ዙሮች ለተካሄደው የWIDE ጥናት የገንዘብ ዕገዛ ላደረጉ የተለያዩ ድጋፍ ሰጪ ተቋማት፤ እና (3) በኢልምተ ሰብሳቢነትና በኢኮኖሚ ፖሊሲ ትንተና ክፍሉ በWIDE አጭር የጥናት መግለጫዎች ሁለተኛ ጥራዝ ላይ ለመወያየት መጋቢት 28 ቀን 2016 ዓ.ም በተዘጋጀው መድረክ ላይ የተሳተፉ ከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣናት፣ ላሳዩት ፍላጎትና ለከፈሉት የጊዜ መስዋዕትነት--- ምስጋና ይገባቸዋል። የጥናት መግለጫው፤ በከፍተኛ ደረጃ በተዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ፣ ከመንግስት ባለሥልጣናት ጋር በተደረገው ውይይት የተሰጡ አስተያየቶችን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ከለሳና ማሻሻያ ተደርጎበታል። አጭር የጥናት መግለጫው፤ የኢትዮጵያ የልማት ምርምር ተቋምን (ኢልምተ) ወይም የኢትዮጵያ መንግስትን አሊያም የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርጉለትን የልማት አጋሮች አመለካከትም ሆነ አቋም አይወክልም፤ ይልቁንም የፖሊስ ውይይት ለማነቃቃት የታለመ ነው። ሌሎች የጥራዝ ሁለት የውይይት መነሻ አጭር መግለጫዎችንና የጥናትና ምርምር ውጤቶችን በhttp://ethiopiawide.net/ ድረ-ገጽ ላይ ማግኘት ይቻላል።

- የሞዴሎች ስርዓት ተግባራዊ ውጤታማነት፣ ከግብርና ልማት እና ከጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ጋር ያሏቸው ግንኙነቶችና የሚጫወቷቸው ሚናዎች እንዲሁም በሰፊው ማህበረሰብ ላይ በምን መልኩ ተጽዕኖ ያሳድራሉ የሚሉት ጉዳዮች በሙሉ መገምገም ይገባቸዋል፡፡ የWIDE ጥናትም በአስተዳደራዊና በማህበረሰባዊ አመለካከቶች መካከል ተደጋጋሚ ልዩነቶች እንደሚከሰቱ አመላክቷል፡፡
- በሥራ አስፈጻሚ፣ በፖለቲካዊና በልማት መዋቅሮች ውስጥ የሴቶችን ተሳትፎ ማሳደግ እንዲሁም በወጣትነት የዕድሜ ክልል ውስጥ ለሚገኙ የገጠር ነዋሪዎች የተለየ ትኩረት መስጠት አዎንታዊ ለውጥ ለማስመዝገብ እንደሚያስችልም በጥናቱ የተገኙት መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡
- ጠንካራና የተቀናጀ ፖለቲካዊ አመራር፤ ድሃዎች ን ተጠቃሚ ያደረገ ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ለማስመዝገብ በሚደረገው ጥረት ውስጥ ቁልፍ ሚና የሚጫወት ሲሆን የቀበሌና የወረዳ አመራሮች መንግስታዊ ካልሆኑ ወይም ከፖለቲካው ጋር ንክኪ ከሌላቸው አካላት ጋር ያላቸውን ትብብር ወይም የእውቀት ልውውጥ እንዲያሳድጉ ድጋፍ ሊደረግላቸው እንደሚገባም የWIDE መረጃ ይጠቁማል፡፡
- የኢትዮጵያ መንግስት፣ በአካባቢያዊ አስተዳደርና የፖሊሲ የትግበራ ሂደት ሞዴሎች ላይ ፍተሻና ሙከራ የሚያከናውን የምሁራን ወይም የልሂቃን ቡድን የማቋቋም አማራጭን ቢያጤንም መልካም ነው፡፡ ኢኮኖሚው ብዝሃነት እያገኘ፣ የኮሙኒኬሽንና የወረዳ ተቋማዊ አቅም እየተለወጠ ሲሄድ፣ መሰል ቡድን ማቋቋም፣ ማህበረሰቦች በአካባቢያቸው ያፈሩትን ምርጥ ተሞክሮ ይዘው እንዲዘልቁ፣ እንዲያስፋፉ ወይም እንዲያሳድጉ በማድረግ ረገድ ሊያግዛቸው ይችላል፡፡

<u>መግቢያ፡- የጥቃቅን አቅምን አሟጦ መጠቀም</u>

የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ በወርሃ ታህሳስ 2010 በተደረገላቸው አንድ ቃለመጠይቅ ላይ፣ ሥርዓት ለመፍጠር የአገሪቱ መንግስት ያለውን ቁርጠኝነት በተመለከተ አስተያየታቸውን ሲሰጡ እንደሚከተለው ነበር፡፡

> *"እያንዳንዱ ቡድን፣ እያንዳንዱ መንደር፣ የየራሱን ዕቅድ መቅረጽ ይችላል [ይህም…] ሰዎች በአገር አቀፉ ዕቅዳችን ጥላ ሥር ሆነው፣ የራሳቸውን አቅምና ጉልበት ለማውጣት፣ የራሳቸውን ጥሪት አሟጠው ለመጠቀም የሚያስችላቸው ነው::"*[2]

በWIDE የተፈጠረው የመረጃ ቋት፣ ትልቁ ፋይዳው፣ ሰፊውን የገጠር ህይወት ወካይ በሆነችው በዚህች በትንሿ መንደር ዜጎች በዕውን እየኖሩት ያለውን መሰረታዊ ቀጣይ ለውጥን ግንዛቤ ማሳደጉ ነው፡፡ ይህን የሚያደርገውም የሚበጀውንና የማይበጀውን በማመላከትና ማህበረሰቡ ሂደቶችን በምን መልኩ እንደሚገነዘባቸው፣ አንዳንዴ ደግሞ አዛብቶ እንደሚያያቸው በማሳየት ነው፡፡ ይህም ብቻ አይደለም፤ ተጎራባቾች ከራሳቸው፣ ከእድሜ እኩዮቻቸውና ከቤተሰቦቻቸው ወይም

[2] የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በ5ኛው ዓለም አቀፍ የፌደራሊዝም ጉባኤ ላይ በሾን ሆሊሃን የተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ፤ ከኢትዮጵያ ፌደራሊዝም፡ http://www.ethiopianfederalism.org/ ላይ የተገኘ ቪዲዮ፡፡

ከአካባቢያቸው አስተዳዳሪዎች፣ የህዝብ ተወካዮች፣ ፖለቲከኞችና የዕድሜ ባለጸጎች ጋር በጋራም ሆነ በተናጠል በሚያከናውኗቸው ስራዎች ካገኙት ልምድ በመነሳት በልማት አሉታዊና አዎንታዊ ተጽዕኖዎች ላይ ያላቸውን አመለካከቶች እንዴት በሚገርም ሁኔታ ሊቀያይሩ እንደሚችሉምያመለክታል።

የWIDE3 የማህበረሰብ አጭር መግለጫዎች፣ ከ2010 አንስቶ፤ በተነቃቃ የለውጥ ሂደቶች የታጀበ መንግስት-መር የገጠር ትራንስፎርሜሽንና በዚህም ሳቢያ የተፈጠሩትን ፈጣንና ተጠቃሽ የለውጥ ሂደቶች ይሰንዳል። ብዙዎቹ፣ ለበርካቶች በጉልህ በሚጠቀስ መልኩ ምርታማ፣ አዋጪ ወይም ትርፋማ ሲሆኑ አብዛኛውን ጊዜም ተሳትፎ ያደረጉትን ያማከሉ ናቸው። ጥናቱ ከዚህ ባሻገርም፣ ከለውጥ ጋር ተያይዘው የመጡ ተስፋ መቁረጦችን፣ ጭንቀቶችን፣ ውጥረቶችንና ቅሬታዎችን የተመለከቱ የዳበሩና ጠቃሚ ማስረጃዎችንም ይሰጣል።

ይህ የውይይት መነሻ አጭር መግለጫ፣ ከኢትዮጵያ የትራንስፎርሜሽን ሞዴል የተገኙ ውጤቶችን በምን መልኩ ማሻሻል ይቻላል የሚለውን ጉዳይ በቀጣይነት ለማጤን በግብዓትነት እንዲውል ታስቦ እንደመዘጋጀቱ፣ በሁሉም ወይም በብዙዎቹ የ WIDE ማህበረሰቦች በተደጋጋሚነት የሚታዩና የባሰ ችግር ያለባቸውን አንዳንድ አሰራሮች የሚዳስስ ነው። ትኩረት የሚሰጠውም ከገጠመኞች ለዘለሉና ስር ለሰደዱ አካሄዶች ነው። የፖሊሲ አማራጮችን ባይሰጥም፣ የኢትዮጵያ መንግስት ፖሊሲ አውጭዎችና የልማትአጋሮቻቸው፣ የገጠሩ ህዝብ ተዳፍኖ የቆየ ውስጣዊ አቅሙን፣ ኃይልና ጉልበቱን፣ ከታመቀበት አውጥቶ እንዲያቀጣጥልና እንዲገለግስ ለማድረግ በሚያከናውኑት ቀጣይ የትብብር ጉዞአቸው፣ የሚያተኩሩባቸው ጉዳዮችንና ታሳቢዎችን በየጭብጣቸውና በየፈርጃቸው ነቅሶ ያወጣል።

<u>ለእያንዳንዱ ማህበረሰብ የሚሰሩ "ማዕቀፎች"</u>

የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር እንዳሉት፣ የኢትዮጵያ የልማት ራዕይ አንዱ ጥንካሬው፣ ለብዝሃነት እውቅና መስጠቱና ለማነልበት ትኩረት መስጠቱ ነው። የWIDE 3 ጥናት አንኳር ነጥብም፣ ይህ ብዝሃነት ወይም ልዩነት ከክልላዊ መንግስት ወይም ወረዳ እስከ አነስተኛ የመንደር ደረጃ ይዘልቃል የሚል ነው። ከቀበሌና ከንዑስ ቀበሌ (ጎጥ) ወይም ዞን እስከ ልማት ቡድኖች፣ የአንድ ለአምስት አደረጃጀቶች፣ ቤተሰቦችና ግለሰቦች ድረስ ይዘልቃል። ይህም ማለት፣ ከልማት የለውጥ እርምጃዎች ጋር በተያያዘ "ለአንዱ የተሰፋው ለሁሉም እንደማይበቃ" በጣም ግልጽ ነው። በWIDE የጥናት ግኝቶች በተደጋጋሚ የሚስተጋባው መሰረታዊ መልዕክትም ይሄው ነው።

የWIDE3 መረጃ፣ በንዑስ ቀበሌ ደረጃ የሚከናወኑ የልማት እንቅስቃሴዎችና ጥረቶች መጠነ ርዕይ ሰፊና ከፍ ተደርጎ የታቀደበትና አብዛኛውን ጊዜም በእጅጉ ውጤታማ የሆነበትን ብሄራዊ አውድ ሰንዷል። የዲዛይንና የትግበራ አካሄዳቸው ሁልጊዜም በወረዳ ወይም በከፍተኛ ደረጃ ባሉት አመራሮች የሚመራ ነው። ይህም ጠንካራ “የአቅርቦት ወገን” አመራር መኖር፣ በአንዳንድ የሽግግራዊ ሁኔታዎች[3] ውስጥ የተፋጠነ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ለማስመዝገብ ቁልፍ ሚና ሊጫወት

[3] Booth, David (2011) ‘Working with the Grain and Swimming Against the Tide: Barriers to Uptake of Research Findings on Governance and Public Services in Low-Income Countries’, *APPP Working Paper* no.18, April 2011

ይችላል ከሚለው ጥናት ጋር የሚሄድ ነው፡፡ ይህ አካሄድ ከፍ ባለው ደረጃ ላይ አዎንታዊ ውጤቶችን (ለምሳሌ፡- በምዕተ ዓመቱ የልማት ግቦች) አስመዝግቧል፡፡ ነገር ግን፣ የጥቃቅኑን ደረጃ አጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታና የየቀበሌዎችን ወይም ጎጦችን ወይም ንዑስ ቀበሌ ዞኖችን የተለየ ፍላጎት በበቂ ሁኔታ ጠንቅቆ አለመገንዘብ፣ ተገቢ ወዳልሆኑ ወይም በቅጡ ወዳልተተገበሩ "ማዕቀፎች" ሊያመራ እንደሚችል፣ ይህም በግለሰቦች፣ በማህበረሰቦችና በወረዳ አስተዳደሮች ዘንድ ተስፋ መቁረጥን እንደሚፈጥር የWIDE 3 መረጃ፣ በተጨባጭ ማስረጃ ያሳያል፡፡

ምንም እንኳን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መንግስት እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ጥረት ቢያደርግም፣ በርካታ የWIDE ጥናት አካባቢዎች የሚያሳዩት ግን፣ ማህበረሰቦች እየተፈጠሩ ያሉ ዕድሎችንና ትስስሮችን ለመጠቀም እንዲችሉ በማገዝ ረገድ አሁንም ድረስ ድክመቶች መኖራቸውን ነው (ይህ ጉዳይ ለውጥ በሚለው አጭር ጽሁፍ ውስጥ በስፋት ተዳስሷል)፡፡ አካባቢያዊ የከተሞች መስፋፋትንና አዳዲስ ገበያዎችን ለአብነት መውሰድ ይቻላል፡፡ የከተማ ዳርቻ ማህበረሰብ አባላት፣ በአጎራባች ከተማ (ጉራጌ/ ግራር) ከሚገኙ ምርታማና እሴትን የሚጨምሩ ጥቅማጥቅሞችንና እድሎችን ከመጠቀም ጋር በተሻለ መልኩ የተያያዙ ግቦችን ከማስቀመጥ ይልቅ፣ የኤክስቴንሽን ምርት ግቦች ደረጃ በመውጣቱ የተሰማቸውን ቅሬታ ገልጸዋል፡፡ በገጠራማ ነገር ግን በተቀናጀ አካባቢ የሚኖሩ ግለሰቦች፣ ከጎረቤት ቀበሌ ለተማሩት የዕደ ጥበባት ሙያ ምርታቸው፣ እውቅና ያልተሰጣቸውን የገበያ ዕድሎች ለመጠቀም ፍላጎት ቢኖራቸውም ድጋፍ ለማግኘት ግን አዳጋች ሆኖባቸዋል (ጅማ/ሶሞዶ)፡፡ ቡና አምራች የሆነ አንድ አካባቢ (ጌዲኦ/አዳዶ) ምርቱን ለገበያ ለማቅረብ የሚያስችለው የተሻለ የትራንስፖርት መንገድ ሲሻ፣ በመስኖ ታግዞ አትክልቶችን የሚያበቅል ሌላ ማህበረሰብ በበኩሉ፤ የገበያ ተደራሽነቱን ለማሻሻል በአዋሽ ወንዝ ላይ ድልድይ እንዲገነባለት ጠይቋል (ምስራቅ ሸዋ/ቆሮዶጋጋ)፤ ሁለቱም ግን አልተሳኩም (ማጣቀሻ፡- የገጠር ከተሜነት መስፋፋት)፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም፣ ለመሰረተ-ልማት ኢንቨስትመንት ቅድሚያ በመስጠት ረገድም ልዩነቶች መኖራቸውን ጥናቱ ያመለክታል፡፡ ቅድሚያ የተሰጣቸው አካባቢያዊ አንገብጋቢ ጉዳዮች፣ ለሌሎች አካባቢያዊ ፍላጎቶች ቅድሚያ ለመስጠት ሲባል እንዲዘገዩ ይደረጋሉ፡፡ የህንጻዎች ግንባታ፣ ለምሳሌ፡- በተደጋጋሚ ተቃውሞ አስነስቷል፡፡ በምስራቅ ሸዋ/ገልቻ እና በምስራቅ ትግራይ ከሚገኙ ተደራሽ ያልሆኑ አካባቢዎች አንዷ በሆነቺው ሃረሳው (ማህበረሰቡ የውሃ ቱቦዎችን ለማስዘርጋት ገንዘብ አዋጥቶ እንኳን) ያለው የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ችግር እንዲሁም የአካባቢው ማህበረሰብ የመስኖ ግንባታ ፍላጎት፣ የወረዳው የበጀት ድልድል ለጤናና ለትምህርት ቅድሚያን በመስጠቱ ሳቢያ ሊሳካ ያልቻለበት (ሰሜን ወሎ/ ሹምሸሃ) አጋጣሚም ከዚህ ጋር በተያያዘ ሊጠቀሱ የሚችሉ ሌሎች ምሳሌዎች ናቸው፡፡

ፖሊሲ አውጭዎች፣ ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚመጣው የማህበረሰብ ተስፋ መቁረጥ፣ ወደፊት እየተራመደ ባለው የኢትዮጵያ ጥልቅ የልማት ሞዴል ዘላቂነት ላይ ሊፈጥረው የሚችለውን አሉታዊ ተጽዕኖ እንደዋዛ ሊመለከቱት አይገባም፡፡ በተደጋጋሚ የሚታየው ይህ ችግር፣ በቀበሌዎች ውስጥ ተግባራዊ በሚደረጉ የግብረ መልስና የልማት እንቅስቃሴዎች የግምገማ (ችግሮችን የመለየትና ሪፖርት የማድረግ) ስልቶች ላይ የሚታዩ ድክመቶችን ያመላክታል፡፡ የግብረ መልስና የግምገማ ስልቶቹ በአብዛኛው ትኩረት የሚሰጡት ለውጤቶችና ለሂደቶች ጥራት ሳይሆን፣ በቁጥር ላይ የተመሰረቱ ግቦችን በማስቀመጥ ላይ ሲሆን፤ ከዚህ በተጨማሪም በወረዳ ክትትል ስርዓቶች ላይም አንዳንድ ድክመቶች ይታያሉ፡፡ በቀበሌ ደረጃ የሚገኙ ሰራተኞች፣ የልማት እንቅስቃሴዎችንና

ጥረቶችን አካባቢያዊ ምርጫዎችን ወይም ነባራዊ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ለመቅረጽ ወይም ለማሻሻል ጥረት ያደረጉባቸው አጋጣሚዎች ጥቂት እንደሆኑ የWIDE3 ጥናት ያመለክታል። ይሄም ሆኖ ግን፣ በጥቅሉ ሲታይ፣ የአካባቢ ባለስልጣናት የልማት እንቅስቃሴዎችንና ጥረቶችን ብሄራዊ መመሪያዎችን ባገናዘበ መልኩ የሚያሻሽሉበት አካሄድ በአብዛኛው የተለመደ ክስተት እንደሆነ ነው የጥናት ውጤቶቹ የሚያመላክቱት። (በሰሜን ሸዋ/ኮርማርገፍያ፣ በምስራቅ ሸዋ/ ሲርባ፣ በአርሲ/አዳዳዋታ እና በምዕራብ ሸዋ/ አዳ ሃሮ የታዩት አጋጣሚዎች ከብዙዎቹ መካከል ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸው)። ዜጎች ግን፣ ከዚህ በተቃራኒው ዜጎች ቅድሚያ የሚሰጧቸውን ጉዳዮች ለማሳካት ቀጥተኛ ያልሆኑ መንገዶችን ወደ መከተል ነው የሚያዘነብሉት። የወረዳና የቀበሌ ባለስልጣናት አቅም እያደገና እየተቀናጀ ሲመጣ፣ ከማህበረሰቦች ጋር በመተባበር፣ የእያንዳንዱን አካባቢ ልዩ ፍላጎቶችና ተቀዳሚ ጉዳዮች ከግምት ውስጥ ያስገቡ ማዕቀፎችን፣ ለራሳቸው የበለጠ ቅርብ በሆነ መልኩ ለመቅረጽና ተጽዕኗቸውን በተሻለ ሁኔታ ለመከታተል የሚያደርጉት ጥረት ድጋፍ ሊደረግለት ይገባል ተብሎ ይታመናል።

ኢኮኖሚው እያደገና ብዝሃነትን እያገኘ ሲመጣ፣ የተፈለጉት እሴትን የመጨመር አካሄዶች የበለጠ ብዝሃነት ያላቸው፣ የተወሳሰቡና ያልተመለዱ እየሆኑ ይመጣሉ። የWIDE3 ጥናቶች፣ አገሪቱ ቀጣይነት ባለው ብሄራዊ የማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ ልዩነት የመፍጠር ሂደት ውስጥ እንደምትገኝ የሚያመላክቱ በርካታ ማስረጃዎችን ያቀርባሉ። ይህ ክስተት የተሻለ ሃብት ባፈሩ የገበያ ሰብል አምራች አካባቢዎች (ጅማ/ ሶሞዶ፣ ጌዲኦ/ አዳዶ) የበለጠ ጎልቶ የሚታይ ቢሆንም፣ ጥናቱ በተደረገባቸው ሁሉም አካባቢዎችም ተስተውሏል። ከ2010 እስከ 2013 በነበሩት አመታትም የመጨመር አዝማሚያ ታይቶበታል። አካባቢያዊ ሂደቶችና በአነስተኛ ማዕከል የከተሞች መስፋፋት ዙሪያ የሚገኙ የግንኙነት ሰንሰለቶች በተለይ ደግሞ ከስራ ክፍያ ላቅ ያለ ፋይዳ ያላቸው የምርታማነት ዕድሎች ለሚያበረክቱት ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ትኩረት መስጠት፣ በአካባቢያዊ የዲዛይንና የማማከር ሂደቶች ውስጥ ዋነኛ ጉዳይ ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል (ማጣቀሻ፡- የገጠር ከተሜነት መስፋፋት)። የፖሊሲ ትኩረት፤ በማደግ ላይ በሚገኙ አነስተኛ (ንዑስ ወረዳ) የከተማ ማዕከላት ላይ የሚጫወተውን ቁልፍ ሚና፣ የሚያሳድረውን አወንታዊ ተጽዕኖ እንዲሁም የሚያጋጥሙትን አዳዲስ እንቅፋቶች በተመለከተ የWIDE 3 ጥናት፣ ማስረጃ የሚያቀርብ ቢሆንም፣ ለሙያ ስልጠና እና ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ግንባታ የተሰጠው ጠንካራ አገራዊ ትኩረት፣ ከወረዳዎችና ከፍ ያሉ የከተማ ማዕከላት ባለፈ እምብዛም የማይታይ መሆኑን ማጤን ተገቢ ነው (ማጣቀሻ፡- ትምህርት)። አካባቢያዊ የልማት እንቅስቃሴዎችንና ጥረቶችን ለአካባቢያዊ ተጨባጭ ሁኔታዎች የሚስማሙ የማድረጉን ተሞክሮ ማሳደግ፣ ወሳኝ የጅማሬ ምዕራፍ ሲሆን የቀበሌና የንዑስ ቀበሌ መዋቅሮች ለወደፊት ማደጋቸውንና መለወጣቸውን ሲቀጥሉም በተጨባጭ የሚሳካ ጉዳይ ሊሆን ይችላል። ይህም ብቻ አይደለም፤ ስኬት ከዚህ በታች በሚዘረዘሩትና በጥቅሉ ሲታዩ ሁሉንም ተጠቃሚ የሚያደርጉ “መልካም ኡደቶችን” የመፍጠር አቅም ባላቸው ሌሎች የሂደት ጥራት ጉዳዮች ላይም የተመሰረተ ነው።

<u>“የለውጥ አንቀሳቃሶች/ አራማጆች”? ማሰገደድ፣ ማሳመን፣ ጫና ማድረግ እና ሰምምነት</u>

የWIDE3 መረጃ፣ ጫና ከማድረግ ይልቅ የጋራ ስምምነት መፍጠርን እንዲሁም ሰርቶ ማሳየትንና የአርሶ አደሩን ምርጫ ማስቀደምን በሚደግፍ የብሄራዊ ፖሊሲ አውድ ውስጥ፣ ልማታዊ ግቦችን ለማሳካት ተብሎ የሚፈጸምን "ማስገደድ" የተመለከተ አስደናቂ ዘርፈ ብዙ ማስረጃ ያቀርባል፡፡ በ2006/7 የወጣው የመንግስት “የመልካም አስተዳደር ማዕቀፍ” በመግቢያው ላይ፤ በስብሰባዎች፣ በማህበረሰብ ስራዎችና በመዋጮዎች ላይ የማይሳተፉ ዜጎችን መቅጣትን ጨምሮ መደበኛ የሆነ ማዕቀብ የማድረግ እርምጃ ማብቃቱን ያትታል፡፡ ምንም እንኳን በአመዛኙ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተው ይህ አካሄድ፣ በWIDE የጥናት አካባቢዎች ዘንድ የታወቀና ቅቡልነትን ያገኘ ቢሆንም፣ ከዚህ ጋር በተያያዘ የሚነሱ ሁለት ጉዳዮች አሉ፡፡ የመጀመሪያው፣ ከአካባቢው የአስተዳደር መዋቅሮች ውጭ የሆኑትን ጨምሮ በአማራ ክልል አካባቢዎች የሚገኙ ምንጮች፣ የመንግስት አገልግሎቶችና ስልጣኖች፤ የመፈጸም አቅማቸው አነስተኛ እንደሆነ በመግለጽ ትችት መሰንዘራቸው ነው (ምስራቅ ጎጃም/ የትመን፣ ሰሜን ሸዋ/ ዲንki)፡፡ ተጨባጭ ኢኮኖሚያዊ ማበረታቻዎችን በመስጠት በፍጥነት ቅቡልነትን እንዲያገኝ ማድረግ ከሚቻልበት ሁኔታ ውጪ፣ የተፈለገውን የተፋጠነ ማህበራዊ ለውጥን ማምጣት እጅግ አስቸጋሪ መሆኑን በተለይም የልማት አጋሮች ችላ ሊሉት አይገባም፡፡ በቅርብ አመታት ከተመዘገቡት እጅግ ወሳኝና አዎንታዊ ማህበራዊ ለውጦች መካከል አንዳንዶቹ (የትግራይ ሴቶች በአካባቢያዊ የፖለቲካና የመንግስት የስልጣን እርከኖች ላይ ያላቸው ተሳትፎ በፍጥነት ማደጉ ጥሩ ምሳሌ ነው) አለመግባባትን የፈጠሩና ተቃውሞ ያጋጠማቸው ነበሩ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ፣ የWIDE መረጃ ቋት፣አካባቢያዊ የመንግስት አካላት በማህበረሰቡ ዘንድ ቅቡልነት አላገኙም ያሏቸውን የልማት ዕቅዶች ለማስቀጠል ሲሉ፣ ህዝቡ እንደማስገደድ ያያቸውን ጠንካራ ጫናዎች በማሳደራቸው ሳቢያ የተፈጠሩ አሉታዊ ማህበራዊ፣ ልማታዊና አልፎ ተርፎም ፖለቲካዊ ውጤቶችን በሚያሳዩ በርካታ ማስረጃዎች የተሞላ ነው፡፡ ማስረጃዎቹ፣ በተለይ ደግሞ ዕቅዶቹ የኋላኋላ በስፋት ተጠቃሚ የማያደርጉ ሆነው ከተገኙባቸው አልያም ደግሞ የሚያበረክቷቸው ጥቅሞች በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ሌላ ችግር ያመጣሉ ተብለው ከታሰቡባቸው አካባቢዎች የተገኙ ናቸው፡፡ የከብቶች ግጦሽ ቦታ ላይ ትምህርት ቤት ለመገንባት የተያዘውና በማህበረሰቡ ዘንድ ተቃውሞ የገጠመው ዕቅድ ከእነዚህኞቹ ማስረጃዎች አንዱ ነው (ምስራቅ ጎጃም/ የትመን)፡፡ የመሬት ይዞታን የሚነኩ የልማት ዕቅዶች፣ ጥቅሞችን ከአንዱ ቡድን ወደሌላኛው የማስተላለፍ አዝማሚያ ያላቸው ከመሆኑ ጋር በተያያዘ፣ በተደጋጋሚ ውዝግብ ሲፈጥሩ ታይቷል (ማጣቀሻ፡- የገጠር ከተሜነት መስፋፋት)፡፡ መሬት ለብሄራዊ ፓርክ በተሰጠበት አጋጣሚ (ጋሞ/ ዶአማ) ወይም በተለያዩ አካባቢዎች የጋራ የግጦሽ መሬቶች ወይም የማገዶ ምንጭ የሆኑ አካባቢዎች ለወጣት የህብረት ስራ ማህበራት ወይም ለጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ተቋማት እንዲጠቀሙባቸው በተሰጡባቸው አጋጣሚዎች፣ መሰል ዕቅዶች ተቃውሞ ገጥሟቸዋል፡፡

አብዛኞቹ መሰል አጋጣሚዎች በአካባቢያዊ አመራር ላይ የሚታዩትን የጥራትና የአቅም ችግሮች በሚገባ ሊያመለክቱ ቢችሉም፣ የአመራርና የማንቀሳቀስ ስራ የበለጠ ውጤታማና አካታች የሚሆንበትን እንዲሁም በአብዛኛው “በማዳመጥና በመናገር” መካከል የተሻለ ሚዛናዊነት የተፈጠረበትን ወይም ለመፍጠር የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መኖሩን የሚያመላክተውን ከማህበረሰቦች

ጋር የሚደረግ መደበኛ የፖሊሲ አካሄድ አያሳዩም፡፡ የአካባቢ የመንግስት አካላት አመራሮች፤ ህዝባቸውን በአራቱ የመንግስት መዋቅር እርከኖች፣ ማለትም በቀበሌ፣ በንዑስ ቀበሌ ጎጥ/ ዞን፣ በልማት ቡድንና በ1 ለ 5 አደረጃጀቶች አማካይነት የማንቀሳቀስና የማስተባበር አቅም ከ2010 ወዲህ ባሉት አመታት እያደገ መምጣቱን የWIDE3 መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ እነዚህ መዋቅሮች የበለጠ ካደጉና ከተቀናጁ፤ የአካታች፣ ምላሽ ሰጪና በአካባቢያዊ ፍላጎት ላይ የተመሰረቱ ሂደቶች አስፈላጊነት እያደገ ሊመጣ እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ መሃይምነት በተስፋፋበት፣ የኮሙኒኬሽን መሰረተ ልማት ደካማ በሆነበትና አነስተኛ የአስተዳደርና የአመራር አቅም ባለበት ሁኔታ ውስጥ (የWIDE3 ጥናት በተከናወነበት ወቅት፣ የአገልግሎት አሰጣጥን ወደ ወረዳ ደረጃ የማውረዱ ስራ ከተጀመረ ገና አስር ያህል አመታትን ብቻ ያስቆጠረ ነበር)፡፡ የተራዘሙ በአካል ተገኝቶ ስልጠናዎችንና በቀላሉ በቁጥር ሊለኩ የሚችሉ ተጨባጭ ግቦችን መሰረት ያደረገ አካሄድን መከተል፣ የተፋጠነ የሽግግር ተቋም ግንባታን ሊያቀላጥፍ እንደሚችል ይታመናል፡፡ በአሁኑ ወቅት እነዚህ ሁሉ ችግሮች እየተቀረፉ የሚገኙ ሲሆን፣ ሞዴሉ ለአካባቢያዊ ባለቤትነት ቅድሚያ በመስጠትና አካባቢያዊ ምርጫዎችን በማስከበር በመንደር ደረጃ አቅምን መጠቀምና ሃብትን ማፍራት በሚያስችል መልኩ የበለጠ ሊያድግ እንደሚችልና ማደግ እንደሚገባውም የWIDE 3 የጥናት ውጤቶች ይጠቁማሉ፡፡

ሂደቶችን ለማሻሻል በሚደረግ ጥረት ውስጥ ተጨማሪ “የጅማሬ ምዕራፍ” ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው በWIDE3 ጥናት የተጠቀሱት ስድስት ነጥቦችም እንደሚከተለው በአጭሩ ተዘርዝረዋል፡፡

- በጥቂቶች እጅ ውስጥ የተከማቹ የሚመስሉ ተደራራቢ ሃላፊነቶችን ለሌሎችም ማከፋፈል፤
- የሴቶችንና የወጣቶችን የውሳኔ ሰጪነት ተሳትፎ የሚያሳድጉ ስልቶችን ማጠናከር፤
- የቀበሌ ሊቀመንበሮችን የሚያሳትፉ ቁልፍ ሚናዎችንና ግንኙነቶችን መፈተሽ፤
- የ“ሞዴሎች” ስርዓት ሰፊውን ማህበረሰብ በመድረስ ረገድ ያለውን ብቃት መልሶ መቃኘት፤
- በሶስቱ የመንግስት መዋቅሮች መካከል ያሉትን ግንኙነቶች መልሶ ሚዛናዊ ማድረግ እና
- በልማትና በፖለቲካ መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ዜጎች ለያዟቸው የተለያዩ አመለካከቶች የበለጠ ትኩረት መስጠት፡፡

<u>በጥቂቶች ላይ ጫና ማብዛት? ዘላቂ አካታችነትን ማስቀጠል/ ማስፋፋትእና ማጠናከር</u>

በሁሉም የWIDE የጥናት አካባቢዎች፤ በቀበሌና በንዑስ ቀበሌ ደረጃዎች በደመወዝና በፈቃደኝነት የሚያገለግሉ እጅግ በርካታ አመራሮች፤ የሚሸከሟቸው የተለያዩ የስራ ሃላፊነቶች እየጨመሩ መምጣታቸውን፣ እጅግ ከፍተኛ የስራ ጫና እንዳለባቸውና ከአስተዳደራዊ ሃላፊነቶቻቸው ጋር በተያያዘ ኢኮኖሚያዊ ወይም ማህበራዊ መስዋዕትነቶችን እንደሚከፍሉ በመጥቀስ ቅሬታቸውን አቅርበዋል፡፡ የስራ ጫና የበዛበት አንድ የቀበሌ ሊቀመንበርና ባለቤቱ፤ ከጫት የሚያገኙትን ገቢና ለንግድ የሚያውሉትን ጊዜ አጥተዋል፡፡ መስፈርቱን በቅጡ የሚያሟላና ስኬታማ የሆነ አንድ ግለሰብ፣ ስራው የሚወስደው ጊዜ ከንግዱ የሚያገኘውን ጥቅም እንዳያሳጣው በመስጋት ለመሳተፍ ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቷል፡፡ እንዲሁም ንቁ ፖለቲካዊ ተሳትፎ ያላት፣ የፓርቲና የሚሊሻ አባል የሆነች ሴት፤ ከባድ የስራ ሃላፊነቶችን በመሸከሟ ሳቢያ ከትዳር አጋሯ ጋር ውዝግብ ውስጥ መግባቷን ተናግራለች (ምስራቅ ሃረርጌ/ አዴሌ ኬኬ)፡፡ እነዚህ ሁሉ በአንድ አካባቢ የተመዘገቡ ክስተቶች

ቢሆኑም በሁሉም አካባቢዎች የሚታዩ የተለመዱ አጋጣሚዎች ናቸው። ግብር መሰብሰብ፣ ከእርሻ ውጭ የሆኑ ስራዎች በሚከናወኑባቸው የከተማ ዳርቻ አካባቢዎች ሳይቀር፣ በቀበሌ ሊቀመንበሮች ወይም ሌሎች አመራሮች ላይ በተለየ ሁኔታ ጫና የሚያሳድር ከባድ ስራ እንደሆነ በተደጋጋሚ ተጠቅሷል። በ2008 በመንግስት የተካሄደውና የቀበሌ ተወካዮች ምክር ቤት አባላትን ቁጥር ማሳደግን ከአላማዎቹ አንዱ ያደረገው የፖሊሲ ለውጥም፣ የማህበረሰቡን ተሳትፎ በማስፋት በየአካባቢው በሚገኙ አስፈጻሚ አካላት ላይ የሚታየውን የስራ ጫና መደራረብ ችግር ለመፍታት ያለመ ጭምር ነበር። ሆኖም ግን፣ በወረዳ የምክር ቤት አሰራርና የምክር ቤት አባላት በሆኑ ግለሰቦች ላይ ዛሬም ድረስ የሚስተዋሉ አንጻራዊ ድክመቶች፣ የለውጡን ውጤት ወደ ኋላ አስቀርተውታል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ፤ የተለያዩ ተደራራቢ የስራ ሃላፊነቶች ጥቂት ቁጥር ባላቸው የወረዳ ወይም የቀበሌ አመራሮች ትከሻ ላይ መጫናቸው፣ በኢትዮጵያ የልማት ውጤቶች ላይ የከፋና አደገኛ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ስርዓታዊ ጥፋቶችን የሚያስከትል የተለመደና ስር የሰደደ ክስተት እንደሆነ የWIDE3 መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህ ሁለት ገጽታዎች አሉት፡- አንደኛው፣ ሂደቱን በሚመሩት አካላት ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የመምራት ፍላጎት ባላቸው ሰዎች ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ነው። የአካባቢ አመራሮች ከፍተኛ የስራ ጫና ማለት ብዙ ጊዜ፣ የስራ ተነሳሽነትን የሚያዳክም ሲሆን ከፍተኛ የድካምና የተስፋ መቁረጥ ስሜቶችንም ይፈጥራል። በበርካታ አካባቢዎች፣ ክፍያ የሌላቸው የቀበሌ አመራሮች ስራቸውን ለመልቀቅ ይፈልጋሉ። ነገር ግን፣ በተቋማዊ ጫና ወይም ፖለቲካዊ ፍርሃት የተነሳ፣ መልቀቅ እንዳልቻሉ ያስባሉ። በሌሎች አካባቢዎች ደግሞ፣ ስርዓቱ ከፍተኛ አቅም ያላቸው ወይም ውጤታማ የሆኑ ግለሰቦች የአመራርነት ሃላፊነቶችን እንዳይወስዱ በግልጽ በማከላከል፣ የግል ጥቅማቸውን የሚያሳድጉ የማህበረሰቡ አባላትን፣ ለሃላፊነት ቦታዎቹ የማበረታታት ተግባር ይፈጽማል። በዚህም የመንግስት የለውጥ እርምጃዎች ጥራትና ፍትሃዊነትን ለአደጋ ያጋልጣል።

ይህ ሁኔታ፣ ከዚህ ባለፈም፣ በመንደር ደረጃ ያለውን የማህበረሰብ መስተጋብር ልማዶች የመለወጥ ተጽዕኖ እንዳለው የWIDE3 መረጃዎች ትንተና ይጠቁማል። በአንዳንድ አካባቢዎች፣ በፖለቲካውና በልማቱ ውስጥ የሚሳተፉ የአካባቢ የስራ አስፈጻሚ አባላት እንዲገለሉ እስከማድረግ የደረሰ ተጽዕኖ የፈጠረ ሲሆን፤ ይህም በልማትና በወረዳ አስተዳደር አሰራሮች ላይ የጋራ መግባባትን ሊያጠናክሩ የሚችሉ መደበኛ ያልሆኑ ጠንካራ ማህበራዊ ትስስሮችን ከማጥበቅ ይልቅ ሊያዳክም ይችላል። የአካባቢ አመራሮች ከሚገባው በላይ በስብሰባዎች በሚወጠሩበት ጊዜ፣ ከወከሏቸው ወይም ከሚመሯቸው ህዝቦች ጋር የሚያሳልፉት ጊዜ አነስተኛ ይሆናል። በእንዲህ አይነት ሁኔታዎች ውስጥ፣ ሰዎች በአመራሮቻቸው ከአካባቢው መሰወር ጥርጣሬ ቢያድርባቸውና ከአካባቢው የተሰወሩት ስራቸውን በትጋት ለማከናወን ወይም መስዋዕትነት ለመክፈል ሳይሆን ህዝቡን እየበደሉ የራሳቸውን ጥቅም ለማሳደድ ነው ብለው ቢያስቡ የሚያስገርም አይሆንም። በሁሉም አካባቢዎች፣ አመራሮችን በአድዕሎአዊነት፣ በሙስና ወይም በስግብግብነት የማየት አደገኛ ወይም ጨለምተኛ አመለካከቶች እንደሚንጸባረቅ የተነገረ ሲሆን በብዙ አካባቢዎች (ከምባታ/ አዜ ዬቦአ፣ ጌዴኦ/ አዳዶ፣ ጅማ/ ሶሞዶ፣ ደቡብ ኦሞ/ ሉቃ) ከዚህም የባሱ ችግሮች ይታያሉ። የጎሳ አኗኗር ደግሞ ሌሎች በርካቶችን ለችግር ዳርገዋል (በተለይ ደግሞ በምስራቅ ሸዋ/ቆሮዴጋጋ እና በአርሲ/ ኡዳ ዳዋታ)። ከሙስና ወይም ጎሳዊነት ጋር ከተያያዙ አመለካከቶች ባለፈም፣ ከብድር አቅርቦት፣ የህብረት ስራ ማህበራትን

ከማቋቋምና ከውጤታማነታቸው ጋር በተያያዘ የሚታዩትና በዚህ ጥራዝ በተካተቱ ሌሎች አጭር የውይይት መግለጫዎች ላይ የተዳሰሱት ችግሮችም፣ ጠንካራ ትችት ተሰንዝሮባቸዋል።

ፖሊሲ አውጭዎች፣ በሥራ ጫናና ደካማ ወይም አድሎአዊ የመስተጋብር አዝማሚያዎች ዙሪያ ሥርዓታዊ ተጽዕኖዎች መኖራቸውን መፈተሽ ይገባቸዋል። ይሄ መስተጋብር የልማት አቅጣጫ (ሞዴል) ለጉዳት በሚያጋልጥና በፍትሃዊነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ በሚፈጥር ኡደት በመሪዎችና በዜጎች መካከል የሚጠበቀውን የጋራ ትስስር እንዲዳከም ያደርጋል። ይሄን ችግር ለመቅረፍ ያግዙ ዘንድ የወረዳ የህዝብ ተወካዮችን የማጠናከር አቅም፣ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

<u>የሁሉም ኢትዮጵያውያን ውሳኔ ሰጪዎችን መፍጠር</u>

WIDE3 የጥናት ክትትል ካደረገባቸው ማህበረሰቦች (አከራካሪ ቢሆንም፣ ከምስራቅ ትግራይ/ገብለን እና ሃረሳው ውጭ) የተሰበሰቡ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት፤ ሴቶች በአካባቢ ፖለቲካዊ፣ አስተዳደራዊ፣ እንዲሁም ልማታዊ አመራር ላይ እና በውሳኔ ሰጪነት የሚያደርጉት ተሳትፎ በጣም ውስን ነው። በተግባር፣ የተለየ አቅም ያላቸው ግለሰቦችን ጠብቆ ማቆየት ነው። ጥናቱ በተካሄደ ወቅት፣ የወረዳ አስተዳደርና የልማት አመራርን በመቅረጽና በመሙላት ረገድ፣በገዢው ፓርቲ አባላት የተከናወነውን ወሳኝ ሚና፣ የWIDE 3 መረጃ ያብራራል። ሆኖም ግን፣ ገዢው ፓርቲ (እንዲሁም ሁሉም ፓርቲዎች) በመላው አገሪቱ እኩል ቁጥር ያላቸው ሴቶችና ወንዶችን የመመልመል ተነሳሽነት ያለው ስትራቴጂ ካልቀረጸ በስተቀር፣ ጾታዊ ጥንቅሩ የተመጣጠነ አመራርም ሆነ ምርጥ ልማታዊ ውጤቶችን መቀዳጀት አይቻልም። ሴቶች፣ በሴት የልማት ቡድኖችና በ1ለ5 አደረጃጀት ውስጥ ከሚያደርጉት ተሳትፎ በተጨማሪ በዋና የሥራ አስፈጻሚ አካልና በፖለቲካዊ መዋቅሮች ውስጥ ተሳትፎአቸውን እንዲያጎለብቱ ይበልጥ ማበረታታትም ያስፈልጋል። የWIDE3 ጥናት ክትትል ካደረገባቸው ማህበረሰቦች በገጠር አካባቢ የወጣቱን ጥቅሞች ማዕከል ያደረጉ ድርጅታዊ መዋቅሮች ደካማ መሆን፣ በአብዛኞቹ የታየ ክስተት - ከትላልቅ የከተማ ማዕከሎች፣ የመንግስት ፕሮግራሞች ጋር ሲነጻጸር ሲሆን ቀደም ብሎ ለተጠቀሰው የጥቃቅንና አነስተኛ የንግድ ተቋማት ወይም የሥራ ፈጠራ ፕሮግራሞች አንጻራዊ እጥረት አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል ።

<u>"የቀበሌ ሥራ አስኪያጆች እንደ ጨው የማይገቡበት የለም"</u>

የቀበሌ ሥራ አስኪያጆች እንደ መንግስት የልማት ሞዴል ወሳኝ ሚና ተጫዋችነታቸው፣ ያላቸውን ጉልህ አስተዋጽኦ የWIDE3 ጥናት ያሳያል። የቀበሌ ሥራ አስኪያጆች፣ ፊት አውራሪ የሆኑ የልማት ሰራተኞችን (የግብርና ልማት እና የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች) ሥራ እንደሚያስተባብሩ፣ በ2010 የጥናቱ 3ኛ ክፍል የኋላ መረጃ ላይ ተጠቁሟል። እንደ ውጤታማና ገለልተኛ (ብዙ ጊዜ "የፖለቲካ ንኪኪ የሌለው" በሚል ይተረጎማል) የሚታይ ጥሩ የቀበሌ ሥራ አስኪያጅ፣ የሚፈጥረውን በጎ ተጽዕኖም ሆነ በሃላፊነት ቦታው ላይ አመኔታ ሲጓደል፣ ማህበረሰቡ ለመንግስት ፕሮጀክቶች የሚኖረው እርግጠኝነት ሊሸረሸር እንደሚችል የWIDE ጥናት ማስረጃ ያቀርባል። በቀበሌው ሥራ አስኪያጅና በቀበሌው ሊቀመንበር መካከል ያለው ግንኙነት ጤናማ መሆን (ብዙ ጊዜ በዕድሜያቸው፣በትምህርትና በተለይ ደግሞ በደሞዝ ልዩነት ሳቢያ ይሻከራል) ቁልፍ መመዘኛ እንደሆነም ጥናቱ ያሳያል። ይህም ተጠያቂነትና ቁጥጥርን ያሳድጋል ወይም ለአደጋ ያጋልጣል።

ቅቡልነትና ብቃትን በተመለከተም በማህበረሰብ አመለካከት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡ እኒህ ከሰፊው ማህበረሰብ ጥቅም አንጻር ለማረቅ አስቸጋሪ የሆኑ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ጥናቶችና ግምገማዎች፤ በዚህ ቁልፍ ቡድን ውስጥ ተፈላጊና ወይም የማይፈለጉ አሰራሮች አፍላቂና አንቀሳቃሽ የሆኑ ሃይሎችን ጥቅም ባለው መንገድ በመለየትና በመገንዘብ ላይ ሊያተኩሩ ይችላሉ፡፡ የWIDE3 ቀዳሚ ትኩረት ባይሆንም በወረዳ ደረጃ ከሚገኙ ሃላፊዎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት መረዳትም፣ የአጠቃላይ ምስሉ ወሳኝ ግብአት ይሆናል፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት፤ በእያንዳንዱ የመንግስት መዋቅር ውስጥ ግለሰቦችና ተቋማት ያላቸውን ህጋዊ ሥልጣን በመደንገግ፣ በመለየትና ተቋማዊ በማድረግ ረገድ በጣም መሰረታዊ የሆነ ሥራ አከናውኗል፡፡ ፖሊሲ አውጭዎች፣ በተለያዩ አካባቢዎች ከተከናወነው ከዚህ የሥልጣን ወሰንን መደንገግ ጋር የተገናኙ የህብረተሰብ ተቋማትንና አሰራራቸውን ይበልጥ በጥልቀት በመገንዘብ እንደሚጠቀሙ የWIDE3 መረጃ ይጠቁማል፡፡ በቀበሌ ሊቀመንበር ዙሪያ እንዲሁም በወረዳና በቀበሌ አስተዳደሮች መካከል) እንዴት በላቀ መንገድ መቅረጽ፣ ዘለቄታዊ ማድረግና ማሳደግ እንደሚቻል ለመረዳት፤ አካታች የተጨባጭ ዓለም ለውጥ የማፋጠን እንቅስቃሴያቸውን የሚቀጥሉትን ቁልፍ ሚናዎች፣ግንኙነቶችና ሃላፊነቶች ማጤን ያሻል፡፡

ከላይ ወደ ታች፣ ሞዴሎችና ኩላካይዜሽን[4]/Kulakisation ["የአርሶአደሮች መበልጸግ"]

ፖሊሲ አውጭዎች፤ በWIDE3 መረጃ የተሰነደውንና በማህበረሰቦች ሁሉ ተደጋግሞ የሚስተዋለውን ክስተት በትኩረት ሊያጤኑት ይገባል - ይኸውም ሞዴል-ተኮር አሰራር በሚያስገኘው የጥቅም ስፋት ዙሪያ ያለው ጥርጣሬ ነው፡፡ በሞዴሎችና በሰፊው ማህበረሰብ መካከል ያለው የመማማር፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርና ስኬት የመድገም የአሰራር አቅጣጫ ትኩረትና ጥናት ይሻል (ማጣቀሻ፡- ለውጥ)፡፡ የመንግስት ፍልስፍና፤ ሞዴል-ተኮር የአሰራር ስትራቴጂውን፤ የሁሉንም ማህበረሰባዊ እርከን አማራጮችና ብልጽግና ለማሳደግ እንደ ቁልፍ መሳሪያ የሚመለከት ሲሆን፤ በዚህም "ከላይ ወደ ታች" ወይም በዋናነት በሃብት ከበለጸጉ አሊያም አቅም ካላቸው ገበሬዎች ጋር ለመሥራት ከተቀረጸው ፖሊሲ የተለየ ያደርገዋል፡፡ እንዲያም ሆኖ መንግስት፤ ይሄን ሞዴል-ተኮር ስትራቴጂ በተቀናጀ ሁኔታ በማስፋፋት ረገድ ያለበትን ትልቅ ድክመት ይገነዘባል፡፡ ይህ በዚህ እንዳለ፣ የልማት ሰራዊቶች በዋናነት ከሞዴሎች ጋር በስፋት የሚሰሩበት ሁኔታ "ጉልሃን ያልሆኑ ወገኖች" በበጎ የሚያዩት አይመስልም - በተጨባጭ ፍላጎታቸውን ከግምት ውስጥ ያላስገባና የአገልግሎት አሰጣጥ ፍትሃዊነት የሚገዳደር አድርገው እንደሚቆጥሩት የWIDE3 መረጃ ይጠቁማል (ማጣቀሻ፡- ኢ-እኩልነት)፡፡

የWIDE ጥናት እንደሚያመለክተው፤ በፖለቲካው ወይም በልማቱ ተሳታፊ በሆኑት የቀበሌ ሥራ አስፈጻሚዎች ወይም በራሳቸው በሞዴሎቹ (አሰራሩን በአጠቃላይ በበጎ የሚመለከቱቱ) አመለካከትና ይበልጥ ትችት በሚሰነዝረው የማህበረሰብ ክፍል ዕይታ መካከል ትልቅ ልዩነት ይስተዋላል፡፡ ይሄ ከላይ ከተጠቀሰው ደካማ የማህበረሰባዊ መስተጋብር አዝማሚያ ጋር ሊያያዝ ይችላል፡፡ ሁኔታው በተለይ በWIDE ክፍል ፣ ጥናት፣ ክትትል በተደረገባቸው አንዳንድ ማህበረሰቦች በግልጽ የሚታይ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- በተለይ፣የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች "ከሁሉም ጋር የሚሰሩ"፣

[4] ኩላኮች ሃብታም አርሶአደሮች ናቸው፤ ብዙ ጊዜ (ሁልጊዜ አይደለም)ከኢትዮጵያ "ሞዴሎች" እርከን ጋር ይመሳሰላሉ፤ የአርሶአደሮች የመበልጸግ ሂደት፡- የግለሰብ ገቢን በማሳደግ እውን የሚደረግ የግብርና እድገት ሂደትን የሚያመለክት ነው፤ ከኢኮኖሚያዊ እርከን ደረጃ ጋርም ጥምረት ያለው ነው፡፡

የግብርኛ ልማት ሰራተኞች ደግሞ "ከሞዴሎች ጋር ብቻ የሚሰሩ" በሚል የሚነጻጸሩበት፣ አርሲ/ቱሩፌ ከጨማ እና ጉራጌ/ግራር ተጠቃሽ ናቸው፡፡ እንዲሁም በክፍል 2 ጥናት በተካተቱት ብዙዎቹ የምግብ ዋስትና ባልተረጋገጠባቸው ማህበረሰቦች፣ እያበበ ያለው ኢኮኖሚያዊ እርከን "በታችኛው መደብ" ላሉቱ ትልቅ አደጋ ሊያስከትል ይችላል፡፡ በክፍል 3 ጥናት በተካተቱትና የግብርና አቅም ባላቸው ሃብታም ማህበረሰቦች የተገኘው ማስረጃ ወጥ አይደለም፡፡ ለዚህ ምክንያቱ የWIDE3 ጥናት በተካሄደባቸው ዓመታት (ከ2010-13) ከሞዴሎቹ ጋር የመስራት ተቋማዊ ሥርዓት ተሻሽሎ ይሁን ወይም ሞዴል-ተኮር ለሆነው አሰራር ችግር ነው የሚባለው ጉዳይ፣ ዝቅተኛ ኢኮኖሚያዊ አቅም ባላቸው ማህበረሰቦች፣ የባሰ ሆኖ ታይቶ ይሁን አሊያም በሌሎች ምክንያቶች ግልጽ አይደለም፡፡

ከ2001 በኋላ የተደረገው በሞዴሎች አማካኝነት ሰፊውን ማህበረሰብ የማነቃነቅ እንቅስቃሴ ላይ የማተኮር እርምጃ፤ የኢትዮጵያ ልማት ሞዴል ወሳኝ ምሰሶ ሲሆን ኢኮኖሚው እያደገ ሲመጣ፣ የዚህ አሰራር የአመራር፣ የአፈጻጸምና ውጤት ገጽታዎች ጥብቅ ክትትል ይሻሉ፡፡ በWIDE3 ጥናት ወቅት፤ በምስራቅ ሸዋ /ሲርባ ከ835 ቤተሰቦች መካከል 203 ሞዴሎች የነበሩ ሲሆን በሰሜን ሸዋ/ኮርማርገፍያ 283 ነበሩ፡፡ ይሄም በንጽጽር ጥናት በተደረገባቸው አካባቢዎች ዓይነተኛ መገለጫ ይመስላል፤ ቁጥሮቹ ተለዋዋጭ ቢሆኑም፡፡ (WIDE ጥናት ያደረገባቸው ማህበረሰቦች፣ ከቀበሌዎች በእጅጉ ያነሱ መሆናቸውን ልብ ይሏል)፡፡ ሞዴል-ተኮር የሆነው አሰራር፣ አብዛኛውን የህብረተሰብ ክፍል ለማሳተፍ ታልሞ የተቀረጸ ነው፡፡ ነገር ግን የስኬት ተሞክሮን በሁሉም ማህበረሰባዊ እርከን ላይ መድገምን በተመለከተ እርግጠኛ መሆን አይቻልም፡፡ በሥነ ህብረተሰብ ዘርፍ የተደረጉ ጥናቶች፤ ውስን የሃብት አቅም ያላቸው ማህበረሰቦች፤ በባህል፣ በመረጃና በአማራጮች እጦት እንዲሁም በአነስተኛ ማህበራዊ መስተጋብር የተነሳ ሊገጥማቸው የሚችለውን አስቸጋሪ ፈተና ይጠቁማሉ፡፡ ውጤቶችን ለማሻሻል፤ ሃብታም ወይም በይፋ ስኬታማ "ሞዴሎች" በሚባሉትና በሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎች መካከል ያለውን ግንኙነት በየጊዜው መገምገምና መቃኘት አስፈላጊ ነው፡ ለምሳሌ፡- ድሃ ወይም ስኬታማ ካልሆኑ ጎረቤቶቻቸው፤ ከሥርዓቱ ውጭ ከሆኑ (ከመረጡ) ሌሎች ስኬታማ ግለሰቦች (አቅም ያላቸው መጤ ገበሬዎች፣ በጋሞ/ዶኦማ)፣ እንዲሁም አነስተኛ ድጋፍ ከሚያደርጉላቸው ነገር ግን የአንዳንድ ገበሬዎች ኢኮኖሚያዊ ደረጃና ክህሎት ከደሞዝተኛ መብለጡን ተከትሎ፣ ሚናቸው፣ ፍላጎታቸውና ማትጊያቸው ባልተለመዱ መንገዶች እየተለወጡ ከመጡ የመንግስት ሰራተኞች (የቀበሌ ሥራ አስኪያጆች፣የግብርና ልማት ሰራተኞች፣ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች) ጋር ያላቸውን ግንኙነት መገምገም ያስፈልጋል፡፡

<u>የሥራ አስፈጻሚውን ሥልጣን ማመጣጠን፤ ፍትህና ውክልና</u>

የWIDE3 ጥናት፤ የወረዳ አስተዳደር ስራ አስፈፃሚ፣ ሁለንተናዊ የገጠር ህይወት ላይ ተፅዕኖ የመፍጠር ከፍተኛ አቅም ያለው የፖለቲካሥርዓትን ይተርካል፡፡ ይሄ በአንጻራዊነት ደካማ የሆነ የወረዳ የፍትህና የውክልና መዋቅሮች መከሰትን ከሚያሳይ ምስል ጋር የሚቃረን ነው፡፡ ከአንዳንድ በአዎንታዊነት ከሚጠቀሱ ተንቀሳቃሽ የፍትህ አገልግሎቶች በስተቀር፣ በወረዳ ደረጃ ያሉ የመደበኛ ፍርድ ቤት መዋቅሮች አብዛኛውን ጊዜ ተደራሽ አይደሉም፡፡ በወረዳው ውስጥ ያሉ የተለያዩ አካባቢዎችን በመደበኛነት የሚጎበኙ "ተንቀሳቃሽ ፍ/ቤቶች"ን በጠንካራ የወረዳ ተቋማዊ ሥርዓት ውስጥ ማካተት፣ የፍትህ ተደራሽነትን በማስፋት ረገድ የላቀ አዎንታዊ ውጤት እንደሚኖረው

ይጠበቃል፡፡ የዘመናዊና ባህላዊ የፍትህ ተቋማት ጥምረትና ትብብር በእጅጉ አስፈላጊ በሆኑባቸው የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች (ምስራቅ ሸዋ/ገልቻ፣ ደቡብ ኦሞ/ሉቃ) ብቻ ግን አይደለም፡፡የWIDE3 መረጃ እንደሚጠቁመው፤ በአንዳንድ ቦታዎች፣ የማህበራዊ ፍ/ቤቶች ሚና፣ በመጠንም ሆነ በአቅም ቀስ በቀስ እየቀነሰ የመጣ ይመስላል፡፡ ምናልባት ተጽዕኗቸው እየጎላ በሚገኝ ሌሎች ተዋንያን ተተክቶ ይሆናል፡፡ የሽማግሌዎች ኮሚቴ፣ የመሬት አስተዳደር ኮሚቴ፣ ወይም ጠንካራ ፖለቲካዊ አቅም በፈጠሩ የልማት ቡድኖችና የነ5 አደረጃጀቶች፡፡ የማህበራዊ ፍ/ቤት አባላት፤ በፈቃደኝነት የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ፣ ከባድ ጫና እንዳለው በመጠቆም፣ ይሄም አገልግሎታቸው ተገቢውን ዕውቅና እንዳላገኘ ስጋታቸውን ይገልጻሉ፡፡ በWIDE3 ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ሌሎች በርካቶች ደግሞ የፍትህ ተደራሽነት ውስንነት ችግሩን በሚያብስበት በወረዳ ደረጃ (የማህበራዊ ፍ/ቤት አባላትና የሰፊው ማህበረሰቦች አባላት) በፍትህ ሥርዓቱ ላይ አመኔታ የላቸውም፡፡ የገጠር አካባቢዎች የኢኮኖሚ ብዝሃነትና እድገት፣ አዳዲስ ከመሬት ጋር ያልተያያዙ የንብረት መብቶች ጥበቃ ፍላጎትን ስለሚያበረታቱ፣ ማንኛውም የወረዳ መደበኛ የፍትህ ሥርዓት ተደራሽነት መዳከም ተጨማሪ ፈተናዎችን ይጋርጣል፡፡ መደበኛ ባልሆኑ ቁልፍ የማህበራዊ ፍትህ ተቋማት ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖም ቀላል አይደለም፡፡

በWIDE3 የመረጃ ቋት ውስጥ የተጠቀሱ በቀበሌ ደረጃ የተመረጡ የህዝብ ተወካዮች በንፅፅር በእጅጉ የሳሱ ናቸው፡፡ ይሄ ምናልባት ከ2008 ወዲህ እነዚህ መዋቅሮች ከየቀበሌው ከ200-300 ግለሰቦችን፣ እንዲሁም ከየቀበሌው አንድ ወይም ሁለት በወረዳ ደረጃ ከማሳተፋቸው አንጻር፣ ሊያስገርም ይችላል፡፡ ይሄ የጥናት ግኝት፤ የተወካዮች ም/ቤቶች (በቀበሌ ብቻ ሳይሆን በወረዳም ጭምር) በተለየ ሁኔታ ደካማ እንደሆኑ ቀጥለዋል በሚል የቀረበ የሌላ ጥናት ድምዳሜን ያጠናክራል፡፡ በማህበረሰብ ደረጃ የቁጥጥር ወይም የተጠያቂነት ተግባራቸውን የመወጣት ሃላፊነታቸው ወይም ከፍተኛ የሥራ ጫና ያለበትን የአካባቢ ሥራ አስፈፃሚን የማገዝ አቅማቸው አሁንም በአሳዛኝ ሁኔታ አላደገም (የደቡብ ኦሞ/ሉቃ የቀበሌ ም/ቤት ጥሩ ያልሆነ አርአያ ነው ለሁለት ዓመት አልተሰበሰበም)፡፡

የኢትዮጵያ የህዝብ ተወካይ ም/ቤቶች፣ አካታች ማህበረሰባዊ ትራንስፎርሜሽንን እውን ለማድረግ የሚያስችል፣ ነገር ግን በቅጡ ጥቅም ላይ ያልዋለ ከፍተኛ አቅም አለው፡፡ በመላው አገሪቱ 3.5 ሚሊዮን የፓርላማ አባላት የተመረጡ ሲሆን ይሄም ቅድሚያ በሚሰጣቸው የልማት ትኩረቶች ላይ የሚደረገውን ወቅታዊ ውይይት ለማስፋት ከፍተኛ ዕድል ይሰጣል፡፡ የWIDE3 ጥናት፤ ቅሬታዎችን በማቅረብ ረገድ ጉልህ የም/ቤቶች ሚናን የሚያሳዩ ማስረጃዎችን ያቀርባል፤ ሚናቸው የግድ ተነሳሽነት፣ ነጻነት ወይም ተቃውሞ የሚንፀባረቅበት ባይሆንም፡፡ ም/ቤቶች ግለሰቦችን ለመተካት ድምፅ የሰጡበት በርካታ አጋጣሚዎች አሉ (እነዚህ አጋጣሚዎች በራሳቸው የተፈጠሩ ይሁኑ አሊያም ለሥራ አስፈፃሚው ስጋቶች ምላሽ የሰጡበት ግልፅ አይደለም)፡፡ ነገር ግን የሥራ አስፈፃሚውን ፖሊሲ ወይም የአካባቢ የልማት ስትራቴጂዎችን በቀጥታ የተገዳደሩበት አጋጣሚ የለም፡፡ ይልቁንም ማህበረሰቦች ለእንዲህ ያሉት እንቅስቃሴዎች አማራጭ ማህበራዊ መዋቅሮችን መጠቀማቸውን የሚያሳይ ማስረጃ አለ (በምስራቅ ጎጃም/የትመን፣ ለት/ቤት መሥሪያ የሚሆን መሬት እንዳይወሰድ፣ በዕድር አማካኝነት የተቃውሞ እንቅስቃሴ ተደርጓል)፤ ይሄም የቀበሌ የተወካይ ም/ቤቶች የዜጎች ፍላጎት የሚያስተጋባበት (የሚሰማበት) ማዕከል መሆን ገና እንደሚቀራቸው የሚጠቁም ነው፡፡ ነዋሪዎች የቀበሌ ውሳኔዎችን ለመቃወም ሲሹ፣ ለም/ቤት ተወካዮች ከማቅረብ ይልቅ እድር፣

የሽማግሌዎች ኮሚቴ ወይም መደበኛ ያልሆኑ አደረጃጀቶችን ከተጠቀሙ፤ የልማት ንቅናቄ የተባለው፣ የፖለቲካ ወይም የፓርቲ ትርጓሜ ሊሰጠው የሚችልበት አደጋ የሚፈጥር ሲሆን "በሥርዓቱ ውስጥ ያለው" አመራር ሊፈታቸው የሚችሉ ውጥረቶችና ንግግሮችንም ያባብሳል፡፡ የWIDE3 ጥናት ክፍል 3 መረጃ፣ የቀበሌ ሥራ አስፈፃሚዎች ከእድሮች ጋር የሚተባበሩበትን አጋጣሚዎች የሚያሳይ ቢሆንም በወረዳ የህዝብ ተወካዮችና በሰፊው የማህበረሰብ አደረጃጀቶች መካከል ግንኙነት መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ የለም፡፡

በአሁኑ ወቅት በአብላጫው የተመረጡ የፓርላማ አባላት የኢህአዴግ አባላት በመሆናቸው ወይም በገዢው ፓርቲ በመሞላቱ የተነሳ፣ ከአካባቢ ተወካዮች ም/ቤቶች ጋር የመሳተፍ ፈቃደኝነትን ሳያዳክመው አልቀረም - ይሄም የህዝብ ተወካይ ም/ቤቶች አንዳንዴ በውጭ ሰዎች፣ ከ"ተወካይነት" ይልቅ "ፖለቲካዊ" ተደርገው እንዲቆጠሩ አድርጓቸዋል፡፡ ከአካባቢ ም/ቤቶች ጋር ለመሥራት ፍቃደኝነት የማጣት ሁኔታ መቀጠል፣ የአካባቢ ም/ቤቶችን አናሳ ሚና እና ደካማነት ዘላቂ የሚያደርግ ሲሆን ማህበረሰቦችን የመወከል አቅማቸውን ችግር ለመፍታት አያግዛቸውም፡፡ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ብቸኛ የፆታ ውክልና ያለው ተቋም የቀበሌና ወረዳ ም/ቤቶች ከመሆናቸው (50 በመቶ የፓርላማ አባላት ሴቶች ቢሆኑም ብዙ ጊዜ በደካማ የተሳትፎ ሪከርድና በአንዳንድ ቦታዎች ዝቅተኛ የሴቶች ቁጥር ባሉበት ሁኔታ) አንጻር ይህ ሁኔታ አመርቂ አይደለም፡፡ ለረዥም ዘመን የዘለቀ የኢትዮጵያ መንግስት ታሪካዊ ገፅታ የሆነውን ሥልጣን ወደ ሥራ አስፈፃሚው ያጋደለበትን መንግስታዊ ሥርአት፣ ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ማመጣጠን ፖሊሲ አውጭዎችና የልማት አጋሮቻቸው፣ የተዘነጋ በሚመስለው አቅም ላይ ማተኮር ይኖርባቸዋል፡፡

በፖለቲካና በልማት መካከል ያለው ግንኙነት የሚሰራውን መገንዘብ

የማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት በጠንካራ ፖለቲካዊ አመራር ላይ የተመረኮዘ ነው የሚለው እሳቤ፤ ለኢትዮጵያ መንግስትና ለኢህአዴግ እንዲሁም ለኢትዮጵያ የልማት ሞዴል ቁልፍ ፍልስፍና ነው፡፡[5] በእጅጉ የተቀናጀ የአሰራር አቅጣጫ፣ አያሌ ጠቀሜታዎች ያሉት ሲሆን የWIDE ጥናት ክትትል ባደረገባቸው አካባቢዎች፣ ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው በርካታ ግለሰቦችም ትልቅ ዋጋ የሰጡት ጉዳይ ነው፡፡ መረጃው፣ ዋነኛ ችግርን በተመለከተም የአካባቢ አመለካከቶችን ይሰንዳል፡፡ ይኸውም የልማትና የፓርቲ ፖለቲካዊ ጥቅሞችን በተመለከተ አካባቢያዊ አመለካከቶችን የማደባለቅ ወይም የማደናገር አዝማሚያ ነው፡፡ በአንዳንድ አጋጣሚዎች ራሳቸው ያገለሏቸው የሚያንፀባርቁትን አመለካከት ከፖለቲካ ውጭ ወይም ፀረ- ፖለቲካ በሆኑት ውስጥ የማጠናከር ሁኔታ ይታያል፡፡ የፓርቲ መሪዎች፣ እንደ "ግንዛቤ ችግር" የሚመለከቷቸው አብነቶችም በቀረቡት የማህበረሰቡ እማኝነት ውስጥ ተሰራጭተው ይገኛሉ፡- በ(ፓርቲ) ሊጎች እና (ፓርቲ-ባልሆኑ) ማህበራት መካከል ባለው ልዩነት ላይ ስላለው .... ብዥታ፤ የለ5 አደረጃጀት - የፓርቲ ሴሎች ጭምር - የፓርቲ ይሁኑ የመንግስት አሊያም የማህበረሰብ መዋቅሮች ጥርት ብሎ አለመታወቅ፡፡ ከፍተኛ የፓርቲ አመራሮች፤ በፓርቲና በመንግስት መካከል ስላለው ልዩነት በአንፃራዊነት የጠራ አቋም ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ነገር

[5] ለምሳሌ Meles Zenawi (2012) 'States and Markets: Neoliberal Limitations and the Case for the Developmental State' in Noman, Akbar, Kwesi Botchwey, Howard Stein and Joseph Stiglitz (eds) *Good Growth and Governance in Africa: Rethinking Development Strategies*, OUP, 140-174 ይመልከቱ፡፡

ግን የWIDE3 መረጃ አንኳር ነጥብ እንደሚያመለክተው፣ ዜጎች (ብዙ አባላትን ጨምሮ) አብዛኛውን ጊዜ ይሄን የጠራ አቋም አይጋሩትም፡፡

የአካባቢ የፖለቲካ መሪዎች ብዙውን ጊዜ በማህበረሰቡ ውስጥ ሌሎች በርካታ መደበኛ ያልሆኑ ሚናዎች ያሏቸው ሲሆን በልማዳዊና ማህበራዊ እንዲሁም በፖለቲካዊ አደረጃጀት ቡድን ወይም ማህበር ውስጥ ይሳተፋሉ፡፡ የጥናት ፅሁፉ እንደሚጠቁመው፤ እንዲህ ዓይነቶቹ ተቋማት አንዳንድ ጊዜ በመደበኛው ዘርፍ ከሚታየው ይልቅ የበለጠ አካታች፣ የተቀናጀና ተጠያቂነት ያለው ማህበራዊ ልማዶችን ይጠቀማሉ፡፡[6] የWIDE ትንተና፣ ዓላማ ተኮር የሆነው የወረዳ አስተዳደር አሰራር ልማዶች ብዙውን ጊዜ ከማህበረሰቡ የአሰራር መንገዶች ጋር እንደሚለያይ በመጠቆም ይህንን ምልከታ ያጠናክራል፡፡ (ለምሳሌ፡- በwww.ethiopiawide.net የቀረበውን የWIDE ጥናት ክፍል2 የማጠቃለያ ሪፖርት ይመልከቱ)፡፡ፖሊሲ አውጭዎች፤ የቀበሌና ወረዳ አመራሮች ትምህርት የመቅሰም አድማሳቸውን ከመንግስታዊ ወይም ፖለቲካዊ ንፍቀ ክበቦች በማስፋት፣የሌሎች ማህበራዊ ተቋማትን አቅምና አሰራር ለመጠቀም እንዲሁም የላቀ ትብብርን ለማጎልበት (ማጣቀሻ፡- ለውጥ) እንዲችሉ የሚያግዙባቸውን መንገዶች መፈተሽ ይገባቸዋል፡፡ የኢትዮጵያ የልማት ሞዴል የተቀረጸው፣ የፖለቲካ አመራሩንና የሰፊውን ህብረተሰብ ተሳትፎ ሙሉ አቅም አሟጦ ሲጠቀም ይበልጥ ስኬታማ እንዲሆን ታልሞ ነው፡፡

በጠንካራ የትራንስፎርሜሽን ቁልፍ ራዕይ የተቀረፀ የልማት ሞዴል፣ በመርህ ደረጃ ለመንደር ተጨባጭ ሁኔታዎች የማይሰራበት ምክንያት የለም፡፡ ነገር ግን አካባቢያዊ የችግር አፈታት (ማለትም ክፍት የሆነ፣ እንደየሁኔታው ተጣጥሞ የሚዛመድና በዕውቀት ላይ የተቃኘ) ስትራቴጂን ይጠይቃል፡፡ ይሄም ብቻ አይደለም፤ በመንደር ደረጃ ስላለው ፖሊሲና አተገባበር ጥናት የማድረግ፣ መረጃ የመሰብሰብ፣ ግብረ መልስ የመያዝ፣ ትንተና የመስራትና ዕውቀት የማደራጀት ጠንካራ ዘዴዎችንም ይፈልጋል፡፡[7] የኢትዮጵያ መንግስት፤ የተለያዩ የማህበረሰብ አስተዳደርና ከውጤታማ የጋራ እንቅስቃሴ ጋር የተያያዙ የፖሊሲ የትግበራ ሂደት ሞዴሎችን ማጥናትና መፈተሽ ዓላማው ያደረገ የልሂቃን ቡድን ወይም የምርምር ተቋም መመስረትን በትኩረት ሊያጤነው ይችላል፡፡ ለአነስተኛ የህብረተሰብ ጥናት እንዲሁም የልማታዊ ለውጥ ሂደቶች መሰረት ለሆኑት የጋራ ግንዛቤ ሁኔታዎች፣ ለማህበረሰብ ልማድ እንዲሁም ስኬትን ለመድገም ትኩረት አለመስጠት፣ በዓለም አቀፍ ደረጃና በታሪክ የተለመደ ችግር ሆኖ ዘልቋል፡፡ ዜጎች ዕውቀት የሚቀስሙበትንና ከአካባቢያቸው ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር አጣጥመው የሚያዛምዱባቸውን ሂደቶች ወደ አደባባይ ማምጣት (ምን እንደሚሰራና ምን እንደማይሰራ እንዲሁም መቼና ለምን እንደሆነ በማጤን)፣ በግብርና ዘዴዎችና የገበያ ትስስሮች ወይም በኢንዱስትሪ የቴክኖሎጂ ሽግግር ሂደቶች ላይ እንደሚደረገው ጥናትና ሙከራ ሁሉ፣ ለኢትዮጵያ ትራንስፎርሜሽን ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ እንደሚችሉ፣ የWIDE3

[6] Pankhurst, Alula (2008) Community-Initiated Association and Customary Institutions in Ethiopia: Categorisation, Characeristics, Comparisons and Potential for Involvement in Development and Social Accountability, ያልታተመ ጥናታዊ ጽሁፍ ይመልከቱ፡፡

[7] Booth, David (2012) Development as a collective action problem: Addressing the real challenges of African governance, ODI for Africa Power and Politics Programme, October 2012.

የጥናት ግኝቶች ይጠቁማሉ፡፡ ይህ ርዕሰ ጉዳይ ለውጥ በሚለው አጭር ጽሁፍ ላይ በስፋት ተዳስሷል፡፡

<u>ማጠቃለያ፡- ከእያንዳንዱ ማህበረሰብ ጋርና ለእያንዳንዱ ማህበረሰብ የሚሰራ ሂደት</u>

የWIDE ጥናት ዋነኛ ነጥብ - እንዲሁም የኢትዮጵያ መንግስት ፖሊሲ አውጭዎችና የልማት አጋሮቻቸው ዋነኛ ተግዳሮት - "ፈተናው ያለው በዝርዝር ውስጥ"፣ በትንሿ የመንደር ደረጃ መሆኑ ነው፡፡ የኢትዮጵያ የልማት ሞዴል፣ ከየትም በተገኘ የኒዮ-ሊበራል ፍልስፍና የማይተነተን፣ የራሱ የተለየ ባህርይ እንዳለው ሁሉ፣ በተመሳሳይ ሁኔታ፣ እያንዳንዱ የኢትዮጵያ ንኡስ ቀበሌ ማህበረሰቦችም፣ ከላይ ባሉት መሪዎች ወይም ከእነሱ ልቀው በሚገኙቱ ትንታኔ የማይገዛ፣ የራሱ የተለየ የለውጥ ሂደቶችና ፈተናዎች አሉት፡፡ ጄምስ ስኮት፤ *“Seeing Like a State: how certain schemes to improve the human condition have failed”* (Yale, 1998) በሚል ርዕስ የጻፈው ዘመን ተሻጋሪ ሥራው፤ ስኬታማ ለሆነ የማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ለውጥ ቁልፍ ሚና የሚጫወተው፣ የገበሬ ማህበረሰቦች አካባቢ በቀል ሙያዊ ክህሎት (ብዙ ጊዜ እንደ ኋላቀርነት፣ ጠባብነት ወይም ወግ አጥባቂነት ተቆጥሮ ውድቅ የሚደረግ) መሆኑን በመጥቀስ፣ ለዚህ አካባቢ በቀል ሙያዊ ክህሎት፣ አድናቆትና ክብር ይቸረዋል፡፡ የWIDE መረጃ እንደሚጠቁመው፤ የኢትዮጵያ የልማት ሞዴል ውጤት፣ በአብዛኛው የሚወሰነው፣ ምን ያህል ተመሳሳይ አቅጣጫ ይከተላል በሚለው ነው፡፡

“የቴክኖሎጂ ሽግግር” እና ለውጥ

የዕውቀት ስርጸት፣ ከተሞክሮዎች መማር፣ “የቴክኖሎጂ ሽግግር” እና ለውጥ በገጠር ማህበረሰቦች

WIDE የውይይት መነሻ አጭር መግለጫ ቁ. 10/...10[1]

<u>ዋና ዋና ነጥቦች - ከWIDE የጥናት መረጃዎች</u>

- ኢትዮጵያ፤ ከዳር እስከ ዳር ባዳረሰው፣ አዲስ ልማታዊ አሰራሯ፣ ትደነቃለች:: ይሄ እንዴት መንግስት- መር የተነቃቃ የገጠር ትራንስፎርሜሽን እንደፈጠረ የWIDE መረጃ ያሣያል::
- ነገር ግን “የአንዱ እውነት ለሁሉም አይሆንም”:: በመንግስት ማዕቀፎች ወይም ሞዴሎች አማካኝነት የሚደረግ የቴክኖሎጂ ሽግግር ሁሌ፣ ከእያንዳንዱ አካባቢ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ጋር ተጣጥሞ የተቀረጸ አይደለም፤ መልዕክቱም በጥንቃቄ አይተላለፍም፤ ወይም የቅድመ ፍተሻ ሙከራም በአግባቡ አይደረግም፤ የበለጠ ይጠቀሙበታል በሚባሉት አካባቢዎችም ሰርቶ ማሳያ አይዘጋጅም::
  - “የቴክኖሎጂ ሽግግር” ውጤቶች የበለጠ ሊሻሻሉ የሚችሉት፣ ለሚከተሉት ጉዳዮች የቅርብ ትኩረት በመስጠት ነው:-
    - አካባቢያዊ ዕድሎች ለትምህርትና ለፈጠራ ያላቸው አመቺነት፤
    - መደበኛ ያልሆነ የማኅበረሰብ እውቀት ስርጸት ሂደቶች፣ ውስብስብነት እንዲሁም ውጤታማ "የቴክኖሎጂ ሽግግርን" የሚያጠናክር አካባቢያዊ ጥቅምን ማስላት፤ እና
    - አካባቢው የግለሰብ ወይም "አፈንጋጭ" ፈጠራን ለመቅዳት አካባቢው ያለው ልማታዊ አቅም፤
  - ይሁንና፣ እንዲህ ዓይነት አካባቢያዊ ልዩነቶች፣በአሃዛዊ ግቦች ወይም ብሄራዊ ማዕቀፎች አማካኝነት ማግኘት አስቸጋሪ ነው::

[1] ይህ አጭር ጥናት መግለጫ፤ በWIDE የውይይት መነሻ አጭር የጥናት መግለጫዎች ሁለተኛ ጥራዝ (ስብስብ) ውስጥ ከተካተቱት አስር መግለጫዎች አንዱ ነው:: መግለጫው፤ በሣራ ሾን የተዘጋጀ ሲሆን በዘሪሁን ሞሃመድ ተገምግሟል:: አዘጋጁ፤ መግለጫዎቹ ይሰናዱ ዘንድ በገንዘብ ለደገፉት ለእንግሊዝ ዓለም አቀፍ የልማት ተቋም፣ ለአይሪሽ ኤይድና ለስዊድን ዓለምአቀፍ የልማት ኤጀንሲ ልባዊ ምስጋናዋን ታቀርባለች:: በተጨማሪም የጥናት ሪፖርቱን በማርቀቅ ሂደት የተሳተፉና አጭር የጥናት መግለጫው የትኩረት አቅጣጫ እንዲሰላ እገዛ ያደረጉ ሌሎች የጥናት ቡድን አባላትና ባለሙያ ገምጋሚዎች፣ ለሥራው ለሰጡት ጊዜና ድጋፍ ታመሰግናለች:: ሌሎች ምስጋናና ዕውቅና የሚያሻቸውም አሉ:- (1) ለዓመታት የጥናት መግለጫው የተዘጋጀበትን መረጃዎች ያሰባሰቡና ያደራጁ የጥናት መኮንኖችና ተቆጣጣሪዎች ሙሉ ጊዜያቸውን ሰጥተው ላበረከቱት አስተዋጽኦ፤ (2) በሶስት ዙሮች ለተካሄደው የWIDE ጥናት የገንዘብ ዕገዛ ላደረጉ የተለያዩ ድጋፍ ሰጪ ተቋማት፤ እና (3) በኢልምት ሰብሳቢነትና በኢኮኖሚ ፖሊሲ ትንተና ክፍሉ በWIDE አጭር የጥናት መግለጫዎች ሁለተኛ ጥራዝ ላይ ለመወያየት መጋቢት 28 ቀን 2016 ዓ.ም በተዘጋጀው መድረክ ላይ የተሳተፉ ከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣናት፣ ላሳዩት ፍላጎትና ለከፈሉት የጊዜ መስዋዕትነት--- ምስጋና ይገባቸዋል:: የጥናት መግለጫው፤ በከፍተኛ ደረጃ በተዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ፣ ከመንግስት ባለሥልጣናት ጋር በተደረገው ውይይት የተሰጡ አስተያየቶችን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ከለሳና ማሻሻያ ተደርጎበታል:: አጭር የጥናት መግለጫው፤ የኢትዮጵያ የልማት ምርምር ተቋምን (ኢልምት) ወይም የኢትዮጵያ መንግስትን አሊያም የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርጉለትን የልማት አጋሮች አመለካከትም ሆነ አቋም አይወክልም፤ ይልቁንም የፖሊስ ውይይት ለማነቃቃት የታለመ ነው:: ሌሎች የጥራዝ ሁለት የውይይት መነሻ አጭር መግለጫዎችንና የጥናትና ምርምር ውጤቶችን በhttp://ethiopiawide.net/ ድረ-ገጽ ላይ ማግኘት ይቻላል::

- የመስኖ መስፋፋት ብዙ ጊዜ፣ ሰፊ የአካባቢ ኢኮኖሚያዊ ፍላጎቶችንና አማራጮችን ይለውጣል፡፡ ይህም በፊናው የእርሻ ባለሙያዎች ከሚያስቡት የላቀ፣ አዳዲስ የአሰራር ልማዶችንና ለውጥን ይፈጥራል፡፡
  - የተለያዩ የገበያ አዝዕርትን የማምረት እንዲሁም በደሞዝ ተቀጥሮ የመስራት ወይም የቀን ሥራ ዕድሎችንና አዲስ ተሞክሮዎችን ይፈጥራል፤
  - የአካባቢ የገበያ ትስስሮችና ከነጋዴዎች ጋር የሚፈጠር ግንኙነትን ያጠናክራል፤
  - የኑሮ መተዳደርያና የምግብ ፍጆታ አማራጮችን ያሰፋል፤ በዚህም ሳቢያ የምግብ ዋስትና ባልተረጋገጠባቸው አካባቢዎች፣ የምግብ ዋስትናን ያሻሽላል፡፡
  - ለሁሉም ባይሆን ለአንዳንድ የማኅበረሰብ አባላት ከፍተኛ የመበልጸግ አቅምን ያሳድጋል፤ እና የከተማ ትስስሮችን ያጠናክራል፡፡
    - የገጠር የሥራ ፈጠራን ለማሳደግ የሚጀመሩ ፕሮጀክቶች፤ ሁሉንም በመስኖ ዙሪያ እያበቡ ያሉ አነስተኛ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ለውጦች አሟጠው መጠቀም ላይ ሊያተኩሩ ይችላሉ፡፡ እያደገ ባለው አካባቢያዊ የገንዘብ ኢኮኖሚ ዕድሎች ውስጥ፣ ከአካባቢ አገልግሎቶች እስከ ቀን ሰራተኞች ወይም ነጋዴዎችና የግል ዘርፉ አዳዲስ ፍላጎቶች ይፈጠራሉ፡፡
    - በመስኖ ልማት ስኬታማ የሆኑ አርሶ አደሮች፣ የኪሳራ ሥጋትን በሁሉም የገቢ ምንጮች ላይ በማዳረስ፣ አዳዲስ አሰራሮችን በጥንቃቄ ይተገብራሉ- ይሄ መንግሥት ምርትን ለማሳደግ ሲፈልግ ሊተገብረው የሚችል በስፋት የተለመደ ስልት ነው፡፡
    - ከአካባቢ ሥነ-ምህዳሮችና የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር ከሚጣጣሙ፣ የተለያዩ ዓይነት የለውጥ እርምጃዎች ወይም ፕሮግራሞች ድጋፍ ጋር ከአንድ በላይ የመስኖ አሰራር ዘዴን ከግምት ውስጥ ማስገባት ይገባል፡፡
- በገጠር አካባቢዎች የእርሻና ሌሎች ፈጠራዎች በጣም የተነቃቃና የተለያየ ነው፤ በሁሉም የህብረተሰብ ቡድኖችና ግለሰቦች ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎችን እንዲሁም ማህበራዊ፣ ባህላዊና ሌሎች የማህበረሰብ እምነቶችንና ልማዶችን ያካትታል፤ እነዚህ ብዙዎቹ ደግሞ እርስ በርስ ይደጋገፋሉ፡፡
- ከፈጠራ የሚገኘው ትምህርት፣ ቀጥተኛ ያልሆነና የማይገመት ነው፤ ብዙ ጊዜም በጣም አካባቢ ተኮር ነው፡፡ እጅግ የተዋጣለት ፈጠራ ወይም እንደየሁኔታው ተጣጥሞ የተሻሻለ ትግበራ በአብዛኛው የሚገኘው በይፋ ሞዴል ተብለው ከተሰየሙት አይደለም፤ ጎረቤቶችን ጨምሮ ዳግም ሰፋሪ ማህበረሰቦች፣ የስደት ተመላሾች፣ መጤዎች፣ ተማሪዎችና ሌሎች የቤተሰብ አባላት፤ ሁሉም (ብዙ ጊዜ አይጠበቁም) የአዳዲስ አሰራር፣ ዋና ምሳሌዎች ሆነው ብቅ ይላሉ፡፡
- ፈጠራ፣ ብዙ ጊዜ፣ ከሃብት ልዩነት መከሰት እንዲሁም ከአነስተኛ የከተማ ማዕከላት ዕድገት ጋር ትስስር ባላቸው የገጠር አካባቢዎች በሚገኙ ወጣቶች ዘንድ እያደገ የመጣውን የሥራ ፈጠራ ግንዛቤን ያመለክታል፡፡ አነስተኛ-የኢኮኖሚ የሥራ ፈጠራ፣ (ለምሳሌ፡- ከብት ማደለብ ወይም የወተት ምርት) በተለየ ሁኔታ፣ ለዋጋ መዋዠቅ የተጋለጠ ነው፤ ይሄ ግን የእርሻ ምርት አብቃይ በሆኑ አካባቢዎች ብቻ አይደለም፡፡

- የገጠር የሥራ ፈጠራን እንዲሁም ገቢና ምርትን ለማሳደግ የሚቀየሱ ስልቶች፣ ከመደበኛው የጥቃቅን እና አነስተኛ ዘርፍ ውጭ ከሚገኙ የኢኮኖሚ ፈጠራዎች መማር አለባቸው፡፡ ሁሉም ሰው አዲስ ነገር የመፍጠር አቅም አለው ማለት አይደለም፤ ቴክኒካዊ ያልሆነ እውቀትና ሀብት የሚጠቀሙ እንዲሁም ቴክኒካዊ ወይም የቴክኖሎጂ ክህሎት ያላቸው ናቸው የሚፈጥሩት፡፡

- መደበኛ ባልሆነ መንገድ እንደየሁኔታው ተጣጥመው፣ የተቀረጹ ስኬታማ አሰራሮችና ፈጠራዎች ዙሪያ የተደራጀ የገጠር መረጃ እንደሚጠቁመው፤ ለውጥ የአዲስ አመለካከቶች ሚና የሆነውን ያህል፣ የማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ሃብቶች፣ ዕድሎችና መልካም አጋጣሚዎችም ሚና ነው - በተለይ በወጣቶች ዘንድና የተነቃቃ ኢኮኖሚ ባላቸው ማህበረሰቦች፡፡

  - ለማኅበረሰባዊ መስተጋብርና ተቋማዊ በሆነ የሰርቶ ማሳያ ወይም ሞዴሎች አሰራር ትምህርት ለመቅሰም ትኩረት የሚሰጡት የመንግስት አቅጣጫዎች፣ ተጠቃሽ ስኬት አስመዝግበዋል፡፡ የ"አመለካከት ለውጥ" ለማምጣት የሚቀየሰው ስትራቴጂ ግን በጥንቃቄ መቃኘት ይፈልጋል፡፡

- ፈጠራ ወይም ውጤቱ፣ አዎንታዊ አሊያም አሉታዊ ሊሆን ይችላል፡፡ በእጅጉ ከተስፋፉ፣ የከተማ ትስስሮች፣ከሰዎች ዝውውር፣ ከተለወጡ የሥነ ፆታ ግንኙነቶችና የሃይማኖት ሐሳቦች ጋር የተያያዙ አዳዲስ አሰራሮች፣ ብዙውን ጊዜ፣ በትውልዶች መካከል ወይም በማኅበረሰባዊ ዘርፎች የተለያዩ ምላሾችን ያስከትላሉ - ግጭትም ጭምር፡፡

- ተጨባጭ የፈጠራ አቅምን የሚያጠናክር ትምህርት፣ አብዛኛውን ጊዜ አዲስ የዕውቀት ፕሮግራም በጅምላ ወይም በማዕቀፍ በማዳረስ አይሳካም፡፡ ለ“ዘመናዊ ሙያዊ ክህሎት” የተለየ ክብር የሚሰጥ የተዋረድ አመለካከት፣ በማህበረሰብ ደረጃ የሚካሄዱ ፈጠራዎችን ሊያደናቅፍ ይችላል፡፡ ይሄን አመለካከት ማስወገድ፣ የማህበረሰብ ትምህርትን ነጻ ለማውጣት ወሳኝ ይመስላል፡፡

  - የመንግስት የአሰራር አቅጣጫዎች የበለጠ ሊሻሻሉ የሚችሉት፡-
    - በአማራጭ የፖሊሲ ትምህርት ወይም ስርጸት ሞዴሎች ላይ በቅጡ የታቀደ ጥናት በማካሄድ፤
    - ለአካባቢ-በቀል ፈጠራና አዲስ አሰራር እንዲሁም ለማኅበራዊ እሴት ትኩረት በመስጠት፤ እና
    - የ"አዎንታዊ ማፈንገጥ" ልማታዊ አቅምን ለማወቅና ለመጠቀም፣ ማህበረሰብ-ተኮር የፕሮጀክት ጥንሰሶችን በመፈተሽ ነው፡፡
  - ኢኮኖሚው በተለያየ ዘርፍ ሲሰፋ፣ የአካባቢ ተቋማዊ አቅም ያድጋል፣ የመረጃና የትምህርት ግብረ-መልስ ክፍተቶችም ይሻሻላሉ፤ በየአካባቢው፣ የመንግሥት ተዋናዮችን የአሰራር ስትራቴጂ ማሻሻል፣ ማህበረሰቦች፣ አሁን ያለውን "ምርጥ ተሞክሮ" ጠብቆ ለማቆየት ወይም ለማሳደግ አሊያም አዲስ ለመፍጠር ሊያግዛቸው ይችላል፣ ይሄም በአካባቢ የተፈጠረና በአካባቢ ባለቤትነት የተያዘ፣ አነስተኛ የቴክኖሎጂ ሽግግርና የዕውቀት ስርጸትን ያስፋፋል፡፡

<u>መግቢያ፡- የማህበረሰቦችና ግለሰቦችን የፈጠራ አቅም አሟጥጦ መጠቀም</u>

“የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች ኢኮኖሚ በሽግግር ላይ ነው፤ ከዚህ በኋላ ወደፊት እንጂ ወደ ኋላ መመለስ የለም”[2] የሚለው ጉዳይ፣ ሲያነጋግር ቆይቷል። በረኸርም ጊዜ የጥናት ክትትል የተገኘው፣ የWIDE ንጽጽራዊ መረጃ፣ አዲስ ግኝት፣ ፈጠራ፣ ትምህርት መቅሰምና ለውጥ በሚሉ ሃሳቦችና አብነቶች የታጨቀ ነው። ኢትዮጵያ፤ የገጠሩን ክፍል ከዳር እስከ ዳር ባዳረሰው፣ አዲስ ልማታዊ አሰራሯ፣ በስፋት ስትደነቅ ቆይታለች። በተለይም በግብርና እና በጤና ዘርፎች[3] እንዲሁም ከመቼውም ጊዜ በላቀ ሁኔታ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎችን ወደ ት/ቤት በማስገባት ተወድሳለች(ማጣቀሻ፡- ትምህርት)። ይሁን እንጂ፣ በWIDE ኢትዮጵያ ጥናት፣ በመንደር ደረጃ የተሰነዱ፣ ተጨባጭ የህይወት ተሞክሮዎች ሁለት ነገሮችን ያረጋግጣሉ ፡- ውጭያዊ የለውጥ እርምጃዎች፣የትልቁ ስዕል አንድ አካል ብቻ መሆናቸውን፣ እንዲሁም እነሱም ቢሆኑ ሁሌም እጅግ የተዋጣላቸው እንዳልሆኑ ነው።

በመንግስት ማዕቀፎች ወይም ሞዴሎች አማካኝነት የሚደረግ የቴክኖሎጂ ሽግግር ሁሌ፣ ከእያንዳንዱ አካባቢ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ጋር ተጣጥሞ የተቀረጸ አይደለም(ማጣቀሻ፡- ስኬት)። መልዕክቱም በጥንቃቄ አልተላለፈም፤ የቅድመ ፍተሻ ሙከራም በአግባቡ አልተደረገም፤የተሻለ ሊጠቀሙበት በሚችሉበት አካባቢም፣ ሰርቶ ማሳያ አልተዘጋጀም። ይሄ አጭር የጥናት መግለጫ፤ አርአያዎች/ሞዴሎች በሚለው ጽሁፍ ላይ በመመስረት የዕውቀት ስርጸት፣ ትምህርት መቅሰም፣ አዲስ ፈጠራና ለውጥ፤ እንዴት፣ መቼና ለምን እንደተከሰቱ (እና መቼ እንዳልተከሰቱ) ለማወቅ፣ የWIDE ኢትዮጵያ ጥናት መረጃን፣ አንኳር ርዕሰ ጉዳዮች ይፈትሻል። በተጨማሪም፣ የፖሊሲ አንደምታዎችና የተገኙ ተሞክሮዎችንም ይዳስሳል። የWIDE ጥናት ግኝቶች፤ በሁሉም ክትትል በተደረገባቸው ማህበረሰቦች፣ ፈጠራን፣ ትምህርት መቅሰምን፣ የዕውቀት ስርጸትንና የአሰራር ለውጥን በተመለከተ የዳበሩ ማስረጃዎችን የሚያቀርብ ሲሆን ሁሉም ከመንግስት ተጽዕኖ አልፈው ተሻግረዋል። ይሄ ብዝሃነትና ውስብስብነት በራሱ እንደሚጠቁመው፤ በተመሳሳይ የሙያ ክህሎት ተዋረድ,፣ አርሶአደሮችን ለማነቃቃት፣ አዲስ የልማት ማዕቀፎችን በጅምላ የማዳረስ ዝንባሌ አሳሳች ነው። ሊያከራክር ቢችልም እንዲህ ያለው አካሄድ፣ የለውጥ መንገዶችን ከማፍካት ይልቅ የማዳፈን ሚናው የበረታ ነው። የዚህ አጭር መግለጫ ሁለተኛ አጋማሽ፤ እንዲህ መሰሉን ለውጥ፣ በግለሰቦችና በሰፊው የማኅበረሰብ ትስስሮች ዘንድ፤ ከሚከተሉት ፍሬ ሃሳቦች አንጻር ይዳስሳል ፡-

- የእርሻ ፈጠራ ቁልፍ ገጽታዎች፤ያልተጠበቁ ምንጮችና ምሳሌዎችን ጨምሮ፤
- የከተማ ባህል፣ ትስስሮችና የሰዎች ዝውውር ተጽዕኖ፣ አብነቶች፤
- የቤተሰብ አባላት ሚና እና የሃሳብና የቁስ ሃብታቸው፤ እና
- የንግድ፣ በማኅበረሰብ ውስጥ ያለ ደረጃና “የስኬት ትስስሮች” ፋይዳ።

[2] Ege, Svein (2015) ‘The New Economy: Agricultural Transformation in North Shäwa, Ethiopia,’ በ19ኛው የኢትዮጵያ ጥናቶች ዓለም አቀፍ ጉባኤ ላይ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ፤ ዋርሶው፡ ከነሐሴ 24-28፣ 2015።

[3] ለምሳሌ Gates, Bill (2012) ‘Exciting innovations in agriculture and health’ GatesNotes, 8 May, ይመልከቱ፤ https://www.gatesnotes.com/Development/Ethiopia-Exciting-Innovations-in-Agriculture-and-Health ድረገጽ ላይ ይገኛል።

የመንግሥት ስትራቴጂ - ለፈጠራና ለቴክኖሎጂ ሽግግር

አንድ ኢትዮጵያዊ ተንታኝ፤ (አሁን ከፍተኛ የመንግሥት ባለስልጣን ሆነዋል) በአንድ ወቅት እንዲህ ብለው ነበር፡-

> *ፈጠራ፤ አካባቢ በቀል ልማትን፣ ማኅበረሰባዊ መማማርንና የተቀናጀ ተግባርን የሚያካትት ሲሆን እነዚህም ከመስተጋብርና ከተቋማዊ ለውጥ ይከሰታሉ* (ይናገር ደሴ 2012: 8)::[4]

ይህ አቅጣጫ - የአመለካከትና አሰራሮች ለውጥ ለማምጣት፣ የጋራ መማማርንና የተቀናጀ ተግባርን የሚደግፍ ሲሆን ለገጠር የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የመንግሥት ስትራቴጂ መሰረት ጥሏል:: ትምህርት የመቅሰም፣ የፈጠራና "አመለካከቶች መለወጥ" የሚለው አቅጣጫ፤ በመንግሥት ልማታዊ (እና ፖለቲካዊ) ስትራቴጂዎች እምብርት ላይ ነው:: ተቋማዊ በሆነ መንገድ ሞዴሎችንና ትስስሮችን በመጠቀም የመስራት ሥርዓት፣ በመንግስት በውጭ የተቀረጹ ልማታዊ ፈጠራዎችን፣ በከፍተኛ መጠን መተግበርን ለማሳደግ፣ የታለመ ነው:: በጌዴኦ ዞን፣ አንድ ሞዴል አርሶ አደር፣ የአስተዳዳሪዎቹን ሃሳብ እንዲህ ሲል ይጋራል፡-

> *ብዙ ጊዜ ስኬታማና ሞዴል አርሶ አደሮች አዲስ ነገሮችን ለመቀበል ጥሩ ናቸው:: ስለዚህ አዲስ ቴክኖሎጂ ለማኅበረሰቡ ለማቅረብ ሲታሰብ፣ ለትግበራ መጀመሪያ ሞዴልና ስኬታማ አርሶ አደሮች ይመረጣሉ፤ እንደ ማሳያም ያገለግላሉ* (ሞዴል አርሶ አደር፤ አዳዶ)።

እንደ ጌዴኦ አካባቢ ሁሉ፣ (ከሌሎቹ የላቀ ሃሳብ አመንጪ፣ የተነቃቃና በእጅጉ ያደገ ጨርሶ አይደለም):: በመላው አገሪቱ የልማት ቡድኖች አባላት፣ የግብርና ትምህርት ይከታተላሉ፣ አትክልት ያበቅላሉ፤ እንዲሁም ልምድ ይለዋወጣሉ:: የሴት የልማት ቡድኖች አባላት፣ "እርስ በርስና ከ1 - ለ5 ቡድናቸው ይማማራሉ"፤ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ደግሞ፤ ብዙ ጊዜ ከ35 ዓመት ዕድሜ በታች ላሉና፣ "አዳዲስ ነገሮችና አዳዲስ ትምህርቶችን ለሚቀበሉ ቅድሚያ ይሰጣሉ":: 1ለ5 አደረጃጀት፤ ለብቻ ከመሥራት ይልቅ በዙር፣ በህብረት የመስራት አዲስና ይበልጥ ውጤታማ አሰራር መተግበሩ ተነግሯል:: በብዙ አካባቢዎች፣ ለቀበሌ ቅርበት ያላቸው አሊያም በሞዴልነት ወይም በፓርቲ አባልነት[5] የሚሳተፉት፣ "አዳዲስ ሐሳቦችን" ወይም "አዲስ የልማት የለውጥ እንቅስቃሴዎችን" በፍጥነት ለማግኘት በስብሰባዎች ላይ መሳተፋቸው እንደጠቀማቸው ይገልጻሉ (ማጣቀሻ፡- ስኬት):: ቴሌቪዥንና ሬዲዮ የአዲስ ሀሳቦችና ፈጠራዎች ምንጮች በመሆን በጋራ ተጠቅሰዋል (ለምሳሌ፡-አዜ

---

[4] ይናገር ደሴ በላይ (2012) 'Assessing the role of social learning, institutions and social capital for soil conservation in Northern Ethiopia' ለቬና ዩኒቨርሲቲ ለፒኤችዲ መመረቂያ የቀረበ፤ http://www.boku.ac.at/fileadmin/data/H04000/H16900/Resources/Scientific Pub/Yinager Dessie Belay_2012 ድረገጽ ላይ ይገኛል፤ *እዚህ የቀረበው መከራከርያ ሃሳብ Röling, N. (2009) 'Conceptual and methodological developments in innovation', in Sanginga, P., Waters-Bayer, A., Kaaria, S., Njuki, J., Wettasinha, C. (eds), Innovation Africa: enriching farmers' livelihoods,* London: Earthscan, ከገጽ 9-34 ይጠቅሳል::

[5] የፓርቲ አባላት ስለ "ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድና አዲስ የተዋወቁ ወይም የታቀዱ የለውጥ እንቅስቃሴዎች ግንዛቤ ማግኘታቸውን" ገልጸዋል:: (አዴሌ ኬኬ/ምስራቅ ሃረርጌ ፤ 145፤ አዜ ደቦአ /ከምባታ፣ 123፤ ገልቻ/ምሥራቅ ሸዋ ፣35፤ ሃሬርሳው /ምሥራቅ ትግራይ፣ 196፤ ሉቃ/ጸማይ፣ 64,106)፤ ብዙ ጊዜ "ከአነበቡት" (ለምሳሌ፡- አዳዶ/ጌዲአ ፣183) በመላው ማህበረሰቦች ውስጥ ዜና መጽሄቶችና የፓርቲ ህዋስ ውይይቶች ለዚህ ሂደት ቁልፍ በመሆን አገልግለዋል:: በበርካታ የWIDE አካባቢዎች የቀበሌ አጠቃላይ ስብሰባዎች የተጀመሩ ሲሆን "አዳዲስ ነገሮች ሲመጡ" መረጃ ለማግኘት ጠቃሚ እንደሆኑ ይታሰባል፤ ቀደም ሲል ግን በውጭያዊ አካል የሚተዋወቁ አዲስ የፈጠራ አሰራሮች ለማህበረሰቡ አደናጋሪ ተደርገው ይታዩ ነበር (ለምሳሌ፡- አዳዶ/ጌዲአ፣ 183)::

ዴቦአ/ከንባታ፣ ጋራ ጎዶ/ወላይታ)፤ የኤች አይቪ/ኤድስ ህሙማን በሌሉባቸው አካባቢዎች እንኳ ስለ በሽታው ያለው ግንዛቤ ጨምሯል (አዳዶ/ጌዴአ)፡፡ “ስለ ገበያ አዳዲስ ሐሳቦች” ለማግኘትም ጠቅሟል፡፡ በበርካታ ማህበረሰቦች፣ ነዋሪዎች፣ ቴሌቪዥን መመልከት፣ "የአኗኗር ሁኔታቸውን ለማሻሻል፣ የተማሩትን ለመተግበር ለሚሞክሩ ቤተሰቦች ጥሩ ነው" ብለው ያስባሉ (አዴሌ ኬኬ/ምስራቅ ሐረርጌ)፡፡ ለምሳሌ፡- የጤና ኤክስቴንሽ መረጃ፡፡ ሥርዓቱ በጣም ተጠቃሽ የሆነ፣ አዲስ ዕውቀትና የልማት ጥቅሞችን አስገኝቷል፡፡ ነገር ግን (አርአያዎች/ሞዴሎች በሚለው ጽሁፍ ላይ እንደተገለጸው) የገጠር ፍላጎቶችን ለማሟላትና የገጠር ኢኮኖሚያዊ አማራጮችን አሟጥጦ ለመጠቀም፣ በእጅጉ ሊሻሻልና ይበልጥ ሊቃኝ ይችላል፡፡ በተለይ፣ ሰፊ ማኅበራዊ ትስስር ያላቸው፣ ለአካባቢው አስተዳደር ቅርብ ከሆኑት ውጭ ያሉት፣ ስለ እነዚህ ፕሮግራሞች አያውቁም፣ አይሳተፉም ወይም ፍላጎት የላቸውም፡፡ ለዚህ አጠቃላይ ችግር የሚቀርበው ማስረጃ ቀልብ የሚስብ ነው፡፡

<u>አሉታዊ ተሞክሮዎችና የመንግሰት መር ፈጠራ ክሸፈቶች</u>

ሁሉም መንግሥት-መር የቴክኖሎጂ ሽግግርና ፈጠራዎች ስኬታማ ነበሩ ማለት አይደለም፡፡ አንዳንድ ችግሮች ከታወቁ የዕይታ አንጻሮችና የቅድሚያ ትኩረቶች የሚፈጠሩ ይመስላሉ፡፡ በአብዛኞቹ አካባቢዎች፣ የሴቶች ማኅበራትና ሊጎች፣ በቀበሌ ደረጃ ይሄ ነው የሚባል ስኬት አልተቀዳጁም (ሀርሬሳው/ምሥራቅ ትግራይ) ወይም እየሰሩ ነው ለማለት ያዳግታል (ዶአማ/ጋሞ)፤ መሪዎቹ አልፎ አልፎ ከወረዳ አስተባባሪዎች ጋር ለመስራት ወይም ኃላፊነታቸውን በትኩረት ለመወጣት ፈቃደኛ እንዳልሆኑ ይገለጻል፡፡ በገለቻ/ምስራቅ ሸዋ፣ አንድ በኑሮዋ የደረጀች ሴት፤ ጓደኞቿ ለረዥም ጊዜያት ለመሰባሰብ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው፣ የወሰደችውን ስልጠና ለነሱ ለማስተላለፍ እንዳልቻለች ታስባለች፡፡

ሌላቹ ችግሮች፣ ከሚሰጠው ምክር ጥራት ጋር ይገናኛሉ፡፡ በአዳዶ/ጌዴአ፣ አዲስ በተዳቀሉ ችግኞች የተነሳ፣ የቡናና የእንሰት በሽታ ተከስቷል፡፡ በቀበሌ ሃላፊዎች የተወደዱ ፈጠራዎች፣ በስፋት ተቀባይነት የሚያገኙ አይመስሉም፡፡ የእንስሳት ፍግና የተለያዩ ነገሮችን አደባልቆ፣ እንደ ማዳበሪያ መጠቀምና በየጊዜው ችግኞቹን በሌላ መተካት ችግር የሌለው ይመስላል፡፡ ነገር ግን በፍጥነት የሚደርሰው አዲስ ዓይነት የቡና ዝርያ ተወዳጅነት አላገኘም፡፡ ገንዘብ የመቆጠብ ሀሳብ በስፋት የተዋወቀ ሲሆን ብዙዎች ግን መፍትሄ ያልተበጀለትን ሥር የሰደደ የብድር እጥረት ክፉኛ ይተቻሉ፡፡ ገንዘብ የተበደሩ ሰዎች ደግሞ አስቸጋሪ ተሞክሮዎችን አሳልፈዋል፤ የኦሞ ማይክሮ ፋይናንስ የአመላለስ ሂደቱን ለማሻሻል ሙከራ ቢያደርግም፡፡ የብድር እጥረት ተጽዕኖ፤ አዳዲስ አሰራርና የሥራ ፈጠራን እንዴት እንደሚያደናቅፍ በWIDE የጥናት መረጃ ውስጥ በስፋት ቀርቧል፡፡

የWIDE መረጃ እንደሚጠቁመው፤ በመንግስት የሚደገፍ ፈጠራ፣ ብዙውን ጊዜ ያልተፈለጉና ያልተጠበቁ የጎንዮሽ ችግሮች አያጡትም፡፡ ከአየር ማረፊያ እስከ ላሊበላ ከተማ የተሰራው አዲስ የአስፋልት ግንባታ፣ በሰሜን ወሎ የምትገኘውን ሹምሸሃ ከተማን ወደ ጎን ትቶ ማለፉ፣ መልካም የኢኮኖሚ ዕድሎችን በማስቀረቱ፣ በአካባቢው ነዋሪ ላይ መከፋትና ቁጣን ፈጥሯል፡፡ ምርታማ የምግብ ዋስትና ዕገዛ ፕሮግራም፣ በበርካታ የጥናቱ አካባቢዎች፣ የሚሰጠውን ማበረታቻ ቅርፅ በመለወጥ ረገድ ጠቃሚ ተፅዕኖ ፈጥሯል፡፡ በአንዳንድ ቦታዎች፣ የሥራ ሥነ ምግባርን ያነቃቃል

ተብሎ ይታሰባል (ገለቻ/ምስራቅ ሸዋ)፡፡ በሌሎች የተለያዩ አጋጣሚዎች፣ አሉታዊ የጎንዮሽ ችግሮች ተስተውለዋል፤ ለምሳሌ በዶኦማ/ጋሞ፣ የምግብ ዋስትና ዕገዛ ፕሮግራም፣ በየአካባቢው የተለመደውን የማኅበረሰብ የጋራ ባህላዊ የበጎ ፍቃደኝነት ሥራን በማዳከም፣ “አዲስ ዝንባሌ እየፈጠረ” መሆኑን በWIDE ቃለመጠይቅ የተደረገላቸው ግለሰቦች ተናግረዋል፡፡ በ2003 የመሬት አስተዳደር ለውጥ፣ በሃረሳው/ምስራቅ ትግራይ፣ ያልተፈለገ ውጤት አስከትሏል፤ ሃላፊነት ከጣቢያ መዋቅር በመቀየሩ በጎጦች መካከል ግጭት ተፈጥሯል፡፡

የሴቶች ማኅበራት ደካማ ከሆኑ፣ በወጣት ማኅበራት ወይም የጎብረት ሥራ ማኅበራት የሚከናወኑ የለውጥ እርምጃዎችም ብዙ ጊዜ በተመሳሳይ ችግሮች መጠቃታቸው እንደማይቀር የWIDE መረጃ ይጠቁማል (ማጣቀሻ፡- ወጣቶች)፡፡ በርካታ የጎብረት ስራ ማኅበራትና የወጣት ማኅበራት ወይም የሴቶች ማኅበራት፣ እያደጉ በሄዱ ቁጥር፣ አመራራቸው አቅም እያነሰውና የመነሻ መዋጮ ገንዘባቸው ጠፍቶ፣ መዘጋታቸው ተነግሯል፡፡ በሌላ በኩል፤ አብዛኛውን ጊዜ አዲስ አሰራር ወይም ፈጠራ አሉታዊ ውጤት ሲገጥመው አሊያም እንደታሰበው ውጤታማ ሳይሆን ሲቀር ተጠያቂ የሚደረጉት ሞዴል አርሶ አደሮች ናቸው፡፡ “አርሶ አደሮች፣ ከአካባቢው ጋር ያልተስማማ የአዲስ ዘር ችግር ሲገጥማቸው፣ ወቀሳ የሚሰነዝሩት መጀመሪያ ዘሩን የሞከረው ሞዴል አርሶ አደር ላይ ነው" (ጎራ ጎዶ/ወላይታ)፡፡ ስኬትን ለማረጋገጥ፣ በቀበሌ ውስጥ ትክክለኛ ሰራተኞችን በትክክለኛ ቦታቸው ላይ ማግኘት፣ አሁንም ፈተና እንደሆነ ቀጥሏል (ማጣቀሻ፡- አርአያዎች/ሞዴሎች)፡፡

<u>ይበልጥ የተቃኙ የፈጠራ “ማዕቀፎች” አስፈላጊነት</u>

የWIDE መረጃ እንደሚጠቁመው፤ በመንግሥት የሚመራ ፈጠራ፣ ተቀባይነት በሚያገኝበትና በሚሰራበት ወቅት እንኳ፣ በዲዛይን ችግር ወይም አካባቢያዊ ሁኔታን ባለማገናዘብ ድክመት አሊያም ማህበረሰብን በስፋት ባለማሳተፍ ችግር በተደጋጋሚ ይጠቃል፡፡ *(አርአያዎች/ሞዴሎች በሚለው ጽሁፍ ላይ ይበልጥ በዝርዝር እንደተገለጸው)* ይህ በተለይም፣ በከብት እርባታና የመኖ ምርት ወይም በአካባቢ ጥበቃ ፕሮጀክቶች ላይ እውነት ይመስላል፡፡ ግን ደግሞ በሥራ ፈጠራና በኢኮኖሚ ማኅበራት ምሥረታ ሙከራዎች ላይም ታይቷል፡፡ በዶኦማ/ጋሞ፣ ለወረዳው የሕንፃ መሳሪያዎች እንዲያቀርብ የተቋቋመ ማኅበር በቀበሌው ታግዷል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ በጋዜጣ በተነገረለት ብሔራዊ ፓርክ ላይ የሚፈጥረውን ተጽእኖ በመፍራት ነው፡፡ በደቡብ ኦሞ፣ የከፊል አርብቶ አደር አካባቢ ፍየሎች፣ አዲስ የመጣ የሳር ዓይነት ግጠው ሞተዋል (ሉቃ/ፀማይ)፡፡ በሌላ በኩል፤ በግብርና ልማት ፕሮገራም አካባቢ፣ በልማት ሰራተኞች የቀረበውን የሳር ዘር፣ አንዳንዶች ተቀብለው ዘርተውታል፡፡ ሌሎች የማኅበረሰብ አባላት ደግሞ ስለ “ሰው ሰራሽ የከብት መኖ” አዘገጃጀት የተሻለ ዝርዝር መረጃ ጠይቀዋል (አዳዶ/ጌዴኦ)።

የዋጋ ውድነት ደግሞ ሌላው ችግር ነው፡፡ በተለያዩ አካባቢዎች እንደታየው ሁሉ፣ በአዳዶ/ጌዴኦ፣ የዋጋ ግሽበት፣ ማኅበረሰቡ በሬ ለማደለብ የነበረውን ከፍተኛ ፍላጎት አዳክሞታል፡፡ የግብርና ልማት ፕሮገራም የድጋፍ ፕሮግራም፣ መነሻ ላይ የሚደረግ የግዢ ወጪን ስለማይሸፍን፣ ህብረተሰቡ “ፕሮጀክቱን መጥላት” ጀምሯል፡፡ አዜ ዴቦአ/ከምባታን ጨምሮ በበርካታ አካባቢዎች፣ አዲስ አይነት የእርሻ ዘዴዎችን ለመተግበር፣ የግብአቶች ዋጋ መናር እንቅፋት መሆኑ ተገልጿል፡፡ በገለቻ/ምዕራብ ሸዋ አካባቢ ባሉ ከፊል አርብቶ አደሮች ዘንድ፣ የብድር አገልግሎት ባለመኖሩ፣ የሚመርጡትንና

በወረዳው በየትም ቦታ የሚተዋወቀውን የቦረና ኮርማ ገዝተው መጠቀም አልቻሉም (እንዲሁም በሉቃ/ፀማይ)። የሰዎች ስህተትም አስተዋፅኦ አድርጓል። በአዬሌ ኬኬ/ምስራቅ ሐረርጌ፣ ኬኬ ተራራ አቅራቢያ የተተከለው የፈጠራ ውጤት የሆነ አዲስ የዛፍ ችግኝ፣ በአካባቢው አጎራባቾች ተነቅሏል። በሹምሸሃ/ወሎ፣ በአካባቢው ደረቅ አፈር ተሳብቦ፣ ችግኝ አልተተከለም። በአዜ ዴቦአ/ከምባታ፣ ቀበሌው፣ በአዲስ የተከለለ ይዞታ ላይ የሚገኝ ሳር ለመሸጥ መወሰኑ፣ የሕዝብ ቁጣ አስነስቷል። በመጨረሻም፣ አንዳንድ ጊዜ ቴክኖሎጂም የተቀባይነት ማጣት ይገጥመዋል። በዶአማ/ጋሞ፣ የግብርና ልማት ሰራተኞች፣ አርሶአደሮች፣ ከባድ ብረት ያለውን ማረሻ እንዲጠቀሙ ያደረጉት ቅስቀሳ ውድቅ ሆኖ፣ በምትኩ የአካባቢው ሰፋሪዎች ያመጡትን ጫፉ ላይ ብረት ያለው ባለ እንጨት ማረሻ ተመርጧል። (ከዚህ በታች የቀረበውንም ይመልከቱ) የዝናብ ውሃን ፕላስቲክ አንጥፈው በማጠራቀም እንዲጠቀሙበት የቀረበው አማራጭም፣ ዝናብ በመጥፋቱና ዕቃዎቹም በመሰረቃቸው፣ ተግባራዊ ሳይሆን ቀርቷል።

በገልቻ/ምሥራቅ ሸዋ፣ በአርብቶ አደር አካባቢዎች ሌላ ሥራ ላይ ከተገኙ የጥናት ውጤቶች ጋር ተመሳሳይ በሆነ መልኩ፣ ወጣቶች በከፍተኛ የእርሻ ልማት ላይ እንዲያተኩሩ ለማበረታታት የተደረገው ይፋ ጥረት በገጠሙት እንቅፋቶች ተሰናክሏል፡-

> *1ኛ፣ አንዳንድ ወጣቶች እስካሁን ድረስ በእርሻ ልማት ለመሳተፍና መሬታቸውን ከመጤዎች ጋር የእኩል ለማሳረስ አሻፈረኝ በማለት፣ በለመዱት የአርብቶ አደር የኑሮ ዘዬአቸው ቀጥለዋል። 2ኛ፣ የገንዘብ አያያዝ በቂ ልምድ ስለሌላቸው፣ የሚያገኙትን ገንዘብ በቀላሉ ያባክናሉ። 3ኛ፣ብዙዎቹ የወጣት ድርጅቶች በአንድ ነገር ላይ የማተኮር አዝማሚያ አላቸው። ለምሳሌ፡- የገቢያውን ፍላጎት ከግምት ውስጥ ሳያስገቡ፣ ሽንኩርት ጭነው ወደ ከተማ ይወስዳሉ። ውጤቱም ከተጠበቀው ያነሰ ገቢ ይሆናል* (የወረዳ ሃላፊ፣ ገልቻ/ምስራቅ ሸዋ)።

- «የቴክኖሎጂ ሽግግር" ውጤቶች፤ ለመማርና ለፈጠራ ያለውን የአካባቢያዊ ዕድሎች ልዩ ሁኔታና መደበኛ ያልሆነ የማኅበረሰብ እውቀት ስርጸት ሂደቶች ውስብስብነትና ውጤታማ "የቴክኖሎጂ ሽግግርን" የሚደግፍ አካባቢያዊ ጥቅምን ለማስላት ልዩ ትኩረት በመስጠት፣ የበለጠ ሊሻሻል ይችላል።
- ይሁንና፣ እንዲህ ዓይነት አካባቢያዊ ልዩነቶች፣ አሃዛዊ ግቦች በማስቀመጥ ወይም በብሄራዊ ማዕቀፎች አማካኝነት ማግኘት አስቸጋሪ ነው።

መሰረታዊው የገጠር የለውጥ ሂደት፣ በመንግሥት የሚመራ በርካታ ስኬታማ ፈጠራ መኖሩን ይጠቁማል። ነገር ግን እነዚህ ምሳሌዎች፣ ለአካባቢ በቀል ጥበብ፣ ለዋና አሳሳቢ ጉዳዮችና ለዕውቀት ልዩ ትኩረት መስጠት ጠቃሚ መሆኑን ያመለክታሉ። ኮሚሽነር ይናገርም፤ በተጠቀሰው ምንጭ፣ እንዲህ ብለዋል፡--

> *ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሚካሄዱ ጥናቶች፣ ከተቋማት በተጨማሪ፣ ማኅበረሰቦች ብዙውን ጊዜ፣ በተፈጥሮ ሀብት አያያዝና አመራር፣ ከመንግሥት ተቋማትና ድርጅቶች የበለጠ ብቃትና አቅም አላቸው በሚል እምነት፣ ማህበረሰባዊ እሴት ትኩረት እያገኘ ነው።[...]* (ይናገር፣ ደሴ 2012: 10-11)

ፈጠራ በግብርና ዘርፍ

የWIDE መረጃ እንደሚጠቁመው፤ በግብርና ውስጥና በግብርና ዙሪያ፣ የማህበረሰብ ፈጠራ በእጅጉ የተነቃቃና የተለያየ ነው- በሁሉም የሕብረተሰብ ቡድኖችና ግለሰቦች፡፡ በሌሎች ዘርፎች ያሉ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎችን እንዲሁም ማህበራዊ፣ ባህላዊና ሌሎች የማህበረሰብ እምነቶችና ልማዶችንም ያካትታል፡፡ እነዚህ ብዙዎቹ የተለያዩ ዓይነት ፈጠራዎች ደግሞ እርስ በእርስ ይደጋገፋሉ፡፡ በግብርና ውስጥ ወይም ከግብርና ውጭ፣ የግብርና ፈጠራና የለውጥ እንቅስቃሴ፣ እንዲሁም ብዝሃነት ብዙ ጊዜ የሂደቱ ማዕከል ናቸው፡፡

- የገጠር የሥራ ፈጠራን፣ ገቢንና ምርትን ለማሳደግ የሚቀየሱ ስልቶች፣ ከመደበኛው የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ዘርፍ ውጭ ከሚገኙ የኢኮኖሚ ፈጠራዎች መማር አለባቸው፡፡

የመስኖ ልማት ፋይዳ

በተለይ የመስኖ መጀመር ወይም መስፋፋት ብዙ ጊዜ፣ ሰፊ አካባቢያዊ የኢኮኖሚ ፍላጎቶችንና አማራጮችን ይለውጣል፡፡ ከሞላ ጎደል ጥናቱ በተካሄደባቸው ሁሉም አካባቢዎች፣ የእርሻ ባለሙያዎች ከሚያስቡት በላይ አዲስ አሰራርና ለውጥ መፍጠሩን ማስረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ለአካባቢው ተዋናዮች፣ ስብጥር ያለው ወይም የገበያ አዝዕርቶች የማምረት አዲስ ተሞክሮ ይፈጥርላቸዋል፤ (ለምሳሌ፡ የከተማ-ገጠር ትስስሮች)፤ ለቀን ሥራና ለደሞዝ ሥራ አዲስ ዕድል ይከፍታል፡፡ (ሶሞዶ/ጅማ) የአካባቢ የገበያ ትስስሮችንና ከነጋዴዎች ጋር ያለን ግንኙነት ያሳድጋል፡፡ ለሁሉም ባይሆንም ለአንዳንድ የማኅበረሰብ አባላት ሁነኛ የብልጽግና አቅምን ይጨምራል፡፡ በዚህም የገጠር-ከተማን ትስስሮችን ያጠናክራል፡፡

- የገጠር የሥራ ፈጠራን ለማሳደግ የሚጀመሩ ፕሮጀክቶች፤ ሁሉንም በመስኖ ዙሪያ እያበቡ ያሉ አነስተኛ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ለውጦች አሟጠው መጠቀም ላይ ሊያተኩሩ ይችላሉ፡፡ እያደገ ባለው አካባቢያዊ የገንዘብ ኢኮኖሚ ዕድሎች ውስጥ፣ ከአካባቢ አገልግሎቶች እስከ ቀን ሰራተኞች ወይም ነጋዴዎችና የግል ዘርፉ አዳዲስ ፍላጎቶች ይፈጠራሉ፡፡

መስኖ፣ የተነቃቁ አነስተኛ የኢኮኖሚ ዘርፎች ከመፍጠር ባሻገር፣ የኑሮ መተዳደሪያዎችና የምግብ ፍጆታን በዓይነት የማስፋት አቅም አለው፡፡ በተጨማሪም የእህል ምርት ዋስትና ባልተረጋገጠባቸው አካባቢዎች፣ የምግብ ዋስትናን ያሳድጋል (ገብለንና ሃረሳው/ምሥራቅ ትግራይ፣ ዲንኪ/ሰሜን ሸዋ፣ ቆሮዶጋጋ/አርሲ፣ ዶአማ/ጋሞ)፤ ነገር ግን በመስኖ ሥራ የተሳካላቸው አርሶ አደሮች፣የኪሳራ ሥጋትን በሁሉም የገቢ ምንጮች ላይ በማሰራጨት፣ አዳዲስ ነገሮችን በጥንቃቄ እንደሚፈጥሩ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

- በተለይ ብዙዎቹ ይበልጥ ስኬታማ አዳዲስ ሃሳብ አፍላቂዎች አስተማማኝ የኢኮኖሚ ጥቅም ገና ያልተቀዳጁ ከመሆናቸው አንጻር፣ ይህ መንግስት ምርት ለማሳደግ (ወይም የተወሰነ ዓይነት ምርት ማስፋፋት) ሲፈልግ፣ ሊተገብረው የሚችል የተለመደ ስልት ነው (ማጣቀሻ፡- ስኬት)፡፡

የWIDE መረጃ፣ የመስኖ ስራ ምን ያህል ውስብስብ እንደሆነ ያሳያል፡፡ የመስኖ ጎብረት ሥራ ማህበራት፣ በብዙ አካባቢዎች ደህና በሚባል ደረጃ ውጤታማ ሆነዋል (ለምሳሌ፡-ሹምሸሃ/ወሎ)፡፡

ሌሎች ደግሞ ግድቦች እንዲሁም የውሃ መሳቢያ ፓምፕና የጠብታ መስኖ ኮሚቴዎች አላቸው (ለምሳሌ፡- ሃረሳው/ምስራቅ ትግራይ)። በአንደኛው አካባቢ፣ ለመስኖ የሚያገለግል የጎርፍ ውሃ ማጠራቀሚያ ትልቅ መሬት ተገኝቷል። በራስ አገዝ የመስኖ ማኅበር፣ በመንግሥትና በመስኖ የኅብረት ሥራ ማኅበራት የተገነቡም አሉ (ቆሮዴጋጋ/አርሲ)። መስኖ፣ ቢያንስ በሦስት ቦታዎች፣ ሁከት ባያስከትልም ውጥረት ፈጥሯል። በአርሲ ቀደም ብሎ የወጣቶች የህብረት ስራ ማኅበር፣ ለመስኖ እንዲጠቀምበት የተሰጠ 29.5 ሄክታር መሬትን፣ ወረዳው፣ ለአውስትራሊያዊ ባለሀብት መስጠቱ ውዝግብ አስከትሏል። በሶሞዶ/ጂማ፣ የግጦሽ መሬት፣ ባለሀብቶች አትክልት እንዲያለሙበት መሰጠቱ ተቃውሞ ገጥሞታል። በሉቃ/ፀማይ እንዲሁ መስኖ፣ በወይጦ ወንዝ ዙሪያ፣ ከኮንሶ መጤዎች ጋር ግጭት ቀስቅሷል።

- ከአካባቢ ሥነ-ምህዳሮችና የኢኮኖሚ ዘርፎች ጋር ከሚጣጣሙ፣ እንዲሁም የአካባቢን ጥቅም ከሚያስጠብቁ የተለያዩ ዓይነት የለውጥ እርምጃዎች ወይም ፕሮግራሞች ድጋፍ ጋር ከአንድ በላይ የመስኖ አሰራር ዘዴን ከግምት ውስጥ ማስገባት ይገባል።

የእርሻ ክህሎት ሌሎች «የፈጠራ ምንጮች"፣ ለውጥ ወይም ብዝሃነት አርሶ አደሮችና ሌሎች፣ ከፈርጀ ብዙ ያልተለመዱና ያልታሰቡ የውጭ ምንጮች፣ በተለያዩ አጋጣሚዎች፣ አዳዲስ ክህሎቶችን ወስደው ይተገብራሉ፤ ይጠቀማሉ። ለምሳሌ፡- በ2006፣ የቻይና የመንገድ ግንባታን በመመልከት፣ መስኖ ለማስፋፋት፣የከርሰ ምድርን ውሃ መጠቀም፣ መማር፣ ቢያንስ የአካባቢ የእውቀት ሥርጸትና እንደ መንግሥት ሥልጠና የባህርይ ለውጥ ለማምጣት ሚና መጫወቱ ለአብነት ሊጠቀስ ይችላል (አዴሌ ኬኬ/ምሥራቅ ሐረርጌ)። ከእርሻ ኮሌጅ ተመርቀው፣ ከዚያም በግንባታ የቀን ሥራ ላይ በመሰማራት፣ ሙያውን ተምረው፣ ታዋቂ የግንባታ ባለሙያ በመሆን፣ 20 ቤቶችና የአካባቢውን ት/ቤት በሃላፊነት ገንብተዋል (አዜ ዴቦአ/ከምባታ)። በ1997/8 አዲሱ የላሊበላ አውሮፕላን ማረፊያ ግንባታ የፈጠረውን መልካም አጋጣሚ በመጠቀም፣የአናጢነትና የግንበኝነት ሙያ በመቅሰማቸው፣ በቂ ገቢ አግኝተው፣ የእርሻ ስራ አቁመዋል (ሹምሸሃ/ወሎ)። እነዚህና ሌሎች በርካታ ምሳሌዎች፣ "አዎንታዊ ማፈንገጥ"[6] ያለውን ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ በተመለከተ መረጃ ይሰጣሉ። ግለሰቦች የተለወጠ አሰራር ያለውን አቅም በመገንዘብና በመተግበር፣ ለረዥም ዘመን ከዘለቁ (ብዙ ጊዜ እርሻ) የሥራ ወይም የማህበረሰብ ልማዶች ይወጣሉ (ማጣቀሻ፡- ስኬት)።

- ውጤታማ ፈጠራን የመማር ሂደት፣ ቀጥተኛ ያልሆነ፣ የማይገመትና በአጋጣሚ ላይ የተመሰረተ ሲሆን በተለይ ለማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ምላሽ የሚሰጥ ነው። የመንግስት የለውጥ እርምጃ፣ እነዚህን ሁኔታዎች በመቅዳት ሊጠቀምበት ይቻላል።

ካልተለመደ የውጭ ምንጭ የተገኙ አዲስ ሃሳቦችና ፈጠራዎችን በተመለከተ፣ በጣም አስገራሚ ምሳሌዎች፣ በጋሞ አካባቢ፣ በዶአማ ተገኝተዋል። "የማኅበረሰቡ አባላት፣ አዳዲስ ሰብሎችና አትክልቶችን ካስተዋወቁት የአማራ ሰፋሪዎች፣ የሥራ ባህል፣ አዳዲስ ጥበቦችን ቀስመዋል"፤ በተጨማሪም ደጋግሞ ማረስ እንዲሁም አዲስ የአተካከል ዘዴዎችንና ረዥም ሰዓት የመሥራት ተሞክሮም ወስደዋል። አንድ ሞዴል አርሶ አደር፤ ስለ ማሽላ እርሻ በእጅጉ የሚያውቁ ሁለት የአማራ መጤዎችን ቀጥሮ ማሰራቱን የገለጸ ሲሆን ከሩብ ሄክታር መሬት ከፍተኛ ምርት መሰብሰብ

[6] *Cf.* Pascale Sternin & Sternin (2010) *The Power of Positive Deviance: how unlikely innovators solve the world's toughest problems*, Boston: Harvard Business Press

እንደሚቻል ማሳየታቸውን በመጠቆም ሃሳቡን ቋጭቷል፡፡ በአንፃሩ ግን የአካባቢው ማኅበረሰብ ጥብቅ ክትትል የማይፈልጉ ሰብሎችን ነው የሚመርጠው፡፡ ውጤቱ፣ በአካባቢው የአመራረት ዘዴዎች ላይ ጉልህ ለውጥ ያመጣ ሲሆን በቀበሌው የመስኖ ልማትና ደረቅ መሬት ላይ በከፍተኛ የቴክኖሎጂ ምርት ረገድ በጣም ከፍተኛ ፍላጎት ተፈጥሯል፡፡

- የግለሰብ ወይም "አፈንጋጭ" ፈጠራዎችን ወስደው ለሚተገብሩ ወይም ካልተጠበቁ ምንጮች ትምህርት ለሚቀስሙ የአካባቢ ማህበረሰቦች ልማታዊ አቅም ልዩ ትኩረት በመስጠት የዕድገት ውጤቶች ሊሻሻሉ ይችላሉ፡፡

ከተሜነት ዘመናዊነትና መዘዋወር

ወጣቶችና የከተማ ባህል

የከተማ ማዕከላት፣ ከWIDE የገጠር አካባቢዎች (በአንፃራዊነት የበለጠ) የዘመናዊነት ወይም የዝመና ሂደት እምብርቶች እንደሆኑ በስፋት ታይቷል (ማጣቀሻ፡- የገጠር ከተሜነት መስፋፋት)፡፡ የዘመናዊነት ደረጃ በጎበኟቸው ሰዎች በተለያዩ መንገዶች ይገለጻል፡- አማርኛ ቋንቋ መማር፣ ሞባይል ስልክ መጠቀም ወይም ጂንስ መልበስና ባርኔጣ በማጥለቅ ከብዙ ጥቂቶቹ ናቸው (ዶአማ/ጋሞ፣ ጋራጎዶ/ወላይታ)፡፡ ወጣቶች ከሚጎበኟቸው ከተሞች አዳዲስ ሃሳቦችን በማምጣት ረገድ በስፋት እውቅና ተሰጥቷቸዋል፡- ለምሳሌ የሞተር ቢስክሌቶች ትራንስፖርት (አዳዶ፣ እንዲሁም ዶአማ) ለሥራ ከትውልድ ቀዬአቸው ብዙ ርቀት መጓዛቸውም እንዲሁ (ከጌዴኦ ለወርቅ ቁፋሮ ወደ ሻኪሶ)፡፡ አሁንም፣ ሁሉም ለውጦች በሁሉም ዘንድ በበጎነት ታይተዋል ማለት ግን አይደለም፡፡ እንደ ሌሎች በርካታ አካባቢዎች ሁሉ፣ በአዴሌ ኬኬ/ምሥራቅ ሐረርጌና ገልቻ/ምስራቅ ሸዋ፣ ጫት መቃም፣ በወጣቶች ዘንድ እንደ አዲስ የጊዜ ማሳለፊያ ልማድ እንደሚታይ ተነግሯል፡፡ ሌላው ለውጥ ደግሞ ፀጉርን ማቆም ነው፡፡ በWIDE ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ግለሰቦች፤ የከተማ የምግብና የልብስ ፋሽን የሚከተሉ ወጣቶች ዘንድ የሚታዩ ለውጦችን በተመለከተ፣ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙት፣ ከአቅማቸው በላይ ሊሆንባቸው እንደሚችል ጠቁመዋል (ለምሳሌ፡- አዳዶ/ጌዴኦ)፡፡ ሌሎች ደግሞ ጨዋነት የጎደላቸው አዳዲስ ፋሽኖች፣ “ወጣቱን ለወሲብ ሊያነሳሱ ይችላሉ” የሚል ስጋት እንዳላቸው ገልጸዋል (ዶአማ/ጋሞ)፡፡ ይሁን እንጂ ይበልጥ ተጨባጭና አበረታች በሆነ መልኩ፣ በአዳዶ/ጌዴኦ፣ አዋቂ ሴቶች፣ የተለያዩ ቀሚሶችና አላባሾችን (አንዳንድ ጊዜ ከስር ከሱሪ ጋር) መልበስ ተምረዋል፡፡ ይህም ከ2008 በፊት ከነበረው ሙሉ ቀሚስ ብቻ የመልበስ ልማድ የተለወጠ ሲሆን የጌዴኦ አካባቢ ሴት ተማሪዎች ያስተዋወቁት አለባበስ ነው፡፡

በከተማ ማዕከላት የቀረበ የፈጠራና የመማር አዲስ አቅም

አዳዲስ ሐሳቦች የሚመነጩት ከመንግሥት ቢሮዎች ወይም ከወረዳ ሳይሆን ከከተሞችና ከእነሱ ጋር ትስስር ካላቸው አካባቢዎች እንደሆነ ሰፊ ግንዛቤ መኖሩን፣ በWIDE የተሰነዱ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ለምሳሌ፡- አዳዶ/ጌዴኦ፣ ሃረሳው/ምሥራቅ ትግራይ)፡፡ በትላልቅ የከተማ ማዕከላት የሚገኙ የግል ት/ቤቶች፣ የላቀ የመማር-ማስተማር ተሞክሮ፣ ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ ተጠቅሷል (ለምሳሌ፡- በአዜ ዴቦአ/ከምባታ)፡፡ በአዴሌ ኬኬ/ምሥራቅ ሐረርጌ፣ በርካታ የሀብታም ቤተሰብ ልጆች፣ ክፍያቸው ውድ ቢሆንም በድሬደዋ ወይም ሐረር በሚገኙ የግል ኮሌጆች ውስጥ ተምረው ተመርቀዋል፡፡

ወላጆች እነዚህን ኮሌጆች የመረጡት፣ ለትምህርት በንጽጽር ዝቅተኛ ትኩረት ከሚሰጡት የገጠር ት/ቤቶች፣ የተሻለ ዕውቀት ያስጨብጣሉ ተብሎ ስለሚታመንና ተማሪዎች፣ በንድፈ ሃሳብ የቀሰሙትን ትምህርት ለመተግበር የሚያስችላቸው የተግባር ልምምድ ስለሚሰጡ ነው (*cf.* DB04:*education*)።

በWIDE የጥናት አካባቢዎች ውስጥ ወይም አቅራቢያ በሚካሄዱ የከተማ መስፋፋቶች፣ አዳዲስ አገልግሎቶች ተጀምረዋል። በአብዛኞቹ የቀበሌ ማዕከላት፡- ግዢና ሽያጭ የሚካሄድባቸው ቦታዎች- ወይም ዳቦ መጋገሪያ፣ የመኪና ባትሪ የመሙላት አዲስ አገልግሎት፣ የእጅ ባትሪ ማደሻና የሴቶች የውበት ሳሎኖችም ተከፍተዋል። በቀበሌ ማዕከል ከሚገኝ አዲስ የቡና አምራቾች ማኅበርና ህንጻዎች ጎን ለጎን (አዳዶ/ጌዴኦ) ወይም የሞባይል ስልኮች ጥገና አገልግሎት ተስተውለዋል (በሶሞዶ/ጂማ)፤ የቢስክሌት፣ የጫማ ጥገና (በሃረሳው/ምሥራቅ ትግራይ)። በጋራጎዶ/ወላይታ፣ ከዋጫ ከተማ መስፋፋት ጋር ተያይዞ፣ የቀበሌው ምክትል ሊቀመንበር እንደገለጹት፤ "አሁን አዲስ መጤዎችን የመቀበል ሂደት ከቀድሞው የበለጠ ፈጣን ሆኗል"። በብዙ አካባቢዎች እንደሚታየው ሁሉ፣ ይበልጥ ስኬታማ በሆኑ የማኅበረሰብ አባላት ዘንድ፣ ወጣቶች በቤተሰቦቻቸው ላይ ጥገኛ መሆናቸው እንደቀነሰና ሰፊ ህልም እንዳላቸው ተስተውሏል (ይህ ለሁሉም ወጣቶች ባይሰራም፤ ወጣቶች የሚለውን አጭር ጽሁፍ ይመልከቱ) የዕድሜ አቻዎቻቸው ደግሞ “ለውጥና ዕድገት የሚጠብቁት ከግለሰቦች ጠንካራ ሥራ ነው”። ለምሳሌ፡- በሃረሳው/ምሥራቅ ትግራይ፣ ስኬታማ የከብቶች ደላላ (በአጽቢ ባየው ነገር ተማርኮ) ወደፊት የቤትና የመሬት ደላላ መሆን ያለውን ጥቅም በመገንዘብ፣ አዲሱን የከተሜ ሙያ ህጋዊ በሆነ መንገድ ለመቀላቀል አልሟል። ስኬት በሚለው አጭር ጽሁፍ እንደተገለፀው፤ የከብት እርባታ ከፈጠራ ብዝሃነት አንጻር፣ በገጠር ኢኮኖሚ ላይ ከእርሻ የበለጠ ሰፊ ቁልፍ ሚና ይጫወታል። በብዙ አካባቢዎች፣ ለከብቶች ያለው አመለካከት መለወጡ በግልጽ የሚታይ ሲሆን የከፊል - አርብቶ አደር አካባቢዎችን ጨምሮ፣ አንዳንድ ሰዎች፣ ከብቶቻቸውን ለመጠበቅ መሬታቸውን ማጠር ጀምረዋል (ሉቃ/ፀማይ)።

የሰዎች ዝውውርና አዳዲስ ሃሳቦች

የሰዎች ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስና ስደት ጠቃሚነቱ ይበልጥ እየጎላ መጥቷል። የተለያዩ ልምዶችን ቀስመው የሚመጡ ስደተኞች፣ አዳዲስ ሐሳቦችና አሰራሮችንም ይዘው ነው የሚመለሱት (ሁሉም ግን በተመሳሳይ ሁኔታ በበጎነት አይታዩም)። ይሁንና በበርካታ ማህበረሰቦች የሰፈነው አጠቃላይ ግንዛቤ የሚመስለው፣ ስደተኞች ከአዳዲስ ሃሳቦች ይልቅ ገንዘብ ይዘው ይመለሳሉ ወይም ይልካሉ የሚለው ነው (ሃረሳው/ምሥራቅ ትግራይ)። በምሥራቅ ትግራይ፣ አንድ ከኤርትራ ሙያውን ቀስሞ የተመለሰ የጣራ ግንበኛ፣ ጥሩ የኑሮ መተዳደሪያ ያደረገው ሲሆን የማታ ማታም ልጁን ጨምሮ በርካታ ረዳቶችን ቀጥሯል። ወደ ማዕድን ቁፋሮ ዘርፎች መግባት ወይም በጉልበት መስራት አሊያም መቀጠር፣ ብዙ ጊዜ አስቸጋሪ ቢሆንም በርካቶች ህይወታቸውን መለወጥ ችለዋል። በአዴሌ ኬኬ/ምሥራቅ ሐረርጌ፣ አርሶ አደሮች፣ ከራሳቸው ቀርሳ ወረዳ፣ “የበለጠ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች” ካለው ጎረቤታቸው ሃሮማያ ወረዳ፣ መማራቸውን ገልፀዋል። ሀብታም አርሶ አደሮች፤ በአወዳይና በሃሮማያ መኖሪያ ቤቶች የገነቡ ሲሆን በእነሱ ተፅዕኖ የአካባቢው የግንባታ ዲዛይን ተለውጧል፤ የአካባቢው ማኅበረሰብ አባላትም፣ ቀድሞ አደጋ በመፍራት ቤቶች ባልቀለሱበት የመንገድ አቅራቢያ፣ አዳዲስ ቤቶችን መገንባት ጀምረዋል። በመጨረሻም፣ ከ2010 አንስቶ፣ ለአዳዲስ ተመራቂዎች ድግስ

ከሚደግሱ ወገኖች (ከእያንዳንዱ ሰው ከ100-200 ብር) የማኅበረሰብ መዋጮ የመሰብሰብ አዲስ ልማድ ተጀምሯል - ተመራቂዎችን ለወደፊት ለማቋቋም የሚውል፡፡

የሩቅ አገራት የስደት ተመላሾች ወይም ከስደት የሚልኩት ገንዘብ፣ በሃገር ቤት ማኅበረሰቦች ላይ የሚፈጥሩት ተጽእኖ ከፍተኛ ነው፤ በተለይም መድረሻቸውን ደቡብ አፍሪካ ላደረጉ የከምባታና አካባቢው ማኅበረሰቦች (አዜ ዴቦአ/ከምባታ) እንዲሁም ወደ መካከለኛው ምሥራቅ አገራት ለተጓዙ (ሃረሳው እና ገብለን/ምሥራቅ ትግራይ) ማህበረሰቦች እንዲሁም የኦሮሚያ በርካታ የሙስሊም አካባቢዎች (ለምሳሌ፡- ሶሞዶ/ጂማ)፡፡ ስደት፣ በትግራይ፣ መደበኛ ትምህርትን ከማቆም ጋር በስፋት የተዛመደ ቢሆንም (ሃረሳው)፤ አዲስ የብድር አቅርቦትን ጨምሮ፣ “በግለሰብና በማኅበረሰብ ደረጃ መልካም ነገሮችን” ያመጣል ተብሎም ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም፣ ከሙስሊም አገራት የሚመለሱ ስደተኞች፣ የቀድሞ የሃይማኖት እሴቶቻቸውን ይቀይራሉ ተብሎ ስለሚታሰብ ስደት፣ “አስፈሪ መልዕክቶችን ያዘሉ አንዳንድ ሃሳቦች” ሊያመጣ እንደሚችል ይነገራል (ማጣቀሻ፡- ፍልሰት)፡፡

<u>ፈጠራ፣ ሥርዓተ ፆታና የቤተሰብ ግንኙነት መለወጥ</u>

በጋብቻ ውስጥ የኢኮኖሚ ነፃነት ማጣት፣ አንዳንድ አዲስ ተጋቢዎችን፣ ከፍተኛ የወሊድ መከላከያ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚገፋፋ ይመስላል፤ ለምሳሌ፡- በአዜ ዴቦአ/ከምባታ፡፡ በአዳዶ/ጌዴኦ፣ በንጽጽር ድሃ የምትባል ሴት እንኳን፣ ህጻናትን የማሳደጊያ አዳዲስ መንገዶች፣ ያመጡትን አዎንታዊ ለውጦች ትገነዘባለች፤ በ5ኛ ክፍል ተማሪዎች፣ በጌዴኦኛ ቋንቋ፣ የሚሰጠውን የመዋለ-ሕፃናት ትምህርት ጨምሮ፡፡ ይህ የመዋለ- ሕፃናት ትምህርት፣ ህፃናቱ ወደ መጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ሲገቡ ትልቅ አቅም እንደሚፈጥርላቸው የሚታመን ሲሆን ከ10 ዓመት በፊት ይሄ ዕድል አልነበረም፡፡ ወላጆች ከ10 ዓመት በፊት እንደሚያደርጉት፣ አሁን ልጆቻቸውን አይመቱም፡፡ ሥራ፣ ለህፃናትና ለወጣቶች፣ የእድገትና የለውጥ ሂደት ምንጭ መሆኑን ቀጥሏል፡፡ በበርካታ አካባቢዎች፣ በተለይም በደቡባዊ የአገሪቱ ክፍል፣ ወጣት ህፃናት (13 ዓመትና ከዚያ የሚያንሱ)፣ ጫማ መጥረግን ወይም ሸንኮራ አገዳ መሸጥን ከታላላቅ ወንድሞቻቸው ይማራሉ፡፡ አግብታ የፈታች ሴት ምርጫም በብዙ ሁኔታዎች አንጻር ተሻሽሏል፡፡ በጋራ ጎዶ/ወላይታ፣ አንድ አግብታ የፈታች ሴት፣ በመሬቷ ላይ መኖሪያ ቤት ለመስራትና ምግብ ቤት ለመክፈት አቅዳለች፡፡

በሌላ ቦታ፣ ወጣት ሴቶች፣ በአዲስ የቡና ማጠቢያ ጣቢያ ውስጥ፣ በጊዜያዊ ስራ መሳተፋቸው፣ ከፍተኛ ነፃነትን የሚያመለክት፣ የቅርብ ጊዜ ክስተት ነው (አዜ ዴቦአ/ከምባታ)፡፡ አካባቢ-በቀል መንግሥታዊ ያልሆነው ድርጅት፣ ኬኤምጂ፣ የሴት ልጅ ግርዛትን በመቃወም የሚያደርገው ቅስቀሳ (ገና የባህርይ ለውጥ ባያመጣም)፣ ቀድሞ አይነኬ በሆነ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ውይይት እንዲፈጠር አድርጓል፡፡ ቀድሞ ለአካባቢው አዲስ ክስተት መሆኑ የተነገረለት ዕድር፤ ለእነዚህ አዳዲስ ውይይቶች መድረክ በመፍጠርና ከኤች አይቪ/ኤድስ ጋር ለሚኖሩ ሰዎች ድጋፍ በመስጠት አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ በዚያው ማኅበረሰብ፣ የቀበሌ ባለስልጣናት፣ “ከማኅበረሰቡ ጋር ማቀድ” አዲስ አዝማሚያ መሆኑን ጠቅሰው፣ “በማህበረሰቡ ከፍተኛ ተቀባይነትን ያገኘ” እና ከአካባቢው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተወሰደ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ በገልቻ/ምሥራቅ ኦሮሚያ፣ የትምህርት ቤትና የልጃገረድ ክበቦች፣ ተመሳሳይ ውጤት አስገኝተዋል፡፡ በሌላ በኩል፣ በዶአማ/ጋሞ እና

ዲንኪ/ሰሜን ሸዋ፣ ለምሳሌ፣ የተለያዩ “ጎጂ ልማዶች”ን ለማጥፋት የተደረገው ዘመቻ፣ በማህበረሰብ አመለካከት ላይ መጠነኛ ለውጥ ከማምጣቱ በስተቀር፣ በአጠቃላይ ስኬታማ የሆነ አይመስልም።

የWIDE መረጃ፣ በተለያዩ አዳዲስ የፈጠራ ደረጃዎች ላይ የማኅበረሰብ አስተሳሰቦች ምን እንደሚያንጸባርቁ የሚጠቁሙ በቂ ማስረጃዎች ያቀርባል። ለምሳሌ፡- በዶአማ/ጋሞ፣ ቃለ-ምልልስ የተደረገላቸው ግለሰቦች፣ ቀበሌያቸው (በንጽጽር ለዋጫ ከተማ ቅርብ ነው)፣ ከአንዳንድ ይበልጥ “ወግ አጥባቂ ደገኛ” ጎረቤቶቹ፣ የተሻለ ለአዲስ አስተሳሰብና ዘመናዊነት ክፍት መሆኑን ገልጸዋል።

…እና ከቤተሰብ አባላት መማር

ሴት ሞዴል አርሶ አደሮች፣ በብዙ አጋጣሚዎች፣ ከቤተሰብ አባላት ተምረዋል። በአዳዶ/ጌዴአ፣ ሦስት የቀን ሰራተኞች ቀጥራ የምታሰራው እንዲሁም የግብርና ልማት ሰራተኞችንና ሌሎች የጉልበት ሰራተኞችን እንደ “መማሪያ የትስስር መረብ” የምትመለከተው ባሏ የሞተባት ሴት ጥሩ ምሣሌ ናት። በገልቻ/ምሥራቅ ሸዋ፣ ታታሪ የቀበሌ ምክትል ሃላፊ፣ የመስኖ ጉድጓድ ዲዛይን በማውጣትና በመጥረግ የተሳተፈ ሲሆን ሙያውን የተማረው ከአባቱ ነው። በሌላ በኩል የ25 ዓመቷ ባለትዳር፣ ባለቤቷ ዩኒቨርሲቲ ሲገባ፣ የሱን የንግድ ሥራ ተረክባ ከማስተዳደሯ በተጨማሪም የአካባቢውን የከብት ህክምና ክፍተት ለመሙላት እንስሳትን መርፌ መውጋትም ተምራለች። ብዙ ጊዜ ለአዲስ ፈጠራ፣ ከቤተሰብ የሚገኝ የመሬት ስጦታና ብድር፣ የሃሳቦችና ሙያዊ ክህሎት ያህል ወሳኝ ናቸው።

- ሁሉም ሰው አይደለም አዲስ ነገር መፍጠር የሚችለው፤ ቴክኒካዊ ያልሆነ እውቀትና ሀብት የሚጠቀሙ እንዲሁም ቴክኒካዊ ወይም የቴክኖሎጂ ክህሎት ያላቸው እንጂ።

በማኅበረሰብ ትምህርት፣ ፈጠራና ለውጥ ላይ የሃይማኖት ተፅዕኖ

ሃይማኖት፣ አዳዲስ ሐሳቦችን እንደ ማስተላለፊያ መሣሪያ ማገልገሉ በስፋት ግንዛቤ ያገኘ ጉዳይ ሲሆን ቢያንስ በአንድ የፐሮቴስታንት አካባቢ (አዜ ዴቦአ/ከምባታ)፣ ብሔራዊና ዓለምአቀፍ መንፈሳዊ የሬዲዮ ፕሮግራሞች በአካባቢው ቋንቋዎች መተላለፋቸው፣ ወሳኝ ጉዳይ ነው። በሌላ ስፍራ፣ ከሌሎች አዳዲስ ቤተ ክርስቲያናት ሰባኪዎች ስለ ሃይማኖት ለመስበክ ይመጣሉ (አዳዶ/ጌዴአ)። ብዙዎች ደግሞ አዳዲስ ሃይማኖቶች ከድሮው ይሻላል በሚል የከተማ ተፅዕኖ የተነሳ፣ ሃይማኖታዊ ልማዳቸው እየተለወጠ እንደሆነ ይሰማቸዋል። አንድ ለስልጠና ወደ ዲላ የሄደ የማኅበረሰብ አባል፣ አሁን የአካባቢው ቤተ ክርስቲያን ፓስተር ሆኗል። ሃይማኖታዊ ሕጎች ጥብቅ መሆናቸውን፣ አንዳንድ ወጣቶች ወደውታል። አዲሱ የፀጋ ቤተ ክርስቲያን፣ በልሳን መናገርን አስተዋውቋል። ሌሎች ደግሞ ቤተ ክርስቲያናት፣ “ማኅበረሰቡን ስለ ጋብቻ ሕይወት፣ ስለ ቤተሰብ ወዘተ” ከቀድሞው የተሻለ በከፍተኛ ትኩረት እያስተማሩ ነው ብለው ያስባሉ። ለበርካታ የፐሮቴስታንት ማህበረሰቦች፣ መጽሃፍ ቅዱስ፣ እንደ ጠቃሚ የጥበብ ምንጭነት ይታያል። በሌላ በኩል፣ በጋራ ጎዶ/ወላይታ፣ የሃዋርያት ቤተ ክርስቲያን፣ ጠንከሮ የመስራት ባህልን በማስረፅ፣ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ፣ ከዓመታዊ የሃይማኖት እንቅስቃሴዎች ውስጥ የበዓላት ቀናትን የመቀነስ ሂደት ላይ ትገኛለች።

በሌሎች አካባቢዎች ደግሞ ሃይማኖት መለወጥ ወይም መቀየር፣ "የማህበረሰቡን ታሪክ መለወጥ" እና አዲስ ማህበረሰባዊ ልማዶችን ማቀንቀን ነው በሚል ተቃውሞ ገጥሞታል። አንዳንድ ፈር-ቀዳጆች

እንኳን ሳይቀሩ መጤ ተብለው ህልውናቸው ለአደጋ ተጋልጧል - ይህ ደግሞ አፍራሽ አመለካከት ይመስላል (ሉቃ/ፀማይ)።

<u>ፈጠራን በማስፋፋት ረገድ፤ የንግድ፣ በማኅበረሰቡ ውስጥ ያለ ደረጃና "የስኬት ትሰሰሮች" ሚና</u>

በሌሎች ዘንድ እንደ ስኬታማ አዲስ ፈጠራ አመንጪ ተደርገው የሚታዩ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ ከቀበሌ ወይም ከሞዴሎች አሰራር ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የላቸውም። ነገር ግን የግለሰቦች አዲስ ነገር የመፍጠር ችሎታ፣ አብዛኛውን ጊዜ ከዘርፈ ብዙ ግብአቶች ተደራሽነት ጋር ይዛመዳል። አዲስ ፈጠራ፣ ብዙ ጊዜ የሃብት ልዩነት በተከሰተባቸው የገጠር አካባቢዎች በሚገኙ ወጣቶች ዘንድ እያደገ የመጣውን የሥራ ፈጠራ ግንዛቤን ያመለክታል። መደበኛ ያልሆነውን ዘዴና አዲስ የአሰራር ለውጥ በመከተል የተገኘው ስኬታማ የገጠር ሀብት ማስረጃዎች ለውጡ፣ የማህበራዊ ጥሬ ዕቃ ሀብቶች፣ የመጀመሪያ ጊዜ አጠቃቀምና የመልጋም ዕድሎች መሆኑን ያመለክታል በተለይም ከፍተኛ ስፍራ ባላቸው ወጣቶችና በኢኮኖሚ በጣም ተንቀሳቃሽ በሆኑ ማህበሰረቦች ዘንድ።

- ለማኅበረሰባዊ መስተጋብርና ተቋማዊ በሆነ የሰርቶ ማሳያ ወይም ሞዴሎች ሥርዓት አማካኝነት ትምህርት ለመቅሰም ጥምረት፣ ትኩረት የሚሰጡት የመንግስት አቅጣጫዎች፣ ተጠቃሽ ስኬት አስመዝግበዋል። የ"አመለካከት ለውጥ" ለማምጣት የሚወሰዱ አቅጣጫዎች ግን ጥንቃቄ የተሞላበት መቃኘት ይፈልጋሉ።

መልካም አጋጣሚዎች በአብዛኛው፣ ከፈጠራና ከተቀማጭ ገንዘብ ጋር ሲገጥሙ ይበራከታሉ። በኢኮኖሚ ስኬታማ የሆኑ ቤተሰብ አባላት፣ ብዙ ጊዜ አዲስ ነገር ፈጥረው የመስራት አቅም አላቸው። ለምሳሌ፦ የአንድ ሀብታም አባወራ ሚስት የገነባችው ባለ መፀዳጃ ክፍል፣ ወለሉ ሊሾ የሆነ ቤትና አዲስ ሶፋ ያለው ቤት፣ ጥናቱ ከመጀመሩ ከሦስት ዓመት በፊት፣ መንገድ ዳር በከፈተችው ሱቅና የሴቶች የውበት ሳሎን፣ ማለፊያ ገቢ እያገኘች ነው (አዜ ዴቦአ/ከምባታ)። ጥሩ የንግድ የትስስር መረብ የፈጠሩትም በጥሩ ደረጃ ላይ ናቸው። ለምሳሌ፦ በጌዴኦ ማኅበረሰብ፣ ሁለት የንግድ ሰዎችና ቤተሰቦቻቸው፣ ቆዳና ሌጦ እንዲሁም ለስላሳ መጠጦች በመሸጥ ሥራ ላይ የተሰማሩ ሲሆን ዳቦ መጋገሪያ በማስተዳደርም፣ ለዲላ ከተማና ለበርካታ የተለያዩ ሱቆች በችርቻሮ ያቀርባሉ። የንግድ የትስስር መረባቸው፣ ተጨማሪ አዲስ ሥራ ለመጀመርም አግዟቸዋል፦

> *ንግድ በራሱ ከብዙ ሰዎች ጋር የመገናኛና የመተዋወቂያ መንገድ ነው። በዚህም አማካኝነት ትስስሩ ያድግና ወደ ትብብር ያመራል። በትስስር መረብ ውስጥ ያሉ ሰዎች እርስ በርስ ለመደጋገፍ ጥሩ ናቸው። ለምሳሌ አትራፊ የሆነ አንድ የተለየ ምርት ለመነገድ፣ ገንዘብ ቢያጥረኝ፣ ከነጋዴዎቹ አንዱን ጠይቄ የማግኘት ዕድል አለኝ* (የንግድ ሰው፣ አዳዶ/ጌዴአ)።

በብዙ ማኅበረሰቦች፣ የተለያዩ ዓይነት ነጋዴዎች፣ ከፈጠራ፣ ከዕድገት ሂደትና ከለውጥ ጋር ይዛመዳሉ፦ በዱራሜ፣ የቡናና የከብት ነጋዴዎች (አዜ ዴቦአ/ከምባታ) ሌሎች አነስተኛ ንግዶችን ጨምሮ - ሁሉም የጀመሩት ብድር አግኝተው ሳይሆን የራሳቸውን ወይም የቤተሰቦቻቸውን ገንዘብ በመጠቀም ነው (ማጣቀሻ፦ ስኬት)። በደቡብ ኦሞ አካባቢ፣ ከመንገዶች ግንባታ፣ ከኤሌክትሪክ፣ ከሞባይል ስልክ ኔትዎርክ መምጣት ጋር ተያይዞ ፈጣን ለውጦች የተከሰቱ ሲሆን በኑሮ መተዳደሪያ እንዲሁም በምግብና አለባበስ ላይ ጉልህ ለውጦች ከንግድ መጀመር (የከብቶችም የጥቃቅን

ንግድም) እንዲሁም በ2001 በገበያ ሰብልነት ከተዋወቀው ሰሊጥ ጋርም (ሉቃ/ፀማይ) ተያይዞ ተከስተዋል፡፡

በሌሎች አጋጣሚዎች፣ አዲስ ሃሳብ አፍላቂዎች የፓርቲ ወይም የቀበሌ አባላት ናቸው፡፡ ነገር ግን አዳዲስ የንግድ ሃሳቦችን በመደበኛ መንገድ ወደ ተግባር በመለወጥ፣ ሥራቸውን በግላቸው ፈጥረዋል፡፡ በአዬሌ ኬኬ/ምስራቅ ሐረርጌ፣ አንድ ኢማም፣ በሌላ የባህል መድኃኒት አዋቂ ከሰለጠኑ በኋላ፣ በባህል ህክምና ለ10 ዓመት ያህል የሰሩ ሲሆን ስራቸውን በይፋ ለመቀጠል የመንግስትን ፈቃድ ጠይቀዋል፡፡ በበርካታ አጋጣሚዎች፣ መደበኛ ባልሆነ መንገድ ከወላጆቻቸው በመማር፣ ራሳቸውን ያሰለጠኑ የባህል አዋላጆች (ዶአማ/ጋሞ፣ ገልቻ/ምሥራቅ ሸዋ) ወይም የእድሜ አቻዎቻቸው (ብዙ ጊዜ ከጎረቤቶች ወይም የቤተሰብ አባላት አሰቃቂ የወሊድ ተሞክሮ በኋላ (አዬሌ ኬኬ/ምሥራቅ ሐረርጌ)) በመደበኛ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች ፕሮግራሞች ውስጥም ተሳትፈዋል (ማጣቀሻ፡- እናቶችና ጨቅላ ህጻናት)፡፡ አዲስ አሰራሮች ለሌሎች የማኅበረሰብ አባላት በግልጽ በሚታዩበት ጊዜያት ሀሳብ አፍላቂዎች፣ እንደ ህብረተሰቡ በሰፊ የዕውቀትና የልምድ አድማስ የረቀቁና የላቁ አባላት ተቆጥረው ከፍተኛ ክብር ይቸራቸዋል፡፡ ለምሳሌ፡- በምስራቅ ትግራይ፣ ጥናቱ እንዲህ በማለት ይደመድመዋል፡-

> *የተማሩ የአሰተሳሰብ መሪዎች፣ የቀድሞ ተዋጊዎች፣ የሃይማኖት ትምህርት መሰረት ያላቸውና ዘመናዊ ትምህርት የቀሰሙ ናቸው፡፡ አዲስ ለውጦችን ለመቀበልና ማኅበረሰቡን ለማደራጀት (ንቅናቄ ለመፍጠር) ፈጣን ናቸው፡፡ ከሌሎች ቦታዎች ጋር ትውውቅ አላቸው* (ሃረሳው)፡፡

ስለዚህም፣ የWIDE መረጃ፣ በገጠር አካባቢዎች፣ አዳዲስ ሃሳቦች የማመንጨት ልማድ ወይም የፈጠራ ዝንባሌ ችግር እንደሌለ ይጠቁማል፡፡

- በመደበኛ ሰርቶ ማሳያ ወይም በሞዴሎች አማካኝነት መንግስት የሚከተላቸው አቅጣጫዎች ብቸኛ - ወይም ብዙ ጊዜ በእርግጥም በጣም ቁልፍ - የፈጠራና የለውጥ ምንጮች አይደሉም፡፡

<u>ማጠቃለያ፡- በተለያዩ ማኅበረሰቦች ውስጥ ፈጠራን የሚያሻሽል ድጋፍ</u>

አብዛኞቹ የዚህ መድበል ሌሎች አጫጭር የጥናት መግለጫዎች፣ አዎንታዊ ለውጥና አዲስ አሰራርን ለማሻሻል መንግስት ድጋፍ እንዲያደርግ፣ ጥልቅ የዘርፍ ምክረ ሃሳቦችን ያቀርባሉ፡፡ የገጠር ኢኮኖሚን የሚወስኑ የአመለካከት፣ የቴክኖሎጂና የሃብት እመርታዎች በመንግስት ከተሰጣቸው ትኩረት አንጻር፣ አርአያዎች/ሞዴሎች በሚለው ጽሁፍ ላይ የተብራሩት የመንግስት አሰራሮችና ተቋማት ውጤታማነትና ምላሽ ሰጪነትም ቁልፍ ናቸው፡፡ መንግሥታዊና ሌሎች ውጭያዊ የለውጥ እንቅስቃሴዎች፣ አዳዲስ አሰራሮችን የመለየትና የመደገፍ መጠነ-ርዕይና አቅምን በማሻሻል ረገድ ከፍተኛ ተፅዕኖ ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡

ሆኖም፡-

> *[…] ምልከታውን የሚያከናውነው ማነው የሚለውም ወሳኝ ነው (ፈተናዎችን ተጋፍጠው ስኬት ለተቀዳጁ አዲስ አሰራር አፍላቂ አፈንጋሪዎችና ከአዎንታዊ ማፈንገጣቸው ለተገኘው ተሞክሮ) ማኅበረሰቡ ግኝቱን ራሱ ማከናወን አለበት - የውጭ ‹ባለሙያዎች› መጥተው፣ (አዎንታዊ ማፈንገጥን) መለየታቸውና ወደ አሰራር መመሪያነት መቀየራቸው ፋይዳ የለውም፡፡ […] አዲስ አሰራሮችን ማበረታታት ማለት ‹ከተለመደው ሁኔታዎች ለየት ያሉ አዲስ አሰራሮችን መለየት መቻልን› መማር ነው፡፡* […] (ዳንከን ግሪን፤ 2016)[7]

የአዎንታዊ ማፈንገጥና የፖሊሲ ትንታኔ ፅሑፍ፣ ከWIDE መረጃዎች ጋር የሚመጡ ከፖሊሲ አንደምታቸው አንጻር የተለያዩና ዘርፈ ብዙ ስዕሎችን ወደ መተርጎም ተጨማሪ ትምህርቶች ሊያመራ ይችላል፡፡ ይህ ሰፊ ብዝሃነትና ውስብስብነት፣ የገጠሩን ሕዝብ የፈጠራ አቅም በላቀ ሁኔታ ለመደገፍ አዲስ አሰራር እንደሚያስፈልግ ይጠቁማል፡፡ በ"ዘመናዊ የሙያ ክህሎት" እና "የቴክኖሎጂ ሽግግር" ተዋረድ ብቻ መሥራት፣ የማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ለውጥ የሚከሰቱባቸውን መንገዶች ከማፍካት ይልቅ የበለጠ ሊያዳፍነው ይችላል፡፡ ዱንካን ግሪን በቅርቡ እንዳስቀመጠው፡-

> *የማህበረሰብ የፈጠራ አቅም ጥቅም ላይ እንዲውል በማድረግ ረገድ ከሁሉም የላቀው ጠቃሚ ትምህርት፣ ቅደም ተከተሎችን መገልበጥ ነው* (ዳንከን ግሪን፤ 2016) ::

የWIDE መረጃ እንደሚጠቁመው፤ በኢትዮጵያ ማኅበረሰቦች ውስጥ ለውጥ፣ በእጅጉ የተነቃቃ የሚሆነው፣ ፖሊሲ አውጪዎች፣ የግለሰቦችንና የትስስር መረባቸውን አዳዲስ የአሰራር ልማዶች ሲከታተሉ፣ ሲያግዙና ምላሽ ሲሰጡ ነው::

[7] Duncan Green (February 2016), review of Pascale *et al.* (*op.cit.*) available at http://oxfamblogs.org/fp2p/book-review-the-power-of-positive-deviance/